መጽሐፍ ቅዱስ



The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

መጽሐፍ ቅዱስ
The New Testament in the Amharic language of Ethiopia

copyright © 1962, 2003 United Bible Societies

Language: አማርኛ (Amharic)

Amharic NT

Revised Amharic Bible in XML (2003).

Printed version by United Bible Societies (C)1962.

E-Text in transliterated ASCII format by Lapsley/Brooks Foundation 1994.

Unicode UTF-8 transformation and XML-tagging by Dirk Röckmann 2003 (www.nt-text.net).

With kind permission of the Bible Society of Ethiopia.

Every non-commercial work using this data in any form must fully include this copyright statement!

Every commercial use of parts or the complete data in any form needs written permission of the Bible Society of Ethiopia!

2014-09-09

PDF generated using Haiola and XeLaTeX on 18 Apr 2025 from source files dated 31 Aug 2023
2432e07d-4260-5d76-afcb-ce35bd1c48b7

Contents

የማቴዎስ ወንጌል 1
የማርቆስ ወንጌል 25
የሉቃስ ወንጌል 40
የዮሐንስ ወንጌል 65
የሐዋርያት ሥራ 85
ወደ ሮሜ ሰዎች 109
1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 119
2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች 130
ወደ ገላትያ ሰዎች 137
ወደ ኤፌሶን ሰዎች 141
ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች 144
ወደ ቆላስይስ ሰዎች 147
1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 149
2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች 151
1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 152
2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 155
ወደ ቲቶ 157
ወደ ፊልሞና 158
ወደ ዕብራውያን 159
የያዕቆብ መልእክት 166
1ኛ የጴጥሮስ መልእክት 169
2ኛ የጴጥሮስ መልእክት 172
1ኛ የዮሐንስ መልእክት 174
2ኛ የዮሐንስ መልእክት 177
3ኛ የዮሐንስ መልእክት 178
የይሁዳ መልእክት 179
የዮሐንስ ራእይ 180

የማቴዎስ ወንጌል

፩ የዳዊት ልጅ የአብርሃም ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ትውልድ መጽሐፍ።
፪ አብርሃም ይስሐቅን ወለደ፤ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ፤ ያዕቆብም ይሁዳንና ወንድሞቹን ወለደ፤
፫ ይሁዳም ከትዕማር ፋሬስንና ዛራን ወለደ፤ ፋሬስም ኤስሮምን ወለደ፤
፬ ኤስሮምም አራምን ወለደ፤ አራምም አሚናዳብን ወለደ፤ አሚናዳብም ነአሶንን ወለደ፤ ነአሶንም ሰልሞንን ወለደ፤
፭ ሰልሞንም ከራኬብ ቦኤዝን ወለደ፤ ቦኤዝም ከሩት ኢዮቤድን ወለደ፤ ኢዮቤድም እሴይን ወለደ፤
፮ እሴይም ንጉሥ ዳዊትን ወለደ።
፯ ሰሎሞንም ሮብዓምን ወለደ፤ ሮብዓምም አቢያን ወለደ፤ አቢያም አሣፍን ወለደ፤
፰ አሣፍም ኢዮሣፍጥን ወለደ፤ ኢዮሣፍጥም ኢዮራምን ወለደ፤ ኢዮራምም ያዝያንን ወለደ፤
፱ ያዝያንም ኢዮአታምን ወለደ፤ ኢዮአታምም አካዝን ወለደ፤
፲ አካዝም ሕዝቅያስን ወለደ፤ ሕዝቅያስም ምናሴን ወለደ፤ ምናሴም አሞፅን ወለደ፤
፲፩ አሞፅም ኢዮስያስን ወለደ፤ ኢዮስያስም በባቢሎን ምርኮ ጊዜ ኢኮንያንንና ወንድሞቹን ወለደ።
፲፪ ከባቢሎንም ምርኮ በኋላ ኢኮንያን ሰላትያልን ወለደ፤ ሰላትያልም ዘሩባቤልን ወለደ፤
፲፫ ዘሩባቤልም አብዩድን ወለደ፤ አብዩድም ኤልያቄምን ወለደ፤ ኤልያቄምም አዛርን ወለደ፤
፲፬ አዛርም ሳዶቅን ወለደ፤ ሳዶቅም አኪምን ወለደ፤ አኪምም ኤልዩድን ወለደ፤
፲፭ ኤልዩድም አልዓዛርን ወለደ፤ አልዓዛርም ማታንን ወለደ፤ ማታንም ያዕቆብን ወለደ፤
፲፮ ያዕቆብም ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን የወለደች የማርያምን እጮኛ ዮሴፍን ወለደ።
፲፯ እንግዲህ ትውልድ ሁሉ ከአብርሃም እስከ ዳዊት አሥራ አራት ትውልድ፥ ከዳዊትም እስከ ባቢሎን ምርኮ አሥራ አራት ትውልድ፥ ከባቢሎንም ምርኮ እስከ ክርስቶስ አሥራ አራት ትውልድ ነው።
፲፰ የኢየሱስ ክርስቶስም ልደት እንዲህ ነበረ። እናቱ ማርያም ለዮሴፍ በታጨች ጊዜ ሳይገናኙ ከመንፈስ ቅዱስ ፀንሳ ተገኘች።
፲፱ እጮኛዋ ዮሴፍም ጻድቅ ሆኖ ሊገልጣት ሰላልወደደ በስውር ሊተዋት አሰበ።
፳ እርሱ ግን ይህን ሲያሰብ፥ እነሆ የጌታ መልአክ በሕልም ታየው፥ እንዲህም አለ። የዳዊት ልጅ ዮሴፍ ሆይ፥ ከእርስዋ የተፀነሰው ከመንፈስ ቅዱስ ነውና እጮኛህን ማርያምን ለመውሰድ አትፍራ።
፳፩ ልጅም ትወልዳለችና፤ እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱስ ትለዋለህ።
፳፪ በነቢይ ከጌታ ዘንድ።
፳፫ እነሆ፥ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች፥ ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል፥ ትርጓሜውም። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የሚል ነው።
፳፬ ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ፤ እጮኛውንም ወሰደ፤
፳፭ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም፤ ስሙንም ኢየሱስ አለው።

፪

፩-፪ ንጉሡ ሄሮድስም ሰምቶ ደነገጠ፥ ኢየሩሳሌምም ሁሉ ከእርሱ ጋር፤
፬ የካህናትንም አለቆች የሕዝቡንም ጻፎች ሁሉ ሰብስቦ ክርስቶስ ወዴት እንዲወለድ ጠየቃቸው።
፭-፮ ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገልን በስውር ጠርቶ ኮከቡ የታየበትን ዘመን ከእነርሱ በጥንቃቄ ተረዳ፥
፰ ወደ ቤተ ልሔምም እነርሱን ሰድዶ። ሂዱ፥ ስለ ሕፃኑ በጥንቃቄ መርምሩ፤ ባገኛችሁትም ጊዜ እኔ ደግሞ መጥቼ እንድሰግድለት ንገሩኝ አላቸው።
፱ እነርሱም ንጉሡን ሰምተው ሄዱ፤ እነሆም፥ በምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ላይ መጥቶ እስኪቆም ድረስ ይመራቸው ነበር።
፲ ኮከቡንም ባዩ ጊዜ በታላቅ ደስታ እጅግ ደስ አላቸው።
፲፩ ወደ ቤትም ገብተው ሕፃኑን ከእናቱ ከማርያም ጋር አዩት፥ ወድቀውም ሰገዱለት፥ ሣጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅና ዕጣን ከርቤም አቀረቡለት።
፲፪ ወደ ሄሮድስም እንዳይመለሱ በሕልም ተረድተው በሌላ መንገድ ወደ አገራቸው ሄዱ።
፲፫ እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ። ሄሮድስ ሕፃኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብፅ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው።
፲፬-፲፭ ከዚህ በኋላ ሄሮድስ ሰብአ ሰገል እንደ ተሣለቁበት ባየ ጊዜ እጅግ ተቆጣና ልኮ ከሰብአ ሰገል እንደ ተረዳው ዘመን በቤተ ልሔምና በአውራጃዋ የነበሩትን፥ ሁለት ዓመት የሆናቸውን ከዚያም የሚያንሱትን ሕፃናት ሁሉ አሰገደለ።
፲፯-፲፰ ሄሮድስም ከሞተ በኋላ፥ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በግብፅ ለዮሴፍ በሕልም ታይቶ።
፳ የሕፃኑን ነፍስ የፈለጉት ሞተዋልና ተነሣ፥ ሕፃኑን እናቱንም ይዘህ ወደ እስራኤል አገር ሂድ አለ።
፳፩ እርሱም ተነሥቶ ሕፃኑንና እናቱን ያዘና ወደ እስራኤል አገር ገባ።
፳፪ በአባቱም በሄሮድስ ፈንታ አርኬላዎስ በይሁዳ እንደ ነገሠ በሰማ ጊዜ፥ ወደዚያ መሄድን ፈራ፤ በሕልምም ተረድቶ ወደ ገሊላ አገር ሄደ፤
፳፫ በነቢያት። ናዝራዊ ይባላል የተባለው ይፈጸም ዘንድ፥ ናዝሬት ወደምትባል ከተማ መጥቶ ኖረ።

፫

፩-፪ በነቢዩ በኢሳይያስ። የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮህ ሰው ድምፅ የተባለለት ይህ ነውና።
፬ ራሱም ዮሐንስ የግመል ጠጕር ልብስ ነበረው፥ በወገቡም ጠፍር ይታጠቅ ነበር፤ ምግቡም አንበጣና የበረሀ ማር ነበረ።
፭ ያን ጊዜ ኢየሩሳሌም ይሁዳም ሁሉ በዮርዳኖስም ዙሪያ ያለ አገር ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፤

፮ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ
ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።
፯ ዳሩ ግን ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ብዙዎች
ወደ ጥምቀቱ ሲመጡ ባየ ጊዜ፥ እንዲህ አላቸው።
እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ከሚመጣው ቊጣ እንድትሸሹ
ማን አመለከታችሁ?
፰ እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤
፱ በልባችሁም። አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ
አይምሰላችሁ፤ እላችኋለሁና። ከነዚህ ድንጋዮች
ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር
ይችላል።
፲ አሁንስ ምሳር በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤
እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ
ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።
፲፩ እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን
እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው
ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ
በእሳትም ያጠምቃችኋል፤
፲፪ መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ
ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን
ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል።
፲፫ ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ
ወደ ዮርዳኖስ መጣ።
፲፬ ዮሐንስ ግን። እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል
አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው
ነበር።
፲፭ ኢየሱስም መልሶ። አሁንስ ፍቀድልኝ፤ እንዲህ
ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው። ያን ጊዜ
ፈቀደለት።
፲፮ ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያው ከውኃ
ወጣ፤ እነሆም፥ ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም
መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ
አየ፤
፲፯ እነሆም፥ ድምፅ ከሰማያት መጥቶ። በእርሱ ደስ
የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው አለ።

፬

፩ ከዚያ ወዲያ ኢየሱስ ከዲያብሎስ ይፈተን ዘንድ
መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፥
፪ አርባ ቀንና አርባ ሌሊትም ከጦመ በኋላ ተራበ።
፫ ፈታኝም ቀርቦ። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥
እነዚህ ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ በል አለው።
፬ እርሱም መልሶ። ሰው ከእግዚአብሔር አፍ
በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም
ተብሎ ተጽፎአል አለው።
፭ ከዚህ በኋላ ዲያቢሎስ ወደ ቅድስት ከተማ
ወሰደውና እርሱን በመቅደስ ጫፍ ላይ አቁሞ።
፮ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝልሃል እግርህንም
በድንጋይ ከቶ እንዳትሰናከል በእጃቸው ያነሡሃል
ተብሎ ተጽፎአልና የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ፥
ወደ ታች ራስህን ወርውር አለው።
፯ ኢየሱስም። ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ
ደግሞ ተጽፎአል አለው።
፰ ደግሞ ዲያቢሎስ እጅግ ረጅም ወደ ሆነ
ተራራ ወሰደው፥ የዓለምንም መንግሥታት ሁሉ
ክብራቸውንም አሳይቶ።
፱ ወድቀህ ብትሰግድልኝ ይህን ሁሉ እሰጥሃለሁ
አለው።
፲ ያን ጊዜ ኢየሱስ። ሂድ፥ አንተ ሰይጣን ለጌታህ
ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ
ተጽፎአልና አለው።
፲፩ ያን ጊዜ ዲያቢሎስ ተወው፥ እነሆም፥ መላእክት
ቀርበው ያገለግሉት ነበር።
፲፪ ኢየሱስም ዮሐንስ አልፎ እንደ ተሰጠ በሰማ ጊዜ
ወደ ገሊላ ፈቀቅ ብሎ ሄደ።
፲፫ ናዝሬትንም ትቶ በዛብሎንና በንፍታሌም አገር
በባሕር አጠገብ ወደ አለችው ወደ ቅፍርናሆም
መጥቶ ኖረ።
፲፬-፲፭ የተባለው ይፈጸም ዘንድ ይህ ሆነ። ከዚያ
ዘመን ጀምሮ ኢየሱስ። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና
ንስሐ ግቡ እያለ ይሰብክ ጀመር።
፲፮ በገሊላ ባሕር አጠገብ ሲመላለስም
ሁለት ወንድማማች ጴጥሮስ የሚሉትን ስምዖንን
ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር
ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና።
፲፱ እርሱም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች
እንድትሆኑ እደርጋችኋለሁ አላቸው።
፳ ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።
፳፩ ከዚያም እልፍ ብሎ ሌሎችን ሁለት
ወንድማማች የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም
ዮሐንስን ከአባታቸው ከዘብዴዎስ ጋር በታንኳ
መረባቸውን ሲያበጁ አየ፤ ጠራቸውም።
፳፪ እነርሱም ወዲያው ታንኳይቱንና አባታቸውን
ትተው ተከተሉት።
፳፫ ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ
የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ በሕዝብም ያለውን
ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ በገሊላ ሁሉ ይዞር ነበር።
፳፬ ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ፤ በልዩ ልዩ
ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም
ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም
ወደ እርሱ አመጡ፥ ፈወሳቸውም።
፳፭ ከገሊላም ከአሥሩ ከተማም ከኢየሩሳሌምም
ከይሁዳም ከዮርዳኖስም ማዶ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

፭

፩ ሕዝቡንም አይቶ ወደ ተራራ ወጣ፤ በተቀመጠም
ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀረቡ፤
፪ አፉንም ከፍቶ አስተማራቸው እንዲህም አለ።
፫ በመንፈስ ድሆች የሆኑ ብፁዓን ናቸው፥
መንግሥተ ሰማያት የእነርሱ ናትና።
፬ የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው፥ መፅናናትን ያገኛሉና።
፭ የዋሆች ብፁዓን ናቸው፥ ምድርን ይወርሳሉና።
፮ ጽድቅን የሚራቡና የሚጠሙ ብፁዓን ናቸው፥
ይጠግባሉና።
፯ የሚምሩ ብፁዓን ናቸው፥ ይማራሉና።
፰ ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው፥ እግዚአብሔርን
ያዩታልና።
፱ የሚያስተራርቁ ብፁዓን ናቸው፥ የእግዚአብሔር
ልጆች ይባላሉና።
፲ ስለ ጽድቅ የሚሰደዱ ብፁዓን ናቸው፥ መንግሥተ
ሰማያት የእነርሱ ናትና።
፲፩ ሲነቅፉአችሁና ሲያሳድዱአችሁ በእኔም ምክንያት
ክፉውን ሁሉ በውሸት ሲናገሩባችሁ ብፁዓን ናችሁ።

፲፪ ዋጋችሁ በሰማያት ታላቅ ነውና ደስ ይበላችሁ፥ ሐሴትም አድርጉ፤ ከእናንተ በፊት የነበሩትን ነቢያትን እንዲሁ አሳድደዋቸዋልና።
፲፫ እናንተ የምድር ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፍጣል? ወደ ውጭ ተጥሎ በሰው ከመረገጥ በቀር ወደ ፊት ለምንም አይጠቅምም።
፲፬ እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ። በተራራ ላይ ያለች ከተማ ልትሰወር አይቻላትም።
፲፭ መብራትንም አብርተው ከዕንቅብ በታች አይደለም እንጂ በመቅረዙ ላይ ያኖሩታል በቤት ላሉት ሁሉም ያበራል።
፲፮ መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ።
፲፯ እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።
፲፰ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።
፲፱ እንግዲህ ከነዚህ ከሁሉ ካነሱት ትእዛዛት አንዲቱን የሚሽር ለሰውም እንዲሁ የሚያስተምር ማንም ሰው በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ ታናሽ ይባላል፤ የሚያደርግ ግን የሚያስተምርም ማንም ቢሆን እርሱ በመንግሥተ ሰማያት ታላቅ ይባላል።
፳ እላችኋለሁና። ጽድቃችሁ ከጸፎችና ከፈሪሳውያን ጽድቅ ካልበለጠ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።
፳፩ ለቀደሙት። አትግደል እንደ ተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል።
፳፪ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል፤ ወንድሙንም ጨርቃም የሚለው ሁሉ የሸንጎ ፍርድ ይገባዋል፤ ደንቆሮ የሚለውም ሁሉ የገሃነመ እሳት ፍርድ ይገባዋል።
፳፫ እንግዲህ መባህን በመሠዊያው ላይ ብታቀርብ፥ በዚያም ወንድምህ አንዳች በአንተ ላይ እንዳለው ብታስብ፥
፳፬ በዚያ በመሠዊያው ፊት መባህን ትተህ ሂድ፥ አስቀድመህም ከወንድምህ ጋር ታረቅ፥ በኋላም መጥተህ መባህን አቅርብ።
፳፭ አብረኸው በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ ጋር ፈጥነህ ተስማማ፤ ባላጋራ ለዳኛ እንዳይሰጥህ ዳኛም ለሎሌው፥ ወደ ወህኒም ትጣላለህ፤
፳፮ እውነት እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከቶ ከዚያ አትወጣም።
፳፯ አታመንዝር እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
፳፰ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ወደ ሴት ያየ ሁሉ የተመኛትም ያን ጊዜ በልቡ ከእርስዋ ጋር አመንዝሮአል።
፳፱ ቀኝ ዓይንህም ብታስናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻልሃልና።
፴ ቀኝ እጅህም ብታስናክልህ ቆርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሙሉ ሰውነትህ በገሃነም ከሚጣል ይልቅ ከአካላትህ አንድ ቢጠፋ ይሻላልና።
፴፩ ሚስቱን የሚፈታት ሁሉ የፍችዋን ጽሕፈት ይስጣት ተባለ።
፴፪ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል።
፴፫ ደግሞ ለቀደሙት። በውሸት አትማል ነገር ግን መሐላዎችህን ለጌታ ሰጥ እንደተባለ ሰምታችኋል።
፴፬ እኔ ግን እላችኋለሁ። ከቶ አትማሉ፤ በሰማይ አይሆንም የእግዚአብሔር ዙፋን ነውና፤
፴፭ በምድርም አይሆንም የእግሩ መረገጫ ናትና፤ በኢየሩሳሌምም አይሆንም የታላቁ ንጉሥ ከተማ ናትና፤
፴፮ በራስህም አትማል፥ አንዲቱን ጠጉር ነጭ ወይም ጥቁር ልታደርግ አትችልምና።
፴፯ ነገር ግን ቃላችሁ አዎን አዎን ወይም አይደለም አይደለም ይሁን፤ ከነዚህም የወጣ ከክፉው ነው።
፴፰ ዓይን ስለ ዓይን ጥርስም ስለ ጥርስ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
፴፱ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ክፉውን አትቃወሙ፤ ዳሩ ግን ቀኝ ጉንጭህን በጥፊ ለሚመታህ ሁሉ ሁለተኛውን ደግሞ አዙርለት፤
፵ እንዲከሰህም እጀ ጠባብህንም እንዲወሰድ ለሚወድ መጎናጸፊያህን ደግሞ ተውለት፤
፵፩ ማንም ሰው አንድ ምዕራፍ ትሄድ ዘንድ ቢያስገድድህ ሁለተኛውን ከእርሱ ጋር ሂድ።
፵፪ ለሚለምንህ ሰጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፈቀቅ አትበል።
፵፫ ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደ ተባለ ሰምታችኋል።
፵፬-፵፭ የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፵፮ ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን?
፵፰ እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማን ሁኑ።

፮

፩ ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ፤ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም።
፪ እንግዲህ ምጽዋት ስታደርግ፥ ግብዞች በሰው ዘንድ ሊከበሩ በምኩራብ በመንገድም እንደሚያደርጉ በፊትህ መለከት አታስነፋ፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።
፫-፬ ስትጸልዩም እንደ ግብዞች አትሁኑ፤ ለሰው ይታዩ ዘንድ በምኩራብና በመንገድ ማዕዘን ቆመው መጸለይን ይወዳሉና፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።
፮ አንተ ግን ስትጸልይ፥ ወደ እልፍኝህ ግባ መዝጊያህንም ዘግተህ በሰውር ላለው አባትህ ጸልይ፤ በሰውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል።
፯ አሕዛብም በመናገራቸው ብዛት እንዲሰሙ ይመስላቸዋልና ስትጸልዩ እንደ እነርሱ በከንቱ አትድገሙ።
፰ ስለዚህ አትምሰሉአቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና።

፱ እንግዲህ እናንተስ እንዲህ ጸልዩ። በሰማያት
የምትኖር አባታችን ሆይ፥
፲ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ ትምጣ፤ ፈቃድህ
በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን፤
፲፩ የዕለት እንጀራችንን ዛሬ ስጠን፤
፲፪ እኛም ደግሞ የበደሉንን ይቅር እንደምንል
በደላችንን ይቅር በለን፤
፲፫ ከክፉም አድነን እንጂ ወደ ፈተና አታግባን፤
መንግሥት ያንተ ናትና ኃይልም ክብርም ለዘለዓለሙ፤
አሜን።
፲፬ ለሰዎች ኃጢአታቸውን ይቅር ብትሉ፥ የሰማዩ
አባታችሁ እናንተን ደግሞ ይቅር ይላችኋልና፤
፲፭ ለሰዎች ግን ኃጢአታቸውን ይቅር ባትሉ፥
አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።
፲፮ ስትጦሙም፥ እንደ ግብዞች አትጠውልጉ፤
ለሰዎች እንደ ጦመኛ ሊታዩ ፊታቸውን ያጠፋሉና፤
እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋቸውን ተቀብለዋል።
፲፯-፲፱ ብልና ዝገት በሚያጠፉት ሌቦችም ቆፍረው
በሚሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በምድር ላይ መዝገብ
አትሰብስቡ፤
፳ ነገር ግን ብልም ዝገትም በማያጠፉት ሌቦችም
ቆፍረው በማይሠርቁት ዘንድ ለእናንተ በሰማይ
መዝገብ ሰብስቡ፤
፳፩ መዝገብህ ባለበት ልብህ ደግሞ በዚያ
ይሆናልና።
፳፪ የሰውነት መብራት ዓይን ናት። ዓይንህ እንግዲህ
ጤናማ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ ብሩህ ይሆናል፤
፳፫ ዓይንህ ግን ታማሚ ብትሆን፥ ሰውነትህ ሁሉ
የጨለመ ይሆናል። እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን
ጨለማ ከሆነ፥ ጨለማውስ እንዴት ይበረታ!
፳፬ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ማንም
የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላል ሁለተኛውንም ይወዳል፤
ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል፤
ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።
፳፭ ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ስለ ነፍሳችሁ በምትበሉትና
በምትጠጡት፥ ወይም ስለ ሰውነታችሁ በምትለብሱት
አትጨነቁ፤ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ
አይበልጥምን?
፳፮ ወደ ሰማይ ወፎች ተመልከቱ፤ አይዘሩም
አያጭዱምም በጎተራም አይከቱም፥ የሰማዩ
አባታችሁም ይመግባቸዋል፤ እናንተ ከእነርሱ እጅግ
አትበልጡምን?
፳፯ ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ
መጨመር የሚችል ማን ነው?
፳፰ ስለ ልብስስ ስለ ምን ትጨነቃላችሁ?
የሜዳ አበቦች እንዴት እንዲያድጉ ልብ አድርጋችሁ
ተመልከቱ፤
፳፱ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን
እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከነዚህ
እንደ አንዱ አልለበሰም።
፴ እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ
እቶን የሚጣለውን የሜዳን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው
ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን
እንዴት?
፴፩ እንግዲህ። ምን እንበላለን? ምንስ እንጠጣለን?
ምንስ እንለብሳለን? ብላችሁ አትጨነቁ፤
፴፪ ይህንስ ሁሉ አሕዛብ ይፈልጋሉ፤ ይህ ሁሉ
እንዲያስፈልጋችሁ የሰማዩ አባታችሁ ያውቃልና።
፴፫ ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን
መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ፥ ይህም ሁሉ
ይጨመርላችኋል።
፴፬ ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ፤ ለቀኑ
ክፋቱ ይበቃዋል።

፯

፩-፫ በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለምን
ታያለህ፥ በዓይንህ ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን
አትመለከትም?
፬ ወይም ወንድምህን። ከዓይንህ ጉድፍ ላውጣ
ፍቀድልኝ እንዴትስ ትለዋለህ? እነሆም፥ በዓይንህ
ምሰሶ አለ።
፭ አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን
አውጣ፥ ከዚያም በኋላ ከወንድምህ ዓይን ጉድፉን
ታወጣ ዘንድ እጥርተህ ታያለህ።
፮ በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም
እንዳይነክሱአችሁ፥ የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ፥
ዕንቁዎቻችሁንም በእሪያዎች ፊት አትጣሉ።
፯ ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥ ታገኙማላችሁ፤
መዝጊያን እንኳኩ፥ ይከፈትላችሁማል።
፰ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልገውም
ያገኛል፥ መዝጊያንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል።
፱ ወይስ ከእናንተ፥ ልጁ እንጀራ ቢለምነው፥
ድንጋይን የሚሰጠው ከእናንተ ማን ሰው ነው?
፲ ዓሣስ ቢለምነው እባብን ይሰጠዋልን?
፲፩ እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ
መልካም ስጦታ መስጠትን ካወቃችሁ፥ በሰማያት
ያለው አባታችሁ ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መልካም
ነገርን ይሰጣቸው?
፲፪ እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን
ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም
ነቢያትም ይህ ነውና።
፲፫ በጠበበው ደጅ ግቡ፤ ወደ ጥፋት የሚወስደው
ደጅ ሰፊ፥ መንገዱም ትልቅ ነውና፥ ወደ እርሱም
የሚገቡ ብዙዎች ናቸው፤
፲፬ ወደ ሕይወት የሚወስደው ደጅ የጠበበ፥
መንገዱም የቀጠነ ነውና፥ የሚያገኙትም ጥቂቶች
ናቸው።
፲፭ የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡባችሁ
በውሥጣቸው ግን ነጣቂዎች ተኩላዎች ከሆኑ
ከሐሰተኞች ነቢያት ተጠንቀቁ።
፲፮ ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ። ከእሾህ ወይን
ከኩርንችትስ በለስ ይለቀማልን?
፲፯ እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬ
ያደርጋል፥ ክፉም ዛፍ ክፉ ፍሬ ያደርጋል።
፲፰ መልካም ዛፍ ክፉ ፍሬ ማፍራት፥ ወይም ክፉ
ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም።
፲፱ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል
ወደ እሳትም ይጣላል።
፳ ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ።
፳፩ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ
እንጂ፥ ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ የሚለኝ ሁሉ መንግሥተ
ሰማያት የሚገባ አይደለም።

፳፪ በዚያ ቀን ብዙዎች። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ በሰምህ ትንቢት አልተናገርንምን፥ በሰምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፥ በሰምህስ ብዙ ተአምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል።
፳፫ የዚያን ጊዜም። ከቶ አላወቅኋችሁም፤ እናንተ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።
፳፬ ስለዚህ ይህን ቃሌን ሰምቶ የሚያደርገው ሁሉ ቤቱን በዓለት ላይ የሠራ ልባም ሰውን ይመስላል።
፳፭ ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሰም ነፈሰ ያንም ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ አልወደቀም።
፳፮ ይህንም ቃሌን ሰምቶ የማያደርገው ሰው ሁሉ ቤቱን በአሸዋ ላይ የሠራ ሰነፍ ሰውን ይመስላል።
፳፯ ዝናብም ወረደ ጎርፍም መጣ ነፋሰም ነፈሰ ያንም ቤት መታው፥ ወደቀም፥ እወዳደቁም ታላቅ ሆነ።
፳፰ ኢየሱሰም ይህን ነገር በጨረሰ ጊዜ ሕዝቡ በትምህርቱ ተገረሙ፤ እንደ ጻፎቻቸው ሳይሆን
፳፱ እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበርና።

፰

፩ ከተራራም በወረደ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።
፪ እነሆም፥ ለምጻም ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ እያለ ሰገደለት።
፫ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና። እወዳለሁ፥ ንጻ አለው። ወዲያውም ለምጹ ነጻ።
፬ ኢየሱሰም። ለማንም እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሙሴ ያዘዘውን መባ አቅርብ አለው።
፭ ወደ ቅፍርናሆምም በገባ ጊዜ የመቶ አለቃ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥
፮ ብላቴናዬ ሽባ ሆኖ እጅግ እየተሣቀየ በቤት ተኝቶአል ብሎ ለመነው።
፯ ኢየሱሰም። እኔ መጥቼ እፈውሰዋለሁ አለው።
፰ የመቶ አለቃውም መልሶ። ጌታ ሆይ፥ በቤቴ ጣራ ከታች ልትገባ አይገባኝም፤ ነገር ግን ቃል ብቻ ተናገር፥ ብላቴናዬም ይፈወሳል።
፱ እኔ ደግሞ ለሌሎች ተገዥ ነኝና፥ ከእኔም በታች ጭፍራ አለኝ፤ እንዱንም። ሂድ ብለው ይሄዳል፥ ሌላውንም። ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም። ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል አለው።
፲ ኢየሱሰም ሰምቶ ተደነቀና ለተከተሉት እንዲህ አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ በእሰራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም።
፲፩ እላችኋለሁም፥ ብዙዎች ከምሥራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይሰሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ፤
፲፪ የመንግሥት ልጆች ግን በውጭ ወደ አለው ጨለማ ይጣላሉ፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
፲፫ ኢየሱሰም ለመቶ አለቃ። ሂድና እንዳመንህ ይሁንልህ አለው። ብላቴናውም በዚያች ሰዓት ተፈወሰ።
፲፬ ኢየሱሰም ወደ ጴጥሮስ ቤት ገብቶ አማቱን በጉዳድ ታማ ተኝታ አያት፤
፲፭ እጅዋንም ዳሰሰ፥ ጉዳዱም ለቀቃት፤ ተነሥታም አገለገለቻቸው።
፲፮-፲፯ ኢየሱሰም ብዙ ሰዎች ሲከቡት አይቶ ወደ ማዶ እንዲሻገሩ አዘዘ።
፲፱ አንድ ጸፊም ቀርቦ። መምህር ሆይ፥ ወደምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው።
፳ ኢየሱሰም። ለቀበሮዎች ጉድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሰጠጋበት የለውም አለው።
፳፩ ከደቀ መዛሙርቱም ሌላው። ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ እንድሄድ አባቴን እንድቀብር ፍቀድልኝ አለው።
፳፪ ኢየሱሰም። ተከተለኝ፥ ሙታናቸውንም እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው አለው።
፳፫ ወደ ታንኳም ሲገባ ደቀ መዛሙርቱ ተከተሉት።
፳፬ እነሆም፥ ማዕበሉ ታንኳይቱን እስኪደፍናት ድረስ በባሕር ታላቅ መናወጥ ሆነ፤ እርሱ ግን ተኝቶ ነበር።
፳፭ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው። ጌታ ሆይ፥ አድነን፥ ጠፋን እያሉ አስነሡት።
፳፮ እርሱም። እናንተ እምነት የጎደላችሁ፥ ስለ ምን ትፈራላችሁ? አላቸው፤ ከዚህ በኋላ ተነሥቶ ነፋሱንና ባሕሩን ገሠጸ፥ ታላቅ ጸጥታም ሆነ።
፳፯ ሰዎቹም። ነፋሳትና ባሕርስ ሰንኳ የሚታዘዙለት፥ ይህ እንዴት ያለ ሰው ነው? እያሉ ተደነቁ።
፳፰ ወደ ማዶም ወደ ጌርጋሴኖን አገር በመጣ ጊዜ፥ አጋንንት ያደሩባቸው ሁለት ሰዎች ከመቃብር ወጥተው ተገናኙት፤ እነርሱም ሰው በዚያ መንገድ ማለፍ እስኪሳነው ድረስ እጅግ ክፉዎች ነበሩ።
፳፱ እነሆም። ኢየሱስ ሆይ፥ የእግዚአብሔር ልጅ፥ ከአንተ ጋር ምን አለን? ጊዜው ሳይደርስ ልትሣቅየን ወደዚህ መጣህን? እያሉ ጮኹ።
፴ ከእነርሱም ርቆ የብዙ እሪያ መንጋ ይሰማራ ነበር።
፴፩ አጋንንቱም። ታወጣንስ እንደሆንህ፥ ወደ እሪያው መንጋ ሰደደን ብለው ለመኑት። ሂዱ አላቸው።
፴፪ እነርሱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ሄዱና ገቡ፤ እነሆም፥ የእሪያዎቹ መንጋ ሁሉ ከእፋፉ ወደ ባሕር እየተጣደፉ ሮጡ በውኃም ውስጥ ሞቱ።
፴፫ እረኞችም ሸሹ፥ ወደ ከተማይቱም ሄደው ነገሩን ሁሉ አጋንንትም በእደሩባቸው የሆነውን አወሩ።
፴፬ እነሆም፥ ከተማው ሁሉ ኢየሱስን ሊገናኝ ወጣ፥ ባዩትም ጊዜ ከአገራቸው እንዲሄድላቸው ለመኑት።

፱

፩ በታንኳም ገብቶ ተሻገረና ወደ ገዛ ከተማው መጣ።
፪ እነሆም፥ በአልጋ የተኛ ሽባ ወደ እርሱ አመጡ። ኢየሱሰም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን። እንተ ልጅ፥ አይዞህ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።
፫ እነሆም፥ ከጸፎቹ አንዳንዱ በልባቸው። ይህስ ይሳደባል አሉ።
፬ ኢየሱሰም አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አለ። ስለ ምን በልባችሁ ክፉ ታሰባላችሁ?
፭ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?
፮ ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአትን ያስተሰርይ ዘንድ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፥

በዚያን ጊዜ ሸባውን። ተነሣ፤ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው።
፯ ተነሥቶም ወደ ቤቱ ሄደ።
፰ ሕዝቡም አይተው ተደነቁ፥ ለሰውም እንዲህ ያለ ሥልጣን የሰጠ እግዚአብሔርን አከበሩ።
፱ ኢየሱስም ከዚያ አልፎ በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረ ማቴዎስ የሚባል እንድ ሰው አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው።
፲ በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ እነሆ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች መጥተው ከኢየሱስና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብረው ተቀመጡ።
፲፩ ፈሪሳውያንም አይተው ደቀ መዛሙርቱን። መምህራችሁ ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር አብሮ ሰለ ምን ይበላል? አሉአቸው።
፲፪ ኢየሱስም ሰምቶ። ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤
፲፫ ነገር ግን ሄዳችሁ። ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም እይደለም ያለው ምን እንደ ሆነ ተማሩ፤ ኃጢአተኞችን ወደ ንሰሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁምና አላቸው።
፲፬ በዚያን ጊዜ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ እርሱ ቀርበው። እኛና ፈሪሳውያን፥ ብዙ ጊዜ የምንጦመው፥ ደቀ መዛሙርትህ ግን የማይጦሙት ሰለ ምንድር ነው? አሉት።
፲፭ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። ሚዜዎች ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊያዝኑ ይችላሉን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ጊዜም ይጦማሉ።
፲፮ በአረጀ ልብስ አዲስ እራፊ የሚያኖር የለም፤ መጣፊያው ልብሱን ይቦጭቀዋልና፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል።
፲፯ በአረጀ አቁማዳ አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ አቁማዳው ይፈነዳል፥ የወይን ጠጁም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል፤ ነገር ግን አዲሱን የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ ያኖረዋል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ።
፲፰ ይህንም ሲነግራቸው፥ አንድ መኰንን መጥቶ። ልጄ አሁን ሞተች፤ ነገር ግን መጥተህ እጅህን ጫንባት፥ በሕይወትም ትኖራለች እያለ ሰገደለት።
፲፱ ኢየሱስም ተነሥቶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተከተለው።
፳ እነሆም፥ ከአሥራ ሁለት ዓመት ጀምሮ ደም የሚፈሰሳት ሴት በኋላው ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፤
፳፩ በልብዋ። ልብሱን ብቻ የዳሰስሁ እንደ ሆነ፥ እድናለሁ ትል ነበረችና።
፳፪ ኢየሱስም ዘወር ብሎ አያትና። ልጄ ሆይ፥ አይዞሽ፤ እምነትሽ አድኖሻል አላት። ሴቲቱም ከዚያች ሰዓት ጀምራ ዳነች።
፳፫ ኢየሱስም ወደ መኰንኑ ቤት በደረሰ ጊዜ፥ እምቢልተኞችንና የሚንጫጫውን ሕዝብ አይቶ።
፳፬ ብላቴናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችምና ፈቀቅ በሉ አላቸው። በጣምም ሳቁበት።
፳፭ ሕዝቡን ግን ከአሰወጡ በኋላ ገብቶ እጅዋን ያዛት፥ ብላቴናይቱም ተነሣች።
፳፮ ያም ዝና ወደዚያ አገር ሁሉ ወጣ።
፳፯ ኢየሱስም ከዚያ ሲያልፍ ሁለት ዕውሮች። የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረን ብለው እየጮሁ ተከተሉት።
፳፰ ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ዕውሮቹ ወደ እርሱ ቀረቡ፥ ኢየሱስም። ይህን ማድረግ እንድችል ታምናላችሁን? አላቸው። እዎን፥ ጌታ ሆይ አሉት።
፳፱ በዚያን ጊዜ። እንደ እምነታችሁ ይሁንላችሁ ብሎ ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ።
፴ ዓይኖቻቸውም ተከፈቱ።
፴፩ ኢየሱስም። ማንም እንዳያውቅ ተጠንቀቁ ብሎ በብርቱ አዘዛቸው። እነርሱ ግን ወጥተው በዚያ አገር ሁሉ ሰለ እርሱ አወሩ።
፴፪ እነርሱም ሲወጡ እነሆ፥ ጋኔን ያደረበትን ዲዳ ሰው ወደ እርሱ አመጡ።
፴፫ ጋኔኑንም ካወጣው በኋላ ዲዳው ተናገረ። ሕዝቡም። እንዲህ ያለ በእስራኤል ዘንድ ከቶ አልታየም እያሉ ተደነቁ።
፴፬ ፈሪሳውያን ግን። በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል አሉ።
፴፭ ኢየሱስም በምኩራቦቻቸው እያስተማረ፥ የመንግሥትንም ወንጌል እየሰበከ፥ በሕዝብም ያለውን ደዌና ሕማም ሁሉ እየፈወሰ፥ በከተማዎችና በመንደሮች ሁሉ ይዞር ነበር።
፴፮ ብዙ ሕዝብም ባየ ጊዜ፥ እረኛ እንደ ሌላቸው በጎች ተጨንቀው ተጥለውም ነበርና እዘነላቸው።
፴፯ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤
፴፰ እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው።

፲

፩ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ወደ እርሱ ጠርቶ፥ እንዲያወጡአቸው በርኩሳን መናፍስት ላይ ደዌንና ሕማምንም ሁሉ እንዲፈውሱ ሥልጣን ሰጣቸው።
፪ የአሥራ ሁለቱም ሐዋርያት ሰም ይህ ነው፤ መጀመሪያው ጴጥሮስ የተባለው ሰምዖን ወንድሙ እንድርያስም፥ የዘብዴዎስ ልጅ ያዕቆብም ወንድሙ ዮሐንስም፥
፫ ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥ ቶማስም ቀራጩ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ታዴዎስም የተባለው ልብድዮስ፥
፬ ቀነናዊውም ሰምዖን ደግሞም አሳልፎ የሰጠው የአስቆሮቱ ይሁዳ።
፭ እነዚህን አሥራ ሁለቱን ኢየሱስ ላካቸው፥ አዘዛቸውም፥ እንዲህም አለ። በአሕዛብ መንገድ አትሂዱ፥ ወደ ሳምራውያንም ከተማ አትግቡ፤
፮ ይልቅስ የእስራኤል ቤት ወደሚሆኑ ወደ ጠፉት በጎች ሂዱ እንጂ።
፯ ሄዳችሁም። መንግሥተ ሰማያት ቀርባለች ብላችሁ ስበኩ።
፰ ድውዮችን ፈውሱ፤ ሙታንን አስነሡ፤ ለምጻሞችን አንጹ፤ አጋንንትን አውጡ፤ በከንቱ ተቀበላችሁ፥ በከንቱ ስጡ።
፱ ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ፥
፲ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጀ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አታግኙ፤ ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና።

፲፩ በምትገቡባትም በማናቸይቱም ከተማ ወይም መንደር፥ በዚያ የሚገባው ማን እንደ ሆነ በጥንቃቄ መርምሩ፤ እስክትወጡም ድረስ በዚያ ተቀመጡ።
፲፪ ወደ ቤትም ስትገቡ ሰላምታ ሰጡ፤
፲፫ ቤቱም የሚገባው ቢሆን ሰላማችሁ ይድረስለት፤ ባይገባው ግን ሰላማችሁ ይመለስላችሁ።
፲፬ ከማይቀበላችሁም ቃላችሁንም ከማይሰሙ ሁሉ፥ ከዚያ ቤት ወይም ከዚያች ከተማ ስትወጡ የእግራችሁን ትቢያ አራግፉ።
፲፭ እውነት እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ አገር ይቀልላቸዋል።
፲፮ እነሆ፥ እኔ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ፤ ስለዚህ እንደ እባብ ልባሞች እንደ ርግብም የዋሆች ሁኑ።
፲፯ ነገር ግን ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ በምኩራቦቻቸውም ይገርፉአችኋልና ከሰዎች ተጠበቁ፤
፲፰ ለእነርሱና ለአሕዛብም ምስክር እንዲሆን፥ ስለ እኔ ወደ ገዥዎች ወደ ነገሥታትም ትወሰዳላችሁ።
፲፱ አሳልፈውም ሲሰጡአችሁ፥ የምትናገሩት በዚያች ሰዓት ይሰጣችኋልና እንዴት ወይስ ምን እንድትናገሩ አትጨነቁ፤
፳ በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ፥ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁምና።
፳፩ ወንድምም ወንድሙን፥ አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ ይገድሉአቸውማል።
፳፪ በሁሉም ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።
፳፫ በአንዲቱ ከተማም መከራ ቢያሳዩአችሁ ወደ ሌላይቱ ሽሹ፤ እውነት እላችኋለሁና፥ የሰው ልጅ እስኪመጣ ድረስ የእስራኤልን ከተማዎች አትዘልቁም።
፳፬ ደቀ መዝሙር ከመምህሩ፥ ባሪያም ከጌታው አይበልጥም።
፳፭ ደቀ መዝሙር እንደ መምህሩ፥ ባሪያም እንደ ጌታው መሆኑ ይበቃዋል። ባለቤቱን ብዔል ዜቡል ካሉት፥ ቤተሰዎቹንማ እንዴት አብዝተው አይሉአቸው!
፳፮ እንግዲህ አትፍሩአቸው፤ የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለምና።
፳፯ በጨለማ የምነግራችሁን በብርሃን ተናገሩ፤ በጆሮም የምትሰሙትን በሰገነት ላይ ሰበኩ።
፳፰ ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።
፳፱ ሁለት ድንቢጦች በአምስት ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ያለ አባታችሁ ፈቃድ በምድር ላይ አትወድቅም።
፴ የእናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቈጥሮአል።
፴፩ እንግዲህ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች እናንተ ትበልጣላችሁ።
፴፪ ስለዚህ በሰው ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ፤
፴፫ በሰው ፊትም የሚክደኝን ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እክደዋለሁ።
፴፬ በምድር ላይ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም።
፴፭ ሰውን ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም ከእናትዋ፥ ምራትንም ከአማትዋ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁና፤
፴፮ ለሰውም ቤተ ሰዎቹ ጠላቶች ይሆኑበታል።
፴፯ ከእኔ ይልቅ አባቱን ወይም እናቱን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤ ከእኔ ይልቅም ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባውም፤
፴፰ መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም።
፴፱ ነፍሱን የሚያገኝ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም ስለ እኔ የሚያጠፋ ያገኛታል።
፵ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።
፵፩ ነቢይን በነቢይ ሰም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል፥ ጻድቅንም በጻድቅ ሰም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል።
፵፪ ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ሰም የሚያጠጣ፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ዋጋው አይጠፋበትም።

፲፩

፩ ኢየሱስም አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርቱን ማዘዝ በፈጸመ ጊዜ በከተሞቻቸው ሊያስተምርና ሊሰብክ ከዚያ አለፈ።
፪ ዮሐንስም በወህኒ ሳለ የክርስቶስን ሥራ ሰምቶ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከና።
፫ የሚመጣው አንተ ነህን? ወይስ ሌላ እንጠብቅ? አለው።
፬ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ሄዳችሁ ያያችሁትን የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤
፭ ዕውሮች ያያሉ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ ደንቆሮችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ
፮ ለድሆችም ወንጌል ይሰበካል፤ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው።
፯ እነዚያም ሲሄዱ ኢየሱስ ለሕዝቡ ስለ ዮሐንስ ሊናገር ጀመረ እንዲህም አለ። ምን ልታዩ ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ?
፰ ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ቀጭን ልብስ የለበሰ ሰውን? እነሆ፥ ቀጭን ልብስ የለበሱ በነገሥታት ቤት አሉ።
፱ ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን።
፲ እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ
፲፩ ተብሎ የተጻፈለት ይህ ነውና። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሣም፤ በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል።
፲፪ ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች፥ ግፈኞችም ይናጠቋታል።
፲፫ ነቢያት ሁሉና ሕጉ እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ፤
፲፬ ልትቀበሉትስ ብትወዱ፥ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው።

፲፭ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ።
፲፮ ነገር ግን ይህን ትውልድ በምን እመሰለዋለሁ? በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመሰላሉ፥ እነርሱም ባልንጀሮቻቸውን እየጠሩ።
፲፯ እንቢልታ ነፋንላችሁ ዘፈንም አልዘፈናችሁም ሙሾ አወጣንላችሁ ዋይ ዋይም አላላችሁም ይሉአቸዋል።
፲፰ ዮሐንስ ሳይበላና ሳይጠጣ መጣ፥ እነርሱም። ጋኔን አለበት አሉት።
፲፱ የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጣ፥ እነርሱም። እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና የኃጢአተኞች ወዳጅ ይሉታል። ጥበብም በልጆችዋ ጸደቀች።
፳ በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተአምራት የተደረገባቸውን ከተማዎች ንስሐ ሰላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ እንዲህም አለ።
፳፩ ወዮልሽ ኮራዚ፤ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንሰሐ በገቡ ነበርና።
፳፪ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል።
፳፫ አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ፤ በእንቺ የተደረገው ተአምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበርና።
፳፬ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል።
፳፭ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ እንዲህ አለ። አባት ሆይ፥ የሰማይና የምድር ጌታ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ሰለ ገለጥህላቸው አመሰግንሃለሁ፤
፳፮ አዎን፥ አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና።
፳፯ ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፤ ከአብ በቀር ወልድን የሚያውቅ የለም፥ ከወልድም በቀር ወልድም ሊገለጥለት ከሚፈቅድ በቀር አብን የሚያውቅ የለም።
፳፰ እናንተ ደካሞች ሸክማችሁ የከበደ ሁሉ፥ ወደ እኔ ኑ፥ እኔም አሳርፋችኋለሁ።
፳፱ ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ ከእኔም ተማሩ፥ እኔ የዋህ በልቤም ትሑት ነኝና፥ ለነፍሳችሁም ዕረፍት ታገኛላችሁ፤
፴ ቀንበሬ ልዝብ ሸክሜም ቀሊል ነውና።

፲፪

፩ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ በሰንበት ቀን በእርሻ መካከል አለፈ፤ ደቀ መዛሙርቱም ተራቡና እሸት ይቀጥፉ ይበሉም ጀመር።
፪ ፈሪሳውያንም አይተው። እነሆ፥ ደቀ መዛሙርትህ በሰንበት ማድረግ ያልተፈቀደውን ያደርጋሉ አሉት።
፫-፭ ካህናትም በሰንበት በመቅደስ ሰንበትን እንዲያረክሱ ኃጢአትም እንዳይሆንባቸው በሕጉ አላነበባችሁምን?
፮ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ከመቅደስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።
፯ ምሕረትን እወዳለሁ መሥዋዕትንም አይደለም ያለው ምን እንደሆነ ብታውቁስ ኃጢአት የሌለባቸውን ባልኰነናችሁም ነበር።
፰ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነውና።
፱ ከዚያም አልፎ ወደ ምኩራባቸው ገባ።
፲ እነሆም፥ እጁ የሰለለች ሰው ነበረ፤ ይከሱትም ዘንድ። በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን? ብለው ጠየቁት።
፲፩ እርሱ ግን። ከእናንተ አንድ በግ ያለው በሰንበት በጉድጓድ ቢወድቅበት፥ ይዞ የማያወጣው ሰው ማን ነው?
፲፪ እንግዲህ ሰው ከበግ ይልቅ እንደምን አይበልጥም! ሰለዚህ በሰንበት መልካም መሥራት ተፈቅዶአል አላቸው።
፲፫ ከዚያም በኋላ ሰውየውን። እጅህን ዘርጋ አለው። ዘረጋትም፥ እንደ ሁለተኛይቱም ደህና ሆነች።
፲፬ ፈሪሳውያን ግን ወጥተው እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ተማከሩበት።
፲፭ ኢየሱስም አውቆ ከዚያ ፈቀቅ አለ። ብዙ ሰዎችም ተከተሉት፥ ሁሉንም ፈወሳቸው፥ እንዳይገለጡትም አዘዛቸው፤
፲፮-፲፯ እነሆ የመረጥሁት ብላቴናዬ፥ ነፍሴ ደስ የተሰኘችበት ወዳጄ፤ መንፈሴን በእርሱ ላይ አኖራለሁ፥ ፍርድንም ለአሕዛብ ያወራል።
፲፰ አይከራከርም አይጮህምም፥ ድምፁንም በአደባባይ የሚሰማ የለም።
፲፱ ፍርድን ድል ለመንሣት እስኪያወጣ፥ የተቀጠቀጠን ሸምበቆ አይሰብርም የሚጤስን የጥዋፍ ክርም አያጠፋም።
፳፩ አሕዛብም በስሙ ተስፋ ያደርጋሉ።
፳፪ ከዚህም በኋላ ጋኔን ያደረበትን ዕውር ዲዳም ወደ እርሱ አመጡ፤ ዕውሩም ዲዳውም እስኪያይና እስኪናገር ድረስ ፈወሰው።
፳፫ ሕዝቡም ሁሉ ተገረሙና። እንጃ ይህ ሰው የዳዊት ልጅ ይሆንን? አሉ።
፳፬ ፈሪሳውያን ግን ሰምተው። ይህ በብዔል ዜቡል በአጋንንት አለቃ ካልሆነ በቀር አጋንንትን አያወጣም አሉ።
፳፭ ኢየሱስ ግን አሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው። እርስ በርሰዋ የምትለያይ መንግሥት ሁላ ትጠፋለች፥ እርስ በርሱ የሚለያይ ከተማም ሁሉ ወይም ቤት አይቆምም።
፳፮ ሰይጣንም ሰይጣንን የሚያወጣ ከሆነ፥ እርስ በርሱ ተለያየ፥ እንግዲህ መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?
፳፯ እኔስ በብዔል ዜቡል አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ ልጆቻችሁ በማን ያወጡአቸዋል? ሰለዚህ እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል።
፳፰ እኔ ግን በእግዚአብሔር መንፈስ አጋንንትን የማወጣ ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ደርሳለች።
፳፱ ወይስ ሰው አሰቀድሞ ኃይለኛውን ሳያስር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ እቃውን ሊነጥቀው እንዴት ይችላል? ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።
፴ ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፥ ከእኔ ጋርም የማያከማች ይበትናል።
፴፩ ሰለዚህ እላችኋለሁ፥ ኃጢአትና ሰድብ ሁሉ ለሰዎች ይሰረይላቸዋል፥ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን ለሰደበ አይሰረይለትም።
፴፪ በሰው ልጅ ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ግን የሚናገር

ሁሉ በዚህ ዓለም ቢሆን ወይም በሚመጣው አይሰረይለትም።
፴፫ ዛፍ ከፍሬዋ ትታወቃለችና ዛፍዋን መልካም፥ ፍሬዋንም መልካም እድርጉ፥ ወይም ዛፍዋን ክፉ ፍሬዋንም ክፉ እድርጉ።
፴፬ እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ክፉዎች ስትሆኑ መልካም ለመናገር እንዴት ትችላላችሁ? በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፍ ይናገራልና።
፴፭ መልካም ሰው ከልቡ መልካም መዝገብ መልካም ነገርን ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከክፉ መዝገብ ክፉ ነገርን ያወጣል።
፴፮ እኔ እላችኋለሁ፥ ሰዎች ስለሚናገሩት ስለ ከንቱ ነገር ሁሉ በፍርድ ቀን መልስ ይሰጡበታል፤
፴፯ ከቃልህ የተነሣ ትጸድቃለህና ከቃልህም የተነሣ ትኰነናለህ።
፴፰ በዚያን ጊዜ ከጻፎችና ከፈሪሳውያን አንዳንዶቹ መለሱና። መምህር ሆይ፥ ከአንተ ምልክት እንድናይ እንወዳለን አሉ።
፴፱ እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው። ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም።
፵ ዮናስ በዓሣ አንባሪ ሆድ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት እንደ ነበረ፥ እንዲሁ የሰው ልጅ በምድር ልብ ሦስት ቀንና ሦስት ሌሊት ይኖራል።
፵፩ የነነዌ ሰዎች በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ሰብክት ንሰሐ ገብተዋልና፥ እነሆም፥ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።
፵፪ ንግሥተ ዓዜብ በፍርድ ቀን ከዚህ ትውልድ ጋር ተነሥታ ትፈርድበታለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም፥ ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ።
፵፫ ርኩስ መንፈስ ግን ከሰው በወጣ ጊዜ፥ ዕረፍት እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፥ አያገኝምም።
፵፬ በዚያን ጊዜም። ወደ ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤ ቢመጣም ባዶ ሆኖ ተጠርጎና አጊጦ ያገኘዋል።
፵፭ ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሰባት ሌሎችን አጋንንት ከእርሱ ጋር ይወስዳል፥ ገብተውም በዚያ ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው ይብስበታል። ለዚህ ክፉ ትውልድ ደግሞ እንዲሁ ይሆንበታል።
፵፮ ገናም ለሕዝቡ ሲናገር፥ እነሆ፥ እናቱና ወንድሞቹ ሊነጋገሩት ፈልገው በውጭ ቆመው ነበር።
፵፯ እንዲህ። እነሆ፥ እናትህና ወንድሞችህ ሊነጋገሩህ ፈልገው በውጭ ቆመዋል አለው።
፵፰ እርሱ ግን ለነገረው መልሶ። እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነማን ናቸው? አለው።
፵፱ እጁንም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዘርግቶ። እነሆ እናቴና ወንድሞቼ፤
፶ በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ እኅቴም እናቴም ነውና አለ።

፲፫

፩ በዚያን ቀን ኢየሱስ ከቤት ወጥቶ በባሕር አጠገብ ተቀመጠ፤
፪ እርሱም በታንኳ ገብቶ እስኪቀመጥ ድረስ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥ ሕዝቡም ሁሉ በወደቡ ቆመው ነበር።
፫ በምሳሌም ብዙ ነገራቸው እንዲህም አላቸው። እነሆ፥ ዘሪ ሊዘራ ወጣ።
፬ እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፥ ወፎችም መጥተው በሉት።
፭ ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀ፤ ጥልቅ መሬትም ስላልነበረው ወዲያው በቀለ፥
፮ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ግን ጠወለገ፥ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ።
፯ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው።
፰ ሌላውም በመልካም መሬት ወደቀ፤ አንዱም መቶ፥ አንዱም ሰድሳ፥ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ።
፱ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ።
፲ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው። ስለ ምን በምሳሌ ትነግራቸዋለህ? አሉት።
፲፩ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው። ለእናንተ የመንግሥተ ሰማያትን ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፥ ለእነርሱ ግን አልተሰጣቸውም።
፲፪ ላለው ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
፲፫ ስለዚህ እያዩ ስለማያዩ እየሰሙም ስለማይሰሙ ስለማያስተውሉም በምሳሌ እነግራቸዋለሁ።
፲፬ መሰማት ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትም ታያላችሁና አትመለከቱም።
፲፭ በዓይናቸው እንዳያዩ፥ በጆሮአቸውም እንዳይሰሙ፥ በልባቸውም እንዳያስተውሉ፥ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአልና ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል የሚል የኢሳይያስ ትንቢት በእነርሱ ይፈጸማል።
፲፮ የእናንተ ግን ዓይኖቻችሁ ስለሚያዩ ጆሮቻችሁም ስለሚሰሙ ብፁዓን ናቸው።
፲፯ እውነት እላችኋለሁ፥ ብዙዎች ነቢያትና ጻድቃን የምታዩትን ሊያዩ ተመኝተው አላዩም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ተመኝተው አልሰሙም።
፲፰ እንግዲህ እናንተ የዘሪውን ምሳሌ ስሙ።
፲፱ የመንግሥትን ቃል ሰምቶ በማያስተውል ሁሉ፥ ክፉው ይመጣል፥ በልቡ የተዘራውንም ይነጥቃል፤ በመንገድ ዳር የተዘራው ይህ ነው።
፳ በጭንጫ ላይ የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ ወዲያው በደስታ የሚቀበለው ነው፤
፳፩ ነገር ግን ለጊዜው ነው እንጂ በእርሱ ሥር የለውም፥ በቃሉ ምክንያትም መከራ ወይም ስደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላል።
፳፪ በእሾህ መካከል የተዘራውም ይህ ቃሉን የሚሰማ ነው፥ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት መታለል ቃሉን ያንቃል፥ የማያፈራም ይሆናል።
፳፫ በመልካም መሬት የተዘራውም ይህ ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውል ነው፤ እርሱም ፍሬ ያፈራል አንዱም መቶ አንዱም ሰድሳ አንዱም ሠላሳ ያደርጋል።
፳፬ ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ። መንግሥተ ሰማያት በእርሻው መልካም ዘርን የዘራን ሰው ትመስላለች።
፳፭ ሰዎቹ ሲተኙ ግን ጠላቱ መጣና በስንዴው መካከል እንክርዳድን ዘርቶ ሄደ።
፳፮ ስንዴውም በበቀለና በአፈራ ጊዜ እንክርዳዱ ደግሞ ያን ጊዜ ታየ።

፳፯ የባለቤቱም ባሮች ቀርበው። ጌታ ሆይ፥ መልካምን ዘር በእርሻህ ዘርተህ አልነበርህምን? እንክርዳዱንስ ከወዴት አገኘ? አሉት።
፳፰ እርሱም። ጠላት ይህን አደረገ አላቸው። ባሮቹም። እንግዲህ ሄደን ብንለቅመው ትወዳለህን? አሉት።
፳፱ እርሱ ግን። እንክርዳዱን ስትለቅሙ ስንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም።
፴ ተዉአቸው፤ እስከ መከር ጊዜ አብረው ይደጉ፤ በመከር ጊዜም አጫጆችን። እንክርዳዱን አስቀድማችሁ ልቀሙ በእሳትም ለማቃጠል በየነደው እሰሩ፥ ስንዴውን ግን በጎተራዬ ክተቱ እላለሁ አለ።
፴፩ ሌላ ምሳሌ አቀረበላቸው እንዲህም አለ። መንግሥተ ሰማያት ሰው ወስዶ በእርሻው የዘራትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመስላለች፤
፴፪ እርስዋም ከዘር ሁሉ ታንሳለች፥ በእደገች ጊዜ ግን፥ ከአታክልቶች ትበልጣለች የሰማይም ወፎች መጥተው በቅርንጫፎችዋ እስኪሰፍሩ ድረስ ዛፍ ትሆናለች።
፴፫ ሌላ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ። መንግሥተ ሰማያት ሁሉ እስኪቦካ ድረስ ሴት ወስዳ በሦስት መስፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመስላለች።
፴፬-፴፭ በዚያን ጊዜ ሕዝቡን ትቶ ወደ ቤት ገባ። ደቀ መዛሙርቱም ወደ እርሱ ቀርበው። የእርሻውን እንክርዳድ ምሳሌ ተርጕምልን አሉት።
፴፯ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው። መልካምን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፤ እርሻውም ዓለም ነው፤
፴፰ መልካሙም ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤
፴፱ እንክርዳዱም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው፤ መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፥ አጫጆችም መላእክት ናቸው።
፵ እንግዲህ እንክርዳድ ተለቅሞ በእሳት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል።
፵፩ የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥
፵፪ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
፵፫ በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ይበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ።
፵፬ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት በእርሻ ውስጥ የተሰወረውን መዝገብ ትመስላለች፤ ሰውም አግኝቶ ሰወረው፥ ከደስታውም የተነሣ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ያን እርሻ ገዛ።
፵፭ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት መልካምን ዕንቁ የሚሻ ነጋዴን ትመስላለች፤
፵፮ ዋጋዋም እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ በአገኘ ጊዜ ሄዶ ያለውን ሁሉ ሸጠና ገዛት።
፵፯ ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብን ትመስላለች፤
፵፰ በሞላችም ጊዜ ወደ ወደቡ አወጡአት፥ ተቀምጠውም መልካሙን ለቅመው በዕቃዎች ውስጥ አከማቹ ክፉውን ግን ወደ ውጭ ጣሉት።
፵፱ በዓለም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፤ መላእክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል፥ ወደ እቶነ እሳትም ይጥሉአቸዋል፤
፶ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
፶፩ ኢየሱስም። ይህን ሁሉ አስተዋላችሁን? አላቸው አዎን አሉት።
፶፪ እርሱም። ስለዚህ የመንግሥተ ሰማያት ደቀ መዝሙር የሆነ ጸሐፊ ሁሉ ከመዝገቡ አዲሱንና አሮጌውን የሚያወጣ ባለቤትን ይመስላል አላቸው።
፶፫ ኢየሱስም እነዚህም ምሳሌዎች ከጨረሰ በኋላ ከዚያ ሄደ።
፶፬ ወደ ገዛ አገሩም መጥቶ እስኪገረሙ ድረስ በምኩራባቸው ያስተምራቸው ነበር፤ እንዲህም አሉ። ይህን ጥበብና ተአምራት ይህ ከወዴት አገኘው?
፶፭ ይህ የጸራቢ ልጅ አይደለምን? እናቱስ ማርያም ትባል የለምን? ወንድሞቹስ ያዕቆብና ዮሳ ስምዖንም ይሁዳም አይደሉምን?
፶፮ እኅቶቹስ ሁሉ በእኛ ዘንድ ያሉ አይደሉምን? እንኪያስ ይህን ሁሉ ከወዴት አገኘው? ተሰናከሉበትም።
፶፯ ኢየሱስ ግን። ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ቤቱ በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።
፶፰ በአለማመናቸውም ምክንያት በዚያ ብዙ ተአምራት አላደረገም።

፲፬

፩ በዚያ ዘመን የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ የኢየሱስን ዝና ሰማ፥
፪ ለሎሌዎቹም። ይህ መጥምቁ ዮሐንስ ነው፤ እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል፥ ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ።
፫ ሄሮድስ በወንድሙ በፊልጶስ ሚስት በሄሮድያዳ ምክንያት ዮሐንስን አስይዞ አሳስሮት በወህኒ አኑሮት ነበርና፤
፬ ዮሐንስ። እርስዋ ለእንተ ትሆን ዘንድ አልተፈቀደም ይለው ነበርና።
፭ ሊገድለውም ወደ ሳለ፥ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስለ እዩት ፈሩአቸው።
፮ ነገር ግን ሄሮድስ የተወለደበት ቀን በሆነ ጊዜ፥ የሄሮድያዳ ልጅ በመካከላቸው ዘፈነች ሄሮድስንም ደስ አሰኘችው፤
፯ ስለዚህም የምትለምነውን ሁሉ እንዲሰጣት በመሐላ ተስፋ አደረገላት።
፰ እርስዋም በእናትዋ ተመክራ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በዚህ በወጭት ሰጠኝ አለችው።
፱ ንጉሡም አዘነ፥ ነገር ግን ስለ መሐላው ከእርሱም ጋር ተቀምጠው ስላሉት ሰዎች እንዲሰጡአት አዘዘ፤
፲ ልኮም የዮሐንስን ራስ በወህኒ አስቆረጠው።
፲፩ ራሱንም በወጭት አምጥተው ለብላቴናይቱ ሰጡአት፥ ወደ እናትዋም ወሰደችው።
፲፪ ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው በድኑን ወሰዱና ቀበሩት፥ መጥተውም ለኢየሱስ አወሩለት።
፲፫ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ ከዚያ ብቻውን ወደ ምድረ በዳ በታንኳ ፈቀቅ አለ፤ ሕዝቡም ሰምተው ከከተማዎቹ በእግር ተከተሉት።
፲፬ ወጥቶም ብዙ ሕዝብ አየና አዘነላቸው ድውዮቻቸውንም ፈወሰ።
፲፭ በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው። ቦታው ምድረ በዳ ነው አሁንም ሰዓቱ አልፎአል፤ ወደ መንደሮች ሄደው ለራሳቸው ምግብ እንዲገዙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት።

፲፮ ኢየሱስም። እናንተ የሚበሉትን ሰጡአቸው እንጂ ሊሄዱ እያሰፈልግም አላቸው።
፲፯ እነርሱም። ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ በቀር በዚህ የለንም አሉት።
፲፰ እርሱም። እነዚያን ወደዚህ አምጡልኝ አላቸው።
፲፱ ሕዝቡም በሣር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፥ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቆርሶ ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።
፳ ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርሰራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሙሉ አነሡ።
፳፩ ከሴቶችና ከልጆችም በቀር የበሉት አምስት ሺህ ወንዶች ያህሉ ነበር።
፳፪ ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳይቱ ገብተው ወደ ማዶ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው።
፳፫ ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።
፳፬ ታንኳይቱም አሁን በባሕር መካከል ሳለች፥ ነፋስ ከወደ ፊት ነበርና በማዕበል ትጨነቅ ነበር።
፳፭ ከሌሊቱም በአራተኛው ክፍል ኢየሱስ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ እነርሱ መጣ።
፳፮ ደቀ መዛሙርቱም በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ። ምትሐት ነው ብለው ታወኩ በፍርሃትም ጮኹ።
፳፯ ወዲያውም ኢየሱስ ተናገራቸውና። አይዞአችሁ፥ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው።
፳፰ ጴጥሮስም መልሶ። ጌታ ሆይ፥ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ አለው።
፳፱ እርሱም። ና አለው። ጴጥሮስም ከታንኳይቱ ወርዶ ወደ ኢየሱስ ሊደርስ በውኃው ላይ ሄደ።
፴ ነገር ግን የነፋሱን ኃይል እይቶ ፈራ፥ ሊሰጥምም በጀመረ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ አድነኝ ብሎ ጮኸ።
፴፩ ወዲያውም ኢየሱስ እጁን ዘርግቶ ያዘውና። አንተ እምነት የጎደለህ፥ ስለምን ተጠራጠርህ? አለው።
፴፪ ወደ ታንኳይቱም በወጡ ጊዜ ነፋሱ ተወ።
፴፫ በታንኳይቱም የነበሩት። በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነህ ብለው ሰገዱለት።
፴፬ ተሻግረውም ወደ ጌንሴሬጥ ምድር መጡ።
፴፭ የዚያ ቦታ ሰዎችም ባወቁት ጊዜ በዙርያው ወዳለ አገር ሁሉ ላኩ፥ ሕመምተኞችንም ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤
፴፮ የልብሱንም ጫፍ ብቻ ሊዳሰሱ ይለምኑት ነበር፤ የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ።

፲፭

፩ በዚያን ጊዜ ጻፎችና ፈሪሳውያን ከኢየሩሳሌም ወደ ኢየሱስ ቀረቡና።
፪ ደቀ መዛሙርትህ ስለ ምን የሽማግሌዎችን ወግ ይተላለፋሉ? እንጀራ ሲበሉ እጃቸውን አይታጠቡምና አሉት።
፫ እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው። እናንተስ ስለ ወጋችሁ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ስለ ምን ትተላለፋላችሁ?
፬ እግዚአብሔር። አባትህንና እናትህን አክብር፤ ደግሞ። አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት ብሎአልና፤
፭ እናንተ ግን። አባቱን ወይም እናቱን። ከእኔ የምትጠቀምበት መባ ነው የሚል ሁሉ፥
፮ አባቱን ወይም እናቱን አያክብርም ትላላችሁ፤ ስለ ወጋችሁም የእግዚአብሔርን ቃል ሻራችሁ።
፯ እናንተ ግብዞች፥ ኢሳይያስ ስለ እናንተ።
፰ ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል፥ ልቡ ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤
፱ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ በከንቱ ያመልኩኛል ብሎ በእውነት ትንቢት ተናገረ።
፲ ሕዝቡንም ጠርቶ። ሰሙ አስተውሉም፤
፲፩ ሰውን የሚያረክሰው ወደ አፍ የሚገባ አይደለም፥ ከአፍ የሚወጣው ግን ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው አላቸው።
፲፪ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ቀርበው። ፈሪሳውያን ይህን ቃል ሰምተው እንደ ተሰናከሉ አወቅህን? አሉት።
፲፫ እርሱ ግን መልሶ። የሰማዩ አባቴ ያልተከለው ተክል ሁሉ ይነቀላል።
፲፬ ተዉአቸው፤ ዕውሮችን የሚመሩ ዕውሮች ናቸው፤ ዕውርም ዕውርን ቢመራው ሁለቱም ወደ ጉድጓድ ይወድቃሉ አለ።
፲፭ ጴጥሮስም መልሶ። ምሳሌውን ተርጕምልን አለው።
፲፮ ኢየሱስም እንዲህ አለ። እናንተ ደግሞ እስካሁን የማታስተውሉ ናችሁን?
፲፯ ወደ አፍ የሚገባ ሁሉ ወደ ሆድ አልፎ ወደ እዳሪ እንዲጣል እትመለከቱምን?
፲፰ ከአፍ የሚወጣ ግን ከልብ ይወጣል፥ ሰውንም የሚያረክሰው ያ ነው።
፲፱ ከልብ ክፉ አሳብ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥ ዝሙት፥ መሰረቅ፥ በውሸት መመስከር፥ ስድብ ይወጣልና።
፳ ሰውን የሚያረክሰው ይህ ነው እንጂ፥ ባልታጠበ እጅ መብላትስ ሰውን አያረክሰውም።
፳፩ ኢየሱስም ከዚያ ወጥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር ሄደ።
፳፪ እነሆም፥ ከነዓዊት ሴት ከዚያ አገር ወጥታ። ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረኝ፤ ልጄን ጋኔን ክፉኛ ይዞአታል ብላ ጮኸች።
፳፫ እርሱ ግን አንዳች አልመለሰላትም። ደቀ መዛሙርቱም ቀርበው። በኋላችን ትጮኻለችና አሰናብታት እያሉ ለመኑት።
፳፬ እርሱም መልሶ። ከእስራኤል ቤት ለጠፉት በጎች በቀር አልተላክሁም አለ።
፳፭ እርስዋ ግን መጥታ። ጌታ ሆይ፥ እርዳኝ እያለች ሰገደችለት።
፳፮ እርሱ ግን መልሶ። የልጆችን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል አይገባም አለ።
፳፯ እርስዋም። አዎን ጌታ ሆይ፤ ቡችሎችም እኮ ከጌቶቻቸው ማዕድ የወደቀውን ፍርፋሪ ይበላሉ አለች።
፳፰ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ መልሶ። አንቺ ሴት፥ እምነትሽ ታላቅ ነው፤ እንደወደድሽ ይሁንልሽ አላት። ልጅዋም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ዳነች።
፳፱ ኢየሱስም ከዚያ አልፎ ወደ ገሊላ ባሕር አጠገብ መጣ፥ ወደ ተራራም ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ።

፱ ብዙ ሕዝብም እንካሶችን፥ ዕውሮችንም፥ ዲዳዎችንም፥ ጉንድሾችንም፥ ሌሎችንም ብዙ ይዘው ወደ እርሱ ቀረቡ፥ በኢየሱስም እግር አጠገብ ጣሉአቸው፤ ፈወሳቸውም፤
፲፩ ስለዚህም ሕዝቡ ዲዳዎች ሲናገሩ፥ ጉንድሾችም ሲድኑ፥ እንካሶችም ሲሄዱ፥ ዕውሮችም ሲያዩ አይተው ተደነቁ፤ የእሰራኤልንም አምላክ አከበሩ።
፲፪ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ። ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለ ሌላቸው እዝንላቸዋለሁ፤ በመንገድም እንዳይዝሉ ጦማቸውን ላሰናብታቸው አልወድም አላቸው።
፲፫ ደቀ መዛሙርቱም። ይህን ያህል ሕዝብ የሚያጠግብ ይህን ያህል እንጀራ በምድረ በዳ ከወዴት እናገኛለን? አሉት።
፲፬ ኢየሱስም። ሰንት እንጀራ አላችሁ? አላቸው። እነርሱም። ሰባት፥ ጥቂትም ትንሽ ዓሣ አሉት።
፲፭ ሕዝቡም በምድር ላይ እንዲቀመጡ አዘዘ፤
፲፮ ሰባቱንም እንጀራ ዓሣውንም ይዞ አመሰገነ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለሕዝቡ።
፲፯ ሁሉም በሉና ጠገቡ፥ የተረፈውንም ቁርሰራሽ ሰባት ቅርጫት ሙሉ አነሡ።
፲፰ የበሉትም ከሴቶችና ከልጆች በቀር አራት ሺህ ወንዶች ነበሩ።
፲፱ ሕዝቡንም ካሰናበተ በኋላ ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ መጌዶል አገር መጣ።

፲፮

፩ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያንም ቀርበው ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት እንዲያሳያቸው ለመኑት።
፪ እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አላቸው። በመሸ ጊዜ። ሰማዩ ቀልቶአልና ብራ ይሆናል ትላላችሁ፤
፫ ማለዳም። ሰማዩ ደምኖ ቀልቶአልና ዛሬ ይዘንባል ትላላችሁ። የሰማዩን ፊትማ መለየት ታውቃላችሁ፥ የዘመኑንስ ምልክት መለየት አትችሉምን?
፬ ክፉና አመንዝራ ትውልድ ምልክት ይሻል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት አይሰጠውም። ትቶአቸውም ሄደ።
፭ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ማዶ በመጡ ጊዜ እንጀራ መያዝን ረሱ።
፮ ኢየሱስም። ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ ተጠንቀቁና ተጠበቁ አላቸው።
፯ እነርሱም። እንጀራ ባንይዝ ነው ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ።
፰ ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው። እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እንጀራ ስለ ሌላችሁ ስለ ምን እርስ በርሳችሁ ትነጋገራላችሁ?
፱ ለአምስቱ ሺህ አምስቱ እንጀራ፥ ሰንት መሶብም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን?
፲ ወይስ ለአራቱ ሺህ ሰባቱ እንጀራ፥ ሰንት ቅርጫትም እንዳነሣችሁ ትዝ አይላችሁምን?
፲፩ ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን እርሾ እንድትጠበቁ ብዬ ስለ እንጀራ እንዳልተናገርኋችሁ እንዴት አታስተውሉምን?
፲፪ እነርሱም ከፈሪሳውያንና ከሰዱቃውያን ትምህርት እንጂ ከእንጀራ እርሾ እንዲጠበቁ እንዳላላቸው ያን ጊዜ አስተዋሉ።
፲፫ ኢየሱስም ወደ ፊልጶስ ቂሣርያ አገር በደረሰ ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን። ሰዎች የሰውን ልጅ ማን እንደ ሆነ ይሉታል? ብሎ ጠየቀ።
፲፬ እነርሱም። አንዳንዱ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ኤርምያስ ወይም ከነቢያት አንዱ ነው ይላሉ አሉት።
፲፭ እርሱም። እናንተስ እኔን ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው።
፲፮ ስምዖን ጴጥሮስም መልሶ። አንተ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ አለ።
፲፯ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ በሰማያት ያለው አባቴ እንጂ ሥጋና ደም ይህን አልገለጠልህምና ብፁዕ ነህ።
፲፰ እኔም እልሃለሁ፥ አንተ ጴጥሮስ ነህ፥ በዚችም ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፥ የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም።
፲፱ የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር የምታሰረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማያት የተፈታ ይሆናል።
፳ ያን ጊዜም እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለማንም እንዳይነግሩ ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው።
፳፩ ከዚያን ቀን ጀምሮ ኢየሱስ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ ከሽማግሌችና ከካህናት አለቆች ከጻፎችም ብዙ መከራ ይቀበልና ይገደል ዘንድ በሦስተኛውም ቀን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጥላቸው ጀመር።
፳፪ ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወሰደ። አይሁንብህ ጌታ ሆይ፤ ይህ ከቶ አይደርስብህም ብሎ ሊገሥጸው ጀመረ።
፳፫ እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን አታስብምና ዕንቅፋት ሆነህብኛል አለው።
፳፬ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ። እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።
፳፭ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታል፤ ስለ እኔ ግን ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ያገኛታል።
፳፮ ሰው ዓለሙን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል? ወይስ ሰው ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?
፳፯ የሰው ልጅ ከመላእክቱ ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና፤ ያን ጊዜም ለሁሉ እንደ ሥራው ያስረክበዋል።
፳፰ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰው ልጅ በመንግሥቱ ሲመጣ እስኪያዩ ድረስ እዚህ ከሚቆሙት ሞትን የማይቀምሱ እንዳንድ አሉ።

፲፯

፩ ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው።
፪ በፊታቸውም ተለወጠ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፥ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ።
፫ እነሆም፥ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው።

፬ ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ እንዱን ለአንተ እንዱንም ለሙሴ እንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ።
፭ እርሱም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፥ እነሆም፥ ከደመናው። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው፤ እርሱን ሰሙት የሚል ድምፅ መጣ።
፮ ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው በፊታቸው ወደቁ እጅግም ፈርተው ነበር።
፯ ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸውና። ተነሡ አትፍሩም አላቸው።
፰ ዓይናቸውንም አቅንተው ሲያዩ ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።
፱ ከተራራውም በወረዱ ጊዜ ኢየሱስ። የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያያችሁትን ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው።
፲ ደቀ መዛሙርቱም። እንግዲህ ጻፎች። ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ ይገባዋል ሰለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት።
፲፩ ኢየሱስም መልሶ። ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናል፤
፲፪ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ከዚህ በፊት መጣ፤ የወደዱትንም ሁሉ እደረጉበት እንጂ አላወቁትም፤ እንዲሁም ደግሞ የሰው ልጅ ከእነርሱ መከራ ይቀበል ዘንድ አለው አላቸው።
፲፫ በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሰለ መጥምቁ ሰለ ዮሐንስ እንደ ነገራቸው አስተዋሉ።
፲፬ ወደ ሕዝቡም ሲደርሱ አንድ ሰው ወደ እርሱ ቀረበና ተንበርክኮ። ጌታ ሆይ፥ ልጄን ማርልኝ፥ በጨረቃ እየተነሣበት ክፉኛ ይሣቀያልና፤
፲፭ ብዙ ጊዜ በእሳት ብዙ ጊዜም በውኃ ይወድቃልና።
፲፮ ወደ ደቀ መዛሙርትህም አመጣሁት ሊፈውሱትም አቃታቸው አለው።
፲፯ ኢየሱስም መልሶ። የማታምን ጠማማ ትውልድ ሆይ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደዚህ ወደ እኔ አምጡት አለ።
፲፰ ኢየሱስም ገሠጸው ጋኔኑም ከእርሱ ወጣ፥ ብላቴናውም ከዚያች ሰዓት ጀምሮ ተፈወሰ።
፲፱ ከዚህ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ብቻቸውን ወደ ኢየሱስ ቀረቡና። እኛ ልናወጣው ያልቻልን ሰለ ምን ነው? አሉት።
፳ ኢየሱስም። ሰለ እምነታችሁ ማነስ ነው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ተራራ። ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል፤ የሚሳናችሁም ነገር የለም።
፳፩ ይህ ዓይነት ግን ከጸሎትና ከጦም በቀር አይወጣም አላቸው።
፳፪ በገሊላም ሲመላለሱ ኢየሱስ። የሰው ልጅ በሰዎች እጅ አልፎ ይሰጥ ዘንድ አለው፥
፳፫ ይገድሉትማል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው። እጅግም አዘኑ።
፳፬ ወደ ቅፍርናሆምም በመጡ ጊዜ ግብር የሚቀበሉ ሰዎች ወደ ጴጥሮስ ቀረቡና። መምህራችሁ ሁለቱን ዲናር*ፍ1* አይገብርምን? አሉት።
፳፭ እዎን ይገብራል አለ። ወደ ቤትም በገባ ጊዜ ኢየሱስ አስቀድሞ። ስምዖን ሆይ፥ ምን ይመስልሃል? የምድር ነገሥታት ቀረጥና ግብር ከማን ይቀበላሉ? ከልጆቻቸውን ወይስ ከእንግዶች? አለው።
፳፮ ጴጥሮስም። ከእንግዶች ባለው ጊዜ ኢየሱስ። እንኪያስ ልጆቻቸው ነጻ ናቸው።
፳፯ ነገር ግን እንዳናሰናክላቸው፥ ወደ ባሕር ሂድና መቃጥን ጣል፥ መጀመሪያም የሚወጣውን ዓሣ ውሰድና አፉን ስትከፍት አስታቴር*ፍ2* ታገኛለህ፤ ያን ወስደህ ሰለ እኔና ሰለ አንተ ሰጣቸው አለው።

፲፰

፩ በዚያች ሰዓት ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው። በመንግሥተ ሰማያት ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? አሉት።
፪ ሕፃንም ጠርቶ በመካከላቸው አቆመ
፫ እንዲህም አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ካልተመለሳችሁ እንደ ሕፃናትም ካልሆናችሁ፥ ወደ መንግሥተ ሰማያት ከቶ አትገቡም።
፬ እንግዲህ እንደዚህ ሕፃን ራሱን የሚያዋርድ ሁሉ፥ በመንግሥተ ሰማያት የሚበልጥ እርሱ ነው።
፭ እንደዚህም ያለውን አንድ ሕፃን በሰሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤
፮ በእኔም ከሚያምኑ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ፥ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ጥልቅ ባሕር መሰጠም ይሻለው ነበር።
፯ ወዮ ለዓለም ሰለ ማሰናከያ፤ ማሰናከያ ሳይመጣ አይቀርምና፥ ነገር ግን በእርሱ ጠንቅ ማሰናከያ ለሚመጣበት ለዚያ ሰው ወዮለት።
፰ እጅህ ወይም እግርህ ብታሰናክልህ፥ ቈርጠህ ከአንተ ጣላት፤ ሁለት እጅ ወይም ሁለት እግር ኖሮህ ወደ ዘላለም እሳት ከምትጣል ይልቅ አንካሳ ወይም ጉንድሽ ሆነህ ወደ ህይወት መግባት ይሻልሀል።
፱ ዓይንህ ብታሰናክልህ አውጥተህ ከአንተ ጣላት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነመ እሳት ከምትጣል ይልቅ አንዲት ዓይን ኖራህ ወደ ሕይወት መግባት ይሻልሃል።
፲ ከነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን እንዳትንቁ ተጠንቀቁ፤ መላእክቶቻቸው በሰማያት ዘወትር በሰማያት ያለውን የአባቴን ፊት ያያሉ እላችኋለሁና።
፲፩ የሰው ልጅ የጠፋውን ለማዳን መጥቶአልና።
፲፪ ምን ይመስላችኋል? ለአንድ ሰው መቶ በጎች ቢኖሩት ከእነርሱም አንዱ ቢባዝን፥ ዘጠና ዘጠኙን በተራራ ትቶ ሄዶም የባዘነውን አይፈልግምን?
፲፫ ቢያገኘውም፥ እውነት እላችኋለሁ፥ ካልባዘኑቱ ከዘጠና ዘጠኙ ይልቅ በእርሱ ደስ ይለዋል።
፲፬ እንደዚሁ ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱ እንዲጠፋ በሰማያት ያለው አባታችሁ ፈቃድ አይደለም።
፲፭ ወንድምህም ቢበድልህ፥ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻችሁን ሆናችሁ ውቀሰው። ቢሰማህ፥ ወንድምህን ገንዘብ አደረግኸው፤
፲፮ ባይሰማህ ግን፥ በሁለት ወይም በሦስት ምስክር አፍ ነገር ሁሉ እንዲጸና፥ ዳግመኛ አንድ ወይም ሁለት ከአንተ ጋር ውሰድ፤

፲፯ እነርሱንም ባይሰማ፥ ለቤተ ክርስቲያን ንገራት፤ ደግሞም ቤተ ክርስቲያንን ባይሰማት፥ እንደ አረመኔና እንደ ቀራጭ ይሁንልህ።
፲፰ እውነት እላችኋለሁ፥ በምድር የምታሰሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል።
፲፱ ደግሞ እላችኋለሁ፥ ከእናንተ ሁለቱ በምድር በማናቸውም በሚለምኑት ነገር ሁሉ ቢሰማሙ በሰማያት ካለው ከአባቴ ዘንድ ይደረግላቸዋል።
፳ ሁለት ወይም ሦስት በሰሜ በሚሰበሰቡበት በዚያ በመካከላቸው እሆናለሁና።
፳፩ በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ ወደ እርሱ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ወንድሜ ቢበድለኝ ስንት ጊዜ ልተውለት? እሰከ ሰባት ጊዜን? አለው።
፳፪ ኢየሱስ እንዲህ አለው። እሰከ ሰባ ጊዜ ሰባት እንጂ እሰከ ሰባት ጊዜ አልልህም።
፳፫ ስለዚህ መንግሥተ ሰማያት ባሮቹን ሊቈጣጠር የወደደን ንጉሥ ትመሰላለች።
፳፬ መቈጣጠርም በጀመረ ጊዜ፥ እልፍ መክሊት ዕዳ ያለበትን አንድ ሰው ወደ እርሱ አመጡ።
፳፭ የሚከፍለውም ቢያጣ፥ እርሱና ሚስቱ ልጆቹም ያለውም ሁሉ እንዲሸጥና ዕዳው እንዲከፈል ጌታው አዘዘ።
፳፮ ስለዚህ ባሪያው ወድቆ ሰገደለትና። ጌታ ሆይ፥ ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ አለው።
፳፯ የዚያም ባሪያ ጌታ አዘነለትና ለቀቀው፥ ዕዳውንም ተወለት።
፳፰ ነገር ግን ያ ባሪያ ወጥቶ ከባልንጀሮቹ ከባሮቹ መቶ ዲናር ዕዳ ያለበትን አንዱን አገኘና። ዕዳህን ክፈለኝ ብሎ ያዘና አነቀው።
፳፱ ስለዚህ ባልንጀራው ባሪያ ወድቆ። ታገሠኝ፥ ሁሉንም እከፍልሃለሁ ብሎ ለመነው።
፴ እርሱም አልወደደም፥ ግን ሄዶ ዕዳውን እስኪከፍል ድረስ በወኅኒ አኖረው።
፴፩ ባልንጀሮቹ የሆኑ ባሮችም ያደረገውን አይተው እጅግ አዘኑ፥ መጥተውም የሆነውን ሁሉ ለጌታቸው ገለጡ።
፴፪ ከዚያ ወዲያ ጌታው ጠርቶ። አንተ ክፉ ባሪያ፥ ስለ ለመንኸኝ ያን ዕዳ ሁሉ ተውሁልህ፤
፴፫ እኔ እንደ ማርሁህ ባልንጀራህ የሆነውን ያን ባሪያ ልትምረው ለአንተስ አይገባህምን? አለው።
፴፬ ጌታውም ተቈጣና ዕዳውን ሁሉ እስኪከፍለው ድረስ ለሚሣቅዩት አሳልፎ ሰጠው።
፴፭ ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።

፲፱

፩ ኢየሱስም ይህን ነገር ከፈጸመ በኋላ፥ ከገሊላ ሄዶ ወደ ይሁዳ አውራጃ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ መጣ።
፪ ብዙ ሕዝብም ተከተሉት፥ በዚያም ፈወሳቸው።
፫ ፈሪሳውያንም ወደ እርሱ ቀረቡና ሲፈትኑት። ሰው በሆነው ምክንያት ሁሉ ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? አሉት።
፬ እርሱ ግን መልሶ እንዲህ አለ። ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው፥
፭ አለም። ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን?
፮ ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው።
፯ እነርሱም። እንኪያስ ሙሴ የፍችዋን ጽሕፈት ሰጥተው እንዲፈቱአት ስለ ምን አዘዘ? አሉት።
፰ እርሱም። ሙሴስ ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ሚስቶቻችሁን ትፈቱ ዘንድ ፈቀደላችሁ፤ ከጥንት ግን እንዲህ አልነበረም።
፱ እኔ ግን እላችኋለሁ፥ ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን ፈትቶ ሌላዪቱን የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ያመነዝራል አላቸው።
፲ ደቀ መዛሙርቱም። የባልና የሚስት ሥርዓት እንዲህ ከሆነ መጋባት አይጠቅምም አሉት።
፲፩ እርሱ ግን። ይህ ነገር ለተሰጣቸው ነው እንጂ ለሁሉ አይደለም፤
፲፪ በእናት ማኅፀን ጃንደረቦች ሆነው የተወለዱ አሉ፥ ሰውም የሰለባቸው ጃንደረቦች አሉ፥ ስለ መንግሥተ ሰማያትም ራሳቸውን የሰለቡ ጃንደረቦች አሉ። ሊቀበለው የሚችል ይቀበለው አላቸው።
፲፫ በዚያን ጊዜ እጁን እንዲጭንባቸውና እንዲጸልይ ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም ገሠጹአቸው።
፲፬ ነገር ግን ኢየሱስ። ሕፃናትን ተዉአቸው፥ ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ እትከልክሉአቸው፤ መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉ ናትና አለ፤
፲፭ እጁንም ጫነባቸውና ከዚያ ሄደ።
፲፮ እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ። መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው።
፲፯ እርሱም። ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።
፲፰ እርሱም። የትኞችን? አለው። ኢየሱስም። አትግደል፥ አታመንዝር፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥
፲፱ አባትህንና እናትህን አክብር፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው።
፳ ጕበዙም። ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፥ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው? አለው።
፳፩ ኢየሱስም። ፍጹም ልትሆን ብትወድ፥ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።
፳፪ ጕበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ።
፳፫ ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ። እውነት እላችኋለሁ፥ ለባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው።
፳፬ ዳግመኛም እላችኋለሁ፥ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል አለ።
፳፭ ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው እጅግ ተገረሙና። እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? አሉ።

፳፮ ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ። ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው።
፳፯ በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ። እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ፤ እንኪያስ ምን እናገኝ ይሆን? አለው።
፳፰ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተስ የተከተላችሁኝ፥ በዳግመኛ ልደት የሰው ልጅ በክብሩ ዙፋን በሚቀመጥበት ጊዜ፥ እናንተ ደግሞ በእሥራ ሁለቱ የእስራኤል ነገድ ሰትፈርዱ በእሥራ ሁለት ዙፋን ትቀመጣላችሁ።
፳፱ ስለ ስሜም ቤቶችን ወይም ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን የተወ ሁሉ መቶ እጥፍ ይቀበላል የዘላለምንም ሕይወት ይወርሳል።
፴ ነገር ግን ብዙዎቹ ፊተኞች ኋለኞች፥ ኋለኞችም ፊተኞች ይሆናሉ።

፳

፩ መንግሥተ ሰማያት ለወይኑ አትክልት ሠራተኞችን ሊቀጥር ማልዶ የወጣ ባለቤት ሰውን ትመስላለችና።
፪ ሠራተኞችንም በቀን አንድ ዲናር ተሰማምቶ ወደ ወይኑ አትክልት ሰደዳቸው።
፫ በሦስት ሰዓትም ወጥቶ ሥራ የፈቱ ሌሎችን በአደባባይ ቆመው አየ፥
፬ እነዚያንም። እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም እሰጣችኋለሁ አላቸው። እነርሱም ሄዱ።
፭ ደግሞም በሰድስትና በዘጠኝ ሰዓት ወጥቶ እንዲሁ አደረገ።
፮ በአሥራ አንደኛውም ሰዓት ወጥቶ ሌሎችን ቆመው አገኘና። ሥራ ፈትታችሁ ቀኑን ሁሉ በዚህ ሰለ ምን ትቆማላችሁ? አላቸው።
፯ የሚቀጥረን ሰለ አጣን ነው አሉት። እርሱም። እናንተ ደግሞ ወደ ወይኔ አትክልት ሂዱ የሚገባውንም ትቀበላላችሁ አላቸው።
፰ በመሸም ጊዜ የወይኑ አትክልት ጌታ አዛዡን። ሠራተኞችን ጥራና ከኋለኞች ጀምረህ እስከ ፊተኞች ድረስ ደመወዝ ሰጣቸው አለው።
፱ በአሥራ አንደኛው ሰዓትም የገቡ መጥተው እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ።
፲ ፊተኞችም በመጡ ጊዜ አብዝተው የሚቀበሉ መሰሎአቸው ነበር፤ እነርሱም ደግሞ እያንዳንዳቸው አንድ ዲናር ተቀበሉ።
፲፩-፲፪ እርሱ ግን መልሶ ከእነርሱ ለአንዱ እንዲህ አለው። ወዳጄ ሆይ፥ አልበደልሁህም በአንድ ዲናር አልተሰማማኸኝምን?
፲፫ ድርሻህን ውሰድና ሂድ፤ እኔ ለዚህ ለኋለኛው እንደ አንተ ልሰጠው እወዳለሁ፤ በገንዘቤ የወደድሁትን አደርግ ዘንድ መብት የለኝምን?
፲፬ ወይስ እኔ መልካም ሰለ ሆንሁ ዓይንህ ምቀኛ ናትን?
፲፭ እንዲሁ ኋለኞች ፊተኞች፥ ፊተኞችም ኋለኞች ይሆናሉ፤ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች ናቸውና።
፲፮ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ሊወጣ ሳለ፥ በመንገድ አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ብቻቸውን ወደ እርሱ አቅርቦ።
፲፯ እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ የሰው ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች ይሰጣል፤ የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥
፲፰ ሊዘባበቱበትም ሊገርፉትም ሊሰቅሉትም ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።
፲፱ በዚያን ጊዜ የዘብዴዎስ ልጆች እናት ከልጆችዋ ጋር እየሰገደችና አንድ ነገር እየለመነች ወደ እርሱ ቀረበች።
፳ እርሱም። ምን ትፈልጊያለሽ? አላት። እርሰዋም። እነዚህ ሁለቱ ልጆቼ አንዱ በቀኝህ አንዱም በግራህ በመንግሥትህ እንዲቀመጡ እዘዝ አለችው።
፳፩ ኢየሱስ ግን መልሶ። የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ ልጠጣው ያለውን ጽዋ ልትጠጡ እኔም የምጠመቀውን ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አለ። እንችላለን አሉት።
፳፪ እርሱም። ጽዋዬንስ ትጠጣላችሁ፤ በቀኜና በግራ መቀመጥ ግን ከአባቴ ዘንድ ለተዘጋጀላቸው ነው እንጂ እኔ የምሰጥ አይደለሁም አላቸው።
፳፫ አሥሩም ሰምተው በሁለቱ ወንድማማች ተቈጡ።
፳፬ ኢየሱስ ግን ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ አላቸው። የአሕዛብ አለቆች እንዲገዙአቸው ታላላቆቹም በላያቸው እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ።
፳፭ በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ ይሁን፥
፳፮ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የእናንተ ባሪያ ይሁን፤
፳፯ እንዲሁም የሰው ልጅ ሊያገለግል ነፍሱንም ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት አልመጣም።
፳፰ ከኢያሪኮም ሲወጡ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።
፳፱ እነሆም፥ ሁለት ዕውሮች በመንገድ ዳር ተቀምጠው፥ ኢየሱስ እንዲያልፍ በሰሙ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን ብለው ጮኹ።
፴ ሕዝቡም ዝም እንዲሉ ገሠጹአቸው፤ እነርሱ ግን። ጌታ ሆይ፥ የዳዊት ልጅ፥ ማረን እያሉ አብዝተው ጮኹ።
፴፩ ኢየሱስም ቆሞ ጠራቸውና። ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ? አለ።
፴፪ ጌታ ሆይ፥ ዓይኖቻችን ይከፈቱ ዘንድ አሉት።
፴፫ ኢየሱስም አዘነላቸውና ዓይኖቻቸውን ዳሰሰ፥ ወዲያውም አዩና ተከተሉት።

፳፩

፩ ወደ ኢየሩሳሌምም ቀርበው ወደ ደብረ ዘይት ወደ ቤተ ፋጌ ሲደርሱ፥ ያንጊዜ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ላከ፥
፪ እንዲህም አላቸው። በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ በዚያን ጊዜም የታሰረችን አህያ ውርንጫም ከእርስዋ ጋር ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ።
፫ ማንም አንዳች ቢላችሁ። ለጌታ ያስፈልጉታል በሉ፤ ወዲያውም ይሰዳቸዋል።

፬-፭ ደቀ መዛሙርቱም ሄደው ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ፥
፮ አህያይቱንና ውርንጫዋንም አመጡለት፥ ልብሳቸውንም በእነርሱ ላይ ጫኑ፥ ተቀመጠባቸውም።
፰ ከሕዝቡም እጅግ ብዙዎች ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ ሌሎችም ከዛፍ ጫፍ ጫፉን እየቈረጡ በመንገድ ላይ ያነጥፉ ነበር።
፱ የሚቀድሙትም ሕዝብ የሚከተሉትም። ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።
፲ ወደ ኢየሩሳሌምም በገባ ጊዜ መላው ከተማ። ይህ ማን ነው? ብሎ ተናወጠ።
፲፩ ሕዝቡም። ይህ ከገሊላ ናዝሬት የመጣ ነቢዩ ኢየሱስ ነው አሉ።
፲፪ ኢየሱስም ወደ መቅደስ ገባና በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ አወጣ፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጮችንም ወንበሮች ገለበጠና።
፲፫ ቤቴ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ ተጽፎአል፥ እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።
፲፬ በመቅደስም ዕውሮችና አንካሶች ወደ እርሱ ቀረቡና ፈወሳቸው።
፲፭ ነገር ግን የካህናት አለቆችና ጻፎች ያደረገውን ድንቃ ድንቅ በመቅደስም። ሆሣዕና ለዳዊት ልጅ እያሉ የሚጮኹትን ልጆች ባዩ ጊዜ፥ ተቈጥተው።
፲፮ እነዚህ የሚሉትን አትሰማምን? አሉት። ኢየሱስም። እሰማለሁ፤ ከሕፃናትና ከሚጠቡት አፍ ምስጋናን ለራስህ አዘጋጀህ የሚለውን ቃል ከቶ አላነበባችሁምን? አላቸው።
፲፯ ትቶአቸውም ከከተማ ወደ ቢታንያ ወጣ በዚያም አደረ።
፲፰ በማለዳም ወደ ከተማ ሲመለስ ተራበ።
፲፱ በመንገድም አጠገብ በለስ አይቶ ወደ እርስዋ መጣ፤ ከቅጠልም ብቻ በቀር ምንም አላገኘባትምና። ለዘላለሙ ፍሬ አይገኝብሽ አላት። በለሲቱም ያንጊዜውን ደረቀች።
፳ ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው። በለሲቱ ያንጊዜውን እንዴት ደረቀች? ብለው ተደነቁ።
፳፩ ኢየሱስም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ እምነት ቢኖራችሁ ባትጠራጠሩም፥ በበለሲቱ እንደ ሆነባት ብቻ አታደርጉም፤ ነገር ግን ይህን ተራራ እንኳ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ብትሉት ይሆናል፤
፳፪ አምናችሁም በጸሎት የምትለምኑትን ሁሉ ትቀበላላችሁ አላቸው።
፳፫ ወደ መቅደስም ገብቶ ሲያስተምር የካህናት አለቆችና የሕዝብ ሽማግሌች ወደ እርሱ ቀረቡና። በምን ሥልጣን እነዚህን ታደርጋለህ? ይህንስ ሥልጣን ማን ሰጠህ? አሉት።
፳፬ ኢየሱስም መልሶ። እኔ ደግሞ እንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ፤ እናንተም ያችን ብትነግሩኝ እኔ ደግሞ እነዚህን በምን ሥልጣን እንዳደርግ እነግራችኋለሁ፤
፳፭ የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ነበረች? ከሰማይን ወይስ ከሰው? አላቸው። እነርሱም እርስ በርሳቸው ሲነጋገሩ። ከሰማይ ብንል። እንኪያስ ሰለ ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤
፳፮ ከሰው ግን ብንል፥ ዮሐንስን ሁሉም እንደ ነቢይ ያዩታልና ሕዝቡን እንፈራለን አሉ።
፳፯ ለኢየሱስም መልሰው። አናውቅም አሉት። እርሱም ደግሞ። እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ እልነግራችሁም አላቸው።
፳፰ ነገር ግን ምን ይመስላችኋል? አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት፤ ወደ አንደኛው ቀርቦ። ልጄ ሆይ፥ ዛሬ ሂድና በወይኔ እትክልት ሥራ አለው።
፳፱ እርሱም መልሶ። አልወድም አለ፤ ኋላ ግን ተጸጸተና ሄደ።
፴ ወደ ሁለተኛውም ቀርቦ እንዲሁ አለው እርሱም መልሶ። እሺ ጌታዬ አለ፤ ነገር ግን አልሄደም።
፴፩ ከሁለቱ የአባቱን ፈቃድ ያደረገ ማን ነው? ፊተኛው አሉት። ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እላችኋለሁ፥ ቀራጮችና ጋለሞቶች ወደ እግዚአብሔር መንግሥት በመግባት ይቀድሙአችኋል።
፴፪ ዮሐንስ በጽድቅ መንገድ መጥቶላችሁ ነበርና፥ አላመናችሁበትም፤ ቀራጮችና ጋለሞቶች ግን አመኑበት፤ እናንተም ይህን አይታችሁ ታምኑበት ዘንድ በኋላ ንስሐ አልገባችሁም።
፴፫ ሌላ ምሳሌ ስሙ። የወይን አትክልት የተከለ ባለቤት ሰው ነበረ፤ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራ ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ።
፴፬ የሚያፈራበትም ጊዜ ሲቀርብ፥ ፍሬውን ሊቀበሉ ባሮቹን ወደ ገበሬዎች ላከ።
፴፭ ገበሬዎቹም ባሮቹን ይዘው አንዱን ደበደቡት አንዱንም ገደሉት ሌላውንም ወገሩት።
፴፮ ደግሞ ከፊተኞች የሚበዙ ሌሎች ባሮችን ላከ፥ እንዲሁም አደረጉባቸው።
፴፯ በኋላ ግን። ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ ልጁን ላከባቸው።
፴፰ ገበሬዎቹ ግን ልጁን ባዩ ጊዜ እርስ በርሳቸው። ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፥ እንግደለውና ርስቱን እናግኝ ተባባሉ።
፴፱ ይዘውም ከወይኑ እትክልት አወጡና ገደሉት።
፵ እንግዲህ የወይኑ እትክልት ጌታ በሚመጣ ጊዜ በእነዚህ ገበሬዎች ምን ያደርግባቸዋል?
፵፩ እነርሱም። ክፉዎችን በክፉ ያጠፋቸዋል፥ የወይኑንም እትክልት ፍሬውን በየጊዜው ለሚያስረክቡ ለሌሎች ገበሬዎች ይሰጠዋል አሉት።
፵፪ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፤ ይህም ከጌታ ዘንድ ሆነ፥ ለዓይኖቻችንም ድንቅ ነው የሚለውን ከቶ በመጽሐፍ አላነበባችሁምን?
፵፫ ስለዚህ እላችኋለሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት ከእናንተ ትወሰዳለች ፍሬዋንም ለሚያደርግ ሕዝብ ትሰጣለች።
፵፬ በዚህም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ይቀጠቀጣል፤ ድንጋዩ ግን የሚወድቅበትን ሁሉ ይፈጨዋል።
፵፭ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያንም ምሳሌዎቹን ሰምተው ስለ እነርሱ እንደ ተናገረ አስተዋሉ፤
፵፮ ሊይዙትም ሲፈልጉት ሳሉ ሕዝቡ እንደ ነቢይ ስላዩት ፈሩአቸው።

፳፪

፩ ኢየሱስም መለሰ ደግሞም በምሳሌ ነገራቸው እንዲህም አለ።

፪ መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሰርግ ያደረገ ንጉሥን
ትመስላለች።
፫ የታደሙትንም ወደ ሰርጉ ይጠሩ ዘንድ ባሮቹን
ላከ ሊመጡም አልወደዱም።
፬ ደግሞ ሌሎችን ባሮች ልኮ። የታደሙትን። እነሆ፥
ድግሴን አዘጋጀሁ፥ ኮርማዎቼና የሰቡት ከብቶቼ
ታርደዋል፥ ሁሉም ተዘጋጅቶአል፤ ወደ ሰርጉ ኑ
በሉአቸው አለ።
፭ እነርሱ ግን ቸል ብለው አንዱ ወደ እርሻው፥
ሌላውም ወደ ንግዱ ሄደ፤
፮ የቀሩትም ባሮቹን ይዘው አንገላቱአቸው
ገደሉአቸውም።
፯ ንጉሡም ተቈጣ፥ ጭፍሮቹንም ልኮ እነዚያን
ገዳዮች አጠፋ፤ ከተማቸውንም አቃጠለ።
፰ በዚያን ጊዜ ባሮቹን። ሰርጉስ ተዘጋጅቶአል፥ ነገር
ግን የታደሙት የማይገባቸው ሆኑ፤
፱ እንግዲህ ወደ መንገድ መተላለፊያ ሄዳችሁ
ያገኛችሁትን ሁሉ ወደ ሰርጉ ጥሩ አለ።
፲ እነዚያም ባሮች ወደ መንገድ ወጥተው ያገኙትን
ሁሉ ክፉዎችንም በጎዎችንም ሰበሰቡ፤ የሰርጉንም ቤት
ተቀማጮች ሞሉት።
፲፩ ንጉሡም የተቀመጡትን ለማየት በገባ ጊዜ
በዚያ የሰርግ ልብስ ያለበሰ አንድ ሰው አየና። ወዳጄ
ሆይ፥
፲፪ የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ?
አለው እርሱም ዝም አለ።
፲፫ በዚያን ጊዜ ንጉሡ አገልጋዮቹን። እጁንና እግሩን
አሰራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ
ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል አለ።
፲፬ የተጠሩ ብዙዎች፥ የተመረጡ ግን ጥቂቶች
ናቸውና።
፲፭ ስለዚህ ፈሪሳውያን ሄዱና እንዴት አድርገው
በነገር እንዲያጠምዱት ተማከሩ።
፲፮ ደቀ መዛሙርታቸውንም ከሄሮድስ ወገን
ጋር ላኩበት፥ እነርሱም። መምህር ሆይ፥ እውነተኛ
እንደ ሆንህ በእውነትም የእግዚአብሔርን መንገድ
እንድታስተምር እናውቃለን፥ ለማንምም አታደላም፥
የሰውን ፊት አትመለከትምና፤
፲፯ እንግዲህ ምን ይመስልሃል? ንገረን ለቄሣር
ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም?
አሉት።
፲፰ ኢየሱስም ክፋታቸውን አውቆ። እናንተ ግብዞች፥
ስለ ምን ትፈትኑኛላችሁ?
፲፱ የግብሩን ብር አሳዩኝ አለ። እነርሱም ዲናር
አመጡለት።
፳ እርሱም። ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት?
አላቸው።
፳፩ የቄሣር ነው አሉት። በዚያን ጊዜ። እንኪያስ
የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር
አስረክቡ አላቸው።
፳፪ ይህንም ሰምተው ተደነቁ፥ ትተውትም ሄዱ።
፳፫ በዚያን ቀን። ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ
ሰዱቃውያን ወደ እርሱ ቀረቡ፥
፳፬ እንዲህም ብለው ጠየቁት። መምህር ሆይ፥ ሙሴ
አንድ ሰው ልጅ ሳይወልድ ሲሞት ወንድሙ ሚስቱን
አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ አለ።
፳፭ ሰባት ወንድማማች በእኛ ዘንድ ነበሩ፤
ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ሞተ፥ ዘርም ስለሌለው
ሚስቱን ለወንድሙ ተወለት፤
፳፮ እንዲሁ ደግሞ ሁለተኛው ሦስተኛውም፥ እስከ
ሰባተኛው ድረስ።
፳፯ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ሞተች።
፳፰ ሁሉ እግብተዋታልና በትንሣኤ ቀንስ፥ ከሰባቱ
ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?
፳፱ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። መጻሕፍትንና
የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ትስታላችሁ።
፴ በትንሣኤስ እንደ እግዚአብሔር መላእክት
በሰማይ ይሆናሉ እንጂ አያገቡም አይጋቡምም።
፴፩-፴፫ ሕዝቡም ይህን ሰምተው በትምህርቱ
ተገረሙ።
፴፬ ፈሪሳውያንም ሰዱቃውያንን ዝም እንዳሰኛቸው
በሰሙ ጊዜ አብረው ተሰበሰቡ።
፴፭ ከእነርሱም አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው።
፴፮ መምህር ሆይ፥ ከሕግ ማናቸይቱ ትእዛዝ ታላቅ
ናት? ብሎ ጠየቀው።
፴፯ ኢየሱስም እንዲህ አለው። ጌታ አምላክህን
በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም አሳብህም
ውደድ።
፴፰ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።
፴፱ ሁለተኛይቱም ይህችን ትመስላለች፥ እርስዋም።
ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ የምትለው ናት።
፵ በእነዚህ በሁለቱ ትእዛዛት ሕጉም ሁሉ ነቢያትም
ተሰቅለዋል።
፵፩-፵፭ ዳዊትስ ጌታ ብሎ ከጠራው፥ እንዴት ልጁ
ይሆናል? አላቸው።
፵፮ አንድም ቃል ሰንኳ ይመልሰለት ዘንድ የተቻለው
የለም፥ ከዚያ ቀንም ጀምሮ ወደ ፊት ማንም
ሊጠይቀው አልደፈረም።

፳፫

፩ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለሕዝቡና ለደቀ መዛሙርቱ
እንዲህ ብሎ ነገራቸው።
፪ ጻፎችና ፈሪሳውያን በሙሴ ወንበር ተቀምጠዋል።
፫ ስለዚህ ያዘዙአችሁን ሁሉ አድርጉ ጠብቁትም፥
ነገር ግን እየተናገሩ አያደርጉትምና እንደ ሥራቸው
አታድርጉ።
፬ ከባድና አስቸጋሪ ሸክም ተብትበው በሰው ትከሻ
ይጭናሉ፥ እነርሱ ግን በጣታቸው ሰንኳ ሊነኩት
አይወዱም።
፭ ለሰውም እንዲታዩ ሥራቸውን ሁሉ ያደርጋሉ፤
ስለዚህ አሸንክታባቸውን ያሰፋሉ ዘርፉንም
ያሰረዝማሉ፥
፮ በምሳም የከበሬታ ሰፍራ፥ በምኩራብም የከበሬታ
ወንበር፥
፯ በገበያም ሰላምታና። መምህር ሆይ መምህር ሆይ
ተብለው እንዲጠሩ ይወዳሉ።
፰ እናንተ ግን። መምህር ተብላችሁ አትጠሩ፤
መምህራችሁ አንድ ሰለ ሆነ እናንተም ሁላችሁ
ወንድማማች ናችሁ።
፱ አባታችሁ አንዱ እርሱም የሰማዩ ነውና በምድር
ላይ ማንንም። አባት ብላችሁ አትጥሩ።
፲ ሊቃችሁ አንድ እርሱም ክርስቶስ ነውና።
ሊቃውንት ተብላችሁ አትጠሩ።
፲፩ ከእናንተም የሚበልጠው አገልጋያችሁ ይሆናል።

፲፪ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳል፥ ራሱንም የሚያዋርድ ሁሉ ከፍ ይላል።
፲፫ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ መንግሥተ ሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ፥ ወዮላችሁ እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ።
፲፬ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ፥ ወዮላችሁ፤ ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ።
፲፭ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ፥ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት፥ ወዮላችሁ።
፲፮ እናንተ፡ ማንም በቤተ መቅደስ የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በቤተ መቅደስ ወርቅ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል የምትሉ፥ ዕውሮች መሪዎች፥ ወዮላችሁ።
፲፯ እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? ወርቁ ነውን? ወይስ ወርቁን የቀደሰው ቤተ መቅደስ?
፲፰ ደግማችሁም፡ ማንም በመሠዊያው የሚምል ምንም የለበትም፤ ማንም በላዩ ባለው መባ የሚምል ግን በመሐላው ይያዛል ትላላችሁ።
፲፱ እናንተ ደንቆሮዎችና ዕውሮች፥ ማናቸው ይበልጣል? መባው ነውን? ወይስ መባውን የሚቀድሰው መሠዊያው?
፳ እንግዲህ በመሠዊያው የሚምለው በእርሱና በእርሱ ላይ ባለው ሁሉ ይምላል፤
፳፩ በቤተ መቅደስም የሚምለው በእርሱና በእርሱ በሚኖረው ይምላል፤
፳፪ በሰማይም የሚምለው በእግዚአብሔር ዙፋንና በእርሱ ላይ በተቀመጠው ይምላል።
፳፫ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ከአዝሙድና ከእንስላል ከኩንም አሥራት ስለምታወጡ፥ ፍርድንና ምሕረትን ታማኝነትንም፥ በሕግ ያለውን ዋና ነገር ስለምትተዉ፥ ወዮላችሁ፤ ሌላውን ሳትተዉ ይህን ልታደርጉ ይገባችሁ ነበር።
፳፬ እናንተ ዕውሮች መሪዎች፥ ትንኝን የምታጠሩ ግመልንም የምትውጡ።
፳፭ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውስጡ ቅሚያና ስስት ሞልቶ ሳለ የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ስለምታጠሩ፥ ወዮላችሁ።
፳፮ አንተ ዕውር ፈሪሳዊ፥ ውጭው ደግሞ ጥሩ እንዲሆን አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጡን አጥራ።
፳፯ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ በውጭ አምረው የሚታዩ በውስጡ ግን የሙታን አጥንት ርኩሰትም ሁሉ የተሞሉ በኖራ የተለሰኑ መቃብሮችን ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።
፳፰ እንዲሁ እናንተ ደግሞ በውጭ ለሰው እንደ ጻድቃን ትታያላችሁ፥ በውስጣችሁ ግን ግብዝነትና ዓመፀኝነት ሞልቶባችኋል።
፳፱ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ የጻድቃንንም መቃብር ስለምታስጌጡና።
፴ በአባቶቻችን ዘመን ኖረን በሆነስ በነቢያት ደም ባልተባበርናቸውም ነበር ስለምትሉ፥ ወዮላችሁ።
፴፩ እንግዲያስ የነቢያት ገዳዮች ልጆች እንደሆናችሁ በራሳችሁ ላይ ትመሰክራላችሁ።
፴፪ እናንተ ደግሞ የአባቶቻችሁን መስፈሪያ ሙሉ።
፴፫ እናንተ እባቦች፥ የእፉኝት ልጆች፥ ከገሃነም ፍርድ እንዴት ታመልጣላችሁ?
፴፬ ስለዚህ፥ እነሆ፥ ነቢያትንና ጥበበኞችን ጸፎችንም ወደ እናንተ እልካለሁ፤ ከእነርሱም ትገድላላችሁ ትሰቅሉማላችሁ፥ ከእነርሱም በምኩራባችሁ ትገርፋላችሁ ከከተማም ወደ ከተማ ታሳድዳላችሁ፤
፴፭ ከጻድቁ ከአቤል ደም ጀምሮ በቤተ መቅደስና በመሠዊያው መካከል እስከ ገደላችሁት እስከ በራክዩ ልጅ እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ በምድር ላይ የፈሰሰው የጻድቅ ደም ሁሉ ይደርሰባችሁ ዘንድ።
፴፮ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ በዚህ ትውልድ ላይ ይደርሳል።
፴፯ ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርሰዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን ከክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እስበስብ ዘንድ ሰንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም።
፴፰ እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል።
፴፱ እላችኋለሁና፥ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም።

፳፬

፩ ኢየሱስም ከመቅደስ ወጥቶ ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም የመቅደሱን ግንቦች ሊያሳዩት ቀረቡ።
፪ እርሱ ግን መልሶ፡ ይህን ሁሉ ታያላችሁን? እውነት እላችኋለሁ፥ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አላቸው።
፫ እርሱም በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ደቀ መዛሙርቱ ለብቻቸው ወደ እርሱ ቀርበው፡ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? የመምጣትህና የዓለም መጨረሻ ምልክቱስ ምንድር ነው? አሉት።
፬ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው፡ ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ።
፭ ብዙዎች፡ እኔ ክርስቶስ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ ብዙዎችንም ያስታሉ።
፮ ጦርንም የጦርንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ እላችሁ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና ተጠበቁ፥ እትደንግጡ፤ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው።
፯ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሰፍራ ይሆናል፤
፰ እነዚህም ሁሉ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።
፱ በዚያን ጊዜ ለመከራ አሳልፈው ይሰጡአችኋል ይገድሉአችሁማል፥ ስለ ስሜም በአሕዛብ ሁሉ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።
፲ በዚያን ጊዜም ብዙዎች ይሰናከላሉ እርስ በርሳቸውም አሳልፈው ይሰጣጣሉ እርስ በርሳቸውም ይጣላሉ፤
፲፩ ብዙ ሐሰተኞች ነቢያትም ይነሣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤
፲፪ ከዓመፃም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።

፲፫ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።
፲፬ ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።
፲፭ እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋትን ርኩሰት በተቀደሰችው ሰፍራ ቆሞ ስታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥
፲፮ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉት ወደ ተራራዎች ይሸሹ፥
፲፯ በሰገነትም ያለ በቤቱ ያለውን ሊወስድ አይውረድ፥
፲፰ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወስድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።
፲፱ በዚያችም ወራት ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው።
፳ ነገር ግን ሸሽታችሁ በክረምት ወይም በሰንበት እንዳይሆን ጸልዩ፤
፳፩ በዚያን ጊዜ ከዓለም መጀመሪያ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ያልሆነ እንግዲህም ከቶ የማይሆን ታላቅ መከራ ይሆናልና።
፳፪ እነዚያ ቀኖችስ ባያጥሩ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም ነበር፤ ነገር ግን እነዚያ ቀኖች ስለ ተመረጡት ሰዎች ያጥራሉ።
፳፫ በዚያን ጊዜ ማንም። እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ ወይም። ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤
፳፬ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ።
፳፭ እነሆ፥ አስቀድሜ ነገርኋችሁ።
፳፮ እንግዲህ። እነሆ፥ በበረሀ ነው ቢሉአችሁ፥ አትውጡ፤ እነሆ፥ በእልፍኝ ነው ቢሉአችሁ፥ አትመኑ፤
፳፯ መብረቅ ከምሥራቅ ወጥቶ እስከ ምዕራብ እንደሚታይ፥ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና፤
፳፰ በድን ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ።
፳፱ ከዚያች ወራትም መከራ በኋላ ወዲያው ፀሐይ ይጨልማል፥ ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥
፴ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥ የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤
፴፩ መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን ይሰበስባሉ።
፴፪ ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤
፴፫ እንዲሁ እናንተ ደግሞ ይህን ሁሉ ስታዩ በደጅ እንደ ቀረበ እወቁ።
፴፬ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።
፴፭ ሰማይና ምድር ያልፋሉ፥ ቃሌ ግን አያልፍም።
፴፮ ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም።
፴፯ የኖኅ ዘመን እንደ ነበረ የሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናልና።
፴፰ በዚያች ወራት ከጥፋት ውኃ በፊት፥ ኖኅ ወደ መርከብ እስከገባበት ቀን ድረስ፥ ሲበሉና ሲጠጡ ሲያገቡና ሲጋቡም እንደ ነበሩ፥
፴፱ የጥፋት ውኃም መጥቶ ሁሉን እስከ ወሰደ ድረስ እንዳላወቁ፥ የሰው ልጅ መምጣት ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።
፵ በዚያን ጊዜ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል አንዱም ይቀራል፤
፵፩ ሁለት ሴቶች በወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች አንዲቱም ትቀራለች።
፵፪ ጌታችሁ በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።
፵፫ ያን ግን እወቁ፤ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ ቤቱም ሊቈፈር ባልተወም ነበር።
፵፬ ስለዚህ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታሰቡበት ሰዓት ይመጣልና።
፵፭ እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎች ላይ የሾመው ታማኝና ልባም ባሪያ ማን ነው?
፵፮ ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው፤
፵፯ እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።
፵፰ ያ ክፉ ባሪያ ግን። ጌታዬ እስኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ፥
፵፱ ባልንጀሮቹን ባሮች ሊመታ ቢጀምር ከሰካሮችም ጋር ቢበላና ቢጠጣ፥
፶ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥
፶፩ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል፥ እድሉንም ከግብዞች ጋር ያደርግበታል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።

፳፭

፩ በዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ አሥር ቆነጃጅትን ትመስላለች።
፪ ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች አምስቱም ልባሞች ነበሩ።
፫ ሰነፎቹ መብራታቸውን ይዘው ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤
፬ ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።
፭ ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ ሁሉ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።
፮ እኩል ሌሊትም ሲሆን። እነሆ፥ ሙሽራው ይመጣል፥ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ።
፯ በዚያን ጊዜ እነዚያ ቆነጃጅት ሁሉ ተነሡና መብራታቸውን አዘጋጁ።
፰ ሰነፎቹም ልባሞቹን። መብራታችን ሊጠፋብን ነውና ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው።
፱ ልባሞቹ ግን መልሰው። ምናልባት ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዳችሁ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።

፲ ለገዙም በሄዱ ጊዜ ሙሽራው መጣ፥ ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፥ ደጁም ተዘጋ።
፲፩ በኋላም ደግሞ የቀሩቱ ቈነጃጅት መጡና። ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን አሉ።
፲፪ እርሱ ግን መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ አላውቃችሁም አለ።
፲፫ ቀኒቱንና ሰዓቲቱን አታውቁምና እንግዲህ ንቁ።
፲፬ ወደ ሌላ አገር የሚሄድ ሰው ባሮቹን ጠርቶ ያለውን ገንዘብ እንደ ሰጣቸው እንዲሁ ይሆናልና፤
፲፭ ለእያንዳንዱ እንደ ዓቅሙ፥ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ።
፲፮ አምስት መክሊትም የተቀበለው ሄዶ ነገደበት ሌላም አምስት አተረፈ፤
፲፯ እንዲሁም ሁለት የተቀበለው ሌላ ሁለት አተረፈ።
፲፰ አንድ የተቀበለው ግን ሄዶ ምድርን ቈፈረና የጌታውን ገንዘብ ቀበረ።
፲፱ ከብዙ ዘመንም በኋላ የእነዚያ ባሮች ጌታ መጣና ተቆጣጠራቸው።
፳ አምስት መክሊት የተቀበለውም ቀረበና ሌላ አምስት መክሊት አሰረክቦ። ጌታ ሆይ፥ አምስት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ አምስት መክሊት አተረፍሁበት አለ።
፳፩ ጌታውም። መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፤ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።
፳፪ ሁለት መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ሁለት መክሊት ሰጥተኸኝ ነበር፤ እነሆ፥ ሌላ ሁለት መክሊት አተረፍሁበት አለ።
፳፫ ጌታውም። መልካም፥ አንተ በጎ፥ ታማኝም ባሪያ፤ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ፥ ወደ ጌታህ ደስታ ግባ አለው።
፳፬ አንድ መክሊትም የተቀበለው ደግሞ ቀርቦ። ጌታ ሆይ፥ ካልዘራህባት የምታጭድ ካልበተንህባትም የምትሰበስብ ጨካኝ ሰው መሆንህን እውቃለሁ፤
፳፭ ፈራሁም ሄጄም መክሊትህን በምድር ቀበርሁት፤ እነሆ፥ መክሊትህ አለህ አለ።
፳፮ ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው። አንተ ክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁባት እንዳጭድ ካልበተንሁባትም እንድሰበስብ ታውቃለህን?
፳፯ ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች ኢደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር፥ እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወሰደው ነበር።
፳፰ ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት አሥር መክሊትም ላለው ስጡት፤
፳፱ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለትማል፤ ከሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
፴ የማይጠቅመውንም ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
፴፩ የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላእክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል፤
፴፪ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎች እንደሚለይ እርሰ በርሳቸው ይለያቸዋል፥
፴፫ በጎችን በቀኙ ፍየሎችንም በግራው ያቆማቸዋል።
፴፬ ንጉሡም በቀኙ ያሉትን እንዲህ ይላቸዋል። እናንተ የአባቴ ቡሩካን፥ ኑ፤ ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ።
፴፭ ተርቤ አብልታችሁኛልና፥ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና፥ እንግዳ ሆኜ ተቀብላችሁኛልና፥
፴፮ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና፥ ታሰሪ ወደ እኔ መጥታችኋልና።
፴፯ ጻድቃንም መልሰው ይሉታል። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ አይተን መቼ አበላንህስ? ወይስ ተጠምተህ አይተን መቼ አጠጣንህ?
፴፰ እንግዳ ሆነህስ አይተን መቼ ተቀበልንህ? ወይስ ታርዘህ አይተን መቼ አለበስንህ?
፴፱ ወይስ ታመህ ወይስ ታሰረህ አይተን መቼ ወደ አንተ መጣን?
፵ ንጉሡም መልሶ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት ይላቸዋል።
፵፩ በዚያን ጊዜ በግራው ያሉትን ደግሞ ይላቸዋል። እናንተ ርጉማን፥ ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ።
፵፪ ተርቤ አላበላችሁኝምና፥ ተጠምቼ አላጠጣችሁኝምና፥ እንግዳ ሆኜ አልተቀበላችሁኝምና፥
፵፫ ታርዤ አላለበሳችሁኝምና፥ ታምሜ ታሰሪም አልጠየቃችሁኝምና።
፵፬ እነርሱ ደግሞ ይመልሱና። ጌታ ሆይ፥ ተርበህ ወይስ ተጠምተህ ወይስ እንግዳ ሆነህ ወይስ ታርዘህ ወይስ ታመህ ወይስ ታሰረህ መቼ አይተን አላገለገልንህም? ይሉታል።
፵፭ ያን ጊዜ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ለአንዱ ስላላደረጋችሁት ለእኔ ደግሞ አላደረጋችሁትም ብሎ ይመልስላቸዋል።
፵፮ እነዚያም ወደ ዘላለም ቅጣት፥ ጻድቃን ግን ወደ ዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ።

፳፮

፩ ኢየሱስም እነዚህን ቃሎች ሁሉ በፈጸመ ጊዜ፥
፪ ለደቀ መዛሙርቱ። ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካ እንዲሆን ታውቃላችሁ፥ የሰው ልጅም ሊሰቀል አልፎ ይሰጣል አለ።
፫ በዚያን ጊዜ የካህናት አለቆች የሕዝብም ሽማግሎች ቀያፋ በሚባለው በሊቀ ካህናቱ ግቢ ተሰበሰቡ፥
፬ ኢየሱስንም በተንኰል ሊያሰይዙት ሊገድሉትም ተማከሩ፤
፭ ነገር ግን። በሕዝቡ ዘንድ ሁከት እንዳይነሣ በበዓል አይሁን አሉ።
፮ ኢየሱስም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት ሳለ፥
፯ አንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የበዛ ሽቱ የሞላው የአልባስጥሮስ ብልቃጥ ይዛ ወደ እርሱ ቀረበች በማዕድም ተቀምጦ ሳለ በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
፰ ደቀ መዛሙርቱም ይህን አይተው ተቈጡና። ይህ ጥፋት ለምንድር ነው?

፱ ይህ በብዙ ዋጋ ተሸጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና አሉ።
፲ ኢየሱስም ይህን አውቆ እንዲህ አላቸው። መልካም ሥራ ሠርታልኛለችና ሴቲቱንስ ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ?
፲፩ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም፤
፲፪ እርሰዋ ይህን ሽቱ በሰውነቴ ላይ አፍስሳ ለመቃብሬ አደረገች።
፲፫ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለም ሁሉ በማናቸውም ሰፍራ በሚሰበክበት እርሰዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርሰዋ መታሰቢያ እንዲሆን ይነገራል።
፲፬ በዚያን ጊዜ የአሰቆሮቱ ይሁዳ የሚባለው ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ወደ ካህናት አለቆች ሄደ።
፲፭ ምን ልትሰጡኝ ትወዳላችሁ እኔም አሳልፌ እሰጣችኋለሁ? እነርሱም ሠላሳ ብር መዘኑለት።
፲፮ ከዚያችም ሰዓት ጀምሮ አሳልፎ ሊሰጠው ምቹ ጊዜ ይሻ ነበር።
፲፯ በቂጣው በዓል በመጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ ወደ ኢየሱስ ቀርበው። ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ልናሰናዳልህ ትወዳለህ አሉት።
፲፰ እርሱም። ወደ ከተማ ከእገሌ ዘንድ ሄዳችሁ። መምህር። ጊዜዬ ቀርቦአል፤ ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ከእንተ ዘንድ ፋሲካን አደርጋለሁ ይላል በሉት አለ።
፲፱ ደቀ መዛሙርቱም ኢየሱስ እንዳዘዛቸው አደረጉ ፋሲካንም አሰናዱ።
፳ በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርቱ ጋር በማዕድ ተቀመጠ።
፳፩ ሲበሉም። እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ እኔን አሳልፎ ይሰጣል አለ።
፳፪ እጅግም አዘነው እያንዳንዱ። ጌታ ሆይ፥ እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር።
፳፫ እርሱም መልሶ። ከእኔ ጋር እጁን በወጭቱ ያጠለቀ፥ እኔን አሳልፎ የሚሰጥ እርሱ ነው።
፳፬ የሰው ልጅስ ሰለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፥ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አለ።
፳፭ አሳልፎ የሚሰጠው ይሁዳም መልሶ። መምህር ሆይ፥ እኔ እሆንን? አለ፤ አንተ አልህ አለው።
፳፮ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና። እንካችሁ፥ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።
፳፯ ጽዋንም አንሥቶ አመሰግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ። ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ፤
፳፰ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈሰ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው።
፳፱ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በአባቴ መንግሥት ከእናንተ ጋር ከዚህ ከወይን ፍሬ አዲሱን እሰከምጠጣበት እሰከዚያ ቀን ድረሰ ከዛሬ ጀምሬ አልጠጣውም።
፴ መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።
፴፩ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ። በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛውን እመታለሁ የመንጋውም በጎች ይበተናሉ የሚል ተጽፎአልና፤
፴፪ ከተነሣሁ በኋላ ግን ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው።
፴፫ ጴጥሮስም መልሶ። ሁሉም በአንተ ቢሰናከሉ እኔ ከቶ አልሰናከልም አለው።
፴፬ ኢየሱስ። እውነት እልሃለሁ፥ በዚች ሌሊት ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው።
፴፭ ጴጥሮስ። ከአንተ ጋር መሞት እንኳ የሚያስፈልገኝ ቢሆን፥ ከቶ አልክድህም አለው። ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ደግሞ እንደዚሁ አሉ።
፴፮ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ከእነርሱ ጋር ጌቴሴማኒ ወደምትባል ሰፍራ መጣ ደቀ መዛሙርቱንም። ወዲያ ሄጄ ሰጸልይ ሳለ በዚህ ተቀመጡ አላቸው።
፴፯ ጴጥሮስንም ሁለቱንም የዘብዴዎስን ልጆች ወስዶ ሊያዝን ሊተክዝም ጀመር።
፴፰ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቆዩ ከእኔም ጋር ትጉ አላቸው።
፴፱ ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በፊቱ ወደቀና ሲጸልይ። አባቴ፥ ቢቻልስ፥ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን አለ።
፵ ወደ ደቀ መዛሙርቱም መጣ፤ ተኝተውም አገኛቸውና ጴጥሮስን። እንዲሁም ከእኔ ጋር አንዲት ሰዓት እንኳ ልትተጉ አልቻላችሁምን?
፵፩ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉና ጸልዩ፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።
፵፪ ደግሞ ሁለተኛ ሄዶ ጸለየና። አባቴ፥ ይህች ጽዋ ሳልጠጣት ታልፍ ዘንድ የማይቻል እንደ ሆነ፥ ፈቃድህ ትሁን አለ።
፵፫ ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው።
፵፬ ደግሞም ትቶአቸው ሄደ፥ ሦስተኛም ያንኑ ቃል ደግሞ ጸለየ።
፵፭ ከዚያ ወዲያ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጥቶ። እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ እነሆ፥ ሰዓቲቱ ቀርባለች የሰው ልጅም በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።
፵፮ ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።
፵፯ ይህንም ገና ሲናገር፥ እነሆ፥ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሕዝብ ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከሕዝቡ ሽማግሎች ዘንድ መጡ።
፵፰ አሳልፎ የሚሰጠውም። የምሰመው እርሱ ነው፤ ያዙት ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር።
፵፱ ወዲያውም ወደ ኢየሱስ ቀረበና። መምህር ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ ሳመው።
፶ ኢየሱስም። ወዳጄ ሆይ፥ ለምን ነገር መጣህ? አለው። በዚያን ጊዜ ቀረቡ እጆቸውንም በኢየሱስ ላይ ጫነው ያዙት።
፶፩ እነሆም፥ ከኢየሱስ ጋር ከነበሩት አንዱ እጁን ዘርግቶ ሰይፉን መዘዘና የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ጆሮውን ቈረጠው።
፶፪ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው። ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ሰፍራው መልሰ።
፶፫ ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?
፶፬ እንዲህ ከሆነስ። እንደዚህ ሊሆን ይገባል የሚሉ መጻሕፍት እንዴት ይፈጸማሉ?

፶፭ በዚያን ሰዓት ኢየሱስ ለሕዝቡ። ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ ወጣችሁን? በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ሰቀመጥ ሳለሁ አልያዛችሁኝም።

፶፮ ነገር ግን ይህ ሁሉ የሆነ የነቢያት መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ነው አለ። በዚያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።

፶፯ ኢየሱስን የያዙትም ጻፎችና ሽማግሌች ወደ ተከማቹበት ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ወሰዱት።

፶፰ ጴጥሮስ ግን እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ድረስ ሩቅ ሆኖ ተከተለው፥ የነገሩንም ፍጻሜ ያይ ዘንድ ወደ ውስጥ ገብቶ ከሎሌዎቹ ጋር ተቀመጠ።

፶፱ የካህናት አለቆችና ሸማግሌች ሸንጐውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ የሐሰት ምስክር ይፈልጉ ነበር፥ አላገኙም፤

፷ ብዙም የሐሰት ምስክሮች ምንም ቢቀርቡ አላገኙም።

፷፩ በኋላም ሁለት ቀርበው። ይህ ሰው። የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ አፍርሼ በሦስት ቀን ልሠራው እችላለሁ ብሎአል አሉ።

፷፪ ሊቀ ካህናቱም ተነሥቶ። እነዚህ ለሚመሰክሩብህ አንድ ስንኳ አትመልሰምን? አለው።

፷፫ ኢየሱስ ግን ዝም አለ። ሊቀ ካህናቱም። አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ የሆንህ እንደ ሆነ እንድትነግረን በሕያው እግዚአብሔር አምልሃለሁ አለው።

፷፬ ኢየሱስም። አንተ አልህ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህ የሰው ልጅ በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለው።

፷፭ በዚያን ጊዜ ሊቀ ካህናቱ ልብሱን ቀደ። ተሳድቦአል እንግዲህ ወዲህ ምስክሮች ሰለ ምን ያስፈልገናል? እነሆ፥ ሰድቡን አሁን ሰምታችኋል፤ ምን ይመስላችኋል? አለ።

፷፮ እነርሱም። ሞት ይገባዋል ብለው መለሱ።

፷፯ በዚያን ጊዜ በፊቱ ተፉበት፤ ጐሰሙትም፥ ሌሎችም በጥፊ መትተው። ክርስቶስ ሆይ፥ በጥፊ የመታህ ማን ነው?

፷፰ ትንቢት ተናገርልን አሉ።

፷፱ ጴጥሮስም ከቤት ውጭ በአጥሩ ግቢ ተቀምጦ ነበር፤ እንዲት ገረድም ወደ እርሱ ቀርባ። እንተ ደግሞ ከገሊላው ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው።

፸ እርሱ ግን። የምትዪውን አላውቀውም ብሎ በሁሉ ፊት ካደ።

፸፩ ወደ በሩም ሲወጣ ሌላይቱ አየችውና በዚያ ላሉት። ይህ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበረ አለች።

፸፪ ዳግመኛም ሲምል። ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ካደ።

፸፫ ጥቂትም ቈይተው በዚያ ቆመው የነበሩ ቀርበው ጴጥሮስን። እነጋገርህ ይገልጥሃልና በእውነት አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ አሉት።

፸፬ በዚያን ጊዜ። ሰውየውን አላውቀውም ብሎ ሊራገምና ሊምል ጀመረ። ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።

፸፭ ጴጥሮስም። ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው የኢየሱስ ቃል ትዝ አለው፤ ወደ ውጭም ወጥቶ መራራ ልቅሶ አለቀሰ።

፳፯

፩ ሲነጋም የካህናት አለቆችና የሕዝቡ ሽማግሌች ሁሉ ሊገድሉት በኢየሱስ ላይ ተማከሩ፤

፪ አሰረውም ወሰዱት፥ ለገዢው ለጴንጤናዊው ጲላጦስም አሳልፈው ሰጡት።

፫ በዚያን ጊዜ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ እንደ ተፈረደበት ይቶ ተጸጸተ፥ ሠላሳውንም ብር ለካህናት አለቆችና ለሽማግሌች መልሶ።

፬ ንጹሕ ደም አሳልፌ በመሰጠቴ በድያለሁ አለ። እነርሱ ግን። እኛስ ምን አግዶን? አንተው ተጠንቀቅ አሉ።

፭ ብሩንም በቤተ መቅደስ ጥሎ ሄደና ታንቆ ሞተ።

፮ የካህናት አለቆችም ብሩን እንሥተው። የደም ዋጋ ነውና ወደ መባ ልንጨምረው አልተፈቀደም አሉ።

፯ ተማክረውም የሸክላ ሠሪውን መሬት ለእንግዶች መቃብር ገዙበት።

፰ ሰለዚህ ያ መሬት እስከ ዛሬ ድረስ የደም መሬት ተባለ።

፱ በዚያን ጊዜ በነቢዩ በኤርምያስ የተባለው። ከእስራኤል ልጆችም አንዳንዶቹ የገመቱትን፥ የተገመተውን ዋጋ ሠላሳ ብር ያዙ፥

፲ ጌታም እንዳዘዘኝ ሰለ ሸክላ ሠሪ መሬት ሰጡት። የሚል ተፈጸመ።

፲፩ ኢየሱስም በገዢው ፊት ቆመ፤ ገዢውም። የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? ብሎ ጠየቀው፤ ኢየሱስም። አንተ አልህ አለው።

፲፪ የካህናት አለቆችም ሽማግሌችም ሲከሱት ምንም አልመለሰም።

፲፫ በዚያን ጊዜ ጲላጦስ። ሰንት ያህል እንዲመስክሩብህ እትሰማምን? አለው።

፲፬ ገዢውም እጅግ እስኪደነቅ ድረስ አንዲት ቃል ሰንኳ አልመለሰለትም።

፲፭ በዚያም በዓል ሕዝቡ የወደዱትን አንድ እሰረኛ ሊፈታላቸው ለገዢው ልማድ ነበረው።

፲፮ በዚያን ጊዜም በርባን የሚባል በጣም የታወቀ እሰረኛ ነበራቸው።

፲፯ እንግዲህ እነርሱ ተሰብሰበው ሳሉ ጲላጦስ። በርባንን ወይስ ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤

፲፰ በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።

፲፱ እርሱም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ሳለ ሚስቱ። ሰለ እርሱ ዛሬ በሕልም እጅግ መከራ ተቀብያለሁና በዚያ ጻድቅ ሰው ምንም አታድርግ ብላ ላከችበት።

፳ የካህናት አለቆችና ሽማግሌች ግን በርባንን እንዲለምኑ ኢየሱስን ግን እንዲያጠፉ ሕዝቡን አባበሉ።

፳፩ ገዢውም መልሶ። ከሁለቱ ማንኛውን ልፈታላችሁ ትወዳላችሁ? አላቸው፤ እነርሱም። በርባንን አሉ።

፳፪ ጲላጦስ። ክርስቶስ የተባለውን ኢየሱስን እንግዲህ ምን ላድርገው? አላቸው፤ ሁሉም። ይሰቀል አሉ።

፳፫ ገዢውም። ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አለ፤ እነርሱ ግን። ይሰቀል እያሉ ጩኸት አበዙ።

፳፬ ጲላጦስም ሁከት እንዲጀመር እንጂ አንዳች እንዳይረባ ባየ ጊዜ፥ ውኃ አንሥቶ። እኔ ከዚህ ጻድቅ ሰው ደም ንጹሕ ነኝ፤ እናንተ ተጠንቀቁ ሲል በሕዝቡ ፊት እጁን ታጠበ።

፳፭ ሕዝቡም ሁሉ መልሰው። ደሙ በእኛና በልጆቻችን ላይ ይሁን አሉ።
፳፮ በዚያን ጊዜ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን ገርፎ ሊሰቀል አሳልፎ ሰጠ።
፳፯ በዚያን ጊዜ የገዢው ወታደሮች ኢየሱስን ወደ ገዢው ግቢ ውስጥ ወሰዱት ጭፍራውንም ሁሉ ወደ እርሱ አከማቹ።
፳፰ ልብሱንም ገፈው ቀይ ልብስ አለበሱት፥
፳፱ ከእሾህም አክሊል ጎንጉነው በራሱ ላይ፥ በቀኝ እጁም መቃ አኖሩ፥ በፊቱም ተንበርክከው። የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ ዘበቱበት፤
፴ ተፉበትም መቃውንም ይዘው ራሱን መቱት።
፴፩ ከዘበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት ሊሰቅሉትም ወሰዱት።
፴፪ ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መሰቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።
፴፫ ትርጓሜው የራስ ቅል ሰፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደሚባለው ሰፍራ በደረሱ ጊዜም፥
፴፬ በሐሞት የተደባለቀ የወይን ጠጅ ሊጠጣ አቀረቡለት፤ ቀምሶም ሊጠጣው አልወደደም።
፴፭ ከሰቀሉትም በኋላ ልብሱን ዕጣ ጥለው ተካፈሉ፥
፴፮ በዚያም ተቀምጠው ይጠብቁት ነበር።
፴፯ ይህ ኢየሱስ የአይሁድ ንጉሥ ነው የሚል የክሱን ጽሕፈት ከራሱ በላይ አኖሩ።
፴፰ በዚያን ጊዜ ሁለት ወንበዶች አንዱ በቀኝ አንዱም በግራ ከእርሱ ጋር ተሰቀሉ።
፴፱ የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና።
፵ ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራው፥ ራስህን አድን፤ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ከመስቀል ውረድ አሉት።
፵፩ እንዲሁም ደግሞ የካህናት አለቆች ከጻፎችና ከሽማግሎች ጋር እየዘበቱበት እንዲህ አሉ።
፵፪ ሌሎችን አዳነ፥ ራሱን ሊያድን አይችልም፤ የእስራኤል ንጉሥ ከሆነ፥ አሁን ከመስቀል ይውረድ እኛም እናምንበታለን።
፵፫ በእግዚአብሔር ታምኖአል፤ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ብሎአልና ከወደደውስ አሁን ያድነው።
፵፬ ከእርሱ ጋር የተሰቀሉት ወንበዶች ደግሞ ያንኑ እያሉ ይነቅፉት ነበር።
፵፭ ከሰድስት ሰዓትም ጀምሮ እስከ ዘጠኝ ሰዓት ድረስ በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
፵፮ በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ። ኤሎሄ ኤሎሄ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህም። አምላኬ አምላኬ፥ ስለ ምን ተውኸኝ? ማለት ነው።
፵፯ በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው። ይህስ ኤልያስን ይጠራል አሉ።
፵፰ ወዲያውም ከእነርሱ አንዱ ሮጠ፤ ስፍነግም ይዞ ሆምጣጤ ሞላበት፥ በመቃም አድርጎ አጠጣው።
፵፱ ሌሎቹ ግን። ተው፥ ኤልያስ መጥቶ ያድነው እንደ ሆነ እንይ አሉ።
፶ ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምፅ ጮኾ ነፍሱን ተወ።
፶፩ እነሆም፥ የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፥ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፤
፶፪ መቃብሮችም ተከፈቱ፥ ተኛተው ከነበሩትም ከቅዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ፤
፶፫ ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።
፶፬ የመቶ አለቃም ከእርሱም ጋር ኢየሱስን የሚጠብቁ መናወጡንና የሆነውን ነገር አይተው። ይህ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ ብለው እጅግ ፈሩ።
፶፭ ኢየሱስን እያገለገሉ ከገሊላ የተከተሉት ብዙ ሴቶች በሩቅ ሆነው ሲመለከቱ በዚያ ነበሩ፤
፶፮ ከእነርሱም መግደላዊት ማርያምና የያዕቆብና የዮሳ እናት ማርያም የዘብዴዎስም የልጆቹ እናት ነበሩ።
፶፯ በመሸም ጊዜ ዮሴፍ የተባለው ባለ ጠጋ ሰው ከአርማትያስ መጣ፥ እርሱም ደግሞ የኢየሱስ ደቀ መዝሙር ነበረ፤
፶፰ ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው።
፶፱ ጲላጦስም እንዲሰጡት አዘዘ። ዮሴፍም ሥጋውን ይዞ በንጹሕ በፍታ ከፈነው፥
፷ ከዓለት በወቀረው በአዲሱ መቃብርም አኖረው፥ በመቃብሩም ደጃፍ ታላቅ ድንጋይ አንከባሎ ሄደ።
፷፩ መግደላዊት ማርያምም ሁለተኛይቱም ማርያም በመቃብሩ አንጻር ተቀምጠው በዚያ ነበሩ።
፷፪ በማግሥቱም ከመዘጋጀት በኋላ በሚሆነው ቀን፥ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ወደ ጲላጦስ ተሰበሰቡና።
፷፫ ጌታ ሆይ፥ ያ አሳች በሕይወቱ ገና ሳለ። ከሦስት ቀን በኋላ እነሣለሁ እንዳለ ትዝ አለን።
፷፬ እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ መጥተው በሌሊት እንዳይሰርቁት ለሕዝቡም። ከሙታን ተነሣ እንዳይሉ፥ የኋለኛይቱ ስሕተት ከፊተኛይቱ ይልቅ የከፋች ትሆናለችና መቃብሩ እስከ ሦስተኛ ቀን ድረስ እንዲጠበቅ እዘዝ አሉት።
፷፭ ጲላጦስም። ጠባቆች አሉአችሁ፤ ሄዳችሁ እንዳወቃችሁ አሰጠብቁ አላቸው።
፷፮ እነርሱም ሄደው ከጠባቆች ጋር ድንጋዩን አትመው መቃብሩን አሰጠበቁ።

፳፰

፩ በሰንበትም መጨረሻ መጀመሪያው ቀን ሲነጋ መግደላዊት ማርያምና ሁለተኛይቱ ማርያም መቃብሩን ሊያዩ መጡ።
፪ እነሆም፥ የጌታ መልአክ ከሰማይ ሰለ ወረደ ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፤ ቀርቦም ድንጋዩን አንከባሎ በላዩ ተቀመጠ።
፫ መልኩም እንደ መብረቅ ልብሱም እንደ በረዶ ነጭ ነበረ።
፬ ጠባቆቹም እርሱን ከመፍራት የተነሣ ተናወጡ እንደ ሞቱም ሆኑ።
፭ መልአኩም መልሶ ሴቶቹን አላቸው። እናንተስ አትፍሩ የተሰቀለውን ኢየሱስን እንድትሹ አውቃለሁና፤
፮ እንደ ተናገረ ተነሥቶአልና በዚህ የለም፤ የተኛበትን ሰፍራ ኑና እዩ።
፯ ፈጥናችሁም ሂዱና። ከሙታን ተነሣ፥ እነሆም፥ ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል በዚያም ታዩታላችሁ ብላችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ንገሩአቸው።

፳፫ እነሆም፥ ነገርኋችሁ። በፍርሃትና በታላቅ ደስታም
ፈጥነው ከመቃብር ሄዱ፥ ለደቀ መዛሙርቱም
ሊያወሩ ሮጡ።
፳፬ እነሆም፥ ኢየሱስ አገኛቸውና። ደስ ይበላችሁ
አላቸው። እነርሱም ቀርበው እግሩን ይዘው ሰገዱለት።
፳፭ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ። አትፍሩ፤ ሄዳችሁ ወደ
ገሊላ እንዲሄዱ ለወንድሞቼ ተናገሩ፥ በዚያም ያዩኛል
አላቸው።
፳፮ ሲሄዱም ሳሉ እነሆ፥ ከጠባቆቹ አንዳንድ ወደ
ከተማ መጥተው የሆነውን ሁሉ ለካህናት አለቆች
አወሩ።
፳፯ ከሽማግሌዎች ጋርም ተሰብሰበው ተማከሩና
ለጭፍሮች ብዙ ገንዘብ ሰጥተዋቸው።
፳፰ እኛ ተኝተን ሳለን ደቀ መዛሙርቱ በሌሊት
መጥተው ሰረቁት በሉ።
፳፱ ይህም በገዢው ዘንድ የተሰማ እንደ ሆነ፥
እኛ እናሰረዳዋለን እናንተም ያለ ሥጋት እንድትሆኑ
እናደርጋለን አሉአቸው።
፴ እነርሱም ገንዘቡን ተቀብለው እንደ
አሰተማሩአቸው አደረጉ። ይህም ነገር በአይሁድ ዘንድ
እስከ ዛሬ ድረስ ሲወራ ይኖራል።
፴፩ አሥራ አንዱ ደቀ መዛሙርት ግን ኢየሱስ
ወዳዘዛቸው ተራራ ወደ ገሊላ ሄዱ፥
፴፪ ባዩትም ጊዜ ሰገዱለት፤ የተጠራጠሩ ግን ነበሩ።
፴፫-፴፭ ኢየሱስም ቀረበና እንዲህ ብሎ ተናገራቸው።
ሥልጣን ሁሉ በሰማይና በምድር ተሰጠኝ።

የማርቆስ ወንጌል

፩ የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ።
፪-፬ ዮሐንስ በምድረ በዳ እያጠመቀ የንስሐንም ጥምቀት ለኃጢአት ስርየት እየሰበከ መጣ።
፭ የይሁዳም አገር ሁሉ የኢየሩሳሌምም ሰዎች ሁሉ ወደ እርሱ ይወጡ ነበር፥ ኃጢአታቸውንም እየተናዘዙ በዮርዳኖስ ወንዝ ከእርሱ ይጠመቁ ነበር።
፮ ዮሐንስም የግመል ጠጕር ለብሶ በወገቡ ጠፍር ይታጠቅ አንበጣና የበረሀ ማርም ይበላ ነበር።
፯ ተጎንብሼ የጫማውን ጠፍር መፍታት የማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ በኋላዬ ይመጣል።
፰ እኔ በውኃ አጠመቅኋችሁ እርሱ ግን በመንፈስ ቅዱስ ያጠምቃችኋል እያለ ይሰብክ ነበር።
፱ በዚያ ወራትም ኢየሱስ ከገሊላ ናዝሬት መጥቶ ከዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ ተጠመቀ።
፲ ወዲያውም ከውኃው በወጣ ጊዜ ሰማያት ሲቀደዱ መንፈስም እንደ ርግብ ሲወርድበት አየና። የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥
፲፩ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅ ከሰማያት መጣ።
፲፪ ወዲያውም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ አወጣው።
፲፫ በምድረ በዳም ከሰይጣን እየተፈተነ እርባ ቀን ሰነበተ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት።
፲፬-፲፭ በገሊላ ባሕርም አጠገብ ሲያልፍ ሰምዖንን ወንድሙንም እንድርያስን መረባቸውን ወደ ባሕር ሲጥሉ አየ፥ ዓሣ አጥማጆች ነበሩና።
፲፯ ኢየሱስም። በኋላዬ ኑና ሰዎችን አጥማጆች እንድትሆኑ አደርጋችኋለሁ አላቸው።
፲፰ ወዲያውም መረባቸውን ትተው ተከተሉት።
፲፱ ከዚያም ጥቂት እልፍ ብሎ የዘብዴዎስን ልጅ ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ደግሞ በታንኳ ላይ መረባቸውን ሲያበጁ አየ።
፳ ወዲያውም ጠራቸው አባታቸውንም ዘብዴዎስን ከሞያተኞቹ ጋር በታንኳ ላይ ትተው ተከትለውት ሄዱ።
፳፩ ወደ ቅፍርናሆምም ገቡ፤ ወዲያውም በሰንበት ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ።
፳፪ እንደ ባለ ሥልጣን ያስተምራቸው ነበር እንጂ እንደ ጻፎች አይደለምና በትምህርቱ ተገረሙ።
፳፫ በዚያን ጊዜም በምኩራባቸው ርኩስ መንፈስ ያለው ሰው ነበረ፤
፳፬ እርሱም። የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከእንተ ጋር ምን አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ አውቄአለሁ፥ የእግዚአብሔር ቅዱሱ ብሎ ጮኸ።
፳፭ ኢየሱስም። ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ ገሠጸው።
፳፮ ርኩሱም መንፈስ አንፈራገጠውና በታላቅ ድምፅ ጮኾ ከእርሱ ወጣ።
፳፯ ሁሉም። ይህ ምንድር ነው? በሥልጣን ርኩሳን መናፍስትን ያዝዛል፤ እነርሱም ይታዘዙለታልና ይህ አዲስ ትምህርት ምንድር ነው? ብለው እስኪጠያየቁ ድረስ አደነቁ።
፳፰ ዝናውም ወዲያው በየሰፍራው ወደ ገሊላ ዙሪያ ሁሉ ወጣ።
፳፱ ወዲያውም ከምኩራብ ወጥቶ ከያዕቆብና ከዮሐንስ ጋር ወደ ሰምዖንና ወደ እንድርያስ ቤት ገባ።
፴ የሰምዖንም አማት በንዳድ ታማ ተኝታ ነበር፥ ስለ እርስዋም ወዲያው ነገሩት።
፴፩ ቀርቦም እጅዋን ይዞ አስነሣት ንዳዱም ወዲያው ለቀቃትና አገለገለቻቸው።
፴፪ ፀሐይም ገብቶ በመሸ ጊዜ፥ የታመሙትንና አጋንንት ያደረባቸውን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡ፤
፴፫ ከተማይቱም ሁላ በደጅ ተሰብሰባ ነበር።
፴፬ በልዩ ልዩ ደዌም የታመሙትን ብዙዎችን ፈወሰ፥ ብዙዎችንም አጋንንት አወጣ፥ አጋንንትም ክርስቶስ መሆኑን አውቀው ነበርና ሊናገሩ አልፈቀደላቸውም።
፴፭ ማለዳም ተነሥቶ ገና ሌሊት ሳለ ወጣ ወደ ምድረ በዳም ሄዶ በዚያ ጸለየ።
፴፮ ሰምዖንና ከእርሱ ጋር የነበሩትም ገሥግሠው ተከተሉት፥
፴፯ ባገኙትም ጊዜ። ሁሉ ይፈልጉሃል አሉት።
፴፰ እርሱም። በዚያ ደግሞ ልሰብክ ወደ ሌላ ሰፍራ በቅርብ ወዳሉ መንደሮች እንሂድ ስለዚህ ወጥቻለሁና አላቸው።
፴፱ በምኩራባቸውም እየሰበከ አጋንንትንም እያወጣ ወደ ገሊላ ሁሉ መጣ።
፵ ለምጻምም ወደ እርሱ መጥቶ ተንበረከከና። ብትወድስ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።
፵፩ ኢየሱስም አዘነለት እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና። እወድዳለሁ፤ ንጻ አለው።
፵፪ በተናገረም ጊዜ ለምጹ ወዲያው ለቀቀውና ነጻ።
፵፫ በብርቱም ተናግሮ ወዲያው አወጣው፤
፵፬ ለማንም አንዳች እንዳትናገር ተጠንቀቅ፥ ነገር ግን ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ስለ መንጻትህ ሙሴ ያዘዘውን አቅርብ አለው።
፵፭ እርሱ ግን ሲወጣ ብዙ ሊሰብክና ነገሩን ሊያወራ ጀመረ፥ ስለዚህም ኢየሱስ ተገልጦ ወደ ከተማ መግባት ወደ ፊት ተሳነው፥ ነገር ግን በውጭ በምድረ በዳ ይኖር ነበር፤ ከየሰፍራውም ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

፪

፩ ከጥቂት ቀን በኋላ ወደ ቅፍርናሆም ደግሞ ገብቶ በቤት እንደ ሆነ ተሰማ።
፪ በደጅ ያለው ሰፍራም እስኪጠባቸው ድረስ ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ፤ ቃሉንም ይነግራቸው ነበር።
፫ አራት ሰዎችም የተሸከሙትን ሽባ አመጡለት።
፬ ስለ ሕዝቡም ብዛት ወደ እርሱ ማቅረብ ቢያቅታቸው እርሱ ያለበትን የቤቱን ጣራ አነሡ፥ ነድለውም ሽባው የተኛበትን አልጋ አወረዱ።
፭ ኢየሱስም እምነታቸውን አይቶ ሽባውን። አንተ ልጅ፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።
፮ ከጻፎችም አንዳንዶቹ በዚያ ተቀምጠው ነበር በልባቸውም። ይህ ሰው ስለ ምን እንደዚህ ያለ ሰድብ ይናገራል?
፯ ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው አሰቡ።

፰ ወዲያውም ኢየሱስ በልባቸው እንዲህ እንዳሰቡ በመንፈስ አውቆ እንዲህ አላቸው። በልባችሁ ይህን ስለ ምን ታሰባላችሁ?
፱ ሽባውን። ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣ አልጋህንም ተሸከምና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?
፲ ነገር ግን ለሰው ልጅ በምድር ላይ ኃጢአትን ሊያሰተሰርይ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ፤
፲፩ ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ተነሣ፥ አልጋህን ተሸከምና ወደ ቤትህ ሂድ አለው።
፲፪ ተነሥቶም ወዲያው አልጋውን ተሸክሞ በሁሉ ፊት ወጣ፥ ሰለዚህም ሰዎች ሁሉ ተገረሙና። እንዲህ ያለ ከቶ አላየንም ብለው እግዚአብሔርን አከበሩ።
፲፫ ደግሞም በባሕር አጠገብ ወጣ፤ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡና አሰተማራቸው።
፲፬ ሲያልፍም በመቅረጫው ተቀምጦ የነበረውን የእልፍዮሰን ልጅ ሌዊን አየና። ተከተለኝ አለው። ተነሥቶም ተከተለው።
፲፭ በቤቱም በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ ብዙ ቀራጮችና ኃጢአተኞች ከኢየሱሰና ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጡ፤ ብዙ ነበሩ ይከተሉትም ነበር።
፲፮ ጻፎችና ፈሪሳውያንም ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ሲበላ አይተው ለደቀ መዛሙርቱ። ከቀራ ጮችና ከኃጢአተኞች ጋር የሚበላና የሚጠጣ ሰለ ምንድር ነው? አሉ።
፲፯ ኢየሱሰም ሰምቶ። ሕመምተኞች እንጂ ብርቱዎች ባለ መድኃኒት አያሰፈልጋቸውም ኃጢአተኞችን እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።
፲፰ የዮሐንሰ ደቀ መዛሙርትና ፈሪሳውያን ይጦሙ ነበር። መጥተውም። የዮሐንሰና የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት የሚጦሙት የእነተ ደቀ መዛሙርት ግን የማይጦሙት ሰለ ምንድር ነው? አሉት።
፲፱ ኢየሱሰም አላቸው። ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎች ሊጦሙ ይችላሉን? ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሊጦሙ አይችሉም።
፳ ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ወራት ይመጣል፥ በዚያ ወራትም ይጦማሉ።
፳፩ በአረጀ ልብሰ አዲሰ እራፊ የሚጥፍ የለም፤ ቢደረግ ግን፥ አዲሱ መጣፊያ አሮጌውን ይቦጭቀዋል፥ መቀደዱም የባሰ ይሆናል።
፳፪ በአረጀ አቁማዳም አዲሰ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን፥ የወይን ጠጁ አቁማዳውን ያፈነዳል የወይኑም ጠጅ ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲሰ አቁማዳ ያኖራሉ።
፳፫ በሰንበትም በእርሻ መካከል ሲያልፍ ደቀ መዛሙርቱ እየሄዱ እሸት ይቀጥፉ ጀመር።
፳፬ ፈሪሳውያንም። እነሆ፥ በሰንበት ያልተፈቀደውን ሰለ ምን ያደርጋሉ? አሉት።
፳፭ እርሱም። ዳዊት ባሰፈለገውና በተራበ ጊዜ፥ እርሱ አብረውት ከነበሩት ጋር ያደረገውን፥ አብያተር ሊቀ ካህናት በነበረ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ቤት እንደ ገባ፥
፳፮ ከካህናት በቀር መብላት ያልተፈቀደውን የመሥዋዕትን እንጀራ እንደ በላ፥ ከእርሱም ጋር ለነበሩት እንደ ሰጣቸው ከቶ አላነበባችሁምን? አላቸው።
፳፯ ደግሞ። ሰንበት ሰለ ሰው ተፈጥሮአል እንጂ ሰው ሰለ ሰንበት አልተፈጠረም፤
፳፰ እንዲሁም የሰው ልጅ ለሰንበት እንኳ ጌታዋ ነው አላቸው።

፫

፩ ደግሞም ወደ ምኩራብ ገባ፥ በዚያም እጁ የሰለለች ሰው ነበር፤
፪ ሊከሱትም፥ በሰንበት ይፈውሰው እንደ ሆነ ይጠባበቁት ነበር።
፫ እጁ የሰለለችውንም ሰው። ተነሥተህ ወደ መካከል ና አለው።
፬ በሰንበት በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን? ወይስ ክፉ? ነፍሰ ማዳን ወይስ መግደል? አላቸው፤ እነርሱም ዝም አሉ።
፭ ሰለ ልባቸውም ድንዛዜ አዝኖ ዙሪያውን እየተመለከተ በቍጣ አያቸው፥ ሰውየውንም። እጅህን ዘርጋ አለው።
፮ ዘረጋትም፥ እጁም ዳነች። ፈሪሳውያንም ወጥተው ወዲያው እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ከሄሮድስ ወገን ጋር ተማከሩበት።
፯ ኢየሱሰም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ባህር ፈቀቅ አለ፤ ከገሊላ የመጡም ብዙ ሰዎች ተከተሉት፤
፰ እንዴት ትልቅ ነገርም እንዳደረገው ሰምተው ብዙ ሰዎች ከይሁዳ ከኢየሩሳሌምም ከኤዶምያሰም ከዮርዳኖሰ ማዶም ከጢሮሰና ከሲዶና ምድርም ወደ እርሱ መጡ።
፱ ሰዎቹም እንዳያጋፉት ታንኳን ያቆዩለት ዘንድ ደቀ መዛሙርቱን እዘዛቸው፤
፲ ብዙ ሰዎችን አድኖ ነበርና፥ ሰለዚህም ሥቃይ ያለባቸው ሁሉ እንዲዳሰሱት ይወድቁበት ነበር።
፲፩ ርኩሳን መናፍሰትም ባዩት ጊዜ በፊቱ ተደፍተው። እንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ ጮኹ።
፲፪ እንዳይገልጡትም በጣም አዘዛቸው።
፲፫ ወደ ተራራም ወጣ፥ ራሱም የወደዳቸውን ወደ እርሱ ጠራ፥ ወደ እርሱም ሄዱ።
፲፬ ከእርሱም ጋር እንዲኖሩና ለመሰበክ እንዲልካቸው፥
፲፭ ድውዮችንም ሊፈውሱ አጋንንትንም ሊያወጡ ሥልጣን ይሆንላቸው ዘንድ አሥራ ሁለት አደረገ፤
፲፮ ሰምዖንንም ጴጥሮሰ ብሎ ሰየመው፤
፲፯ የዘብዴዎሰንም ልጅ ያዕቆብን የያዕቆብንም ወንድም ዮሐንሰን ቦአኔርጌስ ብሎ ሰየማቸው፥ የነጎድጓድ ልጆች ማለት ነው፤
፲፰ እንድርያሰንም ፊልጶሰንም በርተሎሜውሰንም ማቴዎሰንም ቶማሰንም የእልፍዮሰን ልጅ ያዕቆብንም ታዴዎሰንም ቀነናዊውንም ሰምዖንን፥
፲፱ አሳልፎ የሰጠውንም የአሰቆሮቱን ይሁዳን።
፳ ወደ ቤትም መጡ፤ እንጀራም መብላት ሰንኳ እሰኪሳናቸው ድረስ እንደ ገና ብዙ ሰዎች ተሰበሰቡ።
፳፩ ዘመዶቹም ሰምተው። አበደ ብለዋልና ሊይዙት ወጡ።
፳፪ ከኢየሩሳሌም የወረዱ ጻፎችም። ብዔል ዜቡል አለበት፤ ደግሞ። በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል ብለው ተናገሩ።

፳፫ እነርሱንም ወደ እርሱ ጠርቶ በምሳሌ አላቸው። ሰይጣን ሰይጣንን ሊያወጣው እንዴት ይችላል?
፳፬ መንግሥትም እርስ በርሰዋ ከተለያየች ያች መንግሥት ልትቆም አትችልም፤
፳፭ ቤትም እርስ በርሱ ከተለያየ ያ ቤት ሊቆም አይችልም።
፳፮ ሰይጣንም ራሱን ተቃውሞ ከተለያየ፥ መጨረሻ ይሆንበታል እንጂ ሊቆም አይችልም።
፳፯ ነገር ግን አስቀድሞ ኃይለኛውን ሳያሰር ወደ ኃይለኛው ቤት ገብቶ ዕቃውን ሊበዘብዝ የሚችል የለም፥ ከዚያም ወዲያ ቤቱን ይበዘብዛል።
፳፰ እውነት እላችኋለሁ፥ ለሰው ልጆች ኃጢአት ሁሉ የሚሳደቡትም ሰድብ ሁሉ ይሰረይላቸዋል፤
፳፱ በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሳደብ ሁሉ ግን የዘላለም ኃጢአት ዕዳ ይሆንበታል እንጂ ለዘላለም አይሰረይለትም።
፴ ርኩስ መንፈስ አለበት ይሉ ነበርና።
፴፩ እናቱና ወንድሞቹም መጡ በውጭም ቆመው ወደ እርሱ ልከው አሰጠሩት።
፴፪ ብዙ ሰዎችም በዙሪያው ተቀምጠው ነበሩና። እነሆ፥ እናትህ ወንድሞችህም በውጭ ቆመው ይፈልጉሃል አሉት።
፴፫ መልሶም። እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? አላቸው።
፴፬ በዙሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩትም ተመለከተና። እነሆ እናቴ ወንድሞቼም።
፴፭ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ ነው እኅቴም እናቴም አለ።

፬

፩ ደግሞም በባሕር ዳር ሊያስተምር ጀመረ። እጅግ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ ሰለ ተሰበሰቡ እርሱ በታንኳ ገብቶ በባሕር ላይ ተቀመጠ፤ ሕዝቡም ሁሉ በባሕር ዳር በምድር ላይ ነበሩ።
፪ በምሳሌም ብዙ ያስተምራቸው ነበር፥ በትምህርቱም አላቸው። ሰሙ።
፫-፭ ሌላውም ብዙ መሬት በሌለበት በጭንጫ ላይ ወደቀና ጥልቅ መሬት ሰላልነበረው ወዲያው በቀለ፤
፮ ፀሐይም ሲወጣ ጠወለገ፥ ሥርም ሰላልነበረው ደረቀ።
፯ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾህም ወጣና አነቀው፥ ፍሬም አልሰጠም።
፰ ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀና ወጥቶ አድጎ ፍሬ ሰጠ፥ አንዱም ሠላሳ አንዱም ሰድሳ አንዱም መቶ አፈራ።
፱ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ አለ።
፲ ብቻውንም በሆነ ጊዜ፥ በዙሪያው የነበሩት ከአሥራ ሁለቱ ጋር ሰለ ምሳሌው ጠየቁት።
፲፩-፲፫ አላቸውም። ይህን ምሳሌ አታውቁምን? እንዴትሰ ምሳሌዎቹን ሁሉ ታውቃላችሁ?
፲፬ ዘሪው ቃሉን ይዘራል። ቃልም በተዘራበት በመንገድ ዳር የሆኑት እነዚህ ናቸው፥
፲፭ በሰሙት ጊዜም ሰይጣን ወዲያው መጥቶ በልባቸው የተዘራውን ቃል ይወሰዳል።
፲፮ እንዲሁም በጭንጫ ላይ የተዘሩት እነዚህ ናቸው፥ ቃሉንም ሰምተው ወዲያው በደስታ ይቀበሉታል፥
፲፯ ለጊዜውም ነው እንጂ በእነርሱ ሥር የላቸውም፥ ኋላም በቃሉ ምክንያት መከራ ወይም ሰደት በሆነ ጊዜ ወዲያው ይሰናከላሉ።
፲፰ በእሾህም የተዘሩት ሌሎች ናቸው፥ ቃሉን የሰሙት እነዚህ ናቸው፥
፲፱ የዚህም ዓለም አሳብና የባለጠግነት ማታለል የሌላውም ነገር ምኞት ገብተው ቃሉን ያንቃሉ፥ የማያፈራም ይሆናል።
፳ በመልካምም መሬት የተዘሩት ቃሉን ሰምተው የሚቀበሉት አንዱም ሠላሳ አንዱም ሰድሳ አንዱም መቶ ፍሬ የሚያፈሩት እነዚህ ናቸው።
፳፩ እንዲህም አላቸው። መብራትን ከዕንቅብ ወይስ ከአልጋ በታች ሊያኖሩት ያመጡታልን? በመቅረዝ ላይ ሊያኖሩት አይደለምን?
፳፪ እንዲገለጥ ባይሆን የተሰወረ የለምና፤ ወደ ግልጥ እንዲመጣ እንጂ የተሸሸገ የለም።
፳፫ የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይሰማ።
፳፬ አላቸውም። ምን እንድትሰሙ ተጠበቁ። በምትሰፍሩበት መሰፈሪያ ይሰፈርላችኋል ለእናንተም ይጨመርላችኋል።
፳፭ ላለው ይሰጠዋልና፤ ከሌለውም ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።
፳፮ እርሱም አለ። በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት ሌሊትና ቀን ይተኛልም ይነሣልም፥
፳፯ እርሱም እንዴት እንደሚሆን ሳያውቅ ዘሩ ይበቅላል ያድግማል።
፳፰ ምድሪቱም አውቃ በመጀመሪያ ቡቃያ ኋላም ዛላ ኋላም በዛላው ፍጹም ሰብል ታፈራለች።
፳፱ ፍሬ ግን ሲበስል መከር ደርሶአልና ወዲያው ማጭድ ይልካል።
፴ እርሱም አለ። የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን እናሰመስላታለን? ወይስ በምን ምሳሌ እንመስላታለን?
፴፩ እንደ ሰናፍጭ ቅንጣት ናት፥ እርስዋም በምድር በተዘራች ጊዜ በምድር ካለ ዘር ሁሉ ታንሳለች፤
፴፪ በተዘራችም ጊዜ ትወጣለች ከአትክልትም ሁሉ የምትበልጥ ትሆናለች፥
፴፫ የሰማይ ወፎችም በጥላዋ ሊሰፍሩ እስኪችሉ ታላላቅ ቅርንጫፎች ታደርጋለች።
፴፬ መሰማትም በሚችሉበት መጠን እነዚህን በሚመስል በብዙ ምሳሌ ቃሉን ይነግራቸው ነበር፤ ያለ ምሳሌ ግን አልነገራቸውም፥
፴፭ ለብቻቸውም ሲሆኑ ነገሩን ሁሉ ለገዛ ደቀ መዛሙርቱ ይፈታላቸው ነበር።
፴፮ በዚያም ቀን በመሸ ጊዜ። ወደ ማዶ እንሻገር አላቸው።
፴፯ ሕዝቡንም ትተው በታንኳ እንዲያው ወሰዱት፥ ሌሎች ታንኳዎችም ከእርሱ ጋር ነበሩ።
፴፰ ብርቱ ዐውሎ ነፋስም ተነሣና ውኃ በታንኳይቱ እስኪሞላ ድረስ ማዕበሉ በታንኳይቱ ይገባ ነበር።
፴፱ እርሱም በሰተኋላዋ ትራስ ተንተርሶ ተኝቶ ነበር፤ እንቅተውም። መምህር ሆይ፥ ስንጠፋ አይገድህምን? አሉት።
፵ ነቅቶም ነፋሱን ገሠጸው ባሕሩንም። ዝም በል፥ ፀጥ በል አለው። ነፋሱም ተወ ታላቅ ፀጥታም ሆነ።

፵ እንዲህ የምትፈሩ ስለ ምን ነው? እንዴትስ እምነት የላችሁም? አላቸው።
፵፩ እጅግም ፈሩና። እንግዲህ ነፋሰም ባሕርም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? ተባባሉ።

፭

፩ ወደ ባሕር ማዶም ወደ ጌርጌሴኖን አገር መጡ።
፪ ከታንኳይቱም በወጣ ጊዜ፥ ርኩስ መንፈስ የያዘው ሰው ከመቃብር ወጥቶ ወዲያው ተገናኘው፤
፫ እርሱም በመቃብር ይኖር ነበር፥ በሰንሰለትም ሰንኳ ማንም ሊያሰረው በዚያን ጊዜ አይችልም ነበር፤
፬ ብዙ ጊዜ በእግር ብረትና በሰንሰለት ይታሰር ነበርና ዳሩ ግን ሰንሰለቱን ይበጣጥስ እግር ብረቱንም ይሰባብር ነበር፥ ሊያሸንፈውም የሚችል አልነበረም፤
፭ ሁልጊዜም ሌሊትና ቀን በመቃብርና በተራራ ሆኖ ይጮኽ ነበር ሰውነቱንም በድንጋይ ይቧጭር ነበር።
፮ ኢየሱስንም ከሩቅ ባየ ጊዜ ሮጦ ሰገደለት፥
፯ በታላቅ ድምፅም እየጮኸ። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳታሠቃየኝ በእግዚአብሔር እምልሃለሁ አለ፤
፰ አንተ ርኩስ መንፈስ፥ ከዚህ ሰው ውጣ ብሎት ነበርና።
፱ ሰምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። ብዙዎች ነንና ሰሜ ሌጌዎን ነው አለው፥
፲ ከአገርም ውጭ እንዲይሰዳቸው አጥብቆ ለመነው።
፲፩ በዚያም በተራራ ጥግ ብዙ የእሪያ መንጋ ይሰማራ ነበርና።
፲፪ ወደ እሪያዎቹ እንድንገባ ሰደደን ብለው ለመኑት።
፲፫ ኢየሱስም ፈቀደላቸው። ርኩሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ገቡ፥ ሁለት ሺህም የሚያህል መንጋ ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና በባሕር ሰጠሙ።
፲፬ እረኞቹም ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩ፤ ነገሩም ምን እንደ ሆነ ለማየት መጡ።
፲፭ ወደ ኢየሱስም መጡ፥ አጋንንትም ያደሩበትን ሌጌዎንም የነበረበትን ሰው ተቀምጦ ለብሶም ልቡም ተመልሶ አዩና ፈሩ።
፲፮ ያዩት ሰዎችም አጋንንት ላደሩበት ሰው የሆነውንና ሰለ እሪያዎቹ ተረኩላቸው።
፲፯ ከአገራቸውም እንዲሄድላቸው ይለምኑት ጀመር።
፲፰ ወደ ታንኳይቱም በገባ ጊዜ አጋንንት አድረውበት የነበረው ሰው ከእርሱ ጋር እንዲኖር ለመነው።
፲፱ ኢየሱስም አልፈቀደለትም፥ ነገር ግን። ወደ ቤትህ በቤተ ሰዎችህ ዘንድ ሄደህ ጌታ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገልህ እንዴትስ እንደ ማረህ አውራላቸው አለው።
፳ ሄደም ኢየሱስ እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት አሥር ከተማ በሚባል አገር ይሰብክ ጀመር፥ ሁሉም ተደነቁ።
፳፩ ኢየሱስም ደግሞ በታንኳይቱ ወደ ማዶ ከተሻገረ በኋላ ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ፥ በባሕርም አጠገብ ነበረ።
፳፪ ኢያኢሮስ የተባለ ከምኩራብ አለቆች አንዱ መጣ፤ ባየውም ጊዜ በእግሩ ላይ ወደቀና።
፳፫ ታናሽቱ ልጄ ልትሞት ቀርባለችና እንድትድንና በሕይወት እንድትኖር መጥተህ እጅህን ጫንባት ብሎ አጥብቆ ለመነው።
፳፬ ከእርሱም ጋር ሄደ። ብዙ ሕዝብም ተከተሉት አጋፉትም።
፳፭ ከአሥራ ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ነበረች፥
፳፮ ከብዙ ባለ መድኃኒቶችም ብዙ ተሠቃየች፤ ገንዘብዋንም ሁሉ ከሰራ ባሰባት እንጂ ምንም አልተጠቀመችም፤
፳፯ የኢየሱስንም ወሬ ሰምታ በሰተኋላው በሰዎች መካከል መጥታ ልብሱን ዳሰሰች።
፳፰ ልብሱን ብቻ የዳሰሰሁ እንደ ሆነ እድናለሁ ብላለችና።
፳፱ ወዲያውም የደምዋ ምንጭ ደረቀ ከሥቃይዋም እንደዳነች በሰውነትዋ አወቀች።
፴ ወዲያውም ኢየሱስ ከእርሱ ኃይል እንደ ወጣ በገዛ ራሱ አውቆ በሕዝቡ መካከል ዘወር ብሎ። ልብሴን የዳሰሰ ማን ነው? አለ።
፴፩ ደቀ መዛሙርቱም። ሕዝቡ ሲያጋፉህ እያየህ። ማን ዳሰሰኝ ትላለህን? አሉት።
፴፪ ይህንም ያደረገችውን ለማየት ዘወር ብሎ ይመለከት ነበር።
፴፫ ሴቲቱ ግን የተደረገላትን ሰላወቀች፥ እየፈራች እየተንቀጠቀጠችም፥ መጥታ በፊቱ ተደፋች እውነቱንም ሁሉ ነገረችው።
፴፬ እርሱም። ልጄ ሆይ፥ እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ ከሥቃይሽም ተፈወሽ አላት።
፴፭ እርሱም ገና ሲናገር ከምኩራብ አለቃው ቤት ዘንድ የመጡት። ልጅህ ሞታለች፤ ሰለ ምን መምህሩን አሁን ታደክመዋለህ? አሉት።
፴፮ ኢየሱስ ግን የተናገሩትን ቃል አድምጦ ለምኩራቡ አለቃ። እመን ብቻ እንጂ አትፍራ አለው።
፴፯ ከጴጥሮስም ከያዕቆብም ከያዕቆብም ወንድም ከዮሐንስ በቀር ማንም እንዲከተለው አልፈቀደም።
፴፰ ወደ ምኩራቡ አለቃ ቤትም መጥቶ ሰዎች ሲንጫጩና ሲያለቅሱ ዋይታም ሲያበዙ አየ፤
፴፱ ገብቶም። ሰለ ምን ትንጫጫላችሁ ታለቅሳላችሁም? ብላቴናይቱ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አላቸው።
፵ በጣምም ሳቁበት። እርሱ ግን ሁሉን አሰወጥቶ የብላቴናይቱን አባትና እናትም ከእርሱ ጋር የነበሩትንም ይዞ ብላቴናይቱ ወዳለችበት ገባ።
፵፩ የብላቴናይቱንም እጅ ይዞ። ጣሊታ ቁሚ አላት፤ ፍችውም አንቺ ብላቴና ተነሽ እልሻለሁ ነው።
፵፪ ብላቴናይቱም የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ ነበረችና ወዲያው ቆማ ተመላለሰች። ወዲያውም ታላቅ መገረም ተገረሙ።
፵፫ ይህንም ማንም እንዳያውቅ አጥብቆ አዞአቸው። የምትበላውን ሰጡአት አላቸው።

፮

፩ ከዚያም ወጥቶ ወደ ገዛ አገሩ መጣ ደቀ መዛሙርቱም ተከተሉት።
፪ ሰንበትም በሆነ ጊዜ በምኩራብ ያስተምር ጀመር፤ ብዙዎችም ሰምተው ተገረሙና። እነዚህን

ነገሮች ይህ ከወዴት አገኛቸው? ለዚህ የተሰጠችው ጥበብ ምንድር ናት? በእጁም የሚደረጉ እንደነዚህ ያሉ ተአምራት ምንድር ናቸው?
፫ ይህስ ጸራቢው የማርያም ልጅ የያቆብም የዮሳም የይሁዳም የሰምዖንም ወንድም እይደለምን? እኅቶቹስ በዚህ በእኛ ዘንድ አይደሉምን? አሉ፤ ይሰናከሉበትም ነበር።
፬ ኢየሱስም። ነቢይ ከገዛ አገሩና ከገዛ ዘመደቹ ከገዛ ቤቱም በቀር ሳይከበር አይቀርም አላቸው።
፭ በዚያም በጥቂቶች ድውዮች ላይ እጁን ጭኖ ከመፈወስ በቀር፥ ተአምር ሊያደርግ ምንም አልቻለም።
፮ ስለ አለማመናቸውም ተደነቀ። በመንደሮችም እያስተማረ ይዞር ነበር።
፯ አሰራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፥ በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው፥
፰ ለመንገድም ከበትር በቀር እንጀራም ቢሆን ከረጢትም ቢሆን መሐለቅም በመቀነታቸው ቢሆን እንዳይዙ አዘዛቸው።
፱ በእግራችሁ ጫማ አድርጉ እንጂ ሁለት እጀ ጠባብ አትልበሱ አለ።
፲ በማናቸውም ሰፍራ ወደ ቤት ብትገቡ ከዚያ እስክትወጡ ድረስ በዚያው ተቀመጡ።
፲፩ ከማይቀበሉአችሁና ከማይሰሙአችሁ ሰፍራ ሁሉ፥ ከዚያ ወጥታችሁ ምስክር ይሆንባቸው ዘንድ ከእግራችሁ በታች ያለውን ትቢያ አራግፉ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶምና ለገሞራ በፍርድ ቀን ይቀልላቸዋል አላቸው።
፲፪ ወጥተውም ንሰሐ እንዲገቡ ሰበኩ፥ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፥
፲፫ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሱአቸው።
፲፬ ሰሙም ተገልጦአልና ንጉሡ ሄሮድስ በሰማ ጊዜ። መጥምቁ ዮሐንስ ከሙታን ተነሥቶአል ስለዚህም ኃይል በእርሱ ይደረጋል አለ።
፲፭ ሌሎችም። ኤልያስ ነው አሉ፤ ሌሎችም። ከነቢያት እንደ አንዱ ነቢይ ነው አሉ።
፲፮ ሄሮድስ ግን ሰምቶ። እኔ ራሱን ያሰቈረጥሁት ዮሐንስ ይህ ነው እርሱ ከሙታን ተነሥቶአል አለ።
፲፯ ሄሮድስ የወንድሙን የፊልጶስን ሚስት ሄሮድያዳን አግብቶ ነበርና በእርሷዋ ምክንያት ራሱ ልኮ ዮሐንስን አሰይዞ በወኅኒ አሳሰሮት ነበር፤
፲፰ ዮሐንስ ሄሮድስን። የወንድምህ ሚስት ለእነተ ልትሆን አልተፈቀደም ይለው ነበርና።
፲፱ ሄሮድያዳ ግን ተቃውማው ልትገድለው ትፈልግ ነበር አልቻለችም፤
፳ ሄሮድስ ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው እንደ ሆነ አውቆ ይፈራውና ይጠባበቀው ነበር፤ እርሱንም ሰምቶ በብዙ ነገር ያመነታ ነበር፤
፳፩ በደስታም ይሰማው ነበር። ሄሮድስም በተወለደበት ቀን ለመኳንንቱና ለሻለቆቹ ለገሊላም ሹማምንት ግብር ባደረገ ጊዜ ምቹ ቀን ሆነላትና
፳፪ የሄሮድያዳ ልጅ ገብታ ሰትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው። ንጉሡም ብላቴናይቱን። የምትወጂውን ሁሉ ለምኚኝ እሰጥሽማለሁ አላት፤
፳፫ የመንግሥቴ እኩሌታ ሰንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት።
፳፬ ወጥታም ለእናትዋ። ምን ልለምነው? አለች። እርሰዋም። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አለች።
፳፭ ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ ብላ ለመነችው።
፳፮ ንጉሡም እጅግ አዘኖ ሰለ መሐላው ከእርሱም ጋር ሰለ ተቀመጡት ሊነሣት አልወደደም።
፳፯ ወዲያውም ንጉሡ ባለ ወግ ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘው። ሄዶም በወኅኒ ራሱን ቈረጠ፥
፳፰ ራሱንም በወጭት አምጥቶ ለብላቴናይቱ ሰጣት፥ ብላቴናይቱም ለእናትዋ ሰጠች።
፳፱ ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው መጡ በድኑንም ወሰደው ቀበሩት።
፴ ሐዋርያትም ወደ ኢየሱስ ተሰብሰበው ያደረጉትንና ያስተማሩትን ሁሉ ነገሩት።
፴፩ እናንት ራሳችሁ ብቻችሁን ወደ ምድረ በዳ ኑና ጥቂት ዕረፉ አላቸው፤ የሚመጡና የሚሄዱ ብዙዎች ነበሩና፥ ለመብላት እንኳ ጊዜ አጡ።
፴፪ በታንኳውም ብቻቸውን ወደ ምድረ በዳ ሄዱ።
፴፫ ሰዎችም ሲሄዱ አዩአቸው ብዙዎችም አወቁአቸውና ከከተሞች ሁሉ በእግር እየሮጡ ወዲያ ቀደሙአቸው ወደ እርሱም ተሰበሰቡ።
፴፬ ኢየሱስም ወጥቶ ብዙ ሕዝብ አየና እረኛ እንደሌላቸው በጎች ሰለ ነበሩ አዘነላቸው፥ ብዙም ነገር ያስተምራቸው ጀመር።
፴፭ በዚያን ጊዜም ብዙ ሰዓት ካለፈ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ወደ እርሱ ቀርበው። ቦታው ምድረ በዳ ነው አሁንም መሸቶአል፤
፴፮ የሚበሉት የላቸውምና በዙሪያ ወዳሉ ገጠሮችና መንደሮች ሄደው እንጀራ ለራሳቸው እንዲገዙ አሰናብታቸው አሉት።
፴፯ እርሱ ግን መልሶ። እናንተ የሚበሉትን ሰጡአቸው አላቸው። ሄደን እንጀራ በሁለት መቶ ዲናር እንግዛላቸውን? እንዲበሉም እንሰጣቸውን? አሉት።
፴፰ እርሱም። ስንት እንጀራ አላችሁ? ሂዱና እዩ አላቸው። ባወቁም ጊዜ። አምስት፥ ሁለትም ዓሣ አሉት።
፴፱ ሁሉንም በየክፍሉ በለመለመ ሣር ላይ እንዲያሰቀምጡአቸው አዘዛቸው።
፵ መቶ መቶውና አምሳ አምሳው እየሆኑ በተራ በተራ ተቀመጡ።
፵፩ አምስቱንም እንጀራ ሁለቱንም ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ፥ እንጀራውንም ቈርሶ እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥
፵፪ ሁለቱን ዓሣ ደግሞ ለሁሉ ከፈለ። ሁሉም በልተው ጠገቡ፤
፵፫ ከቍርስራሹም አሥራ ሁለት መሶብ የሞላ አነሡ ከዓሣውም ደግሞ።
፵፬ እንጀራውንም የበሉት ወንዶቹ አምስት ሺህ ነበሩ።
፵፭ ወዲያውም ሕዝቡን ሲያሰናብት ሳለ ደቀ መዛሙርቱ በታንኳ ገብተው ወደ ማዶ ወደ ቤተ ሳይዳ እንዲቀድሙት ግድ አላቸው።
፵፮ ካሰናበታቸውም በኋላ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ።

፶፯ በመሸም ጊዜ ታንኳይቱ በባሕር መካከል ሳለች
እርሱ ብቻውን በምድር ላይ ነበረ።
፶፰ ነፋሰ ወደ ፊታቸው ነበረና እየቀዘፉ ሲጨነቁ
አይቶ፥ ከሌሊቱ በአራተኛው ክፍል በባሕር ላይ እየሄደ
ወደ እነርሱ መጣ፤ ሊያልፋቸውም ይወድ ነበር።
፶፱ እነርሱ ግን በባሕር ላይ ሲሄድ ባዩት ጊዜ
ምትሀት መሰላቸውና ጮኹ፥
፷ ሁሉ አይተውታልና፥ ታወኩም። ወዲያውም
ተናገራቸውና። እይዞአችሁ፤ እኔ ነኝ፥ አትፍሩ አላቸው።
፷፩ ወደ እነርሱም ወደ ታንኳይቱ ገባ፥ ነፋሱም ተወ፤
በራሳቸውም ያለ መጠን እጅግ ተገረሙ፤
፷፪ ሰለ እንጀራው አላሰተዋሉምና፤ ነገር ግን
ልባቸው ደንዝዞ ነበር።
፷፫ ተሻግረውም ወደ ምድር ወደ ጌንሴሬጥ ደረሱ
ታንኳይቱንም አሰጠጉ።
፷፬ ከታንኳይቱም ሲወጡ ወዲያው አውቀውት
፷፭ በዚያች አገር ሁሉ ዙሪያ ሮጡና እርሱ እንዳለ
ወደ ሰሙበት ሰፍራ ሕመምተኞችን በአልጋ ላይ
ያመጡ ጀመር።
፷፮ በገባበትም ሰፍራ ሁሉ፥ መንደርም ከተማም
ገጠርም ቢሆን፥ በገበያ ድውዮችን ያኖሩ ነበር፤
የልብሱንም ጫፍ እንኳ ሊዳሰሱ ይለምኑት ነበር
የዳሰሱትም ሁሉ ዳኑ።

፯

፩ ፈሪሳውያንና ከጻፎች ወገን ከኢየሩሳሌም
የመጡትም ወደ እርሱ ተሰበሰቡ።
፪ ከደቀ መዛሙርቱም እንዳንድ በርኩሰ ማለት
ባልታጠበ እጅ እንጀራ ሲበሉ አዩ።
፫ ፈሪሳውያንና አይሁድም ሁሉ የሸማግሎችን
ወግ ሲጠብቁ እጃቸውን ደጋና አድርገው ሳይታጠቡ
አይበሉምና፥
፬ ከገበያም ተመልሰው ካልታጠቡ አይበሉም፥
ጽዋንም ማድጋንም የናስ ዕቃንም አልጋንም እንደ
ማጠብ ሌላ ነገር ሊጠብቁት የተቀበሉት ብዙ አለ።
፭ ፈሪሳውያንም ጸፎችም። ደቀ መዛሙርትህ እንደ
ሸማግሌዎች ወግ ሰለ ምን አይሄዱም? ነገር ግን
እጃቸውን ሳይታጠቡ እንጀራ ይበላሉ ብለው ጠየቁት።
፮ እርሱ ግን እንዲህ አላቸው። ኢሳይያስ ሰለ እናንተ
ሰለ ግብዞች። ይህ ሕዝብ በከንፈሩ ያከብረኛል ልቡ
ግን ከእኔ በጣም የራቀ ነው፤
፯ የሰውም ሥርዓት የሆነ ትምህርት እያስተማሩ
በከንቱ ያመልኩኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ በእውነት
ትንቢት ተናገረ።
፰ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ትታችሁ ጽዋን
ማድጋንም እንደ ማጠብ የሰውን ወግ ትጠብቃላችሁ፥
ይህንም የመሰለ ብዙ ሌላ ነገር ታደርጋላችሁ።
፱ እንዲህም አላቸው። ወጋችሁን ትጠብቁ ዘንድ
የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እጅግ ንቃችኋል።
፲ ሙሴ። አባትህንና እናትህን አክብር፤ ደግሞ።
አባቱን ወይም እናቱን የሰደበ ፈጽሞ ይሙት
ብሎአልና።
፲፩ እናንተ ግን ትላላችሁ። ሰው አባቱን ወይም
እናቱን። ከእኔ የምትጠቀምበት ነገር ሁሉ ቊርባን
ማለት መባ ነው ቢል፥
፲፪ ለአባቱና ለእናቱ ምንም እንኳ ሊያደርግ ወደ
ፊት አትፈቅዱለትም፤
፲፫ ባሰተላለፋችሁትም ወግ የእግዚአብሔርን ቃል
ትሽራላችሁ፤ እንደዚሁም ይህን የሚመሰል ብዙ ነገር
ታደርጋላችሁ።
፲፬ ደግሞም ሕዝቡን ጠርቶ። ሁላችሁ እኔን ሰሙ
አሰተውሉም።
፲፭ ከሰው የሚወጡት ሰውን የሚያረክሱ ናቸው
እንጂ ከሰው ውጭ የሚገባውሰ ሊያረክሰው የሚችል
ምንም የለም።
፲፮ የሚሰማ ጆሮ ያለው ቢኖር ይሰማ አላቸው።
፲፯ ከሕዝቡ ዘንድ ወደ ቤት ከገባ በኋላ ደቀ
መዛሙርቱ ምሳሌውን ጠየቁት።
፲፰ እርሱም። እናንተ ደግሞ እንደዚህ የማታሰተውሉ
ናችሁን? ከውጭ ወደ ሰው የሚገባ ሊያረክሰው
ምንም እንዳይችል አትመለከቱምን?
፲፱ ወደ ሆድ ገብቶ ወደ እዳሪ ይወጣል እንጂ ወደ
ልብ አይገባምና፤ መብልን ሁሉ እያጠራ አላቸው።
፳ እርሱም አለ። ከሰው የሚወጣው ሰውን
የሚያረክሰ ያ ነው።
፳፩ ከውሰጥ ከሰው ልብ የሚወጣ ክፉ አሳብ፥
፳፪ ዝሙት፥ መሰረቅ፥ መግደል፥ ምንዝርነት፥
መጐምጀት፥ ክፋት፥ ተንኰል፥ መዳራት፥ ምቀኝነት፥
ሰድብ፥ ትዕቢት፥ ሰንፍና ናቸውና፤
፳፫ ይህ ክፉው ሁሉ ከውሰጥ ይወጣል ሰውን
ያረክሰዋል።
፳፬ ከዚያም ተነሥቶ ወደ ጢሮስና ወደ ሲዶና አገር
ሄደ። ወደ ቤትም ገብቶ ማንም እንዳያውቅበት ወደደ
ሊሰወርም አልተቻለውም፤
፳፭ ወዲያው ግን ታናሺቱ ልጅዋ ርኩስ መንፈስ
ያደረባት እንዲት ሴት ሰለ እርሱ ሰምታ መጣችና
በእግሩ ላይ ተደፋች
፳፮ ሴቲቱም ግሪክ፥ ትውልድዋም ሲሮፊኒቃዊት
ነበረች፤ ከልጅዋ ጋኔን ያወጣላት ዘንድ ለመነችው።
፳፯ ኢየሱስ ግን። ልጆቹ በፊት ይጠግቡ ዘንድ
ተዪ የልጆቹን እንጀራ ይዞ ለቡችሎች መጣል
አይገባምናአላት።
፳፰ እርሰዋም መልሳ። አዎን፥ ጌታ ሆይ፥ ቡችሎች
እንኳ ከማዕድ በታች ሆነው የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ
አለችው።
፳፱ እርሱም። ሰለዚህ ቃልሽ ሂጂ ጋኔኑ ከልጅሽ
ወጥቶአል አላት።
፴ ወደ ቤትዋም ሄዳ ጋኔኑ ወጥቶ ልጅዋም በአልጋ
ላይ ተኝታ አገኘች።
፴፩ ደግሞም ከጢሮስ አገር ወጥቶ በሲዶና አልፎ
አሥር ከተማ በሚባል አገር መካከል ወደ ገሊላ ባሕር
መጣ።
፴፪ ደንቆሮና ኰልታፋም የሆነ ሰው ወደ እርሱ
አመጡ፥
፴፫ እጁንም ይጭንበት ዘንድ ለመኑት። ከሕዝቡም
ለይቶ ለብቻው ወሰደው፥ ጣቶቹንም በጆሮቹ አገባ
እንትፍም ብሎ መላሱን ዳሰሰ፤
፴፬ ወደ ሰማይም አሻቅቦ እይቶ ቃተተና። ኤፍታህ
አለው፥ እርሱም ተከፈት ማለት ነው።
፴፭ ወዲያውም ጆሮቹ ተከፈቱ የመላሱም እሰራት
ተፈታ አጥርቶም ተናገረ።

፴፮ ለማንም አትንገሩ ብሎ አዘዛቸው እነርሱ ግን ባዘዛቸውም መጠን ይልቅ እጅግ አወሩት።
፴፯ ያለ መጠንም ተገረሙና። ሁሉን ደኅና አድርጎአል፤ ደንቆሮችም እንዲሰሙ ዲዳዎችም እንዲናገሩ ያደርጋል አሉ።

፰

፩ በዚያ ወራት ደግሞ ብዙ ሕዝብ ነበረ የሚበሉትም ስለሌላቸው ደቀ መዛሙርቱን ጠርቶ።
፪ ሕዝቡ ከእኔ ጋር እስካሁን ሦስት ቀን ውለዋልና የሚበሉት ስለሌላቸው አዝንላቸዋለሁ፤
፫ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ከሩቅ መጥተዋልና ጦማቸውን ወደ ቤታቸው ባሰናብታቸው በመንገድ ይዝላሉ አላቸው።
፬ ደቀ መዛሙርቱም። በዚህ በምድረ በዳ እንጀራ ከየት አግኝቶ ሰው እነዚህን ማጥገብ ይችላል? ብለው መለሱለት።
፭ እርሱም። ሰንት እንጀራ አላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው፥ እነርሱም። ሰባት አሉት።
፮ ሕዝቡም በምድር እንዲቀመጡ አዘዘ። ሰባቱንም እንጀራ ይዞ አመሰገነ፥ ቈርሶም እንዲያቀርቡላቸው ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ለሕዝቡም አቀረቡ።
፯ ጥቂትም ትንሽ ዓሣ ነበራቸው፤ ባረከውም ይህንም ደግሞ እንዲያቀርቡላቸው አዘዘ።
፰ በሉም ጠገቡም፥ የተረፈውንም ቍርስራሽ ሰባት ቅርጫት አነሡ።
፱ የበሉትም አራት ሺህ ያህል ነበሩ።
፲ አሰናበታቸውም። ወዲያውም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ ዳልማኑታ አገር መጣ።
፲፩ ፈሪሳውያንም ወጡና ሊፈትኑት ከሰማይ ምልክት ከእርሱ ፈልገው ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ጀመር።
፲፪ በመንፈሱም እጅግ ቃተተና። ይህ ትውልድ ስለ ምን ምልክት ይፈልጋል? እውነት እላችኋለሁ፥ ለዚህ ትውልድ ምልክት አይሰጠውም አለ።
፲፫ ትቶአቸውም እንደ ገና ወደ ታንኳይቱ ገብቶ ወደ ማዶ ሄደ።
፲፬ እንጀራ መያዝም ረሱ፥ ለእነርሱም ከአንድ እንጀራ በቀር በታንኳይቱ አልነበራቸውም።
፲፭ እርሱም። ተጠንቀቁ፤ ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ እርሾ ተጠበቁ ብሎ አዘዛቸው።
፲፮ እርስ በርሳቸውም። እንጀራ ስለሌለን ይሆናል ብለው ተነጋገሩ።
፲፯ ኢየሱስም አውቆ እንዲህ አላቸው። እንጀራ ስለሌላችሁ ስለ ምን ትነጋገራላችሁ? ገና አልተመለከታችሁምን? አላሰተዋላችሁምን? ልባችሁስ ደንዝዞአልን?
፲፰ ዓይን ሳላችሁ አታዩምን? ጆሮስ ሳላችሁ አትሰሙምን? ትዝስ አይላችሁምን?
፲፱ አምስቱን እንጀራ ለአምስት ሺህ በቈረሰሁ ጊዜ፥ ቍርስራሹ የሞላ ሰንት መሶብ አነሣችሁ? እነርሱም። አሥራ ሁለት አሉት።
፳ ሰባቱን እንጀራስ ለአራት ሺህ በቈረሰሁ ጊዜ፥ ቍርስራሹ የሞላ ሰንት ቅርጫት አነሣችሁ? እነርሱም። ሰባት አሉት።
፳፩ ገና አላሰተዋላችሁምን? አላቸው።
፳፪ ወደ ቤተ ሳይዳም መጡ። ዕውርም አመጡለት፥ እንዲዳስሰውም ለመኑት።
፳፫ ዕውሩንም እጁን ይዞ ከመንደር ውጭ አወጣው፥ በዓይኑም ተፍቶበት እጁንም ጭኖበት። አንዳች ታያለህን ብሎ ጠየቀው።
፳፬ አሻቅቦም። ሰዎች እንደ ዛፍ ሲመላለሱ እያለሁ አለ።
፳፭ ከዚህም በኋላ ደግሞ እጁን በዓይኑ ላይ ጫነበት አጥርቶም አየና ዳነም ከሩቅም ሳይቀር ሁሉን ተመለከተ።
፳፮ ወደ ቤቱም ሰደደውና። ወደ መንደሩ አትግባ በመንደሩም ለማንም አንዳች አትናገር አለው።
፳፯ ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱም በፊልጶስ ቂሣርያ ወዳሉ መንደሮች ወጡ በመንገድም። ሰዎች እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ጠየቃቸው።
፳፰ እነርሱም። መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም ኤልያስ፥ ሌሎችም ከነቢያት አንዱ ብለው ነገሩት።
፳፱ እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። ጴጥሮስም። አንተ ክርስቶስ ነህ ብሎ መለሰለት።
፴ ስለ እርሱም ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው።
፴፩ የሰው ልጅ ብዙ መከራ ሊቀበል፥ ከሽማግሌዎችም ከካህናት አለቆችም ከጸሎችም ሊጣል፥ ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሣ እንዲገባው ያስተምራቸው ጀመር፤ ቃሉንም ገልጦ ይናገር ነበር።
፴፪ ጴጥሮስም ወደ እርሱ ወስዶ ይገሥጸው ጀመር።
፴፫ እርሱ ግን ዘወር አለ ደቀ መዛሙርቱንም አይቶ ጴጥሮስን ገሠጸውና። ወደ ኋላዬ ሂድ፥ አንተ ሰይጣን፤ የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና አለው።
፴፬ ሕዝቡንም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ጠርቶ እንዲህ አላቸው። በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።
፴፭ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን ያድናታል።
፴፮ ሰው ዓለምን ሁሉ ቢያተርፍ ነፍሱንም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?
፴፯ ሰውስ ስለ ነፍሱ ቤዛ ምን ይሰጣል?
፴፰ በዚህም በዘማዊና በኃጢአተኛ ትውልድ መካከል በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ በአባቱ ክብር ከቅዱሳን መላእክት ጋር በመጣ ጊዜ በእርሱ ያፍርበታል።

፱

፩ እውነት እላችኋለሁ፥ በዚህ ከቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ስትመጣ እስኪያዩ ድረስ፥ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንዶች አሉ አላቸው።
፪ ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፥ ልብሱም እንጸባረቀ፤
፫ እጣቢም በምድር ላይ እንደዚያ ሊያነጣው እስከማይችል በጣም ነጭ ሆነ።

፬ ኤልያስና ሙሴም ታዩአቸው፥ ከኢየሱስም ጋር ይነጋገሩ ነበር።
፭ ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን። መምህር ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና አንድ ለአንተ አንድም ለሙሴ አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶች እንሥራ አለው።
፮ እጅግ ስለ ፈሩ የሚለውን አያውቅም ነበር።
፯ ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው፥ ከደመናውም። የምወደው ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።
፰ ድንገትም ዞረው ሲመለከቱ ከእነርሱ ጋር ከኢየሱስ ብቻ በቀር ማንንም አላዩም።
፱ ከተራራውም ሲወርዱ የሰው ልጅ ከሙታን እስኪነሣ ድረስ ያዩትን ለማንም እንዲይነግሩ አዘዛቸው።
፲ ቃሉንም ይዘው። ከሙታን መነሣት ምንድር ነው? እያሉ እርስ በርሳቸው ተጠያየቁ።
፲፩ እነርሱም። ኤልያስ አስቀድሞ ሊመጣ እንዲገባው ጸፎች ስለ ምን ይላሉ? ብለው ጠየቁት።
፲፪ እርሱም መልሶ። ኤልያስማ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉንም ያቀናናል፤ ስለ ሰው ልጅም እንዴት ተብሎ ተጽፎአል? ብዙ መከራ እንዲቀበል እንዲናቅም።
፲፫ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ኤልያስ ደግሞ መጥቶአል፥ ስለ እርሱም እንደ ተጸፈ የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት አላቸው።
፲፬ ወደ ደቀ መዛሙርቱም በመጣ ጊዜ ብዙ ሕዝብ ሲከብቡአቸው ጸፎችም ከእነርሱ ጋር ሲከራከሩ አየ።
፲፭ ወዲያውም ሕዝቡ ሁሉ ባዩት ጊዜ ደነገጡ፥ ወደ እርሱም ሮጠው እጅ ነሡት።
፲፮ ጸፎችንም። ስለ ምን ከእነርሱ ጋር ትከራከራላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው።
፲፯ ከሕዝቡ አንዱ መልሶ። መምህር ሆይ፥ ዲዳ መንፈስ ያደረበትን ልጄን ወደ አንተ አምጥቼአለሁ፤
፲፰ በያዘውም ሰፍራ ሁሉ ይጥለዋል፤ አረፋም ይደፍቃል፥ ጥርሱንም ያፋጫል ይደርቃልም፤ እንዲያወጡለትም ለደቀ መዛሙርትህ ነገርኋቸው፥ አልቻሉምም አለው።
፲፱ እርሱም መልሶ። የማታምን ትውልድ ሆይ፥ እስከመቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ወደ እኔ አምጡት አላቸው።
፳ ወደ እርሱም አመጡት። እርሱንም ባየ ጊዜ ያ መንፈስ ወዲያው አንፈራገጠው፤ ወደ ምድርም ወድቆ አረፋ እየደፈቀ ተንፈራፈረ።
፳፩ አባቱንም። ይህ ከያዘው ሰንት ዘመን ነው? ብሎ ጠየቀው። እርሱም። ከሕፃንነቱ ጀምሮ ነው፤
፳፪ ብዙ ጊዜም ሊያጠፋው ወደ እሳትም ወደ ውኃም ጣለው፤ ቢቻልህ ግን እዘንልን እርዳንም አለው።
፳፫ ኢየሱስም። ቢቻልህ ትላለህ፤ ለሚያምን ሁሉ ይቻላል አለው።
፳፬ ወዲያውም የብላቴናው አባት ጮኾ። አምናለሁ፤ አለማመኔን እርዳው አለ።
፳፭ ኢየሱስም ሕዝቡ እንደ ገና ሲራወጥ አይቶ ርኩሱን መንፈስ ገሠጸና። እንተ ዲዳ ደንቆሮም መንፈስ፥ እኔ አዝሃለሁ፥ ከእርሱ ውጣ እንግዲህም አትግባበት አለው።
፳፮ ጮኾም እጅግም አንፈራግጦት ወጣ፤ ብዙዎችም። ሞተ እስኪሉ ድረስ እንደ ሙት ሆነ።
፳፯ ኢየሱስ ግን እጁን ይዞ አስነሣው ቆመም።
፳፰ ወደ ቤትም ከገባ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ። እኛ ልናወጣው ያልቻልን ስለ ምንድር ነው? ብለው ብቻውን ጠየቁት።
፳፱ ይህ ወገን በጸሎትና በጦም ካልሆነ በምንም ሊወጣ አይችልም አላቸው።
፴-፴፩ እነርሱም ነገሩን አላስተዋሉም፥ እንዳይጠይቁትም ፈሩ።
፴፪ ወደ ቅፍርናሆምም መጣ። በቤትም ሆኖ። በመንገድ እርስ በርሳችሁ ምን ተነጋገራችሁ? ብሎ ጠየቃቸው።
፴፫ እነርሱ ግን በመንገድ። ከሁሉ የሚበልጥ ማን ይሆን? ተባብለው ነበርና ዝም አሉ።
፴፬ ተቀምጦም አሥራ ሁለቱን ጠርቶ። ሰው ፊተኛ ሊሆን ቢወድ ከሁሉ በኋላ የሁሉም አገልጋይ ይሁን አላቸው።
፴፭ ሕፃንም ይዞ በመካከላቸው አቆመው አቅፎም።
፴፮ እንደዚህ ካሉ ሕፃናት አንዱን በስሜ የሚቀበል ሁሉ እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን እንጂ እኔን አይቀበልም አላቸው።
፴፯ ዮሐንስ መልሶ። መምህር ሆይ፥ አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አየነው፥
፴፰ ስለማይከተለንም ከለከልነው አለው። ኢየሱስ ግን አለ። በስሜ ተአምር ሠርቶ በቶሎ በእኔ ላይ ክፉ መናገር የሚችል ማንም የለምና አትከልክሉት፤
፴፱ የማይቃወመን እርሱ ከእኛ ጋር ነውና።
፵ የክርስቶስ ስለ ሆናችሁ በስሜ ጽዋ ውኃ የሚያጠጣችሁ ሁሉ፥ ዋጋው እንዳይጠፋበት እውነት እላችኋለሁ።
፵፩ በእኔም ከሚያምኑት ከእነዚህ ከታናናሾቹ አንዱን የሚያሰናክል ሁሉ ትልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይሻለው ነበር።
፵፪-፵፱ ሰው ሁሉ በእሳት ይቀመማልና፥ መሥዋዕትም ሁሉ በጨው ይቀመማል።
፶ ጨው መልካም ነው፤ ጨው ግን አልጫ ቢሆን በምን ታጣፍጡታላችሁ? በነፍሳችሁ ጨው ይኑርባችሁ፥ እርስ በርሳችሁም ተሰማሙ።

፲

፩ ከዚያም ተነሥቶ በዮርዳኖስ ማዶ ወደ ይሁዳ አገር መጣ፥ ደግሞም ብዙ ሰዎች ወደ እርሱ ተሰበሰቡ እንደ ልማዱም ደግሞ ያስተምራቸው ነበር።
፪ ፈሪሳውያንም ቀርበው። ሰው ሚስቱን ሊፈታ ተፈቅዶለታልን? ብለው ሊፈትኑት ጠየቁት።
፫ እርሱ ግን መልሶ። ሙሴ ምን አዘዛችሁ? አላቸው።
፬ እነርሱም። ሙሴስ የፍችዋን ጽሕፈት ጽፎ እንዲፈታት ፈቀደ አሉ።
፭ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። ስለ ልባችሁ ጥንካሬ ይህችን ትእዛዝ ጻፈላችሁ።
፮ ከፍጥረት መጀመሪያ ግን እግዚአብሔር ወንድና ሴት አደረጋቸው፤
፯ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል፥

፷፭ ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ፤ ስለዚህ አንድ ሥጋ
ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም።
፷፮ እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው
አይለየው።
፷፯ በቤትም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ስለዚህ ነገር
ጠየቁት።
፷፰ እርሱም። ሚስቱን ፈትቶ ሌላ የሚያገባ ሁሉ
በእርሷዋ ላይ ያመነዝራል፤
፷፱ እርሷዋም ባልዋን ፈትታ ሌላ ብታገባ
ታመነዝራለች አላቸው።
፸ እንዲዳሰሳቸውም ሕፃናትን ወደ እርሱ አመጡ፤
ደቀ መዛሙርቱም ያመጡአቸውን ገሠጹአቸው።
፸፩ ኢየሱስ ግን አይቶ ተቈጣና። ሕፃናትን ወደ እኔ
ይመጡ ዘንድ ተዉ አትከልክሉአቸው፤ የእግዚአብሔር
መንግሥት እንደነዚህ ላሉት ናትና።
፸፪ እውነት እላችኋለሁ፤ የእግዚአብሔርን መንግሥት
እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም
አላቸው።
፸፫ አቀፋቸውም እጁንም ጭኖ ባረካቸው።
፸፬ እርሱም በመንገድ ሲወጣ አንድ ሰው ወደ
እርሱ ሮጦ ተንበረከከለትና። ቸር መምህር ሆይ፥
የዘላለም ሕይወትን እወርስ ዘንድ ምን ላድርግ?
ብሎ ጠየቀው።
፸፭ ኢየሱስም። ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ
ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።
፸፮ ትእዛዛትን ታውቃለህ፤ አታመንዝር፥ አትግደል፥
አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አታታልል፥ አባትህንና
እናትህን አክብር አለው።
፸፯ እርሱም መልሶ። መምህር ሆይ፥ ይህን ሁሉ
ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለው።
፸፰ ኢየሱስም ወደ እርሱ ተመልክቶ ወደደውና።
አንድ ነገር ጐደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሸጠህ
ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥
መስቀሉንም ተሸክመህ ና፥ ተከተለኝ አለው።
፸፱ ነገር ግን ስለዚህ ነገር ፊቱ ጠቈረ፥ ብዙ ንብረት
ነበረውና እያዘነም ሄደ።
፹ ኢየሱስም ዘወር ብሎ አይቶ ደቀ መዛሙርቱን።
ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት
መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል አላቸው።
፹፩ ደቀ መዛሙርቱም እነዚህን ቃሎች አደነቁ።
ኢየሱስም ደግሞ መልሶ። ልጆች ሆይ፥ በገንዘብ
ለሚታመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት
እንዴት ጭንቅ ነው።
፹፪ ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ
ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢያልፍ ይቀላል አላቸው።
፹፫ እነርሱም ያለ መጠን ተገረሙና እርስ በርሳቸው።
እንግዲያ ማን ሊድን ይችላል? ተባባሉ።
፹፬ ኢየሱስም ተመለከታቸውና። ይህ በእግዚአብሔር
ዘንድ እንጂ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር
ዘንድ ሁሉ ይቻላልና አለ።
፹፭ ጴጥሮስም። እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ
ይለው ጀመር።
፹፮ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ። እውነት
እላችኋለሁ፥ ስለ እኔና ስለ ወንጌል ቤትን ወይም
ወንድሞችን ወይም እኅቶችን ወይም አባትን ወይም
እናትን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን ወይም እርሻን
የተወ፥
፹፯ አሁን በዚህ ዘመን ከስደት ጋር ቤቶችን
ወንድሞችንና እኅቶችንም እናቶችንም ልጆችንም
እርሻንም መቶ እጥፍ፥ በሚመጣውም ዓለም የዘላለም
ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም።
፹፰ ግን ብዙ ፊተኞች ኋለኞች ኋለኞችም ፊተኞች
ይሆናሉ።
፹፱ ወደ ኢየሩሳሌምም ሊወጡ በመንገድ ነበሩ፥
ኢየሱስም ይቀድማቸው ነበርና ተደነቁ፤ የተከተሉትም
ይፈሩ ነበር። ደግሞም አሥራ ሁለቱን ወደ እርሱ
አቅርቦ ይደርስበት ዘንድ ያለውን ይነግራቸው ጀመር።
፺ እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ የሰው
ልጅም ለካህናት አለቆችና ለጻፎች አልፎ ይሰጣል፥
የሞት ፍርድም ይፈርዱበታል፥ ለአሕዛብም አሳልፈው
ይሰጡታል፥
፺፩ ይዘብቱበትማል ይተፉበትማል ይገርፉትማል
ይገድሉትማል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል አላቸው።
፺፪ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ወደ
እርሱ ቀርበው። መምህር ሆይ፥ የምንለምንህን ሁሉ
እንድታደርግልን እንወዳለን አሉት።
፺፫ እርሱም። ምን ላደርግላችሁ ትወዳላችሁ?
አላቸው።
፺፬ እነርሱም። በክብርህ ጊዜ አንዳችን በቀኝ
አንዳችንም በግራህ መቀመጥን ስጠን አሉት።
፺፭ ኢየሱስ ግን። የምትለምኑትን አታውቁም። እኔ
የምጠጣውን ጽዋ ልትጠጡ፥ እኔ የምጠመቀውንስ
ጥምቀት ልትጠመቁ ትችላላችሁን? አላቸው።
፺፮ እነርሱም። እንችላለን አሉት። ኢየሱስም።
እኔ የምጠጣውን ጽዋ ትጠጣላችሁ፥ እኔ
የምጠመቀውንም ጥምቀት ትጠመቃላችሁ፤
፺፯ በቀኝና በግራ መቀመጥ ግን ለተዘጋጀላቸው ነው
እንጂ የምሰጥ እኔ አይደለሁም አላቸው።
፺፰ አሥሩም ሰምተው በያዕቆብና በዮሐንስ ይቈጡ
ጀመር።
፺፱ ኢየሱስም ወደ እርሱ ጠርቶ እንዲህ
አላቸው። የአሕዛብ አለቆች ተብሎ የምታሰቡት
እንዲገዙአቸው ታላላቆቻቸውም በላያቸው
እንዲሠለጥኑ ታውቃላችሁ።
፻ በእናንተስ እንዲህ አይደለም፤ ነገር ግን ማንም
ከእናንተ ታላቅ ሊሆን የሚወድ የእናንተ አገልጋይ
ይሁን፥
፻፩ ከእናንተም ማንም ፊተኛ ሊሆን የሚወድ የሁሉ
ባሪያ ይሁን፤
፻፪ እንዲሁ የሰው ልጅም ሊያገለግልና ነፍሱን
ለብዙዎች ቤዛ ሊሰጥ እንጂ እንዲያገለግሉት
አልመጣም።
፻፫ ወደ ኢያሪኮም መጡ። ከደቀ መዛሙርቱና ከብዙ
ሕዝብ ጋር ከኢያሪኮ ሲወጣ የጤሜዎስ ልጅ ዕውሩ
በርጤሜዎስ እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር።
፻፬ የናዝሬቱ ኢየሱስም እንደ ሆነ በሰማ ጊዜ።
የዳዊት ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ እያለ ይጮኽ ጀመር።
፻፭ ብዙዎችም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን።
የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረኝ እያለ አብዝቶ ጮኸ።
፻፮ ኢየሱስም ቆመና። ጥሩት አለ። ዕውሩንም።
እይዘህ፥ ተነሣ፥ ይጠራሃል ብለው ጠሩት።
፻፯ እርሱም እየዘለለ ተነሣና ልብሱን ጥሎ ወደ
ኢየሱስ መጣ።

፶፭ ኢየሱስም መልሶ። ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? አለው። ዕውሩም። መምህር ሆይ፥ እይ ዘንድ አለው።
፶፪ ኢየሱስም። ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው። ወዲያውም እየ በመንገድም ተከተለው።

፲፩

፩ ወደ ኢየሩሳሌምም ከደብረ ዘይት አጠገብ ወዳሉቱ ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረቡ ጊዜ፥ ከደቀ መዛሙርቱ ሁለቱን ልኮ።
፪ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ ወዲያውም ወደ እርሷዋ ገብታችሁ ከሰው ማንም ገና ያልተቀመጠበት ውርንጫ ታሰሮ ታገኛላችሁ፤ ፈትታችሁ አምጡልኝ።
፫ ማንም። ስለ ምን እንዲህ ታደርጋላችሁ? ቢላችሁ። ለጌታ ያሰፈልገዋል በሉት፥ ወዲያውም ደግሞ ወደዚህ ይሰደዋል አላቸው።
፬ ሄዱም ውርንጫውንም በመንገድ መተላለፊያ በደጅ ውጭ ታሰሮ አገኙት፥ ፈቱትም።
፭ በዚያም ከቆሙት አንዳንዶቹ። ውርንጫውን የምትፈቱት ምን ልታደርጉት ነው አሉአቸው።
፮ እነርሱም ኢየሱስ እንዳዘዘ አሉአቸው፤ ተዉአቸውም።
፯ ውርንጫውንም ወደ ኢየሱስ አመጡት፥ ልብሳቸውንም በላዩ ጣሉ፥ ተቀመጠበትም።
፰ ብዙ ሰዎችም ልብሳቸውን በመንገድ ላይ አነጠፉ፥ ሌሎችም ከዛፍ ቅጠሎችን እየቈረጡ ያነጥፉ ነበር።
፱ የሚቀድሙትም የሚከተሉትም። ሆሣዕና፤ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤
፲ በጌታ ስም የምትመጣ የአባታችን የዳዊት መንግሥት የተባረከች ናት፤ ሆሣዕና በአርያም እያሉ ይጮኹ ነበር።
፲፩ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወደ መቅደስ ገባ፤ ዘወር ብሎም ሁሉን ከተመለከተ በኋላ፥ ጊዜው መሸቶ ሰለ ነበረ ከአሥራ ሁለቱ ጋር ወደ ቢታንያ ወጣ።
፲፪ በማግሥቱም ከቢታንያ ሲወጡ ተራበ።
፲፫ ቅጠልም ያላት በለስ ከሩቅ አይቶ ምናልባት አንዳች ይገኝባት እንደ ሆነ ብሎ መጣ፥ ነገር ግን የበለስ ወራት አልነበረምና መጥቶ ከቅጠል በቀር ምንም አላገኘባትም።
፲፬ መልሶም። ከአሁን ጀምሮ ለዘላለም ማንም ከእንቺ ፍሬ አይብላ አላት። ደቀ መዛሙርቱም ሰሙ።
፲፭ ወደ ኢየሩሳሌምም መጡ። ወደ መቅደስም ገብቶ በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ያወጣ ጀመር፥ የገንዘብ ለዋጮችንም ገበታዎች የርግብ ሻጭዎችንም ወንበሮች ገለበጠ፤
፲፮ ዕቃም ተሸክሞ ማንም በመቅደስ ሊያልፍ አልፈቀደም።
፲፯ አስተማራቸውም። ቤቴ ለአሕዛብ ሁሉ የጸሎት ቤት ትባላለች ተብሎ የተጻፈ አይደለምን? እናንተ ግን የወንበዶች ዋሻ አደረጋችኋት አላቸው።
፲፰ የካህናት አለቆችም ጻፎችም ሰምተው፥ ሕዝቡ ሁሉ በትምህርቱ ይገረሙ ሰለ ነበር ይፈሩት ነበርና እንዴት አድርገው እንዲያጠፉት ፈለጉ።
፲፱ ማታ ማታም ከከተማ ወደ ውጭ ይወጣ ነበር።
፳ ማለዳም ሲያልፉ በለሲቱን ከሥርዋ ደርቃ አዩአት።
፳፩ ጴጥሮስም ትዝ ብሎት። መምህር ሆይ፥ እነሆ፥ የረገምሃት በለስ ደርቃለች አለው።
፳፪ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። በእግዚአብሔር እመኑ።
፳፫ እውነት እላችኋለሁ፥ ማንም ያለው ነገር እንዲደረግለት ቢያምን በልቡ ሳይጠራጠር፥ ይህን ተራራ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተወርወር ቢል ይሆንለታል።
፳፬ ሰለዚህ እላችኋለሁ፥ የጸለያችሁትን የለመናችሁትንም ሁሉ እንዳገኛችሁት እመኑ፥ ይሆንላችሁማል።
፳፭ ለጸሎትም በቆማችሁ ጊዜ፥ በሰማያት ያለው አባታችሁ ደግሞ ኃጢአታችሁን ይቅር እንዲላችሁ፥ በማንም ላይ አነዳች ቢኖርባችሁ ይቅር በሉት።
፳፮ እናንተ ግን ይቅር ባትሉ በሰማያት ያለው አባታችሁም ኃጢአታችሁን ይቅር አይላችሁም።
፳፯ ደግሞም ወደ ኢየሩሳሌም መጡ። እርሱም በመቅደስ ሲመላለስ፥ የካህናት አለቆችና ጻፎች ሽማግሌዎችም ወደ እርሱ መጥተው።
፳፰ እነዚህን በምን ሥልጣን ታደርጋለህ? ወይስ እነዚህን ለማድረግ ይህን ሥልጣን ማን ሰጠህ? አሉት።
፳፱ ኢየሱስም። እኔም አንዲት ነገር እጠይቃችኋለሁ፥ እናንተም መልሱልኝ፥ እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ እነግራችኋለሁ።
፴ የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ ከሰው? መልሱልኝ አላቸው።
፴፩ እርስ በርሳቸውም ሲነጋገሩ። ከሰማይ ነው ብንል። እንግዲያውስ ሰለ ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤
፴፪ ነገር ግን። ከሰው ነው እንበልን? አሉ፤ ሁሉ ዮሐንስን በእውነት እንደ ነቢይ ያዩት ነበርና ሕዝቡን ፈሩ።
፴፫ ለኢየሱስም መልሰው። እናውቅም አሉት ኢየሱስም። እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው።

፲፪

፩ በምሳሌም ይነግራቸው ጀመር። አንድ ሰው የወይን እትክልት ተከለ፥ ቅጥርም ቀጠረለት፥ መጥመቂያም ማሰለት፥ ግንብም ሠራና ለገበሬዎች አከራይቶ ወደ ሌላ አገር ሄደ።
፪ በጊዜውም ከወይን እትክልት ፍሬ ከገበሬዎቹ እንዲቀበል አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎቹ ላከ፤
፫ ይዘውም ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት።
፬ ዳግመኛም ሌላውን ባሪያ ወደ እነርሱ ላከ እርሱንም ወግረው ራሱን አቈሰሉት አዋርደውም ሰደዱት።
፭ ሌላውንም ላከ፤ እርሱንም ገደሉት፥ ከሌሎችም ከብዙዎች አንዳንዱን ደበደቡ አንዳንዱንም ገደሉ።
፮ የሚወደው አንድ ልጅ ገና ነበረው፤ ልጄንስ ያፍሩታል ብሎ እርሱን ከሁሉ በኋላ ወደ እነርሱ ላከ።
፯ እነዚያ ገበሬዎች ግን እርስ በርሳቸው። ወራሹ ይህ ነው፤ ኑ፥ እንግደለው፥ ርስቱም ለኛ ይሆናል ተባባሉ።

፳፭ ይዘውም ገደሉት፥ ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ ጣሉት።
፱ እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን ያደርጋል? ይመጣል ገበሬዎቹንም ያጠፋል፥ የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ይሰጣል።
፩-፲፪ ምሳሌውንም ሰለ እነርሱ እንደ ተናገረ አውቀዋልና ሊይዙት ፈለጉ፥ ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ። ትተውትም ሄዱ።
፲፫ በንግግርም ሊያጠምዱት ከፈሪሳውያንና ከሄሮድስ ወገን የሆኑትን ወደ እርሱ ላኩ።
፲፬ መጥተውም። መምህር ሆይ፥ የሰውን ፊት ሳትመለከት በእውነት የእግዚአብሔር መንገድ ታሰተምራለህና እውነተኛ እንደ ሆንህ ለማንምም እንዳታደላ እናውቃለን፤ ለቄሣር ግብር መስጠት ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? እንሰጥን ወይስ እንስጥ? አሉት።
፲፭ እርሱ ግን ግብዝነታቸውን አውቆ። ለምን ትፈትኑኛላችሁ? አየው ዘንድ አንድ ዲናር አምጡልኝ አላቸው።
፲፮ እነርሱም አመጡለት። ይህች መልክ ጽሕፈቲቱስ የማን ናት? አላቸው፤ እነርሱም። የቄሣር ናት አሉት።
፲፯ ኢየሱስም መልሶ። የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አሰረክቡ አላቸው። በእርሱም ተደነቁ።
፲፰ ትንሣኤ ሙታን የለም የሚሉ ሰዱቃውያን ወደ እርሱ መጥተው ጠየቁት እንዲህም አሉት።
፲፱ መምህር ሆይ፥ ሙሴ። የአንድ ሰው ወንድም ሚስቱን ትቶ ልጅ ሳያስቀር ቢሞት፥ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ጻፈልን።
፳ ሰባት ወንድማማቾች ነበሩ፤ ፊተኛውም ሚስት አግብቶ ዘር ሳያስቀር ሞተ፤
፳፩ ሁለተኛውም አገባት፥ ዘርም ሳይተው ሞተ፤ ሦስተኛውም እንዲሁ፤
፳፪ ሰባቱም አገቡአት፥ ዘርም አላስቀሩም። ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች።
፳፫ ሰባቱ እግብተዋታልና በትንሣኤ ቀን ሲነሡ ከእነርሱ ለማናቸው ሚስት ትሆናለች?
፳፬ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። መጻሕፍትንና የእግዚአብሔርን ኃይል አታውቁምና ሰለዚህ የምትስቱ አይደለምን?
፳፭ ከሙታንስ ሲነሡ በሰማያት እንዳሉ መላእክት ይሆናሉ እንጂ አያገቡም፥ አይጋቡምም።
፳፮ ሰለ ሙታን ግን እንዲነሡ እግዚአብሔር። እኔ የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ ነኝ እንዳለው በሙሴ መጽሐፍ በቍጥቋጦው ዘንድ የተጻፈውን አላነበባችሁምን?
፳፯ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም። እንግዲህ እጅግ ትስታላችሁ።
፳፰ ከጻፎችም አንዱ ቀርቦ ሲከራከሩ ሰማና መልካም አድርጎ እንደ መለሰላቸው አስተውሎ። ከሁሉ ፊተኛይቱ ትእዛዝ ማናቸይቱ ናት? ብሎ ጠየቀው።
፳፱ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። ከትእዛዛቱ ሁሉ ፊተኛይቱ። እስራኤል ሆይ፥ ሰማ፤ ጌታ አምላካችን አንድ ጌታ ነው፥
፴ አንተም በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም አሳብህ በፍጹምም ኃይልህ ጌታ እምላክህን ውደድ የምትል ናት። ፊተኛይቱ ትእዛዝ ይህች ናት።
፴፩ ሁለተኛይቱም። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የምትል እርስዋን የምትመስል ይህች ናት። ከእነዚህ የምትበልጥ ሌላ ትእዛዝ የለችም።
፴፪ ጸፊውም። መልካም ነው፥ መምህር ሆይ፤ እንድ ነው ከእርሱም በቀር ሌላ የለም ብለህ በእውነት ተናገርህ፤
፴፫ በፍጹም ልብ በፍጹም አእምሮም በፍጹም ነፍስም በፍጹም ኃይልም እርሱን መውደድ፥ ባልንጀራንም እንደ ራስ መውደድ በሙሉ ከሚቃጠል መሥዋዕትና ከሌላው መሥዋዕት ሁሉ የሚበልጥ ነው አለው።
፴፬ ኢየሱስም በአእምሮ እንደ መለሰ አይቶ። አንተ ከእግዚአብሔር መንግሥት የራቅህ አይደለህም አለው። ከዚህም በኋላ ማንም ሊጠይቀው አልደፈረም።
፴፭ ኢየሱስም በመቅደስ ሲያስተምር መልሶ እንዲህ አለ። ጻፎች ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ?
፴፮ ዳዊት ራሱ በመንፈስ ቅዱስ። ጌታ ጌታዬን። ጠላቶችህን የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ ተቀመጥ አለው አለ።
፴፯ ዳዊትም ራሱ ጌታ አለው፤ እንዴትስ ልጁ ይሆናል? ብዙ ሕዝብም በደስታ ይሰሙት ነበር።
፴፰-፴ የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ እነዚህ የባስ ፍርድ ይቀበላሉ።
፴፮ ኢየሱስም በመዝገብ አንጻር ተቀምጦ ሕዝቡ በመዝገብ ውስጥ ገንዘብ እንዴት እንዲጥሉ ያይ ነበር፤ ብዙ ባለ ጠጎችም ብዙ ይጥሉ ነበር፤
፴፪ አንዲትም ድህ መበለት መጥታ አንድ ሳንቲም የሚያህሉ ሁለት ናስ ጣለች።
፴፫ ደቀ መዛሙርቱንም ጠርቶ። እውነት እላችኋለሁ፥ በመዝገብ ውስጥ ከሚጥሉት ሁሉ ይልቅ ይህች ድህ መበለት አብልጣ ጣለች፤
፴፬ ሁሉ ከትርፋቸው ጥለዋልና፥ ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ሁሉ ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አላቸው።

፲፫

፩ እርሱም ከመቅደስ ሲወጣ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ። መምህር ሆይ፥ እንዴት ያሉ ድንጋይዎችና እንዴት ያሉ ሕንጻዎች እንደ ሆኑ እይ አለው።
፪ ኢየሱስም መልሶ። እነዚህን ታላላቅ ሕንጻዎች ታያለህን? ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ አይቀርም አለው።
፫ በመቅደስም ትይዩ በደብረ ዘይት ተቀምጦ ሳለ፥ ጴጥሮስና ያዕቆብ ዮሐንስም እንድርያስም።
፬ ንገረን፥ ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ሁሉ ይፈጸም ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው? ብለው ለብቻቸው ጠየቁት።
፭ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ ይላቸው ጀመር። ማንም እንዳያስታችሁ ተጠንቀቁ።
፮ ብዙዎች። እኔ ነኝ እያሉ በስሜ ይመጣሉና፥ ብዙዎችንም ያስታሉ።

፯ ጦርንም የጦርንም ወሬ በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ ሊሆን ግድ ነውና፥ ነገር ግን መጨረሻው ገና ነው።
፰ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፤ በልዩ ልዩ ሰፍራ የምድር መናወጥ ይሆናል፤ ራብ ይሆናል፤ እነዚህ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።
፱ እናንተ ግን ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤ ወደ ሸንጎ አሳልፈው ይሰጡአችኋል በምኵራብም ትገረፋላችሁ ምስክርም ይሆንባቸው ዘንድ ስለ እኔ በገዥዎችና በነገሥታት ፊት ትቆማላችሁ።
፲ አስቀድሞም ወንጌል ለአሕዛብ ሁሉ ይሰበክ ዘንድ ይገባል።
፲፩ ሲጐትቱአችሁና አሳልፈው ሲሰጡአችሁም ምን እንድትናገሩ አስቀድማችሁ አትጨነቁ፥ ዳሩ ግን በዚያች ሰዓት የሚሰጣችሁን ተናገሩ፤ የሚነግረው መንፈስ ቅዱስ ነው እንጂ እናንተ አይደላችሁምና።
፲፪ ወንድምም ወንድሙን አባትም ልጁን ለሞት አሳልፎ ይሰጣል፥ ልጆችም በወላጆቻቸው ላይ ይነሣሉ። ይገድሉአቸውማል፤
፲፫ በሁሉም ዘንድ ስለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ፤ እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።
፲፬ ነገር ግን በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋት ርኩሰት በማይገባው ሰፍራ ቆሞ ብታዩ፥ አንባቢው ያስተውል፥ በዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራሮች ይሸሹ፥
፲፭ በሰገነትም ያለ ወደ ቤት አይውረድ ከቤቱም አንዳች ይወሰድ ዘንድ አይግባ፥
፲፮ በእርሻም ያለ ልብሱን ይወሰድ ዘንድ ወደ ኋላው አይመለስ።
፲፯ በዚያን ወራትም ለርጉዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው።
፲፰ ነገር ግን ሸሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ፤
፲፱ በዚያን ወራት እግዚአብሔር ከፈጠረው ከፍጥረት መጀመሪያ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያልሆነ ደግሞም የማይሆን የመከራ ዓይነት ይሆናልና።
፳ ጌታስ ወራቶቹን ባያሳጥር፥ ሥጋ የለበሰ ሁሉ ባልዳነም፤ ነገር ግን ስለ መረጣቸው ምርጦች ወራቶቹን አሳጠረ።
፳፩ በዚያን ጊዜም ማንም። እነሆ፥ ክርስቶስ ከዚህ አለ፥ ወይም። እነሆ፥ ከዚያ አለ ቢላችሁ አትመኑ፤
፳፪ ሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሣሉና፥ ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ ያስቱ ዘንድ ምልክትና ድንቅ ያደርጋሉ።
፳፫ እናንተ ግን ተጠንቀቁ፤ እነሆ፥ አስቀድሜ ሁሉን ነገርኋችሁ።
፳፬ በዚያን ወራት ግን ከዚያ መከራ በኋላ ፀሐይ ይጨልማል ጨረቃም ብርሃንዋን አትሰጥም፥
፳፭ ከዋክብትም ከሰማይ ይወድቃሉ፥ የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ።
፳፮ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በብዙ ኃይልና ክብር በደመና ሲመጣ ያዩታል።
፳፯ በዚያን ጊዜም መላእክትን ይልካል ከአራቱ ነፋሳትም ከምድር ዳርቻ እስከ ሰማይ ዳርቻ የተመረጡትን ይሰበስባቸዋል።
፳፰ ምሳሌውንም ከበለስ ተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደ ቀረበ ታውቃላችሁ፤
፳፱ እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህን ሁሉ መሆኑን ስታዩ ቀርቦ በደጅ እንደ ሆነ እወቁ።
፴ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ ይህ ትውልድ አያልፍም።
፴፩ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።
፴፪ ስለዚያች ቀን ወይም ስለዚያች ሰዓት ግን የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን ከአባት በቀር የሚያውቅ የለም።
፴፫ ጊዜው መቼ እንዲሆን አታውቁምና ተጠንቀቁ፤ ትጉ፤ ጸልዩም።
፴፬ ቤቱን ትቶ ወደ ሌላ አገር እንደ ሄደ ሰው ነው፥ ለባሮቹም ሥልጣን ለእያንዳንዱም ሥራውን ሰጥቶ በረኛውን እንዲተጋ አዘዘ።
፴፭ እንግዲህ በማታ ቢሆን ወይም በእኩለ ሌሊት ወይም ዶሮ ሲጮኽ ወይም በማለዳ ቢሆን ባለቤቱ መቼ እንዲመጣ አታውቁምና
፴፮ ድንገት መጥቶ ተኝታችሁ እንዳያገኛችሁ ስለዚህ ትጉ።
፴፯ ለእናንተም የምነግራችሁ ለሁሉ እላለሁ፤ ትጉ።

፲፬

፩ ከሁለት ቀን በኋላ ፋሲካና የቂጣ በዓል ነበረ። የካህናት አለቆችም ጸሮችም እንዴት አድርገው በተንኰል እንደሚይዙትና እንደሚገድሉት ይፈልጉ ነበር።
፪ የሕዝብ ሁከት እንዳይሆን በበዓል አይሁን ይሉ ነበርና።
፫ እርሱም በቢታንያ በለምጻሙ በስምዖን ቤት በነበረ ጊዜ፥ በማዕድ ተቀምጦ ሳለ፥ እንዲት ሴት ዋጋው እጅግ የከበረ ጥሩ ናርዶስ ሽቱ የመላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ ይዛ መጣች፤ ቢልቃጡንም ሰብራ በራሱ ላይ አፈሰሰችው።
፬ እንዳንዶችም። ይህ የሽቱ ጥፋት ለምንድር ነው?
፭ ይህ ሽቱ ከሦስት መቶ ዲናር በሚበልጥ ዋጋ ተሸጦ ለድሆች ሊሰጥ ይቻል ነበርና ብለው በራሳቸው ይቈጡ ነበር፤ እርስዋንም ነቀፉአት።
፮ ኢየሱስ ግን እንዲህ አለ። ተዉአት፤ ስለ ምን ታደክሙአታላችሁ? መልካም ሥራ ሠርታልኛለች።
፯ ድሆች ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ በማናቸውም በወደዳችሁት ጊዜ መልካም ልታደርጉላቸው ትችላላችሁ፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም።
፰ የተቻላትን አደረገች፤ አስቀድማ ለመቃብሬ ሥጋዬን ቀባችው።
፱ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ወንጌል በዓለሙ ሁሉ በሚሰበክበት በማናቸውም ሰፍራ፥ እርስዋ ያደረገችው ደግሞ ለእርስዋ መታሰቢያ ሊሆን ይነገራል።
፲ ከአሥራ ሁለቱም አንዱ የአስቆሮቱ ይሁዳ አሳልፎ ሊሰጠው ወደ ካህናት አለቆች ሄደ።
፲፩ ሲሰሙም ደስ አላቸው ብርም ይሰጡት ዘንድ ተስፋ ሰጡት። በሚመች ጊዜም እንዴት አድርጎ አሳልፎ እንዲሰጠው ይፈልግ ነበር።

፲፪ ፋሲካን በሚያርዱበት በቂጣ በዓል መጀመሪያ ቀን ደቀ መዛሙርቱ። ፋሲካን ትበላ ዘንድ ወዴት ሄደን ልናሰናዳ ትወዳለህ? አሉት።
፲፫ ከደቀ መዛሙርቱም ሁለት ላከ እንዲህም አላቸው። ወደ ከተማ ሂዱ፥ ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰውም ይገናኛችኋል፤
፲፬ ተከተሉት፥ የሚገባበትንም የቤቱን ጌታ። መምህሩ። ከደቀ መዛሙርቴ ጋር ፋሲካን የምበላበት የእንግዳ ቤት ወዴት ነው? ይላል በሉት።
፲፭ እርሱም በደርብ ላይ ያለውን የተሰናዳና የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ ያሳያችኋል፤
፲፮ በዚያም አሰናዱልን። ደቀ መዛሙርቱም ወጡ ወደ ከተማም ሄደው እንዳላቸው አገኙ፥ ፋሲካንም አሰናዱ።
፲፯ በመሸም ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ጋር መጣ።
፲፰ ተቀምጠውም ሲበሉ ኢየሱስ። እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ፥ እርሱም ከእኔ ጋር የሚበላው አሳልፎ ይሰጠኛል አለ።
፲፱ እነርሱም ያዝኑ፥ እያንዳንዳቸውም። እኔ እሆንን? ይሉት ጀመር።
፳ እርሱም መልሶ። ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ከእኔ ጋር ወደ ወጭቱ እጁን የሚያጠልቀው ነው።
፳፩ የሰው ልጅስ ስለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይሄዳል፤ ነገር ግን የሰው ልጅ አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት፤ ያ ሰው ባልተወለደ ይሻለው ነበር አላቸው።
፳፪ ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቈርሶም ሰጣቸውና። እንካችሁ፤ ይህ ሥጋዬ ነው አለ።
፳፫ ጽዋንም አንሥቶ አመሰግኖም ሰጣቸው፥ ሁሉም ከእርሱ ጠጡ።
፳፬ እርሱም። ይህ ስለ ብዙዎች የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።
፳፭ እውነት እላችኋለሁ፥ በእግዚአብሔር መንግሥት ከወይኑ ፍሬ አዲሱን እስከምጠጣበት እስከዚያ ቀን ድረስ ደግሞ አልጠጣውም አላቸው።
፳፮ መዝሙርም ከዘመሩ በኋላ ወደ ደብረ ዘይት ወጡ።
፳፯ ኢየሱስም። በዚች ሌሊት ሁላችሁ በእኔ ትሰናከላላችሁ፤ እረኛዉን እመታለሁ በጎችም ይበተናሉ የሚል ተጽፎአልና።
፳፰ ነገር ግን ከተነሣሁ በኋላ ወደ ገሊላ እቀድማችኋለሁ አላቸው።
፳፱ ጴጥሮስም። ሁሉም ቢሰናከሉ እኔ ግን ከቶ አልሰናከልም አለው።
፴ ኢየሱስም። እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ በዚች ሌሊት ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ አለው።
፴፩ እርሱም ቃሉን አበርትቶ። ከእነተ ጋር የምሞት እንኳ ቢሆን ከቶ አልክድህም አለ። ሁሉም ደግሞ እንደዚሁ አሉ።
፴፪ ጌቴሴማኒ ወደምትባልም ሰፍራ መጡ፥ ደቀ መዛሙርቱንም። ስጸልይ ሳለሁ፥ በዚህ ተቀመጡ አላቸው።
፴፫ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ከእርሱ ጋር ወሰደ፤ ሊደነግጥም ሊተክዝም ጀመረና።
፴፬ ነፍሴ እስከ ሞት ድረስ እጅግ አዘነች፤ በዚህ ቈዩ ትጉም አላቸው።
፴፭ ጥቂትም ወደ ፊት እልፍ ብሎ በምድርም ወድቆ፥ ይቻልስ ቢሆን ሰዓቲቱ ከእርሱ እንድታልፍ ጸለየና።
፴፮ አባ አባት ሆይ፥ ሁሉ ይቻልሃል፤ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን አንተ የምትወደው እንጂ እኔ የምወደው አይሁን አለ።
፴፯ መጣም ተኝተውም አገኛቸው፥ ጴጥሮስንም። ስምዖን ሆይ፥ ተኝተሃልን? አንዲት ሰዓት ሰንኳ ልትተጋ አልቻልህምን?
፴፰ ወደ ፈተና እንዳትገቡ ትጉ ጸልዩም፤ መንፈስስ ተዘጋጅታለች፥ ሥጋ ግን ደካማ ነው አለው።
፴፱ ደግሞም ሄዶ ያንኑ ቃል ጸለየ።
፵ ደግሞም መጥቶ ዓይኖቻቸው በእንቅልፍ ከብደው ነበርና ተኝተው አገኛቸው፥ የሚመልሱለትንም አላወቁም።
፵፩ ሦስተኛም መጥቶ። እንግዲህስ ተኙ ዕረፉም፤ ይበቃል፤ ሰዓቲቱ ደረሰች፤ እነሆ፥ የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ይሰጣል።
፵፪ ተነሡ፥ እንሂድ፤ እነሆ፥ አሳልፎ የሚሰጠኝ ቀርቦአል አላቸው።
፵፫ ወዲያውም ገና ሲናገር ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ይሁዳ መጣ፥ ከእርሱም ጋር ብዙ ሰዎች ሰይፍና ጐመድ ይዘው ከካህናት አለቆችና ከጸሮች ከሽማግሌዎችም ዘንድ መጡ።
፵፬ አሳልፎ የሚሰጠውም። የምሰመው እርሱ ነው፤ ያዙት ተጠንቅቃችሁም ውሰዱት ብሎ ምልክት ሰጥቶአቸው ነበር።
፵፭ መጥቶም ወዲያው ወደ እርሱ ቀረበና። መምህር ሆይ፥ መምህር ሆይ፥ ብሎ ሳመው፤
፵፮ እነርሱም እጆቸውን በእርሱ ላይ ጭነው ያዙት።
፵፯ በአጠገብ ከቆሙት ግን አንዱ ሰይፉን መዞ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መታ ጆሮውንም ቈረጠ።
፵፰ ኢየሱስም መልሶ። ወንበዴ እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ልትይዙኝ መጣችሁን?
፵፱ በመቅደስ ዕለት ዕለት እያስተማርሁ ከእናንተ ጋር ሰኖር አልያዛችሁኝም፤ ነገር ግን መጻሕፍት ይፈጸሙ ዘንድ ይህ ሆነ አላቸው።
፶ ሁሉም ትተውት ሸሹ።
፶፩ ዕርቃኑን በነጠላ የሸፈነ አንድ ጎበዝ ይከተለው ነበር፥
፶፪ ጎበዛዝቱም ያዙት፤ እርሱ ግን ነጠላውን ትቶ ዕራቁቱን ሸሸ።
፶፫ ኢየሱስንም ወደ ሊቀ ካህናቱ ወሰዱት፥ የካህናት አለቆችም ሁሉ ሽማግሌዎችም ጸሮችም ተሰበሰቡ።
፶፬ ጴጥሮስም እስከ ሊቀ ካህናቱ ግቢ ውስጥ በሩቁ ተከተለው፥ ከሎሌዎችም ጋር ተቀምጦ እሳት ይሞቅ ነበር።
፶፭ የካህናት አለቆችም ሸንጎውም ሁሉ እንዲገድሉት በኢየሱስ ላይ ምስክር ይፈልጉ ነበር፥ አላገኙምም፤
፶፮ ብዙዎች በሐሰት ይመሰክሩበት ነበርና፥ ምስክርነታቸው ግን አልተሰማማም።
፶፯-፶፱ ምስክርነታቸውም እንዲሁ እንኳ አልተሰማማም።
፷ ሊቀ ካህናቱም በመካከላቸው ተነሥቶ። አንዳች አትመልስምን? እነዚህስ በአንተ ላይ የሚመሰክሩብህ ምንድር ነው? ብሎ ኢየሱስን ጠየቀው።

፷፩ እርሱ ግን ዝም አለ አንዳችም አልመለሰም። ደግሞ ሊቀ ካህናቱ ጠየቀውና። የቡሩክ ልጅ ክርስቶስ አንተ ነህን? አለው።
፷፪ ኢየሱስም። እኔ ነኝ፤ የሰው ልጅም በኃይል ቀኝ ሲቀመጥ በሰማይም ደመና ሲመጣ ታያላችሁ አለ።
፷፫ ሊቀ ካህናቱም ልብሱን ቀደደና። ከእንግዲህ ወዲህ ምሰክሮችን ምን ያሰፈልገናል?
፷፬ ስድቡን ሰማችሁ፤ ምን ይመስላችኋል? አለ። እነርሱም ሁሉ። ሞት ይገባዋል ብለው ፈረዱበት።
፷፭ አንዳንዶችም ይተፉበት ፊቱንም ሸፍነው ይጐሰሙትና። ትንቢት ተናገር ይሉት ጀመር፤ ሎሌዎችም በጥፊ እየመቱ ወሰዱት።
፷፮ ጴጥሮስም በግቢ ውሰጥ ወደ ታች ሳለ ከሊቀ ካህናቱ ገረዶች አንዲቱ መጣች፥
፷፯ ጴጥሮስም እሳት ሲሞቅ አይታ ተመለከተችውና። አንተ ደግሞ ከናዝሬቱ ከኢየሱስ ጋር ነበርህ አለችው።
፷፰ እርሱ ግን። የምትዪውን አላውቅም አላሰተውልምም ብሎ ካደ። ወደ ውጭም ወደ ደጅ ወጣ፤ ዶሮም ጮኸ።
፷፱ ገረዲቱም አይታው በዚያ ለቆሙት። ይህም ከእነርሱ ወገን ነው ሰትል ሁለተኛ ትነግራቸው ጀመር።
፸ እርሱም ደግሞ ካደ። ጥቂት ቈይተውም በዚያ የቆሙት ዳግመኛ ጴጥሮስን። የገሊላ ሰው ነህና ከእነርሱ ወገን በእውነት ነህ አሉት።
፸፩ እርሱ ግን። ይህን የምትሉትን ሰው አላውቀውም ብሎ ይረገምና ይምል ጀመር። ወዲያውም ዶሮ ሁለተኛ ጮኸ።
፸፪ ጴጥሮስንም ኢየሱስ። ዶሮ ሁለት ጊዜ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ ያለው ቃል ትዝ አለው፤ ነገሩንም አሰቦ አለቀሰ።

፲፭

፩ ወዲያውም ማለዳ የካህናት አለቆች ከሸማግሌዎችና ከጸፎች ከሸንጎውም ሁሉ ጋር ከተማከሩ በኋላ፥ ኢየሱስን አሳሰረው ወሰዱትና ለጲላጦስ አሳለፈው ሰጡት።
፪ ጲላጦስም። አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም። አንተ አልህ ብሎ መለሰለት።
፫ የካህናት አለቆችም ብዙ ያሳጡት ነበር፤ እርሱ ግን ምንም አልመለሰም።
፬ ጲላጦስም ደግሞ። አንዳች አትመልሰምን? እነሆ፥ በሰንት ነገር ያሳጡሃል ብሎ ጠየቀው።
፭ ኢየሱስም ከዚያ በኋላ ጲላጦስ እስኪደነቅ ድረስ ምንም አልመለሰም።
፮ በዚያም በዓል የለመኑትን አንድ እሰረኛ ይፈታላቸው ነበር።
፯ በዓመፅም ነፍስ ከገደሉት ከዓመፀኞች ጋር የታሰረ በርባን የተባለ ነበረ።
፰ ሕዝቡም ወጥተው እንደ ልማዱ ያደርግላቸው ዘንድ እየጮኹ ይለምኑት ጀመር።
፱ ጲላጦስም። የአይሁድን ንጉሥ እፈታላችሁ ዘንድ ትወዳላችሁን? ብሎ መለሰላቸው፤
፲ የካህናት አለቆች በቅንዓት አሳልፈው እንደ ሰጡት ያውቅ ነበርና።
፲፩ የካህናት አለቆች ግን በርባንን በእርሱ ፈንታ ይፈታላቸው ዘንድ ሕዝቡን አወኩአቸው።
፲፪ ጲላጦስም ዳግመኛ መልሶ። እንግዲህ የአይሁድ ንጉሥ የምትሉትን ምን ላደርገው ትወዳላችሁ? አላቸው።
፲፫ እነርሱም ዳግመኛ። ሰቀለው እያሉ ጮኹ።
፲፬ ጲላጦስም። ምን ነው? ያደረገው ክፋት ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱ ግን። ሰቀለው እያሉ ጩኸት አበዙ።
፲፭ ጲላጦስም የሕዝቡን ፈቃድ ሊያደርግ ወዶ በርባንን ፈታላቸው፥ ኢየሱስንም ገርፎ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጠ።
፲፮ ወታደሮችም ፕራይቶሪዮን ወደሚባል ግቢ ውሰጥ ወሰዱት፥ ጭፍራውንም ሁሉ በአንድነት ጠሩ።
፲፯ ቀይ ልብስም አለበሱት፥ የእሾህ አክሊልም ጎንጕነው ደፉበት፤
፲፰ የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለአንተ ይሁን እያሉ እጅ ይነሱት ጀመር፤
፲፱ ራሱንም በመቃ መቱት ተፉበትም፥ ተንበርክከውም ሰገዱለት።
፳ ከተዘባበቱበትም በኋላ ቀዩን ልብስ ገፈፉት፥ ልብሱንም አለበሱት፥ ሊሰቅሉትም ወሰዱት።
፳፩ አንድ መንገድ አላፊም የአሌክሳንድሮስና የሩፎስ አባት ሰምዖን የተባለ የቀሬና ሰው ከገጠር ሲመጣ መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።
፳፪ ትርጓሜውም የራስ ቅል ሰፍራ ወደሚሆን ጎልጎታ ወደተባለ ሰፍራ ወሰዱት።
፳፫ ከርቤም የተቀላቀለበትን የወይን ጠጅ እንዲጠጣ ሰጡት፤ እርሱ ግን አልተቀበለም።
፳፬ ሰቀሉትም፥ ልብሱንም ማን ማን እንዲወሰድ ዕጣ ተጣጥለው ተካፈሉ።
፳፭ በሰቀሉትም ጊዜ ሦስት ሰዓት ነበረ።
፳፮ የክሱ ጽሕፈትም። የአይሁድ ንጉሥ የሚል ተጽፎ ነበር።
፳፯ ከእርሱም ጋር ሁለት ወንበዶች አንዱን በቀኙ አንዱንም በግራው ሰቀሉ።
፳፰ መጽሐፍም። ከአመፀኞች ጋር ተቆጠረ ያለው ተፈጸመ።
፳፱ የሚያልፉትም ራሳቸውን እየነቀነቁ ይሰድቡት ነበርና። ዋ፥ ቤተ መቅደስን የምታፈርስ በሦስት ቀንም የምትሠራ፥
፴ ከመሰቀል ወርደህ ራስህን አድን አሉ።
፴፩ እንዲሁም የካህናት አለቆች ደግሞ ከጸፎች ጋር እርስ በርሳቸው እየተዘባበቱ። ሌሎችን አዳነ፤ ራሱን ሊያድን አይችልም፤
፴፪ አይተን እናምን ዘንድ የእሰራኤል ንጉሥ ክርስቶስ አሁን ከመሰቀል ይውረድ አሉ። ከእርሱም ጋር የተሰቀሉት ይነቅፉት ነበር።
፴፫ ሰድስት ሰዓትም በሆነ ጊዜ፥ እሰከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ጨለማ ሆነ።
፴፬ በዘጠኝ ሰዓትም ኢየሱስ። ኤሎሄ፥ ኤሎሄ፥ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ፤ ትርጓሜውም አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ? ማለት ነው።
፴፭ በዚያም ከቆሙት ሰዎች ሰምተው። እነሆ፥ ኤልያስን ይጠራል አሉ።
፴፮ አንዱም ሮጦ ሆምጣጤ በሰፍነግ ሞላ በመቃም አድርጎ። ተዉ፤ ኤልያስ ሊያወርደው ይመጣ እንደ ሆነ እንይ እያለ አጠጣው።
፴፯ ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኸ ነፍሱንም ሰጠ።

፶፫ የቤተ መቅደሰም መጋረጃ ከላይ እሰከ ታች ከሁለት ተቀደደ።
፶፬ በዚያም በአንጻሩ የቆመ የመቶ አለቃ እንደዚህ ጮኾ ነፍሱን እንደ ሰጠ ባየ ጊዜ። ይህ ሰው በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ነበረ አለ።
፶፭-፶፮ አሁንም በመሸ ጊዜ የሰንበት ዋዜማ የሆነ የማዘጋጀት ቀን ሰለ ነበረ፥ የከበረ አማካሪ የሆነ የአርማትያስ ዮሴፍ መጣ፥
፶፯ እርሱም ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር፤ ደፍሮም ወደ ጲላጦስ ገባና የኢየሱስን ሥጋ ለመነው።
፶፰ ጲላጦስም አሁኑን እንዴት ሞተ ብሎ ተደነቀ፥ የመቶ አለቃውንም ጠርቶ ከሞተ ቆይቶአልን? ብሎ ጠየቀው፤
፶፱ ከመቶ አለቃውም ተረድቶ በድኑን ለዮሴፍ ሰጠው።
፷ በፍታም ገዝቶ አውርዶም በበፍታ ከፈነው ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው፥ በመቃብሩ ደጃፍም ድንጋይ አነከባለለ።
፷፩ መግደላዊትም ማርያም የዮሳም እናት ማርያም ወዴት እንዳኖሩት ይመለከቱ ነበር።

፲፮

፩ ሰንበትም ካለፈ በኋላ መግደላዊት ማርያም የያዕቆብም እናት ማርያም ሰሎሜም መጥተው ሊቀቡት ሽቱ ገዙ።
፪ ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን እጅግ በማለዳ ፀሐይ ከወጣ በኋላ ወደ መቃብር መጡ።
፫ እርስ በርሳቸውም። ድንጋዩን ከመቃብር ደጃፍ ማን ያንከባልልልናል? ይባባሉ ነበር፤
፬ ድንጋዩ እጅግ ትልቅ ነበርና፤ አሻቅበውም አይተው ድንጋዩ ተንከባሎ እንደ ነበር ተመለከቱ።
፭ ወደ መቃብሩም ገብተው ነጭ ልብስ የተጎናጸፈ ጎልማሳ በቀኝ በኩል ተቀምጦ አዩና ደነገጡ።
፮ እርሱ ግን። አትደንግጡ፤ የተሰቀለውን የናዝሬቱን ኢየሱስን ትፈልጋላችሁ፤ ተነሥቶአል፥ በዚህ የለም፤ እነሆ እርሱን ያኖሩበት ሰፍራ።
፯ ነገር ግን ሄዳችሁ ለደቀ መዛሙርቱ ለጴጥሮስም። ወደ ገሊላ ይቀድማችኋል፤ እንደ ነገራችሁ በዚያ ታዩታላችሁ ብላችሁ ንገሩአቸው አላቸው።
፰ መንቀጥቀጥና መደንገጥ ይዞአቸው ነበርና ወጥተው ከመቃብር ሸሹ፤ ይፈሩ ነበርና ለማንም አንዳች አልነገሩም።
፱ እነርሱም የዘዛቸውን ሁሉ ለጴጥሮስና ከእርሱ ጋር ላሉት በአጭሩ ተናገሩ። ከዚህም በኋላ ኢየሱስ ራሱ ለዘላለም ድኅነት የሆነውን የማይለወጠውን ቅዱስ ወንጌል ከፀሐይ መውጫ እስከ መጥለቂያው ድረስ በእጆቹው ላከው።
፲ ከሳምንቱም በመጀመሪያው ቀን ማልዶ በተነሣ ጊዜ፥ አስቀድሞ ሰባት አጋንንት ላወጣላት ለመግደላዊት ማርያም ታየ።
፲፩ እርሰዋ ሄዳ ከእርሱ ጋር ሆነው ለነበሩት ሲያዝኑና ሲያለቅሱ ሳሉ አወራችላቸው፤
፲፪ እነርሱም ሕያው እንደ ሆነ ለእርሰዋም እንደ ታያት ሲሰሙ አላመኑም።
፲፫ ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ለሁለቱ ወደ ባላገር ሲሄዱ በመንገድ በሌላ መልክ ተገለጠ፤
፲፬ እነርሱም ሄደው ለሌሎቹ አወሩ፤ እነዚያንም ደግሞ አላመኑአቸውም።
፲፭ ኋላም በማዕድ ተቀምጠው ሳሉ ለአሥራ አንዱ ተገለጠ፥ ተነሥቶም ያዩትን ሰላላመኑአቸው አለማመናቸውንና የልባቸውን ጥንካሬ ነቀፈ።
፲፮ እንዲህም አላቸው። ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ሰበኩ።
፲፯ ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ ያላመነ ግን ይፈረድበታል።
፲፰ ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉአቸዋል፤ በሰሜ አጋንንትን ያወጣሉ፤ በአዲሰ ቋንቋ ይናገራሉ፤ እባቦችን ይይዛሉ፥
፲፱ የሚገድልም ነገር ቢጠጡ አይጎዳቸውም፤ እጆቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይድናሉ።
፳ ጌታ ኢየሱሰም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደ ሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ።
፳፩ እነርሱም ወጥተው በየሰፍራው ሁሉ ሰበኩ፥ ጌታም ከእነርሱ ጋር ይሠራ ነበር፥ በሚከተሉትም ምልክቶች ቃሉን ያጸና ነበር።

የሉቃስ ወንጌል

፩-፭ በይሁዳ ንጉሥ በሄሮድስ ዘመን ከአብያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ፤ ሚስቱም ከአሮን ልጆች ነበረች፥ ስምዋም ኤልሳቤጥ ነበረ።
፮ ሁለቱም በጌታ ትእዛዝና ሕግጋት ሁሉ ያለ ነቀፋ እየሄዱ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ነበሩ።
፯ ኤልሳቤጥም መካን ነበረችና ልጅ አልነበራቸውም፤ ሁለቱም በዕድሜያቸው እርጅተው ነበር።
፰ እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል፥
፱ እንደ ካህናት ሥርዓት ወደ ጌታ ቤተ መቅደስ ገብቶ ለማጠን ዕጣ ደረሰበት።
፲ በዕጣንም ጊዜ ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር።
፲፩ የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው።
፲፪ ዘካርያስም ባየው ጊዜ ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት።
፲፫ መልአኩም እንዲህ አለው። ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና እትፍራ ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።
፲፬ ደስታና ተድላም ይሆንልሃል፥ በመወለዱም ብዙዎች ደስ ይላቸዋል።
፲፭ በጌታ ፊት ታላቅ ይሆናልና፥ የወይን ጠጅና የሚያሰክር መጠጥ አይጠጣም፤ ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል፤
፲፮ ከእስራኤልም ልጆች ብዙዎችን ወደ ጌታ ወደ አምላካቸው ይመልሳል።
፲፯ እርሱም የተዘጋጁትን ሕዝብ ለጌታ እንዲያሰናዳ፥ የአባቶችን ልብ ወደ ልጆች የማይታዘዙትንም ወደ ጻድቃን ጥበብ ይመልስ ዘንድ በኤልያስ መንፈስና ኃይል በፊቱ ይሄዳል።
፲፰ ዘካርያስም መልአኩን። እኔ ሸማግሌ ነኝ ምስቴም በዕድሜዋ አርጅታለችና ይህን በምን አውቃለሁ? አለው።
፲፱ መልአኩም መልሶ። እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ፥ እንድናገርህም ይህችንም የምሥራች እንድሰብክልህ ተልኬ ነበር፤
፳ እነሆም፥ በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ሰላላመንህ፥ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም አለው።
፳፩ ሕዝቡም ዘካርያስን ይጠብቁት ነበር፤ በቤተ መቅደስም ውስጥ ስለ ዘገየ ይደነቁ ነበር።
፳፪ በወጣም ጊዜ ሊነግራቸው አልቻለም፥ በቤተ መቅደስም ራእይ እንዳየ አስተዋሉ፤ እርሱም ይጠቅሳቸው ነበር፤ ድዳም ሆኖ ኖረ።
፳፫ የማገልገሉም ወራት ሲፈጸም ወደ ቤቱ ሄደ።
፳፬-፳፭ በስድስተኛውም ወር መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ፥
፳፯ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር ዘንድ ተላከ፥ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።
፳፰ መልአኩም ወደ እርስዋ ገብቶ። ደስ ይበልሽ፥ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ፥ ጌታ ከአንቺ ጋር ነው፤ አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ አላት።
፳፱ እርስዋም ባየችው ጊዜ ከንግግሩ በጣም ደነገጠችና። ይህ እንዴት ያለ ሰላምታ ነው? ብላ አሰበች።
፴ መልአኩም እንዲህ አላት። ማርያም ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸጋ አግኝተሻልና አትፍሪ።
፴፩ እነሆም፥ ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ፥ ስሙንም ኢየሱስ ትዪዋለሽ።
፴፪ እርሱ ታላቅ ይሆናል የልዑል ልጅም ይባላል፥ ጌታ እምላክም የአባቱን የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤
፴፫ በያዕቆብ ቤትም ላይ ለዘለላም ይነግሣል፥ ለመንግሥቱም መጨረሻ የለውም።
፴፬ ማርያምም መልአኩን። ወንድ ስለማላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል? አለችው።
፴፭ መልአኩም መልሶ እንዲህ አላት። መንፈስ ቅዱስ በአንቺ ላይ ይመጣል፥ የልዑልም ኃይል ይጸልልሻል ስለዚህ ደግሞ ከአንቺ የሚወለደው ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል።
፴፮ እነሆም ዘመድሽ ኤልሳቤጥ፥ እርስዋ ደግሞ በእርጅናዋ ወንድ ልጅ ፀንሳለች፥ ለእርስዋም መካን ትባል ለነበረችው ይህ ስድስተኛ ወር ነው፤
፴፯ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና።
፴፰ ማርያምም። እነሆኝ የጌታ ባሪያ እንደ ቃልህ ይሁንልኝ አለች። መልአኩም ከእርስዋ ሄደ።
፴፱ ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች፥
፵ ወደ ዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት።
፵፩ ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥
፵፪ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች። አንቺ ከሴቶች መካከል የተባረክሽ ነሽ፥ የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው።
፵፫ የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?
፵፬ እነሆ፥ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘሎአልና።
፵፭ ከጌታ፤ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት።
፵፮ ማርያምም እንዲህ አለች።
፵፯ ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች፥ መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሴት ታደርጋለች፤
፵፰ የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቶአልና። እነሆም፥ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል፤
፵፱ ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ እድርጎአልና፤ ስሙም ቅዱስ ነው።
፶ ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል።
፶፩ በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤
፶፪ ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል፤

፶፫ የተራቡትን በበጎ ነገር አጥግቦአል፤ ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል።
፶፬-፶፮ ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርሰዋ ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤትዋም ተመለሰች።
፶፯ የኤልሳቤጥም የመውለጃዋ ጊዜ ደረሰ፥ ወንድ ልጅም ወለደች።
፶፰ ጎረቤቶችዋም ዘመዶችዋም ጌታ ምሕረቱን እንዳገነነላት ሰምተው ከእርሰዋ ጋር ደሰ አላቸው።
፶፱ በሰምንተኛውም ቀን ሕፃኑን ሊገርዙት መጡ፥ በአባቱም ሰም ዘካርያስ ሊሉት ወደዱ።
፷ እናቱ ግን መልሳ። እይሆንም፥ ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች።
፷፩ እነርሱም። ከወገንሽ ማንም በዚህ ሰም የተጠራ የለም አሉአት።
፷፪ አባቱንም ማን ሊባል እንዲወድ ጠቀሱት።
፷፫ ብራናም ለምኖ። ሰሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ። ሁሉም አደነቁ።
፷፬ ያንጊዜም አፉ ተከፈተ መላሱም ተፈታ እግዚአብሔርንም እየባረከ ተናገረ።
፷፭ ለጎረቤቶቻቸውም ሁሉ ፍርሃት ሆነ፤ ይህም ሁሉ ነገር በይሁዳ በተራራማው አገር ሁሉ ተወራ፤
፷፮ የሰሙትም ሁሉ። እንኪያ ይህ ሕፃን ምን ይሆን? እያሉ በልባቸው አኖሩት፤ የጌታ እጅ ከእርሱ ጋር ነበረችና።
፷፯ አባቱ ዘካርያስም መንፈስ ቅዱስ ሞላበትና ትንቢት ተናገረ እንዲህም አለ።
፷፰ የእስራኤል ጌታ አምላክ ይባረክ፥ ጐብኝቶ ለሕዝቡ ቤዛ አድርጎአልና፤
፷፱-፸፭ ማዳኑም ከወደረኞቻችንና ከሚጠሉን ሁሉ እጅ ነው፤
፸፪-፸፭ ደግሞም አንተ ሕፃን ሆይ፥ የልዑል ነቢይ ትባላለህ፥ መንገዱን ልትጠርግ በጌታ ፊት ትሄዳለህና፤
፸፮ እንደዚህም የኃጢአታቸው ሰርየት የሆነውን የመዳን እውቀት ለሕዝቡ ትሰጣለህ፤
፸፯ ይህም ከላይ የመጣ ብርሃን በጐበኘበት በአምላካችን ምሕረትና ርኅራኄ ምክንያት ነው፤
፸፰ ብርሃኑም በጨለማና በሞት ጥላ ተቀምጠው ላሉት ያበራል እግሮቻችንንም በሰላም መንገድ ያቀናል።
፸፱ ሕፃኑም እደገ በመንፈሰም ጠነከረ፥ ለእስራኤልም እስከ ታየበት ቀን ድረስ በምድረ በዳ ኖረ።

፪

፩ በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግሰጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጣች።
፪ ቄሬኔዎስ በሶርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ይህ የመጀመሪያ ጽሕፈት ሆነ።
፫ ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ ከተማው ሄደ።
፬-፮ በዚያም ሳሉ የመውለጃዋ ወራት ደረሰ፥
፯ የበኩር ልጅዋንም ወለደች፥ በመጠቅለያም ጠቀለለችው፤ በእንግዶችም ማደሪያ ሰፍራ ሰላልነበራቸው በግርግም አስተኛችው።
፰ በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ።
፱ እነሆም፥ የጌታ መልአክ ወደ እነርሱ ቀረበ የጌታ ክብርም በዙሪያቸው አበራ፥ ታላቅ ፍርሃትም ፈሩ።
፲ መልአኩም እንዲህ አላቸው። እነሆ፥ ለሕዝቡ ሁሉ የሚሆን ታላቅ ደስታ የምሥራች እነግራችኋለሁና አትፍሩ፤
፲፩ ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት እርሱም ክርስቶስ ጌታ የሆነ ተወልዶላችኋልና።
፲፪ ይህም ምልክት ይሆንላችኋል፤ ሕፃን ተጠቅልሎ በግርግምም ተኝቶ ታገኛላችሁ።
፲፫ ድንገትም ብዙ የሰማይ ሠራዊት ከመልአኩ ጋር ነበሩ። እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ።
፲፬ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፈቃድ አሉ።
፲፭ መላእክትም ከእነርሱ ተለይተው ወደ ሰማይ በወጡ ጊዜ፥ እረኞቹ እርስ በርሳቸው። እንግዲህ እስከ ቤተ ልሔም ድረስ እንሂድ እግዚአብሔርም የገለጠልንን ይህን የሆነውን ነገር እንይ ተባባሉ።
፲፮ ፈጥነውም መጡ ማርያምንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ።
፲፯ አይተውም ሰለዚህ ሕፃን የተነገረላቸውን ነገር ገለጡ።
፲፰ የሰሙትን ሁሉ እረኞቹ በነገሩአቸው ነገር አደነቁ፤
፲፱ ማርያም ግን ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ እያሰበች ትጠብቀው ነበር።
፳ እረኞችም እንደ ተባለላቸው ሰለ ሰሙትና ሰላዩት ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እያከበሩ ተመለሱ።
፳፩ ሊገርዙት ሰምንት ቀን በሞላ ጊዜ፥ በማኅፀን ሳይረገዝ በመልአኩ እንደ ተባለ፥ ሰሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ።
፳፪-፳፭ እነሆም፥ በኢየሩሳሌም ሰምዖን የሚባል ሰው ነበረ፥ ይህም ሰው የእስራኤልን መጽናናት ይጠባበቅ ነበር፤ ጻድቅና ትጉህም ነበረ፥ መንፈስ ቅዱስም በእርሱ ላይ ነበረ።
፳፮ በጌታም የተቀባውን ሳያይ ሞትን እንዳያይ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ነበር።
፳፯ በመንፈስም ወደ መቅደስ ወጣ፤ ወላጆቹም እንደ ሕጉ ልማድ ያደርጉለት ዘንድ ሕፃኑን ኢየሱስን በአስገቡት ጊዜ፥
፳፰ እርሱ ደግሞ ተቀብሎ አቀፈው እግዚአብሔርንም እየባረከ እንዲህ አለ።
፳፱ ጌታ ሆይ፥ አሁን እንደ ቃልህ ባሪያህን በሰላም ታሰናብተዋለህ፤
፴-፴፪ ይህም ለአሕዛብ ሁሉን የሚገልጥ ብርሃን ለሕዝብህም ለእስራኤል ክብር ነው።
፴፫ ዮሴፍና እናቱም ሰለ እርሱ በተባለው ነገር ይደነቁ ነበር።
፴፬-፴፮ ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች፤ እርስዋም ከድንግልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች፤
፴፯ እርስዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር።
፴፰ በዚያችም ሰዓት ቀርባ እግዚአብሔርን አመሰገነች፤ የኢየሩሳሌምንም ቤዛ ለሚጠባበቁ ሁሉ ሰለ እርሱ ትናገር ነበር።
፴፱ ሁሉንም እንደ ጌታ ሕግ ከፈጸሙ በኋላ፥ ወደ ገሊላ ወደ ከተማቸው ወደ ናዝሬት ተመለሱ።

፶ ሕፃኑም አደገ፥ ጥበብም ሞልቶበት በመንፈስ ጠነከረ፤ የእግዚአብሔርም ጸጋ በእርሱ ላይ ነበረ።
፶፩ ወላጆቹም በያመቱ በፋሲካ በዓል ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ ነበር።
፶፪ የአሥራ ሁለት ዓመት ልጅ በሆነ ጊዜ፥ እንደ በዓሉ ሥርዓት ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ፤
፶፫ ቀኖቹንም ከፈጸሙ በኋላ፥ ሲመለሱ ብላቴናው ኢየሱስ በኢየሩሳሌም ቀርቶ ነበር፥ ዮሴፍም እናቱም አላወቁም ነበር።
፶፬ ከመንገደኞች ጋር የነበረ ሰለ መስላቸው የአንድ ቀን መንገድ ሄዱ፥ ከዘመዶቻቸውም ከሚያውቋቸውም ዘንድ ፈለጉት፤
፶፭ ባጡትም ጊዜ እየፈለጉት ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ።
፶፮ ከሦስት ቀንም በኋላ በመምህራን መካከል ተቀምጦ ሲሰማቸውም ሲጠይቃቸውም በመቅደስ አገኙት፤
፶፯ የሰሙትም ሁሉ በማስተዋሉና በመልሱ ተገረሙ።
፶፰ ባዩትም ጊዜ ተገረሙ፥ እናቱም። ልጄ ሆይ፥ ለምን እንዲህ አደረግህብን? እነሆ፥ አባትህና እኔ እየተጨነቅን ስንፈልግህ ነበርን አለችው።
፶፱ እርሱም። ስለ ምን ፈለጋችሁኝ? በአባቴ ቤት እሆን ዘንድ እንዲገባኝ አላወቃችሁምን? አላቸው።
፷ እነርሱም የተናገራቸውን ነገር አላስተዋሉም።
፷፩ ከእነርሱም ጋር ወርዶ ወደ ናዝሬት መጣ፥ ይታዘዝላቸውም ነበር። እናቱም ይህን ነገር ሁሉ በልብዋ ትጠብቀው ነበር።
፷፪ ኢየሱስም ደግሞ በጥበብና በቁመት በሞገስም በእግዚአብሔርና በሰው ፊት ያድግ ነበር።

፫

፩ ጢባርዮስ ቄሣርም በነገሠ በአሥራ አምስተኛይቱ ዓመት፥ ጴንጤናዊው ጲላጦስም በይሁዳ ሲገዛ፥ ሄሮድስም በገሊላ የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ ወንድሙ ፊልጶስም በኢጡርያስ በጥራኮንኒደስም አገር የአራተኛው ክፍል ገዥ፥ ሊሳኒዮስም በሳቢላኒስ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሆነው ሳሉ፥
፪ ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፥ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ።
፫-፮ ስለዚህ ከእርሱ ሊጠመቁ ለወጡት ሕዝብ እንዲህ ይላቸው ነበር። እናንተ የእፉኝት ልጆች፥ ከሚመጣው ቍጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ?
፰ እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ በልባችሁም። አብርሃም አባት አለን ማለትን አትጀምሩ፤ ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች ሊያስነሣለት እግዚአብሔር እንዲችል እላችኋለሁና።
፱ አሁንስ ምሳር ደግሞ በዛፎች ሥር ተቀምጦአል፤ እንግዲህ መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቆረጣል ወደ እሳትም ይጣላል።
፲ ሕዝቡም። እንግዲህ ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር።
፲፩ መልሶም። ሁለት ልብስ ያለው ለሌለው ያካፍል፥ ምግብም ያለው እንዲሁ ያድርግ ይል ነበር።
፲፪ ቀራጮችም ደግሞ ሊጠመቁ መጥተው። መምህር ሆይ፥ ምን እናድርግ? አሉት።
፲፫ ከታዘዘላችሁ አብልጣችሁ አትውሰዱ አላቸው።
፲፬ ጭፍሮችም ደግሞ። እኛ ደግሞ ምን እናድርግ? ብለው ይጠይቁት ነበር። እርሱም። በማንም ግፍ አትሥሩ ማንንም በሐሰት አትክሰሱ፥ ደመወዛችሁም ይብቃችሁ አላቸው።
፲፭ ሕዝቡም ሲጠብቁ ሳሉ ሁሉም በልባቸው ስለ ዮሐንስ። ይህ ክርስቶስ ይሆንን? ብለው ሲያሰቡ ነበር፥
፲፮ ዮሐንስ መልሶ። እኔስ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ነገር ግን የጫማውን ጠፍር መፍታት ከማይገባኝ ከእኔ የሚበረታ ይመጣል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስና በእሳት ያጠምቃችኋል፤
፲፯ መንሹም በእጁ ነው፥ አውድማውንም ፈጽሞ ያጠራል፥ ስንዴውንም በጎተራው ይከታል፥ ገለባውን ግን በማይጠፋ እሳት ያቃጥለዋል አላቸው።
፲፰ ስለዚህ ሕዝቡን በብዙ ሌላ ምክር እየመከራቸው ወንጌልን ይሰብክላቸው ነበር፤
፲፱ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስ ግን፥ ስለ ሄሮድያዳ ስለ ወንድሙ ስለ ፊልጶስ ሚስትና ሄሮድስ ስላደረገው ሌላ ክፋት ሁሉ ዮሐንስ ስለ ገሠጸው፥
፳ ይህን ደግሞ ከሁሉ በላይ ጨምሮ ዮሐንስን በወኅኒ አገባው።
፳፩ ሕዝቡም ሁሉ ከተጠመቁ በኋላ ኢየሱስ ደግሞ ተጠመቀ። ሲጸልይም ሰማይ ተከፈተ፥
፳፪ መንፈስ ቅዱስም በአካል መልክ እንደ ርግብ በእርሱ ላይ ወረደ፤ የምወድህ ልጄ አንተ ነህ፥ በአንተ ደስ ይለኛል የሚል ድምፅም ከሰማይ መጣ።
፳፫ ኢየሱስም ሊያስተምር ሲጀምር ዕድሜው ሠላሳ ዓመት ያህል ሆኖት ነበር እንደመሰላቸው የዮሴፍ ልጅ ሆኖ፥ የኤሊ ልጅ፥
፳፬ የማቲ ልጅ፥ የሌዊ ልጅ፥ የሚልኪ ልጅ፥
፳፭ የዮና ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥ የማታትዩ ልጅ፥ የአሞጽ ልጅ፥ የናሆም ልጅ፥ የኤሲሊም ልጅ
፳፮ የናጌ ልጅ፥ የማአት ልጅ፥ የማታትዩ ልጅ የሴሜይ ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥
፳፯ የዮዳ ልጅ፥ የዮናን ልጅ፥ የሬሰ ልጅ፥ የዘሩባቤል ልጅ፥ የሰላትያል ልጅ፥ የኔሪ ልጅ፥
፳፰ የሚልኪ ልጅ፥ የሐዲ ልጅ፥ የዮሳሰ ልጅ፥ የቆሳም ልጅ፥ የኤልሞዳም ልጅ፥ የኤር ልጅ፥
፳፱ የዮሴዕ ልጅ፥ የኤልዓዘር ልጅ የዮራም ልጅ፥ የማጣት ልጅ፥ የሌዊ ልጅ፥
፴ የሰምዖን ልጅ፥ የይሁዳ ልጅ፥ የዮሴፍ ልጅ፥
፴፩ የዮናን ልጅ፥ የኤልያቄም ልጅ፥ የሜልያ ልጅ፥ የማይናን ልጅ፥ የማጣት ልጅ፥ የናታን ልጅ
፴፪ የዳዊት ልጅ፥ የእሴይ ልጅ፥ የኢዮቤድ ልጅ፥ የቦዔዝ ልጅ፥ የሰልሞን ልጅ፥
፴፫ የነአሶን ልጅ፥ የአሚናዳብ ልጅ፥ የአራም ልጅ፥ የእሮኒ ልጅ፥ የኤስሮም ልጅ፥
፴፬ የፋሬስ ልጅ፥ የይሁዳ ልጅ፥ የያዕቆብ ልጅ፥ የይሰሐቅ ልጅ፥ የአብርሃም ልጅ፥ የታራ ልጅ፥
፴፭ የናኮር ልጅ፥ የሴሮህ ልጅ፥ የራጋው ልጅ፥ የፋሌቅ ልጅ፥ የአቤር ልጅ፥ የሳላ ልጅ፥
፴፮ የቃይንም ልጅ፥ የአርፋክስድ ልጅ፥ የሴም ልጅ፥ የኖኅ ልጅ፥ የላሜህ ልጅ፥
፴፯ የማቱሳላ ልጅ፥ የሄኖክ ልጅ፥ የያሬድ ልጅ፥

፴፫ የመላልኤል ልጅ፥ የቃይናን ልጅ፥ የሄኖስ ልጅ፥
የሴት ልጅ፥ የአዳም ልጅ፥ የእግዚአብሔር ልጅ።

፬

፩ ኢየሱስም መንፈስ ቅዱስ መልቶበት ከዮርዳኖስ
ተመለሰ፥ በመንፈስም ወደ ምድረ በዳ ተመርቶ፥
፪ አርባ ቀን ከዲያብሎስ ተፈተነ። በነዚያም ቀኖች
ምንም አልበላም፥ ከተጨረሱም በኋላ ተራበ።
፫ ዲያብሎስም። የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፥
ይህን ድንጋይ። እንጀራ ሁን ብለህ እዘዝ አለው።
፬ ኢየሱስም። ሰው በእግዚአብሔር ቃል ሁሉ እንጂ
በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል ብሎ
መለሰለት።
፭ ዲያብሎስም ረጅም ወደ ሆነ ተራራ አውጥቶ
የዓለምን መንግሥታት ሁሉ በቅጽበት አሳየው።
፮ ዲያብሎስም። ይህ ሥልጣን ሁሉ ክብራቸውም
ለእኔ ተሰጥቶአል ለምወደውም ለማንም እሰጠዋለሁና
ለአንተ እሰጥሃለሁ፤
፯ ስለዚህ አንተ በእኔ ፊት ብትሰግድ፥ ሁሉ ለአንተ
ይሆናል አለው።
፰ ኢየሱስም መልሶ። ለጌታ ለአምላክህ ሰገድ
እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል አለው።
፱-፲፪ ኢየሱስም መልሶ። ጌታን አምላክህን
አትፈታተነው ተብሎአል አለው።
፲፫ ዲያቢሎስም ፈተናውን ሁሉ ከጨረሰ በኋላ
እስከ ጊዜው ከእርሱ ተለየ።
፲፬ ኢየሱስም በመንፈስ ኃይል ወደ ገሊላ ተመለሰ፤
ስለ እርሱም በዙሪያው ባለችው አገር ሁሉ ዝና ወጣ።
፲፭ እርሱም በምኩራባቸው ያስተምር፥ ሁሉም
ያመሰግኑት ነበር።
፲፮ ወዳደገበትም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም
በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገባ፥ ሊያነብም ተነሣ።
፲፯-፳ መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና
ተቀመጠ፤ በምኩራብም የነበሩት ሁሉ ትኩር ብለው
ይመለከቱት ነበር።
፳፩ እርሱም። ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ
ይላቸው ጀመር።
፳፪ ሁሉም ይመሰክሩለት ነበር ከአፉም ከሚወጣው
ከጸጋው ቃል የተነሣ እየተደነቁ። ይህ የዮሴፍ ልጅ
አይደለምን? ይሉ ነበር።
፳፫ እርሱም። ያለ ጥርጥር ይህን ምሳሌ። ባለ
መድኃኒት ሆይ፥ ራስህን ፈውስ፤ በቅፍርናሆም
እንዳደረግኸው የሰማነውን ሁሉ በዚህ በገዛ አገርህ
ደግሞ እድርግ ትሉኛላችሁ አላቸው።
፳፬ እንዲህም አለ። እውነት እላችኋለሁ፥ ነቢይ በገዛ
አገሩ ከቶ እይወደድም።
፳፭ ነገር ግን እውነት እላችኋለሁ፥ በኤልያስ ዘመን
ሦስት ዓመት ከሰድስት ወር ሰማይ ተዘግቶ ሳለ
በምድር ሁሉ ብርቱ ራብ በነበረ ጊዜ፥ በእስራኤል
ብዙ መበለቶች ነበሩ፤
፳፮ ኤልያስም በሲዶና አገር ወዳለች ወደ ሰራፕታ
ወደ አንዲት መበለት እንጂ ከእነርሱ ወደ አንዲቱ
አልተላከም።
፳፯ በነቢዩ በኤልሳዕ ዘመንም በእስራኤል ብዙ
ለምጻሞች ነበሩ፥ ከሶርያዊው ከንዕማን በቀር ከእነርሱ
አንድ ሰንኳ አልነጻም።
፳፰ በምኩራብም የነበሩ ሁሉ ይህን ሰምተው
ቊጣ ሞላባቸው፥ ተነሥተውም ከከተማ ወደ ውጭ
አወጡት፥
፳፱ ይጥሉትም ዘንድ ከተማቸው ተሠርታባት ወደ
ነበረች ወደ ተራራው አፋፍ ወሰዱት፤
፴ እርሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሄደ።
፴፩ ወደ ገሊላ ከተማም ወደ ቅፍርናሆም ወረደ።
በሰንበትም ያስተምራቸው ነበር፤
፴፪ ቃሉ በሥልጣን ነበርና በትምህርቱ ተገረሙ።
፴፫ በምኩራብም የርኩሰ ጋኔን መንፈስ ያደረበት
ሰው ነበረ፥ በታላቅ ድምፅም ጮኸ።
፴፬ ተው፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ ሆይ፥ ከእኛ ጋር ምን
አለን? ልታጠፋን መጣህን? ማን እንደ ሆንህ
አውቄሃለሁ፥ አንተ የእግዚአብሔር ቅዱሱ አለ።
፴፭ ኢየሱስም። ዝም በል ከእርሱም ውጣ ብሎ
ገሠጸው። ጋኔኑም በመካከላቸው ጥሎት ሳይጐዳው
ከእርሱ ወጣ።
፴፮ ሁሉንም መደነቅ ያዛቸው፥ እርስ በርሳቸውም።
ይህ ቃል ምንድር ነው? በሥልጣንና በኃይል ርኩሳን
መናፍስትን ያዝዛልና፥ ይወጡማል ብለው ተነጋገሩ።
፴፯ ዝናም በዙሪያው ባለች አገር ወደ ሰፍራው ሁሉ
ሰለ እርሱ ወጣ።
፴፰ በምኩራብም ተነሥቶ ወደ ሰምዖን ቤት ገባ።
የሰምዖንም አማት በብርቱ ጉዳድ ታማ ነበር ስለ
እርሷዋም ለመኑት።
፴፱ በአጠገብዋም ቆሞ ጉዳዱን ገሠጸውና ለቀቃት፤
ያንጊዜውንም ተነሥታ አገለገለቻቸው።
፵ ፀሐይም በገባ ጊዜ በልዩ ልዩ ደዌ የተያዙ
በሽተኞችን ሁሉ ወደ እርሱ አመጡአቸው፤ እርሱም
በእያንዳቸው ላይ እጁን ጭኖ ፈወሳቸው።
፵፩ አጋንንትም ደግሞ። አንተ ክርስቶስ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ እያሉ እየጮኹም ከብዙዎች
ይወጡ ነበር፤ ገሠጻቸውም ክርስቶስም እንደ ሆነ
አውቀውት ነበርና እንዲናገሩ አልፈቀደላቸውም።
፵፪ በጸባም ጊዜ ወጥቶ ወደ ምድረ በዳ ሄደ፤
ሕዝቡም ይፈልጉት ነበር፤ ወደ እርሱም መጡ፥
ከእነርሱም ተለይቶ እንዳይሄድ ሊከለክሉት ወደዱ።
፵፫ እርሱ ግን። ስለዚህ ተልኬአለሁና ለሌሎቹ
ከተማዎች ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል
እሰብክ ዘንድ ይገባኛል አላቸው።
፵፬ በገሊላም ምኩራቦች ይሰብክ ነበር።

፭

፩ ሕዝቡም የእግዚአብሔርን ቃል እየሰሙ
ሲያሰጠብቡት ሳሉ፥ እርሱ ራሱ በጌንሳሬጥ ባሕር ዳር
ቆሞ ነበር፤
፪ በባሕር ዳርም ቆመው የነበሩትን ሁለት ታንኳዎች
አየ፤ ዓሣ አጥማጆች ግን ከእነርሱ ውሰጥ ወጥተው
መረቦቻቸውን ያጥቡ ነበር።
፫ ከታንኳዎቹም የሰምዖን ወደ ነበረች ወደ አንዲቱ
ገብቶ ከምድር ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጋት ለመነው፤
በታንኳይቱም ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተምር ነበር።
፬ ነገሩንም ከጨረሰ በኋላ፥ ሰምዖንን። ወደ ጥልቁ
ፈቀቅ በል መረቦቻችሁንም ለማጥመድ ጣሉ አለው።
፭ ሰምዖንም መልሶ። አቤቱ፥ ሌሊቱን ሁሉ አድረን
ሰንደክም ምንም አልያዝንም፤ ነገር ግን በቃልህ
መረቦቹን እጥላለሁ አለው።

፮ ይህንም ባደረጉ ጊዜ እጅግ ብዙ ዓሣ ያዙ፤ መረቦቻቸውም ተቀደዱ።
፯ በሌላ ታንኳም የነበሩትን ጓደኞቻቸውን መጥተው እንዲያግዙአቸው ጠቀሱ፤ መጥተውም ሁለቱ ታንኳዎች እስኪሰጥሙ ድረስ ሞሉአቸው።
፰ ሰምዖን ጴጥሮስ ግን ባየ ጊዜ በኢየሱስ ጕልበት ላይ ወድቆ። ጌታ ሆይ፥ እኔ ኃጢአተኛ ነኝና ከኔ ተለይ አለው።
፱ ሰላጠመዱት ዓሣ እርሱ ከእርሱ ጋርም የነበሩ ሁሉ ተደንቀዋልና፥
፲ እንዲሁም ደግሞ የሰምዖን ባልንጀሮች የነበሩ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ። ኢየሱስም ሰምዖንን። አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ አለው።
፲፩ ታንኳዎችንም ወደ ምድር አድርሰው ሁሉን ትተው ተከተሉት።
፲፪ ከከተማዎችም በአንዲቱ ሳለ፥ እነሆ፥ ለምጽ የሞላበት ሰው ነበረ፤ ኢየሱስንም አይቶ በፊቱ ወደቀና። ጌታ ሆይ፥ ብትወድስ፥ ልታነጻኝ ትችላለህ ብሎ ለመነው።
፲፫ እጁንም ዘርግቶ ዳሰሰውና። እወዳለሁ፥ ንጻ አለው፤ ወዲያውም ለምጹ ለቀቀው።
፲፬ እርሱም ለማንም እንዳይናገር አዘዘው፥ ነገር ግን። ሄደህ ራስህን ለካህን አሳይ፥ ለእነርሱም ምስክር እንዲሆን ሰለ መንጻትህ ሙሴ እንዳዘዘ መሥዋዕት አቅርብ አለው።
፲፭ ወሬው ግን አብዝቶ ወጣ፥ ብዙ ሕዝብም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ይሰበሰቡ ነበር፤
፲፮ ነገር ግን እርሱ ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር።
፲፯ አንድ ቀንም ያስተምር ነበር፤ ከገሊላና ከይሁዳ መንደሮችም ሁሉ ከኢየሩሳሌምም መጥተው የነበሩ ፈሪሳውያንና የሕግ መምህራን ይቀመጡ ነበር፤ እርሱም እንዲፈውስ የጌታ ኃይል ሆነለት።
፲፰ እነሆም፥ አንድ ሽባ በአልጋ ተሸክመው አመጡ፤ አግብተውም በፊቱ ሊያኖሩት ይሹ ነበር።
፲፱ ሰለ ሕዝቡም ብዛት እንዴት አድርገው እንዲያገቡት ሲያቅታቸው፥ ወደ ሰገነቱ ወጡ የጣራውንም ጡብ አሳልፈው በመካከል በኢየሱስ ፊት ከነአልጋው አወረዱት።
፳ እምነታቸውንም አይቶ። አንተ ሰው፥ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ አለው።
፳፩ ጻፎችና ፈሪሳውያንም። ይህ የሚሳደብ ማን ነው? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ኃጢአት ሊያስተሰርይ ማን ይችላል? ብለው ያስቡ ጀመር።
፳፪ ኢየሱስም አሳባቸውን እያወቀ መልሶ። በልባችሁ ምን ታስባላችሁ?
፳፫ ኃጢአትህ ተሰረየችልህ ከማለት ወይስ። ተነሣና ሂድ ከማለት ማናቸው ይቀላል?
፳፬ ነገር ግን በምድር ላይ ኃጢአት ሊያስተሰርይ ለሰው ልጅ ሥልጣን እንዳለው እንድታውቁ ብሎ፥ ሽባውን። አንተን እልሃለሁ፥ ነተሣ፥ አልጋህን ተሸክመህ ወደ ቤትህ ሂድ አለው።
፳፭ በዚያን ጊዜም በፊታቸው ተነሣ፥ ተኝቶበትም የነበረውን ተሸክሞ እግዚአብሔርን እያመሰገነ ወደ ቤቱ ሄደ።
፳፮ ሁሉንም መገረም ያዛቸው፥ እግዚአብሔርንም አመሰግነው። ዛሬስ ድንቅ ነገር አየን እያሉ ፍርሃት ሞላባቸው።
፳፯ ከዚህም በኋላ ወጥቶ ሌዊ የሚባል ቀራጭ በመቅረጫው ተቀምጦ ተመለከተና። ተከተለኝ አለው።
፳፰ ሁሉንም ተወ፤ ተነሥቶም ተከተለው።
፳፱ ሌዊም በቤቱ ታላቅ ግብዣ አደረገለት፤ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩ ከቀራጮችና ከሌሎች ሰዎች ብዙ ሕዝብ ነበሩ።
፴ ፈሪሳውያንና ጸፎቻቸውም በደቀ መዛሙርቱ ላይ። ሰለ ምን ከቀራጮችና ከኃጢአተኞች ጋር ትበላላችሁ ትጠጡማላችሁ? ብለው አንጐራጐሩ።
፴፩ ኢየሱስም መልሶ። ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች ባለ መድኃኒት አያስፈልጋቸውም፤
፴፪ ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው።
፴፫ እነርሱም። የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሰለ ምን ብዙ ይጦማሉ ጸሎትስ ሰለ ምን ያደርጋሉ፥ ደግሞም የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርት ሰለ ምን እንደዚሁ ያደርጋሉ፤ የአንተ ደቀ መዛሙርት ግን ይበላሉ ይጠጣሉም? አሉት።
፴፬ ኢየሱስም። ሙሽራው ከእነርሱ ጋር ሳለ ሚዜዎችን ልታሰጦሙ ትችላላችሁን?
፴፭ ነገር ግን ወራት ይመጣል፥ ሙሽራውም ከእነርሱ ሲወሰድ ያንጊዜ፥ በዚያ ወራት ይጦማሉ አላቸው።
፴፮ ደግሞም ምሳሌ እንዲህ ሲል ነገራቸው። የአዲስ ልብስ እራፊ ባረጀ ልብስ ላይ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን አዲሱን ይቀደዋል ደግሞም አዲስ እራፊ ለአሮጌው አይስማማውም።
፴፯ ባረጀ አቁማዳም አዲስ የወይን ጠጅ የሚያኖር የለም፤ ቢደረግ ግን አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳል፥ እርሱም ይፈሳል አቁማዳውም ይጠፋል።
፴፰ አዲሱን የወይን ጠጅ ግን በአዲስ አቁማዳ ማኖር ይገባል፥ ሁለቱም ይጠባበቃሉ።
፴፱ አሮጌ የወይን ጠጅ ሲጠጣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ አሮጌው ይጣፍጣል ይላልና።

፮

፩ በሰንበትም በእርሻ መካከል ያልፍ ነበር ደቀ መዛሙርቱም እሸት ይቀጥፉ በእጃቸውም እያሹ ይበሉ ነበር።
፪ ከፈሪሳውያን ግን አንዳንዶቹ። በሰንበት ሊያደርግ ያልተፈቀደውን ሰለ ምን ታደርጋላችሁ? አሉአቸው።
፫-፭ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ ነው አላቸውም።
፮ በሌላው ሰንበትም ወደ ምኩራብ ገብቶ አስተማረ፤ በዚያም ቀኝ እጁ የሰለለች ሰው ነበረ፤
፯ ጸፎችና ፈሪሳውያንም መክሰሻ ሊያገኙበት በሰንበት ይፈውስ እንደ ሆነ ይጠባበቁት ነበር።
፰ እርሱ ግን አሳባቸውን አውቆ እጁ የሰለለችውን ሰው። ተነሣና በመካከል ቁም አለው፤ ተነሥቶም ቆመ።
፱ ኢየሱስም። እጠይቃችኋለሁ፤ በሰንበት በጎ ማድረግ ተፈቅዶአልን ወይስ ክፉ? ነፍስ ማዳንን ወይስ መግደል? አላቸው።
፲ ሁላቸውንም ዙሪያውን አየና ሰውዬውን። እጅህን ዘርጋ አለው። እርሱም እንዲህ አደረገ፥ እጁም እንደ ሁለተኛይቱ ዳነች።

፲፭ እነርሱም ቊጣ ሞላባቸው፥ በኢየሱስም ምን እንዲያደርጉበት እርስ በርሳቸው ተባባሉ።
፲፮ በነዚህም ወራት ይጸልይ ዘንድ ወደ ተራራ ወጣ፥ ሌሊቱንም ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ አደረ።
፲፯ በነጋም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱን ጠራ፥ ከእነርሱም አሥራ ሁለት መረጠ ደግሞም ሐዋርያት ብሎ ሰየማቸው፤
፲፰ እነርሱም፥ ጴጥሮስ ብሎ እንደ ገና የሰየመው ስምዖን፥ ወንድሙም እንድርያስ፥ ያዕቆብም ዮሐንስም፥ ፊልጶስም በርተሎሜዎስም፥
፲፱ ማቴዎስም ቶማስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥
፳ የያዕቆብ ይሁዳም፥ አሳልፎ የሰጠውም የአስቆሮቱ ይሁዳ ናቸው።
፳፩ ከእነርሱም ጋር ወርዶ በተካከለ ሰፍራ ቆመ፥ ከደቀ መዛሙርቱም ወገን ብዙ ሕዝብ ነበረ፥ ደግሞም ሊሰሙትና ከደዌአቸው ሊፈወሱ ከይሁዳ ሁሉ ከኢየሩሳሌምም ከጢሮስና ከሲዶና ባሕር ዳርም የመጡ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤
፳፪ ከርኩሳንም መናፍስት ይሠቃዩ የነበሩት ተፈወሱ፤
፳፫ ከእርሱም ኃይል ወጥቶ ሁሉን ይፈውስ ነበርና ሕዝቡ ሁሉ ሊዳስሱት ይሹ ነበር።
፳፬ እርሱም ወደ ደቀ መዛሙርቱ ዓይኑን አነሣ እንዲህም አላቸው። እናንተ ድሆች ብፁዓን ናችሁ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት የእናንተ ነውና።
፳፭ እናንተ አሁን የምትራቡ ብፁዓን ናችሁ፥ ትጠግባላችሁና። እናንተ አሁን የምታለቅሱ ብፁዓን ናችሁ፥ ትሰቃላችሁና።
፳፮ ሰዎች ስለ ሰው ልጅ ሲጠሉአችሁ ሲለዩአችሁም ሲነቅፉአችሁም ስማችሁንም እንደ ክፉ ሲያወጡ፥ ብፁዓን ናችሁ።
፳፯ እነሆ፥ ዋጋችሁ በሰማይ ታላቅ ነውና በዚያን ቀን ደስ ይበላችሁ ዝለሉም፤ አባቶቻቸው ነቢያትን እንዲህ ያደርጉባቸው ነበርና።
፳፰ ነገር ግን እናንተ ባለ ጠጎች ወዮላችሁ፥ መጽናናታችሁን ተቀብላችኋልና።
፳፱ እናንተ አሁን የጠገባችሁ ወዮላችሁ፥ ትራባላችሁና። እናንተ አሁን የምትስቁ ወዮላችሁ፥ ታዝናላችሁና ታለቅሱማላችሁ።
፴ ሰዎች ሁሉ መልካም ሲናገሩላችሁ፥ ወዮላችሁ፤ አባቶቻቸው ለሐሰተኞች ነቢያት እንዲሁ ያደርጉላቸው ነበርና።
፴፩ ነገር ግን ለእናንተ ለምትሰሙ እላችኋለሁ፥ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ ለሚጠሉአችሁ መልካም አድርጉ፥
፴፪ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ስለሚበድሉአችሁም ጸልዩ።
፴፫ ጕንጭህን ለሚመታህ ደግሞ ሁለተኛውን ስጠው፥ መጐናጸፊያህንም ለሚወስድ እጀ ጠባብህን ደግሞ አትከልክለው።
፴፬ ለሚለምንህ ሁሉ ስጥ፥ ገንዘብህንም የሚወሰድ እንዲመልስ አትጠይቀው።
፴፭ ሰዎችም ሊያደርጉላችሁ እንደምትወዱ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው።
፴፮ የሚወዱአችሁንማ ብትወዱ፥ ምን ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ የሚወዱአቸውን ይወዳሉና።
፴፯ መልካምም ለሚያደርጉላችሁ መልካም ብታደርጉ፥ ምን ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ ያን ያደርጋሉና።
፴፰ እንድትወሰዱባቸው ተስፋ ለምታደርጉአቸው ብታበድሩ፥ ምን ምስጋና አላችሁ? ኃጢአተኞች ደግሞ በትክክል እንዲቀበሉ ለኃጢአተኞች ያበድራሉ።
፴፱ ነገር ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ፤ መልካም አድርጉ፤ ምንም ተስፋ ሳታደርጉም አበድሩ፥ ዋጋችሁም ታላቅ ይሆናል፥ የልዑልም ልጆች ትሆናላችሁ፥ እርሱ ለማያመሰግኑ ለክፉዎችም ቸር ነውና።
፵ አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ ርኅሩኆች ሁኑ።
፵፩ አትፍረዱ አይፈረድባችሁምም፤ አትኰንኑ አትኰነኑምም። ይቅር በሉ ይቅርም ትባላላችሁ።
፵፪ ስጡ ይሰጣችሁማል፤ በምትሰፍሩበት መሰፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋልና፥ የተጨቈነና የተነቀነቀ የተትረፈረፈም መልካም መሰፈሪያ በእቅፋችሁ ይሰጣችኋል።
፵፫ ምሳሌም አላቸው። ዕውር ዕውርን ሊመራ ይችላልን? ሁለቱ በጕድጓድ አይወድቁምን?
፵፬ ደቀ መዝሙር ከመምህሩ አይበልጥም፤ ፈጽሞ የተማረ ሁሉ ግን እንደ መምህሩ ይሆናል።
፵፭ በወንድምህም ዓይን ያለውን ጉድፍ ስለ ምን ታያለህ፥ በራስህ ዓይን ግን ያለውን ምሰሶ ስለ ምን አትመለከትም?
፵፮ በዓይንህ ያለውን ምሰሶ ራስህ ሳታይ፥ እንዴት ወንድምህን። ወንድሜ ሆይ፥ በዓይንህ ያለውን ጉድፍ ላውጣ ፍቀድልኝ ልትል ትችላለህ? አንተ ግብዝ፥ አስቀድመህ ከዓይንህ ምሰሶውን አውጣ ከዚያም በኋላ በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ ታወጣ ዘንድ አጥርተህ ታያለህ።
፵፯ ክፉ ፍሬ የሚያደርግ መልካም ዛፍ የለምና፥ እንዲሁም መልካም ፍሬ የሚያደርግ ክፉ ዛፍ የለም።
፵፰ ዛፍ ሁሉ ከፍሬው ይታወቃልና፤ ከእሾህ በለስ አይለቅሙም፥ ከእጣጥ ቊጥቋጦም ወይን አይቈርጡም።
፵፱ በልብ ሞልቶ ከተረፈው አፉ ይናገራልና መልካም ሰው ከልብ መልካም መዝገብ መልካሙን ያወጣል፥ ክፉ ሰውም ከልብ ክፉ መዝገብ ክፉውን ያወጣል።
፶ ስለ ምን። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ትሉኛላችሁ፥ የምለውንም እታደርጉም?
፶፩ ወደ እኔ የሚመጣ ሁሉ ቃሌንም ሰምቶ የሚያደርገው፥ ማንን እንዲመስል አሳያችኋለሁ።
፶፪ ቤት ሲሠራ አጥልቆ የቆፈረ በዓለት ላይም የመሠረተ ሰውን ይመስላል፤ ጐርፍም በመጣ ጊዜ ወንዙ ያን ቤት ገፋው፥ በዓለት ላይም ስለ ተመሠረተ ሊያናውጠው አልቻለም።
፶፫ ሰምቶ የማያደርገው ግን ያለ መሠረት በምድር ላይ ቤቱን የሠራ ሰውን ይመስላል፤ ወንዙም ገፋው ወዲያውም ወደቀ የዚያ ቤት አወዳደቅም ታላቅ ሆነ።

፯

፩ ቃሉን ሁሉ በሕዝብ ጆሮዎች በጨረሰ ጊዜ ወደ ቅፍርናሆም ገባ።
፪ አንድ የመቶ አለቃም ነበረ፤ የሚወደውም ባሪያው ታሞ ሊሞት ቀርቦ ነበር።

፫ ስለ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሎች
ወደ እርሱ ላከና መጥቶ ባሪያውን እንዲያድን
ለመነው።
፬ እነርሱም ወደ ኢየሱስ መጥተው። ይህን
ልታደርግለት ይገባዋል፤
፭ ሕዝባችንን ይወዳልና ምኩራብም ራሱ
ሠርቶልናል ብለው አጽንተው ለመኑት።
፮ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ሄደ። አሁንም ወደ ቤቱ
በቀረበ ጊዜ የመቶው አለቃ ወዳጆቹን ወደ እርሱ
ላከ፤ አለውም። ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች ልትገባ
አይገባኝምና እትድከም፤
፯ ስለዚህም ወደ አንተ ልመጣ እንዲገባኝ ስውነቴን
አልቈጠርሁትም፤ ነገር ግን ቃል ተናገር፥ ብላቴናዬም
ይፈወሳል።
፰ እኔ ደግሞ ከሌሎች በታች የምገዛ ሰው ነኝ፥
ከእኔም በታች ወታደሮች አሉኝ፥ እንዱንም። ሂድ ብለው
ይሄዳል፥ ሌላውንም። ና ብለው ይመጣል፥ ባሪያዬንም።
ይህን አድርግ ብለው ያደርጋል።
፱ ኢየሱስም ይህን ሰምቶ በእርሱ ተደነቀ፥ ዘወርም
ብሎ ለተከተሉት ሕዝብ። እላችኋለሁ፥ በእስራኤልስ
እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም አላቸው።
፲ የተላኩትም ወደ ቤት ተመልሰው ባሪያውን ባለ
ጤና ሆኖ አገኙት።
፲፩ በነገውም ናይን ወደምትባል ወደ እንዲት ከተማ
ሄደ፥ ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ሕዝብም ከእርሱ ጋር
አብረው ሄዱ።
፲፪ ወደ ከተማይቱም በር በቀረበ ጊዜ፥ እነሆ፥ የሞተ
ሰው ተሸክመው አወጡ፤ እርሱም ለእናቱ አንድ ልጅ
ነበረ፥ እርስዋም መበለት ነበረች፥ ብዙም የከተማ
ሕዝብ ከእርስዋ ጋር አብረው ነበሩ።
፲፫ ጌታም ባያት ጊዜ አዘነላትና። አታልቅሽ አላት።
፲፬ ቀርቦም ቃሬዛውን ነካ፥ የተሸከሙትም ቆሙ፤
አለውም። አንተ ጕበዝ፥ እልሃለሁ፥ ተነሣ።
፲፭ የሞተውም ቀና ብሎ ተቀመጠ ሊናገርም ጀመረ፥
ለእናቱም ሰጣት።
፲፮ ሁሉንም ፍርሃት ያዛቸውና። ታላቅ ነቢይ በእኛ
መካከል ተነሥቶአል፥ ደግሞ። እግዚአብሔር ሕዝቡን
ጐበኘ እያሉ እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
፲፯ ይህም ዝና ስለ እርሱ በይሁዳ ሁሉ በዙሪያውም
ባለች አገር ሁሉ ወጣ።
፲፰ ደቀ መዛሙርቱም ለዮሐንስ እነዚህን ሁሉ
አወሩ።
፲፱ ዮሐንስም ከደቀ መዛሙርቱ ሁለት ወደ እርሱ
ጠርቶ። የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን
እንጠብቅ? ብሎ ወደ ኢየሱስ ላከ።
፳ ሰዎቹም ወደ እርሱ መጥተው። መጥምቁ
ዮሐንስ። የሚመጣው አንተ ነህን ወይስ ሌላውን
እንጠብቅ? ብሎ ወደ አንተ ላከን አሉት።
፳፩ በዚያች ሰዓት ከደዌና ከሥቃይ ከክፉዎች
መናፍስትም ብዙዎችን ፈወሰ፥ ለብዙ ዕውሮችም
ማየትን ሰጠ።
፳፪ ኢየሱስም መልሶ። ሄዳችሁ ያያችሁትን
የሰማችሁትንም ለዮሐንስ አውሩለት፤ ዕውሮች
ያያሉ፥ አንካሶችም ይሄዳሉ፥ ለምጻሞችም ይነጻሉ፥
ደንቆሮዎችም ይሰማሉ፥ ሙታንም ይነሣሉ፥ ለድሆችም
ወንጌል ይሰበካል፤
፳፫ በእኔም የማይሰናከለው ሁሉ ብፁዕ ነው
አላቸው።
፳፬ የዮሐንስ መልክተኞችም ከሄዱ በኋላ፥ ለሕዝቡ
ስለ ዮሐንስ ይናገር ጀመር እንዲህም አለ። ምን ልታዩ
ወደ ምድረ በዳ ወጣችሁ? ነፋስ የሚወዘውዘውን
ሸምበቆን? ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ?
፳፭ ቀጭን ልብስ የለበሰውን ሰውን? እነሆ፥ ጌጠኛ
ልብስ የሚለብሱና በቅምጥልነት የሚኖሩ በነገሥታት
ቤት አሉ።
፳፮ ወይስ ምን ልታዩ ወጣችሁ? ነቢይን? አዎን
እላችኋለሁ፥ ከነቢይም የሚበልጠውን።
፳፯ እነሆ፥ መንገድህን በፊትህ የሚጠርግ
መልክተኛዬን በፊትህ እልካለሁ ተብሎ የተጻፈለት ይህ
ነው።
፳፰ እላችኋለሁ፥ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል
ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ ማንም የለም፤
በእግዚአብሔር መንግሥት ግን ከሁሉ የሚያንሰው
ይበልጠዋል።
፳፱ የሰሙትም ሕዝብ ሁሉ ቀራጮች እንኳ ሳይቀሩ
በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው እግዚአብሔርን
አጸደቁ፤
፴ ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ግን በእርሱ ሰለ
አልተጠመቁ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ።
፴፩ እንግዲህ የዚችን ትውልድ ሰዎች በምን
አሰመስላቸዋለሁ? ማንንስ ይመስላሉ?
፴፪ በገበያ የሚቀመጡትን ልጆች ይመስላሉ፥
እርስ በርሳቸውም እየተጠራሩ። እንቢልታ
ነፋንላችሁ አልዘፈናችሁምም፤ ሙሾ አወጣንላችሁ
አላለቀሳችሁምም ይላል።
፴፫ መጥምቁ ዮሐንስ እንጀራ ሳይበላ የወይን ጠጅም
ሳይጠጣ መጥቶ ነበርና። ጋኔን አለበት አላችሁት።
፴፬ የሰው ልጅ እየበላና እየጠጣ መጥቶአልና።
እነሆ፥ በላተኛና የወይን ጠጅ ጠጭ፥ የቀራጮችና
የኃጢአተኞች ወዳጅ አላችሁት።
፴፭ ጥበብም ለልጆችዋ ሁሉ ጸደቀች።
፴፮ ከፈሪሳውያንም አንድ ከእርሱ ጋር ይበላ
ዘንድ ለመነው፤ በፈሪሳዊው ቤትም ገብቶ በማዕድ
ተቀመጠ።
፴፯ እነሆም በዚያች ከተማ ኃጢአተኛ የነበረች
አንዲት ሴት፤ በፈሪሳዊው ቤት በማዕድ እንደ ተቀመጠ
ባወቀች ጊዜ፥ ሽቱ የሞላበት የአልባስጥሮስ ቢልቃጥ
አመጣች።
፴፰ በሰተ ኋላውም በእግሩ አጠገብ ቆማ እያለቀሰች
በእንባዋ እግሩን ታርስ ጀመረች፥ በራስ ጠጕርዋም
ታብሰው እግሩንም ትሰመው ሽቱም ትቀባው ነበረች።
፴፱ የጠራው ፈሪሳዊም አይቶ። ይህስ ነቢይ ቢሆን፥
ይህች የምትዳሰሰው ሴት ማን እንደ ሆነች እንዴትስ
እንደ ነበረች ባወቀ ነበር፥ ኃጢአተኛ ናትና ብሎ በልቡ
አሰበ።
፵ ኢየሱስም መልሶ። ሰምዖን ሆይ፥ የምነግርህ ነገር
አለኝ አለው። እርሱም። መምህር ሆይ፥ ተናገር አለ።
፵፩ ለአንድ አበዳሪ ሁለት ተበዳሪዎች ነበሩት በአንዱ
አምስት መቶ ዲናር ነበረበት በሁለተኛውም አምሳ።
፵፪ የሚከፍሉትም ቢያጡ ለሁለቱም ተወላቸው።
እንግዲህ ከእነርሱ አብልጦ የሚወደው ማንኛው ነው?
፵፫ ስምዖንም መልሶ። ብዙ የተወለቱ ይመስለኛል
አለ። እርሱም። በእውነት ፈረድህ አለው።

፴፯ ወደ ሴቲቱም ዘወር ብሎ ስምዖንን እንዲህ አለው። ይህችን ሴት ታያለህን? እኔ ወደ ቤትህ ገባሁ፥ ውኃ ሰንኳ ለእግሬ አላቀረብህልኝም፤ እርሰዋ ግን በእንባዋ እግሬን አራሰች በጠጕርዋም አበሰች።
፴፰ አንተ አልሳምኸኝም፤ እርሰዋ ግን ከገባሁ ጀምራ እግሬን ከመሳም አላቋረጠችም።
፴፱ አንተ ራሴን ዘይት አልቀባኸኝም፤ እርሰዋ ግን እግሬን ሽቱ ቀባች።
፵ ስለዚህ እልሃለሁ፥ እጅግ ወዳለችና ብዙ ያለው ኃጢአትዋ ተሰርዮላታል፤ ጥቂት ግን የሚሰረይለት ጥቂት ይወዳል።
፵፩ እርሰዋንም። ኃጢአትሽ ተሰርዮልሻል አላት።
፵፪ ከእርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጠው የነበሩት በልባቸው። ኃጢአትን እንኳ የሚያሰተሰርይ ይህ ማን ነው? ይሉ ጀመር።
፵፫ ሴቲቱንም። እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት።

፰

፩ ከዚህም በኋላ እየሰበከና ስለ እግዚአብሔር መንግሥት የምሥራች እየተናገረ በየከተማይቱ በየመንደሩም ያልፍ ነበር፤
፪ አሥራ ሁለቱም ከእርሱ ጋር ነበሩ፥ ክክፉዎች መናፍሰትና ከደዌም ተፈውሰው የነበሩ አንዳንድ ሴቶች፤ እነርሱም ሰባት አጋንንት የወጡላት መግደላዊት የምትባል ማርያም፥
፫ የሄሮድስ እዛዥ የኩዛ ሚስት ዮሐናም ሶሰናም ብዙዎች ሌሎችም ሆነው በገንዘባቸው ያገለግሉት ነበር።
፬ ብዙ ሕዝብም በተሰበሰቡ ጊዜ ከከተማዎችም ሁሉ ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በምሳሌ እንዲህ ሲል ተናገራቸው።
፭ ዘሪ ዘሩን ሊዘራ ወጣ። ሲዘራም አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ ተረገጠም፥ የሰማይ ወፎችም በሉት።
፮ ሌላውም በዓለት ላይ ወደቀ፥ በበቀለም ጊዜ እርጥበት ስላልነበረው ደረቀ።
፯ ሌላውም በእሾህ መካከል ወደቀ፥ እሾሁም አብሮ በቀለና አነቀው።
፰ ሌላውም በመልካም መሬት ላይ ወደቀ፤ በበቀለም ጊዜ መቶ እጥፍ አፈራ። ይህን በተናገረ ጊዜ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ ብሎ ጮኸ።
፱ ደቀ መዛሙርቱም። ይህ ምሳሌ ምንድር ነው? ብለው ጠየቁት።
፲ እርሱም እንዲህ አለ። ለእናንተ የእግዚአብሔርን መንግሥት ምሥጢር ማወቅ ተሰጥቶአችኋል፤ ለሌሎች ግን እያዩ እንዳያዩ እየሰሙም እንዳያስተውሉ በምሳሌ ነው።
፲፩ ምሳሌው ይህ ነው። ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው።
፲፪ በመንገድ ዳርም ያሉት የሚሰሙ ናቸው፤ ከዚህ በኋላም ዲያብሎስ ይመጣል አምነውም እንዳይድኑ ቃሉን ከልባቸው ይወስዳል።
፲፫ በዓለት ላይም ያሉት ሲሰሙ ቃሉን በደስታ የሚቀበሉ ናቸው፤ እነርሱም ለጊዜው ብቻ ያምናሉ እንጂ በፈተና ጊዜ የሚክዱ ሥር የሌላቸው ናቸው።
፲፬ በእሾህ መካከልም የወደቀ እነዚህ የሚሰሙት ናቸው፤ መንገዳቸውንም ሂደው በሕይወት ዘመን በአሳብና በባለ ጠግነት ምኞት ይታነቃሉ፥ ሙሉ ፍሬም አያፈሩም።
፲፭ በመልካም መሬት ላይም የወደቀ እነርሱ በመልካምና በበጎ ልብ ቃሉን ሰምተው የሚጠብቁት በመጽናትም ፍሬ የሚያፈሩ ናቸው።
፲፮ መብራትንም አብርቶ በዕቃ የሚከድነው ወይም ከአልጋ በታች የሚያኖረው የለም፥ የሚገቡት ሰዎች ብርሃኑን እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል እንጂ።
፲፯ የማይገለጥ የተሰወረ የለምና፥ የማይታወቅም ወደ ግልጥም የማይመጣ የተሸሸገ የለም።
፲፰ እንግዲህ እንዴት እንድትሰሙ ተጠበቁ፤ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና፥ ከሌለውም ሁሉ፥ ያው ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።
፲፱ እናቱና ወንድሞቹም ወደ እርሱ መጡ፥ ከሕዝቡም ብዛት የተነሣ ሊያገኙት አልተቻላቸውም።
፳ እናትህና ወንድሞችህ ሊያዩህ ወድደው በውጭ ቆመዋል ብለው ነገሩት።
፳፩ እርሱም መልሶ። እናቴና ወንድሞቼስ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው የሚያደርጉት እነዚህ ናቸው አላቸው።
፳፪ ከዕለታቱም በአንዱ እርሱ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳ ገብቶ። ወደ ባሕር ማዶ እንሻገር አላቸው፤ ተነሡም።
፳፫ ሲሄዱም እንቀላፋ። ዓውሎ ነፋሰም በባሕር ላይ ወረደ፥ ውኃውም ታንኳይቱን ይሞላ ነበርና ይጨነቁ ነበር።
፳፬ ቀርበውም። አቤቱ፥ አቤቱ ጠፋን እያሉ አስነሡት። እርሱም ነቅቶ ነፋሱንና የውኃውን ማዕበል ገሠጻቸው፤ ተዉም፥ ጽጥታም ሆነ።
፳፭ እርሱም። እምነታችሁ የት ነው? አላቸው። ፈርተውም ተደነቁ፥ እርስ በርሳቸውም። እንዲህ ነፋሳትንና ውኃን እንኳ የሚያዝ ለእርሱም የሚታዘዙለት ይህ ማን ነው? አሉ።
፳፮ በገሊላም አንጻር ወዳለችው ወደ ጌርጌሴኖን አገር በታንኳ ደረሱ።
፳፯ ወደ ምድርም በወጣ ጊዜ አጋንንት ያደሩበት አንድ ሰው ከከተማ ወጥቶ ተገናኘው፥ ከብዙ ዘመንም ጀምሮ ልብስ ሳይለብስ በመቃብር እንጂ በቤት አይኖርም ነበር።
፳፰ ኢየሱስንም ባየ ጊዜ ጮኾ በፊቱ ተደፋ በታላቅ ድምፅም። የልዑል እግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ሆይ፥ ከአንተ ጋር ምን አለኝ? እንዳትሣቀየኝ እለምንሃለሁ አለ።
፳፱ ርኩሱን መንፈስ ከሰውዬው እንዲወጣ ያዘው ነበርና። ብዙ ዘመንም ይዞት ነበርና፥ በሰንሰለትና በእግር ብረትም ታስሮ ይጠበቅ ነበር፤ እስራቱንም ሰብሮ በጋኔኑ ወደ ምድረ በዳ ይነዳ ነበር።
፴ ኢየሱስም። ስምህ ማን ነው? ብሎ ጠየቀው። እርሱም ብዙዎች አጋንንት ገብተውበት ነበርና።
፴፩ ወደ ጥልቁም ሊሄዱ እንዳያዛቸው ለመኑት።
፴፪ በዚያም በተራራው የብዙ እሪያ መንጋ ይሰማሩ ነበር፤ ወደ እነርሱም ሊገቡ እንዲፈቅድላቸው ለመኑት፤ ፈቀደላቸውም።

፶፫ አጋንንትም ከሰውዬው ወጥተው ወደ እሪያዎች ገቡ፥ መንጋውም ከአፋፉ ወደ ባሕር ተጣደፉና ሰጠሙ።
፶፬ እረኞችም የሆነውን ባዩ ጊዜ ሸሽተው በከተማውና በአገሩ አወሩት።
፶፭ የሆነውን ነገር ሊያዩ ወጥተውም ወደ ኢየሱስ መጡ፥ አጋንንትም የወጡለትን ሰው ለብሶ ልቡም ተመልሶ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጦ አገኙትና ፈሩ።
፶፮ ያዩትም ደግሞ አጋንንት ያደሩበት ሰው እንዴት እንደ ዳነ አወሩላቸው።
፶፯ በዙሪያውም በጌርጌሴኖን አገር ያሉት ሕዝብ ሁሉ ታላቅ ፍርሃት ይዞአቸዋልና ከእነርሱ እንዲሄድ ለመኑት በታንኳም ገብቶ ተመለሰ።
፶፰ አጋንንት የወጡለት ሰውም ከእርሱ ጋር ይኖር ዘንድ ለመነው፤
፶፱ ነገር ግን። ወደ ቤትህ ተመለስ፥ እግዚአብሔር እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረግልህ ንገር ብሎ አሰናበተው። ኢየሱስም እንዴት ያለ ታላቅ ነገር እንዳደረገለት በከተማው ሁሉ እየሰበከ ሄደ።
፷ ኢየሱስም በተመለሰ ጊዜ ሁሉ ይጠብቁት ነበርና ሕዝቡ ተቀበሉት።
፷፩ እነሆም፥ ኢያኢሮስ የሚባል ሰው መጣ፥ እርሱም የምኩራብ አለቃ ነበረ በኢየሱስም እግር ላይ ወድቆ ወደ ቤቱ እንዲገባ ለመነው፤
፷፪ አሥራ ሁለት ዓመት የሆናት አንዲት ሴት ልጅ ነበረችውና፤ እርስዋም ለሞት ቀርባ ነበረች። ሲሄድም ሕዝቡ ያጨናንቁት ነበር።
፷፫ ከአሥራ ሁለት ዓመትም ጀምሮ ደም የሚፈሳት ሴት ነበረች፥ ትዳርዋንም ሁሉ ለባለመድኃኒቶች ከሰራ ማንም ሊፈውሳት አልተቻለውም።
፷፬ በኋላውም ቀርባ የልብሱን ጫፍ ዳሰሰች፥ የደምዋም ፈሳሽ በዚያን ጊዜ ቆመ።
፷፭ ኢየሱስም። የዳሰሰኝ ማን ነው? አለ። ሁሉም በካዱ ጊዜ፥ ጴጥሮስና ከእርሱ ጋር የነበሩት። አቤቱ፥ ሕዝቡ ያጫነቁሃልና ያጋፉህማል፤ የዳሰሰኝ ማን ነው ትላለህን? አሉ።
፷፮ ኢየሱስ ግን። አንድ ሰው ዳሰሶኛል፥ ኃይል ከእኔ እንደ ወጣ እኔ አውቃለሁና አለ።
፷፯ ሴቲቱም እንዳልተሰወረች ባየች ጊዜ እየተንቀጠቀጠች መጥታ በፊቱ ተደፋች፥ በምን ምክንያትም እንደ ዳሰሰችው ፈጥናም እንደ ተፈወሰች በሕዝቡ ሁሉ ፊት አወራች።
፷፰ እርሱም። ልጄ ሆይ፥ እምነትሽ አድኖሻል፤ በሰላም ሂጂ አላት።
፷፱ እርሱም ገና ሲናገር አንድ ሰው ከምኩራብ አለቃው ቤት መጥቶ። ልጅህ ሞታለች፤ እንግዲህ መምህሩን አታድክም አለ።
፸ ኢየሱስ ግን ሰምቶ። አትፍራ፤ እመን ብቻ ትድንማለች ብሎ መለሰለት።
፸፩ ወደ ቤትም ሲገባ ከጴጥሮስና ከያዕቆብ ከዮሐንስም ከብላቴናይቱም አባትና እናት በቀር ማንም ከእርሱ ጋር ይገባ ዘንድ አልፈቀደም።
፸፪ ሁሉም እያለቀሱላት ዋይ ዋይ ይሉ ነበር። እርሱ ግን። አታልቅሱ፤ ተኝታለች እንጂ አልሞተችም አለ።
፸፫ እነደ ሞተችም አውቀው በጣም ሳቁበት።
፸፬ እርሱ ግን እጅዋን ይዞ። አንቺ ብላቴና፥ ተነሺ ብሎ ጮኸ።
፸፭ ነፍስዋም ተመለሰች፥ ፈጥናም ቆመች፥ የምትበላውንም እንዲሰጡአት አዘዘ።
፸፮ ወላጆችዋም ተገረሙ፤ እርሱ ግን የሆነውን ለማንም እንዳይነግሩ አዘዛቸው።

፱

፩ አሥራ ሁለቱንም ሐዋርያት በአንድነት ወደ እርሱ ጠርቶ በአጋንንት ሁሉ ላይ ደዌንም ይፈውሱ ዘንድ ኃይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤
፪ የእግዚአብሔርንም መንግሥት እንዲሰብኩና ድውዮችን እንዲፈውሱ ላካቸው፥
፫ እንዲህም አላቸው። በትርም ቢሆን፥ ከረጢትም ቢሆን፥ እንጀራም ቢሆን፥ ብርም ቢሆን ለመንገድ ምንም አትያዙ፥ ሁለት እጀ ጠባብም አይሁንላችሁ።
፬ በማናቸውም በምትገቡበት ቤት በዚያ ተቀመጡ ከዚያም ውጡ።
፭ ማናቸውም የማይቀበሉአችሁ ቢሆኑ፥ ከዚያ ከተማ ወጥታችሁ ምስክር እንዲሆንባቸው ከእግራችሁ ትቢያ አራግፉ።
፮ ወጥተውም ወንጌልን እየሰበኩና በሰፍራው ሁሉ እየፈወሱ በየመንደሩ ያልፉ ነበር።
፯ የአራተኛው ክፍል ገዥ ሄሮድስም የተደረገውን ነገር ሁሉ ሰምቶ፥ እንዳንድ ሰዎች።
፰ ዮሐንስ ከሙታን ተነሣ፥ ሌሎችም። ኤልያስ ተገለጠ፥ ሌሎችም። ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል ይሉ ስለ ነበሩ አመነታ።
፱ ሄሮድስም። ዮሐንስን እኔ ራሱን አስቈረጥሁት፤ ይህ እንዲህ ያለ ነገር የምሰማበት ማን ነው? አለ። ሊያየውም ይሻ ነበር።
፲ ሐዋርያትም ተመልሰው ያደረጉትን ሁሉ ነገሩት። ከእርሱ ጋርም ወሰዶአቸው ቤተ ሳይዳ ከምትባል ከተማ አጠገብ ወደ ምድረ በዳ ለብቻው ፈቀቅ አለ።
፲፩ ሕዝቡም አውቀው ተከተሉት፤ ተቀብሎአቸውም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ይነግራቸው ነበር፥ መፈወስ ያስፈለጋቸውንም ፈወሳቸው።
፲፪ ቀኑም ይመሸ ጀመር፤ አሥራ ሁለቱም ቀርበው። በዚህ በምድረ በዳ ነንና በዙሪያችን ወዳሉ መንደሮችና ገጠሮች ሄደው እንዲያድሩና ምግብ እንዲያገኙ ሕዝቡን አሰናብት አሉት።
፲፫ እርሱ ግን። እናንተ የሚበሉትን ስጡአቸው አላቸው። እነርሱም። ሄደን ለዚህ ሁሉ ሕዝብ ምግብ ካልገዛን፥ ከአምስት እንጀራና ከሁለት ዓሣ የሚበልጥ የለንም አሉት፤
፲፬ አምስት ሺህ ሰዎች ያህሉ ነበርና። ለደቀ መዛሙርቱ። በየክፍሉ አምሳ አምሳውን አሰቀምጡአቸው አላቸው።
፲፭ እንዲህም አደረጉ ሁሉንም አሰቀመጡአቸው።
፲፮ አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ፥ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረካቸው ቈርሶም ለሕዝቡ እንዲያቀርቡ ለደቀ መዛርሙርቱ ሰጠ።
፲፯ ሁሉም በልተው ጠገቡ፥ ከእነርሱም የተረፈውን ቍርሰራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ወሰዱ።
፲፰ ለብቻውም ሲጸልይ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ ጋር ነበሩ። ሕዝቡ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ይላሉ? ብሎ ጠየቃቸው።

፶፱ እነርሱም መልሰው። መጥምቁ ዮሐንስ፥ ሌሎችም። ኤልያስ፥ ሌሎችም። ከቀደሙት ነቢያት አንዱ ተነሥቶአል ይላሉ አሉት።
፷ እናንተስ እኔ ማን እንደ ሆንሁ ትላላችሁ? አላቸው። ጴጥሮስም መልሶ። ከእግዚአብሔር የተቀባህ ነህ አለ።
፷፩-፷፪ ለሁሉም እንዲህ አላቸው። በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መሰቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ።
፷፫ ነፍሱን ሊያድን የሚወድ ሁሉ ያጠፋታልና፤ ስለ እኔ ነፍሱን የሚያጠፋ ሁሉ ግን እርሱ ያድናታል።
፷፬ ሰው ዓለሙን ሁሉ አትርፎ ራሱን ቢያጠፋ ወይም ቢያጐድል ምን ይጠቅመዋል?
፷፭ በእኔና በቃሌ የሚያፍር ሁሉ፥ የሰው ልጅ በክብሩ በአባቱና በቅዱሳን መላእክቱ ክብርም ሲመጣ በእርሱ ያፍርበታል።
፷፮ እውነት እላችኋለሁ፥ በዚህ ከሚቆሙት ሰዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት እስኪያዩ ድረስ ሞትን የማይቀምሱ አንዳንድ አሉ።
፷፯ ከዚህም ቃል በኋላ ስምንት ቀን ያህል ቈይቶ ጴጥሮስንና ዮሐንስን ያዕቆብንም ይዞ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ።
፷፰ ሲጸልይም የፊቱ መልክ ተለወጠ፤ ልብሱም ተብለጭልጮ ነጭ ሆነ።
፷፱ እነሆም፥ ሁለት ሰዎች እነርሱም ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ይነጋገሩ ነበር፤
፸ በክብርም ታይተው በኢየሩሳሌም ሊፈጽም ስላለው ስለ መውጣቱ ይናገሩ ነበር።
፸፩ ነገር ግን ጴጥሮስንና ከእርሱ ጋር የነበሩት እንቅልፍ ከበደባቸው፤ ነቅተው ግን ክብሩንና ከእርሱ ጋር ቆመው የነበሩትን ሁለት ሰዎች አዩ።
፸፪ ከእርሱም ሲለዩ ጴጥሮስ ኢየሱስን። አቤቱ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነውና አንድ ለእንተ አንድም ለሙሴ አንድም ለኤልያስ ሦስት ዳሶች እንሥራ አለው፤ የሚለውንም አያውቅም ነበር።
፸፫ ይህንም ሲናገር ደመና መጣና ጋረዳቸው፤ ወደ ደመናውም ሲገቡ ሳሉ ፈሩ።
፸፬ ከደመናውም። የመረጥሁት ልጄ ይህ ነው፥ እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ።
፸፭ ድምፁም ከመጣ በኋላ ኢየሱስ ብቻውን ሆኖ ተገኘ። እነርሱም ዝም አሉ ካዩትም ነገር በዚያ ወራት ምንም ለማንም አላወሩም።
፸፮ በነገውም ከተራራ ሲወርዱ ብዙ ሕዝብ ተገናኙት።
፸፯ እነሆም፥ ከሕዝቡ አንድ ሰው እንዲህ እያለ ጮኸ። መምህር ሆይ፥ ለእኔ አንድ ልጅ ነውና ልጄን እንድታይልኝ እለምንሃለሁ።
፸፰ እነሆም፥ ጋኔን ይይዘዋል፥ ድንገትም ይጮኻል አረፋም እያስደፈቀው ያንፈራግጠዋል፥ እየቀጠቀጠም በጭንቅ ይለቀዋል፤
፸፱ ደቀ መዛሙርትህንም እንዲያወጡት ለመንሁ፥ አልቻሉምም።
፹ ኢየሱስም መልሶ። እናንተ የማታምን ጠማማ ትውልድ፥ እስከ መቼ ከእናንተ ጋር እኖራለሁ? እስከ መቼስ እታገሣችኋለሁ? ልጅህን ወደዚህ አምጣው አለ።
፹፩ ሲቀርብም ጋኔኑ ጣለውና አንፈራገጠው፤ ኢየሱስ ግን ርኩሱን መንፈስ ገሥጾ ብላቴናውን ፈወሰው ለአባቱም መለሰው።
፹፪ ሁሉም ከእግዚአብሔር ታላቅነት የተነሣ ተገረሙ። ሁሉም ኢየሱስ ባደረገው ሁሉ ሲደነቁ፥
፹፬ ለደቀ መዛሙርቱ። የሰው ልጅ በሰው እጅ ይሰጥ ዘንድ አለውና እናንተ ይህን ቃል በጆሮአችሁ አኑሩ አለ።
፹፭ እነርሱ ግን ይህን ነገር አላሰተዋሉም፥ እንዳይገባቸውም ተሰውሮባቸው ነበር፤ ስለዚህ ነገርም እንዳይጠይቁት ፈሩ።
፹፮ ከእነርሱም ማን እንዲበልጥ ክርክር ተነሣባቸው።
፹፯ ኢየሱስም የልባቸውን አሳብ አውቆ ሕፃንን ያዘ፤ በአጠገቡም አቁሞ።
፹፰ ማንም ይህን ሕፃን በስሜ የሚቀበል እኔን ይቀበላል፤ የሚቀበለኝም ሁሉ የላከኝን ይቀበላል፤ ከሁላችሁ የሚያንስ እርሱ ታላቅ ነውና አላቸው።
፹፱ ዮሐንስም መልሶ። አቤቱ፥ አንድ ሰው በስምህ አጋንንትን ሲያወጣ አየነው፥ ከእኛ ጋርም ስለማይከተል ከለከልነው አለው።
፺ ኢየሱስ ግን። የማይቃወማችሁ ከእናንተ ጋር ነውና አትከልክሉት አለው።
፺፩ የሚወጣበትም ወራት በቀረበ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ለመሄድ ፊቱን አቀና፥
፺፪ በፊቱም መልክተኞችን ሰደደ። ሄደውም ሊያሰናዱለት ወደ አንድ ወደ ሳምራውያን መንደር ገቡ፤
፺፫ ፊቱም ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሄድ ስለ ነበረ አልተቀበሉትም።
፺፬ ደቀ መዛሙርቱም ያዕቆብና ዮሐንስ አይተው። ጌታ ሆይ፥ ኤልያስ ደግሞ እንዳደረገ እሳት ከሰማይ ወርዶ ያጥፋቸው እንል ዘንድ ትወዳለህን? አሉት።
፺፭ እርሱ ግን ዘወር ብሎ ገሠጻቸውና። ምን ዓይነት መንፈስ እንደ ሆነላችሁ አታውቁም፤
፺፮ የሰው ልጅ የሰውን ነፍስ ሊያድን እንጂ ሊያጠፋ አልመጣም አለ። ወደ ሌላ መንደርም ሄዱ።
፺፯ እነርሱም በመንገድ ሲሄዱ አንድ ሰው። ጌታ ሆይ፥ ወደ ምትሄድበት ሁሉ እከተልሃለሁ አለው።
፺፰ ኢየሱስም። ለቀበሮዎች ጕድጓድ ለሰማይም ወፎች መሳፈሪያ አላቸው፥ ለሰው ልጅ ግን ራሱን የሚያሰጠጋበት የለውም አለው።
፺፱ ሌላውንም። ተከተለኝ አለው። እርሱ ግን። ጌታ ሆይ፥ አስቀድሜ ልሂድና አባቴን እቀብር ዘንድ ፍቀድልኝ አለ።
፻ ኢየሱስም። ሙታናቸውን እንዲቀብሩ ሙታንን ተዋቸው፤ አንተስ ሄደህ የእግዚአብሔርን መንግሥት ስበክ አለው።
፻፩ ደግሞ ሌላው። ጌታ ሆይ፥ እከተልሃለሁ፤ ነገር ግን አስቀድሜ ከቤቴ ሰዎች እንድሰናበት ፍቀድልኝ አለ።
፻፪ ኢየሱስ ግን። ማንም ዕርፍ በእጁ ይዞ ወደ ኋላ የሚመለከት ለእግዚአብሔር መንግሥት የተገባ አይደለም አለው።

፲

፩ ከዚህም በኋላ ጌታ ሌሎቹን ሰብዓ ሾመ፥ ሁለት ሁለትም አድርጎ እርሱ ሊሄድበት ወዳለው ከተማና ሰፍራ ሁሉ በፊቱ ላካቸው።

፪ አላቸውም። መከሩስ ብዙ ነው፥ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ እንግዴህ የመከሩን ጌታ ለመከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት።
፫ ሂዱ፤ እነሆ፥ እንደ በጎች በተኩላዎች መካከል እልካችኋለሁ።
፬ ኮረጆም ከረጢትም ጫማም አትያዙ፤ በመንገድም ለማንም እጅ አትንሡ።
፭ ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ። ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ።
፮ በዚያም የሰላም ልጅ ቢኖር፥ ሰላማችሁ ያድርበታል፤ አለዚያም ይመለስላችኋል።
፯ በዚያም ቤት ከእነርሱ ዘንድ ካለው እየበላችሁና እየጠጣችሁ ተቀመጡ፤ ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋልና። ከቤት ወደ ቤት አትተላለፉ።
፰ ወደምትገቡባትም ከተማ ሁሉ ቢቀበሉአችሁ፥ ያቀረቡላችሁን ብሉ፤
፱ በእርስዋም ያሉትን ድውዮችን ፈውሱና። የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ እናንተ ቀረበች በሉአቸው።
፲ ነገር ግን ወደምትገቡባት ከተማ ሁሉ ባይቀበሉአችሁ፥ ወደ አደባባይዋ ወጥታችሁ።
፲፩ ከኪተማችሁ የተጣበቀብንን ትቢያ እንኳን እናራግፍላችኋለን፤ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን ወደ እናንተ እንደ ቀረበች ይህን እወቁ በሉ።
፲፪ እላችኋለሁ፥ በዚያን ቀን ከዚያች ከተማ ይልቅ ለሰዶም ይቀልላታል።
፲፫ ወዮልሽ ኮራዚን፥ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፤ በእናንተ የተደረገው ተአምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን፥ ማቅ ለብሰው በአመድም ተቀምጠው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር።
፲፬ ነገር ግን በፍርድ ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀልላቸዋል።
፲፭ አንቺም ቅፍርናሆም፥ እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲኦል ትወርጃለሽ።
፲፮ የሚሰማችሁ እኔን ይሰማል፥ እናንተንም የጣለ እኔን ይጥላል፤ እኔንም የጣለ የላከኝን ይጥላል።
፲፯ ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው። ጌታ ሆይ፥ አጋንንት ሰንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት።
፲፰ እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ።
፲፱ እነሆ፥ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ፥ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፥ የሚጐዳችሁም ምንም የለም።
፳ ነገር ግን መናፍስት ስለ ተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማያት ስለ ተጻፈ ደስ ይበላችሁ።
፳፩ በዚያን ሰዓት ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ሐሤት አደረገና። የሰማይና የምድር ጌታ አባት ሆይ፥ ይህን ከጥበበኞችና ከአስተዋዮች ሰውረህ ለሕፃናት ስለ ገለጥህላቸው አመሰግናለሁ፤ አዎን አባት ሆይ፥ ፈቃድህ በፊትህ እንዲህ ሆኖአልና።
፳፪ ሁሉ ከአባቴ ዘንድ ተሰጥቶኛል፥ ወልድንም ማን እንደ ሆነ ከአብ በቀር የሚያውቅ የለም፥ አብንም ማን እንደ ሆነ ከወልድ በቀር ወልድም ሊገልጥለት ከሚፈቅድ በቀር የሚያውቅ የለም አለ።
፳፫ ወደ ደቀ መዛሙርቱም ዘወር ብሎ ለብቻቸው። የምታዩትን የሚያዩ ዓይኖች ብፁዓን ናቸው።
፳፬ እላችኋለሁና፥ እናንተ የምታዩትን ብዙዎች ነቢያትና ነገሥታት ሊያዩ ወደዱ አላዩምም፥ የምትሰሙትንም ሊሰሙ ወድደው አልሰሙም አለ።
፳፭ እነሆም፥ አንድ ሕግ አዋቂ ሊፈትነው ተነሥቶ። መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? እለው።
፳፮ እርሱም በሕግ የተጻፈው ምንድር ነው? እንዴትስ ታነባለህ? አለው።
፳፯ እርሱም መልሶ። ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም በፍጹም ኃይልህም በፍጹም አሳብህም ውደድ፥ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው።
፳፰ ኢየሱስም። እውነት መለስህ፤ ይህን አድርግ በሕይወትም ትኖራለህ አለው።
፳፱ እርሱ ግን ራሱን ሊያጸድቅ ወድዶ ኢየሱስን። ባልንጀራዬስ ማን ነው? አለው።
፴ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለ። አንድ ሰው ከኢየሩሳሌም ወደ ኢያሪኮ ወረደ በወንበዴዎችም እጅ ወደቀ፤ እነርሱም ደግሞ ገፈፉት ደበደቡትም በሕይወትና በሞት መካከልም ትተውት ሄዱ።
፴፩ ድንገትም አንድ ካህን በዚያ መንገድ ወረደ አይቶትም ገለል ብሎ አለፈ።
፴፪ እንዲሁም ደግሞ አንድ ሌዋዊ ወደዚያ ሰፍራ መጣና አይቶት ገለል ብሎ አለፈ።
፴፫ አንድ ሳምራዊ ግን ሲሄድ ወደ እርሱ መጣ አይቶትም አዘነለት፥
፴፬ ቀርቦም ዘይትና የወይን ጠጅ በቍሰሎቹ ላይ አፍስሶ አሰራቸው፥ በራሱ አህያም ላይ አስቀምጦት ወደ እንግዶች ማደርያ ወስደው ጠበቀውም።
፴፭ በማግሥቱም ሁለት ዲናር አውጥቶ ለባለቤቱ ሰጠና። ጠብቀው፥ ከዚህም በላይ የምትከሰረውን ሁሉ እኔ ስመለስ እከፍልሃለሁ አለው።
፴፮ እንግዲህ ከነዚህ ከሦስቱ በወንበዴዎች እጅ ለወደቀው ባልንጀራ የሆነው ማንኛው ይመስልሃል?
፴፯ እርሱም። ምሕረት ያደረገለት አለ። ኢየሱስም። ሂድ አንተም እንዲሁ እድርግ አለው።
፴፰ ሲሄዱም እርሱ ወደ አንዲት መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤትዋ ተቀበለችው።
፴፱ ለእርስዋም ማርያም የምትባል እኅት ነበረቻት፥ እርስዋም ደግሞ ቃሉን ልትሰማ በኢየሱስ እግር አጠገብ ተቀምጣ ነበረች።
፵ ማርታ ግን አገልግሎት ሰለ በዛባት ባከነች፤ ቀርባም። ጌታ ሆይ፥ እኔ እንድሠራ እኅቴ ብቻዬን ስትተወኝ አይገድህምን? እንኪያስ እንድታግዘኝ ንገራት አለችው።
፵፩ ኢየሱስም መልሶ። ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥
፵፪ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም አላት።

፲፩

፩ እርሱም በአንድ ሰፍራ ይጸልይ ነበር፥ በጨረሰም ጊዜ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ። ጌታ ሆይ፥ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርቱን እንዳስተማረ እንጸልይ ዘንድ አስተምረን አለው።

፪ አላቸውም። ሰትጸልዩ እንዲህ በሉ። በሰማያት
የምትኖር አባታችን ሆይ፤ ስምህ ይቀደስ፤ መንግሥትህ
ትምጣ፤ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር
ትሁን፤
፫ የዕለት እንጀራችንን ዕለት ዕለት ስጠን፤
፬ ኃጢአታችንንም ይቅር በለን፥ እኛ ደግሞ
የበደሉንን ሁሉ ይቅር ብለናልና፤ ከክፉ አድነን እንጂ
ወደ ፈተና አታግባን።
፭ እንዲህም አላቸው። ከእናንተ ማናቸውም ወዳጅ
ያለው፥ በእኩል ሌሊትስ ወደ እርሱ ሄዶ። ወዳጄ ሆይ፥
ሦስት እንጀራ አበድረኝ፥
፮ አንድ ወዳጄ ከመንገድ ወደ እኔ መጥቶ
የማቀርብለት የለኝምና ይላልን?
፯ ያም ከውስጥ መልሶ። አታድክመኝ፤ አሁን ደጁ
ተቈልፎአል ልጆቼም ከእኔ ጋር በአልጋ ላይ አሉ፤
ተነሥቼ ልስጥህ አልችልም ይላልን?
፰ እላችኋለሁ፥ ወዳጅ ስለ ሆነ ተነሥቶ ባይሰጠው
እንኳ፥ ሰለ ንዝነዛው ተነስቶ የሚፈልገውን ሁሉ
ይሰጠዋል።
፱ እኔም እላችኋለሁ። ለምኑ፥ ይሰጣችሁማል፤ ፈልጉ፥
ታገኙማላችሁ፤ መዝጊያን አንኳኩ፥ ይከፍትላችሁማል።
፲ የሚለምን ሁሉ ይቀበላልና፥ የሚፈልግም ያገኛል፥
መዝጊያውንም ለሚያንኳኳው ይከፈትለታል።
፲፩ አባት ከሆናችሁ ከእናንተ ከማንኛችሁም ልጁ
እንጀራ ቢለምነው፥ እርሱም ድንጋይ ይሰጠዋልን? ዓሣ
ደግሞ ቢለምነው በዓሣ ፋንታ እባብ ይሰጠዋልን?
፲፪ ወይስ እንቁላል ቢለምነው ጊንጥ ይሰጠዋልን?
፲፫ እንኪያስ እናንተ ክፉዎች ስትሆኑ ለልጆቻችሁ
መልካም ስጦታ መስጠት ካወቃችሁ፥ በሰማይ ያለው
አባት ለሚለምኑት እንዴት አብልጦ መንፈስ ቅዱስን
ይሰጣቸው?
፲፬ ዲዳውንም ጋኔን ያወጣ ነበር፤ ጋኔኑም ከወጣ
በኋላ ዲዳው ተናገረ ሕዝቡም ተደነቁ፤
፲፭ ነገር ግን ከእነርሱ አንዳንዱ። በብዔል ዜቡል
በአጋንንት አለቃ አጋንንትን ያወጣል አሉ።
፲፮ ሌሎችም ሲፈትኑት ከሰማይ ምልክት ከእርሱ
ይፈልጉ ነበር።
፲፯ እርሱ ግን ኣሳባቸውን አውቆ እንዲህ አላቸው።
እርስ በርሰዋ የምትለያይ መንግሥት ሁሉ ትጠፋለች፤
ቤትም በቤት ላይ ይወድቃል።
፲፰ እኔ አጋንንትን በብዔል ዜቡል እንዳወጣ
ትላላችሁና ሰይጣን ደግሞ እርስ በርሱ ከተለያየ
መንግሥቱ እንዴት ትቆማለች?
፲፱ እኔስ በብዔል ዜቡል አጋንንትን የማወጣ
ከሆንሁ፥ ልጆቻችሁ በማን ያወጡአቸዋል? ሰለዚህ
እነርሱ ፈራጆች ይሆኑባችኋል።
፳ እኔ ግን በእግዚአብሔር ጣት አጋንንትን የማወጣ
ከሆንሁ፥ እንግዲህ የእግዚአብሔር መንግሥት ወደ
እናንተ ደርሳለች።
፳፩ ኃይለኛ ሰው ጋሻና ጦር ይዞ የራሱን ግቢ
ቢጠብቅ፥ ያለው ገንዘቡ በሰላም ይሆናል፤
፳፪ ከእርሱ ይልቅ የሚበረታ መጥቶ ሲያሸንፈው
ግን፥ ታምኖበት የነበረውን ጋሻና ጦር ይወስድበታል
ምርኮውንም ያካፍላል።
፳፫ ከእኔ ጋር ያልሆነ ይቃወመኛል፥ ከእኔ ጋርም
የማያከማች ይበትናል።
፳፬ ርኩስ መንፈስ ከሰው በወጣ ጊዜ ዕረፍትን
እየፈለገ ውኃ በሌለበት ቦታ ያልፋል፤ ባያገኝም። ወደ
ወጣሁበት ቤቴ እመለሳለሁ ይላል፤
፳፭ ሲመጣም ተጠርጎ አጊጦም ያገኘዋል።
፳፮ ከዚያ ወዲያ ይሄድና ከእርሱ የከፉትን ሌሎችን
ሰባት አጋንንት ከእርሱ ጋር ይይዛል፥ ገብተውም በዚያ
ይኖራሉ፤ ለዚያም ሰው ከፊተኛው ይልቅ የኋለኛው
ይብሰበታል።
፳፯ ይህንም ሲናገር፥ ከሕዝቡ አንዲት ሴት
ድምፅዋን ከፍ አድርጋ። የተሸከመችህ ማኅፀንና
የጠባሃቸው ጡቶች ብፁዓን ናቸው አለችው።
፳፰ እርሱ ግን። እዎን፥ ብፁዓንስ የእግዚአብሔርን
ቃል ሰምተው የሚጠብቁት ናቸው አለ።
፳፱ ብዙ ሕዝብም በተሰበሰቡ ጊዜ እንዲህ
ይል ጀመር። ይህ ትውልድ ክፉ ነው፤ ምልክት
ይፈልጋል፥ ከነቢዩም ከዮናስ ምልክት በቀር ምልክት
አይሰጠውም።
፴ ዮናስ ለነነዌ ሰዎች ምልክት እንደ ሆናቸው፥
እንዲሁ ደግሞ የሰው ልጅ ለዚህ ትውልድ ምልክት
ይሆናል።
፴፩ ንግሥተ አዜብ በፍርድ ከዚህ ትውልድ ሰዎች
ጋር ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች፤ የሰሎሞንን ጥበብ
ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና፥ እነሆም፥
ከሰሎሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ።
፴፪ የነነዌ ሰዎች በፍርድ ከዚህ ትውልድ ጋር
ተነሥተው ይፈርዱበታል፤ በዮናስ ሰብከት ንስሐ
ገብተዋልና፥ እነሆም፥ ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።
፴፫ መብራትንም አብርቶ በሰውር ወይም በእንቅብ
በታች የሚያኖረው የለም፥ የሚገቡ ሰዎች ብርሃኑን
እንዲያዩ በመቅረዝ ላይ ያኖረዋል እንጂ።
፴፬ የሰውነትህ መብራት ዓይንህ ናት። ዓይንህ
ጤናማ በሆነች ጊዜ ሰውነትህ ሁሉ ደግሞ ብሩህ
ይሆናል። ዓይንህ ታማሚ በሆነች ጊዜ ግን ሰውነትህ
ደግሞ የጨለመ ይሆናል።
፴፭ እንግዲህ በአንተ ያለው ብርሃን ጨለማ
እንዳይሆን ተመልከት።
፴፮ እንግዲህ ሰውነትህ ሁሉ የጨለማ ቊራጭ
የሌለበት ብሩህ ቢሆን፥ መብራት በደመቀ ብርሃን
እንደሚያበራልህ በጭራሽ ብሩህ ይሆናል።
፴፯ ይህንንም ሲናገር አንድ ፈሪሳዊ ከእርሱ ጋር ምሳ
ይበላ ዘንድ ለመነው ገብቶም ተቀመጠ።
፴፰ ከምሳም በፊት አሰቀድሞ እንዳልታጠበ ባየው
ጊዜ ፈሪሳዊው ተደነቀ።
፴፱ ጌታም እንዲህ አለው። አሁን እናንተ ፈሪሳውያን
የጽዋውንና የወጭቱን ውጭ ታጠራላችሁ፥ ውስጣችሁ
ግን ቅሚያና ክፋት ሞልቶበታል
፵ እናንት ደንቆሮዎች፥ የውጭውን የፈጠረ
የውስጡን ደግሞ አልፈጠረምን?
፵፩ ነገር ግን በውስጥ ያለውን ምጽዋት አድርጋችሁ
ስጡ፥ እነሆም፥ ሁሉ ንጹሕ ይሆንላችኋል።
፵፪ ነገር ግን እናንተ ፈሪሳውያን፥ ከአዝሙድና
ከጤና አዳም ከአትክልትም ሁሉ አሥራት
ስለምታወጡ፥ ፍርድንና እግዚአብሔርን መውደድ
ስለምትተላለፉ፥ ወዮላችሁ፤ ነገር ግን ሌላውን
ሳትተዉ ይህን ልታደርጉት ይገባችሁ ነበር።
፵፫ እናንተ ፈሪሳውያን፥ በምኩራብ የከበሬታ ወንበር
በገበያም ሰላምታ ስለምትወዱ፥ ወዮላችሁ።

፵፩ እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን፥ ሰዎች ሳያውቁ በላዩ የሚሄዱበት የተሰወረ መቃብር ስለምትመስሉ፥ ወዮላችሁ።
፵፪ ከሕግ አዋቂዎችም እንዱ መልሶ። መምህር ሆይ፥ ይህን ማለትህ እኛን ደግሞ መሰደብህ ነው አለው።
፵፫ እርሱም እንዲህ አለ። እናንተ ደግሞ ሕግ አዋቂዎች፥ አሰቸጋሪ ሸክም ለሰዎች ስለምታሸክሙ፥ ራሳችሁም በአንዲት ጣታችሁ ሰንኳ ሸክሙን ስለማትነኩት፥ ወዮላችሁ።
፵፬ አባቶቻችሁ የገደሉአቸውን የነቢያትን መቃብር ስለምትሠሩ፥ ወዮላችሁ።
፵፭ እንግዲህ ለአባቶቻችሁ ሥራ ትመሰክራላችሁ ትሰማማላችሁም፤ እነርሱ ገድለዋቸዋልና፥ እናንተም መቃብራቸውን ትሠራላችሁ።
፵፮ ስለዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበብ እንዲህ አለች። ወደ እነርሱ ነቢያትንና ሐዋርያትን እልካለሁ፥ ከእነርሱም ይገድላሉ ያሳድዱማል፥
፶ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ የፈሰሰው የነቢያት ሁሉ ደም፥
፶፩ ከአቤል ደም ጀምሮ በመሠዊያውና በቤተ መቅደስ መካከል እስከ ጠፋው እስከ ዘካርያስ ደም ድረስ፥ ከዚህ ትውልድ እንዲፈለግ አዎን እላችኋለሁ፥ ከዚህ ትውልድ ይፈለጋል።
፶፪-፶፫ እናንተ ሕግ አዋቂዎች፥ የእውቀትን መክፈቻ ስለ ወሰዳችሁ፥ ወዮላችሁ ራሳችሁ አልገባችሁም የሚገቡትንም ከለከላችሁ።

፲፪

፩ በዚያን ጊዜ የሕዝብ አእላፍ እርስ በርሳቸው እስኪረጋገጡ ድረስ ተሰብስበው ሳሉ፥ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ ይል ጀመር። አስቀድማችሁ ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ፥ እርሱም ግብዝነት ነው።
፪ ነገር ግን የማይገለጥ የተከደነ፥ የማይታወቅም የተሰወረ ምንም የለም።
፫ ስለዚህ በጨለማ የምትናገሩት ሁሉ በብርሃን ይሰማል፥ በእልፍኝም ውስጥ በጆሮ የምትናገሩት በሰገነት ላይ ይሰበካል።
፬ ለእናንተም ለወዳጆቼ እላችኋለሁ፥ ሥጋን የሚገድሉትን በኋላም እንድ ሰንኳ የሚበልጥ ሊያደርጉ የማይችሉትን አትፍሩ።
፭ እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ፥ እርሱን ፍሩ።
፮ አምስት ድንቢጦች በአሥር ሳንቲም ይሸጡ የለምን? ከእነርሱም አንዲቱ ሰንኳ በእግዚአብሔር ፊት አትረሳም።
፯ ነገር ግን የእናንተ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ የተቈጠረ ነው፤ እንግዲያስ አትፍሩ ከብዙ ድንቢጦች ትበልጣላችሁ።
፰ እላችሁማለሁ፥ በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ፥ የሰው ልጅ ደግሞ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይመሰክርለታል፤
፱ በሰውም ፊት የሚክደኝ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ይካዳል።
፲ በሰው ልጅም ላይ ቃል የሚናገር ሁሉ ይሰረይለታል፤ መንፈስ ቅዱስን የሚሰድብ ግን አይሰረይለትም።
፲፩ ወደ ምኩራቦችና ወደ መኳንንቶችም ወደ ገዢዎችም ሲጐትቱአችሁ፥ እንዴት ወይም ምን እንድትመልሱ ወይም እንድትናገሩ አትጨነቁ፤
፲፪ መንፈስ ቅዱስ በዚያች ሰዓት ልትናገሩ የሚገባችሁን ያስተምራችኋልና።
፲፫ ከሕዝቡም አንድ ሰው። መምህር ሆይ፥ ርስቱን ከእኔ ጋር እንዲካፈል ለወንድሜ ንገረው አለው።
፲፬ እርሱም። አንተ ሰው፥ ፈራጅና አካፋይ በላያችሁ አንድሆን ማን ሾመኝ? አለው።
፲፭ የሰው ሕይወት በገንዘቡ ብዛት አይደለምና ተጠንቀቁ፥ ከመጐምጀትም ሁሉ ተጠበቁ አላቸው።
፲፮ ምሳሌም ነገራቸው እንዲህ ሲል። አንድ ባለ ጠጋ ሰው እርሻ እጅግ ፍሬያም ሆነችለት።
፲፯ እርሱም። ፍሬዬን የማከማችበት ሰፍራ አጥቻለሁና ምን ላድርግ? ብሎ በልቡ አሰበ።
፲፰ እንዲህ አደርጋለሁ፤ ጐተራዬን አፍርሼ ሌላ የሚበልጥ እሠራለሁ፥ በዚያም ፍሬዬንና በረከቴን ሁሉ አከማቻለሁ፤
፲፱ ነፍሴንም። አንቺ ነፍሴ፥ ለብዙ ዘመን የሚቀር ብዙ በረከት አለሽ፤ ዕረፊ፥ ብዪ፥ ጠጪ፥ ደስ ይበልሽ እላታለሁ አለ።
፳ እግዚአብሔር ግን። አንተ ሰነፍ፥ በዚች ሌሊት ነፍስህን ከአንተ ሊወስዱአት ይፈልጓታል፤ ይህስ የሰበሰብኸው ለማን ይሆናል? አለው።
፳፩ ለራሱ ገንዘብ የሚያከማች፥ በእግዚአብሔር ዘንድም ባለ ጠጋ ያልሆነ እንዲህ ነው።
፳፪ ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ። ስለዚህ እላችኋለሁ፥ ለነፍሳችሁ በምትበሉት ወይም ለሰውነታችሁ በምትለብሱት አትጨነቁ።
፳፫ ነፍስ ከመብል ሰውነትም ከልብስ ይበልጣልና።
፳፬ ቊራዎችን ተመልከቱ፤ አይዘሩም አያጭዱምም፥ ዕቃ ቤትም ወይም ጎተራ የላቸውም፥ እግዚአብሔርም ይመግባቸዋል፤ እናንተስ ከወፎች እንዴት ትበልጣላችሁ?
፳፭ ከእናንተ ተጨንቆ በቁመቱ ላይ አንድ ክንድ መጨመር የሚችል ማን ነው?
፳፮ እንግዲህ ትንሹን ነገር ሰንኳ የማትችሉ ከሆናችሁ፥ ስለ ምን በሌላ ትጨነቃላችሁ?
፳፯ አበቦችን እንዴት እንዲያድጉ ተመልከቱ፤ አይደክሙም አይፈትሉምም፤ ነገር ግን እላችኋለሁ፥ ሰሎሞንስ እንኳ በክብሩ ሁሉ ከእነዚህ እንደ አንዲቱ አለበሰም።
፳፰ እግዚአብሔር ግን ዛሬ ያለውን ነገም ወደ እቶን የሚጣለውን በሜዳ የሆነውን ሣር እንዲህ የሚያለብሰው ከሆነ፥ እናንተ እምነት የጐደላችሁ፥ እናንተንማ ይልቁን እንዴት?
፳፱ እናንተም የምትበሉትን የምትጠጡትንም አትፈልጉ፥ አታወላውሉም፤
፴ ይህንስ ሁሉ በዓለም ያሉ አሕዛብ ይፈልጉታልና፤ የእናንተም አባት ይህ እንዲያስፈልጋችሁ ያውቃል።
፴፩ ዳሩ ግን መንግሥቱን ፈልጉ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል።
፴፪ አንተ ታናሽ መንጋ፥ መንግሥትን ሊሰጣችሁ የአባታችሁ በጎ ፈቃድ ነውና አትፍሩ።
፴፫ ያላችሁን ሸጡ ምጽዋትም ስጡ፤ ሌባ በማይቀርብበት ብልም በማያጠፋበት በሰማያት

የማያልቅ መዝገብ የሚሆኑትን የማያረጁትንም ኮረጆዎች ለራሳችሁ አድርጉ፤
፴፫ መዝገባችሁ ባለበት ልባችሁ ደግሞ በዚያ ይሆናልና።
፴፬ ወገባችሁ የታጠቀ መብራታችሁም የበራ ይሁን፤
፴፭ እናንተም ጌታቸው መጥቶ ደጁን ሲያንኳኳ ወዲያው እንዲከፍቱለት ከሰርግ እሰኪመለስ ድረስ የሚጠብቁ ሰዎችን ምሰሉ
፴፮ ጌታቸው በመጣ ጊዜ ሲተጉ የሚያገኛቸው እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው፤ እውነት እላችኋለሁ፥ ታጥቆ በማዕድ ያስቀምጣቸዋል ቀርቦም ያገለግላቸዋል።
፴፯ ከሌሊቱም በሁለተኛው ወይም በሦስተኛው ክፍል መጥቶ እንዲሁ ቢያገኛቸው፥ እነዚያ ባሪያዎች ብፁዓን ናቸው።
፴፰ ይህን ግን እወቁ ባለቤት በምን ሰዓት ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፥ በነቃ፥ ቤቱም እንዲቆፈር ባልፈቀደም ነበር።
፴፱ እናንተ ደግሞ ተዘጋጅታችሁ ኑሩ፥ የሰው ልጅ በማታሰቡበት ሰዓት ይመጣልና።
፵ ጴጥሮስም። ጌታ ሆይ፥ ይህን ምሳሌ ለእኛ ወይስ ደግሞ ለሁሉ ትናገራለህን? አለው።
፵፩ ጌታም አለ። እንኪያስ ምግባቸውን በጊዜው ይሰጣቸው ዘንድ ጌታው በቤተ ሰዎቹ ላይ የሚሾመው ታማኝና ልባም መጋቢ ማን ነው?
፵፪ ጌታው መጥቶ እንዲህ ሲያደርግ የሚያገኘው ያ ባሪያ ብፁዕ ነው።
፵፫ እውነት እላችኋለሁ፥ ባለው ሁሉ ላይ ይሾመዋል።
፵፬ ያ ባሪያ ግን። ጌታዬ እሰኪመጣ ይዘገያል ብሎ በልቡ ቢያስብ ሎሌዎችንና ገረዶችንም ይመታ ይበላም ይጠጣም ይሰክርም ዘንድ ቢጀምር፥
፵፭ የዚያ ባሪያ ጌታ ባልጠበቃት ቀን ባላወቃትም ሰዓት ይመጣል፥ ከሁለትም ይሰነጥቀዋል እድሉንም ከማይታመኑ ጋር ያደርጋል።
፵፮ የጌታውንም ፈቃድ አውቆ ያልተዘጋጀ እንደ ፈቃዱም ያላደረገ ያ ባሪያ እጅግ ይገረፋል፤
፵፯ ያላወቀ ግን መገረፍ የሚገባውንም ያደረገ ጥቂት ይገረፋል። ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል፥ ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል።
፵፰ በምድር ላይ እሳት ልጥል መጣሁ፥ አሁንም የነደደ ከሆነ ዘንድ ምን እፈልጋለሁ?
፵፱ ነገር ግን የምጠመቃት ጥምቀት አለችኝ፥ እሰክትፈጸምም ድረስ እንዴት እጨነቃለሁ?
፶ በምድር ላይ ሰላምንም ለመስጠት የመጣሁ ይመስላችኋልን? እላችኋለሁ፥ አይደለም፥ መለያየትን እንጂ።
፶፩ ከአሁን ጀምሮ በእንዲት ቤት አምስት ሰዎች ይኖራሉና፤ ሦስቱም በሁለቱ ላይ ሁለቱም በሦስቱ ላይ ተነሥተው ይለያያሉ።
፶፪ አባት በልጁ ላይ ልጅም በአባቱ ላይ፥ እናት በልጅዋ ላይ ልጅዋም በእናትዋ ላይ፥ አማት በምራትዋ ላይ ምራትም በአማትዋ ላይ ተነሥተው ይለያያሉ።
፶፫ ደግሞም ሕዝቡን እንዲህ አለ። ደመና ከምዕራብ ሲወጣ ባያችሁ ጊዜ፥ ወዲያው። ዝናብ ይመጣል ትላላችሁ፥ እንዲሁም ይሆናል፤
፶፬ በአዜብም ነፋስ ሲነፍስ። ትኩሳት ይሆናል ትላላችሁ፥ ይሆንማል።
፶፭ እናንት ግብዞች፥ የምድሩንና የሰማዩን ፊት ልትመረምሩ ታውቃላችሁ፥ ነገር ግን ይህን ዘመን የማትመረምሩ እንዴት ነው?
፶፮ ራሳችሁ ደግሞ ጽድቅን የማትፈርዱ ስለ ምን ነው?
፶፯ ከባላጋራህ ጋር ወደ ሹም ብትሄድ፥ ወደ ዳኛ እንዳይጐትትህ ዳኛውም ለሎሌው አሳልፎ እንዳይሰጥህ ሎሌውም በወኅኒ እንዳይጥልህ፥ ገና በመንገድ ሳለህ ከባላጋራህ እንድትታረቅ ትጋ።
፶፰ እልሃለሁ፥ የመጨረሻዋን ግማሽ ሳንቲም እስክትከፍል ድረስ ከዚያ ከቶ አትወጣም።

፲፫

፩ በዚያን ጊዜም ሰዎች መጥተው ጲላጦስ ደማቸውን ከመሥዋዕታቸው ጋር ስላደባለቀው ስለ ገሊላ ሰዎች አወሩለት።
፪ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። እነዚህ የገሊላ ሰዎች ይህ ስለ ደረሰባቸው ከገሊላ ሰዎች ሁሉ ይልቅ ኃጢአተኞች የሆኑ ይመስሉአችኋልን?
፫ እላችኋለሁ፥ አይደለም፤ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ።
፬ ወይስ በሰሌሆም ግንቡ የወደቀባቸውና የገደላቸው እነዚያ አሥራ ሰምንት ሰዎች በኢየሩሳሌም ከሚኖሩት ሁሉ ይልቅ በደለኞች ይመስሉአችኋልን? አይደለም፥ እላችኋለሁ፤
፭ ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንደዚሁ ትጠፋላችሁ።
፮ ይህንም ምሳሌ አለ። ለአንድ ሰው በወይኑ እትክልት የተተከለች በለስ ነበረችው፥ ፍሬም ሊፈልግባት መጥቶ ምንም አላገኘም።
፯ የወይን እትክልት ሠራተኛውንም። እነሆ፥ ከዚህች በለስ ፍሬ ልፈልግ ሦስት ዓመት እየመጣሁ ምንም አላገኘሁም፤ ቍረጣት፤ ስለ ምን ደግሞ መሬቱን ታጐሳቍላለች? አለው።
፰ እርሱ ግን መልሶ። ጌታ ሆይ፥ ዙሪያዋን እስክኰተኩትላትና ፋንድያ እስካፈሰላት ድረስ በዚች ዓመት ደግሞ ተዋት።
፱ ወደ ፊትም ብታፈራ፥ ደኅና ነው፤ ያለዚያ ግን ትቈርጣታለህ አለው።
፲ በሰንበትም በአንድ ምኩራብ ያስተምር ነበር።
፲፩ እነሆም፥ ከአሥራ ሰምንት ዓመት ጀምሮ የድካም መንፈስ ያደረባት ሴት ነበረች፥ እርስዋም ጐባጣ ነበረች ቀንታም ልትቆም ከቶ አልተቻላትም።
፲፪ ኢየሱስም ባያት ጊዜ ጠራትና። አንቺ ሴት፥ ከድካምሽ ተፈትተሻል አላት፥ እጁንም ጫነባት፤
፲፫ ያን ጊዜም ቀጥ አለች፥ እግዚአብሔርንም አመሰገነች።
፲፬ የምኩራብ አለቃ ግን ኢየሱስ በሰንበት ስለ ፈወሰ ተቈጥቶ መለሰና ሕዝቡን። ሊሠራባቸው የሚገባ ስድስት ቀኖች አሉ፤ እንግዲህ በእነርሱ መጥታችሁ ተፈወሱ እንጂ በሰንበት አይደለም አለ።
፲፭ ጌታም መልሶ። እናንተ ግብዞች፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በሰንበት በሬውን ወይስ አህያውን ከግርግሙ ፈትቶ ውኃ ሊያጠጣው ይወስደው የለምን?

፲፮ ይህችም የአብርሃም ልጅ ሆና ከአሥራ ሰምንት ዓመት ጀምሮ ሰይጣን ያሰራት በሰንበት ቀን ከዚህ እሰራት ልትፈታ አይገባምን? አለው።
፲፯ ይህንም ሲናገር ሳለ የተቃወሙት ሁሉ አፈሩ፤ ከእርሱም በተደረገው ድንቅ ሁሉ ሕዝቡ ሁሉ ደሰ አላቸው።
፲፰ እርሱም። የእግዚአብሔር መንግሥት ምን ትመሰላለች፥ በምንስ አስመስላታለሁ?
፲፱ ሰው ወሰደ በአትክልቱ የጣላትን የሰናፍጭ ቅንጣት ትመሰላለች፤ አደገችም ታላቅ ዛፍም ሆነች፥ የሰማይ ወፎችም በቅርንጫፎችዋ ሰፈሩ አለ።
፳ ደግሞም፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት በምን አስመስላታለሁ?
፳፩ ሴት ወሰዳ ሁሉ እስኪቦካ ድረስ በሦስት መሰፈሪያ ዱቄት የሸሸገችውን እርሾ ትመሰላለች አለ።
፳፪ ወደ ኢየሩሳሌም ሲሄድ ከተማዎችንና መንደሮችን እያስተማረ ያልፍ ነበር።
፳፫ አንድ ሰውም። ጌታ ሆይ፥ የሚድኑ ጥቂቶች ናቸውን? አለው። እርሱም እንዲህ አላቸው።
፳፬ በጠበበው በር ለመግባት ተጋደሉ፤ እላችኋለሁና፥ ብዙዎች ሊገቡ ይፈልጋሉ አይችሉምም።
፳፭ ባለቤቱ ተነሥቶ በሩን ከቈለፈ በኋላ፥ እናንተ በውጭ ቆማችሁ። ጌታ ሆይ፥ ጌታ ሆይ፥ ክፈትልን እያላችሁ በሩን ልታንኳኩ ትጀምራላችሁ እርሱም መልሶ። ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም ይላችኋል።
፳፮ በዚያን ጊዜም። በፊትህ በላን ጠጣንም በአደባባያችንም አስተማርህ ልትሉ ትጀምራላችሁ፤
፳፯ እርሱም። እላችኋለሁ፥ ከወዴት እንደ ሆናችሁ አላውቃችሁም፤ ሁላችሁ ዓመፀኞች፥ ከእኔ ራቁ ይላችኋል።
፳፰ አብርሃምንና ይስሐቅን ያዕቆብንም ነቢያትንም ሁሉ በእግዚአብሔር መንግሥት ባያችሁ ጊዜ፥ እናንተ ግን ወደ ውጭ ተጥላችሁ ሰትቀሩ፥ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።
፳፱ ከምሥራቅና ከምዕራብም ከሰሜንና ከደቡብም ይመጣሉ፥ በእግዚአብሔርም መንግሥት በማዕድ ይቀመጣሉ።
፴ እነሆም፥ ከኋለኞች ፊተኞች የሚሆኑ አሉ፥ ከፊተኞችም ኋለኞች የሚሆኑ አሉ።
፴፩ በዚያን ሰዓት ከፈሪሳውያን አንዳንዱ ቀርበው። ሄሮድስ ሊገድልህ ይወዳልና ከዚህ ውጣና ሂድ አሉት።
፴፪ እንዲህም አላቸው። ሄዳችሁ ለዚያች ቀበሮ። እነሆ፥ ዛሬና ነገ አጋንንትን አወጣለሁ በሽተኞችንም እፈውሳለሁ፥ በሦስተኛውም ቀን እፈጸማለሁ በሉአት።
፴፫ ዳሩ ግን ነቢይ ከኢየሩሳሌም ውጭ ይጠፋ ዘንድ እይገባውምና ዛሬና ነገ ከነገ በሰቲያም ልሄድ ያስፈልገኛል።
፴፬ ኢየሩሳሌም፥ ኢየሩሳሌም፥ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርስዋ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶችዋን በክንፎችዋ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እስበሰብ ዘንድ ሰንት ጊዜ ወደድሁ፥ እናንተም አልወደዳችሁም።
፴፭ እነሆ፥ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። እላችኋለሁም፥ በጌታ ሰም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም።

፲፬

፩ በሰንበትም ከፈሪሳውያን አለቆች ወደ አንዱ ቤት እንጀራ ሊበላ በገባ ጊዜ እነርሱ ይጠባበቁት ነበር።
፪ እነሆም፥ ሆዱ የተነፋ ሰው በፊቱ ነበረ።
፫ ኢየሱስም መልሶ። በሰንበት መፈወስ ተፈቅዶአልን ወይስ አልተፈቀደም? ብሎ ለሕግ አዋቂዎችና ለፈሪሳውያን ተናገረ።
፬ እነርሱ ግን ዝም አሉ። ይዞም ፈወሰውና አሰናበተው።
፭ ከእናንተ አህያው ወይስ በሬው በጕድጓድ ቢወድቅ በሰንበት ወዲያው የማያወጣው ማን ነው? አላቸው።
፮ ሰለዚህ ነገርም ሊመልሱለት አልተቻላቸውም።
፯ የታደሙትንም የከበሬታ ሰፍራ እንደ መረጡ ተመልክቶ ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል።
፰ ማንም ለሰርግ ቢጠራህ በከበሬታ ሰፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና አንተን እርሱንም የጠራ መጥቶ።
፱ ለዚህ ሰፍራ ተውለት ይልሃል፥ በዚያን ጊዜም እያፈርህ በዝቅተኛው ሰፍራ ልትሆን ትጀምራለህ።
፲ ነገር ግን በተጠራህ ጊዜ፥ የጠራህ መጥቶ። ወዳጄ ሆይ፥ ወደ ላይ ውጣ እንዲልህ፥ ሂደህ በዝቅተኛው ሰፍራ ተቀመጥ፤ ያን ጊዜም ከአንተ ጋር በተቀመጡት ሁሉ ፊት ክብር ይሆንልሃል።
፲፩ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱንም የሚያዋርድ ከፍ ይላል።
፲፪ የጠራውንም ደግሞ እንዲህ አለው። ምሳ ወይም እራት ባደረግህ ጊዜ፥ እነርሱ ደግሞ በተራቸው ምናልባት እንዳይጠሩህ ብድራትም እንዳይመልሱልህ፥ ወዳጆችህንና ወንድሞችህን ዘመዶችህንም ባለ ጠጎች ጎረቤቶችህንም አትጥራ።
፲፫ ነገር ግን ግብዣ ባደረግህ ጊዜ ድሆችንና ጕንድሾችን አንካሶችንም ዕውሮችንም ጥራ፤
፲፬ የሚመልሱት ብድራት የላቸውምና ብፁዕ ትሆናለህ፤ በጻድቃን ትንሣኤ ይመለሰልሃልና።
፲፭ ከተቀመጡትም አንዱ ይህን ሰምቶ። በእግዚአብሔር መንግሥት እንጀራ የሚበላ ብፁዕ ነው አለው።
፲፮ እርሱ ግን እንዲህ አለው። አንድ ሰው ታላቅ እራት አድርጎ ብዙዎችን ጠራ፤
፲፯ በእራትም ሰዓት የታደሙትን። አሁን ተዘጋጅቶአልና ኑ እንዲላቸው ባሪያውን ላከ።
፲፰ ሁላቸውም በአንድነት ያመካኙ ጀመር። የፊተኛው። መሬት ገዝቼአለሁ ወጥቼም ላየው በግድ ያስፈልገኛል፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው።
፲፱ ሌላውም። አምስት ጥምድ በሬዎች ገዝቼአለሁ ልፈትናቸውም እሄዳለሁ፤ ይቅር እንድትለኝ እለምንሃለሁ አለው።
፳ ሌላውም። ሚስት አግብቼአለሁ ሰለዚህም ልመጣ አልችልም አለው።
፳፩ ባሪያውም ደርሶ ይህን ለጌታው ነገረው። በዚያን ጊዜ ባለቤቱ ተቆጥቶ ባሪያውን። ወደ ከተማ ጎዳናና ወደ ሰላች ፈጥነህ ውጣ ድሆችንና ጕንድሾችን አንካሶችንና ዕውሮችንም ወደዚህ አግባ አለው።
፳፪ ባሪያውም። ጌታ ሆይ፥ እንዳዘዝኸኝ ተደርጎአል፥ ገናም ሰፍራ አለ አለው።

፳፫ ጌታውም ባሪያውን። ቤቴ እንዲሞላ ወደ መንገድና ወደ ቅጥር ውጣና ይገቡ ዘንድ ግድ በላቸው፤
፳፬ እላችኋለሁና፥ ከታደሙት ከእነዚያ ሰዎች አንድ ሰንኳ እራቴን አይቀምሰም አለው።
፳፭ ብዙም ሕዝብ ከእርሱ ጋር ይሄዱ ነበር፥ ዘወር ብሎም እንዲህ አላቸው።
፳፮ ማንም ወደ እኔ የሚመጣ ቢኖር አባቱንና እናቱን ሚስቱንም ልጆቹንም ወንድሞቹንም እኅቶቹንም የራሱን ሕይወት ሰንኳ ሳይቀር ባይጠላ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
፳፯ ማንም መስቀሉን ተሸክሞ በኋላዬ የማይመጣ፥ ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
፳፰ ከእናንተ ግንብ ሊሠራ የሚወድ ለመደምደሚያ የሚበቃ ያለው እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ ከሳራውን የማይቈጥር ማን ነው?
፳፱ ያለዚያ መሠረቱን ቢመሠርት፥ ሊደመድመውም ቢያቅተው፥ ያዩት ሁሉ።
፴ ይህ ሰው ሊሠራ ጀምሮ ሊደመድመው አቃተው ብለው ሊዘብቱበት ይጀምራሉ።
፴፩ ወይም ሌላውን ንጉሥ በጦርነት ሊጋጠም የሚሄድ፥ ከሁለት እልፍ ጋር የሚመጣበትን በአንድ እልፍ ሊገናኝ የሚችል እንደ ሆነ አስቀድሞ ተቀምጦ የማያሰብ ንጉሥ ማን ነው?
፴፪ ባይሆንስ ሌላው ገና ሩቅ ሳለ መልክተኞች ልኮ ዕርቅ ይለምናል።
፴፫ እንግዲህ እንደዚሁ ማንም ከእናንተ ያለውን ሁሉ የማይተው ደቀ መዝሙሬ ሊሆን አይችልም።
፴፬ ጨው መልካም ነው፤ ጨው አልጫ ቢሆን ግን በምን ይጣፈጣል?
፴፭ ለምድር ቢሆን ለፍግ መቈለያም ቢሆን አይረባም፤ ወደ ውጭ ይጥሉታል። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይሰማ።

፲፭

፩ ቀራጮችና ኃጢአተኞችም ሁሉ ሊሰሙት ወደ እርሱ ይቀርቡ ነበር።
፪ ፈሪሳውያንና ጸሮችም። ይህስ ኃጢአተኞችን ይቀበላል ከእነርሱም ጋር ይበላል ብለው እርስ በርሳቸው እንጕራጕሩ።
፫ ይህንም ምሳሌ ነገራቸው እንዲህ ሲል።
፬ መቶ በግ ያለው ከእነርሱም አንዱ ቢጠፋ፥ ዘጠና ዘጠኙን በበረሃ ትቶ የጠፋውን እስኪያገኘው ድረስ ሊፈልገው የማይሄድ ከእናንተ ማን ነው?
፭ ባገኘውም ጊዜ ደስ ብሎት በጫንቃው ይሸከመዋል፤
፮ ወደ ቤትም በመጣ ጊዜ ወዳጆቹንና ጐረቤቶቹን በአንድነት ጠርቶ። የጠፋውን በጌን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላቸዋል።
፯ እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ ከማያስፈልጋቸው ከዘጠና ዘጠኝ ጻድቃን ይልቅ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በሰማይ ደስታ ይሆናል።
፰ ወይም አሥር ድሪም ያላት አንድ ድሪም ቢጠፋባት፥ መብራት አብርታ ቤትዋንም ጠርጋ እስክታገኘው ድረስ አጥብቃ የማትፈልግ ሴት ማን ናት?
፱ ባገኘችውም ጊዜ ወዳጆችዋንና ጐረቤቶችዋን በአንድነት ጠርታ። የጠፋውን ድሪሜን አግኝቼዋለሁና ከእኔ ጋር ደስ ይበላችሁ ትላቸዋለች።
፲ እላችኋለሁ፥ እንዲሁ ንስሐ በሚገባ በአንድ ኃጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።
፲፩ እንዲህም አለ። አንድ ሰው ሁለት ልጆች ነበሩት።
፲፪ ከእነርሱም ታናሹ አባቱን። አባቴ ሆይ፥ ከገንዘብህ የሚደርሰኝን ክፍል ስጠኝ አለው። ገንዘቡንም አካፈላቸው።
፲፫ ከጥቂት ቀንም በኋላ ታናሹ ልጅ ገንዘቡን ሁሉ ሰብስቦ ወደ ሩቅ አገር ሄደ፥ ከዚያም እያባከነ ገዘቡን በተነ።
፲፬ ሁሉንም ከከሰረ በኋላ በዚያች አገር ጽኑ ራብ ሆነ፥ እርሱም ይጨነቅ ጀመር።
፲፭ ሄዶም ከዚያች አገር ሰዎች ከአንዱ ጋር ተዳበለ፥ እርሱም እሪያ ሊያሰማራ ወደ ሜዳ ሰደደው።
፲፮ እሪያዎችም ከሚበሉት አሰር ሊጠግብ ይመኝ ነበር፥ የሚሰጠውም አልነበረም።
፲፯ ወደ ልቡም ተመልሶ እንዲህ አለ። እንጀራ የሚተርፋቸው የአባቴ ሞያተኞች ስንት ናቸው? እኔ ግን ከዚህ በራብ እጠፋለሁ።
፲፰ ተነሥቼም ወደ አባቴ እሄዳለሁና። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥
፲፱ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም፤ ከሞያተኞችህ እንደ አንዱ አድርገኝ እለዋለሁ።
፳ ተነሥቶም ወደ አባቱ መጣ። እርሱም ገና ሩቅ ሳለ አባቱ አየውና አዘነለት፥ ሮጦም አንገቱን አቀፈውና ሳመው።
፳፩ ልጁም። አባቴ ሆይ፥ በሰማይና በፊትህ በደልሁ፥ ወደ ፊትም ልጅህ ልባል አይገባኝም አለው።
፳፪ አባቱ ግን ባሪያዎቹን አለ። ፈጥናችሁ ከሁሉ የተሻለ ልብስ አምጡና አልብሱት፥ ለእጁ ቀለበት ለእግሩም ጫማ ስጡ፤
፳፫ የሰባውን ፊሪዳ አምጥታችሁ እረዱት፥ እንብላም ደስም ይበለን፤
፳፬ ይህ ልጄ ሞቶ ነበርና ደግሞም ሕያው ሆኖአል፤ ጠፍቶም ነበር ተገኝቶአልም። ደስም ይላቸው ጀመር።
፳፭ ታላቁ ልጁ በእርሻ ነበረ፤ መጥቶም ወደ ቤት በቀረበ ጊዜ የመስንቆና የዘፈን ድምፅ ሰማ፤
፳፮ ከብላቴናዎችም አንዱን ጠርቶ። ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ።
፳፯ እርሱም። ወንድምህ መጥቶአልና በደኅና ስላገኘው አባትህ የሰባውን ፊሪዳ አረደለት አለው።
፳፰ ተቈጣም ለገባም አልወደደም፤ አባቱም ወጥቶ ለመነው።
፳፱ እርሱ ግን መልሶ አባቱን። እነሆ፥ ይህን ያህል ዓመት እንደ ባሪያ ተገዝቼልሃለሁ ከትእዛዝህም ከቶ አልተላለፍሁም፤ ለእኔም ከወዳጆቼ ጋር ደስ እንዲለኝ አንድ ጥቦት ሰንኳ አልሰጠኸኝም፤
፴ ነገር ግን ገንዘብህን ከጋለሞቶች ጋር በልቶ ይህ ልጅህ በመጣ ጊዜ፥ የሰባውን ፊሪዳ አረድህለት አለው።
፴፩ እርሱ ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ ሁልጊዜ ከእኔ ጋር ነህ፥ ለእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው፤
፴፪ ደሩ ግን ይህ ወንድምህ ሞቶ ነበረ ሕያው ሰለ ሆነ ጠፍቶም ነበር ሰለ ተገኘ ደስ እንዲለን ፍሥሐም እንድናደርግ ይገባናል አለው።

፲፮

፩ ደግሞም ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ። መጋቢ የነበረው አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ በእርሱ ዘንድ። ይህ ሰው ያለህን ይበትናል ብለው ከሰሱት።
፪ ጠርቶም። ይህ የምሰማብህ ምንድር ነው? ወደ ፊት ለእኔ መጋቢ ልትሆን አትችልምና የመጋቢነትህን ሂሳብ አስረክበኝ አለው።
፫ መጋቢውም በልቡ። ጌታዬ መጋቢነቴን ከእኔ ይወስዳልና ምን ላድርግ? ለመቄፈር ኃይል የለኝም፥ መለመንም አፍራለሁ።
፬ ከመጋቢነቴ ብሻር በቤታቸው እንዲቀበሉኝ የማደርገውን አውቃለሁ አለ።
፭ የጌታውንም ባለ ዕዳዎች እያንዳንዳቸውን ጠርቶ የፊተኛውን። ለጌታዬ ምን ያህል ዕዳ አለብህ? አለው።
፮ እርሱም። መቶ ማድጋ ዘይት አለ። ደብዳቤህን እነካ ፈጥነህም ተቀምጠህ አምሳ ብለህ ጻፍ አለው።
፯ በኋላም ሌላውን። አንተስ ስንት ዕዳ አለብህ? አለው። እርሱም። መቶ ጫን ስንዴ አለ። ደብዳቤህን እነካ ሰማንያ ብለህም ጻፍ አለው።
፰ ጌታውም ዓመፀኛውን መጋቢ በልባምነት ስላደረገ አመሰገነው የዚህ ዓለም ልጆች ለትውልዳቸው ከብርሃን ልጆች ይልቅ ልባሞች ናቸውና።
፱ እኔም እላችኋለሁ፥ የዓመፃ ገንዘብ ሲያልቅ በዘላለም ቤቶች እንዲቀበሉአችሁ፥ በእርሱ ወዳጆችን ለራሳችሁ አድርጉ።
፲ ከሁሉ በሚያንስ የታመነ በብዙ ደግሞ የታመነ ነው፥ ከሁሉ በሚያንሰም የሚያምፅ በብዙ ደግሞ ዓመፀኛ ነው።
፲፩ እንግዲያስ በዓመፃ ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ እውነተኛውን ገንዘብ ማን አደራ ይሰጣችኋል?
፲፪ በሌላ ሰው ገንዘብ ካልታመናችሁ፥ የእናንተን ማን ይሰጣችኋል?
፲፫ ለሁለት ጌቶች መገዛት የሚቻለው ባርያ ማንም የለም፤ ወይም አንዱን ይጠላልና ሁለተኛውንም ይወዳል፥ ወይም ወደ አንዱ ይጠጋል ሁለተኛውንም ይንቃል። ለእግዚአብሔርና ለገንዘብ መገዛት አትችሉም።
፲፬ ገንዘብንም የሚወዱ ፈሪሳውያን ይህን ሁሉ ሰምተው ያፌዙበት ነበር።
፲፭ እንዲህም አላቸው። ራሳችሁን በሰው ፊት የምታጸድቁ እናንተ ናችሁ፥ ነገር ግን እግዚአብሔር ልባችሁን ያውቃል፤ በሰው ዘንድ የከበረ በእግዚአብሔር ፊት ርኩስት ነውና።
፲፮ ሕግና ነቢያት እስከ ዮሐንስ ነበሩ፤ ከዚያ ጀምሮ የእግዚአብሔር መንግሥት ይሰበካል፤ ሁሉም ወደ እርሷ በኃይል ይገቡባታል።
፲፯ ነገር ግን ከሕግ አንዲት ነጥብ ከምትወድቅ ሰማይና ምድር ሊያልፍ ይቀላል።
፲፰ ሚስቱንም የሚፈታ ሁሉ ሌላይቱንም የሚያገባ ያመነዝራል፥ ከባልዋም የተፈታችውን የሚያገባ ያመነዝራል።
፲፱ ቀይ ልብስና ቀጭን የተልባ እግር የለበሰ አንድ ባለ ጠጋ ሰው ነበረ፥ ዕለት ዕለትም እየተመቸው በደስታ ይኖር ነበር።
፳ አልዓዛርም የሚባል አንድ ድህ በቍስል ተወርሶ በደጁ ተኝቶ ነበር፥
፳፩ ከባለ ጠጋውም ማዕድ ከሚወድቀው ፍርፋሪ ሊጠግብ ይመኝ ነበር፤ ውሾች እንኳ መጥተው ቍስሎቹን ይልሱ ነበር።
፳፪ ድህውም ሞተ፥ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለ ጠጋው ደግሞ ሞተና ተቀበረ።
፳፫ በሲኦልም በሥቃይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ አልዓዛርንም በእቅፉ።
፳፬ እርሱም እየጮኸ። አብርሃም አባት ሆይ፥ ማረኝ፥ በዚህ ነበልባል እሣቀያለሁና የጣቱን ጫፍ በውኃ ነክሮ መላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ሰደድልኝ አለ።
፳፭ አብርሃም ግን። ልጄ ሆይ፥ አንተ በሕይወትህ ሳለህ መልካም እንደ ተቀበልህ አስብ አልዓዛርም እንዲሁ ክፉ፤ አሁን ግን እርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሣቀያለህ።
፳፮ ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።
፳፯ እርሱም። እንኪያስ፥ አባት ሆይ፥ ወደ አባቴ ቤት እንድትሰደው እለምንሃለሁ፤ አምስት ወንድሞች አሉኝና፤
፳፰ እነርሱ ደግሞ ወደዚህ ሥቃይ ስፍራ እንዳይመጡ ይመስክርላቸው አለ።
፳፱ አብርሃም ግን። ሙሴና ነቢያት አሉአቸው፤ እነርሱን ይሰሙ አለው።
፴ እርሱም። አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ አለ።
፴፩ ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ፥ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም አለው።

፲፯

፩ ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ። መሰናክል ግድ ሳይመጣ አይቀርም፥ ነገር ግን መሰናክሉን ለሚያመጣው ወዮለት፤
፪ ከእነዚህ ከታናናሾች አንዱን ከማሰናከል ይልቅ የወፍጮ ድንጋይ በአንገቱ ታስሮ ወደ ባሕር ቢጣል ይጠቅመው ነበር።
፫ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ። ወንድምህ ቢበድልህ ገሥጸው፥ ቢጸጸትም ይቅር በለው።
፬ በቀንም ሰባት ጊዜ እንኳ ቢበድልህ በቀንም ሰባት ጊዜ። ተጸጸትሁ እያለ ወደ አንተ ቢመለስ፥ ይቅር በለው።
፭ ሐዋርያትም ጌታን። እምነት ጨምርልን አሉት።
፮ ጌታም አለ። የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ፥ ይህን ሾላ። ተነቅለህ ወደ ባሕር ተተከል ብትሉት፥ ይታዘዝላችሁ ነበር።
፯ ከእናንተም የሚያርስ ወይም ከብትን የሚጠብቅ ባሪያ ያለው፥ ከእርሻ ሲመለስ። ወዲያው ቅረብና በማዕድ ተቀመጥ የሚለው ማን ነው?
፰ የምበላውን እራቴን አሰናዳልኝ፥ እስክበላና እስክጠጣ ድረስ ታጥቀህ አገልግለኝ፥ በኋላም አንተ ብላና ጠጣ የሚለው አይደለምን?
፱ ያንን ባሪያ ያዘዘውን ስላደረገ ያመሰግነዋልን?

፲ እንዲሁ እናንተ ደግሞ የታዘዛችሁትን ሁሉ ባደረጋችሁ ጊዜ። የማንጠቅም ባሪያዎች ነን፥ ልናደርገው የሚገባንን አድርገናል በሉ።
፲፩ ወደ ኢየሩሳሌምም ሲሄድ በገሊላና በሰማርያ መካከል አለፈ።
፲፪ ወደ አንዲት መንደርም ሲገባ በሩቅ የቆሙት አሥር ለምጻሞች ተገናኙት፤
፲፫ እነርሱም እየጮኹ። ኢየሱስ ሆይ፥ አቤቱ፥ ማረን አሉ።
፲፬ አይቶም። ሂዱ፥ ራሳችሁን ለካህናት አሳዩ አላቸው።
፲፭ እነሆም፥ ሲሄዱ ነጹ። ከእነርሱም አንዱ እንደ ተፈወሰ ባየ ጊዜ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን እያከበረ ተመለሰ፥
፲፮ እያመሰገነውም በእግሩ ፊት በግንባሩ ወደቀ፤ እርሱም ሳምራዊ ነበረ።
፲፯ ኢየሱስም መልሶ። አሥሩ አልነጹምን? ዘጠኙስ ወዴት አሉ?
፲፰ ከዚህ ከልዩ ወገን በቀር እግዚአብሔርን ሊያከብሩ የተመለሱ አልተገኙም አለ።
፲፱ እርሱንም። ተነሣና ሂድ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።
፳ ፈሪሳውያንም። የእግዚአብሔር መንግሥት መቼ ትመጣለች ብለው ቢጠይቁት፥ መልሶ። የእግዚአብሔር መንግሥት በመጠባበቅ አትመጣም፤
፳፩ ደግሞም። እንኋት በዚህ ወይም። እንኋት በዚያ አይሉአትም። እነሆ፥ የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላችሁ ናትና አላቸው።
፳፪ ለደቀ መዛሙርቱም እንዲህ አለ። ከሰው ልጅ ቀኖች አንዱን ልታዩ የምትመኙበት ወራት ይመጣል አታዩትምም።
፳፫ እነርሱም። እነሆ በዚህ፥ ወይም። እነሆ በዚያ ይሉአችኋል፤ አትሂዱ አትከተሉአቸውም።
፳፬ መብረቅ በርቆ ከሰማይ በታች ካለ ከአንድ አገር ከሰማይ በታች ወዳለው ወደ ሌላ አገር እንደሚያበራ፥ የሰው ልጅ በቀኑ እንዲህ ይሆናል።
፳፭ አስቀድሞ ግን ብዙ መከራ እንዲቀበል ከዚህም ትውልድ እንዲጣል ይገባዋል።
፳፮ በኖኅ ዘመንም እንደ ሆነ፥ በሰው ልጅ ዘመን ደግሞ እንዲሁ ይሆናል።
፳፯ ኖኅ ወደ መርከብ እስከ ገባበት ቀን ድረስ፥ ይበሉና ይጠጡ ያገቡና ይጋቡም ነበር፥ የጥፋት ውኃም መጣ ሁሉንም አጠፋ።
፳፰ እንዲሁ በሎጥ ዘመን እንደ ሆነ፤ ይበሉ ይጠጡም ይገዙም ይሸጡም ይተክሉም ቤትም ይሠሩ ነበር፤
፳፱ ሎጥ ከሰዶም በወጣበት ቀን ግን ከሰማይ እሳትና ዲን ዘነበ ሁሉንም አጠፋ።
፴ የሰው ልጅ በሚገለጥበት ቀን እንዲሁ ይሆናል።
፴፩ በዚያም ቀን በሰገነት ያለ በቤቱ ያለውን ዕቃ ሊወስድ አይውረድ፥ እንዲሁም በእርሻ ያለ ወደ ኋላው አይመለስ።
፴፪ የሎጥን ሚስት አስቡአት።
፴፫ ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም የሚያጠፋ ሁሉ በሕይወት ይጠብቃታል።
፴፬ እላችኋለሁ፥ በዚያች ሌሊት ሁለት ሰዎች በአንድ አልጋ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል።
፴፭ ሁለት ሴቶች በአንድ ወፍጮ ይፈጫሉ፤ አንዲቱ ትወሰዳለች ሁለተኛይቱም ትቀራለች።
፴፮ ሁለት ሰዎች በእርሻ ይሆናሉ፤ አንዱ ይወሰዳል ሁለተኛውም ይቀራል።
፴፯ መልሰውም። ጌታ ሆይ፥ ወዴት ነው? አሉት። እርሱም። ሥጋ ወዳለበት በዚያ አሞራዎች ይሰበሰባሉ አላቸው።

፲፰

፩ ሳይታክቱም ዘወትር ሊጸልዩ እንዲገባቸው የሚል ምሳሌን ነገራቸው፥
፪ እንዲህ ሲል። በአንዲት ከተማ እግዚአብሔርን የማይፈራ ሰውንም የማያፍር አንድ ዳኛ ነበረ።
፫ በዚያችም ከተማ አንዲት መበለት ነበረች፥ ወደ እርሱም እየመጣች። ከባላጋራዬ ፍረድልኝ ትለው ነበር።
፬ አያሌ ቀንም አልወደደም፤ ከዚህ በኋላ ግን በልቡ። ምንም እግዚአብሔርን ባልፈራ ሰውንም ባላፍር፥
፭ ይህች መበለት ስለምታደክመኝ ሁልጊዜም እየመጣች እንዳታውከኝ እፈርድላታለሁ አለ።
፮ ጌታም አለ። ዓመፀኛው ዳኛ ያለውን ሰሙ።
፯ እግዚአብሔር እኪያስ ቀንና ሌሊት ወደ እርሱ ለሚጮኹ ለሚታገሣቸውም ምርጦቹ አይፈርድላቸውምን?
፰ እላችኋለሁ፥ ፈጥኖ ይፈርድላቸዋል። ነገር ግን የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር እምነትን ያገኛ ይሆንን?
፱ ጻድቃን እንደ ሆኑ በራሳቸው ለሚታመኑና ሌሎቹን ሁሉ በጣም ለሚንቁ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፥
፲ እንዲህ ሲል። ሁለት ሰዎች ሊጸልዩ ወደ መቅደስ ወጡ፥ አንዱ ፈሪሳዊ ሁለተኛውም ቀራጭ።
፲፩ ፈሪሳዊም ቆሞ በልቡ ይህን ሲጸልይ። እግዚአብሔር ሆይ፥ እንደ ሌላ ሰው ሁሉ፥ ቀማኞችና ዓመፀኞች አመንዝሮችም፥ ወይም እንደዚህ ቀራጭ ሰላልሆንሁ አመሰግንሃለሁ፤
፲፪ በየሳምንቱ ሁለት ጊዜ እጦማለሁ፥ ከማገኘውም ሁሉ አሥራት አወጣለሁ አለ።
፲፫ ቀራጩ ግን በሩቅ ቆሞ ዓይኖቹን ወደ ሰማይ ሊያነሣ እንኳ አልወደደም፥ ነገር ግን። እምላክ ሆይ፥ እኔን ኃጢአተኛውን ማረኝ እያለ ደረቱን ይደቃ ነበር።
፲፬ እላችኋለሁ፥ ከዚያ ይልቅ ይህ ጻድቅ ሆኖ ወደ ቤቱ ተመለሰ፤ ራሱን ከፍ የሚያደርግ ሁሉ ይዋረዳልና፥ ራሱን ግን የሚያዋርድ ከፍ ይላል።
፲፭ እንዲዳሰሳቸውም ሕፃናትን ደግሞ ወደ እርሱ አመጡ፤ ደቀ መዛሙርቱም አይተው ገሠጹአቸው።
፲፮ ኢየሱስ ግን ሕፃናትን ወደ እርሱ ጠርቶ። ሕፃናት ወደ እኔ ይመጡ ዘንድ ተዉአቸው አትከልክሉአቸውም፤ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ እነዚህ ላሉት ናትና።
፲፯ እውነት እላችኋለሁ፥ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደ ሕፃን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባባትም አለ።
፲፰ ከአለቆችም አንዱ። ቸር መምህር፥ የዘላለምን ሕይወት እንድወርስ ምን ላድርግ? ብሎ ጠየቀው።
፲፱ ኢየሱስም። ስለ ምን ቸር ትለኛለህ? ከአንዱ ከእግዚአብሔር በቀር ቸር ማንም የለም።

፳ ትእዛዛቱን ታውቃለህ፥ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በሐሰት አትመስክር፥ አባትህንና እናትህን አክብር አለው።
፳፩ እርሱም። ይህን ሁሉ ከሕፃንናቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ አለ።
፳፪ ኢየሱስም ይህን ሰምቶ። አንዲት ገና ቀርታሃለች፤ ያለህን ሁሉ ሸጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መጥተህም ተከተለኝ አለው።
፳፫ እርሱ ግን ይህን ሰምቶ እጅግ ባለ ጠጋ ነበርና ብዙ አዘነ።
፳፬ ኢየሱስም ብዙ እንዳዘነ አይቶ። ገንዘብ ላላቸው ወደ እግዚአብሔር መንግሥት መግባት እንዴት ጭንቅ ይሆናል።
፳፭ ባለ ጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ይልቅ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ሊገባ ይቀላል አለ።
፳፮ የሰሙትም። እንግዲህ ማን ሊድን ይችላል? አሉ።
፳፯ እርሱ ግን። በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል አለ።
፳፰ ጴጥሮስም። እነሆ፥ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ አለ።
፳፱ እርሱም። እውነት እላችኋለሁ፥ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቤትን ወይም ወላጆችን ወይም ወንድሞችን ወይም ሚስትን ወይም ልጆችን የተወ፥
፴ በዚህ ዘመን ብዙ እጥፍ በሚመጣውም ዓለም የዘላለምን ሕይወት የማይቀበል ማንም የለም አላቸው።
፴፩ አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ አቅርቦ እንዲህ አላቸው። እነሆ፥ ወደ ኢየሩሳሌም እንወጣለን፥ ስለ ሰው ልጅም በነቢያት የተጻፈው ሁሉ ይፈጸማል።
፴፪ ለአሕዛብ አሳልፈው ይሰጡታልና፥ ይዘብቱበትማል ያንገላቱትማል ይተፉበትማል፤
፴፫ ከገረፉትም በኋላ ይገድሉታል፥ በሦስተኛውም ቀን ይነሣል።
፴፬ እነርሱም ከዚህ ነገር ምንም አላስተዋሉም፥ ይህም ቃል ተሰውሮባቸው ነበር፥ የተናገረውንም አላወቁም።
፴፭ ወደ ኢያሪኮም በቀረበ ጊዜ አንድ ዕውር እየለመነ በመንገድ ዳር ተቀምጦ ነበር።
፴፮ ሕዝብም ሲያልፍ ሰምቶ። ይህ ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀ።
፴፯ እነርሱም። የናዝሬቱ ኢየሱስ ያልፋል ብለው አወሩለት።
፴፰ እርሱም። የዳዊት ልጅ፥ ኢየሱስ ሆይ፥ ማረኝ እያለ ጮኸ።
፴፱ በስተ ፊት ይሄዱ የነበሩትም ዝም እንዲል ገሠጹት፤ እርሱ ግን። የዳዊት ልጅ ሆይ፥ ማረኝ እያለ አብዝቶ ጮኸ።
፵ ኢየሱስም ቆሞ ወደ እርሱ እንዲያመጡት አዘዘ። በቀረበም ጊዜ። ምን ላደርግልህ ትወዳለህ? ብሎ ጠየቀው።
፵፩ እርሱም። ጌታ ሆይ፥ አይ ዘንድ ነው አለው።
፵፪ ኢየሱስም። እይ፤ እምነትህ አድኖሃል አለው።
፵፫ በዚያን ጊዜም አየ፥ እግዚአብሔንም እያከበረ ተከተለው። ሕዝቡም ሁሉ አይተው እግዚአብሔርን አመሰገኑ።

፲፱

፩-፫ ኢየሱስንም የትኛው እንደ ሆነ ሊያይ ይፈልግ ነበር፤ ቁመቱም አጭር ነበረና ሰለ ሕዝቡ ብዛት አቃተው።
፬ በዚያችም መንገድ ያልፍ ዘንድ አለውና ያየው ዘንድ ወደ ፊት ሮጦ በአንድ ሾላ ላይ ወጣ።
፭ ኢየሱስም ወደዚያ ሰፍራ በደረሰ ጊዜ፥ አሻቅቦ አየና። ዘኬዎስ ሆይ፥ ዛሬ በቤትህ እውል ዘንድ ይገባኛልና ፈጥነህ ውረድ አለው።
፮ ፈጥኖም ወረደ በደስታም ተቀበለው።
፯ ሁሉም አይተው። ከኃጢአተኛ ሰው ጋር ሊውል ገባ ብለው አንጐራጐሩ።
፰ ዘኬዎስ ግን ቆሞ ጌታን። ጌታ ሆይ፥ ካለኝ ሁሉ እኩሌታውን ለድሆች እሰጣለሁ፤ ማንንም በሐሰት ከሰሼ እንደ ሆንሁ አራት እጥፍ እመልሳለሁ አለው።
፱ ኢየሱስም። እርሱ ደግሞ የአብርሃም ልጅ ነውና ዛሬ ለዚህ ቤት መዳን ሆኖለታል፤
፲ የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው።
፲፩ እነርሱም ይህን ሲሰሙ፥ ወደ ኢየሩሳሌም መቅረቡ ሰለ ሆነ የእግዚአብሔርም መንግሥት ፈጥኖ ሊገለጥ እንዳለው ሰለ መሰላቸው ምሳሌ ጭምር ተናገረ።
፲፪ ሰለዚህም እንዲህ አላቸው። አንድ መኰንን ለራሱ መንግሥትን ይዞ ሊመለስ ወደ ሩቅ አገር ሄደ።
፲፫ አሥር ባሪያዎችንም ጠርቶ አሥር ምናን ሰጣቸውና። እስክመጣ ድረስ ነግዱ አላቸው።
፲፬ የአገሩ ሰዎች ግን ይጠሉት ነበርና። ይህ በላያችን ሊነግሥ አንወድም ብለው በኋላው መልክተኞችን ላኩ።
፲፭ መንግሥትንም ይዞ በተመለሰ ጊዜ፥ ገንዘብ የሰጣቸውን እነዚህን ባሪያዎች ነግደው ምን ያህል እንዳተረፉ ያውቅ ዘንድ እንዲጠሩለት አዘዘ።
፲፮ የፊተኛውም ደርሶ። ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ አለው።
፲፯ እርሱም። መልካም፥ አንተ በጎ ባሪያ፥ በጥቂት የታመንህ ሰለ ሆንህ በአሥር ከተማዎች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ አለው።
፲፰ ሁለተኛውም መጥቶ። ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አምስት ምናን አተረፈ አለው።
፲፱ ይህንም ደግሞ። አንተም በአምስት ከተማዎች ላይ ሁን አለው።
፳ ሌላውም መጥቶ። ጌታ ሆይ፥ በጨርቅ ጠቅልዬ የጠበቅኋት ምናንህ እነሆ፤
፳፩ ፈርቼሃለሁና፥ ጨካኝ ሰው ሰለ ሆንህ፤ ያላኖርኸውን ትወሰዳለህ ያልዘራኸውንም ታጭዳለህ አለው።
፳፪ እርሱም። አንተ ክፉ ባሪያ፥ አፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ። እኔ ያላኖርሁትን የምወሰድና ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው እንደ ሆንሁ አወቅህ፤ ምን ነው ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ያልሰጠኸው?
፳፫ እኔም መጥቼ ከትርፉ ጋር እወሰደው ነበር አለው።
፳፬ በዚያም ቆመው የነበሩትን። ምናኑን ውሰዱበት አሥሩ ምናን ላለውም ሰጡት አላቸው።
፳፭ እነርሱም። ጌታ ሆይ፥ አሥር ምናን አለው አሉት።

፳፯ እላችኋለሁ፥ ላለው ሁሉ ይሰጠዋል፥ ከሌለው
ግን ያው ያለው ሰንኳ ይወሰድበታል።
፳፰ ነገር ግን እነዚያን በላያቸው ልነግሥ
ያልወደዱትን ጠላቶቼን ወደዚህ አምጡአቸው
በፊቴም እረዱአቸው።
፳፱ ይህንም ከተናገረ በኋላ፥ ወደ ኢየሩሳሌም ሲወጣ
ይቀድማቸው ነበር።
፴ ደብረ ዘይትም በሚባል ተራራ አጠገብ ወዳሉት
ወደ ቤተ ፋጌና ወደ ቢታንያ በቀረበ ጊዜ፥ ከደቀ
መዛሙርቱ ሁለቱን ላከና።
፴፩ በፊታችሁ ወዳለችው መንደር ሂዱ፥ ወደ
እርሷዋም ገብታችሁ ከሷው ማንም ገና ያልተቀመጠበት
ውርንጫ ታሰሮ ታገኛላችሁ፥ ፈትታችሁም አምጡት።
፴፪ ማንም። ስለ ምን ትፈቱታላችሁ? ብሎ
ቢጠይቃችሁ፥ እንዲሁ። ለጌታ ያሰፈልገዋል በሉ
አላቸው።
፴፫ የተላኩትም ሄደው እንዳላቸው አገኙ።
፴፬ እነርሱም ውርንጫውን ሲፈቱ ጌቶቹ።
ውርንጫውን ስለ ምን ትፈቱታላችሁ? አሉአቸውም
፴፭ እነርሱም። ለጌታ ያሰፈልገዋል አሉ።
፴፮ ወደ ኢየሱሰም አመጡት፥ በውርንጫውም ላይ
ልብሳቸውን ጭነው ኢየሱሰን አሰቀመጡት።
፴፯ ሲሄድም ልብሳቸውን በመንገድ ያነጥፉ ነበር።
፴፰ ወደ ደብረ ዘይት ቍልቍለትም አሁን በቀረበ
ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ሁላቸው ደስ እያላቸው
ተአምራትን ሁሉ ሰላዩ በታላቅ ድምፅ እግዚአብሔርን
ሊያመሰግኑ ጀምረው።
፴፱ በጌታ ሰም የሚመጣ ንጉሥ የተባረከ ነው፤
በሰማይ ሰላም በአርያምም ክብር አሉ።
፵ ከሕዝብም መካከል ከፈሪሳውያን አንዳንዱ።
መምህር ሆይ፥ ደቀ መዛሙርትህን ገሥጻቸው አሉት።
፵፩ መልሶም። እላችኋለሁ፥ እነዚህ ዝም ቢሉ
ድንጋዮች ይጮኻሉ አላቸው።
፵፪ ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት፥
፵፫ እንዲህ እያለ። ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ
ቀን አንቺሰ ሰንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ
ተሰውሮአል።
፵፬ ወራት ይመጣብሻልና፥ ጠላቶችሽም
ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም በየበኩሉም
ያሰጨንቁሻል፤
፵፭ አንቺንም በአንቺም ውሰጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን
ወደ ታች ይጥላሉ፥ በአንቺ ውሰጥም ድንጋይ በድንጋይ
ላይ አይተዉም፥ የመጐብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና።
፵፮ ወደ መቅደሰም ገብቶ በእርሱ የሚሸጡትን
የሚገዙትንም ያወጣ ጀመር፤
፵፯ እርሱም። ቤቴ የጸሎት ቤት ይሆናል ተብሎ
ተጽፎአል፤ እናንተ ግን የወንበዴዎች ዋሻ አደረጋችሁት
አላቸው።
፵፰ ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፤ ነገር
ግን የካህናት አለቆችና ጸፎች የሕዝቡ ታላላቆችም
ሊገድሉት ይፈልጉ ነበር፥
፵፱ የሚያደርጉበትንም አጡ፤ ሕዝቡ ሁሉ ሲሰሙት
ተጎጠልጥለውበት ነበርና።

፳

፩ አንድ ቀንም ሕዝቡን በመቅደስ ሲያስተምር
ወንጌልንም ሲሰብክላቸው፥ የካህናት አለቆችና ጸፎች
ከሸማግሌዎች ጋር ወደ እርሱ ቀረቡና።
፪ እስኪ ንገረን፤ እነዚህን በምን ሥልጣን ታደርጋለህ
ወይስ ይህን ሥልጣን የሰጠህ ማን ነው? ብለው
ተናገሩት።
፫ መልሶም። እኔ ደግሞ አንዲት ነገር
እጠይቃችኋለሁ፥ እናንተም ንገሩኝ፤
፬ የዮሐንስ ጥምቀት ከሰማይ ነበረችን ወይስ
ከሰው? አላቸው።
፭ እርስ በርሳቸውም ሲነጋገሩ። ከሰማይ ብንል። ስለ
ምን አላመናችሁበትም? ይለናል፤
፮ ከሰው ብንል ግን ሕዝቡ ሁሉ ይወግሩናል፤ ዮሐንስ
ነቢይ እንደ ነበረ ሁሉ ያምኑ ነበርና አሉ።
፯ መልሰውም። ከወዴት እንደ ሆነ እናውቅም አሉት።
፰ ኢየሱሰም። እኔም በምን ሥልጣን እነዚህን
እንዳደርግ አልነግራችሁም አላቸው።
፱ ይህንም ምሳሌ ለሕዝቡ ይላቸው ጀመር። አንድ
ሰው የወይን አትክልት ተከለ ለገበሬዎችም አከራይቶ
ለብዙ ዘመን ወደ ሌላ አገር ሄደ።
፲ በጊዜውም ከወይኑ አትክልት ፍሬ እንዲሰጡት
አንድ ባሪያ ወደ ገበሬዎች ላከ፤ ገበሬዎቹ ግን
ደበደቡት ባዶውንም ሰደዱት።
፲፩ ጨምሮም ሌላውን ባሪያ ላከ፤ እነርሱም ያን
ደግሞ ደበደቡት አዋርደውም ባዶውን ሰደዱት።
፲፪ ጨምሮም ሦስተኛውን ላከ፤ እነርሱም ይህን
ደግሞ አቍሰለው አወጡት።
፲፫ የወይኑም አትክልት ጌታ። ምን ላድርግ?
የምወደውን ልጄን እልካለሁ፤ ምናልባት እርሱን
አይተው ያፍሩታል አለ።
፲፬ ገበሬዎቹ ግን አይተውት እርስ በርሳቸው
ሲነጋገሩ። ወራሹ ይህ ነው፤ ርስቱ ለእኛ እንዲሆን ኑ
እንግደለው አሉ።
፲፭ ከወይኑም አትክልት ወደ ውጭ አውጥተው
ገደሉት። እንግዲህ የወይኑ አትክልት ጌታ ምን
ያደርጋቸዋል?
፲፮ ይመጣል እነዚህንም ገበሬዎች ያጠፋል፥
የወይኑንም አትክልት ለሌሎች ይሰጣል። ይህንም
በሰሙ ጊዜ። ይህስ አይሁን አሉ።
፲፯ እርሱ ግን ወደ እነርሱ ተመልክቶ። እንግዲህ።
ግንበኞች የናቁት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ
ተብሎ የተጻፈው ይህ ምንድር ነው?
፲፰ በዚያም ድንጋይ ላይ የሚወድቅ ሁሉ
ይቀጠቀጣል፤ የሚወድቅበትን ሁሉ ግን ይፈጨዋል
አለ።
፲፱ የካህናት አለቆችና ጸፎችም ይህን ምሳሌ
በእነርሱ ላይ እንደ ተናገረ አውቀው በዚያች ሰዓት
እጃቸውን ሊጭኑበት ፈለጉ ነገር ግን ሕዝቡን ፈሩ።
፳ ሲጠባበቁም ወደ ገዢ ግዛትና ሥልጣን አሳልፈው
እንዲሰጡት ጻድቃን መስለው በቃሉ የሚያጠምዱትን
ሸማቂዎች ሰደዱበት።
፳፩ ጠይቀውም። መምህር ሆይ፥ እውነትን
እንድትናገርና እንድታሰተምር ለሰው ፊትም እንዳታደላ
እናውቃለን፥ በእውነት የእግዚአብሔርን መንገድ
ታሰተምራለህ እንጂ፤
፳፪ ለቄሣር ግብር ልንሰጥ ተፈቅዶአልን? ወይስ
አልተፈቀደም? አሉት።

፲፫ እርሱ ግን ተንኰላቸውንም ተመልክቶ። ሰለ ምን ትፈትኑኛላችሁ? አንድ ዲናር አሳዩኝ፤
፲፬ መልኩ ጽሕፈቱስ የማን ነው? አላቸው። መልሰውም። የቄሣር ነው አሉት።
፲፭ እርሱም። እንኪያስ የቄሣርን ለቄሣር የእግዚአብሔርንም ለእግዚአብሔር አሰረክቡ አላቸው።
፲፮ በሕዝቡም ፊት በቃሉ ሊያጠምዱት አልቻሉም በመልሱም እየተደነቁ ዝም አሉ።
፲፯ ትንሣኤ ሙታንንም የሚክዱ ከሰዱቃውያን አንዳንዶቹ ቀርበው ጠየቁት፥
፲፰ እንዲህ ሲሉ። መምህር ሆይ፥ ሙሴ። ሚስት ያለችው የአንድ ሰው ወንድም ልጅ ሳይወልድ ቢሞት፥ ወንድሙ ሚስቱን አግብቶ ለወንድሙ ዘር ይተካ ብሎ ጻፈልን።
፲፱ እንግዲያስ ሰባት ወንድማማች ነበሩ፤ የፊተኛውም ሚስት አግብቶ ልጅ ሳይወልድ ሞተ፤
፳-፳፩ ከሁሉም በኋላ ሴቲቱ ደግሞ ሞተች።
፳፪ እንግዲህ ሰባቱ አግብተዋታልና ሴቲቱ በትንሣኤ ከእነርሱ ለማንኛቸው ሚስት ትሆናለች?
፳፫ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አላቸው። የዚህ ዓለም ልጆች ያገባሉ ይጋባሉም፥
፳፬ ያን ዓለምና ከሙታን ትንሣኤ ሊያገኙ የሚገባቸው እነዚያ ግን አያገቡም አይጋቡምም፥ እንደ መላእክት ናቸውና፥
፳፭ ሊሞቱም ወደ ፊት አይቻላቸውም፥ የትንሣኤም ልጆች ሰለ ሆኑ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው።
፳፮ ሙታን እንዲነሡ ግን ሙሴ ደግሞ በቍጥቋጦው ዘንድ ጌታን የአብርሃም አምላክ የይስሐቅም አምላክ የያዕቆብም አምላክ በማለቱ አስታወቀ፤
፳፯ ሁሉ ለእርሱ ሕያዋን ሰለ ሆኑ፥ የሕያዋን አምላክ ነው እንጂ የሙታን አይደለም።
፳፰ ከጻፎችም አንዳንዶቹ መልሰው። መምህር ሆይ፥ መልካም ተናገርህ አሉት።
፳፱ ወደ ፊትም አንድ ነገር ሰንኳ ሊጠይቁት አልደፈሩም።
፴ እንዲህም አላቸው። ክርስቶስ የዳዊት ልጅ ነው እንዴት ይላሉ?
፴፩-፴፪ እንግዲህ ዳዊት። ጌታ ብሎ ይጠራዋል፥ እንዴትሰ ልጁ ይሆናል?
፴፫ ሕዝቡም ሁሉ ሲሰሙ ደቀ መዛሙርቱን።
፴፬ ረጃጅም ልብሰ ለብሰው መዞር ከሚፈልጉ፥ በገበያም ሰላምታ፥ በምኩራብም የከበሬታ ወንበር፥ በምሳም የከበሬታ ሰፍራ ከሚወዱ ከጻፎች ተጠበቁ፤
፴፭ የመበለቶችን ቤት የሚበሉ ጸሎታቸውንም በማስረዘም የሚያመካኙ፥ እነዚህ የባሰ ፍርድ ይቀበላሉ አለ።

፳፩

፩ ዓይኑንም አንሥቶ መባቸውን በመዝገብ የሚጥሉ ባለ ጠጎችን አየ።
፪ አንዲትም ድህ መበለት ሁለት ሳንቲም በዚያ ስትጥል አየና።
፫ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህች ድህ መበለት ከሁሉ ይልቅ አብልጣ ጣለች፤
፬ እነዚህ ሁሉ ከትርፋቸው ወደ እግዚአብሔር መዝገብ ጥለዋልና፤ ይህች ግን ከጕድለትዋ የነበራትን ትዳርዋን ሁሉ ጣለች አለ።
፭ እንዳንዶቹም ሰለ መቅደስ በመልካም ድንጋይና በተሰጠው ሸልማት እንዳጌጠ ሲነጋገሩ። ይህማ የምታዩት ሁሉ፥
፮ ድንጋይ በድንጋይ ላይ ሳይፈርስ በዚህ የማይቀርበት ዘመን ይመጣል አለ።
፯ እነርሱም። መምህር ሆይ፥ እንግዲህ ይህ መቼ ይሆናል? ይህስ ይሆን ዘንድ እንዳለው ምልክቱ ምንድር ነው? ብለው ጠየቁት።
፰ እንዲህም አለ። እንዳትሰቱ ተጠንቀቁ፤ ብዙዎች። እኔ ነኝ፥ ዘመኑም ቀርቦአል እያሉ በስሜ ይመጣሉና፤ እነርሱን ተከትላችሁ አትሂዱ።
፱ ጦርንና ሁከትንም በሰማችሁ ጊዜ አትደንግጡ፤ ይህ አስቀድሞ ይሆን ዘንድ ግድ ነውና፥ ነገር ግን መጨረሻው ወዲያው አይሆንም።
፲ በዚያን ጊዜ እንዲህ አላቸው። ሕዝብ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣል፤
፲፩ ታላቅም የምድር መናወጥና በልዩ ልዩ ሰፍራ ቸነፈር ራብም ይሆናል፤ የሚያሰፈራም ነገር ከሰማይም ታላቅ ምልክት ይሆናል።
፲፪ ከዚህም ሁሉ በፊት እጆቸውን በላያችሁ ይጭናሉ ያሳድዱአችሁማል፤ ሰለ ሰሜም ወደ ምኩራብና ወደ ወኅኒ አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ወደ ነገሥታትና ወደ ገዥዎችም ይወሰዱአችኋል፤
፲፫ ይህም ለምስክርነት ይሆንላችኋል።
፲፬ ሰለዚህ እንዴት እንድትመልሱ አስቀድማችሁ እንዳታስቡ በልባችሁ አኑሩት፤
፲፭ ወደረኞቻችሁ ሁሉ ሊቃወሙና ሊከራከሩ የማይችሉትን አፍና ጥበብ እሰጣችኋለሁና።
፲፮ ወላጆችም ሰንኳ ወንድሞችም ዘመዶችም ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል፥ ከእናንተም አንዳንዱን ይገድላሉ፤
፲፯ በሁሉም ሰለ ሰሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ።
፲፰ ከራሳችሁም አንዲት ጠጕር ሰንኳ አትጠፋም፤
፲፱ በመታገሣችሁም ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ።
፳ ኢየሩሳሌም ግን በጭፍራ ተከባ ሰታዩ በዚያን ጊዜ ጥፋትዋ እንደ ቀረበ እወቁ።
፳፩ የዚያን ጊዜ በይሁዳ ያሉ ወደ ተራራዎች ይሸሹ፥ በመካከልዋም ያሉ ከእርስዋ ፈቀቅ ይበሉ፥ በገጠር ያሉም ወደ እርስዋ አይግቡ፤
፳፪ የተጻፈው ሁሉ እንዲፈጸም ይህ የበቀል ጊዜ ነውና።
፳፫ በዚያን ወራት ለእርጕዞችና ለሚያጠቡ ወዮላቸው፤ ታላቅ ችግር በምድር ላይ፥ በዚህም ሕዝብ ላይ ቍጣ ይሆናልና፤
፳፬ በሰይፍ ሰለትም ይወድቃሉ፤ ወደ አሕዛብ ሁሉም ይማረካሉ፤ የአሕዛብም ዘመን እስኪፈጸም ድረስ ኢየሩሳሌም በአሕዛብ የተረገጠች ትሆናለች።
፳፭ በፀሐይና በጨረቃም በከዋክብትም ምልክት ይሆናል፤ በምድር ላይም አሕዛብ ከባሕሩና ከሞገዱም ድምፅ የተነሣ እያመነቱ ይጨነቃሉ፤
፳፮ ሰዎችም ከፍርሃትና በዓለም የሚመጣበትን ከመጠበቅ የተነሣ ይደክማሉ፤ የሰማያት ኃይላት ይናወጣሉና።

፳፯ በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ በኃይልና በብዙ ክብር
በደመና ሲመጣ ያዩታል።
፳፰ ይህም ሊሆን ሲጀምር ቤዛችሁ ቀርቦአልና
አሻቅባችሁ ራሳችሁን አንሡ።
፳፱ ምሳሌንም ነገራቸው እንዲህ ሲል። በለሰንና
ዛፎችን ሁሉ እዩ፤
፴ ሲያቈጠቍጡ ተመልክታችሁ በጋ አሁን እንደ
ቀረበ ራሳችሁ ታውቃላችሁ።
፴፩ እንዲሁ ደግሞ እናንተ ይህ ሁሉ መሆኑን ስታዩ
የእግዚአብሔር መንግሥት እንደ ቀረበች እወቁ።
፴፪ እውነት እላችኋለሁ፥ ይህ ሁሉ እስኪሆን ድረስ
ይህ ትውልድ አያልፍም።
፴፫ ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም።
፴፬ ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በሰካር ሰለ
ትዳርም በማስብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት
እንዳይመጣባችሁ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤
፴፭ በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመጡ ሁሉ እንደ
ወጥመድ ይደርስባቸዋልና።
፴፮ እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ
ለማምለጥ፥ በሰው ልጅም ፊት ለመቆም እንድትችሉ
ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ።
፴፯ ዕለት ዕለትም በመቅደስ ያስተምር ነበር፥ ሌሊት
ግን ደብረ ዘይት ወደምትባል ተራራ ወጥቶ ያድር
ነበር።
፴፰ ሕዝቡም ሁሉ ይሰሙት ዘንድ ማልደው
በመቅደስ ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።

፳፪

፩ ቂጣም የሚባለው የቂጣ በዓል ቀረበ።
፪ የካህናት አለቆችና ጻፎችም እንዴት እንዲያጠፉት
ይፈልጉ ነበር፤ ሕዝቡን ይፈሩ ነበርና።
፫ ሰይጣንም ከአሥራ ሁለቱ ቍጥር አንዱ በነበረው
የአስቆሮቱ በሚባለው በይሁዳ ገባ፤
፬ ሄዶም እንዴት አሳልፎ እንዲሰጣቸው ከካህናት
አለቆችና ከመቅደስ አዛዦች ጋር ተነጋገረ።
፭ እነርሱም ደስ አላቸው፥ ገንዘብም ሊሰጡት
ተዋዋሉ።
፮ እሺም አለ፥ ሕዝብም በሌለበት አሳልፎ
እንዲሰጣቸው ምቹ ጊዜ ይፈልግ ነበር።
፯ ቂጣውንም ሊያርዱበት የሚገባው የቂጣ በዓል
ደረሰ፤
፰ ጴጥሮስንና ዮሐንስንም። ቂጣውን እንድንበላ
ሄዳችሁ አዘጋጁልን ብሎ ላካቸው።
፱ እነርሱም። ወዴት እናዘጋጅ ዘንድ ትወዳለህ?
አሉት።
፲ እርሱም አላቸው። እነሆ፥ ወደ ከተማ ስትገቡ
ማድጋ ውኃ የተሸከመ ሰው ይገናኛችኋል፤ ወደ
ሚገባበት ቤት ተከተሉት፤
፲፩ ለባለቤቱም። መምህሩ። ከደቀ መዛሙርቴ ጋር
ቂጣውን የምበላበት የእንግዳ ቤት ክፍል ወዴት ነው?
ይልሃል በሉት፤
፲፪ ያም በደርብ ላይ ያለውን የተነጠፈ ታላቅ አዳራሽ
ያሳያችኋል፤ በዚያም አስናዱልን።
፲፫ ሄደውም እንዳላቸው አገኙና ቂጣውን አስናዱ።
፲፬ ሰዓቱም በደረሰ ጊዜ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት
ጋር በማዕድ ተቀመጠ።
፲፭ እርሱም። ከመከራዬ በፊት ከእናንተ ጋር ይህን
ቂጣውን ልበላ እጅግ እመኝ ነበር፤
፲፮ እላችኋለሁና፥ በእግዚአብሔር መንግሥት
እስኪፈጸም ድረስ፥ ወደ ፊት ከዚህ አልበላም
አላቸው።
፲፯ ጽዋንም ተቀበለ አመሰግኖም። ይህን እንካችሁ
በመካከላችሁም ተካፈሉት፤
፲፰ እላችኋለሁና፥ የእግዚአብሔር መንግሥት
እስክትመጣ ድረስ ከአሁን ጀምሮ ከወይኑ ፍሬ
አልጠጣም አለ።
፲፱ እንጀራንም እንሥቶ አመሰገነ ቆርሶም ሰጣቸውና።
ስለ እናንተ የሚሰጠው ሥጋዬ ይህ ነው፤ ይህን
ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።
፳ እንዲሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን እንሥቶ እንዲህ
አለ። ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን
አዲስ ኪዳን ነው።
፳፩ ነገር ግን አሳልፎ የሚሰጠኝ እጅ እነሆ በማዕድ
ከእኔ ጋር ናት።
፳፪ የሰው ልጅስ እንደ ተወሰነው ይሄዳል፥ ነገር ግን
አልፎ ለሚሰጥበት ለዚያ ሰው ወዮለት።
፳፫ ከእነርሱም ይህን ሊያደርግ ያለው ማን እንደ
ሆነ እርስ በርሳቸው ይጠያየቁ ጀመር።
፳፬ ደግሞም ማናቸውም ታላቅ ሆኖ እንዲቈጠር
በመካከላቸው ክርክር ሆነ።
፳፭ እንዲህም አላቸው። የአሕዛብ ነገሥታት
ይገዙአቸዋል፥ በላያቸውም የሚሠለጥኑት ቸርነት
አድራጊዎች ይባላሉ።
፳፮ እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ
ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፥ የሚገዛም
እንደሚያገለግል ይሁን።
፳፯ በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው
ታላቅ ነው? የተቀመጠው አይደለምን? እኔ ግን
በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ።
፳፰ ነገር ግን እናንተ በፈተናዎቼ ከእኔ ጋር ጸንታችሁ
የኖራችሁ ናችሁ፤
፳፱-፴ ጌታም። ስምዖን ስምዖን ሆይ፥ እነሆ፥ ሰይጣን
እንደ ስንዴ ሊያበጥራችሁ ለመነ፤
፴፩ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለ አንተ
አማለድሁ፤ አንተም በተመለስህ ጊዜ ወንድሞችህን
አጽና አለ።
፴፪ እርሱም። ጌታ ሆይ፥ ወደ ወኅኒም ወደ ሞትም
ከአንተ ጋር ለመሄድ የተዘጋጀሁ ነኝ አለው።
፴፫ እርሱ ግን። ጴጥሮስ ሆይ፥ እልሃለሁ፥
እንዳታውቀኝ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዛሬ ዶሮ
አይጮኽም አለው።
፴፬ ደግሞም። ያለ ኮረጆና ያለ ከረጢት ያለ ጫማም
በላክኋችሁ ጊዜ፥ አንዳች ጐደለባችሁን? አላቸው።
እነርሱም። አንዳች እንኳ አሉ።
፴፭ እርሱም። አሁን ግን ኮረጆ ያለው ከእርሱ
ጋር ይውሰድ፥ ከረጢትም ያለው እንዲሁ፤ የሌለውም
ልብሱን ሸጦ ሰይፍ ይግዛ።
፴፮ እላችኋለሁና፥ ይህ። ከዓመፀኞች ጋር ተቈጠረ
ተብሎ የተጻፈው በእኔ ሊፈጸም ግድ ነው፤ እዋን፥ ስለ
እኔ የሚሆነው አሁን ይፈጸማልና አላቸው።
፴፯ እነርሱም። ጌታ ሆይ፥ እነሆ፥ በዚህ ሁለት
ሰይፎች አሉ አሉት። እርሱም። ይበቃል አላቸው።

፴፱ ወጥቶም እንደ ልማዱ ወደ ደብረ ዘይት ሄደ፤ ደቀ መዛሙርቱም ደግሞ ተከተሉት።
፵ ወደ ሰፍራውም ደርሶ። ወደ ፈተና እንዳትገቡ ጸልዩ አላቸው።
፵፩ ከእነርሱም የድንጋይ ውርወራ የሚያህል ራቀ፥ ተንበርክኮም። አባት ሆይ፥
፵፪ ብትፈቅድ ይህችን ጽዋ ከእኔ ውሰድ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ አይሁን የአንተ እንጂ እያለ ይጸልይ ነበር።
፵፫ ከሰማይም መጥቶ የሚያበረታ መልአክ ታየው።
፵፬ በፍርሃትም ሲጣጣር አጽንቶ ይጸልይ ነበር፤ ወዙም በምድር ላይ እንደሚወርድ እንደ ደም ነጠብጣብ ነበረ።
፵፭ ከጸሎትም ተነሥቶ ወደ ደቀ መዛሙርቱ መጣና ከኀዘን የተነሣ ተኝተው ሲያገኛቸው።
፵፮ ስለ ምን ትተኛላችሁ? ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተነሥታችሁ ጸልዩ አላቸው።
፵፯ ገናም ሲናገር እነሆ፥ ሰዎች መጡ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱም ይሁዳ የሚባለው ይቀድማቸው ነበር፥ ሊሳመውም ወደ ኢየሱስ ቀረበ።
፵፰ ኢየሱስ ግን። ይሁዳ ሆይ፥ በመሳም የሰውን ልጅ አሳልፈህ ትሰጣለህን? አለው።
፵፱ በዙሪያውም የነበሩት የሚሆነውን ባዩ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በሰይፍ እንምታቸውን? አሉት።
፶ ከእነርሱም አንዱ የሊቀ ካህናቱን ባሪያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠው።
፶፩ ኢየሱስ ግን መልሶ። ይህንስ ፍቀዱ አለ፤ ጆሮውንም ዳሰሶ ፈወሰው።
፶፪ ኢየሱስም ወደ እርሱ ለመጡበት ለካህናት አለቆችና ለመቅደስ አዛዦች ለሽማግሌዎችም። ወንበዴን እንደምትይዙ ሰይፍና ጐመድ ይዛችሁ ወጣችሁን?
፶፫ በመቅደስ ዕለት ዕለት ከእናንተ ጋር ሰሆን እጆቻችሁን አልዘረጋችሁብኝም፤ ይህ ግን ጊዜያችሁና የጨለማው ሥልጣን ነው አላቸው።
፶፬ ይዘውም ወሰዱት ወደ ሊቀ ካህናት ቤትም አገቡት፤ ጴጥሮስም ርቆ ይከተለው ነበር።
፶፭ በግቢ መካከልም እሳት አንድደው በአንድነት ተቀምጠው ሳሉ ጴጥሮስ በመካከላቸው ተቀመጠ።
፶፮ በብርሃኑም በኩል ተቀምጦ ሳለ አንዲት ገረድ አየችውና ትኩር ብላ። ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ አለች።
፶፯ እርሱ ግን። አንቺ ሴት፥ አላውቀውም ብሎ ካደ።
፶፰ ከጥቂት ጊዜም በኋላ ሌላው አይቶት። አንተ ደግሞ ከእነርሱ ወገን ነህ አለው። ጴጥሮስ ግን። አንተ ሰው፥ እኔ እይደለሁም አለ።
፶፱ አንድ ሰዓትም የሚያህል ቆይቶ ሌላው አሰረግጦ። እርሱ የገሊላ ሰው ነውና በእውነት ይህ ደግሞ ከእርሱ ጋር ነበረ አለ።
፷ ጴጥሮስ ግን። አንተ ሰው፥ የምትለውን አላውቀም አለ። ያን ጊዜም ገና ሲናገር ዶሮ ጮኸ።
፷፩ ጌታም ዘወር ብሎ ጴጥሮስን ተመለከተው፤ ጴጥሮስም። ዛሬ ዶሮ ሳይጮኽ ሦስት ጊዜ ትክደኛለህ እንዳለው የጌታ ቃል ትዝ አለው።
፷፪ ጴጥሮስም ወደ ውጭ ወጥቶ ምርር ብሎ አለቀሰ።
፷፫ ኢየሱስንም የያዙት ሰዎች ይዘብቱበትና ይደበድቡት ነበር፤
፷፬ ሸፍነውም ፊቱን ይመቱት ነበርና። በጥፊ የመታህ ማን ነው? ትንቢት ተናገር እያሉ ይጠይቁት ነበር።
፷፭ ሌላም ብዙ ነገር እየተሳደቡ በእርሱ ላይ ይናገሩ ነበር።
፷፮ በነጋም ጊዜ የሕዝቡ ሽማግሌዎችና የካህናት አለቆች ጸሮችም ተሰብስበው ወደ ሸንጎአቸው ወሰዱትና
፷፯ ክርስቶስ አንተ ነህን? ንገረን አሉት። እርሱ ግን እንዲህ አላቸው። ብነግራችሁ አታምኑም፤
፷፰ ብጠይቅም አትመልሱልኝም አትፈቱኝምም።
፷፱ ነገር ግን ከአሁን ጀምሮ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ኃይል ቀኝ ይቀመጣል።
፸ ሁላቸውም። እንግዲያስ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ ነህን? አሉት። እርሱም። እኔ እንደ ሆንሁ እናንተ ትላላችሁ አላቸው።
፸፩ እነርሱም። ራሳችን ከአፉ ሰምተናልና ከእንግዲህ ወዲህ ምን ምስክር ያስፈልገናል? አሉ።

፳፫

፩ ሁሉም በሞላው ተነሥተው ወደ ጲላጦስ ወሰዱትና።
፪ ይህ ሕዝባችንን ሲያጣምም ለቄሣርም ግብር እንዳይሰጥ ሲከለክል ደግሞም። እኔ ክርስቶስ ንጉሥ ነኝ ሲል አገኘነው ብለው ይከሱት ጀመር።
፫ ጲላጦስም። አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህን? ብሎ ጠየቀው። እርሱም መልሶ። አንተ አልህ አለው።
፬ ጲላጦስም ለካህናት አለቆችና ለሕዝቡ። በዚህ ሰው እንድ በደል ሰንኳ አላገኘሁበትም አለ።
፭ እነርሱ ግን እጽንተው። ከገሊላ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ በይሁዳ ሁሉ እያስተማረ ሕዝቡን ያውካል አሉ።
፮ ጲላጦስ ግን። ገሊላ ሲሉ በሰማ ጊዜ። የገሊላ ሰው ነውን? ብሎ ጠየቀ፤
፯ ከሄሮድስም ግዛት እንደ ሆነ ባወቀ ጊዜ ወደ ሄሮድስ ሰደደው፤ እርሱ ደግሞ በዚያ ጊዜ በኢየሩሳሌም ነበረና።
፰ ሄሮድስም ኢየሱስን ባየው ጊዜ እጅግ ደስ አለው፤ ስለ እርሱ ስለ ሰማ ከብዙ ጊዜ ጀምሮ ሊያየው ይመኝ ነበርና፥ ምልክትም ሲያደርግ ሊያይ ተሰፋ ያደርግ ነበር።
፱ በብዙ ቃልም ጠየቀው፤ እርሱ ግን አንድ ሰንኳ አልመለሰለትም።
፲ የካህናት አለቆችና ጸሮችም አጽንተው ሲከሱት ቆመው ነበር።
፲፩ ሄሮድስም ከሠራዊቱ ጋር ናቀው ዘበተበትም፥ የጌጥ ልብስም አልብሶ ወደ ጲላጦስ መልሶ ሰደደው።
፲፪ ሄሮድስና ጲላጦስም በዚያን ቀን እርስ በርሳቸው ወዳጆች ሆኑ፥ ቀድሞ በመካከላቸው ጥል ነበረና።
፲፫ ጲላጦስም፥ የካህናትን አለቆችና መኳንንትን ሕዝቡንም በአንድነት ጠርቶ እንዲህ አላቸው።
፲፬ ሕዝቡን ያጣምማል ብላችሁ ይህን ሰው ወደ እኔ አመጣችሁት፤ እነሆም፥ በፊታችሁ መርምሬ ከምትከሱበት ነገር አንድ በደል ሰንኳ በዚህ ሰው አላገኘሁበትም።
፲፭ ሄሮድስም ደግሞ ምንም አላገኘም፤ ወደ እኛ መልሶታልና፤ እነሆም፥ ለሞት የሚያደርሰው ምንም አላደረገም፤

፲፭-፲፰ ሁላቸውም በእንድነት። ይህን አሰወግድ፥ በርባንንም ፍታልን እያሉ ጮኹ፤
፲፱ እርሱም ሁከትን በከተማ አንሥቶ ሰውን ሰለ ገደለ በወኅኒ ታስሮ ነበር።
፳ ጲላጦስም ኢየሱስን ሊፈታ ወድዶ ዳግመኛ ተናገራቸው፤
፳፩ ነገር ግን እነርሱ። ሰቀለው ሰቀለው እያሉ ይጮኹ ነበር።
፳፪ ሦስተኛም። ምን ነው? ያደረገውስ ክፋት ምንድር ነው? ለሞት የሚያደርስው በደል አላገኘሁበትም፤ ሰለዚህ ቀጥቼ እፈታዋለሁ አላቸው።
፳፫ እነርሱ ግን እንዲሰቀል በታላቅ ድምፅ አጽንተው ለመኑት። የእነርሱ ጩኸትና የካህናት አለቆችም ቃል በረታ።
፳፬ ጲላጦስም ልመናቸው እንዲሆንላቸው ፈረደበት።
፳፭ ያንን የለመኑትንም፥ ሰለ ሁከት ሰውንም ሰለ መግደል በወኅኒ ታስሮ የነበረውን አሰፈታላቸው፥ ኢየሱስን ግን ለፈቃዳቸው አሳልፎ ሰጠው።
፳፮ በወሰዱትም ጊዜ ሰምዖን የተባለ የቀሬናን ሰው ከገጠር ሲመጣ ይዘው ከኢየሱስ በኋላ መሰቀልን እንዲሸከም ጫኑበት።
፳፯ ዋይ ዋይ ከሚሉና ሙሾ ከሚያወጡ ሴቶችና ከሕዝቡ እጅግ ብዙዎች ተከተሉት።
፳፰-፴ በዚያን ጊዜ ተራራዎችን። በላያችን ውደቁ፥ ኮረብቶችንም። ሰውሩን ይሉ ዘንድ ይጀምራሉ፤
፴፩ በእርጥብ እንጨት እንዲህ የሚያደርጉ ከሆኑ፥ በደረቀውስ እንዴት ይሆን?
፴፪ ሌሎችንም ሁለት ክፉ አድራጊዎች ደግሞ ከእርሱ ጋር ይገድሉ ዘንድ ወሰዱ።
፴፫ ቀራንዮም ወደሚባል ሰፍራ በደረሱ ጊዜ፥ በዚያ እርሱን ክፉ አድራጊዎቹንም አንዱን በቀኝ ሁለተኛውንም በግራ ሰቀሉ።
፴፬ ኢየሱስም። አባት ሆይ፥ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው አለ። ልብሱንም ተካፍለው ዕጣ ተጣጣሉበት።
፴፭ ሕዝቡም ቆመው ይመለከቱ ነበር። መኳንንቱም ደግሞ። ሌሎችን አዳነ፤ እርሱ በእግዚአብሔር የተመረጠው ክርስቶስ ከሆነ፥ ራሱን ያድን እያሉ ያፌዙበት ነበር።
፴፮ ጭፍሮችም ደግሞ ወደ እርሱ ቀርበው ሆምጣጤም እምጥተው።
፴፯ እንተስ የአሁድ ንጉሥ ከሆንህ፥ ራስህን አድን እያሉ ይዘብቱበት ነበር።
፴፰ ይህ የአይሁድ ንጉሥ ነው ተብሎ በግሪክና በሮማይስጥ በዕብራይስጥም ፊደል የተጻፈ ጽሕፈት ደግሞ በእርሱ ላይ ነበረ።
፴፱ ከተሰቀሉት ከክፉ አድራጊዎቹም አንዱ። አንተስ ክርስቶስ አይደለህምን? ራስህንም እኛንም አድን ብሎ ሰደበው።
፵ ሁለተኛው ግን መልሶ። አንተ እንደዚህ ባለ ፍርድ ሳለህ እግዚአብሔርን ከቶ አትፈራውምን?
፵፩ ሰለ አደረግነውም የሚገባንን እንቀበላለንና በእኛስ እውነተኛ ፍርድ ነው፤ ይህ ግን ምንም ክፋት አላደረገም ብሎ ገሠጸው።
፵፪ ኢየሱስንም። ጌታ ሆይ፥ በመንግሥትህ በመጣህ ጊዜ አሰበኝ አለው።
፵፫ ኢየሱስም። እውነት እልሃለሁ፥ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ አለው።
፵፬ ሰድስት ሰዓትም ያህል ነበረ፥ ጨለማም እስከ ዘጠኝ ሰዓት በምድር ሁሉ ላይ ሆነ፥ ፀሐይም ጨለመ፥
፵፭ የቤተ መቅደስም መጋረጃ ከመካከሉ ተቀደደ።
፵፮ ኢየሱስም በታላቅ ድምፅ ጮኾ። አባት ሆይ፥ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጣለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።
፵፯ የመቶ አለቃውም የሆነውን ነገር ባየ ጊዜ። ይህ ሰው በእውነት ጻድቅ ነበረ ብሎ እግዚአብሔርን አከበረ።
፵፰ ይህንም ለማየት ተከማችተው የነበሩ ሕዝብ ሁሉ፥ የሆነውን ባዩ ጊዜ፥ ደረታቸውን እየደቁ ተመለሱ።
፵፱ የሚያውቁቱ ግን ሁሉ ከገሊላ የተከተሉት ሴቶችም ይህን እያዩ በሩቅ ቆመው ነበር።
፶ እነሆም፥ በጎና ጻድቅ ሰው የሸንጎ አማካሪም የሆነ ዮሴፍ የሚባል ሰው ነበረ፤
፶፩ ይህም በምክራቸውና በሥራቸው አልተባበረም ነበር፤ አርማትያሰም ከምትባል ከአይሁድ ከተማ ሆኖ እርሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንግሥት ይጠባበቅ ነበር።
፶፪ ይኸውም ወደ ጲላጦስ ቀርቦ የኢየሱስን ሥጋ ለመነው፤
፶፫ አውርዶም በተልባ እግር ልብሰ ከፈነው፥ ማንም ገና ባልተቀበረበት ከዓለትም በተወቀረ መቃብር አኖረው።
፶፬ የመዘጋጀት ቀንም ነበረ፤ ሰንበትም ሊጀምር ነበረ።
፶፭ ከገሊላም ከእርሱ ጋር የመጡት ሴቶች ተከትለው መቃብሩን ሥጋውንም እንዴት እንዳኖሩት አዩ።
፶፮ ተመልሰውም ሽቱና ቅባት አዘጋጁ። በሰንበትም እንደ ትእዛዙ ዐረፉ።

፳፬

፩ ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ።
፪ ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፥
፫ ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም።
፬ እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፥ እነሆ፥ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤
፭ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፥ እንዲህ አሉአቸው። ሕያውን ከሙታን መካከል ሰለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም።
፮-፯ ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ።
፲፩ ይህም ቃል ቅዠት መሰሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም።
፲፪ ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ መቃብር ሮጠ፤ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር ልብሰን ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ።

፲፫ እነሆም፥ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያ ቀን ከኢየሩሳሌም ሰድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር፤
፲፬ ስለዚህም ሰለ ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር።
፲፭ ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤
፲፮ ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።
፲፯ እርሱም። እየጠወለጋችሁ ሰትሄዱ፥ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው? አላቸው።
፲፰ ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ። አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀናች በዚያ የሆነውን ነገር አታውቅምን? አለው።
፲፱ እርሱም። ይህ ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱም እንዲህ አሉት። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ሰለ ነበረው ሰለ ናዝሬቱ ሰለ ኢየሱስ፤
፳ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው።
፳፩ እኛ ግን እሰራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተሰፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።
፳፪ ደግሞም ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አሰገረሙን፤
፳፫ ሥጋውንም ባጡ ጊዜ። ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር።
፳፬ ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፥ እርሱን ግን አላዩትም።
፳፭ እርሱም። እናንተ የማታስተውሉ፥ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤
፳፮ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው።
፳፯ ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ሰለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።
፳፰ ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፥ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው።
፳፱ እነርሱ። ከእኛ ጋር እደር፥ ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ።
፴ ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን እንሥቶ ባረከው፥ ቈርሶም ሰጣቸው፤
፴፩ ዓይናቸውም ተከፈተ፥ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ።
፴፪ እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ።
፴፫-፴፭ እነርሱም በመንገድ የሆነውን እንጀራውንም በቈረሰ ጊዜ እንዴት እንደ ታወቀላቸው ተረኩላቸው።
፴፮ ይህንም ሲነጋገሩ ኢየሱስ ራሱ በመካከላቸው ቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።
፴፯ ነገር ግን ደነገጡና ፈሩ መንፈስም ያዩ መሰላቸው።
፴፰ እርሱም። ሰለ ምን ትደነግጣላችሁ? ሰለ ምንስ አሳብ በልባችሁ ይነሣል?
፴፱ እኔ ራሴ እንደ ሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን እዩ፤ በእኔ እንደምታዩት፥ መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳስሳችሁ እዩ አላቸው።
፵ ይህንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው።
፵፩ እነርሱም ከደስታ የተነሣ ገና ሰላላመኑ ሲደነቁ ሳሉ። በዚህ አንዳች የሚበላ አላችሁን? አላቸው።
፵፪ እነርሱም ከተጠበሰ ዓሣ አንድ ቁራጭ፥ ከማር ወለላም ሰጡት፤
፵፫ ተቀብሎም በፊታቸው በላ።
፵፬ እርሱም። ከእናንተ ጋር ሳለሁ በሙሴ ሕግና በነቢያት በመዝሙራትም ሰለ እኔ የተጻፈው ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ይገባል ብዬ የነገርኋችሁ ቃሌ ይህ ነው አላቸው።
፵፭ በዚያን ጊዜም መጻሕፍትን ያሰተውሉ ዘንድ አእምሮአቸውን ከፈተላቸው፤
፵፮ እንዲህም አላቸው። ክርስቶስ መከራ ይቀበላል በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ይነሣል፥
፵፯ በሰሙም ንሰሐና የኃጢአት ሰርየት ከኢየሩሳሌም ጀምሮ በአሕዛብ ሁሉ ይሰበካል ተብሎ እንዲሁ ተጽፎአል።
፵፰ እናንተም ለዚህ ምስክሮች ናችሁ።
፵፱ እነሆም፥ አባቴ የሰጠውን ተሰፋ እኔ እልክላችኋለሁ፤ እናንተ ግን ከላይ ኃይል እሰክትለብሱ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ።
፶ እሰከ ቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አነሥቶ ባረካቸው።
፶፩ ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ።
፶፪ እነርሱም፤ ሰገዱለትና በብዙ ደስታ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥
፶፫ ዘወትርም እግዚአብሔርን እያመሰገኑና እየባረኩ በመቅደስ ኖሩ።

የዮሐንስ ወንጌል

፩ በመጀመሪያው ቃል ነበረ፥ ቃልም በእግዚአብሔር
ዘንድ ነበረ፥ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ።
፪ ይህ በመጀመሪያው በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ።
፫ ሁሉ በእርሱ ሆነ፥ ከሆነውም አንዳች ሰንኳ ያለ
እርሱ አልሆነም።
፬ በእርሱ ሕይወት ነበረች፥ ሕይወትም የሰው ብርሃን
ነበረች።
፭ ብርሃንም በጨለማ ይበራል፥ ጨለማም
አላሸነፈውም።
፮ ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው ዮሐንስ የሚባል
አንድ ሰው ነበረ፤
፯ ሁሉ በእርሱ በኩል እንዲያምኑ ይህ ስለ ብርሃን
ይመሰክር ዘንድ ለምስክር መጣ።
፰ ስለ ብርሃን ሊመሰክር መጣ እንጂ፥ እርሱ ብርሃን
አልነበረም።
፱ ለሰው ሁሉ የሚያበራው እውነተኛው ብርሃን ወደ
ዓለም ይመጣ ነበር።
፲ በዓለም ነበረ፥ ዓለሙም በእርሱ ሆነ፥ ዓለሙም
አላወቀውም።
፲፩ የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም
አልተቀበሉትም።
፲፪ ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በሰሙ ለሚያምኑት
ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ
ሥልጣንን ሰጣቸው፤
፲፫ እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ
ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ
አልተወለዱም።
፲፬ ቃልም ሥጋ ሆነ፤ ጸጋንና እውነትንም ተመልቶ
በእኛ አደረ፥ አንድ ልጅም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው
ክብር የሆነው ክብሩን አየን።
፲፭ ዮሐንስ ስለ እርሱ መሰከረ እንዲህም ብሎ ጮኸ።
ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ከእኔ በፊት ነበረና ከእኔ
ይልቅ የከበረ ሆኖአል፤ ስለ እርሱ ያልሁት ይህ ነበረ።
፲፮ እኛ ሁላችን ከሙላቱ ተቀብለን በጸጋ ላይ ጸጋ
ተሰጥቶናልና ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበርና፤
፲፯ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።
፲፰ መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድ ሰንኳ
የለም፤ በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጁ እርሱ ተረከው።
፲፱ አይሁድም። አንተ ማን ነህ? ብለው ይጠይቁት
ዘንድ ከኢየሩሳሌም ካህናትንና ሌዋውያንን በላኩበት
ጊዜ፥ የዮሐንስ ምስክርነት ይህ ነው።
፳ መሰከረም አልካደምም፤ እኔ ክርስቶስ
አይደለሁም ብሎ መሰከረ።
፳፩ እንኪያስ ማን ነህ? ኤልያስ ነህን? ብለው
ጠየቁት። አይደለሁም አለ። ነቢዩ ነህን? አይደለሁም
ብሎ መለሰ።
፳፪ እንኪያስ። ማን ነህ? ለላኩን መልስ እንድንሰጥ፤
ስለራስህ ምን ትላለህ? አሉት።
፳፫ እርሱም። ነቢዩ ኢሳይያስ እንዳለ። የጌታን
መንገድ አቅኑ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው
ድምፅ እኔ ነኝ አለ።
፳፬-፳፭ ዮሐንስ መልሶ። እኔ በውኃ አጠምቃለሁ፤ ዳሩ
ግን እናንተ የማታውቁት በመካከላችሁ ቆሞአል፤
፳፮ እኔ የጫማውን ጠፍር ልፈታ የማይገባኝ፥ ከእኔ
በኋላ የሚመጣው ከእኔ ይልቅ የሚከብር ይህ ነው
አላቸው።
፳፰ ይህ ነገር ዮሐንስ ያጠምቅበት በነበረው
በዮርዳኖስ ማዶ በቢታንያ በቤተ ራባ ሆነ።
፳፱ በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ
አይቶ እንዲህ አለ። እነሆ የዓለምን ኃጢአት
የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ።
፴ እንድ ሰው ከእኔ በኋላ ይመጣል፥ ከእኔም በፊት
ነበርና ከእኔ ይልቅ የከበረ ሆኖአል ብዬ ስለ እርሱ
ያልሁት ይህ ነው።
፴፩ እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን ለእስራኤል
ይገለጥ ዘንድ ስለዚህ በውኃ እያጠመቅሁ እኔ
መጣሁ።
፴፪ ዮሐንስም እንዲህ ብሎ መሰከረ። መንፈስ
ከሰማይ እንደ ርግብ ሆኖ ሲወርድ አየሁ፤ በእርሱ
ላይም ኖረ።
፴፫ እኔም አላውቀውም ነበር፥ ዳሩ ግን በውኃ
አጠምቅ ዘንድ የላከኝ እርሱ። መንፈስ ሲወርድበትና
ሲኖርበት የምታየው፥ በመንፈስ ቅዱስ የሚያጠምቅ
እርሱ ነው አለኝ።
፴፬ እኔም አይቻለሁ እርሱም የእግዚአብሔር ልጅ
እንደ ሆነ መሰክሬአለሁ።
፴፭ በነገው ደግሞ ዮሐንስ ከደቀ መዛሙርቱም
ሁለት ቆመው ነበር፥
፴፮ ኢየሱስም ሲሄድ ተመልክቶ። እነሆ
የእግዚአብሔር በግ አለ።
፴፯ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሲናገር ሰምተው
ኢየሱስን ተከተሉት።
፴፰-፴፱ መጥታችሁ እዩ አላቸው። መጥተው
የሚኖርበትን አዩ፥ በዚያም ቀን በእርሱ ዘንድ ዋሉ፤
አሥር ሰዓት ያህል ነበረ።
፵ ከዮሐንስ ዘንድ ሰምተው ከተከተሉት ከሁለቱ
አንዱ የስምዖን ጴጥሮስ ወንድም እንድርያስ ነበረ።
፵፩ እርሱ አስቀድሞ የራሱን ወንድም ሰምዖንን
አገኘውና። መሢሕን አግኝተናል አለው፤ ትርጓሜውም
ክርስቶስ ማለት ነው።
፵፪ ወደ ኢየሱስም አመጣው። ኢየሱስም ተመልክቶ።
አንተ የዮና ልጅ ስምዖን ነህ፤ አንተ ኬፋ ትባላለህ
አለው፤ ትርጓሜው ጴጥሮስ ማለት ነው።
፵፫ በነገው ኢየሱስ ወደ ገሊላ ሊወጣ ወደደ፥
ፊልጶስንም አገኘና። ተከተለኝ አለው።
፵፬ ፊልጶስም ከእንድርያስና ከጴጥሮስ ከተማ ከቤተ
ሳይዳ ነበረ።
፵፭ ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ። ሙሴ በሕግ
ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን
ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው።
፵፮ ናትናኤልም። ከናዝሬት መልካም ነገር ሊወጣ
ይችላልን? አለው። ፊልጶስ። መጥተህ እይ አለው።
፵፯ ኢየሱስ ናትናኤልን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ ስለ
እርሱ። ተንኰል የሌለበት በእውነት የእስራኤል ሰው
እነሆ አለ።
፵፰ ናትናኤልም። ከወዴት ታውቀኛለህ? አለው።
ኢየሱስም መልሶ። ፊልጶስ ሳይጠራህ፥ ከበለስ በታች
ሳለህ፥ አየሁህ አለው።
፵፱ ናትናኤልም መልሶ። መምህር ሆይ፥ አንተ
የእግዚአብሔር ልጅ ነህ፤ አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ
አለው።

፶፩ ኢየሱስም መልሶ። ከበለስ በታች እየሁህ ሰላልሁህ አመንህን? ከዚህ የሚበልጥ ነገር ታያለህ አለው።
፶፪ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይ ሲከፈት የእግዚአብሔርም መላእክት በሰው ልጅ ላይ ሲወጡና ሲወርዱ ታያላችሁ አለው።

፪

፩ በሦስተኛውም ቀን በገሊላ ቃና ሰርግ ነበረ፥ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤
፪ ኢየሱስም ደግሞ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሰርጉ ታደሙ።
፫ የወይን ጠጅም ባለቀ ጊዜ የኢየሱስ እናት። የወይን ጠጅ እኮ የላቸውም አለችው።
፬ ኢየሱስም። አንቺ ሴት፥ ከአንቺ ጋር ምን አለኝ? ጊዜዬ ገና አልደረሰም አላት።
፭ እናቱም ለአገልጋዮቹ። የሚላችሁን ሁሉ አድርጉ አለቻቸው።
፮ አይሁድም እንደሚያደርጉት የማንጻት ልማድ ሰድስት የድንጋይ ጋኖች በዚያ ተቀምጠው ነበር፥ እያንዳንዳቸውም ሁለት ወይም ሦስት እንሰራ ይይዙ ነበር።
፯ ኢየሱስም። ጋኖቹን ውኃ ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሙሉአቸው አላቸው። እስከ አፋቸውም ሞሉአቸው።
፰ አሁን ቀድታችሁ ለአሳዳሪው ሰጡት አላቸው፤ ሰጡትም።
፱ አሳዳሪውም የወይን ጠጅ የሆነውን ውሃ በቀመሰ ጊዜ ከወዴት እንደ መጣ አላወቀም፤ ውኃውን የቀዱት አገልጋዮች ግን ያውቁ ነበር፤ አሳዳሪው ሙሽራውን ጠርቶ።
፲ ሰው ሁሉ አስቀድሞ መልካሙን የወይን ጠጅ ያቀርባል፥ ከሰከሩም በኋላ መናኛውን፤ አንተስ መልካሙን የወይን ጠጅ እስከ አሁን አቆይተሃል አለው።
፲፩ ኢየሱስ ይህን የምልክቶች መጀመሪያ በገሊላ ቃና አደረገ፤ ክብሩንም ገለጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም በእርሱ አመኑ።
፲፪ ከዚህ በኋላ ከእናቱና ከወንድሞቹ ከደቀ መዛሙርቱም ጋር ወደ ቅፍርናሆም ወረደ፥ በዚያም ጥቂት ቀን ኖሩ።
፲፫ የአይሁድ ፋሲካም ቀርቦ ነበር፥ ኢየሱስም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
፲፬ በመቅደስም በሬዎችንና በጎችን ርግቦችንም የሚሸጡትን ገንዘብ ለዋጮችንም ተቀምጠው አገኘ፤
፲፭ የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፥ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፥
፲፮ ርግብ ሻጪዎችንም። ይህን ከዚህ ውሰዱ፤ የአባቴን ቤት የንግድ ቤት አታድርጉት አላቸው።
፲፯ ደቀ መዛሙርቱም። የቤትህ ቅናት ይበላኛል ተብሎ እንደ ተጻፈ አስቡ።
፲፰ ሰለዚህ አይሁድ መልሰው። ይህን ሰለምታደርግ ምን ምልክት ታሳየናለህ? አሉት።
፲፱ ኢየሱስም መልሶ። ይህን ቤተ መቅደስ አፍርሱት፥ በሦስት ቀንም አነሣዋለሁ አላቸው።
፳ ሰለዚህ አይሁድ። ይህ ቤተ መቅደስ ከአርባ ሰድስት ዓመት ጀምሮ ይሠራ ነበር፥ አንተስ በሦስት ቀን ታነሣዋለህን? አሉት።
፳፩ እርሱ ግን ሰለ ሰውነቱ ቤተ መቅደስ ይል ነበር።
፳፪ ሰለዚህ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ደቀ መዛሙርቱ ይህን እንደ ተናገረ አሰቡና መጽሐፍንና ኢየሱስ የተናገረውን ቃል አመኑ።
፳፫-፳፭ በፋሲካ በዓልም በኢየሩሳሌም ሳለ፥ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ ብዙ ሰዎች በሰሙ አመኑ፤

፫

፩ ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ፤ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ።
፪ መምህር ሆይ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ መጣህ እናውቃለን አለው።
፫ ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።
፬ ኒቆዲሞስም። ሰው ከሸመገለ በኋላ እንዴት ሊወለድ ይችላል? ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው።
፭ ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ሊገባ አይችልም።
፮ ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፥ ከመንፈስም የተወለደ መንፈስ ነው።
፯ ዳግመኛ ልትወለዱ ያሰፈልጋችኋል ሰላልሁህ አታድንቅ።
፰ ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፥ ድምፁንም ትሰማለህ፥ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲሁ ነው።
፱ ኒቆዲሞስ መልሶ። ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል? አለው።
፲ ኢየሱስም መልሶ እንዲህ አለው። አንተ የእስራኤል መምህር ሰትሆን ይህን አታውቅምን?
፲፩ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውንም እንመሰክራለን፥ ምስክራችንንም አትቀበሉትም።
፲፪ ሰለ ምድራዊ ነገር በነገርኋችሁ ጊዜ ካላመናችሁ፥ ሰለ ሰማያዊ ነገር ብነግራችሁ እንዴት ታምናላችሁ?
፲፫ ከሰማይም ከወረደ በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፥ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው።
፲፬-፲፮ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና።
፲፯ ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።

፳፭ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።
፲፰ ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው።
፳ ክፉ የሚያደርግ ሁሉ ብርሃንን ይጠላልና፥ ሥራውም እንዳይገለጥ ወደ ብርሃን አይመጣም፤
፳፩ እውነትን የሚያደርግ ግን ሥራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደ ሆነ ይገለጥ ዘንድ ወደ ብርሃን ይመጣል።
፳፪ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ይሁዳ አገር መጣ፥ በዚያም ከእነርሱ ጋር ተቀምጦ ያጠምቅ ነበር።
፳፫ ዮሐንስም ደግሞ በሳሌም አቅራቢያ በሄኖን በዚያ ብዙ ውኃ ነበርና ያጠምቅ ነበር፥
፳፬ እየመጡም ይጠመቁ ነበር ዮሐንስ ገና ወደ ወኅኒ አልተጨመረም ነበርና።
፳፭ ስለዚህም በዮሐንስ ደቀ መዛሙርትና በአይሁድ መካከል ስለ ማንጻት ክርክር ሆነ።
፳፮ ወደ ዮሐንስም መጥተው። መምህር ሆይ፥ በዮርዳኖስ ማዶ ከአንተ ጋር የነበረው አንተም የመሰከርህለት፥ እነሆ፥ እርሱ ያጠምቃል ሁሉም ወደ እርሱ ይመጣሉ አሉት።
፳፯ ዮሐንስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል። ከሰማይ ካልተሰጠው ሰው እንዳች ሊቀበል አይችልም።
፳፰ እናንተ። እኔ ክርስቶስ አይደለሁም፥ ነገር ግን። ከእርሱ በፊት ተልኬአለሁ እንዳልሁ ራሳችሁ ትመሰክሩልኛላችሁ።
፳፱ ሙሽራይቱ ያለችው እርሱ ሙሽራ ነው፤ ቆሞ የሚሰማው ሚዜው ግን በሙሽራው ድምጽ እጅግ ደስ ይለዋል። እንግዲህ ይህ ደስታዬ ተፈጸመ።
፴ እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል።
፴፩ ከላይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው፤ ከምድር የሚሆነው የምድር ነው የምድሩንም ይናገራል። ከሰማይ የሚመጣው ከሁሉ በላይ ነው።
፴፪ ያየውንና የሰማውንም ይህን ይመሰክራል፥ ምስክሩንም የሚቀበለው የለም።
፴፫ ምስክሩን የተቀበለ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ አተመ።
፴፬ እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራልና፤ እግዚአብሔር መንፈሱን ሰፍሮ አይሰጥምና።
፴፭ አባት ልጁን ይወዳል ሁሉንም በእጁ ሰጥቶታል።
፴፮ በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቍጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም።

፬

፩ እንግዲህ። ኢየሱስ ከዮሐንስ ይልቅ ደቀ መዛሙርት ያደርጋል ያጠምቅማል ማለትን ፈሪሳውያን እንደ ሰሙ ጌታ ባወቀ ጊዜ፥
፪-፬ በሰማርያም ሊያልፍ ግድ ሆነበት።
፭ ስለዚህ ያዕቆብ ለልጁ ለዮሴፍ በሰጠው ሰፍራ አጠገብ ወደምትሆን ሲካር ወደምትባል የሰማርያ ከተማ መጣ፤
፮ በዚያም የያዕቆብ ጕድጓድ ነበረ። ኢየሱስም መንገድ ከመሄድ ደክሞ በጕድጓድ አጠገብ እንዲህ ተቀመጠ፤ ጊዜውም ስድስት ሰዓት ያህል ነበረ።
፯ ከሰማርያ አንዲት ሴት ውኃ ልትቀዳ መጣች። ኢየሱስም። ውኃ አጠጪኝ አላት፤
፰ ደቀ መዛሙርቱ ምግብ ሊገዙ ወደ ከተማ ሄደው ነበርና።
፱ ስለዚህ ሳምራዊቲቱ። አንተ የይሁዳ ሰው ስትሆን ሳምራዊት ሴት ከምሆን ከእኔ መጠጥ እንዴት ትለምናለህ? አለችው፤ አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበርና።
፲ ኢየሱስ መልሶ። የእግዚአብሔርን ስጦታና። ውኃ አጠጪኝ የሚልሽ ማን መሆኑንስ ብታውቂ፥ አንቺ ትለምኚው ነበርሽ የሕይወትም ውኃ ይሰጥሽ ነበር አላት።
፲፩ ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ መቅጃ የለህም ጕድጓዱም ጥልቅ ነው፤ እንግዲህ የሕይወት ውኃ ከወዴት ታገኛለህ?
፲፪ በእውኑ አንተ ይህን ጕድጓድ ከሰጠን ከአባታችን ከያዕቆብ ትበልጣለህን? ራሱም ልጆቹም ከብቶቹም ከዚህ ጠጥተዋል አለችው።
፲፫ ኢየሱስም መልሶ። ከዚህ ውኃ የሚጠጣ ሁሉ እንደ ገና ይጠማል፤
፲፬ እኔ ከምሰጠው ውኃ የሚጠጣ ሁሉ ግን ለዘላለም አይጠማም፥ እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል እንጂ አላት።
፲፭ ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውኃ ስጠኝ አለችው።
፲፮ ኢየሱስም። ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነዪ አላት።
፲፯ ሴቲቱ መልሳ። ባል የለኝም አለችው። ኢየሱስ። ባል የለኝም በማለትሽ መልካም ተናገርሽ፤
፲፰ አምስት ባሎች ነበሩሽና፥ አሁን ከአንቺ ጋር ያለው ባልሽ አይደለም፤ በዚህስ እውነት ተናገርሽ አላት።
፲፱ ሴቲቱ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ነቢይ እንደ ሆንህ አያለሁ።
፳ አባቶቻችን በዚህ ተራራ ሰገዱ፤ እናንተም። ሰው ሊሰግድበት የሚገባው ስፍራ በኢየሩሳሌም ነው ትላላችሁ አለችው።
፳፩ ኢየሱስም እንዲህ አላት። አንቺ ሴት፥ እመኚኝ፥ በዚህ ተራራ ወይም በኢየሩሳሌም ለአብ የማትሰግዱበት ጊዜ ይመጣል።
፳፪ እናንተስ ለማታውቁት ትሰግዳላችሁ፤ እኛ መዳን ከአይሁድ ነውና ለምናውቀው እንሰግዳለን።
፳፫ ነገር ግን በእውነት የሚሰግዱ ለአብ በመንፈስና በእውነት የሚሰግዱበት ጊዜ ይመጣል አሁንም ሆኖአል፤ አብ ሊሰግዱለት እንደ እነዚህ ያሉትን ይሻልና፤
፳፬ እግዚአብሔር መንፈስ ነው፥ የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል።
፳፭ ሴቲቱ። ክርስቶስ የሚባል መሲሕ እንዲመጣ አውቃለሁ፤ እርሱ ሲመጣ ሁሉን ይነግረናል አለችው።
፳፮ ኢየሱስ። የምናገርሽ እኔ እርሱ ነኝ አላት።
፳፯ በዚያም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ መጡና ከሴት ጋር በመነጋገሩ ተደነቁ፤ ነገር ግን። ምን ትፈልጊያለሽ?

ወይም። ስለ ምን ትናገራታለህ? ያለ ማንም አልነበረም።
፳፫ ሴቲቱም እንሰራዋን ትታ ወደ ከተማ ሄደች ለሰዎችም።
፳፬ ያደረግሁትን ሁሉ የነገረኝን ሰው ኑና እዩ፤ እንጂ እርሱ ክርስቶስ ይሆንን? አለች።
፳፭ ከከተማ ወጥተው ወደ እርሱ ይመጡ ነበር።
፳፮ ይህም ሲሆን ሳለ ደቀ መዛሙርቱ። መምህር ሆይ፥ ብላ ብለው ለመኑት።
፳፯ እርሱ ግን። እናንተ የማታውቁት የምበላው መብል ለእኔ አለኝ አላቸው።
፳፰ ስለዚህ ደቀ መዛሙርቱ። የሚበላው አንዳች ሰው አምጥቶለት ይሆንን? ተባባሉ።
፳፱ ኢየሱሰም እንዲህ አላቸው። የእኔሰ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።
፴ እናንተ። ገና አራት ወር ቀርቶአል መከርም ይመጣል ትሉ የለምን? እነሆ እላችኋለሁ፥ ዓይናችሁን አንሡ አዝመራውም አሁን እንደ ነጣ እርሻውን ተመልከቱ።
፴፩ የሚያጭድ ደመወዝን ይቀበላል፥ የሚዘራና የሚያጭድም አብረው ደሰ እንዲላቸው ለዘላለም ሕይወት ፍሬን ይሰበስባል።
፴፪ አንዱ ይዘራል አንዱም ያጭዳል የሚለው ቃል በዚህ እውነት ሆኖአልና።
፴፫ እኔም እናንተ ያልደከማችሁበትን ታጭዱ ዘንድ ሰደድኋችሁ፤ ሌሎች ደከሙ እናንተም በድካማቸው ገባችሁ።
፴፬ ሴቲቱም። ያደረግሁትን ሁሉ ነገረኝ ብላ ሰለ መሰከረችው ቃል ከዚያች ከተማ የሰማርያ ሰዎች ብዙ አመኑበት።
፵ የሰማርያ ሰዎችም ወደ እርሱ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ዘንድ እንዲኖር ለመኑት፤ በዚያም ሁለት ቀን ያህል ኖረ።
፵፩ ሰለ ቃሉ ከፊተኞች ይልቅ ብዙ ሰዎች አመኑ፤
፵፪ ሴቲቱንም። አሁን የምናምን ሰለ ቃልሽ አይደለም፥ እኛ ራሳችን ሰምተነዋልና፤ እርሱም በእውነት ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት እንደ ሆነ እናውቃለን ይሉአት ነበር።
፵፫ ከሁለቱ ቀኖችም በኋላ ከዚያ ወጥቶ ወደ ገሊላ ሄደ።
፵፬ ነቢይ በገዛ አገሩ እንዳይከበር ኢየሱስ ራሱ መስክሮአልና።
፵፭ ወደ ገሊላም በመጣ ጊዜ፥ የገሊላ ሰዎች ራሳቸው ደግሞ ለበዓል መጥተው ነበርና በበዓል በኢየሩሳሌም ያደረገውን ሁሉ ሰላዩ ተቀበሉት።
፵፮ ኢየሱሰም ውኃውን የወይን ጠጅ ወዳደረገባት ወደ ገሊላ ቃና ዳግመኛ መጣ። በቅፍርናሆምም ልጁ የታመመበት ከንጉሥ ቤት አንድ ሹም ነበረ።
፵፯ እርሱም ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ እንደ መጣ ሰምቶ ልጁ ሊሞት ሰላለው ወደ እርሱ ሄደ ወርዶም እንዲፈውሰለት ለመነው።
፵፰ ስለዚህም ኢየሱስ። ምልክትና ድንቅ ነገር ካላያችሁ ከቶ አታምኑም አለው።
፵፱ ሹሙም። ጌታ ሆይ፥ ብላቴናዬ ሳይሞት ውረድ አለው።
፶ ኢየሱሰም። ሂድ፤ ልጅህ በሕይወት አለ አለው። ሰውዬውም ኢየሱስ የነገረውን ቃል አምኖ ሄደ።
፶፩ እርሱም ሲወርድ ሳለ ባሮቹ ተገናኙትና። ብላቴናህ በሕይወት አለ ብለው ነገሩት።
፶፪ እርሱም በጎ የሆነበትን ሰዓት ጠየቃቸው፤ እነርሱም። ትናንት በሰባት ሰዓት ንዳዱ ለቀቀው አሉት።
፶፫ አባቱም ኢየሱስ። ልጅህ በሕይወት አለ ባለው በዚያ ሰዓት እንደ ሆነ አወቀ፤ እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር አመነ።
፶፬ ይህም ደግሞ ኢየሱስ ከይሁዳ ወደ ገሊላ መጥቶ ያደረገው ሁለተኛ ምልክት ነው።

፭

፩ ከዚህ በኋላ የአይሁድ በዓል ነበረ፥ ኢየሱሰም ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
፪ በኢየሩሳሌምም በበጎች በር አጠገብ በዕብራይስጥ ቤተ ሳይዳ የምትባል አንዲት መጠመቂያ ነበረች፤ አምስትም መመላለሻ ነበረባት።
፫ በእነዚህ ውስጥ የውኃውን መነቀሳቀስ እየጠበቁ በሽተኞችና ዕውሮች አንካሶችም ሰውነታቸውም የሰለለ ብዙ ሕዝብ ይተኙ ነበር።
፬ አንዳንድ ጊዜ የጌታ መልአክ ወደ መጠመቂያይቱ ወርዶ ውኃውን ያናውጥ ነበርና፤ እንግዲህ ከውኃው መናወጥ በኋላ በመጀመሪያ የገባ ከማናቸው ካለበት ደዌ ጤናማ ይሆን ነበር።
፭ በዚያም ከሠላሳ ሰምንት ዓመት ጀምሮ የታመመ አንድ ሰው ነበረ፤
፮ ኢየሱስ ይህን ሰው ተኝቶ ባየ ጊዜ፥ እስከ አሁን ብዙ ዘመን እንዲሁ እንደ ነበረ አውቆ። ልትድን ትወዳለህን? አለው።
፯ ድውዬም። ጌታ ሆይ፥ ውኃው በተናወጠ ጊዜ በመጠመቂያይቱ ውስጥ የሚያኖረኝ ሰው የለኝም ነገር ግን እኔ ሰመጣ ሳለሁ ሌላው ቀድሞኝ ይወርዳል ብሎ መለሰለት።
፰ ኢየሱስ። ተነሣና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለው።
፱ ወዲያውም ሰውዬው ዳነ አልጋውንም ተሸክሞ ሄደ።
፲ ያም ቀን ሰንበት ነበረ። ሰለዚህ አይሁድ የተፈወሰውን ሰው። ሰንበት ነው አልጋህንም ልትሸከም አልተፈቀደልህም አሉት።
፲፩ እርሱ ግን። ያዳነኝ ያ ሰው። አልጋህን ተሸክመህ ሂድ አለኝ ብሎ መለሰላቸው።
፲፪ እነርሱም። አልጋህን ተሸክመህ ሂድ ያለህ ሰው ማን ነው? ብለው ጠየቁት።
፲፫ ዳሩ ግን በዚያ ሰፍራ ሕዝብ ሰለ ነበሩ ኢየሱስ ፈቀቅ ብሎ ነበርና የተፈወሰው ሰው ማን እንደ ሆነ አላወቀም።
፲፬ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በመቅደስ አገኘውና። እነሆ፥ ድነሃል፤ ከዚህ የሚብስ እንዳይደርሰብህ ወደ ፊት ኃጢአት አትሥራ አለው።
፲፭ ሰውዬው ሄዶ ያዳነው ኢየሱስ እንደ ሆነ ለአይሁድ ነገረ።
፲፮ ሰለዚህም በሰንበት ይህን ሰላደረገ አይሁድ ኢየሱሰን ያሳድዱት ነበር ሊገድሉትም ይፈልጉ ነበር።
፲፯ ኢየሱስ ግን። አባቴ እስከ ዛሬ ይሠራል እኔም ደግሞ እሠራለሁ ብሎ መለሰላቸው።
፲፰ እንግዲህ ሰንበትን ሰለ ሻረ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ደግሞ ራሱን ከእግዚአብሔር ጋር አስተካክሎ።

እግዚአብሔር አባቴ ነው ሰላለ፥ ሰለዚህ አይሁድ ለገድሉት አብዝተው ይፈልጉት ነበር።

፲፱ ሰለዚህ ኢየሱሰ መለሰ እንዲህም አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ ሲያደርግ ያየውን ነው እንጂ ወልድ ከራሱ ሊያደርግ ምንም አይችልም፤ ያ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ይህን እንዲሁ ያደርጋልና።

፳ አብ ወልድን ይወዳልና፥ የሚያደርገውንም ሁሉ ያሳየዋል፤ እናንተም ትደነቁ ዘንድ ከዚህ የሚበልጥ ሥራ ያሳየዋል።

፳፩ አብ ሙታንን እንደሚያነሣ ሕይወትም እንደሚሰጣቸው፥ እንዲሁ ወልድ ደግሞ ለሚወዳቸው ሕይወትን ይሰጣቸዋል።

፳፪-፳፬ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም።

፳፭ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።

፳፮ አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና።

፳፯ የሰው ልጅም ሰለ ሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን ሰጠው።

፳፰-፴ እኔ ከራሴ እንዳች ላደርግ አይቻለኝም፤ እንደ ሰማሁ እፈርዳለሁ ፍርዴም ቅን ነው፥ የላከኝን ፈቃድ እንጂ ፈቃዴን አልሻምና።

፴፩ እኔ ሰለ እኔ ሰለ ራሴ ብመሰክር ምሰክሬ እውነት አይደለም፤

፴፪ ሰለ እኔ የሚመሰክር ሌላ ነው፥ እርሱም ሰለ እኔ የሚመሰክረው ምሰክር እውነት እንደ ሆነ አውቃለሁ።

፴፫ እናንተ ወደ ዮሐንሰ ልካችኋል እርሱም ለእውነት መሰክሮአል።

፴፬ እኔ ግን ከሰው ምሰክር አልቀበልም፥ እናንተ እንድትድኑ ይህን እላለሁ እንጂ።

፴፭ እርሱ የሚነድና የሚያበራ መብራት ነበረ፥ እናንተም ጥቂት ዘመን በብርሃኑ ደሰ ሊላችሁ ወደዳችሁ።

፴፮ እኔ ግን ከዮሐንሰ ምሰክር የሚበልጥ ምሰክር አለኝ፤ አብ ልፈጽመው የሰጠኝ ሥራ፥ ይህ የማደርገው ሥራ፥ አብ እንደ ላከኝ ሰለ እኔ ይመሰክራልና።

፴፯ የላከኝ አብም እርሱ ሰለ እኔ መሰክሮአል። ድምፁን ከቶ አልሰማችሁም፥ መልኩንም አላያችሁም፤

፴፰ እርሱም የላከውን እናንተ አታምኑምና በእናንተ ዘንድ የሚኖር ቃሉ የላችሁም።

፴፱ እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመሰላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ሰለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤

፵ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።

፵፩-፵፫ እኔ በአባቴ ሰም መጥቻለሁ አልተቀበላችሁኝምም፤ ሌላው በራሱ ሰም ቢመጣ እርሱን ትቀበሉታላችሁ።

፵፬ እናንተ እርስ በርሳችሁ ክብር የምትቀባበሉ ከእንዱም ከእግዚአብሔር ያለውን ክብር የማትፈልጉ፥ እንዴት ልታምኑ ትችላላችሁ?

፵፭ እኔ በአብ ዘንድ የምከሳችሁ አይምሰላችሁ፤ የሚከሳችሁ አለ፤ እርሱም ተሰፋ የምታደርጉት ሙሴ ነው።

፵፮ ሙሴንሰ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር፤ እርሱ ሰለ እኔ ጽፎአልና።

፵፯ መጻሕፍትን ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ?

፮

፩ ከዚህ በኋላ ኢየሱሰ ወደ ገሊላ ባሕር ማዶ ተሻገረ፤ እርሱም የጥብርያዶሰ ባሕር ነው።

፪ በበሽተኞችም ያደረገውን ምልክቶች ሰላዩ ብዙ ሕዝብ ተከተሉት።

፫ ኢየሱሰም ወደ ተራራ ወጣና በዚያ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ።

፬ የአይሁድ በዓልም ፋሲካ ቀርቦ ነበር።

፭ ኢየሱሰም ዓይኖቹን አነሥቶ ብዙ ሕዝብ ወደ እርሱ ሲመጣ አየና ፊልጶስን። እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን? አለው።

፮ ራሱ ሊያደርግ ያለውን ያውቅ ነበርና ሊፈትነው ይህን ተናገረ።

፯ ፊልጶሰ። እያንዳንዳቸው ትንሽ ትንሽ እንኳ እንዲቀበሉ የሁለት መቶ ዲናር እንጀራ አይበቃቸውም ብሎ መለሰለት።

፰ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ የሰምዖን ጴጥሮሰ ወንድም እንድርያሰ።

፱ አምሰት የገብሰ እንጀራና ሁለት ዓሣ የያዘ ብላቴና በዚህ አለ፤ ነገር ግን እነዚህን ለሚያህሉ ሰዎች ይህ ምን ይሆናል? አለው።

፲ ኢየሱሰም። ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ ኢለ። በዚያም ሰፍራ ብዙ ሣር ነበረበት። ወንደችም ተቀመጡ ቍጥራቸውም አምሰት ሺህ የሚያህል ነበር።

፲፩ ኢየሱሰም እንጀራውን ያዘ፥ አመሰግኖም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠ፥ ደቀ መዛሙርቱም ለተቀመጡት ሰዎች ሰጡአቸው እንዲሁም ከዓሣው በፈለጉት መጠን።

፲፪ ከጠገቡም በኋላ ደቀ መዛሙርቱን። አንድ ሰንኳ እንዳይጠፋ የተረፈውን ቍርሰራሽ አከማቹ አላቸው።

፲፫ ሰለዚህ አከማቹ፥ ከበሉትም ከአምሰቱ የገብሰ እንጀራ የተረፈውን ቍርሰራሽ አሥራ ሁለት መሶብ ሞሉ።

፲፬ ከዚህ የተነሣ ሰዎቹ ኢየሱሰ ያደረገውን ምልክት ባዩ ጊዜ። ይህ በእውነት ወደ ዓለም የሚመጣው ነቢይ ነው አሉ።

፲፭ በዚህም ምክንያት ኢየሱሰ ያነግሡት ዘንድ ሊመጡና ሊነጥቁት እንዳላቸው አውቆ ደግሞ ወደ ተራራ ብቻውን ፈቀቅ አለ።

፲፮ በመሸም ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ወደ ባሕር ወረዱ፥

፲፯ በታንኳም ገብተው በባሕር ማዶ ወደ ቅፍርናሆም ይመጡ ነበር። አሁንም ጨልሞ ነበር፤ ኢየሱሰም ገና ወደ እነርሱ አልመጣም ነበር፤

፲፰ ብርቱ ነፋሰም ሰለ ነፈሰ ባሕሩ ተናወጠ።

፲፱ ሀያ አምሰት ወይም ሠላሳ ምዕራፍ ከቀዘፉ በኋላም፥ ኢየሱሰ በባሕር ላይ እየሄደ ወደ ታንኳይቱ ሲቀርብ አይተው ፈሩ።

፳ እርሱ ግን። እኔ ነኝ፤ አትፍሩ አላቸው።

፳፩ ሰለዚህ በታንኳይቱ ሊቀበሉት ወደዱ፤ ወዲያውም ታንኳይቱ ወደሚሄዱበት ምድር ደረሰች።

፳፪ በነገው በባሕር ማዶ ቆመው የነበሩ ሕዝቡ ከአንዲት ጀልባ በቀር በዚያ ሌላ ጀልባ እንዳልነበረች፥ ደቀ መዛሙርቱም ለብቻቸው እንደ ሄዱ እንጂ ኢየሱስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወደ ታንኳይቱ እንዳልገባ አዩ፤
፳፫ ዳሩ ግን ሌሎች ጀልባዎች ጌታ የባረከውን እንጀራ ወደ በሉበት ሰፍራ አጠገብ ከጥብርያዶስ መጡ።
፳፬ ሕዝቡም ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ እንዳልነበሩ ባዩ ጊዜ፥ ራሳቸው በጀልባዎቹ ገብተው ኢየሱስን እየፈለጉ ወደ ቅፍርናሆም መጡ።
፳፭ በባሕር ማዶም ሲያገኙት። መምህር ሆይ፥ ወደዚህ መቼ መጣህ? አሉት።
፳፮ ኢየሱስም መልሶ። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የምትፈልጉኝ እንጀራን ሰለ በላችሁና ሰለ ጠገባችሁ ነው እንጂ ምልክቶችን ሰላያችሁ አይደለም።
፳፯ ለሚጠፋ መብል አትሥሩ፤ ነገር ግን ለዘላለም ሕይወት ለሚኖር መብል የሰው ልጅ ለሚሰጣችሁ ሥሩ፤ እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታልና።
፳፰ እንግዲህ። የእግዚአብሔርን ሥራ እንድንሠራ ምን እናድርግ? አሉት።
፳፱ ኢየሱስ መልሶ። ይህ የእግዚአብሔር ሥራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው።
፴ እንግዲህ። እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሠራለህ?
፴፩ ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት።
፴፪ ኢየሱስም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እውነተኛ እንጀራ ከሰማይ የሚሰጣችሁ አባቴ ነው እንጂ ከሰማይ እንጀራ የሰጣችሁ ሙሴ አይደለም፤
፴፫ የእግዚአብሔር እንጀራ ከሰማይ የሚወርድ ለዓለምም ሕይወትን የሚሰጥ ነውና አላቸው።
፴፬ ሰለዚህ። ጌታ ሆይ፥ ይህን እንጀራ ዘወትር ሰጠን አሉት።
፴፭ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ፤ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም።
፴፮ ነገር ግን አይታችሁኝ እንዳላመናችሁ አልኋችሁ።
፴፯ አብ የሚሰጠኝ ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል፥ ወደ እኔም የሚመጣውን ከቶ ወደ ውጭ አላወጣውም፤
፴፰ ፈቃዴን ለማድረግ አይደለም እንጂ የላከኝን ፈቃድ ለማድረግ ከሰማይ ወርጀለሁና።
፴፱ ከሰጠኝም ሁሉ አንድን ሰንኳ እንዳላጠፋ በመጨረሻው ቀን እንዳስነሣው እንጂ የላከኝ የአብ ፈቃድ ይህ ነው።
፵ ልጅንም አይቶ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወትን እንዲያገኝ የአባቴ ፈቃድ ይህ ነው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።
፵፩ እንግዲህ አይሁድ። ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ሰላለ ሰለ እርሱ እንጕራጕሩና።
፵፪ አባቱንና እናቱን የምናውቃቸው ይህ የዮሴፍ ልጅ ኢየሱስ አይደለምን? እንግዲህ። ከሰማይ ወርጃለሁ እንዴት ይላል? አሉ።
፵፫ ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። እርስ በርሳችሁ አታንጕራጕሩ።
፵፬ የላከኝ አብ ከሳበው በቀር ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።
፵፭ ሁሉም ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ ተብሎ በነቢያት ተጽፎአል፤ እንግዲህ ከአብ የሰማ የተማረም ሁሉ ወደ እኔ ይመጣል።
፵፮ አብን ያየ ማንም የለም፤ ከእግዚአብሔር ከሆነ በቀር፥ እርሱ አብን አይቶአል።
፵፯ እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው።
፵፰ የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ።
፵፱ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም፤
፶ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው።
፶፩ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ፤ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል፤ እኔም ሰለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።
፶፪ እንግዲህ አይሁድ። ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል? ብለው እርስ በርሳቸው ተከራከሩ።
፶፫ ሰለዚህ ኢየሱስ እንዲህ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።
፶፬ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፥ እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሣዋለሁ።
፶፭ ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።
፶፮ ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ።
፶፯ ሕያው አብ እንደ ላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን፥ እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።
፶፰ ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደ ሞቱ አይደለም፤ ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል
፶፱ በቅፍርናሆም ሲያስተምር ይህን በምኩራብ አለ።
፷ ከደቀ መዛሙርቱም ብዙዎች በሰሙ ጊዜ። ይህ የሚያሰጨንቅ ንግግር ነው፤ ማን ሊሰማው ይችላል? አሉ።
፷፩ ኢየሱስ ግን ደቀ መዛሙርቱ ሰለዚህ እንዳንጕራጕሩ በልቡ አውቆ አላቸው። ይህ ያሰናክላችኋልን?
፷፪ እንግዲህ የሰው ልጅ አሰቀድሞ ወደ ነበረበት ሲወጣ ብታዩ እንዴት ይሆናል?
፷፫ ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ነው፤ ሥጋ ምንም አይጠቅምም፤ እኔ የነገርኋችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው።
፷፬ ነገር ግን ከእናንተ የማያምኑ አሉ። ኢየሱስ የማያምኑት እነማን እንደ ሆኑ አሳልፎ የሚሰጠውም ማን እንደ ሆነ ከመጀመሪያ ያውቅ ነበርና።
፷፭ ደግሞ። ሰለዚህ አልኋችሁ፥ ከአብ የተሰጠው ካልሆነ ወደ እኔ ሊመጣ የሚችል የለም አለ።
፷፮ ከዚህም የተነሣ ከደቀ መዛሙርቱ ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም።
፷፯ ኢየሱስም ለአሥራ ሁለቱ። እናንተ ደግሞ ልትሄዱ ትወዳላችሁን? አለ።
፷፰ ሰምዖን ጴጥሮስ። ጌታ ሆይ፥ ወደ ማን እንሄዳለን? አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ፤

፷፱ እኛስ አንተ ክርስቶስ የሕያው የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ አምነናል አውቀናልም ብሎ መለሰለት።
፸ ኢየሱስም። እኔ እናንተን አሥራ ሁለታችሁን የመረጥኋችሁ አይደለምን? ከእናንተም አንዱ ዲያብሎስ ነው ብሎ መለሰላቸው።
፸፩ ስለ ስምዖንም ልጅ ስለ አስቆሮቴ ይሁዳ ተናገረ፤ ከአሥራ ሁለቱ አንዱ የሆነ እርሱ አሳልፎ ይሰጠው ዘንድ አለውና።

፯

፩ ከዚህም በኋላ ኢየሱስ አይሁድ ሊገድሉት ይፈልጉ ስለ ነበር በይሁዳ ሊመላለስ አይወድም ነበርና በገሊላ ይመላለስ ነበር።
፪ የአይሁድም የዳስ በዓል ቀርቦ ነበር።
፫ እንግዲህ ወንድሞቹ። ደቀ መዛሙርትህ ደግሞ የምታደርገውን ሥራ እንዲያዩ ከዚህ ተነሣና ወደ ይሁዳ ሂድ፤
፬ ራሱ ሊገለጥ እየፈለገ በሰውር የሚሠራ የለምና። እነዚህን ብታደርግ ራስህን ለዓለም ግለጥ አሉት።
፭ ወንድሞቹ ሰንኳ አላመኑበትም ነበርና።
፮ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው። ጊዜዬ ገና አልደረሰም፥ ጊዜያችሁ ግን ዘወትር የተመቸ ነው።
፯ ዓለም እናንተን ሊጠላ አይቻለውም፤ እኔ ግን ሥራው ክፉ መሆኑን እመሰክርበታለሁና እኔን ይጠላኛል።
፰ እናንተ ወደዚህ በዓል ውጡ፤ እኔስ ጊዜዬ ገና ስላልተፈጸመ ወደዚህ በዓል ገና አልወጣም።
፱ ይህንም አላቸውና በገሊላ ቀረ።
፲ ወንድሞቹ ግን ወደ በዓሉ ከወጡ በኋላ በዚያን ጊዜ እርሱ ደግሞ በግልጥ ሳይሆን ተሰውሮ ወጣ።
፲፩ አይሁድም። እርሱ ወዴት ነው? እያሉ በበዓሉ ይፈልጉት ነበር።
፲፪ በሕዝብም መካከል ስለ እርሱ ብዙ ማጒራጒር ነበረ፤ አንዳንዱም። ደግ ሰው ነው፤ ሌሎች ግን። አይደለም፥ ሕዝቡን ግን ያስታል ይሉ ነበር።
፲፫ ዳሩ ግን አይሁድን ስለ ፈሩ ማንም ስለ እርሱ በግልጥ አይናገርም ነበር።
፲፬ አሁንም በበዓሉ እኩሌታ ኢየሱስ ወደ መቅደስ ወጥቶ ያስተምር ነበር።
፲፭ አይሁድም። ይህ ሰው ሳይማር መጻሕፍትን እንዴት ያውቃል? ብለው ይደነቁ ነበር።
፲፮ ስለዚህ ኢየሱስ መለሰ እንዲህም አላቸው። ትምህርቴስ ከላከኝ ነው እንጂ ከእኔ አይደለም፤
፲፯ ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር፥ እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል።
፲፰ ከራሱ የሚናገር የራሱን ክብር ይፈልጋል፤ የላከውን ክብር የሚፈልግ ግን እርሱ እውነተኛ ነው በእርሱም ዓመፃ የለበትም።
፲፱ ሙሴ ሕግን አልሰጣችሁምን? ከእናንተ ግን ሕግን የሚያደርግ አንድ ሰንኳ የለም። ልትገድሉኝ ስለ ምን ትፈልጋላችሁ?
፳ ሕዝቡ መለሱና። ጋኔን አለብህ፤ ማን ሊገድልህ ይፈልጋል? አሉት።
፳፩ ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። አንድ ሥራ አደረግሁ ሁላችሁም ታደንቃላችሁ።
፳፪ ስለዚህ ሙሴ መገረዝን ሰጣችሁ፤ ከአባቶችም ነው እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ በሰንበትም ሰውን ትገርዛላችሁ።
፳፫ የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቈጡኛላችሁን?
፳፬ ቅን ፍርድ ፍረዱ እንጂ በመልክ አትፍረዱ።
፳፭ እንግዲህ ከኢየሩሳሌም ሰዎች እንዳንዶቹ እንዲህ አሉ። ሊገድሉት የሚፈልጉት ይህ አይደለምን?
፳፮ እነሆም፥ በግልጥ ይናገራል አንዳችም አይሉትም። አለቆቹ ይህ ሰው በእውነት ክርስቶስ እንደ ሆነ በእውነት አወቁን?
፳፯ ነገር ግን ይህን ከወዴት እንደ ሆነ አውቀናል፤ ክርስቶስ ሲመጣ ግን ከወዴት እንደ ሆነ ማንም አያውቅም።
፳፰ እንግዲህ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር። እኔንም ታውቁኛላችሁ ከወዴትም እንደ ሆንሁ ታውቃላችሁ፤ እኔም በራሴ አልመጣሁም ነገር ግን እናንተ የማታውቁት የላከኝ እውነተኛ ነው፤
፳፱ እኔ ግን ከእርሱ ዘንድ ነኝ እርሱም ልኮኛልና አውቀዋለሁ ብሎ ጮኸ።
፴ ስለዚህ ሊይዙት ይፈልጉ ነበር፤ ነገር ግን ጊዜው ገና ስላልደረሰ ማንም እጁን አልጫነበትም።
፴፩ ከሕዝቡ ግን ብዙዎች አመኑበትና። ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ይህ ካደረጋቸው ምልክቶች ይልቅ ያደርጋልን? አሉ።
፴፪ ፈሪሳውያንም ሕዝቡ ስለ እርሱ እንደዚህ ሲያንጒራጒሩ ሰሙ፤ የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያንም ሊይዙት ሎሌዎችን ላኩ።
፴፫ ኢየሱስም። ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር እቆያለሁ ወደ ላከኝም እሄዳለሁ።
፴፬ ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም፤ እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አለ።
፴፭ እንግዲህ አይሁድ። እኛ እንዳናገኘው ይህ ወዴት ይሄድ ዘንድ አለው? በግሪክ ሰዎች መካከል ተበትነው ወደሚኖሩት ሊሄድና የግሪክን ሰዎች ሊያስተምር አለውን?
፴፮ እርሱ። ትፈልጉኛላችሁ አታገኙኝምም እኔም ወዳለሁበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም የሚለው ይህ ቃል ምንድር ነው? ብለው እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ።
፴፯ ከበዓሉም በታላቁ በኋለኛው ቀን ኢየሱስ ቆሞ። ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ።
፴፰ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ፥ የሕይወት ውኃ ወንዝ ከሆዱ ይፈልቃል ብሎ ጮኸ።
፴፱ ይህን ግን በእርሱ የሚያምኑ ሊቀበሉት ስላላቸው ስለ መንፈስ ተናገረ፤ ኢየሱስ ገና ስላልከበረ መንፈስ ገና አልወረደም ነበርና።
፵ ስለዚህ ከሕዝቡ አያሌ ሰዎች ይህን ቃል ሲሰሙ። ይህ በእውነት ነቢዩ ነው አሉ፤
፵፩ ሌሎች። ይህ ክርስቶስ ነው አሉ፤ ሌሎች ግን። ክርስቶስ በእውኑ ከገሊላ ይመጣልን?
፵፪ ክርስቶስ ከዳዊት ዘር ዳዊትም ከነበረባት መንደር ከቤተ ልሔም እንዲመጣ መጽሐፍ አላለምን? አሉ።
፵፫ እንግዲህ ከእርሱ የተነሣ በሕዝቡ መካከል መለያየት ሆነ፤

፶፩ ከእነርሱም እንዳንዶቹ ሊይዙት ወደዱ ነገር ግን እጁን ማንም አልጫነበትም።
፶፪ ሎሌዎቹም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ፈሪሳውያን መጡ፤ እነዚያም። ያላመጣችሁት ስለ ምን ነው? አሉአቸው።
፶፫ ሎሌዎቹ። እንደዚህ ሰው ማንም እንዲሁ ከቶ አልተናገረም ብለው መለሱ።
፶፬ እንግዲህ ፈሪሳውያን። እናንተ ደግሞ ሳታችሁን?
፶፭ ከአለቆች ወይስ ከፈሪሳውያን በእርሱ ያመነ አለን?
፶፮ ነገር ግን ሕግን የማያውቀው ይህ ሕዝብ ርጉም ነው ብለው መለሱላቸው።
፶፯ ከእነርሱ አንዱ በሌሊት ቀድሞ ወደ እርሱ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ።
፶፰ ሕጋችን አስቀድሞ ከእርሱ ሳይሰማ ምንስ እንዲደረገ ሳያውቅ በሰው ይፈርዳልን? አላቸው።
፶፱ እነርሱም መለሱና። አንተም ደግሞ ከገሊላ ነህን? ነቢይ ከገሊላ እንዳይነሣ መርምርና እይ አሉት።
፷ እያንዳንዱም ወደ ቤቱ ሄደ።

፰

፩ ኢየሱስ ግን ወደ ደብረ ዘይት ሄደ።
፪ ማለዳም ደግሞ ወደ መቅደስ ደረሰ ሕዝቡም ሁሉ ወደ እርሱ መጡ። ተቀምጦም ያስተምራቸው ነበር።
፫ ጸሮችና ፈሪሳውያንም በምንዝር የተያዘችን ሴት ወደ እርሱ አመጡ በመካከልም እርሱዋን አቁመው።
፬ መምህር ሆይ፥ ይህች ሴት ስታመነዝር ተገኝታ ተያዘች።
፭ ሙሴም እንደነዚህ ያሉት እንዲወገሩ በሕግ አዘዘን፤ አንተስ ስለ እርስዋ ምን ትላለህ? አሉት።
፮ የሚከሱበትንም እንዲያገኙ ሊፈትኑት ይህን አሉ። ኢየሱስ ግን ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ፤
፯ መላልሰው በጠየቁት ጊዜ ግን ቀና ብሎ። ከእናንተ ኃጢአት የሌለበት አስቀድሞ በድንጋይ ይውገራት አላቸው።
፰ ደግሞም ጐንበስ ብሎ በጣቱ በምድር ላይ ጻፈ።
፱ እነርሱም ይህን ሲሰሙ ሕሊናቸው ወቀሳቸውና ከሽማግሌዎች ጀምረው እስከ ኋለኞች አንድ አንድ እያሉ ወጡ፤ ኢየሱስም ብቻውን ቀረ ሴቲቱም በመካከል ቆማ ነበረች።
፲ ኢየሱስም ቀና ብሎ ከሴቲቱ በቀር ማንንም ባላየ ጊዜ። አንቺ ሴት፥ እነዚያ ከሳሾችሽ ወዴት አሉ? የፈረደብሽ የለምን? አላት።
፲፩ እርስዋም። ጌታ ሆይ፥ አንድ ሰንኳ አለች። ኢየሱስም። እኔም አልፈርድብሽም፤ ሂጂ ከአሁንም ጀምሮ ደግመሽ ኃጢአት አትሥሪ አላት።
፲፪ ደግሞም ኢየሱስ። እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ፤ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለስም ብሎ ተናገራቸው።
፲፫ ፈሪሳውያንም። አንተ ስለ ራስህ ትመሰክራለህ፤ ምስክርነትህ እውነት አይደለም አሉት።
፲፬ ኢየሱስ መለሰ አላቸውም። እኔ ስለ ራሴ ምንም እንኳ ብመሰክር ከወዴት እንደመጣሁ ወዴትም እንድሄድ አውቃለሁና ምስክርነቴ እውነት ነው፤ እናንተ ግን ከወዴት እንደ መጣሁ ወዴትም እንድሄድ አታውቁም።
፲፭ እናንተ ሥጋዊ ፍርድን ትፈርዳላችሁ፤ እኔ በአንድ ሰው ሰንኳ አልፈርድም።
፲፮ የላከኝ አብ ከእኔ ጋር ነው እንጂ ብቻዬን አይደለሁምና እኔ ብፈርድ ፍርዴ እውነት ነው።
፲፯ የሁለት ሰዎችም ምስክርነት እውነት እንደ ሆነ በሕጋችሁ ተጽፎአል።
፲፰ ስለ ራሴ የምመሰክር እኔ ነኝ፥ የላከኝም አብ ስለ እኔ ይመሰክራል።
፲፱ እንግዲህ። አባትህ ወዴት ነው? አሉት። ኢየሱስ መለሰ። እኔንም ወይም አባቴንም አታውቁም፤ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር አላቸው።
፳ ኢየሱስ በመቅደስ ሲያስተምር በግምጃ ቤት አጠገብ ይህን ነገር ተናገረ፤ ጊዜው ገና አልደረሰምና ማንም አልያዘውም።
፳፩ ኢየሱስም ደግሞ። እኔ እሄዳለሁ ትፈልጉኛላችሁም በኃጢአታችሁም ትሞታላችሁ እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም አላቸው።
፳፪ አይሁድም። እኔ ወደ ምሄድበት እናንተ ልትመጡ አትችሉም ማለቱ ራሱን ይገድላልን? እንጂ አሉ።
፳፫ እናንተ ከታች ናችሁ፥ እኔ ከላይ ነኝ፤ እናንተ ከዚህ ዓለም ናችሁ፥ እኔ ከዚህ ዓለም አይደለሁም።
፳፬ እንግዲህ። በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ፤ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና አላቸው።
፳፭ እንግዲህ። አንተ ማን ነህ? አሉት። ኢየሱስም። ከመጀመሪያ ለእናንተ የተናገርሁት ነኝ።
፳፮ ስለ እናንተ የምናገረው የምፈርደውም ብዙ ነገር አለኝ፤ ዳሩ ግን የላከኝ እውነተኛ ነው እኔም ከእርሱ የሰማሁትን ይህን ለዓለም እናገራለሁ አላቸው።
፳፯ ስለ አብ እንደ ነገራቸው አላስተዋሉም።
፳፰ ስለዚህም ኢየሱስ። የሰውን ልጅ ከፍ ከፍ ባደረጋችሁት ጊዜ እኔ እሆን ዘንድ አባቴም እንዳስተማረኝ እነዚህን እናገር ዘንድ እንጂ ከራሴ አንዳች እንዳላደርግ በዚያን ጊዜ ታውቃላችሁ።
፳፱ የላከኝም ከእኔ ጋር ነው፤ እኔ ደስ የሚያሰኘውን ዘወትር አደርጋለሁና አብ ብቻዬን አይተወኝም አላቸው።
፴ ይህን ሲናገር ብዙዎች በእርሱ አመኑ።
፴፩ ኢየሱስም ያመኑትን አይሁድ። እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤
፴፪ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው።
፴፫ እነርሱም መልሰው። የአብርሃም ዘር ነን ለአንድም ሰንኳ ከቶ ባሪያዎች አልሆንም፤ አንተ። አርነት ትወጣላችሁ እንዴት ትላለህ? አሉት።
፴፬ ኢየሱስ መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባርያ ነው።
፴፭ ባርያም ለዘላለም በቤት አይኖርም፤ ልጁ ለዘላለም ይኖራል።
፴፮ እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።
፴፯ የአብርሃም ዘር መሆናችሁንስ አውቃለሁ ነገር ግን ቃሌ በእናንተ አይኖርምና ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ።
፴፰ እኔ በአባቴ ዘንድ ያየሁትን እናገራለሁ፤ እናንተም ደግሞ በአባታችሁ ዘንድ ያያችሁትን ታደርጋላችሁ።

፴፪ መልሰውም። አባታችንስ አብርሃም ነው አሉት። ኢየሱስም። የአብሃም ልጆች ብትሆኑ የአብርሃምን ሥራ ባደረጋችሁ ነበር።
፴፫ ነገር ግን አሁን ከእግዚአብሔር የሰማሁትን እውነት የነገርኋችሁን ሰው ልትገድሉኝ ትፈልጋላችሁ፤ አብርሃም እንዲህ አላደረገም።
፴፬ እናንተ የአባታችሁን ሥራ ታደርጋላችሁ አላቸው። እኛስ ከዝሙት አልተወለድንም አንድ አባት አለን እርሱም እግዚአብሔር ነው አሉት።
፴፭ ኢየሱስም አላቸው። እግዚአብሔርስ አባታችሁ ከሆነ በወደዳችሁኝ ነበር፤ እኔ ከእግዚአብሔር ወጥቼ መጥቻለሁና፤ እርሱ ላከኝ እንጂ ከራሴ አልመጣሁምና።
፴፮ ንግግሬን የማታስተውሉ ስለ ምንድር ነው? ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው።
፴፯ እናንተ ከአባታችሁ ከዲያብሎስ ናችሁ የአባታችሁንም ምኞት ልታደርጉ ትወዳላችሁ። እርሱ ከመጀመሪያ ነፍስ ገዳይ ነበረ፤ እውነትም በእርሱ ስለ ሌለ በእውነት አልቆመም። ሐሰትን ሲናገር ከራሱ ይናገራል፥ ሐሰተኛ የሐሰትም አባት ነውና።
፴፰ እኔ ግን እውነትን የምናገር ስለ ሆንሁ አታምኑኝም።
፴፱ ከእናንተ ስለ ኃጢአት የሚወቅሰኝ ማን ነው? እውነት የምናገር ከሆንሁ እናንተ ስለ ምን አታምኑኝም?
፵ ከእግዚአብሔር የሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማል፤ እናንተ ከእግዚአብሔር አይደላችሁምና ስለዚህ አትሰሙም።
፵፩ አይሁድ መልሰው። ሳምራዊ እንደ ሆንህ ጋኔንም እንዳለብህ በማለታችን እኛ መልካም እነል የለምን? አሉት።
፵፪ ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። እኔስ ጋኔን የለብኝም ነገር ግን አባቴን አከብራለሁ እናንተም ታዋርዱኛላችሁ።
፵፫ እኔ ግን የራሴን ክብር አልፈልግም፤ የሚፈልግ የሚፈርድም አለ።
፵፬ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም።
፵፭ አይሁድ። ጋኔን እንዳለብህ አሁን አወቅን። አብርሃም ሰንኳ ሞተ ነቢያትም፤ አንተም። ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አይቀምስም ትላለህ።
፵፮ በእውኑ አንተ ከሞተው ከአባታችን ከአብርሃም ትበልጣለህን? ነቢያትም ሞቱ፤ ራስህን ማንን ታደርጋለህ? አሉት።
፵፯ ኢየሱስም መለሰ አለም። እኔ ራሴን ባከብር ክብሬ ከንቱ ነው፤ የሚያከብረኝ እናንተ አምላካችን የምትሉት አባቴ ነው፤
፵፰ አላወቃችሁትምም፥ እኔ ግን አውቀዋለሁ። አላውቀውም ብል እንደ እናንተ ሐሰተኛ በሆንሁ፤ ዳሩ ግን አውቀዋለሁ ቃሉንም እጠብቃለሁ።
፵፱ አባታችሁ አብርሃም ቀኔን ያይ ዘንድ ሐሤት አደረገ፥ አየም ደሰም አለው።
፶ አይሁድም። ገና አምሳ ዓመት ያልሆነህ አብርሃምን አይተሃልን? አሉት።
፶፩ ኢየሱስም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ አላቸው።
፶፪ ስለዚህ ሊወግሩት ድንጋይ አነሡ፤ ኢየሱስ ግን ተሰወራቸው ከመቅደስም ወጥቶ በመካከላቸው አልፎ ሄደ።

፱

፩ ሲያልፍም ከመወለዱ ጀምሮ ዕውር የሆነውን ሰው አየ።
፪ ደቀ መዛሙርቱም። መምህር ሆይ፥ ይህ ሰው ዕውር ሆኖ እንዲወለድ ኃጢአት የሠራ ማን ነው? እርሱ ወይስ ወላጆቹ? ብለው ጠየቁት።
፫ ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰ። የእግዚአብሔር ሥራ በእርሱ እንዲገለጥ ነው እንጂ እርሱ ወይም ወላጆቹ ኃጢአት አልሠሩም።
፬ ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች።
፭ በዓለም ሳለሁ የዓለም ብርሃን ነኝ።
፮ ይህን ብሎ ወደ መሬት እንትፍ አለ በምራቁም ጭቃ አድርጎ በጭቃው የዕውሩን ዓይኖች ቀባና።
፯ ሂድና በሰሊሆም መጠመቂያ ታጠብ አለው፤ ትርጓሜው የተላከ ነው። ስለዚህ ሄዶ ታጠበ እያየም መጣ።
፰ ጐረቤቶቹም ቀድሞም ሲለምን አይተውት የነበሩ። ይህ ተቀምጦ ይለምን የነበረ አይደለምን? አሉ።
፱ ሌሎች። እርሱ ነው አሉ፤ ሌሎች። አይደለም እርሱን ይመስላል እንጂ አሉ፤ እርሱ። እኔ ነኝ አለ።
፲ ታድያ። ዓይኖችህ እንዴት ተከፈቱ? አሉት።
፲፩ እርሱ መልሶ። ኢየሱስ የሚባለው ሰው ጭቃ አድርጎ አይኖቼን ቀባና። ወደ ስሊሆም መጠመቂያ ሄደህ ታጠብ አለኝ፤ ሄጄ ታጥቤም አየሁ አለ።
፲፪ ያ ሰው ወዴት ነው? አሉት። አላውቅም አለ።
፲፫ በፊት ዕውር የነበረውን ሰው ወደ ፈሪሳውያን ወሰዱት።
፲፬ ኢየሱስም ጭቃ አድርጎ ዓይኖቹን የከፈተበት ቀን ሰንበት ነበረ።
፲፭ ስለዚህ ፈሪሳውያንም ደግሞ እንዴት እንዳየ እንደ ገና ጠየቁት። እርሱም። ጭቃ በዓይኖቼ አኖረ ታጠብሁም አያለሁም አላቸው።
፲፮ ከፈሪሳውያንም አንዳንዶቹ። ይህ ሰው ሰንበትን እያከብርምና ከእግዚአብሔር አይደለም አሉ። ሌሎች ግን። ኃጢአትኛ ሰው እንደነዚህ ያሉ ምልክቶች ሊያደርግ እንዴት ይችላል? አሉ።
፲፯ በመካከላቸውም መለያየት ሆነ። ከዚህም የተነሣ ዕውሩን። አንተ ዓይኖችህን ስለ ከፈተ ስለ እርሱ ምን ትላለህ? ደግሞ አሉት። እርሱም። ነቢይ ነው አለ።
፲፰ አይሁድ የዚያን ያየውን ወላጆች እስኪጠሩ ድረስ ዕውር እንደ ነበረ እንዳየም ስለ እርሱ አላመኑም፥
፲፱ እነርሱንም። እናንተ ዕውር ሆኖ ተወለደ የምትሉት ልጃችሁ ይህ ነውን? ታድያ አሁን እንዴት ያያል? ብለው ጠየቁአቸው።
፳ ወላጆቹም መልሰው። ይህ ልጃችን እንደ ሆነ ዕውርም ሆኖ እንደ ተወለደ እናውቃለን፤
፳፩ ዳሩ ግን አሁን እንዴት እንዳየ እናውቅም፥ ወይም ዓይኖቹን ማን እንደ ከፈተ እኛ አናውቅም፤ ጠይቁት እርሱ ሙሉ ሰው ነው፤ እርሱ ስለ ራሱ ይናገራል አሉ።

፳፪ ወላጆቹ እይሁድን ሰለ ፈሩ ይህን አሉ፤ እርሱ ክርስቶስ ነው ብሎ የሚመስክር ቢኖር ከምኩራብ እንዲያወጡት አይሁድ ከዚህ በፊት ተሰማምተው ነበርና።
፳፫ ሰለዚህ ወላጆቹ። ሙሉ ሰው ነው፥ ጠይቁት አሉ።
፳፬ ሰለዚህ ዕውር የነበረውን ሰው ሁለተኛ ጠርተው። እግዚአብሔርን አክብር፤ ይህ ሰው ኃጢአተኛ መሆኑን እኛ እናውቃለን አሉት።
፳፭ እርሱም መልሶ። ኃጢአተኛ መሆኑን አላውቅም፤ ዕውር እንደ ነበርሁ አሁንም እንዳይ ይህን አንድ ነገር አውቃለሁ አለ።
፳፮ ደግመውም። ምን አደረገልህ? እንዴትስ ዓይኖችህን ከፈተ? አሉት።
፳፯ እርሱም መልሶ። አሰቀድሜ ነገርኋችሁ አልሰማችሁምም፤ ሰለ ምን ዳግመኛ ልትሰሙ ትወዳላችሁ? እናንተ ደግሞ ደቀ መዛሙርቱ ልትሆኑ ትወዳላችሁን? አላቸው።
፳፰ ተሳድበውም። አንተ የእርሱ ደቀ መዝሙር ነህ፥ እኛ ግን የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን፤
፳፱ እግዚአብሔር ሙሴን እንደ ተናገረው እኛ እናውቃለን፥ ይህ ሰው ግን ከወዴት እንደ ሆነ አናውቅም አሉት።
፴ ሰውዬው መለሰ እንዲህም አላቸው። ከወዴት እንደ ሆነ እናንተ አለማወቃችሁ ይህ ድንቅ ነገር ነው፥ ዳሩ ግን ዓይኖቼን ከፈተ።
፴፩ እግዚአብሔርን የሚፈራ ፈቃዱንም የሚያደርግ ቢኖር ያንን እግዚአብሔር ይሰማዋል እንጂ ኃጢአተኞችን እንዳይሰማ እናውቃለን።
፴፪ ዕውር ሆኖ የተወለደውን ዓይኖች ማንም እንደ ከፈተ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ አልተሰማም፤
፴፫ ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ባይሆን ምንም ሊያደርግ ባልቻለም ነበር።
፴፬ መልሰው። አንተ ሁለንተናህ በኃጢአት ተወልድህ፥ አንተም እኛን ታሰተምረናለህን? አሉት። ወደ ውጭም አወጡት።
፴፭ ኢየሱሰም ወደ ውጭ እንዳወጡት ሰማ ሲያገኘውም። አንተ በእግዚአብሔር ልጅ ታምናለህን? አለው።
፴፮ እርሱም መልሶ። ጌታ ሆይ፥ በእርሱ አምን ዘንድ ማን ነው? አለ።
፴፯ ኢየሱሰም። አይተኸዋልም ከአንተ ጋርም የሚናገረው እርሱ ነው አለው።
፴፰ እርሱም። ጌታ ሆይ፥ አምናለሁ አለ፤ ሰገደለትም።
፴፱ ኢየሱሰም። የማያዩ እንዲያዩ የሚያዩም እንዲታወሩ እኔ ወደዚህ ዓለም ለፍርድ መጣሁ አለ።
፵ ከፈሪሳውያንም ከእርሱ ጋር የነበሩት ይህን ሰምተው። እኛ ደግሞ ዕውሮች ነንን? አሉት።
፵፩ ኢየሱሰም አላቸው። ዕውሮችሰ ብትሆኑ ኃጢአት ባልሆነባችሁም ነበር፤ አሁን ግን። እናያለን ትላላችሁ፤ ኃጢአታችሁ ይኖራል።

፲

፩ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ወደ በጎች በረት በበሩ የማይገባ በሌላ መንገድ ግን የሚወጣ እርሱ ሌባ ወንበዴም ነው፤
፪ በበሩ የሚገባ ግን የበጎች እረኛ ነው።
፫ ለእርሱ በረኛው ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰሙታል፥ የራሱንም በጎች በየሰማቸው ጠርቶ ይወሰዳቸዋል።
፬ የራሱንም ሁሉ ካወጣቸው በኋላ በፊታቸው ይሄዳል፥ በጎቹም ድምፁን ያውቃሉና ይከተሉታል፤
፭ ከሌላው ግን ይሸሻሉ እንጂ አይከተሉትም፥ የሌሎችን ድምፅ አያውቁምና።
፮ ኢየሱሰ ይህን ምሳሌ ነገራቸው፤ እነርሱ ግን የነገራቸው ምን እንደ ሆነ አላሰተዋሉም።
፯ ኢየሱሰም ደግሞ አላቸው። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እኔ የበጎች በር ነኝ።
፰ ከእኔ በፊት የመጡ ሁሉ ሌቦችና ወንበዴዎች ናቸው፤ ዳሩ ግን በጎቹ አልሰሙአቸውም።
፱ በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል፥ ይገባልም ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል።
፲ ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ሰለ ሌላ አይመጣም፤ እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ።
፲፩ መልካም እረኛ እኔ ነኝ። መልካም እረኛ ነፍሱን ሰለ በጎቹ ያኖራል።
፲፪ እረኛ ያልሆነው በጎቹም የእርሱ ያልሆኑ ሞያተኛ ግን ተኵላ ሲመጣ ባየ ጊዜ በጎቹን ትቶ ይሸሻል፤ ተኵላም ይነጥቃቸዋል በጎቹንም ይበትናቸዋል።
፲፫ ሞያተኛ ሰለ ሆነ ለበጎቹም ሰለማይገደው ሞያተኛው ይሸሻል።
፲፬-፲፭ ከዚህም በረት ያልሆኑ ሌሎች በጎች አሉኝ፤ እነርሱን ደግሞ ላመጣ ይገባኛል ድምፄንም ይሰማሉ፥ አንድም መንጋ ይሆናሉ እረኛውም አንድ።
፲፯ ነፍሴን ደግሞ አነሣት ዘንድ እኖራለሁና ሰለዚህ አብ ይወደኛል።
፲፰ እኔ በፈቃዴ እኖራታለሁ እንጂ ከእኔ ማንም አይወሰዳትም። ላኖራት ሥልጣን አለኝ ደግሞም ላነሣት ሥልጣን አለኝ ይህችን ትእዛዝ ከአባቴ ተቀበልሁ።
፲፱ እንግዲህ ከዚህ ቃል የተነሣ በአይሁድ መካከል እንደ ገና መለያየት ሆነ።
፳ ከእነርሱም ብዙዎች። ጋኔን አለበት አብዶአልም፤ ሰለ ምንስ ትሰሙታላችሁ? አሉ።
፳፩ ሌሎችም። ይህ ጋኔን ያለበት ሰው ቃል አይደለም፤ ጋኔን የዕውሮችን ዓይኖች ሊከፍት ይችላልን? አሉ።
፳፪ በኢየሩሳሌምም የመቅደስ መታደስ በዓል ሆነ፤
፳፫ ክረምትም ነበረ። ኢየሱሰም በመቅደስ በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ይመላለስ ነበር።
፳፬ አይሁድም እርሱን ከበው። እስከ መቼ ድረስ በጥርጣሪ ታቆየናለህ? አንተ ክርስቶስ እንደ ሆንህ ገልጠህ ንገረን አሉት።
፳፭ ኢየሱሰም መለሰላቸው፥ እንዲህ ሲል። ነገርኋችሁ አታምኑምም እኔ በአባቴ ሰም የማደርገው ሥራ ይህ ሰለ እኔ ይመሰክራል፤
፳፮ እናንተ ግን እንደ ነገርኋችሁ ከበጎቼ ሰላልሆናችሁ አታምኑም።
፳፯ በጎቼ ድምፄን ይሰማሉ እኔም አውቃቸዋለሁ ይከተሉኛማል፤

፳፯ እኔም የዘላለም ሕይወትን እሰጣቸዋለሁ፥ ለዘላለምም አይጠፉም፥ ከእጄም ማንም አይነጥቃቸውም።
፳፰ የሰጠኝ አባቴ ከሁሉ ይበልጣል፥ ከአባቴም እጅ ሊነጥቃቸው ማንም አይችልም።
፳፱ እኔና አብ አንድ ነን።
፴ አይሁድ ሊወግሩት ደግመው ድንጋይ አነሡ።
፴፩ ኢየሱስ። ከአባቴ ብዙ መልካም ሥራ አሳየኋችሁ፤ ከእነርሱ ስለ ማናቸው ሥራ ትወግሩኛላችሁ? ብሎ መለሰላቸው።
፴፪ አይሁድም። ስለ መልካም ሥራ አንወግርህም፤ ስለ ስድብ፤ አንተም ሰው ስትሆን ራስህን አምላክ ስለ ማድረግህ ነው እንጂ ብለው መለሱለት።
፴፫ ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። እኔ። አማልክት ናችሁ አልሁ ተብሎ በሕጋችሁ የተጻፈ አይደለምን?
፴፬ መጽሐፉ ሊሻር አይቻልምና እነዚያን የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸውን አማልክት ካላቸው፥
፴፭ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልሁ እናንተ አብ የቀደሰውን ወደ ዓለምም የላከውን። ትሳደባለህ ትሉታላችሁን?
፴፮ እኔ የአባቴን ሥራ ባላደርግ አትመኑኝ፤
፴፯ ባደርገው ግን፥ እኔን ሰንኳ ባታምኑ አብ በእኔ እንደ ሆነ እኔም በአብ እንደ ሆንሁ ታውቁና ታስተውሉ ዘንድ ሥራውን እመኑ።
፴፰ እንግዲህ ደግመው ሊይዙት ፈለጉ፤ ከእጃቸውም ወጣ።
፴፱ ዮሐንስም በመጀመሪያ ያጠምቅበት ወደ ነበረው ሰፍራ ወደ ዮርዳኖስ ማዶ እንደ ገና ሄደ በዚያም ኖረ።
፵ ብዙ ሰዎችም ወደ እርሱ መጥተው። ዮሐንስ አንድ ምልክት ሰንኳ አላደረገም፥ ነገር ግን ዮሐንስ ስለዚህ ሰው የተናገረው ሁሉ እውነት ነበረ አሉ።
፵፩ በዚያም ብዙዎች በእርሱ አመኑ።

፲፩

፩ ከማርያምና ከእኅትዋ ከማርታ መንደር ከቢታንያ የሆነ አልዓዛር የሚባል አንድ ሰው ታሞ ነበር።
፪ ማርያምም ጌታን ሽቱ የቀባችው እግሩንም በጠጕርዋ ያበሰችው ነበረች፤ ወንድምዋም አልዓዛር ታሞ ነበር።
፫ ስለዚህ እኅቶቹ ጌታ ሆይ፥ እነሆ የምትወደው ታሞአል ብለው ወደ እርሱ ላኩ።
፬ ኢየሱስም ሰምቶ። ይህ ህመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ስለ እግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም አለ።
፭ ኢየሱስም ማርታንና እኅትዋን አልዓዛርንም ይወድ ነበር።
፮ እንደ ታመመም በሰማ ጊዜ ያን ጊዜ በነበረበት ሰፍራ ሁለት ቀን ዋለ፤
፯ ከዚህም በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ። ወደ ይሁዳ ደግሞ እንሂድ አላቸው።
፰ ደቀ መዛሙርቱ። መምህር ሆይ፥ አይሁድ ከጥቂት ጊዜ በፊት ሊወግሩህ ይፈልጉ ነበር፥ ደግሞም ወደዚያ ትሄዳለህን? አሉት።
፱ ኢየሱስም መልሶ። ቀኑ አሥራ ሁለት ሰዓት አይደለምን? በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም፤
፲ በሌሊት የሚመላለስ ቢኖር ግን ብርሃን በእርሱ ስለ ሌለ ይሰናከላል አላቸው።
፲፩ ይህን ተናገረ፤ ከዚህም በኋላ። ወዳጃችን አልዓዛር ተኝቶአል፤ ነገር ግን ከእንቅልፉ ላሰነሣው እሄዳለሁ አላቸው።
፲፪ እንግዲህ ደቀ መዛሙርቱ። ጌታ ሆይ፥ ተኝቶ እንደ ሆነ ይድናል አሉት።
፲፫ ኢየሱስስ ስለ ሞቱ ተናግሮ ነበር፤ እነርሱ ግን ስለ እንቅልፍ መተኛት እንደ ተናገረ መሰላቸው።
፲፬ እንግዲህ ያን ጊዜ ኢየሱስ በግልጥ። አልዓዛር ሞተ፤
፲፭ እንድታምኑም በዚያ ባለመኖሬ ስለ እናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ወደ እርሱ እንሂድ አላቸው።
፲፮ ስለዚህ ዲዲሞስ የሚሉት ቶማስ ለባልንጀሮቹ ለደቀ መዛሙርት። ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እኛ ደግሞ እንሂድ አለ።
፲፯ ኢየሱስም በመጣ ጊዜ በመቃብር እሰከ አሁን አራት ቀን ሆኖት አገኘው።
፲፰ ቢታንያም አሥራ አምስት ምዕራፍ ያህል ለኢየሩሳሌም ቅርብ ነበረች።
፲፱ ከአይሁድም ብዙዎች ስለ ወንድማቸው ሊያጽናኑአቸው ወደ ማርታና ወደ ማርያም መጥተው ነበር።
፳ ማርታም ኢየሱስ እንደ መጣ በሰማች ጊዜ ልትቀበለው ወጣች፤ ማርያም ግን በቤት ተቀምጣ ነበር።
፳፩ ማርታም ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር፤
፳፪ አሁንም ከእግዚአብሔር የምትለምነውን ሁሉ እግዚአብሔር እንዲሰጥህ አውቃለሁ አለችው።
፳፫ ኢየሱስም። ወንድምሽ ይነሣል አላት።
፳፬ ማርታም። በመጨረሻው ቀን በትንሣኤ እንዲነሣ አውቃለሁ አለችው።
፳፭ ኢየሱስም። ትንሣኤና ሕይወት እኔ ነኝ፤ የሚያምንብኝ ቢሞት እንኳ ሕያው ይሆናል፤
፳፮ ሕያው የሆነም የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘላለም አይሞትም፤ ይህን ታምኚያለሽን? አላት።
፳፯ እርሰዋም። አዎን ጌታ ሆይ፤ አንተ ወደ ዓለም የሚመጣው ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ እኔ አምናለሁ አለችው።
፳፰ ይህንም ብላ ሄደች እኅትዋንም ማርያምን በሰውር ጠርታ። መምህሩ መጥቶአል ይጠራሽማል አለቻት።
፳፱ እርሰዋም በሰማች ጊዜ ፈጥና ተነሣች ወደ እርሱም መጣች፤
፴ ኢየሱስም ማርታ በተቀበለችበት ሰፍራ ነበረ እንጂ ገና ወደ መንደሩ አልገባም ነበር።
፴፩ ሲያጽናኑአት ከእርሰዋ ጋር በቤት የነበሩ አይሁድም ማርያም ፈጥና እንደ ተነሣችና እንደ ወጣች ባዩ ጊዜ፥ ወደ መቃብር ሄዳ በዚያ ልታለቅስ መሰሎአቸው ተከተሉአት።
፴፪ ማርያምም ኢየሱስ ወዳለበት መጥታ ባየችው ጊዜ በእግሩ ላይ ወድቃ። ጌታ ሆይ፥ አንተ በዚህ ኖረህ ብትሆን ወንድሜ ባልሞተም ነበር አለችው።

፶፫ ኢየሱሰም እርሰዋ ሰታለቅሰ ከእርሰዋም ጋር የመጡት አይሁድ ሲያለቅሱ አይቶ በመንፈሱ አዘነ በራሱም ታወከ፤
፶፬ ወዴት አኖራችሁት? አለም። እነርሱም። ጌታ ሆይ፥ መጥተህ እይ አሉት።
፶፭ ኢየሱሰም እንባውን አፈሰሰ።
፶፮ ሰለዚህ አይሁድ። እንዴት ይወደው እንደ ነበረ እዩ አሉ።
፶፯ ከእነርሱ ግን አንዳንዶቹ። ይህ የዕውሩን ዓይኖች የከፈተ ይህን ደግሞ እንዳይሞት ያደርግ ዘንድ ባልቻለም ነበርን? አሉ።
፶፰ ኢየሱሰም በራሱ አዝኖ ወደ መቃብሩ መጣ፤ እርሱም ዋሻ ነበረ፤ ድንጋይም ተገጥሞበት ነበር።
፶፱ ኢየሱሰ። ድንጋዩን አንሡ አለ። የሞተውም እኅት ማርታ። ጌታ ሆይ፥ ከሞተ አራት ቀን ሆኖታልና አሁን ይሸታል አለችው።
፷ ኢየሱሰ። ብታምኚሰ የእግዚአብሔርን ክብር እንድታዪ አልነገርሁሽምን? አላት።
፷፩ ድንጋዩንም አነሡት። ኢየሱሰም ዓይኖቹን ወደ ላይ አንሥቶ። አባት ሆይ፥ ሰለ ሰማኸኝ አመሰግንሃለሁ።
፷፪ ሁልጊዜም እንድትሰማኝ አወቅሁ፤ ነገር ግን አንተ እንደ ላክኸኝ ያምኑ ዘንድ በዚህ ዙሪያ ሰለ ቆሙት ሕዝብ ተናገርሁ አለ።
፷፫ ይህንም ብሎ በታላቅ ድምፅ። አልዓዛር ሆይ፥ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ።
፷፬ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደ ተገነዙ ወጣ፤ ፊቱም በጨርቅ እንደ ተጠመጠመ ነበር። ኢየሱሰም። ፍቱትና ይሂድ ተዉት አላቸው።
፷፭ ሰለዚህ ወደ ማርያም ከመጡት፥ ኢየሱሰም ያደረገውን ካዩት ከአይሁድ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤
፷፮ ከእነርሱ አንዳንዶቹ ግን ወደ ፈሪሳውያን ሄደው ኢየሱሰ ያደረገውን ነገሩአቸው።
፷፯ እንግዲህ የካህናት አለቆችና ፈሪሳውያን ሸንጎ ሰብሰበው። ምን እናድርግ? ይህ ሰው ብዙ ምልክቶች ያደርጋልና።
፷፰ እንዲሁ ብንተወው ሁሉ በእርሱ ያምናሉ፤ የሮሜም ሰዎች መጥተው አገራችንን ወገናችንንም ይወሰዳሉ አሉ።
፷፱ በዚያችም ዓመት ሊቀ ካህናት የነበረ ቀያፋ የሚሉት ከእነርሱ አንዱ። እናንተ ምንም አታውቁም፤
፸ ሕዝቡም ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ሰለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ እንዲሻለን አታሰቡም አላቸው።
፸፩ ይህንም የተናገረ ከራሱ አይደለም፥ ነገር ግን በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ነበረና ኢየሱሰ ሰለ ሕዝቡ ሊሞት እንዳለው ትንቢት ተናገረ፤
፸፪ ሰለ ሕዝቡም ሁሉ አይደለም፥ ነገር ግን የተበተኑትን የእግዚአብሔርን ልጆች ደግሞ በአንድነት እንዲሰበሰባቸው ነው እንጂ።
፸፫ እንግዲህ ከዚያ ቀን ጀምረው ሊገድሉት ተማከሩ።
፸፬ ከዚያ ወዲያም ኢየሱሰ በአይሁድ መካከል ተገለጦ አልተመላለሰም፤ ነገር ግን ከዚያ በምድረ በዳ አጠገብ ወዳለች ምድር፥ ኤፍሬም ወደምትባል ከተማ ሄደ፤ በዚያም ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ተቀመጠ።
፸፭ የአይሁድም ፋሲካ ቀርቦ ነበር። ብዙ ሰዎችም ራሳቸውን ያነጹ ዘንድ ከፋሲካ በፊት ከአገሩ ወደ ኢየሩሳሌም ወጡ።
፸፮ ኢየሱሰንም ይፈልጉት ነበር፤ በመቅደሰም ቆመው እርስ በርሳቸው። ምን ይመሰላችኋል? ወደ በዓሉ አይመጣም ይሆንን? ተባባሉ።
፸፯ የካህናት አለቆችም ፈሪሳውያንም ይይዙት ዘንድ እርሱ ያለበትን ሰፍራ የሚያውቀው ሰው ቢኖር እንዲያመለክታቸው አዘው ነበር።

፲፪

፩ ከፋሲካም በፊት በሰድሰተኛው ቀን ኢየሱሰ ከሙታን ያሰነሣው አልዓዛር ወደ ነበረበት ወደ ቢታንያ መጣ።
፪ በዚያም እራት አደረጉለት፤ ማርታም ታገለግል ነበር፤ አልዓዛር ግን ከእርሱ ጋር ከተቀመጡት አንዱ ነበረ።
፫ ማርያምም ዋጋው እጅግ የከበረ የጥሩ ናርዶስ ሽቱ ንጥር ወሰዳ የኢየሱሰን እግር ቀባች፤ በጠጕርዋም እግሩን አበሰች፤ ቤቱም ከናርዶስ ሽቱ ሞላ።
፬ ነገር ግን ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ አሳልፎ ሊሰጠው ያለው የሰምዖን ልጅ የአስቆሮቱ ይሁዳ።
፭ ይህ ሽቱ ለሦስት መቶ ዲናር ተሸጦ ለድሆች ያልተሰጠ ሰለ ምን ነው? አለ።
፮ ይህንም የተናገረ ሌባ ሰለ ነበረ ነው እንጂ ለድሆች ተገድዶላቸው አይደለም፤ ከረጢትም ይዞ በውሰጡ ከሚገባው ይወሰድ ሰለ ነበረ ነው።
፯ ኢየሱሰም። ለምቀበርበት ቀን እንድትጠብቀው ተውአት፤
፰ ድሆችሰ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ይኖራሉና፥ እኔ ግን ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር አልኖርም አለ።
፱ ከአይሁድም ብዙ ሕዝብ በዚያ እንደ ነበረ አውቀው መጡ፥ ከሙታንም ያሰነሣውን አልዓዛርን ደግሞ እንዲያዩ ነበረ እንጂ ሰለ ኢየሱሰ ብቻ አይደለም።
፲ የካህናት አለቆችም አልዓዛርን ደግሞ ሊገድሉት ተማከሩ፥
፲፩ ከአይሁድ ብዙዎች ከእርሱ የተነሣ ሄደው በኢየሱሰ ያምኑ ነበርና።
፲፪ በማግሥቱ ወደ በዓሉ መጥተው የነበሩ ብዙ ሕዝብ ኢየሱሰ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲመጣ በሰሙ ጊዜ፥
፲፫ የዘንባባ ዛፍ ዝንጣፊ ይዘው ሊቀበሉት ወጡና። ሆሣዕና፤ በጌታ ሰም የሚመጣ የእሰራኤል ንጉሥ የተባረከ ነው እያሉ ጮኹ።
፲፬-፲፭ ደቀ መዛሙርቱም ይህን ነገር በመጀመሪያ አላሰተዋሉም፤ ነገር ግን ኢየሱሰ ከከበረ በኋላ በዚያን ጊዜ ይህ ሰለ እርሱ እንደ ተጻፈ ይህንም እንዳደረጉለት ትዝ አላቸው።
፲፮ አልዓዛርንም ከመቃብር ጠርቶ ከሙታን ሲያሰነሣው ከእርሱ ጋር የነበሩት ሕዝብ ይመሰክሩለት ነበር።
፲፯ ሰለዚህ ደግሞ ሕዝቡ ይህን ምልክት እንዳደረገ ሰለ ሰሙ ሊቀበሉት ወጡ።
፲፰ ሰለዚህ ፈሪሳውያን እርስ በርሳቸው። እንድ ሰንኳ ልታደርጉ እንዳይቻላችሁ ታያላችሁን? እነሆ፥ ዓለሙ በኋላው ተከትሎት ሄዶአል ተባባሉ።
፲፱ በበዓሉም ሊሰግዱ ከወጡት አንዳንዶቹ የግሪክ ሰዎች ነበሩ፤

፳፩ እነርሱም ከገሊላ ቤተ ሳይዳ ወደሚሆን ወደ ፊልጶስ መጥተው። ጌታ ሆይ፥ ኢየሱስን ልናይ እንወዳለን ብለው ለመኑት።
፳፪ ፊልጶስም መጥቶ ለእንድርያስ ነገረው፤ እንድርያስና ፊልጶስ መጥተው ለኢየሱስ ነገሩት።
፳፫ ኢየሱስም መለሰላቸው፥ እንዲህ ሲል። የሰው ልጅ ይከብር ዘንድ ሰዓቱ ደርሶአል።
፳፬ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች፤ ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።
፳፭ ነፍሱን የሚወድ ያጠፋታል፥ ነፍሱንም በዚህ ዓለም የሚጠላ ለዘላለም ሕይወት ይጠብቃታል።
፳፮ የሚያገለግለኝ ቢኖር ይከተለኝ፥ እኔም ባለሁበት አገልጋዬ ደግሞ በዚያ ይሆናል፤ የሚያገለግለኝም ቢኖር አብ ያከብረዋል።
፳፯ አሁን ነፍሴ ታውካለች ምንስ እላለሁ? አባት ሆይ፥ ከዚህ ሰዓት አድነኝ። ነገር ግን ስለዚህ ወደዚህ ሰዓት መጣሁ።
፳፰ አባት ሆይ፥ ስምህን አክብረው። ስለዚህም። እከበርሁት ደግሞም አከብረዋለሁ የሚል ድምፅ ከሰማይ መጣ።
፳፱ በዚያ ቆመው የነበሩትም ሕዝብ በሰሙ ጊዜ። ነጐድጓድ ነው አሉ፤ ሌሎች። መልአክ ተናገረው አሉ።
፴ ኢየሱስም መለሰ፥ እንዲህ ሲል። ይህ ድምፅ ስለ እናንተ መጥቶአል እንጂ ስለ እኔ አይደለም።
፴፩ አሁን የዚህ ዓለም ፍርድ ደርሶአል፤ አሁን የዚህ ዓለም ገዥ ወደ ውጭ ይጣላል፤
፴፪ እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ያልሁ እንደ ሆነ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ።
፴፫ በምን ዓይነትም ሞት ይሞት ዘንድ እንዳለው ሲያመለክታቸው ይህን ተናገረ።
፴፬ እንግዲህ ሕዝቡ። እኛስ ክርስቶስ ለዘላለም እንዲኖር ከሕጉ ሰምተናል፤ አንተስ የሰው ልጅ ከፍ ከፍ ይል ዘንድ እንዲያስፈልገው እንዴት ትላላህ? ይህ የሰው ልጅ ማን ነው? ብለው መለሱለት።
፴፭ ኢየሱስም። ገና ጥቂት ጊዜ ብርሃን ከእናንተ ጋር ነው። ጨለማ እንዳይደርስባችሁ ብርሃን ሳለላችሁ ተመላለሱ፤ በጨለማም የሚመላለስ ወዴት እንዲሄድ አያውቅም።
፴፮ የብርሃን ልጆች እንድትሆኑ ብርሃን ሳለላችሁ በብርሃኑ እመኑ አላቸው። ኢየሱስም ይህን ተናግሮ ሄደና ተሰወረባቸው።
፴፯-፴፰ ክብሩን ስለ አየ ኢሳይያስ ይህን አለ፥ ስለ እርሱም ተናገረ።
፴፱ ከዚህም ጋር ከአለቆች ደግሞ ብዙዎች በእርሱ አመኑ፤ ነገር ግን ከምኩራብ እንዳያስወጡአቸው በፈሪሳውያን ምክንያት አልመሰከሩለትም፤
፵፫ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የሰውን ክብር ወደዋልና።
፵፬ ኢየሱስም ጮኸ፥ እንዲህም አለ። በእኔ የሚያምን በላከኝ ማመኑ ነው እንጂ በእኔ አይደለም፤
፵፭ እኔንም የሚያይ የላከኝን ያያል።
፵፮ በእኔ የሚያምን ሁሉ በጨለማ እንዳይኖር እኔ ብርሃን ሆኜ ወደ ዓለም መጥቻለሁ።
፵፯ ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም።
፵፰ የሚጥለኝ ቃሌንም የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርሁት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።
፵፱ እኔ ከራሴ አልተናገርሁምና፤ ነገር ግን የላከኝ አብ እርሱ የምለውን የምናገረውንም ትእዛዝ ሰጠኝ።
፶ ትእዛዙም የዘላለም ሕይወት እንደ ሆነች አውቃለሁ። ስለዚህ እኔ የምናገረውን አብ እንደ ነገረኝ እንዲሁ እናገራለሁ።

፲፫

፩ ኢየሱስም ከፋሲካ በዓል በፊት፥ ከዚህ ዓለም ወደ አብ የሚሄድበት ሰዓት እንደ ደረሰ አውቆ፥ በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከ መጨረሻ ወደዳቸው።
፪ እራትም ሲበሉ ዲያብሎስ በሰምዖን ልጅ በአስቆሮቱ በይሁዳ ልብ አሳልፎ እንዲሰጠው አሳብ ካገባ በኋላ፥
፫ ኢየሱስ አብ ሁሉን በልጁ እንደ ሰጠው ከእግዚአብሔርም እንደ ወጣ ወደ እግዚአብሔርም እንዲሄድ አውቆ፥
፬ ከእራት ተነሣ ልብሱንም አኖረ፥ ማበሻም ጨርቅ ወሰደ ታጠቀ፤
፭ በኋላም በመታጠቢያው ውኃ ጨመረ፥ የደቀ መዛሙርቱንም እግር ሊያጥብና በታጠቀበትም ማበሻ ጨርቅ ሊያብስ ጀመረ።
፮ ወደ ስምዖን ጴጥሮስም መጣ፤ እርሱም። ጌታ ሆይ፥ አንተ የእኔን እግር ታጥባለህን? አለው።
፯ ኢየሱስም መልሶ። እኔ የማደርገውን አንተ አሁን አታውቅም፥ በኋላ ግን ታስተውለዋለህ አለው።
፰ ጴጥሮስም። የእኔን እግር ለዘላለም አታጥብም አለው። ኢየሱስም። ካላጠብሁህ፥ ከእኔ ጋር ዕድል የለህም ብሎ መለሰለት።
፱ ስምዖን ጴጥሮስም። ጌታ ሆይ፥ እጄንና ራሴን ደግሞ እንጂ እግሬን ብቻ አይደለም አለው።
፲ ኢየሱስም። የታጠበ እግሩን ከመታጠብ በቀር ሌላ አያስፈልገውም፥ ሁለንተናው ግን ንጹሕ ነው፤ እናንተም ንጹሐን ናችሁ፥ ነገር ግን ሁላችሁ አይደላችሁም አለው።
፲፩ አሳልፎ የሚሰጠውን ያውቅ ነበርና፤ ስለዚህ። ሁላችሁ ንጹሐን አይደላችሁም አለው።
፲፪ እግራቸውንም አጥቦ ልብሱንም አንሥቶ ዳግመኛ ተቀመጠ፥ እንዲህም አላቸው። ያደረግሁላችሁን ታስተውላላችሁን?
፲፫ እናንተ መምህርና ጌታ ትሉኛላችሁ፤ እንዲሁ ነኝና መልካም ትላላችሁ።
፲፬ እንግዲህ እኔ ጌታና መምህር ሰሆን እግራችሁን ካጠብሁ፥ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ እግራችሁን ትተጣጠቡ ዘንድ ይገባችኋል።
፲፭ እኔ ለእናንተ እንዳደረግሁ እናንተ ደግሞ ታደርጉ ዘንድ ምሳሌ ሰጥቻችኋለሁና።
፲፮ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ባሪያ ከጌታው አይበልጥም። መልእክተኛም ከላከው አይበልጥም።
፲፯ ይህን ብታውቁ፥ ብታደርጉትም ብፁዓን ናችሁ።
፲፰ ስለ ሁላችሁ አልናገርም፤ እኔ የመረጥኋቸውን አውቃለሁ፤ ነገር ግን መጽሐፍ። እንጀራዬን የሚበላ በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣብኝ ያለው ይፈጸም ዘንድ ነው።

፲፱ በሆነ ጊዜ እኔ እንደ ሆንሁ ታምኑ ዘንድ፥ ከአሁን ጀምሬ አሰቀድሞ ሳይሆን እነግራችኋለሁ።
፳ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ማናቸውን የምልከውን የሚቀበል እኔን ይቀበላል፥ እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል።
፳፩ ኢየሱስ ይህን ብሎ በመንፈሱ ታወከ መሰክሮም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ከእናንተ አንዱ አሳልፎ ይሰጠኛል አለ።
፳፪ ደቀ መዛሙርቱ ሰለ ማን እንደ ተናገረ አመንትተው እርስ በርሳቸው ተያዩ።
፳፫ ኢየሱስም ይወደው የነበረ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ በኢየሱስ ደረት ላይ ተጠጋ፤
፳፬ ሰለዚህ ሰምዖን ጴጥሮስ እርሱን ጠቅሶ። ሰለማን እንደ ተናገረ ንገረን አለው።
፳፭ እርሱም በኢየሱስ ደረት እንዲህ ተጠግቶ። ጌታ ሆይ፥ ማን ነው? አለው።
፳፮ ኢየሱስም። እኔ ቍራሽ እጥቅሼ የምሰጠው እርሱ ነው ብሎ መለሰለት። ቍራሽም እጥቅሶ ለአስቆሮቱ ለሰምዖን ልጅ ለይሁዳ ሰጠው።
፳፯ ቍራሽም ከተቀበለ በኋላ ያን ጊዜ ሰይጣን ገባበት። እንግዲህ ኢየሱስ። የምታደርገውን ቶሎ ብለህ አድርግ አለው።
፳፰ ነገር ግን ከተቀመጡት ሰለ ምን ይህን እንዳለው ማንም አላወቀም፤
፳፱ ይሁዳ ከረጢቱን የያዘ ሰለ ሆነ፥ ኢየሱስ። ለበዓሉ የሚያሰፈልገንን ግዛ፥ ወይም ለድሆች ምጽዋት እንዲሰጥ ያለው ለአንዳንዱ መሰሎአቸው ነበርና።
፴ እርሱም ቍራሹን ከተቀበለ በኋላ ወዲያው ወጣ፤ ሌሊትም ነበረ።
፴፩ ከወጣም በኋላ ኢየሱስ እንዲ አለ። አሁን የሰው ልጅ ከበረ እግዚአብሔርም ሰለ እርሱ ከበረ፤
፴፪ እግዚአብሔር ሰለ እርሱ የከበረ ከሆነ፥ እግዚአብሔር ደግሞ እርሱን ራሱን ያከብረዋል ወዲያውም ያከብረዋል።
፴፫ ልጆች ሆይ፥ ገና ጥቂት ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፤ ትፈልጉኛላችሁ፤ ለአይሁድም። እኔ ወደምሄድበት እናንተ ልትመጡ አይቻላችሁም እንዳልኋቸው፥ አሁን ለእናንተ ደግሞ እላችኋለሁ።
፴፬ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።
፴፭ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።
፴፮ ሰምዖን ጴጥሮስም። ጌታ ሆይ፥ ወዴት ትሄዳለህ? አለው። ኢየሱስም። ወደምሄድበት አሁን ልትከተለኝ አትችልም፥ ነገር ግን በኋላ ትከተለኛለህ ብሎ መለሰለት።
፴፯ ጴጥሮስም። ጌታ ሆይ፥ አሁን ልከተልህ አለመቻሌ ሰለ ምንድር ነው? ነፍሴን ስንኳ ሰለ አንተ እሰጣለሁ አለው።
፴፰ ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰለት። ነፍስህን ሰለ እኔ ትሰጣለህን? እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሦስት ጊዜ እስክትክደኝ ድረስ ዶሮ አይጮኽም።

፲፬

፩ ልባችሁ አይታወክ፤ በእግዚአብሔር እመኑ፥ በእኔም ደግሞ እመኑ።
፪ በአባቴ ቤት ብዙ መኖሪያ አለ፤ እንዲህስ ባይሆን ባልኋችሁ ነበር፤ ሰፍራ አዘጋጅላችሁ ዘንድ እሄዳለሁና፤
፫ ሄጄም ሰፍራ ባዘጋጅላችሁ፥ እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ ወደ እኔም እወሰዳችኋለሁ።
፬ ወደምሄድበትም ታውቃላችሁ፥ መንገዱንም ታውቃላችሁ።
፭ ቶማስም። ጌታ ሆይ፥ ወደምትሄድበት አናውቅም፤ እንዴትስ መንገዱን እናውቃለን? አለው።
፮ ኢየሱስም። እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም።
፯ እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር። ከአሁንም ጀምራችሁ ታውቁታላችሁ አይታችሁትማል አለው።
፰ ፊልጶስ። ጌታ ሆይ፥ አብን አሳየንና ይበቃናል አለው።
፱ ኢየሱስም አለው። እንተ ፊልጶስ፥ ይህን ያህል ዘመን ከእናንተ ጋር ሰኖር አታውቀኝምን? እኔን ያየ አብን አይቶአል፤ እንዴትስ አንተ። አብን አሳየን ትላለህ?
፲ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ አታምንምን? እኔ የምነግራችሁን ቃል ከራሴ አልናገረውም፤ ነገር ግን በእኔ የሚኖረው አብ እርሱ ሥራውን ይሠራል።
፲፩ እኔ በአብ እንዳለሁ አብም በእኔ እንዳለ እመኑኝ፤ ባይሆንስ ሰለ ራሱ ሰለ ሥራው እመኑኝ።
፲፪ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፤ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል፥
፲፫ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፤ አብም ሰለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ እደርገዋለሁ።
፲፬ ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ እደርገዋለሁ።
፲፭-፲፯ እርሱም ዓለም የማያየውና የማያውቀው ሰለ ሆነ ሊቀበለው የማይቻለው የእውነት መንፈስ ነው፤ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ ሰለሚኖር በውሥጣችሁም ሰለሚሆን እናንተ ታውቃላችሁ።
፲፰ ወላጆች እንደ ሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም፤ ወደ እናንተ እመጣለሁ።
፲፱ ገና ጥቂት ዘመን አለ ከዚህም በኋላ ዓለም አያየኝም፤ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፤ እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ።
፳ እኔ በአባቴ እንዳለሁ እናንተም በእኔ እንዳላችሁ እኔም በእናንተ እንዳለሁ በዚያን ቀን ታውቃላችሁ።
፳፩ ትእዛዜ በእርሱ ዘንድ ያለችው የሚጠብቃትም የሚወደኝ እርሱ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል እኔም እወደዋለሁ ራሴንም እገልጥለታለሁ።
፳፪ የአስቆሮቱ ያይደለ ይሁዳ። ጌታ ሆይ፥ ለዓለም ሳይሆን ራስህን ለእኛ ልትገልጥ ያለህ እንዴት ነው? አለው።
፳፫ ኢየሱስም መለሰ አለውም። የሚወደኝ ቢኖር ቃሌን ይጠብቃል፤ አባቴም ይወደዋል ወደ እርሱም እንመጣለን በእርሱም ዘንድ መኖሪያ እናደርጋለን።
፳፬ የማይወደኝ ቃሌን አይጠብቅም፤ የምትሰሙትም ቃል የላከኝ የአብ ነው እንጂ የእኔ አይደለም።
፳፭ ከእናንተ ዘንድ ሰኖር ይህን ነግሬአችኋለሁ፤

፳፯ አብ በስሜ የሚልከው ግን መንፈስ ቅዱስ
የሆነው አጽናኝ እርሱ ሁሉን ያስተምራችኋል እኔም
የነገርኋችሁን ሁሉ ያሳስባችኋል።
፳፰ ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤
እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም።
ልባችሁ አይታወክ አይፍራም።
፳፱ እኔ እሄዳለሁ ወደ እናንተም እመጣለሁ
እንዳልኋችሁ ሰማችሁ። የምትወዱኝስ ብትሆኑ ከእኔ
አብ ይበልጣልና ወደ አብ በመሄዴ ደስ ባላችሁ ነበር።
፴ ከሆነም በኋላ ታምኑ ዘንድ አሁን አስቀድሞ
ሳይሆን። ነግሬአችኋለሁ።
፴፩ ከእንግዲህ ወዲህ ከእናንተ ጋር ብዙ አልናገርም፥
የዚህ ዓለም ገዥ ይመጣልና፤ በእኔ ላይም አንዳች
የለውም፤
፴፪ ነገር ግን አብን እንድወድ ዓለም ሊያውቅ፥
አብም እንዳዘዘኝ፥ እንዲሁ አደርጋለሁ። ተነሡ፤ ከዚህ
እንሂድ።

፲፭

፩ እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ፤ ገበሬውም አባቴ
ነው።
፪ ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ
ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ
እንዲያፈራ ያጠራዋል።
፫ እናንተ ስለ ነገርኋችሁ ቃል አሁን ንጹሐን ናችሁ፤
፬ በእኔ ኑሩ እኔም በእናንተ። ቅርንጫፍ በወይኑ
ግንድ ባይኖር ከራሱ ፍሬ ሊያፈራ እንዳይቻለው፥
እንዲሁ እናንተ ደግሞ በእኔ ባትኖሩ አትችሉም።
፭ እኔ የወይን ግንድ ነኝ እናንተም ቅርንጫፎች
ናችሁ። ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና በእኔ
የሚኖር እኔም በእርሱ፥ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል።
፮ በእኔ የማይኖር ቢሆን እንደ ቅርንጫፍ ወደ ውጭ
ይጣላል ይደርቅማል፤ እነርሱንም ሰብስበው ወደ እሳት
ይጥሉአቸዋል፥ ያቃጥሉአቸውማል።
፯ በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ
የምትወዱትን ሁሉ ለምኑ ይሆንላችሁማል።
፰ ብዙ ፍሬ ብታፈሩና ደቀ መዛሙርቴ ብትሆኑ በዚህ
አባቴ ይከበራል።
፱ አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፤ በፍቅሬ
ኑሩ።
፲ እኔ የአባቴን ትእዛዝ እንደ ጠበቅሁ በፍቅሩም
እንደምኖር፥ ትእዛዜን ብትጠብቁ በፍቅሬ ትኖራላችሁ።
፲፩ ደስታዬም በእናንተ እንዲሆን ደስታችሁም
እንዲፈጸም ይህን ነግሬአችኋለሁ።
፲፪ እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ
ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት።
፲፫ ነፍሱን ስለ ወዳጆቹ ከመሰጠት ይልቅ ከዚህ
የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም።
፲፬ እኔ ያዘዝኋችሁን ሁሉ ብታደርጉ እናንተ ወዳጆቼ
ናችሁ።
፲፭ ከእንግዲህ ወዲህ ባሮች አልላችሁም፤ ባርያ
ጌታው የሚያደርገውን አያውቅምና፤ ወዳጆች ግን
ብያችኋለሁ፥ ከአባቴ የሰማሁትን ሁሉ ለእናንተ
አስታውቄአችኋለሁና።
፲፮ እኔ መረጥኋችሁ እንጂ እናንተ
አልመረጣችሁኝም፤ አብም በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ
እንዲሰጣችሁ፥ ልትሄዱና ፍሬ ልታፈሩ ፍሬአችሁም
ሊኖር ሾምኋችሁ።
፲፯ እርስ በርሳችሁ እንድትዋደዱ ይህን አዛችኋለሁ።
፲፰ ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ
ጠላኝ እወቁ።
፲፱ ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ
ነበር፤ ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ
ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል።
፳ ባርያ ከጌታው አይበልጥም ብዬ የነገርኋችሁን
ቃል አስቡ። እኔን አሳደውኝ እንደ ሆኑ እናንተን ደግሞ
ያሳድዱአችኋል፤ ቃሌን ጠብቀው እንደ ሆኑ ቃላችሁን
ደግሞ ይጠብቃሉ።
፳፩ ዳሩ ግን የላከኝን አያውቁምና ይህን ሁሉ ስለ
ስሜ ያደርጉባችኋል።
፳፪ እኔ መጥቼ ባልነገርኋቸውስ ኃጢአት
ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን ለኃጢአታቸው
ምክንያት የላቸውም።
፳፫ እኔን የሚጠላ አባቴን ደግሞ ይጠላል።
፳፬ ሌላ ሰው ያላደረገውን ሥራ በመካከላቸው
ባላደረግሁ፥ ኃጢአት ባልሆነባቸውም ነበር፤ አሁን ግን
እኔንም አባቴንም አይተውማል ጠልተውማል።
፳፭ ነገር ግን በሕጋቸው። በከንቱ ጠሉኝ ተብሎ
የተጻፈው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፳፮ ዳሩ ግን እኔ ከአብ ዘንድ የምልክላችሁ አጽናኝ
እርሱም ከአብ የሚወጣ የእውነት መንፈስ በመጣ
ጊዜ፥ እርሱ ስለ እኔ ይመሰክራል፤
፳፯ እናንተም ደግሞ ከመጀመሪያ ከእኔ ጋር
ኖራችኋልና ትመሰክራላችሁ።

፲፮

፩ እንዳትሰናከሉ ይህን ተናግሬአችኋለሁ።
፪ ከምኩራባቸው ያወጡአችኋል፤ ከዚህ
በላይ ደግሞ የሚገድላችሁ ሁሉ እግዚአብሔርን
እንደሚያገለግል የሚመሰልበት ጊዜ ይመጣል።
፫ ይህንም የሚያደርጉባችሁ አብንና እኔን ስላላወቁ
ነው።
፬ ነገር ግን ጊዜው ሲደርስ እኔ እንደ ነገርኋችሁ
ታስቡ ዘንድ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። ከእንናንተም ጋር
ስለ ነበርሁ በመጀመሪያ ይህን አልነገርኋችሁም።
፭ አሁን ግን ወደ ላከኝ እሄዳለሁ ከእናንተም። ወዴት
ትሄዳለህ? ብሎ የሚጠይቀኝ የለም።
፮ ነገር ግን ይህን ስለ ተናገርኋችሁ ኀዘን በልባችሁ
ሞልቶአል።
፯ እኔ ግን እውነት እነግራችኋለሁ፤ እኔ እንድሄድ
ይሻላችኋል። እኔ ባልሄድ አጽናኙ ወደ እናንተ
አይመጣምና፤ እኔ ብሄድ ግን እርሱን እልክላችኋለሁ።
፰ እርሱም መጥቶ ስለ ኃጢአት ስለ ጽድቅም ስለ
ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤
፱-፲፩ ስለ ፍርድም፥ የዚህ ዓለም ገዥ ስለ
ተፈረደበት ነው።
፲፪ የምነግራችሁ ገና ብዙ አለኝ፥ ነገር ግን አሁን
ልትሸከሙት አትችሉም።
፲፫ ግን እርሱ የእውነት መንፈስ በመጣ ጊዜ
ወደ እውነት ሁሉ ይመራችኋል፤ የሚሰማውን ሁሉ
ይናገራል እንጂ ከራሱ አይነግርምና፤ የሚመጣውንም
ይነግራችኋል።

፲፩ እርሱ ያከብረኛል፥ ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋልና።
፲፬ ለአብ ያለው ሁሉ የእኔ ነው፤ ስለዚህ። ለእኔ ካለኝ ወስዶ ይነግራችኋል አልሁ።
፲፮ ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፥ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና።
፲፯ ከደቀ መዛሙርቱም አንዳንዶቹ እርስ በርሳቸው። ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁም፤ ደግሞ። ወደ አብ እሄዳለሁና የሚለን ይህ ምንድር ነው? ተባባሉ።
፲፰ እንግዲህ። ጥቂት የሚለው ይህ ምንድር ነው? የሚናገረውን እናውቅም አሉ።
፲፱ ኢየሱስም ሊጠይቁት እንደ ወደዱ አውቆ እንዲህ አላቸው። ጥቂት ጊዜ አለ፥ አታዩኝምም፤ ደግሞም ጥቂት ጊዜ አለ፥ ታዩኛላችሁ ስላልሁ፥ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ ትመራመራላችሁን?
፳ እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ እናንተ ታለቅሳለችሁ ሙሾም ታወጣላችሁ፥ ዓለም ግን ደስ ይለዋል፤ እናንተም ታዝናላችሁ፥ ነገር ግን ኀዘናችሁ ወደ ደስታ ይለወጣል።
፳፩ ሴት በምትወልድበት ጊዜ ወራትዋ ስለ ደረሰ ታዝናለች፤ ነገር ግን ሕፃን ከወለደች በኋላ፥ ሰው በዓለም ተወልዶአልና ስለ ደስታዋ መከራዋን ኋላ አታስበውም።
፳፪ እንግዲህ እናንተ ደግሞ አሁን ታዝናላችሁ፤ ነገር ግን እንደ ገና አያችኋለሁ ልባችሁም ደስ ይለዋል፥ ደስታችሁንም የሚወስድባችሁ የለም።
፳፫ በዚያን ቀንም ከእኔ አንዳች አትለምኑም። እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ አብ በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ ይሰጣችኋል።
፳፬ እስከ አሁን በስሜ ምንም አልለመናችሁም፤ ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ለምኑ ትቀበሉማላችሁ።
፳፭ ይህን በምሳሌ ነግሬአችኋለሁ፤ ነገር ግን ስለ አብ ለእናንተ በግልጥ የምናገርበት እንጂ ከዚያ ወዲያ በምሳሌ የማልናገርበት ሰዓት ይመጣል።
፳፮ በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ፤ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም፤
፳፯ እናንተ ስለ ወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደ ወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና።
፳፰ ከአብ ወጥቼ ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ደግሞ ዓለምን እተወዋለሁ ወደ አብም እሄዳለሁ።
፳፱ ደቀ መዛሙርቱ። እነሆ፥ አሁን በግልጥ ትናገራለህ በምሳሌም ምንም አትነግርም።
፴ ሁሉን እንድታውቅ ማንምም ሊጠይቅህ እንዳትፈልግ አሁን እናውቃለን፤ ስለዚህ ከእግዚአብሔር እንደ ወጣህ እናምናለን አሉት።
፴፩ ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው። አሁን ታምናላችሁን?
፴፪ እነሆ፥ እያንዳንዳችሁ ወደ ቤት የምትበታተኑበት እኔንም ለብቻዬ የምትተዉበት ሰዓት ይመጣል፥ አሁንም ደርሶአል፤ ነገር ግን አብ ከእኔ ጋር ስለ ሆነ ብቻዬን አይደለሁም።
፴፫ በእኔ ሳላችሁ ሰላም እንዲሆንላችሁ ይህን ተናግሬአችኋለሁ። በዓለም ሳላችሁ መከራ አለባችሁ፤ ነገር ግን አይዞአችሁ፤ እኔ ዓለምን አሸንፌዋለሁ።

፲፯

፩-፫ እውነተኛ አምላክ ብቻ የሆንህ አንተን የላክኸውንም ኢየሱስ ክርስቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት።
፬ እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ፤
፭ አሁንም፥ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር በአንተ ዘንድ በነበረኝ ክብር አንተ በራስህ ዘንድ አክብረኝ።
፮ ከዓለም ለሰጠኸኝ ስዎች ስምህን ገለጥሁላቸው። የአንተ ነበሩ ለእኔም ሰጠሃቸው፤
፯ ቃልህንም ጠብቀዋል። የሰጠኸኝ ሁሉ ከአንተ እንደ ሆነ አሁን ያውቃሉ፤
፰ የሰጠኸኝን ቃል ሰጥቻቸዋለሁና፤ እነርሱም ተቀበሉት፥ ከአንተም ዘንድ እንደ ወጣሁ በእውነት አወቁ፥ አንተም እንደ ላክኸኝ አመኑ።
፱ እኔ ስለ እነዚህ እለምናለሁ፤ ስለ ዓለም አልለምንም ስለ ሰጠኸኝ እንጂ፤ የአንተ ናቸውና፤
፲ የእኔም የሆነ ሁሉ የአንተ ነው የአንተውም የእኔ ነው፤ እኔም ስለ እነርሱ ከብሬአለሁ።
፲፩ ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።
፲፪ ከእነርሱ ጋር በዓለም ሳለሁ የሰጠኸኝን በስምህ እኔ እጠብቃቸው ነበር፤ ጠበቅኋቸውም መጽሐፉም እንዲፈጸም ከጥፋት ልጅ በቀር ከእነርሱ ማንም አልጠፋም።
፲፫ አሁንም ወደ አንተ እመጣለሁ፤ በእነርሱም ዘንድ ደስታዬ የተፈጸመ እንዲሆንላቸው ይህን በዓለም እናገራለሁ።
፲፬ እኔ ቃልህን ሰጥቻቸዋለሁ፤ እኔም ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉምና ዓለም ጠላቸው።
፲፭ ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም።
፲፮ እኔ ከዓለም እንዳይደለሁ ከዓለም አይደሉም።
፲፯ በእውነትህ ቀድሳቸው፤ ቃልህ እውነት ነው።
፲፰ ወደ ዓለም እንደ ላክኸኝ እንዲሁ እኔ ወደ ዓለም ላክኋቸው፤
፲፱ እነርሱም ደግሞ በእውነት የተቀደሱ እንዲሆኑ እኔ ራሴን ስለ እነርሱ እቀድሳለሁ።
፳-፳፩ አባት ሆይ፥ ዓለም ሳይፈጠር ስለ ወደድኸኝ የሰጠኸኝን ክብሬን እንዲያዩ እኔ ባለሁበት የሰጠኸኝ እነርሱ ደግሞ ከእኔ ጋር ይሆኑ ዘንድ እወዳለሁ።
፳፪ ጻድቅ አባት ሆይ፥ ዓለም አላወቀህም፥ እኔ ግን አወቅሁህ እነዚህም አንተ እንደ ላክኸኝ አወቁ፤
፳፮ እኔንም የወደድህባት ፍቅር በእነርሱ እንድትሆን እኔም በእነርሱ፥ ስምህን አስታወቅኋቸው አስታውቃቸውማለሁ።

፲፰

፩ ኢየሱስም ይህን ብሎ እትክልት ወዳለበት ስፍራ ወደ ቄድሮን ወንዝ ማዶ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ወጣ፤ እርሱም ደቀ መዛሙርቱም በዚያ ገቡ።
፪ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ብዙ ጊዜ ወደዚያ ስለ ተሰበሰቡ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳ ደግሞ ሰፍራውን ያውቅ ነበር።

፫ ሰለዚህ ይሁዳ ጭፍሮችንና ከካህናት አለቆች ከፈሪሳውያንም ሎሌዎችን ተቀብሎ በችቦና በፋና በጋሻ ጦርም ወደዚያ መጣ።
፬ ኢየሱስም የሚመጣበትን ሁሉ አውቆ ወጣና። ማንን ትፈልጋላችሁ አላቸው።
፭ የናዝሬቱን ኢየሱስን ብለው መለሱለት። ኢየሱስ። እኔ ነኝ አላቸው። አሳልፎ የሰጠውም ይሁዳ ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ነበር።
፮ እንግዲህ። እኔ ነኝ ባላቸው ጊዜ ወደ ኋላ አፈግፍገው በምድር ወደቁ።
፯ ደግሞም። ማንን ትፈልጋላችሁ? ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም። የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት።
፰ ኢየሱስ መልሶ። እኔ ነኝ አልኋችሁ፤ እንግዲህ እኔን ትፈልጉ እንደ ሆናችሁ እነዚህ ይሂዱ ተዉአቸው አለ፤
፱ ይህም። ከእነዚህ ከሰጠኸኝ አንዱን ሰንኳ አላጠፋሁም ያለው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፲ ሰምዖን ጴጥሮስም ሰይፍ ሰለ ነበረው መዘዘው፥ የሊቀ ካህናቱንም ባርያ መትቶ ቀኝ ጆሮውን ቈረጠ፤ የባርያውም ሰም ማልኮስ ነበረ።
፲፩ ኢየሱስም ጴጥሮስን። ሰይፍህን ወደ ሰገባው ክተተው፤ አብ የሰጠኝን ጽዋ አልጠጣትምን? አለው።
፲፪ እንግዲህ የሻለቃውና ጭፍሮቹ የአይሁድም ሎሌዎች ኢየሱስን ይዘው አሰሩት፥
፲፫ አሰቀድመውም ወደ ሐና ወሰዱት፤ በዚያች ዓመት ሊቀ ካህናት ለነበረው ለቀያፋ አማቱ ነበርና።
፲፬ ቀያፋም። አንድ ሰው ሰለ ሕዝብ ይሞት ዘንድ ይሻላል ብሎ ለአይሁድ የመከራቸው ነበረ።
፲፭ ሰምዖን ጴጥሮስም ሌላውም ደቀ መዝሙር ኢየሱስን ተከተሉ። ያም ደቀ መዝሙር በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀ ነበረ፥ ወደ ሊቀ ካህናቱም ግቢ ከኢየሱስ ጋር ገባ፤
፲፮ ጴጥሮስ ግን በውጭ በበሩ ቆሞ ነበር። እንግዲህ በሊቀ ካህናቱ ዘንድ የታወቀው ሌላው ደቀ መዝሙር ወጣ ለበረኛይቱም ነግሮ ጴጥሮስን አስገባው።
፲፯ በረኛ የነበረችይቱም ገረድ ጴጥሮስን። አንተ ደግሞ ከዚህ ሰው ደቀ መዛሙርት አንዱ አይደለህምን? አለችው። እርሱ። አይደለሁም አለ።
፲፰ ብርድ ነበረና ባሮችና ሎሌዎች የፍም እሳት አንድደው ቆሙ ይሞቁም ነበር፤ ጴጥሮስም ደግሞ ከእነርሱ ጋር ቆሞ ይሞቅ ነበር።
፲፱ ሊቀ ካህናቱም ኢየሱስን ሰለ ደቀ መዛሙርቱና ሰለ ትምህርቱ ጠየቀው።
፳ ኢየሰሰም መልሶ። እኔ በግልጥ ለዓለም ተናገርሁ፤ አይሁድ ሁሉ በሚሰበሰቡበት በምኩራብና በመቅደስ እኔ ሁልጊዜ አስተማርሁ፥ በሰውርም ምንም አልተናገርሁም።
፳፩ ሰለምን ትጠይቀኛለህ? ለእነርሱ የተናገርሁትን የሰሙትን ጠይቅ፤ እነሆ፥ እነዚህ እኔ የነገርሁትን ያውቃሉ አለው።
፳፪ ይህንም ሲል በዚያ ቆሞ የነበረው ከሎሌዎች አንዱ። ለሊቀ ካህናቱ እንዲህ ትመልሳለህን? ብሎ ኢየሱስን በጥፊ መታው።
፳፫ ኢየሱስም መልሶ። ክፉ ተናግሬ እንደ ሆንሁ ሰለ ክፉ መሰክር፤ መልካም ተናግሬ እንደ ሆንሁ ግን ሰለ ምን ትመታኛለህ? አለው።
፳፬ ሰለዚህ ሐና እንደ ታሰረ ወደ ሊቀ ካህናቱ ወደ ቀያፋ ሰደደው።
፳፭ ሰምዖን ጴጥሮስም ቆሞ እሳት ይሞቅ ነበር። እንግዲህ። እንተ ደግሞ ከደቀ መዛሙርቱ አይደለህምን? አሉት። እርሱም። አይደለሁም ብሎ ካደ።
፳፮ ጴጥሮስ ጆሮውን የቈረጠው ዘመድ የሆነ ከሊቀ ካህናቱ ባሮች አንዱ። በእትክልቱ ከእርሱ ጋር እኔ አይቼህ አልነበረምን? አለው።
፳፯ ጴጥሮስም እንደ ገና ካደ፥ ወዲያውም ዶሮ ጮኸ።
፳፰ ኢየሱስንም ከቀያፋ ወደ ገዡ ግቢ ወሰዱት፤ ማለዳም ነበረ፤ እነርሱም የፋሲካ በግ ይበሉ ዘንድ እንጂ እንዳይረክሱ ወደ ገዡ ግቢ አልገቡም።
፳፱ ሰለዚህ ጲላጦስ ወደ ውጭ ወደ እነርሱ ወጥቶ። ይህን ሰው ሰለ ምን ትከሱታላችሁ አላቸው።
፴ እነርሱም መልሰው። ይህስ ክፉ አድራጊ ባይሆን ወደ እንተ አሳልፈን ባልሰጠነውም ነበር አሉት።
፴፩ ጲላጦስም። እናንተ ወሰዳችሁ እንደ ሕጋችሁ ፍረዱበት አላቸው። አይሁድም። ለእኛስ ማንንም ልንገድል አልተፈቀደልንም አሉት፤
፴፪ ኢየሱስ በምን ዓይነት ሞት ሊሞት እንዳለው ሲያመለክት የተናገረው ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፴፫ ጲላጦስም እንደ ገና ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን ጠርቶ። የአይሁድ ንጉሥ አንተ ነህን? አለው።
፴፬ ኢየሱስም መልሶ። አንተ ይህን የምትለው ከራስህ ነውን ወይስ ሌሎች ሰለ እኔ ነገሩህን? አለው።
፴፭ ጲላጦስ መልሶ። እኔ አይሁዳዊ ነኝን? ወገኖችህና የካህናት አለቆች ለእኔ አሳልፈው ሰጡህ፤ ምን አድርገሃል? አለው።
፴፮ ኢየሱስም መልሶ። መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም፤ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን፥ ወደ አይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ ይዋጉልኝ ነበር፤ አሁን ግን መንግሥቴ ከዚህ አይደለችም አለው።
፴፯ ጲላጦስም። እንግዲያ ንጉሥ ነህን? አለው። ኢየሱስም መልሶ። እኔ ንጉሥ እንደ ሆንሁ አንተ ትላለህ። እኔ ለእውነት ልመሰክር ሰለዚህ ተወልጄለሁ ሰለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል አለው።
፴፰ ጲላጦስ። እውነት ምንድር ነው? አለው። ይህንም ብሎ ዳግመኛ ወደ አይሁድ ወጥቶ። እኔስ አንዲት በደል ሰንኳ አላገኘሁበትም።
፴፱ ነገር ግን በፋሲካ አንድ ልፈታላችሁ ልማድ አላችሁ፤ እንግዲህ የአይሁድን ንጉሥ ልፈታላችሁ ትወዳላችሁን? አላቸው።
፵ ሁሉም ደግመው። በርባንን እንጂ ይህን አይደለም እያሉ ጮኹ። በርባን ግን ወንበዴ ነበረ።

፲፱

፩ በዚያን ጊዜም ጲላጦስ ኢየሱስን ይዞ ገረፈው።
፪ ወታደሮችም ከእሾህ አክሊል ጐንጕነው በራሱ ላይ አኖሩ ቀይ ልብስም አለበሱት፤
፫ እየቀረቡም። የአይሁድ ንጉሥ ሆይ፥ ሰላም ለእንተ ይሁን ይሉት ነበር፤
፬ በጥፊም ይመቱት ነበር። ጲላጦስም ደግሞ ወደ ውጭ ወጥቶ። እነሆ፥ እንዲት በደል ሰንኳ

እንዳላገኘሁበት ታውቁ ዘንድ እርሱን ወደ ውጭ አወጣላችኋለሁ አላቸው።
፭ ኢየሱስም የእሾህ አክሊል ደፍቶ ቀይ ልብስም ለብሶ ወደ ውጭ ወጣ።
፮ ጲላጦስም። እነሆ ሰውዬው አላቸው። የካህናት አለቆችና ሎሌዎች ባዩትም ጊዜ። ሰቀለው ሰቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። እኔስ እንዲት በደል ስንኳ አላገኘሁበትምና እናንተ ወስዳችሁ ሰቀሉት አላቸው።
፯ አይሁድም መልሰው። እኛ ሕግ አለን፥ እንደ ሕጋችንም ሊሞት ይገባዋል፥ ራሱን የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎአልና አሉት።
፰ ሰለዚህ ጲላጦስ ይህን ነገር በሰማ ጊዜ እግጅ ፈራ፤
፱ ተመልሶም ወደ ገዡ ግቢ ገባና ኢየሱስን። አንተ ከወዴት ነህ? አለው። ኢየሱስ ግን አንድ እንኳ አልመለሰለትም።
፲ ሰለዚህ ጲላጦስ። አትነግረኝምን? ልሰቅልህ ሥልጣን እንዳለኝ ወይም ልፈታህ ሥልጣን እንዳለኝ አታውቅምን? አለው።
፲፩ ኢየሱስም መልሶ። ከላይ ካልተሰጠህ በቀር በእኔ ላይ ምንም ሥልጣን ባልነበረህም፤ ሰለዚህ ለአንተ አሳልፎ የሰጠኝ ኃጢአቱ የባሰ ነው አለው።
፲፪ ከዚህ በኋላ ጲላጦስ ሊፈታው ፈለገ፤ ነገር ግን አይሁድ። ይህንስ ብትፈታው የቄሣር ወዳጅ አይደለህም፤ ራሱን ንጉሥ የሚያደርግ ሁሉ የቄሣር ተቃዋሚ ነው እያሉ ጮኹ።
፲፫ ጲላጦስም ይህን ነገር ሰምቶ ኢየሱስን ወደ ውጭ አወጣው፥ በዕብራይስጥም ገበታ በተባለው ጸፍጸፍ በሚሉት ሰፍራ በፍርድ ወንበር ተቀመጠ።
፲፬ ለፋሲካም የማዘጋጀት ቀን ነበረ፤ ሰድስት ሰዓትም የሚያህል ነበረ፤ አይሁድንም። እነሆ ንጉሣችሁ አላቸው።
፲፭ እነርሱ ግን። አስወግደው፥ አስወግደው፥ ሰቀለው እያሉ ጮኹ። ጲላጦስም። ንጉሣችሁን ልሰቀለውን? አላቸው። የካህናት አለቆችም። ከቄሣር በቀር ሌላ ንጉሥ የለንም ብለው መለሱለት።
፲፮ ሰለዚህ በዚያን ጊዜ እንዲሰቀል አሳልፎ ሰጣቸው።
፲፯ ኢየሱስንም ይዘው ወሰዱት፤ መስቀሉንም ተሸክሞ በዕብራይስጥ ጎልጎታ ወደ ተባለው የራስ ቅል ሰፍራ ወደሚሉት ወጣ።
፲፰ በዚያም ሰቀሉት፥ ከእርሱም ጋር ሌሎች ሁለት፥ አንዱን በዚህ አንዱን በዚያ ኢየሱስንም በመካከላቸው ሰቀሉ።
፲፱ ጲላጦስም ደግሞ ጽሕፈት ጽፎ በመስቀሉ ላይ አኖረው፤ ጽሕፈቱም። የአይሁድ ንጉሥ የናዝሬቱ ኢየሱስ የሚል ነበረ።
፳ ኢየሱስም የተሰቀለበት ሰፍራ ለከተማ ቅርብ ነበረና ከአይሁድ ብዙዎች ይህን ጽሕፈት አነበቡት፤ በዕብራይስጥና በሮማይስጥ በግሪክም ተጽፎ ነበር።
፳፩ ሰለዚህ የአይሁድ ካህናት አለቆች ጲላጦስን። እርሱ። የአይሁድ ንጉስ ነኝ እንዳለ እንጂ የአይሁድ ንጉሥ ብለህ አትጻፍ አሉት።
፳፪ ጲላጦስም። የጻፍሁትን ጽፌአለሁ ብሎ መለሰ።
፳፫ ጭፍሮችም ኢየሱስን በሰቀሉት ጊዜ ልብሶቹን ወሰደው ለእያንዳንዱ ጭፍራ አንድ ክፍል ሆኖ በአራት ከፋፈሉት፤ እጀጠባቡን ደግሞ ወሰዱ። እጀ ጠባቡም ከላይ ጀምሮ ወጥ ሆኖ የተሠራ ነበረ እንጂ የተሰፋ አልነበረም።
፳፬ ሰለዚህ እርስ በርሳቸው። ለማን እንዲሆን በእርሱ ዕጣ እንጣጣልበት እንጂ አንቅደደው ተባባሉ። ይህም። ልብሴን እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ በእጅ ጠባቤም ዕጣ ተጣጣሉበት የሚለው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ነው።
፳፭ ጭፍሮችም እንዲህ አደረጉ። ነገር ግን በኢየሱስ መስቀል አጠገብ እናቱ፥ የእናቱም እኅት፥ የቀለዮጳም ሚስት ማርያም፥ መግደላዊትም ማርያም ቆመው ነበር።
፳፮ ኢየሱስም እናቱን ይወደው የነበረውንም ደቀ መዝሙር በአጠገቡ ቆሞ ባየ ጊዜ እናቱን። እነቺ ሴት፥ እነሆ ልጅሽ አላት።
፳፯ ከዚህ በኋላ ደቀ መዝሙሩን። እናትህ እነኋት አለው። ከዚህም ሰዓት ጀምሮ ደቀ መዝሙሩ ወደ ቤቱ ወሰዳት።
፳፰ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ አሁን ሁሉ እንደተፈጸመ እውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ። ተጠማሁ አለ።
፳፱ በዚያም ሆምጣጤ የሞላበት ዕቃ ተቀምጦ ነበር፤ እነርሱም ሆምጣጤውን በሰፍነግ ሞልተው በሁሶጵም እድርገው ወደ አፉ አቀረቡለት።
፴ ኢየሱስም ሆምጣጤውን ከተቀበለ በኋላ። ተፈጸመ አለ፥ ራሱንም አዘንብሎ ነፍሱን አሳልፎ ሰጠ።
፴፩ አይሁድም የማዘጋጀት ቀን ሰለ ሆነ ያ ሰንበት ትልቅ ነበረና ሥጋቸው በሰንበት በመስቀል ላይ እንዳይኖር፥ ጭናቸውን ሰብረው እንዲያወርዱአቸው ጲላጦስን ለመኑት።
፴፪ ጭፍሮችም መጥተው የፊተኛውን ጭን ከእርሱም ጋር የተሰቀለውን የሌላውን ጭን ሰበሩ፤
፴፫ ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን እርሱ ፈጽሞ እንደ ሞተ አይተው ጭኑን አልሰበሩም፤
፴፬ ነገር ግን ከጭፍሮች አንዱ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ወዲያውም ደምና ውኃ ወጣ።
፴፭ ያየውም መሰክሮአል፤ ምስክሩም እውነት ነው፤ እናንተም ደግሞ ታምኑ ዘንድ እርሱ እውነት እንዲናገር ያውቃል።
፴፮ ይህ የሆነ። ከእርሱ አጥንት አይሰበርም የሚል የመጽሐፉ ቃል እንዲፈጸም ነው።
፴፯ ደግሞም ሌላው መጽሐፍ። የወጉትን ያዩታል ይላል።
፴፰ ከዚህም በኋላ አይሁድን ሰለ ፈራ በሰውር የኢየሱስ ደቀ መዝሙር የነበረ የአርማትያስ ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ሊወስድ ጲላጦስን ለመነ፤ ጲላጦስም ፈቀደለት። ሰለዚህም መጥቶ የኢየሱስን ሥጋ ወሰደ።
፴፱ ደግሞም አስቀድሞ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ የነበረ ኒቆዲሞስ መቶ ንጥር የሚያህል የከርቤና የእሬት ቅልቅል ይዞ መጣ።
፵ የኢየሱስንም ሥጋ ወሰደው እንደ አይሁድ አገናነዝ ልማድ ከሽቱ ጋር በተልባ እግር ልብስ ከፈኑት።
፵፩ በተሰቀለበትም ሰፍራ አትክልት ነበረ፥ በአትክልቱም ማንም ገና ያልተቀበረበት አዲስ መቃብር ነበረ።
፵፪ ሰለዚህ መቃብሩ ቅርብ ነበረና ሰለ አይሁድ ማዘጋጀት ቀን ኢየሱስን በዚያ አኖሩት።

፳

፩ ከሳምንቱም በፊተኛው ቀን መግደላዊት ማርያም
ገና ጨለማ ሳለ ማለዳ ወደ መቃብር መጣች ድንጋዩም
ከመቃብሩ ተፈንቅሎ አየች።
፪ እየሮጠችም ወደ ሲምዖን ጴጥሮስና ኢየሱስ
ይወደው ወደ ነበረው ወደ ሌላው ደቀ መዝሙር
መጥታ። ጌታን ከመቃብር ወሰደውታል ወዴትም
እንዳኖሩት አናውቅም አለቻቸው።
፫ ስለዚህ ጴጥሮስና ሌላው ደቀ መዝሙር
ወጥተው ወደ መቃብሩ ሄዱ።
፬ ሁለቱም አብረው ሮጡ፤ ሌላው ደቀ መዝሙርም
ከጴጥሮስ ይልቅ ፈጥኖ ወደ ፊት ሮጠና አስቀድሞ
ከመቃብሩ ደረሰ፤
፭ ዝቅም ብሎ ቢመለከት የተልባ እግሩን ልብስ
ተቀምጦ አየ፥ ነገር ግን አልገባም።
፮ ሲምዖን ጴጥሮስም ተከትሎት መጣ ወደ
መቃብሩም ገባ፤ የተልባ እግሩን ልብስ ተቀምጦ አየ፥
፯ ደግሞም በራሱ የነበረውን ጨርቅ ለብቻው
በአንድ ሰፍራ ተጠምጥሞ እንደ ነበረ እንጂ ከተልባ
እግሩ ልብስ ጋር ተቀምጦ እንዳልነበረ አየ።
፰ በዚያን ጊዜ አስቀድሞ ወደ መቃብር የመጣውም
ሌላው ደቀ መዝሙር ደግሞ ገባ፥ አየም፥ አመነም፤
፱ ከሙታን ይነሣ ዘንድ እንዲገባው የሚለውን
የመጽሐፉን ቃል ገና አላወቁምና ነበርና።
፲ ደቀ መዛሙርቱም ወደ ቤታቸው ደግሞ ሄዱ።
፲፩ ማርያም ግን እያለቀሰች ከመቃብሩ በስተ ውጭ
ቆማ ነበር። ስታለቅስም ወደ መቃብር ዝቅ ብላ
ተመለከተች፤
፲፪ ሁለት መላእክትም ነጭ ልብስ ለብሰው የኢየሱስ
ሥጋ ተኝቶበት በነበረው አንዱ በራስጌ ሌላውም
በእግርጌ ተቀምጠው አየች።
፲፫ እነርሱም። አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ?
አሉአት። እርስዋም። ጌታዬን ወሰደውታል ወዴትም
እንዳኖሩት አላውቅም አለቻቸው።
፲፬ ይህንም ብላ ወደ ኋላ ዘወር ስትል ኢየሱስን
ቆሞ አየችው፤ ኢየሱስም እንደ ሆነ አላወቀችም።
፲፭ ኢየሱስም። አንቺ ሴት፥ ስለ ምን ታለቅሻለሽ?
ማንንስ ትፈልጊያለሽ? አላት። እርስዋም የአትክልት
ጠባቂ መስሎአት። ጌታ ሆይ፥ አንተ ወሰደኸው እንደ
ሆንህ ወዴት እንዳኖርኸው ንገረኝ እኔም እወሰደዋለሁ
አለችው።
፲፮ ኢየሱስም። ማርያም አላት። እርስዋ ዘወር
ብላ በዕብራይስጥ። ረቡኒ አለችው፤ ትርጓሜውም።
መምህር ሆይ ማለት ነው።
፲፯ ኢየሱስም። ገና ወደ አባቴ አላረግሁምና
አትንኪኝ፤ ነገር ግን ወደ ወንድሞቼ ሄደሽ። እኔ ወደ
አባቴና ወደ አባታችሁ ወደ አምላኬና ወደ አምላካችሁ
ዓርጋለሁ ብለሽ ንገሪአቸው አላት።
፲፰ መግደላዊት ማርያም መጥታ ጌታን እንዳየች
ይህንም እንዳላት ለደቀ መዛሙርቱ ነገረች።
፲፱ ያም ቀን እርሱም ከሳምንቱ ፊተኛው በመሸ
ጊዜ፥ ደቀ መዛሙርቱ ተሰብሰበው በነበሩበት፥
አይሁድን ስለ ፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳሉ፥ ኢየሱስ
መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ። ሰላም ለእናንተ ይሁን
አላቸው።
፳ ይህንም ብሎ እጆቹንም ጎኑንም አሳያቸው። ደቀ
መዛሙርቱም ጌታን ባዩ ጊዜ ደስ አላቸው።
፳፩ ኢየሱስም ዳግመኛ። ሰላም ለእናንተ ይሁን፤ አብ
እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካችኋለሁ አላቸው።
፳፪ ይህንም ብሎ እፍ አለባቸውና። መንፈስ ቅዱስን
ተቀበሉ።
፳፫ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ
ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዘባቸዋል አላቸው።
፳፬ ነገር ግን ከአሥራ ሁለቱ አንዱ ዲዲሞስ የሚሉት
ቶማስ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ ከእነርሱ ጋር አልነበረም።
፳፭ ሌሎቹም ደቀ መዛሙርቱ። ጌታን አይተነዋል
አሉት። እርሱ ግን። የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ
ጣቴንም በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጎኑ
ካላገባሁ አላምንም አላቸው።
፳፮ ከስምንት ቀን በኋላም ደቀ መዛሙርቱ ደግመው
በውስጥ ነበሩ፥ ቶማስም ከእነርሱ ጋር ነበረ። ደጆች
ተዘግተው ሳሉ ኢየሱስ መጣ፤ በመካከላቸውም ቆሞ።
ሰላም ለእናንተ ይሁን አላቸው።
፳፯ ከዚያም በኋላ ቶማስን። ጣትህን ወደዚህ
አምጣና እጆቼን እይ፤ እጅህንም አምጣና በጎኔ
አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።
፳፰ ቶማስም። ጌታዬ አምላኬም ብሎ መለሰለት።
፳፱ ኢየሱስም። ስለ አየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩ
የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው አለው።
፴ ኢየሱስም በዚህ መጽሐፍ ያልተጻፈ ሌላ ብዙ
ምልክት በደቀ መዛሙርቱ ፊት አደረገ፤
፴፩ ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆነ ታምኑ ዘንድ፥ አምናችሁም በስሙ
ሕይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተጽፎአል።

፳፩

፩ ከዚህ በኋላ ኢየሱስ በጥብርያዶስ ባሕር አጠገብ
ለደቀ መዛሙርቱ እንደ ገና ተገለጠላቸው፤
፪ እንዲህም ተገለጠ። ሲምዖን ጴጥሮስና ዲዲሞስ
የሚባለው ቶማስ ከገሊላ ቃና የሆነ ናትናኤልም
የዘብዴዎስም ልጆች ከደቀ መዛሙርቱም ሌሎች
ሁለት በአንድነት ነበሩ።
፫ ስምዖን ጴጥሮስ። ዓሣ ላጠምድ እሄዳለሁ
አላቸው። እነርሱም። እኛም ከአንተ ጋር እንመጣለን
አሉት። ወጥተውም ወደ ታንኳይቱ ገቡ በዚያችም
ሌሊት ምንም አላጠመዱም።
፬ በነጋም ጊዜ ኢየሱስ በባሕር ዳር ቆመ፤ ደቀ
መዛሙርቱ ግን ኢየሱስ መሆኑን አላወቁም።
፭ ኢየሱስም። ልጆች ሆይ፥ አንዳች የሚበላ
አላችሁን? አላቸው። የለንም ብለው መለሱለት።
፮ እርሱም። መረቡን በታንኳይቱ በስተ ቀኝ ጣሉት
ታገኙማላችሁ አላቸው። ስለዚህ ጣሉት፤ በዚህም
ጊዜ ከዓሣው ብዛት የተነሣ ሊጐትቱት አቃታቸው።
፯ ኢየሱስ ይወደው የነበረውም ደቀ መዝሙር
ጴጥሮስን። ጌታ እኮ ነው አለው። ስለዚህ ስምዖን
ጴጥሮስ ጌታ መሆኑን በሰማ ጊዜ ዕራቁቱን ነበረና
ልብሱን ታጥቆ ወደ ባሕር ራሱን ጣለ።
፰ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ግን ከምድር ሁለት
መቶ ክንድ ያህል እንጂ እጅግ አልራቁም ነበርና ዓሣ
የሞላውን መረብ እየሳቡ በጀልባ መጡ።
፱ ወደ ምድርም በወጡ ጊዜ ፍምና ዓሣ በላዩ
ተቀምጦ እንጀራም አዩ።

፲ ኢየሱስም። እሁን ካጠመዳችሁት ዓሣ አምጡ አላቸው።
፲፩ ስምዖን ጴጥሮስም ወደ ጀልባይቱ ገብቶ መቶ አምሳ ሦስት ታላላቅ ዓሦች ሞልቶ የነበረውን መረብ ወደ ምድር ጐተተ፤ ይህንም ያህል ብዙ ሲሆን መረቡ አልተቀደደም።
፲፪ ኢየሱስም። ኑ፥ ምሳ ብሉ አላቸው። ከደቀ መዛሙርቱ አንድ ስንኳ። አንተ ማን ነህ? ብሎ ሊመረምረው የደፈረ አልነበረም፤ ጌታ መሆኑን አውቀው ነበርና።
፲፫ ኢየሱስም መጣና እንጀራ አንሥቶ ሰጣቸው፥ እንዲሁም ዓሣውን።
፲፬ ኢየሱስ ከሙታን ከተነሣ በኋላ ለደቀ መዛሙርቱ ሲገለጥላቸው ይህ ሦስተኛው ጊዜ ነበረ።
፲፭ ምሳ ከበሉ በኋላም ኢየሱስ ስምዖን ጴጥሮስን። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ከእነዚህ ይልቅ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ግልገሎቼን አሰማራ አለው።
፲፮ ደግሞ ሁለተኛ። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው። አዎን ጌታ ሆይ፥ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው።
፲፯ ጠቦቶቼን ጠብቅ አለው። ሦስተኛ ጊዜ። የዮና ልጅ ስምዖን ሆይ፥ ትወደኛለህን? አለው። ሦስተኛ። ትወደኛለህን? ስላለው ጴጥሮስ አዘነና። ጌታ ሆይ፥ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ አለው። ኢየሱስም። በጎቼን አሰማራ።
፲፰ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ አንተ ጐልማሳ ሳለህ ወገብህን በገዛ ራስህ ታጥቀህ ወደምትወደው ትሄድ ነበር፤ ነገር ግን በሸመገልህ ጊዜ እጆችህን ትዘረጋለህ፥ ሌላውም ያሰታጥቅሃል ወደማትወደውም ይወስድሃል አለው።
፲፱ በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ እንዳለው ሲያመለክት ይህን አለ። ይህንም ብሎ። ተከተለኝ አለው።
፳ ጴጥሮስም ዘወር ብሎ ኢየሱስ ይወደው የነበረውን ደቀ መዝሙር ሲከተለው አየ፤ እርሱም ደግሞ በእራት ጊዜ በደረቱ ተጠግቶ። ጌታ ሆይ፥ አሳልፎ የሚሰጥህ ማን ነው? ያለው ነበረ።
፳፩ ጴጥሮስም ይህን አይቶ ኢየሱስን። ጌታ ሆይ፥ ይህስ እንዴት ይሆናል? አለው።
፳፪ ኢየሱስም። እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ፥ ምን አግዶህ? አንተ ተከተለኝ አለው።
፳፫ ስለዚህ። ያ ደቀ መዝሙር አይሞትም የሚለው ይህ ነገር ወደ ወንድሞች ወጣ፤ ነገር ግን ኢየሱስ። እስክመጣ ድረስ ይኖር ዘንድ ብወድስ ምን አግዶህ? አለው እንጂ አይሞትም አላለውም።
፳፬ ስለ እነዚህም የመሰከረ ይህንንም ጽፎ ያለ ይህ ደቀ መዝሙር ነው፥ ምስክሩም እውነት እንደ ሆነ እናውቃለን።
፳፭ ኢየሱስም ያደረገው ብዙ ሌላ ነገር ደግሞ አለ፤ ሁሉ በእያንዳንዱ ቢጻፍ ለተጻፉት መጻሕፍት ዓለም ራሱ ባልበቃቸውም ይመስለኛል።

የሐዋርያት ሥራ

፩-፫ ደግሞ አርባ ቀን እየታያቸው ስለ እግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፥ በብዙ ማስረጃ ከሕማማቱ በኋላ ሕያው ሆኖ ለእነርሱ ራሱን አሳያቸው።
፬ ከእነርሱም ጋር አብሮ ሳለ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው፥ ነገር ግን። ከእኔ የሰማችሁትን አብ የሰጠውን የተስፋ ቃል ጠብቁ፤
፭ ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና፥ እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ አለ።
፮ እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ። ጌታ ሆይ፥ በዚህ ወራት ለእስራኤል መንግሥትን ትመልሳለህን? ብለው ጠየቁት።
፯ እርሱም። አብ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤
፰ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።
፱ ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው።
፲ እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ፥ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ፤
፲፩ ደግሞም። የገሊላ ሰዎች ሆይ፥ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።
፲፪ በዚያን ጊዜ ደብረ ዘይት ከሚባለው ተራራ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ እርሱም ከኢየሩሳሌም የሰንበት መንገድ ያህል የራቀ ነው።
፲፫ በገቡም ጊዜ ወደሚኖሩበት ሰገነት ወጡ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስም፥ ያዕቆብም፥ እንድርያስም፥ ፊልጶስም፥ ቶማስም፥ በርተሎሜዎስም፥ ማቴዎስም፥ የእልፍዮስ ልጅ ያዕቆብም፥ ቀናተኛ የሚባለው ስምዖንም፥ የያዕቆብ ልጅ ይሁዳም።
፲፬ እነዚህ ሁሉ ከሴቶችና ከኢየሱስ እናት ከማርያም ከወንድሞቹም ጋር በአንድ ልብ ሆነው ለጸሎት ይተጉ ነበር።
፲፭ በዚህም ወራት ጴጥሮስ መቶ ሀያ በሚያህል በሰዎች ማኅበር አብረው በነበሩ በወንድሞቹ መካከል ተነሥቶ አለ።
፲፮ ወንድሞች ሆይ፥ ኢየሱስን ለያዙት መሪ ስለሆናቸው ስለ ይሁዳ መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በዳዊት አፍ የተናገረው የመጽሐፍ ቃል ይፈጸም ዘንድ ይገባ ነበር፤
፲፯ ከእኛ ጋር ተቈጥሮ ነበርና፥ ለዚህም አገልግሎት ታድሎ ነበርና።
፲፰ ይህም ሰው በዓመፅ ዋጋ መሬት ገዛ በግንባሩም ተደፍቶ ከመካከሉ ተሰነጠቀ አንጀቱም ሁሉ ተዘረገፈ፤
፲፱ በኢየሩሳሌምም ለሚኖሩ ሁሉ ታወቀ፤ ስለዚህም ያ መሬት በቋንቋቸው አኬልዳማ ተብሎ ተጠራ፥ እርሱም የደም መሬት ማለት ነው።
፳ በመዝሙር መጽሐፍ። መኖሪያው ምድረ በዳ ትሁን የሚኖርባትም አይኑር፤ ደግሞም። ሹመቱን ሌላ ይውሰዳት ተብሎ ተጽፎአልና።
፳፩-፳፪ ኢዮሰጦስም የሚሉትን በርሰያን የተባለውን ዮሴፍንና ማትያስን ሁለቱን አቆሙ።
፳፫-፳፮ ዕጣም ተጣጣሉላቸው፥ ዕጣውም ለማትያስ ወደቀና ከአሥራ አንዱ ሐዋርያት ጋር ተቈጠረ።

፪

፩ በዓለ ኀምሳ የተባለውም ቀን በደረሰ ጊዜ፥ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፥
፪ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣ፥ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ሁሉ ሞላው።
፫ እንደ እሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው፤ በያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው።
፬ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።
፭ ከሰማይም በታች ካሉ ሕዝብ ሁሉ በጸሎት የተጉ አይሁድ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤
፮ ይህም ድምፅ በሆነ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ ተሰበሰቡ፥ እያንዳንዱም በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለ ነበር የሚሉትን እጡ።
፯ ተገርመውም ተደነቀውም እንዲህ አሉ። እነሆ፥ እነዚህ የሚናገሩት ሁሉ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን?
፰ እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?
፱ የጳርቴና የሜድ የኢላሜጤም ሰዎች፥ በሁለት ወንዝም መካከል በይሁዳም በቀጰዶቅያም በጳንጦስም በእስያም፥
፲ በፍርግያም በጵንፍልያም በግብፅም በቀሬናም በኩል ባሉት በሊቢያ ወረዳዎች የምንኖር፥ በሮሜም የምንቀመጥ፥ አይሁድም ወደ ይሁዲነትም የገባን፥
፲፩ የቀርጤስና የዓረብ ሰዎች፥ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ በልሳኖቻችን ሲናገሩ እንሰማቸዋለን።
፲፪ ሁሉም ተገረሙና እመንትተው እርስ በርሳቸው። እንጂ ይህ ምን ይሆን? አሉ።
፲፫ ሌሎች ግን እያፌዙባቸው። ጉሽ የወይን ጠጅ ጠግበዋል አሉ።
፲፬ ነገር ግን ጴጥሮስ ከአሥራ አንዱ ጋር ቆመ፥ ድምፁንም ከፍ አድርጎ እንዲህ ሲል ተናገራቸው። አይሁድ በኢየሩሳሌምም የምትኖሩ ሁላችሁ፥ ይህ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፥ ቃሎቼንም አድምጡ።
፲፭ ለእናንተ እንደ መሰላችሁ እነዚህ የሰከሩ አይደሉም፥ ከቀኑ ሦስተኛ ሰዓት ነውና፤
፲፮ ነገር ግን ይህ በነቢዩ በኢዩኤል የተባለው ነው።
፲፯ እግዚአብሔር ይላል። በመጨረሻው ቀን እንዲህ ይሆናል፤ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁም ትንቢት ይናገራሉ፥ ጎበዞቻችሁም ራእይ ያያሉ፥ ሽማግሌዎቻችሁም ሕልም ያልማሉ፤
፲፰ ደግሞም በዚያች ወራት በወንዶችና በሴቶች ባሪያዎቼ ላይ ከመንፈሴ አፈሳለሁ ትንቢትም ይናገራሉ።

፲፱ ድንቆችን በላይ በሰማይ፥ ምልክቶችንም በታች
በምድር እሰጣለሁ፤ ደምም እሳትም የጢስ ጭጋግም
ይሆናል፤
፳ ታላቅ የሆነ የተሰማም የጌታ ቀን ሳይመጣ ፀሐይ
ወደ ጨለማ ጨረቃም ወደ ደም ይለወጣሉ።
፳፩ የጌታን ሰም የሚጠራም ሁሉ ይድናል።
፳፪ የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ይህን ቃል
ስሙ፤ ራሳችሁ እንደምታውቁ፥ የናዝሬቱ ኢየሱስ
እግዚአብሔር በመካከላችሁ በእርሱ በኩል ባደረገው
ተአምራትና በድንቆች በምልክቶችም ከእግዚአብሔር
ዘንድ ለእናንተ የተገለጠ ሰው ነበረ፤
፳፫ እርሱንም በእግዚአብሔር በተወሰነው አሳቡና
በቀደመው እውቀቱ ተሰጥቶ በዓመፀኞች እጅ
ሰቅላችሁ ገደላችሁት።
፳፬ እግዚአብሔር ግን የሞትን ጣር አጥፍቶ
አስነሣው፥ ሞት ይይዘው ዘንድ አልቻለምና።
፳፭ ዳዊት ሰለ እርሱ እንዲህ ይላልና። ጌታን ሁልጊዜ
በፊቴ አየሁት፥ እንዳልታወክ በቀኜ ነውና።
፳፮ ሰለዚህ ልቤን ደስ አለው፥ ልሳኔም ሐሤት
አደረገ፥ ደግሞም ሥጋዬ በተስፋ ያድራል፤
፳፯ ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥ ቅዱስህንም
መበሰበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም።
፳፰ የሕይወትን መንገድ አስታወቅኸኝ፤ ከፊትህ ጋር
ደስታን ትሞላብኛለህ።
፳፱ ወንድሞች ሆይ፥ ሰለ አባቶች አለቃ ሰለ ዳዊት
እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም ለእናንተ በግልጥ እናገር
ዘንድ ፍቀዱልኝ፤ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ
ነው።
፴ ነቢይ ሰለ ሆነ፥ ከወገቡም ፍሬ በዙፋኑ ያሰቀምጥ
ዘንድ እግዚአብሔር መሐላ እንደ ማለለት ሰለ እወቀ፥
፴፩ ሰለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስቀድሞ አይቶ፥ ነፍሱ
በሲኦል እንዳልቀረች ሥጋውም መበሰበስን እንዳላየ
ተናገረ።
፴፪ ይህን ኢየሱስን እግዚአብሔር አስነሣው ለዚህም
ነገር እኛ ሁላችን ምስክሮች ነን፤
፴፫ ሰለዚህ በእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ ብሎና
የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ከአብ ተቀብሎ ይህን
እናንተ አሁን የምታዩትንና የምትሰሙትን አፈሰሰው።
፴፬-፴፭ አለ። እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን
ኢየሱስን እግዚአብሔር ጌታም ክርስቶስም
እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።
፴፮ ይህንም በሰሙ ጊዜ ልባቸው ተነካ፥ ጴጥሮስንና
ሌሎችንም ሐዋርያት። ወንድሞች ሆይ፥ ምን
እናድርግ? አሉአቸው።
፴፯ ጴጥሮስም። ንሰሐ ግቡ፥ ኃጢአታችሁም
ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም
ተጠመቁ፤ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ።
፴፰ የተሰፋው ቃል ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ
አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ
ነውና አላቸው።
፴፱ በብዙ ሌላ ቃልም መሰከረና። ከዚህ ጠማማ
ትውልድ ዳኑ ብሎ መከራቸው።
፵ ቃሉንም የተቀበሉ ተጠመቁ፥ በዚያም ቀን ሦስት
ሺህ የሚያህል ነፍስ ተጨመሩ፤
፵፩ በሐዋርያትም ትምህርትና በኅብረት
እንጀራውንም በመቍረስ በየጸሎቱም ይተጉ ነበር።
፵፪ ነገር ግን በሰው ሁሉ ፍርሀት ሆነ፤ በሐዋርያትም
እጅ ብዙ ድንቅና ምልክት ተደረገ።
፵፫ ያመኑትም ሁሉ አብረው ነበሩ፤
፵፬ ያላቸውንም ሁሉ እንድነት አደረጉ።
መሬታቸውንና ጥሪታቸውንም እየሸጡ፥ ማንኛውም
እንደሚፈልግ ለሁሉ ያካፍሉት ነበር።
፵፭ በየቀኑም በአንድ ልብ ሆነው በመቅደስ እየተጉ
በቤታቸውም እንጀራ እየቈረሱ፥ በደስታና በጥሩ ልብ
ምግባቸውን ይመገቡ ነበር፤
፵፮ እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ በሕዝብ ሁሉ ፊት
ሞገስ ነበራቸው። ጌታም የሚድኑትን ዕለት ዕለት
በእነርሱ ላይ ይጨምር ነበር።

፫

፩ ጴጥሮስና ዮሐንስም በጸሎት ጊዜ በዘጠኝ ሰዓት
ወደ መቅደስ ይወጡ ነበር።
፪ ወደ መቅደስም ከሚገቡት ምጽዋት ይለምን
ዘንድ፥ ሰዎች ተሸክመው መልካም በሚሉአት
በመቅደስ ደጅ በየቀኑ ያሰቀምጡት የነበሩ ከእናቱ
ማኅፀን ጀምሮ አንካሳ የሆነ አንድ ሰው ነበረ።
፫ እርሱም ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ
እንዳላቸው ባየ ጊዜ፥ ምጽዋትን ለመናቸው።
፬ ጴጥሮስም ከዮሐንስ ጋር ትኩር ብሎ ወደ እርሱ
ተመልክቶ። ወደ እኛ ተመልከት አለው።
፭ እርሱም አንድ ነገር ከእነርሱ እንዲቀበል ሲጠብቅ
ወደ እነርሱ ተመለከተ።
፮ ጴጥሮስ ግን። ብርና ወርቅ የለኝም፤ ይህን ያለኝን
ግን እሰጥሃለሁ፤ በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም
ተነሣና ተመላለስ አለው።
፯ በቀኝ እጁም ይዞ አስነሣው፤ በዚያን ጊዜም
እግሩና ቍርጭምጭምቱ ጸና፥
፰ ወደ ላይ ዘሎም ቆመ፥ ይመላለስም
ጀመር፤ እየተመላለሰም እየዘለለም እግዚአብሔርንም
እያመሰገነ ከእነርሱ ጋር ወደ መቅደስ ገባ።
፱ ሕዝቡም ሁሉ እግዚአብሔርን እያመሰገነ
ሲመላለስ አዩት፤
፲ መልካምም በሚሉአት በመቅደስ ደጅ ሰለ
ምጽዋት ተቀምጦ የነበረው እርሱ እንደ ሆነ
አወቁት፤ በእርሱም ከሆነው የተነሣ መደነቅና መገረም
ሞላባቸው።
፲፩ እርሱም ጴጥሮስንና ዮሐንስን ይዞ ሳለ፥ ሕዝቡ
ሁሉ እየተደነቁ የሰሎሞን ደጅ መመላለሻ በሚባለው
አብረው ወደ እነርሱ ሮጡ።
፲፪ ጴጥሮስም አይቶ ለሕዝቡ እንዲህ ሲል
መለሰ። የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ በዚህ ሰለ ምን
ትደነቃላችሁ? ወይስ በገዛ ኃይላችን ወይስ
እግዚአብሔርን በመፍራታችን ይህ ይመላለስ ዘንድ
እንዳደረግነው ሰለ ምን ትኩር ብላችሁ ታዩናላችሁ?
፲፫ የአብርሀምና የይስሐቅ የያዕቆብም አምላክ፥
የአባቶቻችን አምላክ፥ እናንተ አሳልፋችሁ
የሰጣችሁትንና ሊፈታው ቈርጦ ሳለ በጲላጦስ ፊት
የካዳችሁትን ብላቴናውን ኢየሱስን አከበረው።
፲፬ እናንተ ግን ቅዱሱን ጻድቁንም ክዳችሁ ነፍስ
ገዳዩን ሰው ይሰጣችሁ ዘንድ ለመናችሁ፥
፲፭ የሕይወትንም ራስ ገደላችሁት፤ እርሱን ግን
እግዚአብሔር ከሙታን አስነሣው፥ ለዚህም ነገር እኛ
ምስክሮች ነን።

፲፭ በሰሙም በማመን ይህን የምታዩትንና
የምታውቁትን የእርሱ ሰም አጸናው፥ በእርሱም በኩል
የሆነው እምነት በሁላችሁ ፊት ይህን ፍጹም ጤና
ሰጠው።
፲፮ አሁንም፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ እንደ
አለቆቻችሁ ደግሞ ባለማወቅ እንዳደረጋችሁት
አውቄአለሁ፤
፲፯ እግዚአብሔር ግን ክርስቶስ መከራ እንዲቀበል
አስቀድሞ በነቢያት ሁሉ አፍ የተናገረውን እንዲሁ
ፈጸመው።
፲፰-፳፩ እግዚአብሔር ከጥንት ጀምሮ በቅዱሳን
ነቢያቱ አፍ የተናገረው፥ ነገር ሁሉ እስከሚታደስበት
ዘመን ድረስ ሰማይ ይቀበለው ዘንድ ይገባልና።
፳፪ ሙሴም ለአባቶች። ጌታ አምላክ እኔን
እንዳስነሣኝ ነቢይን ከወንድሞቻችሁ ያስነሣላችኋል፤
በሚነግራችሁ ሁሉ እርሱን ሰሙት።
፳፫ ያንም ነቢይ የማትሰማው ነፍስ ሁሉ ከሕዝብ
ተለይታ ትጠፋለች አለ።
፳፬ ሁለተኛም ከሳሙኤል ጀምሮ ከእርሱም በኋላ
የተናገሩት ነቢያት ሁሉ ደግሞ ሰለዚህ ወራት ተናገሩ።
፳፭ እናንተ የነቢያት ልጆችና እግዚአብሔር
ለአብርሃም። በዘርህ የምድር ወገኖች ሁሉ ይባረካሉ
ብሎ፥ ከአባቶቻችን ጋር ያደረገው የኪዳን ልጆች
ናችሁ።
፳፮ ለእናንተ አስቀድሞ እግዚአብሔር ብላቴናውን
አስነሥቶ፥ እያንዳንዳችሁን ከክፋታችሁ እየመለሰ
ይባርካችሁ ዘንድ፥ ሰደደው።

፬

፩ ለሕዝቡም ሲናገሩ የካህናት አለቆችና የመቅደስ
አዛዥ ሰዱቃውያንም፥
፪ ሕዝቡን ሰለ አስተማሩና በኢየሱስ የሙታንን
ትንሣኤ ሰለ ሰበኩ ተቸግረው፥ ወደ እነርሱ ቀረቡ፥
፫ እጃቸውንም ጭነውባቸው አሁን መሸቶ ነበርና
እስከ ማግሥቱ ድረስ በወኅኒ አኖሩአቸው።
፬ ነገር ግን ቃሉን ከሰሙት ብዙዎች አመኑ፥
የወንዶችም ቍጥር አምስት ሺህ ያህል ሆነ።
፭-፮ እነርሱንም በመካከል አቁመው። በምን ኃይል
ወይስ በማን ሰም እናንተ ይህን አደረጋችሁ? ብለው
ጠየቁአቸው።
፯ በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መንፈስ ቅዱስንም
ተሞልቶ እንዲህ አላቸው። እናንተ የሕዝብ አለቆችና
ሽማግሌዎች፥
፰ እኛ ዛሬ ለድውዩ ሰው ሰለ ተደረገው መልካም
ሥራ ይህ በምን እንደዳነ ብንመረመር፥
፱ እናንተ በሰቀላችሁት እግዚአብሔርም ከሙታን
ባስነሣው በናዝሬቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም ይህ
ደኅና ሆኖ በፊታችሁ እንደ ቆመ፥ ለእናንተ ለሁላችሁ
ለእስራኤልም ሕዝብ ሁሉ የታወቀ ይሁን።
፲ እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ
የሆነው ይህ ድንጋይ ነው።
፲፩ መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ
የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ሰም ከሰማይ በታች ሌላ
የለምና።
፲፫ ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጥ እንደ ተናገሩ ባዩ
ጊዜ፥ መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች እንደ
ሆኑ አስተውለው አደነቁ፥ ከኢየሱስም ጋር እንደ ነበሩ
አወቁአቸው፤
፲፬ የተፈወሰውንም ሰው ከእነርሱ ጋር ቆሞ ሲያዩ
የሚመልሱትን አጡ።
፲፭ ከሸንጎም ወደ ውጭ ይወጡ ዘንድ አዝዘው።
በእነዚህ ሰዎች ምን እንሥራ?
፲፮ የታወቀ ምልክት በእነርሱ እጅ እንደ ተደረገ
በኢየሩሳሌም ለሚኖሩ ሁሉ ተገልጦአልና፥ እንሸሽገው
ዘንድ አንችልም፤
፲፯ ነገር ግን በሕዝቡ ዘንድ አብዝቶ እንዳይሰፋፋ፥
ከእንግዲህ ወዲህ ለማንም ሰው በዚህ ሰም
እንዳይናገሩ እየዛትን እንዘዛቸው ብለው እርስ
በርሳቸው ተማከሩ።
፲፰ ጠርተውም በኢየሱስ ሰም ፈጽመው
እንዳይናገሩና እንዳያስተምሩ አዘዙአቸው።
፲፱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ግን መልሰው። እግዚአብሔርን
ከመሰማት ይልቅ እናንተን እንሰማ ዘንድ
በእግዚአብሔር ፊት የሚገባ እንደ ሆነ ቍረጡ፤
፳ እኛስ ያየነውንና የሰማነውን ከመናገር ዝም ማለት
አንችልም አሉአቸው።
፳፩ እነርሱም እንደ ምን እንደሚቀጡ ምክንያት
ሰላላገኙባቸው፥ እንደ ገና ዝተው ከሕዝቡ
የተነሣ ፈቱአቸው፤ ሰዎች ሁሉ ሰለ ሆነው ነገር
እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበርና።
፳፪ ይህ የመፈወስ ምልክት የተደረገለት ሰው ከአርባ
ዓመት ይበልጠው ነበርና።
፳፫ ተፈትተውም ወደ ወገኖቻቸው መጡና የካህናት
አለቆችና ሽማግሌዎች ያሉአቸውን ሁሉ ነገሩአቸው።
፳፬ እነርሱም በሰሙ ጊዜ በአንድ ልብ ሆነው ወደ
እግዚአብሔር ድምፃቸውን ከፍ አደረጉ እንዲህም
አሉ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ሰማዩንና ምድሩን ባሕሩንም
በእነርሱም የሚኖረውን ሁሉ የፈጠርህ፥
፳፭ በመንፈስ ቅዱስም በብላቴናህ በአባታችን
በዳዊት አፍ። አሕዛብ ለምን አኵረመረሙ? ሕዝቡስ
ከንቱን ነገር ለምን አሰቡ?
፳፮ የምድር ነገሥታት ተነሡ አለቆችም በጌታና
በተቀባው ላይ አብረው ተከማቹ ብለህ የተናገርህ
አምላክ ነህ።
፳፯-፳፰ ከጸለዩም በኋላ ተሰብስበው የነበሩበት
ሰፍራ ተናወጠ፥ በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥
የእግዚአብሔርንም ቃል በግልጥ ተናገሩ።
፳፱ ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ
ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በእንድነት ነበረ እንጂ
ካለው አንድ ነገር ሰንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም
አልተናገረም።
፴ ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ
በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ
ጸጋ ነበረባቸው።
፴፩ በመካከላቸው አንድ ሰንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤
መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን
ዋጋ ያመጡ ነበርና፥
፴፪ በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤
ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ
ያካፍሉት ነበር።
፴፫ ትውልዱም የቆጵሮስ ሰው የነበረ አንድ ሌዋዊ
ዮሴፍ የሚሉት ነበረ፥ እርሱም በሐዋርያት በርናባስ
ተባለ ትርጓሜውም የመጽናናት ልጅ ነው፤

፴፯ እርሻም ነበረውና ሸጦ ገንዘቡን አምጥቶ ከሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው።

፭

፩ ሐናንያም የተባለ አንድ ሰው ሰጲራ ከተባለች ከሚስቱ ጋር መሬት ሸጠ፥
፪ ሚስቱም ደግሞ ሰታውቅ ከሸያጩ አሰቀረና እኩሌታውን አምጥቶ በሐዋርያት እግር አጠገብ አኖረው።
፫ ጴጥሮስም። ሐናንያ ሆይ፥ መንፈስ ቅዱስን ታታልልና ከመሬቱ ሸያጭ ታሰቀር ዘንድ ሰይጣን በልብህ ሰለ ምን ሞላ?
፬ ሳትሸጠው የአንተ አልነበረምን? ከሸጥኸውሰ በኋላ በሥልጣንህ አልነበረምን? ይህን ነገር ሰለ ምን በልብህ አሰብህ? እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን አልዋሸህም አለው።
፭ ሐናንያም ይህን ቃል ሰምቶ ወደቀ ሞተም፤ በሰሙትም ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።
፮ ጐበዞችም ተነሥተው ከፈኑት አውጥተውም ቀበሩት።
፯ ከሦስት ሰዓት ያህል በኋላም ሚስቱ የሆነውን ሳታውቅ ገባች።
፰ ጴጥሮስም መልሶ። እስቲ ንገሪኝ፥ መሬታችሁን ይህን ለሚያህል ሸጣችሁትን? አላት። እርሰዋም። አዎን፥ ይህን ለሚያህል ነው አለች።
፱ ጴጥሮስም። የጌታን መንፈስ ትፈታተኑ ዘንድ ሰለ ምን ተሰማማችሁ? እነሆ፥ ባልሸጉ የቀበሩት ሰዎች እግር በደጅ ነው እነቺንም ያወጡሻል አላት።
፲ ያን ጊዜም በእግሩ አጠገብ ወደቀች ሞተችም፤ ጐበዞችም ሲገቡ ሞታ አገኙአት አውጥተውም በባልዋ አጠገብ ቀበሩአት።
፲፩ በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ።
፲፪ በሐዋርያትም እጅ ብዙ ምልክትና ድንቅ በሕዝብ መካከል ይደረግ ነበር፤ ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው በሰሎሞን ደጅ መመላለሻ ነበሩ።
፲፫ ከሌሎችም አንድ ሰንኳ ሊተባበራቸው የሚደፍር አልነበረም፥
፲፬ ሕዝቡ ግን ያከብሩአቸው ነበር፤ የሚያምኑትም ከፊት ይልቅ ለጌታ ይጨመሩለት ነበር፤ ወንዶችና ሴቶችም ብዙ ነበሩ።
፲፭ ሰለዚህም ጴጥሮስ ሲያልፍ ጥላውም ቢሆን ከእነርሱ አንዱን ይጋርድ ዘንድ ድውያንን ወደ አደባባይ አውጥተው በአልጋና በወሰካ ያኖሩአቸው ነበር።
፲፮ ደግሞም በኢየሩሳሌም ዙሪያ ካለችው ከተማ ድውያንንና በርኩሳን መናፍስት የተሣቀዩትን እያመጡ ብዙ ሰዎች ይሰበሰቡ ነበር፤ ሁሉም ይፈወሱ ነበር።
፲፯ ሊቀ ካህናቱ ግን የሰዱቃውያን ወገን ሆነውም ከእርሱ ጋር የነበሩት ሁሉ ተነሡ ቅንዓትም ሞላባቸው።
፲፰ በሐዋርያትም ላይ እጆቸውን ጭነው በሕዝቡ ወኅኒ ውሰጥ አኖሩአቸው።
፲፱ የጌታ መልአክ ግን በሌሊት የወኅኒውን ደጅ ከፍቶ አወጣቸውና።
፳ ሂዱና ቆማችሁ የዚህን ሕይወት ቃል ሁሉ ለሕዝብ በመቅደስ ንገሩ አላቸው።
፳፩ በሰሙም ጊዜ ማልደው ወደ መቅደስ ገብተው አስተማሩ። ግን ሊቀ ካህናቱና ከእርሱ ጋር የነበሩት መጥተው ሸንጎውንና የእስራኤልን ልጆች ሽማግሌዎች ሁሉ በአንድነት ጠሩ፥ ያመጡአቸውም ዘንድ ወደ ወኅኒ ላኩ።
፳፪-፳፬ የመቅደስ አዛዥና የካህናት አለቆችም ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ። እንጂ ይህ ምን ይሆን? እያሉ ሰለ እነርሱ አመነቱ።
፳፭ አንድ ሰውም መጥቶ። እነሆ፥ በወኅኒ ያኖራችኋቸው ሰዎች እየቆሙ ሕዝቡንም እያስተማሩ በመቅደስ ናቸው ብሎ አወራላቸው።
፳፮ በዚያን ጊዜ አዛዡ ከሎሌዎች ጋር ሄዶ አመጣቸው፥ በኃይል ግን አይደለም፤ ሕዝቡ እንዳይወግሩአቸው ይፈሩ ነበርና።
፳፯ አምጥተውም በሸንጎ አቆሙአቸው።
፳፰ ሊቀ ካህናቱም። በዚህ ሰም እንዳታስተምሩ አጥብቀን አላዘዝናችሁምን? እነሆም፥ ኢየሩሳሌምን በትምህርታችሁ ሞልታችኋል፤ የዚያንም ሰው ደም በእኛ ታመጡብን ዘንድ ታስባላችሁ ብሎ ጠየቃቸው።
፳፱ ጴጥሮስና ሐዋርያትም መልሰው አሉ። ከሰው ይልቅ ለእግዚአብሔር ልንታዘዝ ይገባል።
፴ እናንተ በእንጨት ላይ ሰቅላችሁ የገደላችሁትን ኢየሱሰን የአባቶቻችን አምላክ አስነሣው፤
፴፩ ይህን እግዚአብሔር፥ ለእስራኤል ንሰሐን የኃጢአትንም ሰርየት ይሰጥ ዘንድ፥ ራሰም መድኃኒትም አድርጎ በቀኙ ከፍ ከፍ አደረገው።
፴፪ እኛም ለዚህ ነገር ምስክሮች ነን፥ ደግሞም እግዚአብሔር ለሚታዘዙት የሰጠው መንፈሰ ቅዱሰ ምስክር ነው።
፴፫ እነርሱም ሲሰሙ በጣም ተቈጡ ሊገድሉአቸውም አሰቡ።
፴፬ ነገር ግን በሕዝብ ሁሉ ዘንድ የከበረ የሕግ መምህር ገማልያል የሚሉት አንድ ፈሪሳዊ በሸንጎ ተነሥቶ ሐዋርያትን ጥቂት ፈቀቅ እንዲያደርጉአቸው አዘዘ፥
፴፭ እንዲህም አላቸው። የእስራኤል ሰዎች ሆይ፥ ሰለ እነዚህ ሰዎች ምን እንደምታደርጉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።
፴፮ ከዚህ ወራት አስቀድሞ ቴዎዳስ። እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ ተነሥቶ ነበርና፥ አራት መቶ የሚያህሉ ሰዎችም ከእርሱ ጋር ተባበሩ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበተኑ እንደ ምናምንም ሆኑ።
፴፯ ከዚህ በኋላ ሰዎች በተጸፉበት ዘመን የገሊላው ይሁዳ ተነሣ ብዙ ሰዎችንም አሸፍቶ አስከተለ፤ እርሱም ጠፋ የሰሙትም ሁሉ ተበታተኑ።
፴፰ አሁንም እላችኋለሁ። ከእነዚህ ሰዎች ተለዩ ተዉአቸውም፤ ይህ አሳብ ወይም ይህ ሥራ ከሰው እንደ ሆነ ይጠፋልና፤
፴፱ ከእግዚአብሔር እንደ ሆነ ግን ታጠፉአቸው ዘንድ አይቻላችሁም፥ በእርግጥ ከእግዚአብሔር ጋር ሰትጣሉ ምናልባት እንዳትገኙ።
፵ ሰሙትም፥ ሐዋርያትንም ወደ እነርሱ ጠርተው ገረፉአቸው፥ በኢየሱሰም ሰም እንዳይናገሩ አዝዘው ፈቱአቸው።
፵፩ እነርሱም ሰለ ሰሙ ይናቁ ዘንድ የተገባቸው ሆነው ሰለ ተቈጠሩ ከሸንጎው ፊት ደስ እያላቸው ወጡ፤

፴፪ ዕለት ዕለትም በመቅደስና በቤታቸው ሰለ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ማስተማርንና መስበክን አይተዉም ነበር።

፮

፩ በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና።

፪ አሥራ ሁለቱም ደቀ መዛሙርት ሁሉን ጠርተው እንዲህ አሉአቸው። የእግዚአብሔር ቃል ትተን ማዕድን እናገለግል ዘንድ የሚገባ ነገር አይደለም።

፫ ወንድሞች ሆይ፥ በመልካም የተመሰከረላቸውን መንፈስ ቅዱስና ጥበብም የሞላባቸውን ሰባት ሰዎች ከእናንተ ምረጡ፥ ለዚህም ጉዳይ እንሾማቸዋለን፤

፬ እኛ ግን ለጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን።

፭ ይህም ቃል ሕዝብን ሁሉ ደስ አሰኛቸው፤ እምነትና መንፈስ ቅዱስም የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ፊልጶስንም ጵሮኮሮስንም ኒቃሮናንም ጢሞናንም ጳርሜናንም ወደ ይሁዲነት ገብቶ የነበረውን የአንጾኪያውን ኒቆላዎስንም መረጡ።

፮ በሐዋርያትም ፊት አቆሙአቸው፥ ከጸለዩም በኋላ እጆቻውን ጫኑባቸው።

፯ የእግዚአብሔርም ቃል እየሰፋ ሄደ፥ በኢየሩሳሌምም የደቀ መዛሙርት ቍጥር እጅግ እየበዛ ሄደ፤ ከካህናትም ብዙ ሰዎች ለሃይማኖት የታዘዙ ሆኑ።

፰ እስጢፋኖስም ጸጋንና ኃይልን ተሞልቶ በሕዝቡ መካከል ድንቅንና ታላቅ ምልክትን ያደርግ ነበር።

፱ የነፃ ወጪዎች ከተባለችው ምኵራብም ከቀሬናና ከእስክንድርያም ሰዎች ከኪልቅያና ከእስያም ከነበሩት አንዳንዶቹ ተነሥተው እስጢፋኖስን ይከራከሩት ነበር፤

፲ ይናገርበት የነበረውንም ጥበብና መንፈስ ይቃወሙ ዘንድ አልቻሉም።

፲፩ በዚያን ጊዜ። በሙሴ ላይ በእግዚአብሔርም ላይ የሰድብን ነገር ሲናገር ሰምተነዋል የሚሉ ሰዎችን አስነሡ።

፲፪ ሕዝቡንና ሽማግሌዎችንም ጸሮችንም አናደዱ፥ ቀርበውም ያዙት ወደ ሸንጎም አመጡትና።

፲፫ ይህ ሰው በዚህ በተቀደሰው ሰፍራ በሕግም ላይ የሰድብን ነገር ለመናገር አይተውም፤

፲፬ ይህ የናዝሬቱ ኢየሱስ ይህን ሰፍራ ያፈርሰዋል ሙሴም ያስተላለፈልንን ሥርዓት ይለውጣል ሲል ሰምተነዋልና የሚሉ የሐሰት ምስክሮችን አቆሙ።

፲፭ በሸንጎም የተቀመጡት ሁሉ ትኵር ብለው ሲመለከቱት እንደ መልአክ ፊት ሆኖ ፊቱን አዩት።

፯

፩ ሊቀ ካህናቱም። ይህ ነገር እንዲህ ነውን? አለው፤

፪ እርሱም እንዲህ አለ። ወንድሞችና አባቶች ሆይ፥ ሰሙ። የክብር አምላክ ለአባታችን ለአብርሃም በካራን ሳይቀመጥ ገና በሁለት ወንዝ መካከል ሳለ ታየና።

፫ ከአገርህና ከዘመዶችህም ወጥተህ ወደማሳይህ ወደ ማንኛውም ምድር ና አለው።

፬ በዚያን ጊዜ ከከለዳውያን አገር ወጥቶ በካራን ተቀመጠ። ከዚያም አባቱ ከሞተ በኋላ እናንተ ዛሬ ወደምትኖሩባት ወደዚች አገር አወጣው።

፭ በዚችም የእግር ጫማ ሰንኳ የሚያህል ርስት አልሰጠውም፤ ነገር ግን ልጅ ሳይኖረው ለእርሱ ከእርሱም በኋላ ለዘሩ ርስት አድርጎ ይሰጠው ዘንድ ተሰፋ ሰጠው።

፮ እግዚአብሔርም ዘሩ በሌላ አገር መጻተኞች እንዲሆኑ እራት መቶ ዓመትም ባሪያዎች እንዲያደርጉአቸው እንዲያሰጨንቁአቸውም እንዲህ ተናገረ፤

፯ ደግሞም እግዚአብሔር። እንደ ባሪያዎች በሚገዙአቸው ሕዝብ ላይ እኔ እፈርድባቸዋለሁ፥ ከዚህም በኋላ ይወጣሉ በዚህም ሰፍራ ያመልኩኛል አለ።

፰ የመገረዝንም ኪዳን ሰጠው፤ እንዲሁም ይስሐቅን ወለደ በሰምንተኛውም ቀን ገረዘው ይስሐቅም ያዕቆብን ያዕቆብም አሥራ ሁለቱን የአባቶችን አለቆች።

፱ የአባቶችም አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብፅ ሸጡት፤ እግዚአብሔርም ከእርሱ ጋር ነበረ፥

፲ ከመከራውም ሁሉ አወጣው፥ በግብፅ ንጉሥ በፈርዖንም ፊት ሞገስንና ጥበብን ሰጠው፥ በግብፅና በቤቱ ሁሉ ላይም ቢትወደድ አድርጎ ሾመው።

፲፩ በግብፅና በከነዓንም አገር ሁሉ ራብና ብዙ ጭንቅ መጣ፥ አባቶቻችንም ምግብን አላገኙም።

፲፪ ያዕቆብም በግብፅ እህል መኖሩን በሰማ ጊዜ በመጀመሪያ አባቶቻችንን ሰደዳቸው፤

፲፫ በሁለተኛውም ዮሴፍ ለወንድሞቹ ታወቀ፥ የዮሴፍም ትውልድ በፈርዖን ዘንድ ተገለጠ።

፲፬ ዮሴፍም አባቱን ያዕቆብንና ሰባ አምስት ነፍስ የነበረውን ቤተ ዘመድ ሁሉ ልኮ አስጠራ።

፲፭ ያዕቆብም ወደ ግብፅ ወረደ እርሱም ሞተ አባቶቻችንም፤

፲፮ ወደ ሴኬምም አፍልሰው አብርሃም ከሴኬም አባት ከኤሞር ልጆች በብር በገዛው መቃብር ቀበሩአቸው።

፲፯-፲፱ እርሱም ወገናችንን ተተንኩሎ ሕፃናትን በሕይወት እንዳይጠብቁ ወደ ውጭ ይጥሉ ዘንድ አድርጎ አባቶቻችንን አሰጨነቀ።

፳ በዚያን ጊዜ ሙሴ ተወለደ በእግዚአብሔርም ፊት ያማረ ነበር፤ በአባቱ ቤትም ሦስት ወር አደገ፤

፳፩ በተጣለም ጊዜ የፈርዖን ልጅ አነሣችው ልጅም ይሆናት ዘንድ አሳደገችው።

፳፪ ሙሴም የግብፆችን ጥበብ ሁሉ ተማረ፥ በቃሉና በሥራውም የበረታ ሆነ።

፳፫ ነገር ግን እርባ ዓመት ሲሞላው ወንድሞቹን የእስራኤልን ልጆች ይጐበኝ ዘንድ በልቡ አሰበ።

፳፬ አንዱም ሲበደል አይቶ ረዳው፥ የግብፅን ሰውም መትቶ ለተገፋው ተበቀለ።

፳፭ ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመሰለው ነበር፥ እነርሱ ግን አላስተዋሉም።

፳፮ በማግሥቱም እርስ በርሳቸው ሲጣሉ አገኛቸው፥ ሊያስታርቃቸውም ወደ። ሰዎች ሆይ፥ እናንተስ ወንድማማች ናችሁ፤ ስለ ምን እርስ በርሳችሁ ትበዳደላላችሁ? አላቸው።

፳፯ ያም ባልንጀራውን የሚበድል ግን። እንተን በእኛ ላይ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው?

፳፯ ወይስ ትናንትና የግብፁን ሰው እንደ ገደልኸው ልትገድለኝ ትወዳለህን? ብሎ ገፋው።
፳፰ ሙሴም ከዚህ ነገር የተነሣ ሸሽቶ በምድያም አገር መጻተኛ ሆኖ ኖረ፤ በዚያም ሁለት ልጆች ወለደ።
፳፱ አርባ ዓመትም ሲሞላ የጌታ መልአክ በሲና ተራራ ምድረ በዳ በቍጥቋጦ መካከል በእሳት ነበልባል ታየው።
፴-፴፫ ጌታም። የቆምህባት ሰፍራ የተቀደሰች ምድር ናትና የእግርህን ጫማ አውልቅ።
፴፬ በግብፅ ያሉትን የሕዝቤን መከራ ፈጽሜ አይቼ መቃተታቸውንም ሰምቼ ላድናቸው ወረድሁ፤ አሁንም ና፥ ወደ ግብፅ እልክሃለሁ አለው።
፴፭ ሹምና ፈራጅ እንድትሆን የሾመህ ማን ነው? ብለው የካዱትን፥ ይህን ሙሴን በቍጥቋጦው በታየው በመልአኩ እጅ እግዚአብሔር ሹምና ቤዛ አድርጎ ላከው።
፴፮ ይህ ሰው በግብፅ ምድርና በኤርትራ ባሕር በምድረ በዳም አርባ ዓመት ድንቅና ምልክት እያደረገ አወጣቸው።
፴፯ ይህ ሰው ለእስራኤል ልጆች። እግዚአብሔር ከወንድሞቻችሁ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣላችኋል፤ እርሱን ሰሙት ያላቸው ሙሴ ነው።
፴፰ ይህ ሰው በሲና ተራራ ከተናገረው መልአክና ከአባቶቻችን ጋር በምድረ በዳ በማኅበሩ ውስጥ የነበረው ነው፤ ይሰጠንም ዘንድ ሕይወት ያላቸውን ቃላት ተቀበለ፤
፴፱ ለእርሱም አባቶቻችን ሊታዘዙት አልወደዱም፤ ነገር ግን ገፉት በልባቸውም ወደ ግብፅ ተመለሱ፤
፵ አሮንንም። በፊታችን የሚሄዱ አማልክት ሥራልን፤ ይህ ከግብፅ ምድር ያወጣን ሙሴ ምን እንደ ሆነ አናውቅምና አሉት።
፵፩ በዚያም ወራት ጥጃ አደረጉ ለጣዖቱም መሥዋዕት አቀረቡ፥ በእጃቸውም ሥራ ደስ አላቸው።
፵፪ እግዚአብሔር ግን ዘወር አለ የሰማይንም ጭፍራ ያመልኩ ዘንድ አሳልፎ ሰጣቸው፥ በነቢያትም መጽሐፍ። እናንተ የእስራኤል ቤት፥ አርባ ዓመት በምድረ በዳ የታረደውን ከብትና መሥዋዕትን አቀረባችሁልኝን?
፵፫ ትሰግዱላቸውም ዘንድ የሠራችኋቸውን ምስሎች እነርሱንም የሞሎክን ድንኳንና ሬምፋም የሚሉትን የአምላካችሁን ኮከብ አነሣችሁ፤ እኔም ከባቢሎን ወዲያ እስዳችኋለሁ ተብሎ እንዲህ ተጽፎአል።
፵፬ እንዳየው ምስል አድርጎ ይሠራት ዘንድ ሙሴን ተናግሮ እንዳዘዘው፥ የምስክር ድንኳን ከአባቶቻችን ዘንድ በምድረ በዳ ነበረች፤
፵፭ አባቶቻችንም ደግሞ በተራ ተቀብለው እግዚአብሔር በፊታቸው ያወጣቸውን የአሕዛብን አገር በያዙት ጊዜ ከኢያሱ ጋር አገቡአት፥ እስከ ዳዊት ዘመንም ድረስ ኖረች።
፵፮ እርሱም በእግዚአብሔር ፊት ሞገስ አግኝቶ ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያን ያገኝ ዘንድ ለመነ።
፵፯ ነገር ግን ሰሎሞን ቤት ሠራለት።
፵፰-፵፱ እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሮአችሁም ያልተገረዘ፥ እናንተ ሁልጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ።
፶-፶፩ ይህንም በሰሙ ጊዜ በልባቸው በጣም ተቈጡ ጥርሳቸውንም አፋጩበት።
፶፪ መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና።
፶፫ እነሆ፥ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።
፶፬ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ ጆሮአቸውን ደፈኑ፥ በእኩድ ልብ ሆነውም ወደ እርሱ ሮጡ፥
፶፭ ከከተማም ወደ ውጭ አውጥተው ወገሩት። ምስክሮችም ልብሳቸውን ሳውል በሚሉት በአንድ ጎበዝ እግር አጠገብ አኖሩ።
፶፮ እስጢፋኖስም። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር።
፶፯ ተንበርክኮም። ጌታ ሆይ፥ ይህን ኃጢአት አትቍጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ። ይህንም ብሎ አንቀላፋ። ሳውልም በእርሱ መገደል ተስማምቶ ነበር።

፰

፩ በዚያን ቀንም በኢየሩሳሌም ባለች ቤተ ክርስቲያን ላይ ታላቅ ስደት ሆነ፤ ሁሉም ከሐዋርያትም በቀር ወደ ይሁዳና ወደ ሰማርያ አገሮች ተበተኑ።
፪ በጸሎትም የተጉ ሰዎች እስጢፋኖስን ቀበሩት ታላቅ ልቅሶም አለቀሱለት።
፫ ሳውል ግን ቤተ ክርስቲያንን ያፈርስ ነበር፤ ወደ ሁሉም ቤት እየገባ ወንዶችንም ሴቶችንም እየጐተተ ወደ ወኅኒ አሳልፎ ይሰጥ ነበር።
፬ የተበተኑትም ቃሉን እየሰበኩ ዞሩ።
፭ ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው።
፮ ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ ያደርጋት የነበረውንም ምልክት ባዩ ጊዜ፥ የተናገረውን በአንድ ልብ እደመጡ።
፯ ርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና፤ ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ፤
፰ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ።
፱ ሲሞን የሚሉት አንድ ሰው ግን። እኔ ታላቅ ነኝ ብሎ፥ እየጠነቈል የሰማርያንም ወገን እያሰገረመ ቀድሞ በከተማ ነበረ።
፲ ከታናናሾችም ጀምሮ እስከ ታላላቆቹ ድረስ። ታላቁ የእግዚአብሔር ኃይል ይህ ነው እያሉ ሁሉ ያደምጡት ነበር።
፲፩ ከብዙ ዘመንም ጀምሮ በጥንቈላ ስላሰገረማቸው ያደምጡት ነበር።
፲፪ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር መንግሥትና ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም እየሰበከላቸው ፊልጶስን ባመኑት ጊዜ፥ ወንዶችም ሴቶችም ተጠመቁ።
፲፫ ሲሞንም ደግሞ ራሱ አመነ፤ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር፤ የሚደረገውንም ምልክትና ታላቅ ተአምራት ባየ ጊዜ ተገረመ።
፲፬ በኢየሩሳሌምም የነበሩት ሐዋርያት የሰማርያ ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል እንደተቀበሉ ሰምተው ጴጥሮስንና ዮሐንስን ሰደዱላቸው።
፲፭ እነርሱም በወረዱ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ይቀበሉ ዘንድ ጸለዩላቸው፤

፲፭ በጌታ በኢየሱስ ስም ብቻ ተጠምቀው ነበር እንጂ
ከእነርሱ በእንዱ ላይ ሰንኳ ገና አልወረደም ነበርና።
፲፮ በዚያን ጊዜ እጆቸውን ጫኑባቸው መንፈስ
ቅዱስንም ተቀበሉ።
፲፯ ሲሞንም በሐዋርያት እጅ መጫን መንፈስ ቅዱስ
እንዲሰጥ ባየ ጊዜ፥ ገንዘብ አመጣላቸውና።
፲፰ እጄን የምጭንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስን ይቀበል
ዘንድ ለእኔ ደግሞ ይህን ሥልጣን ስጡኝ አለ።
፲፱ ጴጥሮስ ግን እንዲህ አለው። የእግዚአብሔርን
ስጦታ በገንዘብ እንድታገኝ አሰበሃልና ብርህ ከአንተ
ጋር ይጥፋ።
፳ ልብህ በእግዚአብሔር ፊት የቀና አይደለምና
ከዚህ ነገር ዕድል ወይም ፈንታ የለህም።
፳፩ እንግዲህ ስለዚህ ክፋትህ ንስሐ ግባ፥
ምናልባትም የልብህን አሳብ ይቅር ይልህ እንደ ሆነ
ወደ እግዚአብሔር ለምን፤
፳፪ በመራራ መርዝና በዓመፅ እሰራት እንዳለህ
አይሃለሁና።
፳፫ ሲሞንም መልሶ። ካላችሁት አንዳች
እንዳይደርስብኝ እናንተው ወደ ጌታ ለምኑልኝ
አላቸው።
፳፬ እነርሱም ከመሰከሩና የጌታን ቃል ከተናገሩ
በኋላ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤ በሳምራውያን በብዙ
መንደሮችም ወንጌልን ሰበኩ።
፳፭ የጌታም መልአክ ፊልጶስን። ተነሥተህ በደቡብ
በኩል ከኢየሩሳሌም ወደ ጋዛ ወደሚያወርደው ምድረ
በዳ ወደ ሆነ መንገድ ሂድ አለው።
፳፮ ተነሥቶም ሄደ። እነሆም፥ ህንደኬ የተባለች
የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥና ጃንደረባ የነበረ
በገንዘብዋም ሁሉ የሠለጠነ አንድ የኢትዮጵያ ሰው
ሊሰግድ ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ነበር፤
፳፯ ሲመለስም በሰረገላ ተቀምጦ የነቢዩን
የኢሳይያስን መጽሐፍ ያነብ ነበር።
፳፰ መንፈስም ፊልጶስን። ወደዚህ ሰረገላ ቅረብና
ተገናኝ አለው።
፳፱ ፊልጶስም ሮጦ የነቢዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ
ሲያነብ ሰማና። በውኑ የምታነበውን ታስተውለዋለህን?
አለው።
፴ እርሱም። የሚመራኝ ሳይኖር ይህ እንዴት
ይቻለኛል? አለው። ወጥቶም ከእርሱ ጋር ይቀመጥ
ዘንድ ፊልጶስን ለመነው።
፴፩ ያነበውም የነበረ የመጽሐፉ ክፍል ይህ ነበረ፤
እንደ በግ ወደ መታረድ ተነዳ፥ የበግ ጠቦትም በሸላቹ
ፊት ዝም እንደሚል፥ እንዲሁ አፉን አልከፈተም።
፴፪ በውርደቱ ፍርዱ ተወገደ፤ ሕይወቱ ከምድር
ተወግዳለችና ትውልዱንስ ማን ይናገራል?
፴፫ ጃንደረባውም ለፊልጶስ መልሶ። እባክህ፥ ነቢዩ
ይህን ስለ ማን ይናገራል? ስለ ራሱ ነውን ወይስ ስለ
ሌላ? አለው።
፴፬ ፊልጶስም አፉን ከፈተ፥ ከዚህም መጽሐፍ ጀምሮ
ስለ ኢየሱስ ወንጌልን ሰበከለት።
፴፭ በመንገድም ሲሄዱ ወደ ውኃ ደረሱ፤
ጃንደረባውም። እነሆ ውኃ፤ እንዳልጠመቅ
የሚከለክለኝ ምንድር ነው? አለው።
፴፮ ፊልጶስም። በፍጹም ልብህ ብታምን፥ ተፈቅዶአል
አለው። መልሶም። ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር
ልጅ እንደ ሆነ አምናለሁ አለ።
፴፯ ሰረገላውም ይቆም ዘንድ አዘዘ፥ ፊልጶስና
ጃንደረባው ሁለቱም ወደ ውኃ ወረዱ፥ አጠመቀውም።
፴፰ ከውኃውም ከወጡ በኋላ የጌታ መንፈስ
ፊልጶስን ነጠቀው፤ ጃንደረባውም ሁለተኛ አላየውም፥
ደስ ብሎት መንገዱን ይሄድ ነበርና።
፴፱ ፊልጶስ ግን በአዛጦን ተገኘ፥ ወደ ቂሣርያም
እስኪመጣ ድረስ እየዞረ በከተማዎች ሁሉ ወንጌልን
ይሰብክ ነበር።

፱

፩ ሳውል ግን የጌታን ደቀ መዛሙርት
እንዲገድላቸው ገና እየዛተ ወደ ሊቀ ካህናት ሄደ፥
፪ በዚህ መንገድ ያሉትንም ሰዎች ወንዶችንም
ሴቶችንም ቢያገኝ፥ እያሰረ ወደ ኢየሩሳሌም ያመጣቸው
ዘንድ በደማስቆ ላሉት ምኩራቦች ደብዳቤ ከእርሱ
ለመነ።
፫ ሲሄድም ወደ ደማስቆ በቀረበ ጊዜ ድንገት
በእርሱ ዙሪያ ከሰማይ ብርሃን አንጸባረቀ፤
፬ በምድርም ላይ ወድቆ ሳለ። ሳውል ሳውል፥ ስለ
ምን ታሳድደኛለህ? የሚለውን ድምፅ ሰማ።
፭ ጌታ ሆይ፥ ማን ነህ? አለው። እርሱም። አንተ
የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ፤ የመውጊያውን ብረት
ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል አለው።
፮ እየተንቀጠቀጠና እየተደነቀ። ጌታ ሆይ፥ ምን
እደርግ ዘንድ ትወዳለህ? አለው። ጌታም። ተነሥተህ
ወደ ከተማ ግባና ታደርገው ዘንድ የሚያስፈልግህን
ይነግሩሃል አለው።
፯ ከእርሱም ጋር በመንገድ የሄዱ ሰዎች ድምፁን
እየሰሙ ማንን ግን ሳያዩ እንደ ዲዳዎች ቁመው።
፰ ሳውልም ከምድር ተነሣ፥ እይኖቹም በተከፈቱ ጊዜ
ምንም አላየም፤ እጁንም ይዘው እየመሩ ወደ ደማስቆ
አገቡት።
፱ ሳያይም ሦስት ቀን ኖረ፤ አልበላምም
አልጠጣምም።
፲ በደማስቆም ሐናንያ የሚሉት አንድ ደቀ መዝሙር
ነበረ፥ ጌታም በራእይ። ሐናንያ ሆይ፥ አለው። እርሱም።
ጌታ ሆይ፥ እነሆኝ አለ።
፲፩ ጌታም። ተነሥተህ ቅን ወደ ሚባለው መንገድ
ሂድ፥ በይሁዳ ቤትም ሳውል የሚሉትን አንድ
የጠርሴስ ሰው ፈልግ፤
፲፪ እነሆ፥ እርሱ ይጸልያልና፤ ሐናንያ የሚሉትም ሰው
ገብቶ ደግሞ እንዲያይ እጁን ሲጭንበት አይቶአል
አለው።
፲፫ ሐናንያም መልሶ። ጌታ ሆይ፥ በኢየሩሳሌም
በቅዱሳንህ ላይ ሰንት ክፉ እንዳደረገ ስለዚህ ሰው
ከብዙዎች ሰምቼአለሁ፤
፲፬ በዚህም ስምህን የሚጠሩትን ሁሉ ለማሰር
ከካህናት አለቆች ሥልጣን አለው አለ።
፲፭ ጌታም። ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም
በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ
የተመረጠ ዕቃ ነውና ሂድ፤
፲፮ ስለ ስሜ ስንት መከራ ሊቀበል እንዲያስፈልገው
እኔ እመለክተዋለሁና አለው።
፲፯ ሐናንያም ሄደ ወደ ቤቱ ገባ፥ እጁንም ጭኖበት።
ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ ጌታ፥ እርሱም በመጣህበት
መንገድ የታየህ ኢየሱስ ነው፥ ደግሞ ታይ ዘንድና
መንፈስ ቅዱስ ይሞላብህ ዘንድ ላከኝ አለ።

፲፭ ወዲያውም እንደ ቅርፊት ያለ ከዓይኑ ወደቀ፥ ያን
ጊዜም ደግሞ አየ፤ ተነሥቶም ተጠመቀ፥
፲፱ መብልም በልቶ በረታ። በደማስቆም ካሉት ደቀ
መዛሙርት ጋር ጥቂት ቀን ኖረ።
፳ ወዲያውም ሰለ ኢየሱስ ክርስቶስ እርሱ
የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በምኩራቦቹ ሰበከ።
፳፩ የሰሙትም ሁሉ ተገረሙና። ይህ በኢየሩሳሌም
ይህን ሰም የሚጠሩትን ያጠፋ አይደለምን? ሰለዚህስ
ታስረው ወደ ካህናት አለቆች ይወስዳቸው ዘንድ
ወደዚህ አልመጣምን? አሉ።
፳፪ ሳውል ግን እየበረታ ሄደ፥ በደማስቆም
ለተቀመጡት አይሁድ ይህ ክርስቶስ እንደ ሆነ
አስረድቶ መልስ ያሳጣቸው ነበር።
፳፫ ብዙ ቀንም ሲሞላ አይሁድ ሊገድሉት ተማከሩ፤
፳፬ ሳውል ግን አሳባቸውን አወቀ። ይገድሉትም
ዘንድ በሌሊትና በቀን የከተማይቱን በር ሁሉ
ይጠብቁ ነበር፤
፳፭ ደቀ መዛሙርት ግን በሌሊት ወስደው በቅጥር
ላይ አሳልፈው በቅርጫት አወረዱት።
፳፮ ሳውልም ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰ ጊዜ ከደቀ
መዛሙርት ጋር ይተባበር ዘንድ ሞከረ፤ ሁሉም ደቀ
መዝሙር እንደ ሆነ ሰላላመኑ ፈሩት።
፳፯ በርናባስ ግን ወስዶ ወደ ሐዋርያት አገባውና
ጌታን በመንገድ እንዴት እንዳየውና እንደ ተናገረው
በደማስቆም በኢየሱስ ሰም ደፍሮ እንዴት እንደ ነገረ
ተረከላቸው።
፳፰ በጌታም በኢየሱስ ሰም ደፍሮ እየተናገረ
በኢየሩሳሌም ሲወጣና ሲገባ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤
፳፱ ከግሪክ አገርም መጥተው ከነበሩት አይሁድ
ጋር ይነጋገርና ይከራከር ነበር፤ እነርሱ ግን ሊገድሉት
ፈለጉ።
፴ ወንድሞችም ይህን ባወቁ ጊዜ ወደ ቂሣርያ
ወሰዱት ወደ ጠርሴስም ሰደዱት።
፴፩ በይሁዳም ሁሉና በገሊላ በሰማርያም
የነበሩት አብያተ ክርስቲያናት በሰላም ኖሩ ታነጹም፤
በእግዚአብሔርም ፍርሃትና በመንፈስ ቅዱስ መጽናናት
እየሄዱ ይበዙ ነበር።
፴፪ ጴጥሮስም በየሰፍራው ሁሉ ሲዞር በልዳ
ወደሚኖሩ ቅዱሳን ደግሞ ወረደ።
፴፫ በዚያም ከሰምንት ዓመት ጀምሮ በአልጋ ላይ
ተኝቶ የነበረውን ኤንያ የሚሉትን አንድ ሰው አገኘ፤
እርሱም ሽባ ነበረ።
፴፬ ጴጥሮስም። ኤንያ ሆይ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ
ይፈውስሃል፤ ተነሣ ለራስህም አንጥፍ አለው።
፴፭ ወዲያውም ተነሣ። በልዳና በሰሮናም የሚኖሩ
ሁሉ እርሱን አይተው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።
፴፮ በኢዮጴም ጣቢታ የሚሉአት አንዲት ደቀ
መዝሙር ነበረች፥ ትርጓሜውም ዶርቃ ማለት ነው፤
እርስዋም መልካም ነገር የሞላባት ምጽዋትም
የምታደርግ ነበረች።
፴፯ በዚያም ወራት ታመመችና ሞተች፤ አጥበውም
በሰገነት አኖሩአት።
፴፰ ልዳም ለኢዮጴ ቅርብ ናትና ደቀ መዛሙርት
ጴጥሮስ በዚያ እንዳለ ሰምተው፥ ወደ እነርሱ
ከመምጣት እንዳይዘገይ እየለመኑ ሁለት ሰዎች ወደ
እርሱ ላኩ።
፴፱ ጴጥሮስም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር መጣ፤
በደረሰም ጊዜ በሰገነት አወጡት መበለቶችም ሁሉ
እያለቀሱ ዶርቃ ከእነርሱ ጋር ሳለች ያደረገቻቸውን
ቀሚሶችንና ልብሶችን ሁሉ እያሳዩት በፊቱ ቆሙ።
፵ ጴጥሮስም ሁሉን ወደ ውጭ አሰወጥቶ
ተንበርክኮም ጸለየ፥ ወደ ሬሳውም ዘወር ብሎ። ጣቢታ
ሆይ፥ ተነሺ አላት። እርስዋም ዓይኖችዋን ከፈተች
ጴጥሮስንም ባየች ጊዜ ተቀመጠች።
፵፩ እጁንም ለእርስዋ ሰጥቶ አስነሣት፤ ቅዱሳንንና
መበለቶችንም ጠራ ሕያውም ሆና በፊታቸው አቆማት።
፵፪ ይህም በኢዮጴ ሁሉ የታወቀ ሆነ፥ ብዙ ሰዎችም
በጌታ አመኑ።
፵፫ በኢዮጴም ስምዖን ከሚሉት ከአንድ ቍርበት ፋቂ
ጋር አያሌ ቀን ኖረ።

፲

፩ በቂሣርያም ኢጣሊቄ ለሚሉት ጭፍራ የመቶ
አለቃ የሆነ ቆርኔሌዎስ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ።
፪ እርሱም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር እግዚአብሔርን
የሚያመልክና የሚፈራ ለሕዝብም እጅግ ምጽዋት
የሚያደርግ ወደ እግዚአብሔርም ሁልጊዜ የሚጸልይ
ነበረ።
፫ ከቀኑም ዘጠኝ ሰዓት ያህል። ቆርኔሌዎስ ሆይ
የሚለው የእግዚአብሔር መልአክ ወደ እርሱ ሲገባ
በራእይ በግልጥ አየው።
፬ እርሱም ትኩር ብሎ ሲመለከተው ደንግጦ።
ጌታ ሆይ፥ ምንድር ነው? አለ። መልአኩም አለው።
ጸሎትህና ምጽዋትህ በእግዚአብሔር ፊት ለመታሰቢያ
እንዲሆን አረገ።
፭ አሁንም ወደ ኢዮጴ ሰዎችን ልከህ ጴጥሮስ
የሚባለውን ሰምዖንን አስመጣ።
፮ እርሱ ቤቱ በባሕር አጠገብ ባለው በቍርበት
ፋቂው በሰምዖን ዘንድ እንግድነት ተቀምጦአል፤
ልታደርገው የሚገባህን እርሱ ይነግርሃል።
፯ የተናገረውም መልአክ በሄደ ጊዜ፥ ከሎሎዎቹ
ሁለቱን፥ ከማይለዩትም ጭፍሮቹ እግዚአብሔርን
የሚያመልክ አንዱን ወታደር ጠርቶ፥
፰ ነገሩን ሁሉ ተረከላቸው ወደ ኢዮጴም ላካቸው።
፱ እነርሱም በነገው ሲሄዱ ወደ ከተማም ሲቀርቡ፥
ጴጥሮስ በስድስት ሰዓት ያህል ይጸልይ ዘንድ ወደ
ጣራው ወጣ።
፲ ተርቦም ሊበላ ወደደ፤ ሲያዘጋጁለት ሳሉም
ተመሰጠ መጣበት፤
፲፩ ሰማይም ተከፍቶ በአራት ማዕዘን የተያዘ ታላቅ
ሸማ የሚመስል ዕቃ ወደ ምድር ሲወርድ አየ፤
፲፪ በዚያውም አራት እግር ያላቸው ሁሉ አራዊትም
በምድርም የሚንቀሳቀሱት የሰማይ ወፎችም ነበሩበት።
፲፫ ጴጥሮስ ሆይ፥ ተነሣና እርደህ ብላ የሚልም
ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።
፲፬ ጴጥሮስ ግን። ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ እንዳች
ርኩስ የሚያስጸይፍም ከቶ በልቼ አላውቅምና አለ።
፲፭ ደግሞም ሁለተኛ። እግዚአብሔር ያነጻውን እንተ
አታርክሰው የሚል ድምፅ ወደ እርሱ መጣ።
፲፮ ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ፥ ወዲያውም ዕቃው ወደ
ሰማይ ተወሰደ።

፲፯ ጴጥሮስም ሰላየው ራእይ። ምን ይሆን? ብሎ በልቡ ሲያመነታ፥ እነሆ፥ ቆርኔሌዎስ የላካቸው ሰዎች ስለ ስምዖን ቤት ጠይቀው ወደ ደጁ ቀረቡ፤
፲፰ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው። ጴጥሮስ የተባለው ስምዖን በዚህ እንግድነት ተቀምጦአልን? ብለው ይጠይቁ ነበር።
፲፱ ጴጥሮስም ስለ ራእዩ ሲያወጣ ሲያወርድ ሳለ፥ መንፈስ። እነሆ፥ ሦስት ሰዎች ይፈልጉሃል፤
፳ ተነሥተህ ውረድ፥ እኔም ልኬአቸዋለሁና ሳትጠራጠር ከእነርሱ ጋር ሂድ አለው።
፳፩ ጴጥሮስም ወደ ሰዎቹ ወርዶ። እነሆ፥ የምትፈልጉኝ እኔ ነኝ፤ የመጣችሁበትስ ምክንያት ምንድር ነው? አላቸው።
፳፪ እነርሱም። ጻድቅ ሰው እግዚአብሔርንም የሚፈራ በአይሁድም ሕዝብ ሁሉ የተመሰከረለት የመቶ አለቃ ቆርኔሌዎስ ወደ ቤቱ ያስመጣህ ዘንድ ከአንተም ቃልን ይሰማ ዘንድ ከቅዱስ መልአክ ተረዳ አሉት።
፳፫ እርሱም ወደ ውስጥ ጠርቶ እንድግድነት ተቀበላቸው። በነገውም ተነሥቶ ከእነርሱ ጋር ወጣ፥ በኢዮጴም ከነበሩት ወንድሞች አንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር አብረው ሄዱ።
፳፬ በነገውም ወደ ቂሣርያ ገቡ፤ ቆርኔሌዎስም ዘመዶቹንና የቅርብ ወዳጆቹን በአንድነት ጠርቶ ይጠባበቃቸው ነበር።
፳፭ ጴጥሮስም በገባ ጊዜ ቆርኔሌዎስ ተገናኝቶ ከእግሩ በታች ወደቀና ሰገደለት።
፳፮ ጴጥሮስ ግን። ተነሣ፤ እኔ ራሴ ደግሞ ሰው ነኝ ብሎ አስነሣው።
፳፯ ከእርሱም ጋር እየተነጋገረ ገባ፥ ብዙዎችም ተከማችተው አግኝቶ።
፳፰ አይሁዳዊ ሰው ከሌላ ወገን ጋር ይተባበር ወይም ይቃረብ ዘንድ እንዳልተፈቀደ እናንተ ታውቃላችሁ፤ ለእኔ ግን እግዚአብሔር ማንንም ሰው ርኩስና የሚያሰጸይፍ ነው እንዳልል አሳየኝ፤
፳፱ ስለዚህም ደግሞ ብትጠሩኝ ሳልከራከር መጣሁ። አሁንም በምን ምክንያት አስመጣችሁኝ? ብዬ እጠይቃችኋለሁ አላቸው።
፴ ቆርኔሌዎስም እንዲህ አለው። በዚች ሰዓት የዛሬ አራት ቀን የዘጠኝ ሰዓት ጸሎት በቤቴ እጸልይ ነበር፤ እነሆም፥ የሚያንጸባርቅ ልብስ የለበሰ ሰው በፊቴ ቆመና።
፴፩ ቆርኔሌዎስ ሆይ፥ በእግዚአብሔር ፊት ጸሎትህ ተሰማ ምጽዋትህም ታሰበ።
፴፪ እንግዲህ ወደ ኢዮጴ ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ስምዖንን አስጠራ፤ እርሱ በቍርበት ፋቂው በስምዖን ቤት በባሕር አጠገብ እንግድነት ተቀምጦአል አለኝ።
፴፫ ስለዚህ ያን ጊዜ ወደ አንተ ላክሁ፥ አንተም በመምጣትህ መልካም አድርገሃል። እንግዲህ አንተ ከእግዚአብሔር ዘንድ የታዘዝኸውን ሁሉ እንድንሰማ እኛ ሁላችን አሁን በእግዚአብሔር ፊት በዚህ አለን።
፴፬-፴፮ የሁሉ ጌታ በሚሆን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እየሰበከ ይህን ቃል ወደ እስራኤል ልጆች ላከ።
፴፯ የሐንስ ከሰበከው ጥምቀት በኋላ ከገሊላ ጀምሮ በይሁዳ ሁሉ የሆነውን ነገር እናንተ ታውቃላችሁ።
፴፰ እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና፤
፴፱ እኛም በአይሁድ አገርና በኢየሩሳሌም ባደረገው ነገር ሁሉ ምስክሮች ነን፤ እርሱንም በእንጨት ላይ ሰቅለው ገደሉት።
፵ እርሱን እግዚአብሔር በሦስተኛው ቀን አስነሣው ይገለጥም ዘንድ ሰጠው፤
፵፩ ይኸውም ለሕዝብ ሁሉ አይደለም ነገር ግን በእግዚአብሔር አስቀድሞ የተመረጡ ምስክሮች ለሆንን ለእኛ ነው እንጂ፤ ከሙታንም ከተነሣ በኋላ ከእርሱ ጋር የበላን የጠጣንም እኛ ነን።
፵፪ ለሕዝብም እንድንሰብክና በሕያዋንና በሙታን ሊፈርድ በእግዚአብሔር የተወሰነ እርሱ እንደ ሆነ እንመስክር ዘንድ አዘዘን።
፵፫ በእርሱ የሚያምን ሁሉ በስሙ የኃጢአቱን ስርየት እንዲቀበል ነቢያት ሁሉ ይመስክሩለታል።
፵፬ ጴጥሮስ ይህን ነገር ገና ሲናገር ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ቅዱስ ወረደ።
፵፭ ከጴጥሮስም ጋር የመጡት ሁሉ ከተገረዙት ወገን የሆኑ ምዕመናን በአሕዛብ ላይ ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ ስለ ፈሰሰ ተገረሙ፤
፵፮ በልሳኖች ሲናገሩ እግዚአብሔርንም ሲያከብሩ ሰምተዋቸዋልና።
፵፯ በዚያን ጊዜ ጴጥሮስ መልሶ። እነዚህ እንደ እኛ ደግሞ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉ እንዳይጠመቁ ውኃን ይከለክላቸው ዘንድ የሚችል ማን ነው? አለ።
፵፰ በኢየሱስ ክርስቶስ ስምም ይጠመቁ ዘንድ አዘዛቸው። ከዚህ በኋላ ጥቂት ቀን እንዲቀመጥ ለመኑት።

፲፩

፩ ሐዋርያትና በይሁዳም የነበሩት ወንድሞች አሕዛብ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ተቀበሉ ሰሙ።
፪ ጴጥሮስም ወደ ኢየሩሳሌም በወጣ ጊዜ ከተገረዙት ወገን የሆኑት ሰዎች ከእርሱ ጋር ተከራከረው።
፫ ወደልተገረዙ ሰዎች ገብተህ ከእነርሱ ጋር በላህ አሉት።
፬ ጴጥሮስ ግን ከመጀመሪያው ጀምሮ በተራ ገለጠላቸው እንዲህም አለ።
፭ እኔ በኢዮጴ ከተማ ሰጸልይ ሳለሁ ተመሰጩ ራእይን አየሁ፤ ታላቅ ሸማ የመሰለ ዕቃ በአራት ማዕዘን ተይዞ ከሰማይ ወረደና ወደ እኔ መጣ፤
፮ ይህንም ትኩር ብዬ ሰመለከት አራት እግር ያላቸውን የምድር እንሰሶች አራዊትንም ተንቀሳቃሾችንም የሰማይ ወፎችንም አየሁ።
፯ ጴጥሮስ ሆይ፥ ተነሣና አርደህ ብላ የሚለኝንም ድምፅ ሰማሁ።
፰ እኔም። ጌታ ሆይ፥ አይሆንም፤ ርኩስ ወይም የሚያሰጸይፍ ከቶ ወደ አፌ ገብቶ አያውቅምና አልሁ።
፱ ሁለተኛም። እግዚአብሔር ያነጻውን አንተ አታርክሰው የሚል ድምፅ ከሰማይ መለሰልኝ።
፲ ይህም ሦስት ጊዜ ሆነ እንደ ገናም ሁሉ ወደ ሰማይ ተሳበ።
፲፩ እነሆም፥ ያን ጊዜ ሦስት ሰዎች ከቂሣርያ ወደ እኔ ተልከው ወዳለሁበት ቤት ቀረቡ።

፲፪ መንፈስም ሳልጠራጠር ከእነርሱ ጋር እሄድ ዘንድ ነገረኝ። እነዚህም ሰድሰቱ ወንድሞች ደግሞ ከእኔ ጋር መጡ ወደዚያ ሰውም ቤት ገባን።
፲፫ እርሱም መልአክ በቤቱ ቆሞ እንዳየና። ወደ ኢዮጴ ሰዎች ልከህ ጴጥሮስ የተባለውን ሰምዖንን አስመጣ፤
፲፬ እርሱም አንተና የቤትህ ሰዎች ሁሉ የምትድኑበትን ነገር ይነግርሃል እንዳለው ነገረን።
፲፭ ለመናገርም በጀመርሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ደግሞ በመጀመሪያ እንደ ወረደ ለእነርሱ ወረደላቸው።
፲፮ የሐንስ በውኃ አጠመቀ እናንተ ግን በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ ያለውም የጌታ ቃል ትዝ አለኝ።
፲፯ እንግዲህ እግዚአብሔር በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላመነው ለእኛ ደግሞ እንደ ሰጠን ያን ስጦታ ለእነርሱ ከሰጠ፥ እግዚአብሔርን ለመከልከል እችል ዘንድ እኔ ማን ነበርሁ?
፲፰ ይህን በሰሙ ጊዜም ዝም አሉና። እንኪያስ እግዚአብሔር ለአሕዛብ ደግሞ ለሕይወት የሚሆን ንስሐን ሰጣቸው እያሉ እግዚአብሔርን አከበሩ።
፲፱ በእስጢፋኖስም ላይ በተደረገው መከራ የተበተኑት እስከ ፊንቄ እስከ ቆጵሮስም እስከ አንጾኪያም ድረስ ዞሩ፥ ቃሉንም ለአይሁድ ብቻ እንጂ ለአንድ ሰንኳ አይናገሩም ነበር።
፳ ከእነርሱ ግን የቆጵሮስና የቀሬና ሰዎች የነበሩት አንዳንዶቹ ወደ አንጾኪያ መጥተው የጌታን የኢየሱስን ወንጌል እየሰበኩ ለግሪክ ሰዎች ተናገሩ።
፳፩ የጌታም እጅ ከእነርሱ ጋር ነበረ፤ ቍጥራቸውም እጅግ የሚሆን ሰዎች አምነው ወደ ጌታ ዘወር አሉ።
፳፪ ወሬውም በኢየሩሳሌም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ስለ እነርሱ ተሰማ፥ በርናባስንም ወደ አንጾኪያ ላኩት፤
፳፫ እርሱም መጥቶ የእግዚአብሔርን ጸጋ ባየ ጊዜ ደስ አለው፥ ሁሉንም በልባቸው ፈቃድ በጌታ ጸንተው ይኖሩ ዘንድ መከራቸው፤
፳፬ ደግ ሰውና መንፈስ ቅዱስ እምነትም የሞላበት ነበረና። ብዙ ሕዝብም ወደ ጌታ ተጨመሩ።
፳፭ በርናባስም ሳውልን ሊፈልግ ወደ ጠርሴስ መጣ፤
፳፮ ባገኘውም ጊዜ ወደ አንጾኪያ አመጣው። በቤተ ክርስቲያንም አንድ ዓመት ሙሉ ተሰበሰቡ፥ ብዙ ሕዝብንም አስተማሩ፤ ደቀ መዛሙርትም መጀመሪያ በአንጾኪያ ክርስቲያን ተባሉ።
፳፯ በዚያም ወራት ነቢያት ከኢየሩሳሌም ወደ አንጾኪያ ወረዱ፤
፳፰ ከእነርሱም አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ተነሥቶ በዓለም ሁሉ ታላቅ ራብ ሊሆን እንዳለው በመንፈስ አመለከተ፤ ይህም በቀላውዴዎስ ቄሣር ዘመን ሆነ።
፳፱ ደቀ መዛሙርትም እያንዳንዳቸው እንደ ችሎታቸው መጠን እዋጥተው በይሁዳ ለሚኖሩት ወንድሞች እርዳታን ይልኩ ዘንድ ወሰኑ፤
፴ እንዲህም ደግሞ አደረጉ፥ በበርናባስና በሳውልም እጅ ወደ ሽማግሌዎቹ ሰደዱት።

፲፪

፩ በዚያም ዘመን ንጉሡ ሄሮድስ መከራ ያጸናባቸው ዘንድ ከቤተ ክርስቲያኑ በአንዳንዶቹ ላይ እጁን ጫነባቸው።
፪ የዮሐንስንም ወንድም ያዕቆብን በሰይፍ ገደለው።
፫ አይሁድንም ደስ እንዳሰኛቸው አይቶ ጨምሮ ጴጥሮስን ደግሞ ያዘው። የቂጣ በዓልም ወራት ነበረ።
፬ በያዘውም ጊዜ ወደ ወኅኒ አገባው ከፋሲካም በኋላ ወደ ሕዝብ ያወጣው ዘንድ አሰቦ እያንዳንዱ አራት ወታደሮች ሆነው እንዲጠብቁት ለአራት ጭፍራ ክፍል አሳልፎ ሰጠው።
፭ ጴጥሮስም በወኅኒ ይጠበቅ ነበር፤ ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ስለ እርሱ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አጥብቆ ይደረግ ነበር።
፮ ሄሮድስም ሊያወጣው ባሰበ ጊዜ፥ በዚያች ሌሊት ጴጥሮስ በሁለት ሰንሰለት ታስሮ ከሁለት ወታደሮች መካከል ተኝቶ ነበር፤ ጠባቂዎችም በደጁ ፊት ሆነው ወኅኒውን ይጠብቁ ነበር።
፯ እነሆም፥ የጌታ መልአክ ቀረበ በቤትም ውስጥ ብርሃን በራ፤ ጴጥሮስንም ጎድኑን መትቶ አነቃውና። ፈጥነህ ተነሣ አለው። ሰንሰለቶቹም ከእጁ ወደቁ።
፰ መልአኩም። ታጠቅና ጫማህን አግባ አለው፥ እንዲሁም አደረገ።
፱ ልብስህንም ልበስና ተከተለኝ አለው። ወጥቶም ተከተለው፤ ራእይንም የሚያይ ይመስለው ነበር እንጂ በመልአኩ የሚደረገው ነገር እውነት እንደ ሆነ አላወቀም።
፲ የመጀመሪያውንና የሁለተኛውንም ዘብ አልፈው ወደ ከተማ ወደሚያወጣው ወደ ብረቱ መዝጊያ ደረሱ፤ እርሱም አውቆ ተከፈተላቸው፤ ወጥተውም አንዲት ሰላች አለፉ ወዲያውም መልአኩ ከእርሱ ተለየ።
፲፩ ጴጥሮስም ወደ ልቡ ተመልሶ። ጌታ መልአኩን ልኮ ከሄሮድስ እጅና የአይሁድ ሕዝብ ይጠብቁት ከነበረው ሁሉ እንደ አዳነኝ አሁን በእውነት አወቅሁ አለ።
፲፪ ባሰተዋለም ጊዜ እጅግ ሰዎች ተከማችተው ይጸልዩበት ወደ ነበረው ማርቆስ ወደ ተባለው ወደ ዮሐንስ እናት ወደ ማርያም ቤት መጣ።
፲፫ ጴጥሮስም የደጁን መዝጊያ ባንኳኳ ጊዜ ሮዴ የሚሉአት አንዲት ገረድ ትሰማ ዘንድ ቀረበች፤
፲፬ የጴጥሮስ ድምፅ መሆኑንም ባወቀች ጊዜ ከደስታዋ የተነሣ ደጁን አልከፈተችም፥ ነገር ግን ወደ ውስጥ ሮጣ ጴጥሮስ በደጅ ፊት ቆሞ እንዳለ አወራች።
፲፭ እነርሱም። አብደሻል አሉአት። እርሰዋ ግን እንዲሁ እንደ ሆነ ታሰረግጥ ነበር። እነርሱም። መልአኩ ነው አሉ።
፲፮ ጴጥሮስ ግን ማንኳኳቱን አዘወተረ፤ ከፍተውም አዩትና ተገረሙ።
፲፯ ግን ዝም እንዲሉ በእጁ ጠቅሶ ጌታ ከወኅኒ እንዴት እንዳወጣው ተረከላቸውና። ይህን ለያዕቆብና ለወንድሞች ንገሩ አላቸው። ወጥቶም ወደ ሌላ ሰፍራ ሄደ።
፲፰ በነጋም ጊዜ። ጴጥሮስን ምን አግኝቶት ይሆን? ብለው በጭፍሮች ዘንድ ብዙ ሁከት ሆነ።
፲፱ ሄሮድስም አሰፈልጎ ባጣው ጊዜ ጠባቂዎችን መረመረ ይገድሉአቸውም ዘንድ አዘዘ፤ ከይሁዳም ወደ ቂሣርያ ወርዶ በዚያ ተቀመጠ።
፳ ከጢሮስና ከሲዶና ሰዎችም ጋር ተጣልቶ ነበር፤ በአንድ ልብ ሆነውም ወደ እርሱ መጡ፥ የንጉሥንም ቢትወደድ ብላስጦስን እሺ አስኝተው ዕርቅ ለመኑ፥ አገራቸው ከንጉሥ አገር ምግብ ያገኝ ነበረና።
፳፩ በተቀጠረ ቀንም ሄሮድስ ልብስ መንግሥቱን ለብሶ በዙፋን ተቀመጠ እነርሱንም ተናገራቸው፤

፳፪ ሕዝቡም። የእግዚአብሔር ድምፅ ነው የሰውም አይደለም ብለው ጮኹ።
፳፫ ለእግዚአብሔርም ክብር ሰላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ።
፳፬ የእግዚአብሔር ቃል ግን ያድግና ይበዛ ነበር።
፳፭ በርናባስና ሳውልም አገልግሎታቸውን ፈጽመው ከኢየሩሳሌም ተመለሱ፥ ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስንም ከእነርሱ ጋር ይዘውት መጡ።

፲፫

፩ በአንጾኪያም ባለችው ቤተ ክርስቲያን ነቢያትና መምህራን ነበሩ፤ እነርሱም በርናባስ፥ ኔጌር የተባለው ስምዖንም፥ የቀሬናው ሉክዮስም፥ የአራተኛው ክፍል ገዥ የሄሮድስም ባለምዋል ምናሔ፥ ሳውልም ነበሩ።
፪ እነዚህም ጌታን ሲያመልኩና ሲጦሙ መንፈስ ቅዱስ። በርናባስንና ሳውልን ለጠራኋቸው ሥራ ለዩልኝ አለ።
፫ በዚያን ጊዜም ከጦሙ ከጸለዩም እጆቸውንም ከጫኑ በኋላ አሰናበቱአቸው።
፬ እነርሱም በመንፈስ ቅዱስ ተልከው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፤ ከዚያም በመርከብ ወደ ቆጵሮስ ሄዱ።
፭ በሰልማናም በነበሩ ጊዜ በእይሁድ ምኩራቦች የእግዚአብሔርን ቃል ሰበኩ፤ አገልጋይም ዮሐንስ ነበራቸው።
፮ ደሴቲቱንም ሁሉ እስከ ጳፋ በዞሩ ጊዜ፥ በርያሱስ የሚሉትን ጠንቋይና ሐሰተኛ ነቢይ የሆነውን አንድ አይሁዳዊ ሰው አገኙ፤
፯ እርሱም አሰተዋይ ሰው ከሆነው ሰርግዮስ ጳውሎስ ከሚባለው አገረ ገዥ ጋር ነበረ። ይህም በርናባስንና ሳውልን ወደ እርሱ ጠርቶ የእግዚአብሔርን ቃል ሊሰማ ፈለገ።
፰ ጠንቋዩ ግን ኤልማስ፥ ሰሙ እንዲሁ ይተረጐማልና፥ አገረ ገዡን ከማመን ሊያጣምም ፈለጎ ተቃወማቸው።
፱ ጳውሎስ የተባለው ሳውል ግን መንፈስ ቅዱስን ተሞልቶ ትኩር ብሎ ሲመለከተው።
፲ አንተ ተንኰል ሁሉ ክፋትም ሁሉ የሞላብህ፥ የዲያብሎስ ልጅ፥ የጽድቅም ሁሉ ጠላት፥ የቀናውን የጌታን መንገድ ከማጣመም አታርፍምን?
፲፩ አሁንም፥ እነሆ፥ የጌታ እጅ በአንተ ላይ ናት፥ ዕውርም ትሆናለህ እስከ ጊዜውም ፀሐይን አታይም አለው። ያን ጊዜም ጭጋግና ጨለማ ወደቀበት፥ በእጁም የሚመራውን እየዞረ ፈለገ።
፲፪ በዚያን ጊዜ አገረ ገዡ የተደረገውን ባየ ጊዜ ከጌታ ትምህርት የተነሣ ተገርሞ አመነ።
፲፫ ጳውሎስም ከጓደኞቹ ጋር ከጳፋ ተነሥቶ የጵንፍልያ ወደምትሆን ወደ ጴርጌን መጣ፤ ዮሐንስም ከእነርሱ ተለይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ።
፲፬ እነርሱ ግን ከጴርጌን አልፈው የጲሲድያ ወደምትሆን ወደ አንጾኪያ ደረሱ፤ በሰንበትም ቀን ወደ ምኩራብ ገብተው ተቀመጡ።
፲፭ ሕግና ነቢያትም ከተነበቡ በኋላ የምኩራቡ አለቆች። ወንድሞች ሆይ፥ ሕዝብን የሚመክር ቃል እንዳላችሁ ተናገሩ ብለው ላኩባቸው።
፲፮ ጳውሎስም ተነሣና በእጁ ጠቅሶ እንዲህ አለ። የእስራኤል ሰዎችና እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሆይ፥ ሰሙ።
፲፯ የዚህ የእስራኤል ሕዝብ አምላክ አባቶቻችንን መርጦ በግብፅ አገር በእንግድነት ሳሉ ሕዝቡን ከፍ ከፍ አደረጋቸው፥ ከፍ ባለችውም ክንዱ ከዚያ አወጣቸው።
፲፰ በበረሀም አርባ ዓመት ያህል መገባቸው።
፲፱ በከነዓንም አገር ሰባት አሕዛብን አጥፍቶ ምድራቸውን አወረሳቸው።
፳ ከዚህም በኋላ እስከ ነቢዩ እስከ ሳሙኤል ድረስ አራት መቶ አምሳ ዓመት ያህል መሳፍንትን ሰጣቸው።
፳፩ ከዚያም ወዲያ ንጉሥን ያነግሥላቸው ዘንድ ለመኑ፥ እግዚአብሔርም ከብንያም ወገን የሚሆን ሰው የቂስን ልጅ ሳኦልን አርባ ዓመት ሰጣቸው፤
፳፪ እርሱንም ከሻረው በኋላ ዳዊትን በእነርሱ ላይ እንዲነግሥ አስነሣው፥ ሲመሰክርለትም። እነደ ልቤ የሆነ ሰው ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ አለ።
፳፫ ከዚህም ሰው ዘር እግዚአብሔር እንደ ተሰፋው ቃል ለእስራኤል መድኃኒትን እርሱም ኢየሱስን አመጣ።
፳፬ ከመምጣቱ በፊት ዮሐንስ አስቀድሞ ለእስራኤል ሕዝብ ሁሉ የንሰሐን ጥምቀት ሰብኮ ነበር።
፳፭ ዮሐንስም ሩጫውን ሲፈጽም ሳለ። እኔ ማን እንደ ሆንሁ ታሰባላችሁ? እኔሰ እርሱን አይደለሁም፤ ነገር ግን እነሆ፥ የእግሩን ጫማ እፈታ ዘንድ ከማይገባኝ ከእኔ በኋላ ይመጣል ይል ነበር።
፳፮ እናንተ ወንድሞቻችን፥ የአብርሃም ዘር ልጆች ከእናንተ መካከልም እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፥ ለእናንተ የዚህ የመዳን ቃል ተላከ።
፳፯ በኢየሩሳሌም የሚኖሩ ሰዎችና አለቆቻቸው እርሱንና በየሰንበቱ የሚነበቡትን የነቢያትን ድምፆች ሰላላወቁ በፍርዳቸው ፈጽመዋልና፤
፳፰ ለሞትም የሚያደርስ ምክንያት አንድ ሰንኳ ባያገኙበት፥ ይገድለው ዘንድ ጲላጦስን ለመኑት፤
፳፱ ሰለ እርሱም የተጻፈውን ሁሉ በፈጸሙ ጊዜ ከእንጨት አውርደው በመቃብር አኖሩት።
፴ እግዚአብሔር ግን ከሙታን አስነሣው፤
፴፩ በሕዝብም ዘንድ ምስክሮቹ ለሆኑት ከእርሱ ጋር ከገሊላ ወደ ኢየሩሳሌም ለወጡት ብዙ ቀን ታያቸው።
፴፪ እኛም ለአባቶች የተሰጠውን ተሰፋ የምሰራቹን ለእናንተ እንሰብካለን፤
፴፫ ይህን ተሰፋ እግዚአብሔር በሁለተኛው መዝሙር ደግሞ። አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወለድሁህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ኢየሱስን አስነሥቶ ለእኛ ለልጆቻቸው ፈጽሞአልና።
፴፬ እንደገናም ወደ መበሰበስ እንዳይመለስ ከሙታን እንደ አስነሣው፥ እንዲህ። የታመነውን የዳዊትን ቅዱስ ተሰፋ እሰጣችኋለሁ ብሎአል።
፴፭ ደግሞ በሌላ ሰፍራ። ቅዱስህን መበሰበስን ያይ ዘንድ አትሰጠውም ይላልና።
፴፮ ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ፥ ከአባቶቹም ጋር ተጨምሮ መበሰበስን አየ፤
፴፯ ይህ እግዚአብሔር ያስነሣው ግን መበሰበስን አላየም።
፴፰-፴፱ በወጡም ጊዜ ይህን ነገር በሚመጣው ሰንበት ይነግሩአቸው ዘንድ ለመኑአቸው።

፴፫ ጉባኤውም ከተፈታ በኋላ ከአይሁድና ወደ
ይሁዲነት ገብተው ከሚያመልኩ ብዙዎች ጳውሎስንና
በርናባስን ተከተሉአቸው፥ እነርሱም ሲነግሩአቸው
በእግዚአብሔር ጸጋ ጸንተው እንዲኖሩ አሰረዱአቸው።
፴፬ በሁለተኛውም ሰንበት ከጥቂቶቹ በቀር
የከተማው ሰው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰሙ
ዘንድ ተሰበሰቡ።
፴፭ አይሁድም ብዙ ሕዝብ ባዩ ጊዜ ቅንዓት
ሞላባቸው፥ እየተሳደቡም ጳውሎስ የተናገረውን ቃል
ተቃወሙ።
፴፮ ጳውሎስና በርናባስም ገልጠው። የእግዚአብሔር
ቃል አስቀድሞ ለእናንተ ይነገር ዘንድ ያስፈልጋል፤
ከገፋችሁትና የዘላለም ሕይወት እንዳይገባችሁ
በራሳችሁ ከፈረዳችሁ ግን፥ እነሆ፥ ወደ አሕዛብ ዘወር
እንላለን።
፴፯ እንዲሁ ጌታ። አስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለማዳን
ትሆን ዘንድ ለአሕዛብ ብርሃን አድርጌሃለሁ ብሎ
አዞናልና አሉ።
፴፰ አሕዛብም ሰምተው ደስ አላቸው
የእግዚአብሔርንም ቃል አከበሩ፥ ለዘላለም ሕይወትም
የተዘጋጁ ሁሉ አመኑ፤
፴፱ የጌታም ቃል በአገሩ ሁሉ ተሰፋፋ።
፵ አይሁድ ግን የሚያመልኩትን የከበሩትንም
ሴቶችና የከተማውን መኳንንት አወኩ፥ በጳውሎስና
በበርናባስም ላይ ስደትን አስነሥተው ከአገራቸው
አወጡአቸው።
፶፩ እነርሱ ግን የእግራቸውን ትቢያ አራግፈውባቸው
ወደ ኢቆንዮን መጡ።
፶፪ በደቀ መዛሙርትም ደስታና መንፈስ ቅዱስ
ሞላባቸው።

፲፬

፩ በኢቆንዮንም እንደ ቀድሞ ወደ አይሁድ ምኩራብ
ገብተው ከአይሁድና ከግሪክ ሰዎች ብዙ እስኪያምኑ
ድረስ ተናገሩ።
፪ ያላመኑት አይሁድ ግን የአሕዛብን ልብ
በወንድሞች ላይ አነሣሡ አስከፉም።
፫ ምልክትና ድንቅ በእጆቻው ይደረግ ዘንድ እየሰጠ
ለጸጋው ቃል ስለ መስክረው ስለ ጌታ ገልጠው
እየተናገሩ ረጅም ወራት ተቀመጡ።
፬ የከተማውም ሕዝብ ተከፍለው እኩሌቶቹ
ከአይሁድ እኩሌቶቹም ከሐዋርያት ጋር ሆኑ።
፭ አሕዛብና አይሁድ ግን ከአለቆቻቸው ጋር
ሊያንገላቱአቸውና ሊወግሩአቸው ባሰቡ ጊዜ፥
፮ አውቀው ልስጥራንና ደርቤን ወደሚባሉት ወደ
ሊቃኦንያ ከተማዎች በእነርሱም ዙሪያ ወዳለው አገር
ሸሹ፤
፯ በዚያም ወንጌልን ይሰብኩ ነበር።
፰ በልስጥራንም እግሩ የሰለለ፥ ከእናቱም ማኅፀን
ጀምሮ አንካሳ የሆነ፥ ከቶም ሄዶ የማያውቅ አንድ ሰው
ተቀምጦ ነበር።
፱ ይህም ሰው ጳውሎስ ሲናገር ይሰማ ነበር፤
እርሱም ትኩር ብሎ ተመለከተውና ይድን ዘንድ
እምነት እንዳለው ባየ ጊዜ፥
፲ በታላቅ ድምፅ። ቀጥ ብለህ በእግርህ ቁም
አለው። ብድግ ብሎም ተንሥቶ ይመላለስ ነበር።
፲፩ ሕዝቡም ጳውሎስ ያደረገውን ባዩ ጊዜ
ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሊቃኦንያ ቋንቋ።
አማልክት ሰዎችን መስለው ወደ እኛ ወርደዋል አሉ፤
፲፪ በርናባስንም ድያ አሉት፤ ጳውሎስንም እርሱ
በመናገር ዋና ስለ ነበረ ሄርሜን አሉት።
፲፫ በከተማውም ፊት ቤተ መቅደስ ያለው የድያ
ካህን ኮርማዎችንና የአበባን አክሊሎች ወደ ደጃፍ
አምጥቶ ከሕዝቡ ጋር ሆኖ ሊሠዋላቸው ወደደ።
፲፬ ሐዋርያት በርናባስና ጳውሎስ ግን ይህን በሰሙ
ጊዜ ልብሳቸውን ቀደው ወደ ሕዝቡ መካከል እየጮኹ
ሮጡ፥
፲፭ እንዲህም አሉ። እናንተ ሰዎች፥ ይህን ስለ ምን
ታደርጋላችሁ? እኛ ደግሞ እንደ እናንተ የምንሰማ
ሰዎች ነን፥ ከዚህም ከንቱ ነገር ሰማይንና ምድርን
ባሕርንም በእነርሱም ያለውን ሁሉ ወደ ፈጠረ ወደ
ሕያው እግዚአብሔር ዘወር ትሉ ዘንድ ወንጌልን
እንሰብካለን።
፲፮ እርሱ ባለፉት ትውልዶች አሕዛብን ሁሉ በገዛ
ራሳቸው ጐዳና ይሄዱ ዘንድ ተዋቸው።
፲፯ ከዚህም ሁሉ ጋር መልካም ሥራ እየሠራ፥
ከሰማይ ዝናብን ፍሬ የሚሆንበትንም ወራት ሲሰጠን፥
ልባችንንም በመብልና በደስታ ሲሞላው ራሱን ያለ
ምስክር አልተወም።
፲፰ ይህንም ብለው እንዳይሠዉላቸው ሕዝቡን
በጭንቅ አስተዉአቸው።
፲፱ አይሁድ ግን ከአንጾኪያና ከኢቆንዮን መጡ፤
ሕዝቡንም አባብለው ጳውሎስን ወገሩ የሞተም
መስሎአቸው ከከተማ ወደ ውጭ ጐተቱት።
፳ ደቀ መዛሙርት ግን ከበውት ሳሉ፥ ተነሰቶ ወደ
ከተማ ገባ። በነገውም ከበርናባስ ጋር ወደ ደርቤን
ወጣ።
፳፩-፳፫ በየቤተ ክርስቲያኑም ሽማግሌዎችን
ከሾሙላቸው በኋላ ጦመውም ከጸለዩ በኋላ፥
ላመኑበት ለጌታ አደራ ሰጡአቸው።
፳፬ በጲሲድያም አልፈው ወደ ጵንፍልያ መጡ፥
፳፭ በጴርጌንም ቃሉን ከተናገሩ በኋላ ወደ አጣልያ
ወረዱ፥
፳፮ ከዚያም ሰለ ፈጸሙት ሥራ ለእግዚአብሔር ጸጋ
አደራ ወደ ተሰጡበት ወደ አንጾኪያ በመርከብ ሄዱ።
፳፯ በደረሱም ጊዜ ቤተ ክርስቲያኑን ሰብስበው
እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ
ለአሕዛብም የሃይማኖትን ደጅ እንደ ከፈተላቸው
ተናገሩ።
፳፰ ከደቀ መዛሙርትም ጋር አያሌ ቀን ተቀመጡ።

፲፭

፩ አንዳንዶችም ከይሁዳ ወረዱና። እንደ ሙሴ
ሥርዓት ካልተገረዛችሁ ትድኑ ዘንድ አትችሉም ብለው
ወንድሞችን ያስተምሩ ነበር።
፪ በእነርሱና በጳውሎስ በበርናባስም መካከል ብዙ
ጥልና ክርክር በሆነ ጊዜ፥ ሰለዚህ ክርክር ጳውሎና
በርናባስ ከእነርሱም አንዳንዶች ሌሎች ሰዎች ወደ
ሐዋርያት ወደ ሽማግሌዎችም ወደ ኢየሩሳሌም ይወጡ
ዘንድ ተቈረጠ።
፫ ቤተ ክርስቲያኑም በመንገድ እየረዳቸው እነርሱ
የአሕዛብን መመለስ እየተረኩ በፊንቄና በሰማርያ
አለፉ፥ ወንድሞችንም ሁሉ እጅግ ደስ አሰኙአቸው።

፩ ወደ ኢየሩሳሌምም በደረሱ ጊዜ ቤተ
ክርስቲያንና ሐዋርያት ሽማግሌዎችም ተቀበሉአቸው፥
እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ያደረገውን ሁሉ አወሩ።
፪ ከፈሪሳውያን ወገን ግን ያመኑት አንዳንዶቹ
ተነሥተው። ትገርዙአቸው ዘንድና የሙሴን ሕግ
እንዲጠብቁ ታዙአቸው ዘንድ ይገባል አሉ።
፫ ሐዋርያትና ሽማግሌዎችም ስለዚህ ነገር
ለመማከር ተሰበሰቡ።
፮ ከብዙ ክርክርም በኋላ ጴጥሮስ ተነሥቶ
እንዲህ አላቸው ወንድሞች ሆይ፥ አሕዛብ ከአፌ
የወንጌልን ቃል ሰምተው ያምኑ ዘንድ እግዚአብሔር
በመጀመሪያው ዘመን ከእናንተ እኔን እንደ መረጠኝ
እናንተ ታውቃላችሁ።
፰ ልብንም የሚያውቅ አምላክ ለእኛ ደግሞ እንደ
ሰጠን መንፈስ ቅዱስን በመስጠት መስክረላቸው፤
፱ ልባቸውንም በእምነት ሲያነጻ በእኛና በእነርሱ
መካከል አንዳች አልለየም።
፲ እንግዲህ አባቶቻችንና እኛ ልንሸከመው
ያልቻልነውን ቀንበር በደቀ መዛሙርት ጫንቃ
ላይ በመጫን እግዚአብሔርን አሁን ስለ ምን
ትፈታተናላችሁ?
፲፩ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ እንደ
እነርሱ ደግሞ እንድን ዘንድ እናምናለን።
፲፪ ሕዝቡም ሁሉ ዝም አሉ፥ በርናባስና ጳውሎስም
እግዚአብሔር በእጆቸው በአሕዛብ መካከል
ያደረገውን ምልክትና ድንቅ ሁሉ ሲተርኩላቸው
ይሰሙ ነበር።
፲፫ እነርሱም ዝም ካሉ በኋላ ያዕቆብ እንዲህ ብሎ
መለሰ። ወንድሞች ሆይ፥ ስሙኝ።
፲፬ እግዚአብሔር ለሰሙ የሚሆንን ወገን ከአሕዛብ
ይወስድ ዘንድ እስቀድሞ እንዴት እንደ ጐበኘ ስምዖን
ተርኮአል።
፲፭ ከዚህም ጋር የነቢያት ቃል ይስማማል፥ እንዲህ
ተብሎ እንደ ተጻፈ።
፲፮-፲፰ ከጥንት ጀምሮ ሥራው ሁሉ በእግዚአብሔር
ዘንድ የታወቀ ነው።
፲፱ ስለዚህ ከአሕዛብ ወደ እግዚአብሔር የዞሩትን
እንዳናስቸግራቸው፥
፳ ነገር ግን ከጣዖት ርኩስትና ከዝሙት ከታነቀም
ከደምም ይርቁ ዘንድ እንድንጽፍላቸው እቈርጣለሁ።
፳፩ ሙሴስ ከቀደሙት ትውልድ ጀምሮ በሰንበት
በሰንበት በምኩራቦቹ ሲያነቡ በየከተማው እርሱን
የሚሰብኩ አሉት።
፳፪ ያን ጊዜ ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ከቤተ
ክርስቲያኑ ሁሉ ጋር ከእነርሱ የተመረጡትን ሰዎች
ከጳውሎስና ከበርናባስ ጋር ወደ አንጾኪያ ይልኩ ዘንድ
ፈቀዱ፤ እነርሱም በወንድሞች መካከል ዋናዎች ሆነው
በርሰያን የተባለው ይሁዳና ሲላስ ነበሩ።
፳፫ እንዲህም ጽፈው በእነርሱ እጅ ላኩ።
ሐዋርያትና ሽማግሌዎች ወንድሞችም በአንጾኪያና
በሶርያ በኪልቅያም ለሚኖሩ ከአሕዛብ ወገን ለሆኑ
ወንድሞች ሰላምታ ያቀርባሉ።
፳፬ ያላዘዝናቸው ሰዎች ከእኛ ወጥተው። ትገረዙ
ዘንድና ሕግን ትጠብቁ ዘንድ ይገባችኋል ብለው
ልባችሁን እያወኩ በቃል እንዳናወጡአችሁ ሰለ ሰማን፥
፳፭-፳፯ ራሳቸውም ደግሞ በቃላቸው ያንኑ
ይነግሩአችሁ ዘንድ ይሁዳንና ሲላስን ልከናል።
፳፰-፳፱ እነርሱም ተሰናብተው ወደ አንጾኪያ ወረዱ፥
ሕዝቡንም ሰብሰበው ደብዳቤውን ሰጡአቸው።
፴ ባነበቡትም ጊዜ ከምክሩ የተነሣ ደስ አላቸው።
፴፩ ይሁዳና ሲላስም ደግሞ ነቢያት ነበሩና
ወንድሞችን በብዙ ቃል መክረው አጸኑአቸው።
፴፫ አያሌ ቀንም ከተቀመጡ በኋላ ከወንድሞች
በሰላም ተሰናብተው ወደ ሐዋርያት ሄዱ።
፴፬ ሲላስ ግን በዚያ ይኖር ዘንድ ፈቀደ።
፴፭ ጳውሎስና በርናባስም ከሌሎች ከብዙ ሰዎች
ጋር ደግሞ የጌታን ቃል እያስተማሩና ወንጌልን እየሰበኩ
በአንጾኪያ ይቀመጡ ነበር።
፴፮ ከጥቂት ቀንም በኋላ ጳውሎስ በርናባስን።
ተመልሰን የጌታን ቃል በተናገርንበት በየከተማው ሁሉ
ወንድሞችን እንጐብኛቸው፥ እንዴት እንዳሉም እንወቅ
አለው።
፴፯ በርናባስም ማርቆስ የተባለውን ዮሐንስን ደግሞ
ከእነርሱ ጋር ይወሰድ ዘንድ አሰበ፤
፴፰ ጳውሎስ ግን ይህን ከእነርሱ ጋር ሊወሰድ
አልፈቀደም፥ ከእነርሱ ዘንድ ከጵንፍልያ ተለይቶ
ነበርና፥ ወደ ሥራም ከእነርሱ ጋር አልመጣም ነበርና።
፴፱ ስለዚህም እርስ በርሳቸው እስኪለያዩ ድረስ
መከፋፋት ሆነ፥ በርናባስም ማርቆስን ይዞ በመርከብ
ወደ ቆጵሮስ ሄደ።
፵ ጳውሎስ ግን ሲላስን መረጠ፥ ወንድሞችም
ለእግዚአብሔር ጸጋ አደራ ከሰጡት በኋላ ወጣ፤
፵፩ አብያተ ክርስትያናትንም እያጸና በሶርያና
በኪልቅያ ይዞር ነበር።

፲፮

፩ ወደ ደርቤንና ወደ ልስጥራንም ደረሰ። እነሆም፥
በዚያ የአንዲት ያመነች አይሁዳዊት ልጅ ጢሞቴዎስ
የሚባል አንድ ደቀ መዝሙር ነበረ፤ አባቱ ግን የግሪክ
ሰው ነበረ።
፪ ለእርሱም በልስጥራንና በኢቆንዮን ያሉ
ወንድሞች መሰከሩለት።
፫ ጳውሎስ ይህ ከእርሱ ጋር ይወጣ ዘንድ ወደደ፥
በእነዚያም ሰፍራዎች ስለ ነበሩ አይሁድ ይዞ ገረዘው፤
አባቱ የግሪክ ሰው እንደ ሆነ ሁሉ ያውቁ ነበርና።
፬ በከተማዎችም ሲዞሩ በኢየሩሳሌም የነበሩት
ሐዋርያትና ሽማግሌዎች የቈረጡትን ሥርዓት
ይጠብቁ ዘንድ ሰጡአቸው።
፭ አብያተ ክርስቲያናትም በሃያማኖት ይበረቱ ነበር፥
በቍጥርም ዕለት ዕለት ይበዙ ነበር።
፮ በእስያም ቃሉን እንዳይናገሩ መንፈስ ቅዱስ ስለ
ከለከላቸው በፍርግያና በገላትያ አገር አለፉ፤
፯ በሚሲያም አንጻር በደረሱ ጊዜ ወደ ቢታንያ ይሄዱ
ዘንድ ሞከሩ፥ የኢየሱስ መንፈስም አልፈቀደላቸውም፤
፰ በሚሲያም አጠገብ አልፈው ወደ ጢሮአዳ ወረዱ።
፱ ራእይም ለጳውሎስ በሌሊት ታየው፤ እንድ
የመቄዶንያ ሰው። ወደ መቄዶንያ ተሻገርና እርዳን እያለ
ቆሞ ሲለምነው ነበር።
፲ ራእዩንም ካየ በኋላ ወዲያው ወደ መቄዶንያ
ልንወጣ ፈለግን፥ ወንጌልን እንሰብክላቸው ዘንድ
እግዚአብሔር እንደ ጠራን መሰሎናልና።
፲፩ ከጢሮአዳም ተነሥተን በቀጥታ ወደ ሳሞትራቄ
በነገውም ወደ ናጵሌ በመርከብ ሄድን፤

፲፪ ከዚያም ወደ ፊልጵስዩስ ደረስን፤ እርስዋም የመቄዶንያ ከተማ ሆና የወረዳ ዋና ከተማና ቅኝ አገር ናት፤ በዚህችም ከተማ አንዳንድ ቀን እነቀመጥ ነበር።
፲፫ በሰንበት ቀንም ከከተማው በር ውጭ የጸሎት ስፍራ በዚያ መሆኑን ሰላስብን ወደ ወንዝ አጠገብ ወጣን፤ ተቀምጠንም ለተሰበሰቡት ሴቶች ተናገርን።
፲፬ ከትያጥሮን ከተማም የመጣች ቀይ ሐር ሻጭ እግዚአብሔርን የምታመልክ ልድያ የሚሉአት አንዲት ሴት ትሰማ ነበረች፤ ጳውሎስም የሚናገረውን ታዳምጥ ዘንድ ጌታ ልብዋን ከፈተላት።
፲፭ እርስዋም ከቤተ ሰዎችዋ ጋር ከተጠመቀች በኋላ። በጌታ የማምን እንድሆን ከፈረዳችሁልኝ፥ ወደ ቤቴ ገብታችሁ ኑሩ ብላ ለመነችን፤ በግድም አለችን።
፲፮ ወደ ጸሎት ሰፍራም ስንሄድ፥ የምዋርተኛነት መንፈስ የነበረባት ለጌቶችዋም እየጠነቈለች ብዙ ትርፍ ታመጣ የነበረች አንዲት ገረድ አገኘችን።
፲፯ እርስዋ ጳውሎስንና እኛን እየተከተለች። የመዳንን መንገድ የሚነግሩአችሁ እነዚህ ሰዎች የልዑል አምላክ ባሪያዎች ናቸው ብላ ትጮኽ ነበር።
፲፰ ይህንም እጅግ ቀን አደረገች። ጳውሎስ ግን ተቸገረና ዘወር ብሎ መንፈሱን። ከእርስዋ እንድትወጣ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አዝሃለሁ አለው፤ በዚያም ሰዓት ወጣ።
፲፱ ጌቶችዋም የትርፋቸው ተስፋ እንደ ወጣ ባዩ ጊዜ ጳውሎስንና ሲላስን ይዘው ወደ ገበያ በሹማምት ፊት ጐተቱአቸው፤
፳ ወደ ገዢዎችም አቅርበው። እነዚህ ሰዎች አይሁድ ሆነው ከተማችንን እጅግ ያናውጣሉ።
፳፩ እኛም የሮሜ ሰዎች ሆነን እነቀበላቸውና እናደርጋቸው ዘንድ ያልተፈቀደልንን ልማዶች ይናገራሉ አሉ።
፳፪ ሕዝቡም አብረው ተነሡባቸው፥ ገዢዎቹም ልብሳቸውን ገፈው በበትር ይመቱአቸው ዘንድ አዘዙ፤
፳፫ በብዙም ከደበደቡአቸው በኋላ ወደ ወኅኒ ጣሉአቸው፥ የወኅኒውንም ጠባቂ ተጠንቅቆ እንዲጠብቃቸው አዘዙት።
፳፬ እርሱም የዚህን ዓይነት ትእዛዝ ተቀብሎ ወደ ውስጠኛው ወኅኒ ጣላቸው፥ እግራቸውንም በግንድ አጣብቆ ጠረቃቸው።
፳፭ በመንፈቀ ሌሊት ግን ጳውሎስና ሲላስ እየጸለዩ እግዚአብሔርን በዜማ ያመሰግኑ ነበር፥ እስረኞቹም ያደምጡአቸው ነበር
፳፮ ድንገትም የወኅኒው መሠረት እስኪናወጥ ድረስ ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ ሆነ፤ በዚያን ጊዜም ደጆቹ ሁሉ ተከፈቱ የሁሉም እስራት ተፈታ።
፳፯ የወኅኒውም ጠባቂ ከእንቅልፉ ነቅቶ የወኅኒው ደጆች ተከፍተው ባየ ጊዜ፥ እስረኞቹ ያመለጡ መስሎት ራሱን ይገድል ዘንድ አሰቦ ሰይፉን መዘዘ።
፳፰ ጳውሎስ ግን በታላቅ ድምፅ። ሁላችን ከዚህ አለንና በራስህ ክፉ ነገር አታድርግ ብሎ ጮኸ።
፳፱ መብራትም ለምኖ ወደ ውስጥ ሮጠ፥ እየተንቀጠቀጠም ከጳውሎስና ከሲላስ ፊት ተደፋ፤
፴ ወደ ውጭም አውጥቶ። ጌቶች ሆይ፥ እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል? ኣላቸው።
፴፩ እነርሱም። በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህ ትድናላችሁ አሉት።
፴፪ ለእርሱና በቤቱም ላሉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ተናገሩአቸው።
፴፫ በሌሊትም በዚያች ሰዓት ወስደ ቍስላቸውን አጠበላቸው፥ ያን ጊዜውንም እርሱ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ተጠመቀ፤
፴፬ ወደ ቤቱም አውጥቶ ማዕድ አቀረበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ሰላመነ ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር ሐሤት አደረገ።
፴፭ በነጋም ጊዜ ገዢዎቹ። እነዚያን ሰዎች ፍታቸው ብለው ሎሌዎቻቸውን ላኩ።
፴፮ የወኅኒውም ጠባቂ። ትፈቱ ዘንድ ገዢዎቹ ልከዋል፤ እንግዲህ አሁን ወጥታችሁ በሰላም ሂዱ ብሎ ይህን ቃል ለጳውሎስ ነገረው።
፴፯ ጳውሎስ ግን። እኛ የሮሜ ሰዎች ስንሆን ያለ ፍርድ በሕዝብ ፊት ደብድበው በወኅኒ ጣሉን፤ አሁንም በሰውር ይጥሉናልን? እይሆንም ራሳቸው ግን መጥተው ያውጡን አላቸው።
፴፰ ሎሌዎቹም ይህን ነገር ለገዢዎች ነገሩ። የሮሜ ሰዎችም እንደ ሆኑ በሰሙ ጊዜ ፈሩ፤
፴፱ መጥተውም ማለዱአቸው፥ አውጥተውም ከከተማ ይወጡ ዘንድ ለመኑአቸው።
፵ ከወኅኒውም ወጥተው ወደ ልድያ ቤት ገቡ፥ ወንድሞችንም ባዩ ጊዜ አጽናኑአቸውና ሄዱ።

፲፯

፩ በአንፊጶልና በአጶሎንያም ካለፉ በኋላ ወደ ተሰሎንቄ መጡ፥ በዚያም የአይሁድ ምኩራብ ነበረ።
፪ ጳውሎስም እንደ ልማዱ ወደ እነርሱ ገባ፥ ሦስት ሰንበትም ያህል ከእነርሱ ጋር ከመጻሕፍት እየጠቀሰ ይነጋገር ነበር፤
፫ ሲተረጕምም ክርስቶስ መከራ እንዲቀበልና ከሙታን እንዲነሣ ይገባው ዘንድ እያሰረዳ። ይህ እኔ የምሰብክላችሁ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ነው ይል ነበር።
፬ ከእነርሱም አንዳንዶቹ ተረድተው ከሚያመልኩም ከግሪክ ሰዎች ብዙ ከከበሩትም ሴቶች ጥቂቶች ያይደሉ፥ ከጳውሎስና ከሲላስ ጋር ተባበሩ።
፭ አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን እመጡ ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን እወኩ፥ ወደ ሕዝብም ያወጡአቸው ዘንድ ፈልገው ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ፤
፮ ባላገኙአቸውም ጊዜ ኢያሶንንና ከወንድሞች አንዳንዶችን ወደ ከተማው አለቆች ጎትተው። ዓለምን ያወኩ እነዚህ ወደዚህ ደግሞ መጥተዋል፥ ኢያሶንም ተቀብሎአቸዋል፤
፯ እነዚህም ሁሉ። ኢየሱስ የሚሉት ሌላ ንጉሥ አለ እያሉ የቄሣርን ትእዛዝ ይቃወማሉ ብለው ጮኹ።
፰ ሕዝቡና የከተማውም አለቆች ይህን ነገር በሰሙ ጊዜ ታወኩ፥
፱ ከኢያሶንና ከሌሎቹም ዋስ ተቀብለው ለቀቁአቸው።
፲ ወዲያውም ወንድሞች ጳውሎስንና ሲላስን በሌሊት ወደ ቤርያ ሰደዱአቸው፥ በደረሱም ጊዜ ወደ አይሁድ ምኩራብ ገቡ፤
፲፩ እነዚህም በተሰሎንቄ ከሚኖሩት ይልቅ ልበ ሰፊዎች ነበሩና። ነገሩ እንደዚሁ ይሆንን? ብለው

ዕለት ዕለት መጻሕፍትን እየመረመሩ ቃሉን በሙሉ ፈቃድ ተቀበሉ።
፲፪ ስለዚህም ከእነርሱ ብዙ፥ ከግሪኮችም የከበሩት ሴቶችና ወንዶች ጥቂት ያይደሉ፥ አመኑ።
፲፫ በተሰሎንቄ ያሉት አይሁድ ግን ጳውሎስ በቤርያ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ሰበከ ባወቁ ጊዜ፥ ወደዚያው ደግሞ መጡና ሕዝቡን አወኩ።
፲፬ በዚያን ጊዜም ወንድሞቹ ወዲያው ጳውሎስን እስከ ባሕር ድረስ ይሄድ ዘንድ ሰደዱት፤ ሲላስና ጢሞቴዎስም በዚያው ቀሩ።
፲፭ ጳውሎስን የሸኙት ግን እስከ አቴና አደረሱት፥ እንደሚቻላቸውም በፍጥነት ወደ እርሱ ይመጡ ዘንድ ወደ ሲላስና ወደ ጢሞቴዎስ ትእዛዝ ተቀብለው ሄዱ።
፲፮ ጳውሎስም በአቴና ሲጠብቃቸው ሳለ፥ በከተማው ጣዖት መሙላቱን እየተመለከተ መንፈሱ ተበሳጨበት።
፲፯ ስለዚህም በምኩራብ ከአይሁድና እግዚአብሔርን ከሚያመልኩ ሰዎች ጋር በየቀኑም በገበያ ከሚያገኛቸው ጋር ይነጋገር ነበር።
፲፰ ከኤፊቆሮስ ወገንና ኢስጦኢኮችም ከተባሉት ፈላስፎች እንዳንዶቹ ከእርሱ ጋር ተገናኙ። እንዳንዶቹም። ይህ ለፍላፊ ምን ሊናገር ይወዳል? አሉ፤ ሌሎችም የኢየሱስንና የትንሣኤውን ወንጌል ሰለ ሰበከላቸው። አዲሶችን አማልክት የሚያወራ ይመስላል አሉ።
፲፱-፳፩ የአቴና ሰዎች ሁሉና በዚያ የኖሩ እንግዶች አዲስ ነገርን ከመናገርና ከመሰማት በቀር በሌላ ጉዳይ አይውሉም ነበርና።
፳፪ ጳውሎስም በኢርዮስፋሳስ መካከል ቆሞ እንዲህ አለ። የአቴና ሰዎች ሆይ፥ እናንተ በሁሉ ነገር አማልክትን እጅግ እንደምትፈሩ እመለከታለሁ።
፳፫ የምታመልኩትን እየተመለከትሁ ሳልፍ። ለማይታወቅ አምላክ የሚል ጽሕፈት ያለበትን መሠዊያ ደግሞ አግኝቼአለሁና። እንግዲህ ይህን ሳታውቁ የምታመልኩትን እኔ እነግራችኋለሁ።
፳፬ ዓለሙንና በእርሱ ያለውን ሁሉ የፈጠረ አምላክ እርሱ የሰማይና የምድር ጌታ ነውና እጅ በሠራው መቅደስ አይኖርም፤
፳፭ እርሱም ሕይወትንና እስትንፋስን ሁሉንም ለሁሉ ይሰጣልና አንዳች እንደሚጎድለው በሰው እጅ አይገለገልም።
፳፮-፳፰ ከእናንተ ከባለ ቅኔዎች አንዳንዶች ደግሞ። እኛ ደግሞ ዘመደቹ ነንና ብለው እንደ ተናገሩ፥ በእርሱ ሕያዋን ነንና እንንቀሳቀሳለን እንኖርማለን።
፳፱ እንግዲህ የእግዚአብሔር ዘመዶች ከሆንን፥ አምላክ በሰው ብልሃትና አሳብ የተቀረጸውን ወርቅ ወይም ብር ወይም ድንጋይ እንዲመስል እናስብ ዘንድ አይገባንም።
፴ እንግዲህ እግዚአብሔር ያለማወቅን ወራት አሳልፎ አሁን በየቦታቸው ንስሐ ይገቡ ዘንድ ሰውን ሁሉ ያዛል፤
፴፩ ቀን ቀጥሮአልና፥ በዚያም ቀን ባዘጋጀው ሰው እጅ በዓለሙ ላይ በጽድቅ ሊፈርድ አለውና፤ ስለዚህም እርሱን ከሙታን በማስነሣቱ ሁሉን አረጋግጦአል።
፴፪ የሙታንንም ትንሣኤ በሰሙ ጊዜ አንዳንዶቹ አፌዙበት፥ አንዶቹ ግን። ስለዚህ ነገር ሁለተኛ እንሰማሃለን አሉት።
፴፫ እንዲሁም ጳውሎስ ከመካከላቸው ወጣ።
፴፬ አንዳንዶች ወንዶች ግን ተባብረው አመኑ፤ ከእነርሱ ደግሞ በአርዮስፋጎስ ያለው የፍርድ ቤት ፈራጅ ዲዮናስዮስ ደማሪስ የሚሉአትም አንዲት ሴት ሌሎችም ከእነርሱ ጋር ነበሩ።

፲፰

፩ ከዚህም በኋላ ጳውሎስ ከአቴና ወጥቶ ወደ ቆሮንቶስ መጣ።
፪ በወገኑም የጳንጦስ ሰው የሚሆን አቂላ የሚሉትን አንድ አይሁዳዊ አገኘ፤ እርሱም ከጥቂት ጊዜ በፊት ከሚስቱ ከጵርስቅላ ጋር ከኢጣልያ መጥቶ ነበር፥ አይሁድ ከሮሜ ይወጡ ዘንድ ቀላውዴዎስ አዞ ነበርና፤ ወደ እነርሱ ቀረበ፥
፫ ሥራቸውም አንድ ሰለ ነበረ በእነርሱ ዘንድ ተቀምጦ በአንድ ላይ ሠሩ፤ ሥራቸው ድንኳን መስፋት ነበረና።
፬ በየሰንበቱም ሁሉ በምኩራብ ይነጋገር ነበር፥ አይሁድንና የግሪክንም ሰዎች ያሰረዳ ነበር።
፭ ሲላስና ጢሞቴዎስም ከመቄዶንያ በወረዱ ጊዜ፥ ጳውሎስ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ለአይሁድ እየመሰከረ ለቃሉ ይተጋ ነበር።
፮ ነገር ግን በተቃወሙትና በተሳደቡ ጊዜ፥ ልብሱን እያራገፈ። ደማችሁ በራሳችሁ ነው፤ እኔ ንጹሕ ነኝ ከእንግዲህ ወዲህ ወደ አሕዛብ እሄዳለሁ አላቸው።
፯ ከዚያም ወጥቶ ኢዮስጦስ ወደሚባል እግዚአብሔርን ወደሚያመልክ ሰው ቤት ገባ ቤቱም በምኩራብ አጠገብ ነበረ።
፰ የምኩራብ አለቃ ቀርስጶስም ከቤተ ሰዎቹ ሁሉ ጋር በጌታ አመነ፥ ከቆሮንቶስ ሰዎችም ብዙ በሰሙ ጊዜ አምነው ተጠመቁ።
፱-፲፩ በመካከላቸውም የእግዚአብሔርን ቃል እያስተማረ ዓመት ከሰድስት ወር ተቀመጠ።
፲፪ ጋልዮስም በአካይያ አገረ ገዥ በነበረ ጊዜ፥ አይሁድ በአንድ ልብ ሆነው በጳውሎስ ላይ ተነሡ፥ ወደ ፍርድ ወንበርም አምጥተው።
፲፫ ይህ ሕግን ተቃውሞ እግዚአብሔርን ያመልኩት ዘንድ ሰዎችን ያባብላል አሉ።
፲፬ ጳውሎስም አፉን ሊከፍት ባሰበ ጊዜ፥ ጋልዮስ አይሁድን። አይሁድ ሆይ፥ ዓመፅ ወይም ክፉ በደል በሆነ እንድታገሣችሁ በተገባኝ፤
፲፭ ስለ ቃልና ስለ ሰሞች ስለ ሕጋችሁም የምትከራከሩ ከሆነ ግን፥ ራሳችሁ ተጠንቀቁ እኔ በዚህ ነገር ፈራጅ እሆን ዘንድ አልፈቅድምና አላቸው።
፲፮ ከፍርድ ወንበርም ፊት አሰወጣቸው።
፲፯ የግሪክ ሰዎችም ሁሉ የምኩራብ አለቃ ሶስቴንስን ይዘው በወንበሩ ፊት መቱት፤ በእነዚህም ነገሮች ጋልዮስ ግድ የለውም ነበር።
፲፰ ከዚህም በኋላ ጳውሎስ እጅግ ቀን ተቀምጦ ወንድሞቹንም ተሰናብቶ በመርከብ ወደ ሶርያ ሄደ፤ ስለትም ነበረበትና ራሱን በክንክራኦስ ተላጨ፤ ጵርስቅላና አቂላም ከእርሱ ጋር ነበሩ።
፲፱ ወደ ኤፌሶንም በደረሱ ጊዜ እነዚያን ከዚያ ተዋቸው፥ ራሱ ግን ወደ ምኩራብ ገብቶ ከአይሁድ ጋር ይነጋገር ነበር።
፳ እነርሱም ብዙ ጊዜ እንዲቀመጥላቸው ሲለምኑት እሺ አላለም፤

፳፩ ነገር ግን ሲሰናበታቸው። የሚመጣውን በዓል በኢየሩሳሌም እደርግ ዘንድ ይገባኛል እግዚአብሔር ቢፈቅድ ግን ወደ እናንተ ደግሞ እመለሳለሁ አላቸው። ከኤፌሶንም በመርከብ ተነሣ።
፳፪ ወደ ቂሣርያም በደረሰ ጊዜ ወጥቶ ለቤተ ክርስቲያን ሰላምታ ከሰጠ በኋላ ወደ አንጾኪያ ወረደ።
፳፫ ጥቂት ቀንም ቆይቶ ወጣ፥ ደቀ መዛሙርትንም ሁሉ እያጸና በገላትያ አገርና በፍርግያ በተራ አለፈ።
፳፬ በወገኑም የእስክንድርያ ሰው የሆነ ነገር አዋቂ የነበረ አጵሎስ የሚሉት አንድ አይሁዳዊ ሰው ወደ ኤፌሶን ወረደ፤ እርሱም በመጻሕፍት እውቀት የበረታ ነበረ።
፳፭ እርሱ የጌታን መንገድ የተማረ ነበረ፥ የዮሐንስንም ጥምቀት ብቻ አውቆ በመንፈስ ሲቃጠል ሰለ ኢየሱስ ይናገርና በትክክል ያሰተምር ነበር።
፳፮ እርሱም በምኩራብ ገልጦ ይናገር ጀመር። ጵርስቅላና አቂላም በሰሙት ጊዜ፥ ወስደው የእግዚአብሔርን መንገድ ከፊት ይልቅ በትክክል ገለጡለት።
፳፯ እርሱም ወደ አካይያ ማለፍ በፈቀደ ጊዜ፥ ወንድሞቹ አጸናኑት፥ ይቀበሉትም ዘንድ ወደ ደቀ መዛሙርት ጻፉለት፤ በደረሰም ጊዜ አምነው የነበሩትን በጸጋ እጅግ ይጠቅማቸው ነበር፤
፳፰ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደ ሆነ ከመጻሕፍት እየገለጠ ለአይሁድ በሁሉ ፊት በጽኑ ያሰረዳቸው ነበርና።

፲፱

፩ አጵሎስም በቆሮንቶስ ሳለ ጳውሎስ በላይኛው አገር አልፎ ወደ ኤፌሶን መጣ፥
፪ አንዳንድ ደቀ መዛሙርትንም አገኘ። ባመናችሁ ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? አላቸው። እነርሱም። እልተቀበልንም መንፈስ ቅዱስ እንዳለ ሰንኳ አልሰማንም አሉት።
፫ እንኪያ በምን ተጠመቃችሁ? አላቸው። እነርሱም። በዮሐንስ ጥምቀት አሉት።
፬ ጳውሎስም። ዮሐንስስ ከእርሱ በኋላ በሚመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ዘንድ ለሕዝብ እየተናገረ በንስሐ ጥምቀት አጠመቀ አላቸው።
፭ ይህንም በሰሙ ጊዜ በጌታ በኢየሱስ ሰም ተጠመቁ፤
፮ ጳውሎስም እጁን በጫነባቸው ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደባቸው በልሳኖችም ተናገሩ፥ ትንቢትም ተናገሩ።
፯ ሰዎቹም ሁሉ አሥራ ሁለት ያህሉ ነበር።
፰ ወደ ምኩራብም ገብቶ ሰለ እግዚአብሔር መንግሥት እየተነጋገረና እያሰረዳቸው ሦስት ወር ያህል በግልጥ ይናገር ነበር።
፱ አንዳንዶች ግን እልከኞች ሆነው በሕዝብ ፊት መንገዱን እየሰደቡ ባላመኑ ጊዜ፥ ከእነርሱ ርቆ ደቀ መዛሙርትን ለየ፥ ጢራኖስም በሚሉት በትምህርት ቤት ዕለት ዕለት ይነጋገር ነበር።
፲ በእስያም የኖሩት ሁሉ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም የጌታን ቃል እስኪሰሙ ድረስ ሁለት ዓመት ያህል እንዲህ ሆነ።
፲፩ እግዚአብሔርም በጳውሎስ እጅ የሚያሰገርም ተአምራት ያደርግ ነበር፤ ሰለዚህም ከአካሉ ጨርቅ ወይም ልብስ ወደ ድውዮች ይወሰዱ ነበር፥
፲፪ ደዌያቸውም ይለቃቸው ነበር ክፉዎች መናፍስትም ይወጡ ነበር።
፲፫ አጋንንትንም እያወጡ ይዞሩ ከነበሩት አይሁድ አንዳንዶች። ጳውሎስ በሚሰብከው በኢየሱስ እናመላችኋለን እያሉ ክፉዎች መናፍስት ባሉባቸው ላይ የጌታን የኢየሱስን ሰም ይጠሩባቸው ዘንድ ሞከሩ።
፲፬ የካህናትም አለቃ ለሆነ አስቄዋ ለሚሉት ለአንድ አይሁዳዊ ይህን ያደረጉ ሰባት ልጆች ነበሩት።
፲፭ ክፉው መንፈስ ግን መልሶ። ኢየሱስንስ አውቀዋለሁ ጳውሎስንም አውቀዋለሁ፤ እናንተሳ እነማን ናችሁ? አላቸው።
፲፮ ክፉው መንፈስም ያለበት ሰው ዘለለባቸው ቆሰለውም ከዚያ ቤት ዕራቁታቸውን እስኪሸሹ ድረስ በረታባቸው አሸነፋቸውም።
፲፯ ይህም በኤፌሶን በሚኖሩት ሁሉ በአይሁድና በግሪክ ሰዎች ዘንድ የታወቀ ሆነ፥ በሁላቸውም ላይ ፍርሃት ወደቀባቸው፥ የጌታም የኢየሱስ ሰም ተከበረ፤
፲፰ አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር።
፲፱ ከአሰማተኞችም ብዙዎቹ መጽሐፋቸውን ሰብስበው በሰው ሁሉ ፊት አቃጠሉት፤ ዋጋውም ቢታሰብ አምሳ ሺህ ብር ሆኖ ተገኘ።
፳ እንዲህም የጌታ ቃል በኃይል ያድግና ያሸንፍ ነበር።
፳፩ ይህም በተፈጸመ ጊዜ ጳውሎስ። ወደዚያ ደርሼ ሮሜን ደግሞ አይ ዘንድ ይገባኛል ብሎ በመቄዶንያና በአካይያ አልፎ ወደ ኢየሩሳሌም እንዲሄድ በመንፈስ አሰበ።
፳፪ ከሚያገለግሉትም ሁለቱን ጢሞቴዎስንና ኤርስጦንን ወደ መቄዶንያ ልኮ ራሱ በእስያ ጥቂት ቀን ቆየ።
፳፫ በዚያም ጊዜ ሰለዚህ መንገድ ብዙ ሁከት ሆነ።
፳፬ ብር ሠሪ የሆነ ድሜጥሮስ የሚሉት አንድ ሰው የአርጤምስን ቤተ መቅደስ ምሰሎች በብር እየሠራ ለአንጥረኞች እጅግ ትርፍ ያገኝ ነበርና፤
፳፭ እነዚህንም ይህንም የሚመሰለውን ሥራ የሠሩትን ሰብሰቦ እንዲህ አላቸው። ሰዎች ሆይ፥ ትርፋችን በዚህ ሥራ እንደ ሆነ ታውቃላችሁ።
፳፮ ይህም ጳውሎስ። በእጅ የተሠሩቱ አማልክት አይደሉም ብሎ፥ በኤፌሶን ብቻ ሳይሆን ከጥቂት ክፍል በቀር በእስያ ሁሉ ብዙ ሕዝብን እንደ አሰረዳና እንደ አሳተ አይታችኋል ሰምታችሁማል።
፳፯ ሥራችንም እንዲናቅ ብቻ አይደለም፥ እስያ ሁሉ ዓለሙም የሚያመልካት የታላቂቱ አምላክ የአርጤምስ መቅደስ ምናምን ሆኖ እንዲቆጠር እንጂ፥ ታላቅነትዋም ደግሞ እንዳይሻር ያሰፈራል።
፳፰ ይህንም በሰሙ ጊዜ ቍጣ ሞላባቸው። የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉም ጮኹ።
፳፱ ከተማውም በሙሉው ተደባለቀ፥ የመቄዶንያም ሰዎች የጳውሎስን ጓደኞች ጋይዮስንና አርስጥሮኮስን ከእነርሱ ጋር ነጥቀው በአንድ ልብ ሆነው ወደ ጨዋታ ሰፍራ ሮጡ።
፴ ጳውሎስም ወደ ሕዝቡ ይገባ ዘንድ በፈቀደ ጊዜ ደቀ መዛሙርት ከለከሉት።
፴፩ ከእስያም አለቆች ወዳጆቹ የሆኑት አንዳንዶች ደግሞ ወደ እርሱ ልከው ወደ ጨዋታ ሰፍራ ራሱን እንዳይሰጥ ለመኑት።

፴፪ ወዲያና ወዲህም እያሉ ይጮኹ ነበር፤ በጉባኤው ድብልቅልቅ ሆኖ የሚበልጡት ሰንኳ ስለ ምን እንደተሰበሰቡ አላወቁም ነበርና።
፴፫ አይሁድም ሲያቀርቡት፥ እስክንድሮስን ከሕዝቡ መካከል ወደ ፊት ገፉት፤ እስክንድሮስም በእጁ ጠቅሶ በሕዝብ ፊት እንዲምዋገትላቸው ወደደ።
፴፬ አይሁዳዊ ግን እንደ ሆነ ባወቁ ጊዜ፥ ሁሉ በአንድ ድምፅ። የኤፌሶን አርጤምስ ታላቅ ናት እያሉ ሁለት ሰዓት ያህል ጮኹ።
፴፭ የከተማይቱም ጸሐፊ ሕዝቡን ጸጥ አሰኝቶ እንዲህ አለ። የኤፌሶን ሰዎች ሆይ፥ የኤፌሶን ከተማ ለታላቂቱ አርጤምስ ከሰማይም ለወረደው ጣያትዋ የመቅደስ ጠባቂ መሆንዋን የማያውቅ ሰው ማን ነው?
፴፮ ይህንም የሚክደው ከሌለ፥ ጸጥ እንድትሉና አንዳች በችኮላ እንዳታደርጉ ይገባል።
፴፯ የመቅደስን ዕቃ ያልሰረቁ አምላካችንንም ያልሰደቡ እነዚህን ሰዎች አምጥታችኋቸዋልና።
፴፰ ድሜጥሮስና ከእርሱ ጋር ያሉት አንጥረኞች ግን በሰው ላይ ነገር እንዳላቸው፥ የመጋቢያ ቀንና አገረ ገዢዎች አሉ፤ እርስ በርሳቸው ይምዋገቱ።
፴፱ ሰለ ሌላ ነገር እንደ ሆነ ግን አንዳች ብትፈልጉ፥ በተደነገገው ጉባኤ ይፈታል።
፵ ዛሬ ስለ ተደረገው። ሁከት ነው ሲሉ እንዳይከሱን ያሰፈራልና፤ ስለዚህም ሰብሰባ ምላሽ መሰጠት እንችልም፥ ምክንያት የለምና።
፵፩ ይህንም ብሎ ጉባኤውን ፈታው።

፳፩

፩ ሁከቱም ከቀረ በኋላ ጳውሎስ ደቀ መዛሙርቱን አሰመጥቶ መከራቸው፥ ተሰናብቶአቸውም ወደ መቄዶንያ ይሄድ ዘንድ ወጣ።
፪ ያንም አገር እያለፈ በብዙ ቃል ከመከራቸው በኋላ ወደ ግሪክ አገር መጣ።
፫ በዚያም ሦስት ወር ተቀምጦ ወደ ሶርያ በመርከብ ሊሄድ ባሰበ ጊዜ፥ አይሁድ ሴራ ሰላደረጉበት በመቄዶንያ አልፎ ይመለስ ዘንድ ቆረጠ።
፬ የሸኙትም የቤርያው ሱሲጳጥሮስ ከተሰሎንቄ ሰዎችም አርስጥሮኮስና ሲኮንዱስ የደርቤኑም ጋይዮስና ጢሞቴዎስ የእስያ ሰዎችም ቲኪቆስ ጥሮፊሞስም ነበሩ፤
፭ እነዚህም ወደ ፊታችን አልፈው በጢሮአዳ ቆዩን።
፮ እኛ ግን ከቂጣ በዓል ቀን በኋላ ከፊልጵስዩስ በመርከብ ተነሥተን በአምስት ቀን ወደ ጢሮአዳ ወደ እነርሱ ደረስንና በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጥን።
፯ ከሳምንቱም በመጀመሪያ ቀን እንጀራ ለመቁረስ ተሰብሰበን ሳለን፥ ጳውሎስ በነገው ሊሄድ ሰላሰበ ከእነርሱ ጋር ይነጋገር ነበር፥ እስከ መንፈቀ ሌሊትም ነገሩን አሰረዘመ።
፰ ተሰብሰበንም በነበርንበት ሰገነት እጅግ መብራት ነበረ።
፱ አውጤኪስ የሚሉትም አንድ ጎበዝ በመስኮት ተቀምጦ ታላቅ እንቅልፍ እንቀላፍቶ ነበር፤ ጳውሎስም ነገርን ባሰረዘመ ጊዜ እንቅልፍ ከብዶት ከሦስተኛው ደርብ ወደ ታች ወደቀ፥ ሞቶም አነሡት።
፲ ጳውሎስም ወርዶ በላዩ ወደቀ፥ አቅፎም። ነፍሱ አለችበትና አትንጫጩ አላቸው።
፲፩ ወጥቶም እንጀራ ቆርሶም በላ፤ ብዙ ጊዜም እስኪነጋ ድረስ ተነጋገረ እንዲህም ሄደ።
፲፪ ብላቴናውንም ደኅና ሆኖ ወሰዱት እጅግም ተጽናኑ።
፲፫ እኛ ግን ጳውሎስን ከዚያ እንቀበለው ዘንድ ሰላለን ወደ መርከብ ቀድመን ሄድንና ወደ አሶን ተነሣን፤ እርሱ በመሬት ይሄድ ዘንድ ሰላሰበ እንደዚህ አዞ ነበርና።
፲፬ በአሶንም ባገኘን ጊዜ ተቀብለነው ወደ ሚጢሊኒ መጣን፤
፲፭ በማግሥቱም ከዚያ በባሕር ተነሥተን በኪዩ ፊት ለፊት ደረስን፥ በነገውም ወደ ሳሞን ተሻገርን በትሮጊሊዮም አድረን በማግሥቱ ወደ ሚሊጢን መጣን።
፲፮ ጳውሎስ በእስያ እጅግ እንዳይቀመጥ ኤፌሶንን ይተው ዘንድ ቆርጦ ነበርና ቢቻለውም በዓለ ኀምሳን በኢየሩሳሌም ይውል ዘንድ ይቸኩል ነበርና።
፲፯ ከሚሊጢንም ወደ ኤፌሶን ልኮ የቤተክርስቲያንን ሽማግሌዎች አሰጠራቸው፤
፲፰-፲፱ እሁንም፥ እነሆ፥ እኔ በመንፈስ ታሰሬ ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ፥ በዚያም የሚያገኘኝ ምን እንደ ሆነ አላውቅም፤
፳ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ። እሰራትና መከራ ይቆይሃል ብሎ በየከተማው ሁሉ ይመሰክርልኛል።
፳፩ ነገር ግን ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልሁትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ።
፳፪ አሁንም፥ እነሆ፥ እኔ የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበክሁ በመካከላችሁ የዞርሁ ሁላችሁ ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እንዳትዩ አውቃለሁ።
፳፭ ሰለዚህ እኔ ከሰው ሁሉ ደም ንጹሕ እንደ ሆንሁ ዛሬ በዚች ቀን እመሰክርላችኋለሁ።
፳፯ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ነግሬአችኋለሁና፥ ምንም አላሰቀረሁባችሁም።
፳፰ በገዛ ደሙ የዋጀትን የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።
፳፱-፴፩ ሰለዚህ ሦስት ዓመት ሌሊትና ቀን በእንባ እያንዳንዳችሁን ከመገሠጽ እንዳላቋረጥሁ እያሰባችሁ ትጉ።
፴፪ አሁንም ለእግዚአብሔርና ያንጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።
፴፫ ከማንም ብር ወይም ወርቅ ወይም ልብስ አልተመኘሁም፤
፴፬ እነዚህ እጆቼ በሚያሰፈልገኝ ነገር ለእኔና ከእኔ ጋር ላሉት እንዳገለገሉ እናንተ ታውቃላችሁ።
፴፭ እንዲሁ እየደከማችሁ ድውዮችን ልትረዱና እርሱ ራሱ። ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው እንዳለ የጌታን የኢየሱስን ቃል ልታሰቡ ይገባችሁ ዘንድ በሁሉ አሳየኋችሁ።
፴፮ ይህንም ብሎ ተንበርክኮ ከሁላቸው ጋር ጸለየ።
፴፯ ሁሉም እጅግ አለቀሱ፥ ጳውሎስንም አንገቱን አቅፈው ይሰሙት ነበር፤
፴፰ ይልቁንም። ከእንግዲህ ወዲህ ፊቴን እታዩም ሰላላቸው ነገር እጅግ አዘኑ። እስከ መርከብም ድረስ

ሸኙት።

፳፩

፩ ከእነርሱም ተለይተን ተነሣን፤ በቀጥታም ሄደን ወደ ቆስ በነገውም ወደ ሩድ ከዚያም ወደ ጳጥራ መጣን፤
፪ ወደ ፊንቄም የሚሻገር መርከብ አግኝተን ገባንና ተነሣን።
፫ ቆጵሮስንም ባየናት ጊዜ በስተ ግራችን ተውናት ወደ ሶርያም ሄደን ወደ ጢሮስ ደረስን፥ መርከቡ ሸክሙን በዚያ የሚያራግፍ ነበርና።
፬ ደቀ መዛሙርትንም ባገኘን ጊዜ በዚያ ሰባት ቀን ተቀመጥን፤ እነርሱም ጳውሎስን ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ በመንፈስ አሉት።
፭ ጊዜውንም በፈጸምን ጊዜ ወጥተን ሄድን፤ ሁላቸውም ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር እስከ ከተማው ውጭ ድረስ ሸኙን፥ በባሕሩም ዳር ተንበርክከን ጸለይን፤
፮ እርስ በርሳችንም ተሰነባብተን ወደ መርከብ ወጣን፥ እነዚያም ወደ ቤታቸው ተመለሱ።
፯ እኛም የባሕሩን መንገድ ጨርሰን ከጢሮስ ወደ አካ ደረስን፥ ለወንድሞችም ሰላምታ ሰጥተን ከእነርሱ ዘንድ አንድ ቀን ተቀመጥን።
፰ በነገውም ወጥተን ወደ ቂሣርያ መጣን፥ ከሰባቱም አንድ በሚሆን በወንጌላዊው ፊልጶስ ቤት ገብተን በእርሱ ዘንድ ተቀመጥን።
፱ ለእርሱም ትንቢት የሚናገሩ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ነበሩት።
፲ አያሌ ቀንም ተቀምጠን ሳለን ነቢይ የነበረ አጋቦስ የሚሉት አንድ ሰው ከይሁዳ ወረደ።
፲፩ ወደ እኛም መጣና የጳውሎስን መታጠቂያ ወሰደ የገዛ እጁንና እግሩን አሰሮ። እንዲሁ መንፈስ ቅዱስ። ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያሰሩታል በአሕዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል ይላል አለ።
፲፪ ይህንም በሰማን ጊዜ እኛም በዚያ የሚኖሩትም ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ ለመንነው።
፲፫ ጳውሎስ ግን መልሶ። እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ሰም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቼአለሁ እንጂ ለእስራት ብቻ አይደለም አለ።
፲፬ ምክርንም ሊቀበል እምቢ ባለ ጊዜ። የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለን ዝም አልን።
፲፭ ከዚህም ቀን በኋላ ተዘጋጅተን ወደ ኢየሩሳሌም ወጣን።
፲፮ በቂሣርያም ከነበሩ ደቀ መዛሙርት አንዳንዶች ደግሞ ከእኛ ጋር መጡ፥ እነርሱም ወደምናድርበት ወደ ቀደመው ደቀ መዝሙር ወደ ቆጵሮሱ ምናሶን ወደሚሉት ቤት መሩን።
፲፯ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰን ጊዜ ወንድሞች በደስታ ተቀበሉን።
፲፰ በነገውም ጳውሎስ ከእኛ ጋር ወደ ያዕቆብ ዘንድ ገባ ሽማግሌዎችም ሁሉ መጡ።
፲፱ ሰላምታም ካቀረበላቸው በኋላ በእርሱ ማገልገል እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ያደረገውን በእያንዳንዱ ተረከላቸው።
፳ እነርሱም በሰሙ ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገኑ አሉትም። ወንድም ሆይ፥ በአይሁድ መካከል እምነው የነበሩት ሰንት እእላፋት እንደ ሆኑ ታያለህ፤ ሁላቸውም ለሕግ የሚቀኑ ናቸው።
፳፩ ልጆቻቸውንም እንዳይገርዙ በሥርዓትም እንዳይሄዱ ብለህ በአሕዛብ መካከል ያሉት አይሁድ ሁሉ ሙሴን ይክዱ ዘንድ እንድታስተምር ሰለ እነተ ነግረዋቸዋል።
፳፪ እንግዲህ ምን ይሁን? የእነተን መምጣት ይሰማሉና ብዙዎች የግድ ሳይሰበሰቡ አይቀሩም።
፳፫ እንግዲህ ይህን የምንልህን አድርግ፤ ሰለት ያለባቸው አራት ሰዎች በእኛ ዘንድ አሉ።
፳፬ እነዚህንም ይዘህ ከእነርሱ ጋር ንጻ፥ ራሳቸውንም እንዲላጩ ገንዘብ ክፈልላቸው፤ ሁሉም ሰለ እነተ የተማሩት ከንቱ እንደ ሆነና አንተ ራስህ ደግሞ ሕጉን እየጠበቅህ በሥርዓት እንድትመላለስ ያውቃሉ።
፳፭ አምነው ሰለ ነበሩ አሕዛብ ግን ለጣዖት ከተሠዋ ከደምም ከታነቀም ከዝሙትም ነፍሳቸውን እንዲጠብቁ ፈርደን እኛ ጽፈንላቸዋል።
፳፮ በዚያን ጊዜ ጳውሎስ ሰዎችን ይዞ በማግሥቱ ከእነርሱ ጋር እየነጻ፥ መንጻታቸውን የሚፈጽሙበትን ቀን አስታውቆ ወደ መቅደስ ገባ። በዚያም ቀን ሰለ እያንዳንዳቸው መሥዋዕትን አቀረቡ።
፳፯-፳፱ በፊት የኤፌሶኑን ጥሮፊሞስን ከእርሱ ጋር በከተማ አይተውት ነበርና ጳውሎስም ወደ መቅደስ ያገባው መስሎአቸው ነው።
፴ ከተማውም ሁሉ ታወከ ሕዝቡም ሁሉ ተሰበሰቡ ጳውሎስንም ይዘው ከመቅደስ ውጭ ጎተቱት፥ ወዲያውም ደጆች ተዘጉ።
፴፩ ሊገድሉትም ሲፈልጉ። ኢየሩሳሌም ፈጽማ ታወከች የሚል ወሬ ወደ ጭፍራው ሻለቃ ወጣ፤
፴፪ እርሱም ያን ጊዜ ወታደሮችን ከመቶ አለቆች ጋር ይዞ እየሮጠ ወረደባቸው፤ እነርሱም የሻለቃውንና ወታደሮችን ባዩ ጊዜ ጳውሎስን መምታት ተዉ።
፴፫ በዚያን ጊዜም የሻለቃው ቀርቦ ያዘውና በሁለት ሰንሰለት ይታሰር ዘንድ አዞ ማን እንደ ሆነና ምን እንዲደረገ ጠየቀ።
፴፬ ሕዝቡም እኩሌቶቹ እንዲህ እኩሌቶቹም እንዲያ እያሉ ይጮኹ ነበር፤ ሰለ ጫጫታውም እርግጡን ማወቅ ባለተቻለ ጊዜ፥ ወደ ወታደሮች ሰፈር ይወሰዱት ዘንድ አዘዘ።
፴፭ ወደ ደረጃውም በደረሰ ጊዜ ሰለ ሕዝቡ ግፊያ ወታደሮች እንዲሸከሙት ሆነ፤
፴፮ ብዙ ሕዝብ። አስወግደው እያሉና እየጮኹ ይከተሉ ነበርና።
፴፯ ወደ ሰፈርም ሊያገቡት በቀረቡ ጊዜ፥ ጳውሎስ የሻለቃውን። እንድ ነገር ብነግርህ ትፈቅዳለህን? አለው። እርሱም። የግሪክ ቋንቋ ታውቃለህን?
፴፰ እንተ ከዚህ ዘመን አስቀድሞ ከነፍስ ገዳዮቹ አራቱን ሺህ ሰዎች አሸፍተህ ወደ ምድረ በዳ ያወጣህ የግብፅ ሰው አይደለህምን? አለ።
፴፱ ጳውሎስ ግን። እኔስ አይሁዳዊ በኪልቅያ ያለው የጠርሴስ ሰው ሆኜ ሰመ ጥር በሆነ ከተማ የምኖር ነኝ፤ ለሕዝቡ እናገር ዘንድ እንድትፈቅድልኝ እለምንሃለሁ አለ።
፵ በፈቀደለትም ጊዜ ጳውሎስ በደረጃው ላይ ቆሞ በእጁ ወደ ሕዝቡ ጠቀሰ እጅግም ጸጥታ በሆነ ጊዜ በዕብራይስጥ ቋንቋ እየተናገረ እንዲህ አለ።

፳፪

፩ እናንተ ወንድሞች አባቶችም፥ አሁን ለእናንተ ነገሬን ሰገልጥ ሰሙኝ።
፪ በዕብራይሰጥም ቋንቋ ሲናገር በሰሙ ጊዜ ከፊት ይልቅ ዝም አሉ። እርሱም አለ።
፫ እኔ የኪልቅያ በምትሆን በጠርሴስ የተወለድሁ፥ በዚችም ከተማ በገማልያል እግር አጠገብ ያደግሁ፥ የአባቶችንም ሕግ ጠንቅቄ የተማርሁ፥ ዛሬውንም እናንተ ሁሉ እንድትሆኑ ለእግዚአብሔር ቀናተኛ የሆንሁ አይሁዳዊ ሰው ነኝ
፬ ወንዶችንም ሴቶችንም እያሰርሁ ወደ ወኅኒም አሳልፌ እየሰጠሁ ይህን መንገድ እስከ ሞት ድረስ አሳደድሁ።
፭ እንዲህም ሊቀ ካህናቱ ደግሞ ሸማግሌዎቹም ሁሉ ይመሰክሩልኛል፤ ከእነርሱ ደግሞ መልእክትን ለወንድሞቻቸው ተቀብዬ፥ በደማስቆ ያሉትን ደግሞ ታሰረው እንዲቀጡ ወደ ኢየሩሳሌም ላመጣ ወደዚያ እሄድ ነበር።
፮ ሰሄድም ወደ ደማስቆ በቀረብሁ ጊዜ፥ ቀትር ሲሆን ድንገት ከሰማይ ታላቅ ብርሃን በዙሪያዬ አንጸባረቀ፤
፯ በምድርም ላይ ወድቄ። ሳውል ሳውል፥ ሰለ ምን ታሳድደኛለህ? የሚለኝን ድምፅ ሰማሁ።
፰ እኔም መልሼ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ማን ነህ? አልሁ። እርሱም። አንተ የምታሳድደኝ የናዝሬቱ ኢየሱስ እኔ ነኝ አለኝ።
፱ ከእኔ ጋር የነበሩትም ብርሃኑን አይተው ፈሩ፥ የሚናገረኝን የእርሱን ድምፅ ግን አልሰሙም።
፲ ጌታ ሆይ፥ ምን ላድርግ? አልሁት። ጌታም። ተነሥተህ ወደ ደማስቆ ሂድና ታደርገው ዘንድ ሰለ ታዘዘው ሁሉን በዚያ ይነግሩሃል አለኝ።
፲፩ ከዚያ ብርሃንም ክብር የተነሣ ማየት ባይሆንልኝ ከእኔ ጋር የነበሩት ሰዎች እጄን ይዘው እየመሩኝ ወደ ደማስቆ ደረስሁ።
፲፪ በዚያም የኖሩት አይሁድ ሁሉ የመሰከሩለት እንደ ሕጉም በጸሎት የተጋ ሐናንያ የሚሉት አንድ ሰው ነበረ።
፲፫ እርሱም ወደ እኔ መጥቶ በአጠገቤም ቆሞ። ወንድሜ ሳውል ሆይ፥ እይ አለኝ። እኔም ያን ጊዜውኑ ወደ እርሱ አየሁ።
፲፬ እርሱም አለኝ። የአባቶቻችን አምላክ ፈቃዱን ታውቅ ዘንድና ጻድቁን ታይ ዘንድ ከአፉም ድምፅን ትሰማ ዘንድ አሰቀድሞ መርጦሃል
፲፭ ባየኸውና በሰማኸው በሰው ሁሉ ፊት ምሰክር ትሆንለታለህና።
፲፮ አሁንስ ለምን ትዘገያለህ? ተነሣና ሰሙን እየጠራህ ተጠመቅ ከኃጢአትህም ታጠብ።
፲፯ ወደ ኢየሩሳሌምም ከተመለሱ በኋላ በመቅደስ ሰጸልይ ተመሰጦ መጣብኝ፥
፲፰ እርሱም። ፍጠን ከኢየሩሳሌምም ቶሎ ውጣ፥ ሰለ እኔ የምትመሰክረውን አይቀበሉህምና ሲለኝ አየሁት።
፲፱ እኔም። ጌታ ሆይ፥ በአንተ የሚያምኑትን በምኩራብ ሁሉ እኔ በወኅኒ አገባና እደበድብ እንደ ነበርሁ እነርሱ ያውቃሉ፤
፳ የሰማዕትህንም የእስጢፋኖስን ደም ባፈሰሱ ጊዜ፥ ራሴ ደግሞ በአጠገባቸው ሰቆም ተሰማምቼ የገዳዮችን ልብስ እጠብቅ ነበር አልሁ።
፳፩ እርሱም። ሂድ፥ እኔ ወደ አሕዛብ ከዚህ ወደ ሩቅ እልክሃለሁና አለኝ።
፳፪ እስከዚህም ቃል ድረስ ይሰሙት ነበር፥ ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው። እንደዚህ ያለውን ሰው ከምድር አስወግደው፥ በሕይወት ይኖር ዘንድ አይገባውምና አሉ።
፳፫ ሲጮኹና ልብሳቸውን ሲወረውሩ ትቢያንም ወደ ላይ ሲበትኑ፥
፳፬ የሻለቃው ወደ ሰፈሩ እንዲያገቡት አዘዘ፥ እንደዚህም የጮኹበትን ምክንያት ያውቅ ዘንድ። እየገረፉትሁ መርምሩት አላቸው።
፳፭ በጠፍርም በገተሩት ጊዜ ጳውሎስ በአጠገቡ የቆመውን የመቶ አለቃ። የሮሜን ሰው ያለ ፍርድ ትገርፉ ዘንድ ተፈቅዶላችኋልን? አለው።
፳፮ የመቶ አለቃውም በሰማ ጊዜ ወደ ሻለቃው ቀርቦ። ይህ ሰው ሮማዊ ነውና ታደርገው ዘንድ ካለህ ተጠበቅ ብሎ ነገረው።
፳፯ የሻለቃውም ቀርቦ። አንተ ሮማዊ ነህን? ንገረኝ አለው፤ እርሱም። አዎን አለ።
፳፰ የሻለቃውም መልሶ። እኔ ይህን ዜግነት በብዙ ገንዘብ አገኘሁት አለ። ጳውሎስም። እኔ ግን በእርስዋ ተወለድሁ አለ።
፳፱ ሰለዚህም ሊመረምሩት ያሰቡት ከእርሱ ወዲያው ተለዩ፤ የሻለቃውም ደግሞ ሮማዊ መሆኑን ባወቀ ጊዜ ፈራ፥ አሳሰሮት ነበርና።
፴ በማግሥቱም እይሁድ የከሰሱት በምን ምክንያት እንደ ሆነ እርግጡን ያውቅ ዘንድ አሰቦ ፈታው፥ የካህናት አለቆችና ሸንጎውም ሁሉ ይሰበሰቡ ዘንድ አዘዘ፥ ጳውሎስንም አውርዶ በፊታቸው አቆመው።

፳፫

፩ ጳውሎስም ሸንጎውን ትኩር ብሎ ተመልክቶ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ እስከዚች ቀን ድረስ በመልካም ሕሊና ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ኖሬአለሁ አለ።
፪ ሊቀ ካህናቱም ሐናንያ አፉን ይመቱት ዘንድ በአጠገቡ ቆመው የነበሩትን አዘዘ።
፫ በዚያን ጊዜ ጳውሎስ። አንተ በኖራ የተለሰነ ግድግዳ፥ እግዚአብሔር አንተን ይመታ ዘንድ አለው፤ አንተ በሕግ ልትፈርድብኝ ተቀምጠህ ሳለህ ያለ ሕግ እመታ ዘንድ ታዛለህን? አለው።
፬ በአጠገቡ የቆሙትም። የእግዚአብሔርን ሊቀ ካህናት ትሳደባለህን? አሉት።
፭ ጳውሎስም። ወንድሞች ሆይ፥ ሊቀ ካህናት መሆኑን ባላውቅ ነው፤ በሕዝብህ አለቃ ላይ ክፉ ቃል አትናገር ተብሎ ተጽፎአልና አላቸው።
፮ ጳውሎስ ግን አኩሌቶቹ ሰዱቃውያን አኩሌቶቹም ፈሪሳውያን መሆናቸውን አይቶ። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ፈሪሳዊ የፈሪሳዊም ልጅ ነኝ፤ ሰለ ተስፋና ሰለ ሙታን መነሣት ይፈርዱብኛል ብሎ በሸንጎው ጮኸ።
፯ ይህንም ባለ ጊዜ በፈሪሳውያንና በሰዱቃውያን መካከል ጥል ሆነ ሸንጎውም ተለያየ።
፰ ሰዱቃውያን። ትንሣኤም መልአክም መንፈስም የለም የሚሉ ናቸውና፤ ፈሪሳውያን ግን ሁለቱን ያምናሉ።
፱ ታላቅ ጩኸትም ሆነ፥ ከፈሪሳውያንም ወገን የሆኑት ጸፎች ተነሥተው። በዚህ ሰው ላይ ምንም ክፉ

ነገር አላገኘንበትም፤ መንፈስ ወይስ መልአክ ተናግሮት ይሆን? ብለው ተከራከሩ።
፱ ብዙ ጥልም በሆነ ጊዜ የሻለቃው ጳውሎስን እንዳይገነጣጥሉት ፈርቶ ጭፍሮቹ ወርደው ከመካከላቸው እንዲነጥቁት ወደ ሰፈሩም እንዲያገቡት አዘዘ።
፲ በሁለተኛውም ሌሊት ጌታ በአጠገቡ ቆሞ። ጳውሎስ ሆይ፥ በኢየሩሳሌም ስለ እኔ እንደ መሰከርህ እንዲሁ በሮሜም ትመሰክርልኛ ዘንድ ይገባሃልና አይዞህ አለው።
፲፩ በጠባም ጊዜ አይሁድ ጳውሎስን እስኪገድሉት ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ በመሐላ ተሰማሙ።
፲፪ ይህንም ሴራ ያደረጉት ሰዎች ከአርባ ይበዙ ነበር፤
፲፫ እነርሱም ወደ ካህናት አለቆችና ወደ ሽማግሌዎቹ መጥተው። ጳውሎስን እስክንገድል ድረስ ምንም እንዳንቀምስ ተረጋግመን ተማምለናል።
፲፬ እንግዲህ አሁን እናንተ ከሸንጎው ጋር ሆናችሁ ስለ እርሱ እጥብቃችሁ እንደምትመረምሩ መሰላችሁ ወደ እናንተ እንዲያወርደው ለሻለቃው አመልክቱት፤ እኛም ሳይቀርብ እንድንገድለው የተዘጋጀን ነን አሉአቸው።
፲፭ የጳውሎስ የእኅቱ ልጅ ግን ደባቸውን በሰማ ጊዜ፥ መጥቶ ወደ ሰፈሩ ገባና ለጳውሎስ ነገረው።
፲፮ ጳውሎስም ከመቶ አለቆች አንዱን ጠርቶ። ይህን ብላቴና ወደ ሻለቃው ውሰድ፥ የሚያወራለት ነገር አለውና አለው።
፲፯ እርሱም ይዞት ወደ ሻለቃው ወሰደውና። ይህ ብላቴና የሚነግርህ ነገር ስላለው እስረኛው ጳውሎስ ጠርቶ ወደ እነተ እንድወሰደው ለመነኝ አለው።
፲፰ የሻለቃውም እጁን ይዞ ፈቀቅ አለና ለብቻው ሆኖ። የምታወራልኝ ነገር ምንድር ነው? ብሎ ጠየቀው።
፲፱ እርሱም። አይሁድ ስለ ጳውሎስ ከፊት ይልቅ አጥብቀህ እንደምትመረምር መሰለህ፥ ነገ ወደ ሸንጎ ታወርደው ዘንድ ሊለምኑህ ተሰማምተዋል።
፳ እንግዲህ አንተ በጅ አትበላቸው፤ እስኪገድሉት ድረስ እንዳይበሉና እንዳይጠጡ ተማምለው ከእነርሱ ከአርባ የሚበዙ ሰዎች ያደቡበታልና፤ አሁንም የተዘጋጁ ናቸው የአንተንም ምላሽ ይጠብቃሉ አለው።
፳፩ የሻለቃውም። ይህን ነገር ለእኔ ማመልከትህን ለማንም እንዳትገልጥ ብሎ ካዘዘ በኋላ ብላቴናውን አሰናበተው።
፳፪ ከመቶ አለቆቹም ሁለት ጠርቶ። ወደ ቂሣርያ ይሄዱ ዘንድ ሁለት መቶ ወታደሮችንና ሰባ ፈረሰኞችን ሁለት መቶም ባለ ጦር መሣሪያዎችን ከሌሊቱ በሦስተኛው ሰዓት አዘጋጁ አላቸው።
፳፫ ጳውሎስንም ወደ አገረ ገዡ ወደ ፊልክስ በደኅና እንዲያደርሱት የሚያሰቀምጡበትን ከብት ያዘጋጁ ዘንድ አዘዛቸው።
፳፬ ደብዳቤም ጻፈ እንዲህ የሚል።
፳፭ ከቀላውዴዎስ ሉስዮስ ወደ ክቡር አገረ ገዡ ወደ ፊልክስ፤ ሰላም ለአንተ ይሁን።
፳፮ ይህን ሰው አይሁድ ይዘው ሊገድሉት ባሰቡ ጊዜ ከጭፍሮቹ ጋር ደርሼ አዳንሁት፥ ሮማዊ እንደ ሆነ አውቄ ነበርና።
፳፯ የሚከሰሰበትንም ምክንያት አውቅ ዘንድ አሰቤ ወደ ሸንጎአቸው አወረድሁት፤
፳፰ በሕጋቸውም ስለ መከራከር እንደ ከሰሱት አገኘሁ እንጂ ለሞት ወይም ለእስራት የሚያደርስ ክስ አይደለም።
፳፱ በዚህም ሰው አይሁድ ሴራ እንዲያደርጉበት ባመለከቱኝ ጊዜ ያን ጊዜውን ወደ አንተ ሰደድሁት፥ ከሳሾቹንም ደግሞ በፊትህ ይከሱት ዘንድ አዘዝኋቸው። ደኅና ሁን።
፴ ወታደሮቹም እንደ ታዘዙት ጳውሎስን ይዘው በሌሊት ወደ አንቲጳጥሪስ አደረሱት፤
፴፩ በነገውም ከእርሱ ጋር ይሄዱ ዘንድ ፈረሰኞችን ትተው ወደ ሰፈር ተመለሱ።
፴፪ እነዚያም ወደ ቂሣርያ ገብተው ደብዳቤውን ለአገረ ገዡ በሰጡ ጊዜ ጳውሎስን ደግሞ በፊቱ አቆሙት።
፴፫ ካነበበውም በኋላ የወዴት አውራጃ እንደ ሆነ ጠየቀው፤ የኪልቅያ ሰው መሆኑንም ባወቀ ጊዜ።
፴፬ ከሳሾችህ ደግሞ ሲመጡ እሰማሃለሁ አለው፤ በሄሮድስም ግቢ ውስጥ ይጠብቁት ዘንድ አዘዘ።

፳፬

፩ ከአምስት ቀንም በኋላ ሊቀ ካህናቱ ሐናንያ ከሸማግሌዎችና ጠርጠሉስ ከሚሉት ከአንድ ጠበቃ ጋር ወረደ፤ እነርሱም ስለ ጳውሎስ ለአገረ ገዡ አመለከቱት።
፪-፬ ነገር ግን እጅግ እንዳላቆይህ በቸርነትህ በአጭሩ ትሰማን ዘንድ እለምንሃለሁ።
፭ ይህ ሰው በሽታ ሆኖ በዓለም ባሉት አይሁድ ሁሉ ሁከት ሲያስነሣ፥ የመናፍቃን የናዝራውያን ወገን መሪ ሆኖ አግኝተነዋልና፤
፮ መቅደስንም ደግሞ ሊያረክስ ሲሞክር ያዝነው፥ እንደ ሕጋችንም እንፈርድበት ዘንድ ወደድን።
፯ ነገር ግን የሻለቃው ሉስዮስ መጥቶ በብዙ ኃይል ከእጃችን ወሰደው፥
፰ ከሳሾቹንም ወደ አንተ ይመጡ ዘንድ አዘዘ፤ አንተም ራስህ እርሱን መርምረህ እኛ ስለምንከሰበት ነገር ሁሉ ልታውቅ ትችላለህ።
፱ አይሁድም ደግሞ። ይህ ነገር እንዲሁ ነው እያሉ ተሰማሙ።
፲ ገዡም በጠቀሰው ጊዜ ጳውሎስ መለሰ እንዲህ ሲል። ከብዙ ዘመን ጀምረህ ለዚህ ሕዝብ አንተ ፈራጅ እንደ ሆንህ እውቃለሁና ደስ እያለኝ ስለ እኔ ነገር እመልሳለሁ፤
፲፩ እሰግድ ዘንድ ወደ ኢየሩሳሌም ከወጣሁ ከአሥራ ሁለት ቀን እንዳይበልጥ ልታውቀው ትችላለህ።
፲፪ ከእንድም ሰንኳ ሰነጋገር ወይም ሕዝብን ሰሰበሰብ በመቅደስ ቢሆን በምኩራብም ቢሆን በከተማም ቢሆን አላገኙኝም።
፲፫ አሁንም ስለሚከሱኝ ያሰረዱህ ዘንድ አይችሉም።
፲፬ ነገር ግን ይህን እመሰክርልሃለሁ፤ በሕጉ ያለውን በነቢያትም የተጻፉትን ሁሉ አምኜ የአባቶቼን አምላክ እነርሱ ኑፋቄ ብለው እንደሚጠሩት መንገድ አመልካለሁ፤
፲፭ እነዚህም ራሳቸው ደግሞ የሚጠብቁት፥ ጻድቃንም ዓመፀኞችም ከሙታን ይነሡ ዘንድ እንዳላቸው ተስፋ በእግዚአብሔር ዘንድ አለኝ።

፲፭ ስለዚህ እኔ ደግሞ በእግዚአብሔርና በሰው
ፊት ሁልጊዜ ነውር የሌለባት ሕሊና ትኖረኝ ዘንድ
እተጋለሁ።
፲፯ ከብዙ ዓመትም በኋላ ለሕዝቤ ምጽዋትና
መሥዋዕት አደርግ ዘንድ መጣሁ፤
፲፰ ይህንም ሳደርግ ሳለሁ ሕዝብ ሳይሰበሰብ
ሁከትም ሳይሆን በመቅደስ ሰነጸ አገኙኝ።
፲፱ ነገር ግን በእኔ ላይ ነገር ያላቸው እንደ ሆነ፥
በፊትህ መጥተው ይከሱኝ ዘንድ የሚገባቸው ከእስያ
የመጡ አንዳንድ አይሁድ እሉ።
፳-፳፩ ፊልክስ ግን የመንገዱን ነገር እጥብቆ
እውቆአልና። የሻለቃው ሉስዮስ በወረደ ጊዜ ነገራችሁን
እቆርጣለሁ ብሎ ወደ ፊት አዘገያቸው።
፳፫ የመቶውንም አለቃ ጳውሎስን ሲጠብቅ
እንዲያደላለት፥ ከወዳጆቹም ማንም ሲያገለግለው
ወይም ወደ እርሱ ሲመጣ እንዳይከለክልበት አዘዘው።
፳፬ ከጥቂት ቀንም በኋላ ፊልክስ አይሁዳዊት
ከነበረች ድሩሲላ ከሚሉአት ከሚስቱ ጋር መጥቶ
ጳውሎስን አስመጣ፥ በኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ማመን
የሚናገረውን ሰማው።
፳፭ እርሱም ስለ ጽድቅና ራስን ስለ መግዛት
ስለሚመጣውም ኩነኔ ሲነጋገር ሳለ፥ ፊልክስ ፈርቶ።
አሁንስ ሂድ፥ በተመቸኝም ጊዜ ልኬ አስጠራሃለሁ
ብሎ መለሰለት።
፳፮ ያን ጊዜም ደግሞ እንዲፈታው ጳውሎስ ገንዘብ
ይሰጠው ዘንድ ተስፋ አደረገ፤ ስለዚህ ደግሞ ብዙ
ጊዜ እያስመጣ ያነጋግረው ነበር።
፳፯ ሁለት ዓመትም ከሞላ በኋላ ጶርቅዮስ ፊስጦስ
በፊልክስ ፈንታ ተተካ። ፊልክስም አይሁድን ደስ ያሰኝ
ዘንድ ወደ ጳውሎስን እንደ ታሰረ ተወው።

ምዕ ፳፭

፩ ፊስጦስም ወደ አውራጃው ገብቶ ከሦስት ቀን
በኋላ ከቂሣርያ ወደ ኢየሩሳሌም ወጣ።
፪ የካህናቱ አለቆችና የአይሁድም ታላላቆች
በጳውሎስ ላይ አመለከቱ፥
፫ ጳውሎስንም ሲቃወም እንዲያደላላቸው እየለመኑ፥
በመንገድ ሸምቀው ይገድሉት ዘንድ አሰበው ወደ
ኢየሩሳሌም እንዲያስመጣው ማለዱት።
፬ ፊስጦስ ግን ጳውሎስ በቂሳርያ እንዲጠበቅ
እርሱም ራሱ ወደዚያ ፈጥኖ ይሄድ ዘንድ እንዳለው
መለሰላቸው፤
፭ እንግዲህ በዚህ ሰው ክፋት ቢሆን ከእናንተ ዘንድ
ያሉት ባለ ሰልጣኖች ከእኔ ጋር ወርደው ይክሰሱት
አላቸው።
፮ በእነርሱም ዘንድ ከሰምንት ወይም ከአሰር
የማይበልጥ ቀን ተቀምጦ ወደ ቂሳርያ ወረደ፤
በነገውም በፍርድ ወንበር ተቀምጦ ጳውሎስን
ያመጡት ዘንድ አዘዘ።
፯ በቀረበም ጊዜ ከኢየሩሳሌም የወረዱት አይሁድ
ከበውት ቆሙ፥ ይረቱበትም ዘንድ የማይችሉትን ብዙና
ከባድ ክስ አነሱበት፤
፰ ጳውሎስም ሲምዋገት። የአይሁድን ህግ ቢሆን
መቅደስንም ቢሆን ቄሳርንም ቢሆን አንዳች ሰንኳ
አልበደልሁም አለ።
፱ ፊስጦስ ግን አይሁድን ደስ ያሰኝ ዘንድ ወዶ
ጳውሎስን። ወደ ኢየሩሳሌም ወጥተህ ስለዚህ ነገር
ከዚያው በፊቴ ትፋረድ ዘንድ ትወዳለህን? ብሎ
መለሰለት።
፲ ጳውሎስ ግን። እፋረድበት ዘንድ በሚገባኝ
በቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ። አንተው
ደግሞ ፈጽመህ እንደምታውቅ አይሁድን ምንም
አልበደልሁም።
፲፩ እንግዲህ በድዬ ወይም ሞት የሚገባውን ነገር
አድርጌ እንደ ሆነ ከሞት ልዳን አልልም፤ እነዚህ
የሚከሱኝ ክስ ከንቱ እንደሆነ ግን ለእነርሱ አሳልፎ
ይሰጠኝ ዘንድ ማንም አይችልም፤ ወደ ቄሳር ይግባኝ
ብዬአለሁ አለ።
፲፪ በዚያን ጊዜ ፊስጦስ ከአማካሪዎቹ ጋር
ተማክሮ። ወደ ቄሳር ይግባኝ ብለሃል፤ ወደ ቄሳር
ትሄዳለህ ብሎ መለሰለት።
፲፫ ከጥቂት ቀንም በኋላ ንጉሡ አግሪጳ በርኒቄም
ለፊስጦስ ሰላምታ እንዲያቀርቡ ወደ ቄሳርያ ወረዱ።
፲፬ በዚያውም ብዙ ቀን ስለተቀመጡ ፊስጦስ
የጳውሎስን ነገር ለንጉሡ እንዲህ ብሎ ገለጠ።
ፊልክስ አሰሮ የተወው አንድ ሰው በዚህ አለ፤
፲፭ በኢየሩሳሌምም ሳለሁ የካህናት አለቆችና
የአይሁድ ሽማግሌዎች እፈርድበት ዘንድ እየለመኑ ስለ
እርሱ አመለከቱኝ።
፲፮ እኔም። ተከሳሹ በከሳሾቹ ፊት ለፊት ሳይቆም
ለተከሰሰበትም መልስ ይሰጥ ዘንድ ፈንታ ሳያገኝ፥
ማንንም ቢሆን አሳልፎ መስጠት የሮማውያን ሥርዓት
አይደለም ብዬ መለስሁላቸው።
፲፯ ስለዚህም በዚህ በተሰበሰቡ ጊዜ፥ ሳልዘገይ
በማግሥቱ በፍርድ ወንበር ተቀምጬ ያንን ሰው
ያመጡት ዘንድ አዘዝሁ።
፲፰ ከሳሾቹም በቆሙ ጊዜ እኔ ያሰብሁትን ክፉ ነገር
ክስ ምንም አላመጡበትም፤
፲፱ ነገር ግን ስለ ገዛ ሃይማኖታቸውና ጳውሎስ።
ሕያው ነው ስለሚለው ስለ ሞተው ኢየሱስ ስለ
ተባለው ከእርሱ ጋር ይከራከሩ ነበር።
፳ እኔም ይህን ነገር እንዴት እንድመረምር እመነትቼ።
ወደ ኢየሩሳሌም ሄደህ በዚህ ነገር ከዚያ ልትፋረድ
ትወዳለህን? አልሁት።
፳፩ ጳውሎስ ግን አውግስጦስ ቄሣር እስኪቈርጥ
ድረስ እንዲጠበቅ ይግባኝ ባለ ጊዜ፥ ወደ ቄሣር
እስክሰደው ድረስ ይጠበቅ ዘንድ አዘዝሁ።
፳፪ አግሪጳም ፊስጦስን። ያንንስ ሰው እኔ ዳግም
እኮ እሰማው ዘንድ እወድ ነበር አለው። እርሱም። ነገ
ትሰማዋለህ አለው።
፳፫ በነገውም አግሪጳና በርኒቄ በብዙ ግርማ
መጥተው ከሻለቆችና ከከተማው ታላላቆች ጋር ወደ
ፍርድ ቤት ገቡ፤ ፊስጦስም ባዘዘ ጊዜ ጳውሎስን
አመጡት።
፳፬ ፊስጦስም አለ። አግሪጳ ንጉሥ ሆይ እናንተም
ከእኛ ጋር ያላችሁ ሰዎች ሁሉ፥ ከእንግዲህ ወዲህ
በሕይወት ይኖር ዘንድ እንዳይገባው እየጮኹ
የአይሁድ ሕዝብ ሁሉ በኢየሩሳሌም በዚህም ስለ
እርሱ የለመኑኝን ይህን ሰው ታዩታላችሁ።
፳፭ እኔ ግን ሞት የሚገባውን ነገር እንዳላደረገ
አስተዋልሁ፥ እርሱም ወደ አውግስጦስ ይግባኝ ስላለ
እስደው ዘንድ ቈረጥሁ።
፳፮ ስለ እርሱም ወደ ጌታዬ የምጽፈው እርግጥ
ነገር የለኝም፤ ስለዚህ ከተመረመረ በኋላ የምጽፈውን

ነገር አገኝ ዘንድ በፊታችሁ ይልቁንም በፊትህ፥ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ አመጣሁት፤
፳፯ እስረኛ ሲላክ የተከሰሰበትን ምክንያት ደግሞ አለማመልከት ሞኝነት መሰሎኛልና።

ምዕ ፳፮

፩ አግሪጳም ጳውሎስን። ስለ ራስህ ትናገር ዘንድ ተፈቅዶልሃል አለው። በዚያን ጊዜ ጳውሎስ እጁን ዘርግቶ መለሰ እንዲህ ሲል።
፪-፬ ከመጀመሪያ አንሥቶ በሕዝቤ መካከል በኢየሩሳሌም የሆነውን፥ ከታናሽነቴ ጀምሬ የኖርሁትን ኑሮዬን አይሁድ ሁሉ ያውቃሉ፤
፭ ሊመሰክሩ ይወዱ እንደ ሆነ፥ በአምልኮአችን ከሁሉ ይልቅ ሕግን በመጠንቀቅ እንደሚተጋ ወገን ፈሪሳዊ ሆኜ እንደኖርሁ ከጥንት ጀምረው አውቀውኛልና።
፮ አሁንም ከእግዚአብሔር ዘንድ ለአባቶቻችን ስለ ተሰጠው ስለ ተሰፋ ቃል አለኝታ ልፋረድ ቆሜአለሁ።
፯ ወደዚህም ወደ ተሰፋ ቃል አሥራ ሁለቱ ወገኖቻችን ሌሊትና ቀን በትጋት እያመለኩ ይደርሱ ዘንድ አለኝታ አላቸው፤ ስለዚህም አለኝታ፥ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ከአይሁድ እከሰሳለሁ።
፰ እግዚአብሔር ሙታንን የሚያስነሣ እንደ ሆነ ስለ ምን በእናንተ ዘንድ የማይታመን ነገር ሆኖ ይቈጠራል?
፱ እኔም ራሴ የናዝሬቱን የኢየሱስን ስም የሚቃወም እጅግ ነገር እደርግ ዘንድ እንዲገባኝ ይመስለኝ ነበር።
፲ ይህንም ደግሞ በኢየሩሳሌም አደረግሁት፤ ከካህናት አለቆችም ሥልጣን ተቀብዬ እኔ ከቅዱሳን ብዙዎችን በወኅኒ አሳስርኋቸው፥ ሲገድሉአቸውም አብሬ ተቸሁ።
፲፩ በምኩራብም ሁሉ ብዙ ጊዜ እየቀጣሁ ይሰድቡት ዘንድ ግድ አልኋቸው፤ ያለ ልክ ስቈጣባቸውም እስከ ውጭ አገር ከተማዎች ድረስ እነኳ አሳድድ ነበር።
፲፪ ስለዚህም ነገ ከካህናት አለቆች ሥልጣንና ትእዛዝ ተቀብዬ ወደ ደማስቆ ሰሄድ፥
፲፫ ንጉሥ ሆይ፥ በመንገድ ሳለሁ እኩል ቀን ሲሆን በዙሪያዬና ከእኔ ጋር በሄዱት ዙሪያ ከፀሐይ ብሩህነት የበለጠ ብርሃን ከሰማይ ሲበራ አየሁ፤
፲፬ ሁላችንም በምድር ላይ በወደቅን ጊዜ። ሳውል ሳውል፥ ስለ ምን ታሳድደኛለህ? የመውጊያውን ብረት ብትቃወም ለአንተ ይብሰብሃል የሚል ድምፅ በዕብራይስጥ ቋንቋ ሲናገረኝ ሰማሁ።
፲፭ እኔም። ጌታ ሆይ፥ ማንነህ? አልሁ። እርሱም አለኝ። አንተ የምታሳድደኝ እኔ ኢየሱስ ነኝ።
፲፮ ነገር ግን ተነሣና በእግርህ ቁም፤ ስለዚህ እኔን ባየህበት ነገር ለአንተም በምታይበት ነገር አገልጋይና ምስክር ትሆን ዘንድ ልሾምህ ታይቼልሃለሁና።
፲፯-፲፱ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ስለዚህ ከሰማይ የታየኝን ራእይ እምቢ አላልሁም።
፳ ነገር ግን አስቀድሜ በደማስቆ ላሉት በኢየሩሳሌምም በይሁዳም አገር ሁሉ ለአሕዛብም ንስሐ ይገቡ ዘንድና ለንስሐ የሚገባ ነገር እያደረጉ ወደ እግዚአብሔር ዘወር ይሉ ዘንድ ተናገርሁ።
፳፩ ስለዚህ አይሁድ በመቅደስ ያዙኝ ሊገድሉኝም ሞከሩ።
፳፪-፳፫ እንዲህም ብሎ ስለ ራሱ ሲመሰክስ ፊስጦስ በታላቅ ድምፅ። ጳውሎስ ሆይ፥ አብድሃል እኮ፤ ብዙ ትምህርትህ ወደ አብደት ያዞርሃል አለው።
፳፬ ጳውሎስ ግን እንዲህ አለ። ክቡር ፊስጦስ ሆይ፥ የእውነትንና የአእምሮን ነገር እናገራለሁ እንጂ አብደትሰ የለብኝም።
፳፭ በእርሱ ፊት ደግሞ በግልጥ የምናገረው ንጉሥ ይህን ነገር ያውቃል፤ ከዚህ ነገር አንዱች እንዳይሰወርበት ተረድቼአለሁና፤ ይህ በሰውር የተደረገ አይደለምና።
፳፯ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፥ ነቢያትን ታምናለህን? እንድታምናቸው አውቃለሁ።
፳፰ አግሪጳም ጳውሎስን። በጥቂት ክርስቲያን ልታደርገኝ ትወዳለህ አለው።
፳፱ ጳውሎስም። በጥቂት ቢሆን ወይም በብዙ አንተ ብቻ አይደለህም ነገር ግን ዛሬ የሚሰሙኝ ሁሉ ደግሞ ከዚህ እሰራቴ በቀር እንደ እኔ ይሆኑ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር እለምናለሁ አለው።
፴ ንጉሡም አገረ ገዡም በርኒቄም ከእነርሱም ጋር ተቀምጠው የነበሩት ተነሡ፥
፴፩ ፈቀቅ ብለውም እርስ በርሳቸው። ይህ ሰው እንኳንስ ለሞት ለእሰራትም የሚገባ ምንም አላደረገ ብለው ተነጋገሩ።
፴፪ አግሪጳም ፈስጦስን። ይህ ሰው እኮ ወደ ቄሣር ይግባኝ ባይል ይፈታ ዘንድ ይቻል ነበር አለው።

ምዕ ፳፯

፩ ወደ ኢጣሊያም በመርከብ እንሄድ ዘንድ በተቈረጠ ጊዜ፥ ጳውሎስንና ሌሎችን እስረኞች ከአውግስጦስ ጭፍራ ለነበረ ዩልዮስ ለሚሉት ለመቶ አለቃ አሳልፈው ሰጡአቸው።
፪ በእስያም ዳርቻ ወዳሉ ሰፍራዎች ይሄድ ዘንድ ባለው በአድራሚጢስ መርከብ ገብተን ተነሣን፤ የመቄዶንያም ሰው የሆነ የተሰሎንቄው አርስጥሮኮስ ከእኛ ጋር ነበረ።
፫ በነገውም ወደ ሲዶና ስንደርስ ዩልዮስ ለጳውሎስ ቸርነት አድርጎ እርዳታቸውን ይቀበል ዘንድ ወደ ወዳጆቹ እንዲሄድ ፈቀደለት።
፬ ከዚያም ተነሥተን ነፋሱ ፊት ለፊት ነበረና በቆጵሮስ ተተግነን ሄድን፤
፭ በኪልቅያና በጵንፍልያም አጠገብ ያለውን ባሕር ከተሻገርን በኋላ በሉቅያ ወዳለ ወደ ሙራ ደረስን።
፮ የመቶ አለቃውም በዚያ ወደ ኢጣሊያ የሚሄድ የእስክንድርያውን መርከብ አግኝቶ ወደ እርሱ አገባን።
፯ ብዙ ቀንም እያዘገምን ሄደን በጭንቅ ወደ ቀኒድስ አንጻር ደረስን፤ ነፋሰም ስለ ከለከለን በቀርጤስ ተተግነን በስልሙና አንጻር ሄድን፤
፰ በጭንቅም ጥግ ጥጉን አልፈን ለላሲያ ከተማ ወደ ቀረበች መልካም ወደብ ወደሚሉአት ሰፍራ መጣን።
፱ ብዙ ጊዜም ካለፈ በኋላ፥ የጦም ወራት አሁን አልፎ ስለ ነበረ በመርከብ ለመሄድ አሁን የሚያስፈራ ነበርና ጳውሎስ።
፲ እናንተ ሰዎች ሆይ፥ ይህ ጕዞ በጥፋትና በብዙ ጕዳት እንዲሆን እያለሁ፤ ጥፋቱም በገዛ ሕይወታችን ነው እንጂ በጭነቱና በመርከቡ ብቻ አይደለም ብሎ መከራቸው።

፲፩ የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስ ከተናገረው ይልቅ
የመርከብ መሪውንና የመርከቡን ባለቤት ያምን ነበር።
፲፪ ያም ወደብ ይከርሙበት ዘንድ የማይመች
ስለ ሆነ፥ የሚበዙቱ ቢቻላቸው በስሜንና በደቡብ
ምዕራብ ትይዩ ወዳለው ፍንቂ ወደሚሉት ወደ
ቀርጤስ ወደብ ደርሰው ይከርሙ ዘንድ ከዚያ
እንዲነሡ መከሩ።
፲፫ ልከኛም የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ፥ እንዳሰቡት
የሆነላቸው መሰሎአቸው ተነሡ በቀርጤስም አጠገብ
ጥግ ጥጉን አለፉ።
፲፬ ነገር ግን እጅግ ሳይዘገይ አውራቂስ የሚሉት
ዓውሎ ነፋስ ከዚያ ወረደባቸው፤
፲፭ መርከቡም ተነጥቆ ነፋሱን ሲቃወም መሄድ
ሰላልቻለ ለቀነው ተነዳን።
፲፮ ቄዳ በሚሉአትም ደሴት በተተገንን ጊዜ
ታንኳይቱን ለመግዛት በጭንቅ ቻልን፤
፲፯ ወደ ላይም ካወጡአት በኋላ መርከቡን በገመድ
አሰታጥቀው አደኑ፤ ሰርቲስም ወደሚሉት ወደ አሸዋ
እንዳይወድቁ ፈርተው ሸራውን አውርደው እንዲሁ
ተነዱ።
፲፰ ነፋሱም በርትቶ ሲያሰጨንቀን በማንግሥቱ
ከጭነቱ ወደ ባሕር ይጥሉ ነበር፥
፲፱ በሦስተኛውም ቀን የመርከቡን ዕቃ በእጃችን
ወረወርን።
፳ ብዙ ቀንም ፀሐይን ከዋክብትንም ሳናይ ትልቅ
ነፋስም ሲበረታብን ጊዜ፥ ወደ ፊት እንድናለን የማለት
ተስፋ ሁሉ ተቈረጠ።
፳፩ ሳይበሉም ብዙ ቀን ከቆዩ በኋላ፥ ያን ጊዜ
ጳውሎስ በመካከላቸው ቆሞ እንዲህ አለ። እናንተ
ሰዎች ሆይ፥ ሰምታችሁኝ በሆነ ኖሮ ከቀርጤስ
እንዳትነሡ ይህንም ጥፋትና ጕዳት እንዳታገኙ
ይገባችሁ ነበር።
፳፪ አሁንም። አይዞአችሁ ብዬ እመክራችኋለሁ፤
ይህ መርከብ እንጂ ከእናንተ አንድ ነፍስ እንኳ
አይጠፋምና።
፳፫ የእርሱ የምሆንና ደግሞ የማመልከው
የእግዚአብሔር መልአክ በዚች ሌሊት በአጠገቤ ቆሞ
ነበርና፥ እርሱም።
፳፬ ጳውሎስ ሆይ፥ አትፍራ፤ በቄሣር ፊት ልትቆም
ይገባሃል፤ እነሆም፥ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር
የሚሄዱትን ሁሉ ሰጥቶሃል አለኝ።
፳፭ ስለዚህ እናንተ ሰዎች ሆይ፥ አይዞአችሁ፤
እንደ ተናገረኝ እንዲሁ እንዲሆን እግዚአብሔርን
አምናለሁና።
፳፮ ነገር ግን ወደ አንዲት ደሴት እንድንወድቅ
ያስፈልገናል።
፳፯ በአሥራ አራተኛውም ሌሊት በአድርያ ባሕር
ወዲህና ወዲያ ስንነዳ፥ መርከበኞች በእኩለ ሌሊት
ወደ አንድ ምድር የቀረቡ መሰላቸው።
፳፰ መለኪያ ገመድም ቢጥሉ ሀያ በሰው ቁመት
አገኙ ጥቂትም ቆይተው ሁለተኛ ቢጥሉ አሥራ አምስት
በሰው ቁመት አገኙ፤
፳፱ ድንጋያማም ወደ ሆነ ስፍራ እንዳይወድቁ
ፈርተው፥ ከመርከቡ በሰተኋላ አራት መልሕቅ
አወረዱ፥ ቀንም እንዲሆን ተመኙ።
፴ መርከበኞቹም ከመርከቡ ይሸሹ ዘንድ ፈልገው
ከመርከቡ በሰተ ፊት መልሕቅ መጣል እንዳላቸው
አመካኝተው ታንኳይቱን ወደ ባሕር ባወረዱ ጊዜ፥
፴፩ ጳውሎስ ለመቶ አለቃውና ለወታደሮቹ። እነዚህ
በመርከቡ ካልቆዩ እናንተ ትድኑ ዘንድ አትችሉም
አላቸው።
፴፪ ያን ጊዜ ወታደሮቹ የታንኳይቱን ገመድ ቈርጠው
ትወድቅ ዘንድ ተዉአት።
፴፫ ቀንም ሲነጋ ጳውሎስ ምግብ ይበሉ ዘንድ
ሁሉን ይለምን ነበር፥ እንዲህም አላቸው። እየጠበቃችሁ
ምንም ሳትቀበሉ ጦማችሁን ከሰነበታችሁ ዛሬ አሥራ
አራተኛ ቀናችሁ ነው።
፴፬ ስለዚህ ምግብ ትበሉ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤
ይህ ለደኅንነታችሁ ይሆናልና፤ ከእናንተ ከአንዱ የራስ
ጠጕር እንኳ አትጠፋምና።
፴፭ ይህንም ብሎ እንጀራን ይዞ በሁሉ ፊት
እግዚአብሔርን አመሰገነ ቈርሶም ይበላ ዘንድ ጀመረ።
፴፮ ሁለም ተጽናንተው ራሳቸው ደግሞ ምግብ
ተቀበሉ።
፴፯ በመርከቡም ያለን ሁላችን ሁለት መቶ ሰባ
ሰድሰት ነፍስ ነበርን።
፴፰ በልተውም በጠገቡ ጊዜ ስንዴውን ወደ ባሕር
እየጣሉ መርከቡን አቃለሉት።
፴፱ በነጋም ጊዜ ምድሩን አላወቁትም፥ ነገር ግን
የአሸዋ ዳር ያለውን የባሕር ሰርጥ ተመለከቱ፥
ቢቻላቸውም መርከቡን ወደዚያ ይገፉ ዘንድ ቈረጡ።
፵ መልሕቆቹንም ፈትተው በባሕር ተዉአቸው፥ ያን
ጊዜም የመቅዘፊያውን ማሠሪያ ፈቱት፤ ታናሹንም ሸራ
ለነፋሰ ከፍ አድርገው ወደ ዳር አቅንተው ይሄዱ ዘንድ
ጀመሩ።
፵፩ ነገር ግን ሁለት ባሕር በተገናኙበት ሰፍራ
ወድቀው መርከቡን በዲብ ላይ ነዱ፤ በሰተ ፊቱም
ተተክሎ የማይነቃነቅ ሆነ፥ በሰተ ኋላው ግን ከማዕበሉ
ግፊያ የተነሣ ይሰበር ነበር።
፵፪ ወታደሮቹም ከእስረኞች አንድ ሰንኳ ዋኝቶ
እንዳያመልጥ ይገድሉአቸው ዘንድ ተማከሩ።
፵፫ የመቶ አለቃው ግን ጳውሎስን ያድነው ዘንድ
አሰቦ ምክራቸውን ከለከለ፤ ዋና የሚያውቁትም
ከመርከብ ራሳቸውን እየወረወሩ አስቀድመው ወደ
ምድር ይወጡ ዘንድ፥
፵፬ የቀሩትም አኩሌቶቹ በሳንቃዎች ላይ
አኩሌቶቹም በመርከቡ ሰባሪ ይወጡ ዘንድ አዘዘ።
እንዲሁም ሁሉ በደኅና ወደ ምድር ደረሱ።

፳፰

፩ በደኅና ከደረሰን በኋላ በዚያን ጊዜ ደሴቲቱ
መልጥያ እንድትባል አወቅን።
፪ አረማውያንም የሚያሰገርም ቸርነት አደረጉልን፤
ዝናብ ሰለ ሆነም ሰለ ብርዱም እሳት አንድደው
ሁላችንን ተቀበሉን።
፫ ጳውሎስ ግን ብዙ ጭራሮ አከማችቶ ወደ እሳት
ሲጨምር እፉኝት ከሙቀት የተነሣ ወጥታ እጁን
ነደፈችው።
፬ አረማውያንም እባብ በእጁ ተንጠልጥላ ባዩ ጊዜ፥
እርስ በርሳቸው። ይህ ሰው በእርግጥ ነፍስ ገዳይ ነው፥
ከባሕርም ሰንኳ በደኅና ቢወጣ የእግዚአብሔር ፍርድ
በሕይወት ይኖር ዘንድ አልተወውም አሉ።
፭ እርሱ ግን እባቢቱን ወደ እሳት አራገፋት አንዳችም
አልጐዳችውም፤

፮ እነርሱም። ሊያብጥ ወይም ወዲያው ሞቶ ሊወድቅ ነው ብለው ይጠባበቁት ነበር ብዙ ጊዜ ግን ሲጠባበቁ በእርሱ ላይ የሚያስገርም ነገር ምንም ባላዩ ጊዜ። ይህስ እምላክ ነው ብለው አሳባቸውን ለወጡ።
፯ በዚያም ሰፍራ አጠገብ ፑፕልዮስ የሚሉት የደሴት አለቃ መሬት ነበረ፥ እርሱም እንግድነት ተቀብሎን ሦስት ቀን በፍቅር አሳደረን።
፰ የፑፕልዮስም አባት በንዳድና በተቅማጥ ታሞ ተኝቶ ነበር፤ ጳውሎስም ወደ እርሱ ገብቶ ጸለየለት እጁንም በላዩ ጭኖ ፈወሰው።
፱ ይህም በሆነ ጊዜ የቀሩት ደግሞ በደሴቲቱ ደዌ የነበረባቸው እየመጡ ተፈወሱ፤
፲ በብዙ ክብርም ደግሞ አከበሩን፥ በተነሣንም ጊዜ በመርከብ ላይ የሚያስፈልገንን ነገር አኖሩልን።
፲፩ ከሦስት ወርም በኋላ በደሴቲቱ ከርሞ በነበረው በእስክንድርያው መርከብ ተነሣን፥ በእርሱም የዲዮስቆሮስ አላማ ነበረበት።
፲፪ ወደ ሰራኩስም በገባን ጊዜ ሦስት ቀን ተቀመጥን፤
፲፫ ከዚያም እየተዛወርን ወደ ሬጊዩም ደረስን። ከአንድ ቀን በኋላም የደቡብ ነፋስ በነፈሰ ጊዜ በሁለተኛው ቀን ወደ ፑቲዮሉስ መጣን።
፲፬ በዚያም ወንድሞችን አግኝተን በእነርሱ ዘንድ ሰባት ቀን እንድንቀመጥ ለመኑን፤ እንዲሁም ወደ ሮሜ መጣን።
፲፭ ከዚያም ወንድሞች ሰለ እኛ ሰምተው እስከ አፍዩስ ፋሩስና ሦስት ማደሪያ እስከሚባለው ሊቀበሉን ወጡ፥ ጳውሎስም ባያቸው ጊዜ እግዚአብሔርን አመሰገነ ልቡም ተጽናና።
፲፮ ወደ ሮሜም በገባን ጊዜ ጳውሎስ ከሚጠብቀው ወታደር ጋር ለብቻው ይቀመጥ ዘንድ ተፈቀደለት።
፲፯ ከሦስት ቀንም በኋላ ጳውሎስ የአይሁድን ታላላቆች ወደ እርሱ ጠራ፤ በተሰበሰቡም ጊዜ እንዲህ አላቸው። ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ሕዝቡን ወይም የአባቶችን ሥርዓት የሚቃወም አንዳች ሳላደርግ፥ ከኢየሩሳሌም እንደ ታሰርሁ በሮማውያን እጅ አሳልፈው ሰጡኝ።
፲፰ እነርሱም መርምረው ለሞት የሚገባ ምክንያት ሰላልነበረብኝ ሊፈቱኝ አሰቡ፤
፲፱ አይሁድ ግን በተቃወሙ ጊዜ፥ ወደ ቄሣር ይግባኝ እንድል ግድ ሆነብኝ እንጂ ሕዝቤን የምከሰበት ነገር ኖሮኝ አይደለም።
፳ ሰለዚህም ምክንያት እያችሁና እነግራችሁ ዘንድ ጠራኋችሁ፤ ሰለ እሰራኤል ተሰፋ ይህን ሰንሰለት ለብሻለሁና።
፳፩ እነርሱም። እኛ ከይሁዳ ሰለ አንተ ደብዳቤ አልተቀበልንም፥ ከወንድሞችም አንድ ሰንኳ መጥቶ ሰለ አንተ ክፉ ነገር አላወራልንም ወይም አልተናገረብህም።
፳፪ ነገር ግን ሰለዚህ ወገን በየሰፍራው ሁሉ እንዲቃወሙ በእኛ ዘንድ ታውቆአልና የምታሰበውን ከአንተ እንሰማ ዘንድ እንፈቅዳለን አሉት።
፳፫ ቀንም ቀጥረውለት ብዙ ሆነው ወደ መኖሪያው ወደ እርሱ መጡ፤ ሰለ እግዚአብሔር መንግሥትም እየመሰከረ ሰለ ኢየሱስም ከሙሴ ሕግና ከነቢያት ጠቅሶ እያሰረዳቸው፥ ከጥዋት ጀምሮ እስከ ማታ ድረስ ይገልጥላቸው ነበር።
፳፬ እኩሌቶቹም የተናገረውን አመኑ፥ እኩሌቶቹ ግን አላመኑም፤
፳፭ እርስ በርሳቸውም ባልተሰማሙ ጊዜ፥ ጳውሎስ አንዲት ቃል ከተናገረ በኋላ ሄዱ፤ እንዲህም አለ። መንፈስ ቅዱስ በነቢዩ በኢሳይያስ ለአባቶቻችን።
፳፮ ወደዚህ ሕዝብ ሂድና። መስማትን ትሰማላችሁና አታስተውሉም፥ ማየትንም ታያላችሁና አትመለከቱም፤
፳፯ በዓይናቸው እንዳያዩ በጆሮአቸው እንዳይሰሙ በልባቸውም እንዳያስተውሉ ተመልሰውም እንዳልፈውሳቸው፥ የዚህ ሕዝብ ልብ ደንድኖአል ጆሮአቸውም ደንቁሮአል ዓይናቸውንም ጨፍነዋል በላቸው
፳፰ ሲል መልካም ተናገረ። እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር ደኅንነት ለአሕዛብ እንደ ተላከ በእናንተ ዘንድ የታወቀ ይሁን፤ እነርሱ ደግሞ ይሰሙታል።
፳፱ ይህንም በተናገረ ጊዜ አይሁድ እርስ በርሳቸው እጅግ እየተከራከሩ ሄዱ።
፴ ጳውሎስም በተከራየው ቤት ሁለት ዓመት ሙሉ ተቀመጠ፥ ወደ እርሱም የሚመጡትን ሁሉ ይቀበል ነበር፤
፴፩ ማንም ሳይከለክለው የእግዚአብሔርን መንግሥት እየሰበከ ሰለ ጌታ ሰለ ኢየሱስ ክርስቶስ እጅግ ገልጦ ያሰተምር ነበር።

ወደ ሮሜ ሰዎች

፩-፭ በእርሱም ስለ ስሙ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሣ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀበልን፤
፮ በእነርሱም መካከል የኢየሱስ ክርስቶስ ልትሆኑ የተጠራችሁ እናንተ ደግሞ ናችሁ።
፯ በእግዚአብሔር ለተወደዳችሁና ቅዱሳን ልትሆኑ ለተጠራችሁ በሮሜ ላላችሁት ሁሉ፥ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፰ እምነታችሁ በዓለም ሁሉ ስለ ተሰማች አስቀድሜ ስለ ሁላችሁ አምላኬን በኢየሱስ ክርስቶስ አመሰግናለሁ።
፱-፲፩ ትጸኑ ዘንድ መንፈሳዊ ስጦታ እንዳካፍላችሁ ላያችሁ እናፍቃለሁና፤
፲፪ ይህንም ማለቴ በመካከላችን ባለች በእናንተና በእኔ እምነት አብረን በእናንተ እንድንጽናና ነው።
፲፫ ወንድሞች ሆይ፥ በሌሎቹ አሕዛብ ደግሞ እንደ ሆነ በእናንተም ፍሬ አገኝ ዘንድ ብዙ ጊዜ ወደ እናንተ ልመጣ እንዳሰብሁ እስከ አሁን ግን እንደ ተከለከልሁ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።
፲፬ ለግሪክ ሰዎችና ላልተማሩም፥ ለጥበበኞችና ለማያስተውሉም ዕዳ አለብኝ፤
፲፭ ስለዚህም በሚቻለኝ መጠን በሮሜ ላላችሁ ለእናንተ ደግሞ ወንጌልን ልሰብክ ተዘጋጅቼአለሁ።
፲፮ በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።
፲፯ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎ እንደ ተጻፈ የእግዚአብሔር ጽድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና።
፲፰ እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቍጣ ከሰማይ ይገለጣልና፤
፲፱ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸው፥ ስለ እግዚአብሔር ሊታወቅ የሚቻለው በእነርሱ ዘንድ ግልጥ ነውና።
፳-፳፪ ጥበበኞች ነን ሲሉ ደንቆሮ ሆኑ፥
፳፫ የማይጠፋውንም የእግዚአብሔር ክብር በሚጠፋ ሰውና በወፎች አራት እግር ባላቸውም በሚንቀሳቀሱትም መልክ መሰለው ለወጡ።
፳፬ ስለዚህ እርስ በርሳቸው ሥጋቸውን ሊያዋርዱ እግዚአብሔር በልባቸው ፍትወት ወደ ርኩሰነት አሳልፎ ሰጣቸው፤
፳፭ ይህም የእግዚአብሔርን እውነት በውሸት ስለ ለወጡ በፈጣሪም ፈንታ የተፈጠረውን ስላመለኩና ስላገለገሉ ነው፤ እርሱም ለዘላለም የተባረከ ነው፤ አሜን።
፳፮ ስለዚህ እግዚአብሔር ለሚያሰነውር ምኞት አሳልፎ ሰጣቸው፤ ሴቶቻቸውም ለባሕርያቸው የሚገባውን ሥራ ለባሕርያቸው በማይገባው ለወጡ፤
፳፯ እንዲሁም ወንዶች ደግሞ ለባሕርያቸው የሚገባውን ሴቶችን መገናኘት ትተው እርስ በርሳቸው በፍትወታቸው ተቃጠሉ፤ ወንዶችም በወንዶች ነውር እድርገው በስሕተታቸው የሚገባውን ብድራት በራሳቸው ተቀበሉ።
፳፰ እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤
፳፱ ዓመፃ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ፥
፴ ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥
፴፩ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤
፴፪ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይሰማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም።

፪

፩ ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፥ የምታመካኘው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኰንናለህና፤ አንተው ፈራጁ እነዚያን ታደርጋለህና።
፪ እንደዚህም በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እውነተኛ እንደ ሆነ እናውቃለን።
፫ አንተም እንደዚህ በሚያደርጉ የምትፈርድ ያንም የምታደርግ ሰው ሆይ፥ አንተ ከእግዚአብሔር ፍርድ የምታመልጥ ይመስልሃልን?
፬ ወይስ የእግዚአብሔር ቸርነት ወደ ንስሐ እንዲመራህ ሳታውቅ የቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለጠግነት ትንቃለህን?
፭ ነገር ግን እንደ ጥንካሬህና ንስሐ እንደማይገባ ልብህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ በሚገለጥበት በቍጣ ቀን ቍጣን በራስህ ላይ ታከማቻለህ።
፮ እርሱ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ያስረክበዋል፤
፯ በበጎ ሥራ በመጽናት ምስጋናንና ክብርን የማይጠፋንም ሕይወት ለሚፈልጉ የዘላለምን ሕይወት ይሰጣቸዋል፤
፰ ለዓመፃ በሚታዘዙ እንጂ ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቍጣና መቅሠፍት ይሆንባቸዋል።
፱ ክፉውን በሚያደርግ ሰው ነፍስ ሁሉ መከራና ጭንቀት ይሆንበታል፥ አስቀድሞ በአይሁዳዊ ደግሞም በግሪክ ሰው፤
፲ ነገር ግን በጎ ሥራ ለሚያደርጉ ሁሉ ምስጋናና ክብር ሰላምም ይሆንላቸዋል፥ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው።
፲፩ እግዚአብሔር ለሰው ፊት አያዳላምና።
፲፪ ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ ሕግ ደግሞ ይጠፋሉና፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል፤
፲፫ በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና።
፲፬ ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ከባሕርያቸው የሕግን ትእዛዝ ሲያደርጉ፥ እነዚያ ሕግ ባይኖራቸው እነኳ ለራሳቸው ሕግ ናቸውና፤

፲፭ እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።
፲፮ ይህም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እኔ በወንጌል እንዳስተማርሁ በሰው ዘንድ የተሰወረውን በሚፈርድበት ቀን ይሆናል።
፲፯ እነተ ግን አይሁዳዊ ብትባል በሕግም ብትደገፍ በእግዚአብሔርም ብትመካ፥
፲፰ ፈቃዱንም ብታውቅ ከሕግም ተምረህ የሚሻለውን ፈትነህ ብትወድ፤
፲፱-፳፩ እንግዲህ አነተ ሌላውን የምታስተምር ራስህን አታስተምርምን? አትሰረቅ ብለህ የምትሰብክ ትሰርቃለህን?
፳፪ አታመንዝር የምትል ታመነዝራለህን? ጣዖትን የምትጸየፍ ቤተ መቅደስን ትዘርፋለህን?
፳፫ በሕግ የምትመካ ሕግን በመተላለፍ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህን?
፳፬ በእናንተ ስበብ የእግዚአብሔር ስም በአሕዛብ መካከል ይሰደባልና ተብሎ እንደ ተጻፈ።
፳፭ ሕግን ብታደርግ መገረዝስ ይጠቅማል፤ ሕግን ተላላፊ ብትሆን ግን መገረዝህ አለ መገረዝ ሆኖአል።
፳፮ እንግዲህ ያልተገረዘ ሰው የሕግን ሥርዓት ቢጠብቅ አለመገረዙ እንደ መገረዝ ሆኖ አይቈጠርለትምን?
፳፯ ከፍጥረቱም ያልተገረዘ ሕግን የሚፈጽም ሰው የሕግ መጽሐፍና መገረዝ ሳለህ ሕግን በምትተላለፈው በአንተ ይፈርድብሃል።
፳፰ በግልጥ አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ አይደለምና፥ በግልጥ በሥጋ የሚደረግ መገረዝም መገረዝ አይደለምና፤
፳፱ ዳሩ ግን በሰውር አይሁዳዊ የሆነ አይሁዳዊ ነው፥ መገረዝም በመንፈስ የሚደረግ የልብ መገረዝ ነው እንጂ በመጽሐፍ አይደለም፤ የእርሱ ምሰጋና ከእግዚአብሔር ነው እንጂ ከሰው አይደለም።

፫

፩ እንግዲህ የአይሁዳዊ ብልጫው ምንድር ነው? ወይስ የመገረዝ ጥቅሙ ምንድር ነው? በሁሉ ነገር ብዙ ነው።
፪ አስቀድሞ የእግዚአብሔር ቃላት አደራ ተሰጡአቸው። ታዲያ ምንድር ነው?
፫ የማያምኑ ቢኖሩ አለማመናቸው የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያሰቀራልን?
፬ እንዲህ አይሁን፤ በቃልህ ትጸድቅ ዘንድ ወደ ፍርድ በገባህም ጊዜ ትረታ ዘንድ ተብሎ እንደ ተጻፈ፥ ሰው ሁሉ ውሸተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን።
፭ ነገር ግን ዓመፃችን የእግዚአብሔርን ጽድቅ የሚያሰረዳ ከሆነ ምን እንላለን? ቍጣን የሚያመጣ እግዚአብሔር ዓመፀኛ ነውን? እንደ ሰው ልማድ እላለሁ።
፮ እንዲህ አይሁን፤ እንዲህ ቢሆን እግዚአብሔር በዓለም እንዴት ይፈርዳል?
፯ በእኔ ውሸት ግን የእግዚአብሔር እውነት ለክብሩ ከላቀ ሰለምን በእኔ ደግሞ እንደ ኃጢአተኛ ገና ይፈርድብኛል?
፰ ሰለ ምንስ መልካም እንዲመጣ ክፉ እናደርግም? እንዲሁ ይሰድቡናልና እንዳንዱም እንዲሁ እንድንል ይናገራሉና። የእነርሱም ፍርድ ቅን ነው።
፱ እንግዲህ ምን ይሁን? ከእነርሱ እንበልጣለንን? ከቶ አይደለም፤ አይሁድም የግሪክ ሰዎችም ሁሉ ከኃጢአት በታች እንደ ሆኑ አስቀድመን ከስናቸዋልና፤
፲ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ።
፲፩ ጻድቅ የለም አንድ ስንኳ፤ አስተዋይም የለም፤ እግዚአብሔርንም የሚፈልግ የለም፤ ሁሉ ተሳስተዋል፥
፲፪ በአንድነትም የማይጠቅሙ ሆነዋል፤ ቸርነት የሚያደርግ የለም፥ አንድ ስንኳ የለም።
፲፫ ጕሮሮአቸው እንደ ተከፈተ መቃብር ነው፥ በመላሳቸውም ሸንገላዋል፤ የእባብ መርዝ ከከንፈሮቻቸው በታች አለ፤
፲፬ አፋቸውም እርግማንና መራርነት ሞልቶበታል፤
፲፭ እግሮቻቸው ደምን ለማፍሰስ ፈጣኖች ናቸው፤
፲፮ ጥፋትና ጕስቁልና በመንገዳቸው ይገኛል፥
፲፯-፲፱ አፍም ሁሉ ይዘጋ ዘንድ ዓለምም ሁሉ ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች ይሆን ዘንድ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንዲናገር እናውቃለን፤
፳ ይህም የሕግን ሥራ በመሥራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ሰለማይጸድቅ ነው፤ ኃጢአት በሕግ ይታወቃልና።
፳፩ አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥
፳፪ እርሱም፥ ለሚያምኑ ሁሉ የሆነ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የሚገኘው የእግዚአብሔር ጽድቅ ነው፤ ልዩነት የለምና፤
፳፫ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤
፳፬ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።
፳፭ እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተሰሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ሰለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥
፳፮ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።
፳፯ ትምክህት እንግዲህ ወዴት ነው? እርሱ ቀርቶአል። በየትኛው ሕግ ነው? በሥራ ሕግ ነውን? አይደለም፥ በእምነት ሕግ ነው እንጂ።
፳፰ ሰው ያለ ሕግ ሥራ በእምነት እንዲጸድቅ እንቆጥራለንና።
፳፱-፴፩ እንግዲህ ሕግን በእምነት እንሽራለንን? አይደለም፤ ሕግን እናጸናለን እንጂ።

፬

፩ እንግዲህ በሥጋ አባታችን የሆነ አብርሃም ምን አገኘ እንላለን?
፪ አብርሃም በሥራ ጸድቆ ቢሆን የሚመካበት አለውና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ አይደለም።
፫ መጽሐፍስ ምን አለ? አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት።
፬ ለሚሠራ ደመወዝ እንደ ዕዳ ነው እንጂ እንደ ጸጋ አይቈጠርለትም፤

፭ ነገር ግን ለማይሠራ፥ ኃጢአተኛውንም በሚያደድቅ ለሚያምን ሰው እምነቱ ጽድቅ ሆኖ ይቆጠርለታል።
፮ እንደዚህ ዳዊት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ሥራ ጽድቅን ስለሚቆጥርለት ስለ ሰው ብፅዕና ይናገራል እንዲህ ሲል።
፯ ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁዓን ናቸው፤
፰ ጌታ ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ብፁዕ ነው።
፱ እንግዲህ ይህ ብፅዕና ስለ መገረዝ ተነገረ? ወይስ ደግሞ ስለ አለመገረዝ? እምነቱ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት እንላለንና።
፲ እንዴት ተቆጠረለት? ተገርዞ ሳለ ነውን? ወይስ ሳይገረዝ? ተገርዞስ አይደለም፥ ሳይገረዝ ነበር እንጂ።
፲፩ ሳይገረዝም በነበረው እምነት ያገኘው የጽድቅ ማኅተም የሆነ የመገረዝን ምልክት ተቀበለ፤ ይህም እነርሱ ደግሞ ጻድቃን ሆነው ይቆጠሩ ዘንድ ሳይገረዙ ለሚያምኑ ሁሉ አባት እንዲሆን ነው፥
፲፪ ለተገረዙትም አባት እንዲሆን ነው፤ ይኸውም ለተገረዙት ብቻ አይደለም ነገር ግን አባታችን አብርሃም ሳይገረዝ የነበረውን የእምነቱን ፍለጋ ደግሞ ለሚከተሉ ነው።
፲፫ የዓለምም ወራሽ እንዲሆን ለአብርሃምና ለዘሩ የተሰጠው የተሰፋ ቃል በእምነት ጽድቅ ነው እንጂ በሕግ አይደለም።
፲፬ ከሕግ የሆኑትስ ወራሾች ከሆኑ እምነት ከንቱ ሆኖአል የተሰፋውም ቃል ተሽሮአል፤
፲፭ ሕጉ መቅሠፍትን ያደርጋልና፤ ነገር ግን ሕግ በሌለበት መተላለፍ የለም።
፲፮-፲፯ ዘርህ እንዲሁ ሊሆን ነው እንደ ተባለ፥ ተሰፋ ባልሆነው ጊዜ የብዙ አሕዛብ አባት እንዲሆን ተሰፋ ይዞ አመነ።
፲፰ የመቶ ዓመትም ሽማግሌ ስለ ሆነ እንደ ምውት የሆነውን የራሱን ሥጋና የሳራ ማኅፀን ምውት መሆኑን በእምነቱ ሳይደክም ተመለከተ፤
፲፱-፳፪ ስለዚህ ደግሞ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት።
፳፫-፳፭ ነገር ግን። ተቈጠረለት የሚለው ቃል ስለ እርሱ ብቻ የተጻፈ አይደለም፥ ስለ እኛም ነው እንጂ፤

ምዕራፍ ፭

፩ እንግዲህ በእምነት ከጸደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ፤
፪ በእርሱም ደግሞ ወደ ቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል፤ በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን።
፫-፭ በተሰጠንም በመንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ፍቅር በልባችን ስለ ፈሰሰ ተስፋ አያሳፍርም።
፮ ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቶአልና።
፯ ስለ ጻድቅ የሚሞት በጭንቅ ይገኛልና፤ ስለ ቸር ሰው ግን ለሞት እንኳ የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል።
፰ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለ እኛ ሞቶአልና እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያስረዳል።
፱ ይልቁንስ እንግዲህ አሁን በደሙ ከጸደቅን በእርሱ ከቍጣው እንድናለን።
፲ ጠላቶች ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤
፲፩ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን።
፲፪ ስለዚህ ምክንያት ኃጢአት በአንድ ሰው ወደ ዓለም ገባ በኃጢአትም ሞት፥ እንደዚሁም ሁሉ ኃጢአትን ስላደረጉ ሞት ለሰው ሁሉ ደረሰ፤
፲፫ ሕግ እስከ መጣ ድረስ ኃጢአት በዓለም ነበረና ነገር ግን ሕግ በሌለበት ጊዜ ኃጢአት አይቈጠርም፤
፲፬ ነገር ግን በአዳም መተላለፍ ምሳሌ ኃጢአትን ባልሠሩት ላይ እንኳ፥ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው ለእርሱ አምሳሉ ነውና።
፲፭ ነገር ግን ስጦታው እንደ በደሉ መጠን እንደዚያው አይደለም፤ በአንድ ሰው በደል ብዙዎቹ ሞተዋልና፥ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋና በአንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የሆነው ስጦታ ከዚያ ይልቅ ለብዙዎች በዛ።
፲፮ አንድ ሰውም ኃጢአትን በማድረጉ እንደ ሆነው መጠን እንደዚያው ስጦታው አይደለም፤ ፍርድ ከአንድ ሰው ለኵነኔ መጥቶአልና፥ ስጦታው ግን በብዙ በደል ለማጽደቅ መጣ።
፲፯ በአንዱም በደል ሞት በአንዱ በኩል ከነገሠ፥ ይልቁን የጸጋን ብዛትና የጽድቅን ስጦታ ብዛት የሚቀበሉ በአንዱ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በሕይወት ይነግሣሉ።
፲፰ እንግዲህ በአንድ በደል ምክንያት ፍርድ ለኵነኔ ወደ ሰው ሁሉ እንደ መጣ፥ እንዲሁም በአንድ ጽድቅ ምክንያት ስጦታው ሕይወትን ለማጽደቅ ወደ ሰው ሁሉ መጣ።
፲፱-፳፩ በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኃጢአተኞች እንደ ሆኑ፥ እንዲሁ ደግሞ በአንዱ መታዘዝ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ።

ምዕራፍ ፮

፩ እንግዲህ ምን እንላለን? ጸጋ እንዲበዛ በኃጢአት ጸንተን እንኑርን? አይደለም።
፪ ለኃጢአት የሞትን እኛ ወደ ፊት እንዴት አድርገን በእርሱ እንኖራለን?
፫ ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን?
፬ እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሣ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ፥ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን።
፭ ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን፤
፮ ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን፤ የሞተስ ከኃጢአቱ ጸድቋልና።
፯-፱ ክርስቶስ ከሙታን ተነሥቶ ወደ ፊት እንዳይሞት ሞትም ወደ ፊት እንዳይገዛው እናውቃለንና።

፲ መሞትን እንድ ጊዜ ፈጽሞ ለኃጢአት ሞቶአልና፤ በሕይወት መኖርን ግን ለእግዚአብሔር ይኖራል።
፲፩ እንዲሁም እናንተ ደግሞ ለኃጢአት እንደ ሞታችሁ፥ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን ሆናችሁ ለእግዚአብሔር ሕያዋን እንደ ሆናችሁ ራሳችሁን ቊጠሩ።
፲፪ እንግዲህ ለምኞቱ እንድትታዘዙ በሚሞት ሥጋችሁ ኃጢአት አይንገሥ፤
፲፫ ብልቶቻችሁንም የዓመፃ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።
፲፬ ኃጢአት አይገዛችሁምና፤ ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች አይደላችሁምና።
፲፭ እንግዲህ ምን ይሁን? ከጸጋ በታች እንጂ ከሕግ በታች ሰላይደለን ኃጢአትን እንሥራን? አይደለም።
፲፮ ለመታዘዝ ባሪያዎች እንድትሆኑ ራሳችሁን ለምታቀርቡለት፥ ለእርሱ ለምትታዘዙለት ባሪያዎች እንደ ሆናችሁ አታውቁምን? ወይም ለሞት የኃጢአት ባሪያዎች ወይም ለጽድቅ የመታዘዝ ባሪያዎች ናችሁ።
፲፯-፲፱ ሰለ ሥጋችሁ ድካም እንደ ሰው ልማድ እላለሁ። ብልቶቻችሁ ዓመፃ ሊያደርጉ ለርኩሰነትና ለዓመፃ ባሪያዎች አድርጋችሁ እንዳቀረባችሁ፥ እንደዚሁ ብልቶቻችሁ ሊቀደሱ ለጽድቅ ባሪያዎች አድርጋችሁ አሁን አቅርቡ።
፳ የኃጢአት ባሪያዎች ሳላችሁ ከጽድቅ ነፃ ነበራችሁና።
፳፩ እንግዲህ ዛሬ ከምታፍሩበት ነገር ያን ጊዜ ምን ፍሬ ነበራችሁ? የዚህ ነገር መጨረሻው ሞት ነውና።
፳፪ አሁን ግን ከኃጢአት እርነት ወጥታችሁ ለእግዚአብሔርም ተገዝታችሁ፥ ልትቀደሱ ፍሬ አላችሁ፤ መጨረሻውም የዘላለም ሕይወት ነው።
፳፫ የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነውና፤ የእግዚአብሔር የጸጋ ሰጦታ ግን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የዘላለም ሕይወት ነው።

፯

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁና ሰው ባለበት ዘመን ሁሉ ሕግ እንዲገዛው አታውቁምን?
፪ ያገባች ሴት ባልዋ በሕይወት ሲኖር ከእርሱ ጋር በሕግ ታሰራለችና፤ ባልዋ ቢሞት ግን ሰለ ባል ከሆነው ሕግ ተፈትታለች።
፫ ሰለዚህ ባልዋ በሕይወት ሳለ ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ ትባላለች፤ ባልዋ ቢሞት ግን ከሕጉ እርነት ወጥታለችና ለሌላ ወንድ ብትሆን አመንዝራ አይደለችም።
፬ እንዲሁ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በክርስቶስ ሥጋ ለሕግ ተገድላችኋል፤ ለእግዚአብሔር ፍሬ እንድናፈራ፥ እናንተ ለሌላው፥ ከሙታን ለተነሣው፥ ለእርሱ ትሆኑ ዘንድ።
፭ በሥጋ ሳለን በሕግ የሚሆን የኃጢአት መሻት ለሞት ፍሬ ሊያፈራ በብልቶቻችን ይሠራ ነበርና፤
፮ አሁን ግን ለእርሱ ለታሰርንበት ሰለ ሞትን፥ ከሕግ ተፈትተናል፥ ሰለዚህም በአዲሱ በመንፈስ ኑሮ እንገዛለን እንጂ በአሮጌው በፊደል ኑሮ አይደለም።
፯ እንግዲህ ምን እንላለን? ሕግ ኃጢአት ነውን? አይደለም፤ ነገር ግን በሕግ ባይሆን ኃጢአትን ባላወቅሁም ነበር፤ ሕጉ። አትመኝ ባላለ ምኞትን ባላወቅሁም ነበርና።
፰ ኃጢአት ግን ምክንያት አግኝቶ ምኞትን ሁሉ በትእዛዝ ሠራብኝ፤ ኃጢአት ያለ ሕግ ምውት ነውና።
፱ እኔም ዱሮ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ፤ ትእዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ኃጢአት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ፤
፲ ለሕይወትም የተሰጠችውን ትእዛዝ እርሰዋን ለሞት ሆና አገኘኋት፤
፲፩ ኃጢአት ምክንያት አግኝቶ በትእዛዝ አታሎኛልና በእርሰዋም ገድሎኛል።
፲፪ ሰለዚህ ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት።
፲፫ እንግዲህ በጎ የሆነው ነገር ለእኔ ሞት ሆነብኝን? አይደለም፥ ነገር ግን ኃጢአት ሆነ፤ ኃጢአትም በትእዛዝ ምክንያት ያለ ልክ ኃጢአተኛ ይሆን ዘንድ፥ ኃጢአትም እንዲሆን ይገለጥ ዘንድ በጎ በሆነው ነገር ለእኔ ሞትን ይሠራ ነበር።
፲፬ ሕግ መንፈሳዊ እንደ ሆነ እናውቃለንና፤ እኔ ግን ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ።
፲፭ የማደርገውን አላውቅምና፤ የምጠላውን ያን እደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን እርሱን አላደርገውም።
፲፮ የማልወደውን ግን የማደርግ ከሆንሁ ሕግ መልካም እንደ ሆነ እመሰክራለሁ።
፲፯ እንደዚህ ከሆነ ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚያድር ኃጢአት ነው እንጂ።
፲፰ በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁና፤ ፈቃድ አለኝና፥ መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም።
፲፱ የማልወደውን ክፉን ነገር እደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።
፳ የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኃጢአት ነው እንጂ።
፳፩ እንግዲያስ መልካሙን አደርግ ዘንድ ሰወድ በእኔ ክፉ እንዲያድርብኝ ሕግን አገኛለሁ።
፳፪ በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥
፳፫ ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ።
፳፬ እኔ ምንኛ ጎስቋላ ሰው ነኝ! ለዚህ ሞት ከተሰጠ ሰውነት ማን ያድነኛል?
፳፭ በኢየሱስ ክርስቶስ በጌታችን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። እንግዲያስ እኔ በአእምሮዬ ለእግዚአብሔር ሕግ፥ በሥጋዬ ግን ለኃጢአት ሕግ አገዛለሁ።

፰

፩ እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም።

፪ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ
ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና።
፫-፬ እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ የሥጋን ነገር ያሰባሉና፥
እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን የመንፈስን ነገር
ያሰባሉ።
፮ ሰለ ሥጋ ማሰብ ሞት ነውና፥ ሰለ መንፈስ ማሰብ
ግን ሕይወትና ሰላም ነው።
፯ ሰለ ሥጋ ማሰብ በእግዚአብሔር ዘንድ ጥል
ነውና፤ ለእግዚአብሔር ሕግ አይገዛምና፥ መገዛትም
ተሰኖታል፤
፰ በሥጋ ያሉትም እግዚአብሔርን ደሰ ሊያሰኙት
አይችሉም።
፱ እናንተ ግን የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ
ዘንድ ቢኖር፥ በመንፈስ እንጂ በሥጋ አይደላችሁም።
የክርስቶስ መንፈስ የሌለው ከሆነ ግን ይኸው የእርሱ
ወገን አይደለም።
፲ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ ቢሆን ሰውነታችሁ
በኃጢአት ምክንያት የሞተ ነው፥ መንፈሳችሁ ግን
በጽድቅ ምክንያት ሕያው ነው።
፲፩ ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው
የእርሱ መንፈስ በእናንተ ዘንድ ቢኖር፥ ክርስቶስ
ኢየሱስን ከሙታን ያስነሣው እርሱ በእናንተ በሚኖረው
በመንፈሱ፥ ለሚሞተው ሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን
ይሰጠዋል።
፲፪ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕዳ አለብን፥ እንደ
ሥጋ ፈቃድ ግን እንኖር ዘንድ ለሥጋ አይደለም።
፲፫ እንደ ሥጋ ፈቃድ ብትኖሩ ትሞቱ ዘንድ አላችሁና፤
በመንፈስ ግን የሰውነትን ሥራ ብትገድሉ በሕይወት
ትኖራላችሁ።
፲፬ በእግዚአብሔር መንፈስ የሚመሩ ሁሉ እነዚህ
የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።
፲፭ አባ አባት ብለን የምንጮኽበትን የልጅነት
መንፈስ ተቀበላችሁ እንጂ እንደገና ለፍርሃት የባርነትን
መንፈስ አልተቀበላችሁምና።
፲፮ የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ
ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ይመሰክራል።
፲፯ ልጆች ከሆንን ወራሾች ደግሞ ነን፤ ማለት
የእግዚአብሔር ወራሾች ነን፥ አብረንም ደግሞ
እንድንከበር አብረን መከራ ብንቀበል ከክርስቶስ ጋር
አብረን ወራሾች ነን።
፲፰ ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር
ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ
እሰባለሁ።
፲፱ የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች
መገለጥ ይጠባበቃልና።
፳ ፍጥረት ለኪንቱነት ተገዝቶአልና፥ በተሰፋ
ሰላሰገዛው ነው እንጂ በፈቃዱ አይደለም፤
፳፩ ተሰፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት
ነፃነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር
ነፃነት እንዲደርስ ነው።
፳፪ ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ
በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና።
፳፫ እርሱም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን የመንፈስ
በኩራት ያለን ራሳችን ደግሞ የሰውነታችን ቤዛ
የሆነውን ልጅነት እየተጠባበቅን ራሳችን በውሰጣችን
እንቃትታለን።
፳፬ በተሰፋ ድነናልና፤ ነገር ግን ተሰፋ የሚደረግበቱ
ነገር ቢታይ ተሰፋ አይደለም፤ የሚያየውንማ ማን ተሰፋ
ያደርገዋል?
፳፭ የማናየውን ግን ተሰፋ ብናደርገው በትዕግሥት
እንጠባበቃለን።
፳፮ እንዲሁም ደግሞ መንፈስ ድካማችንን ያግዛል፤
እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን እናውቅምና፥ ነገር
ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል፤
፳፯ ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ አሳብ ምን
እንደ ሆነ ያውቃል፥ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሰለ
ቅዱሳን ይማልዳልና።
፳፰ እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም
ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።
፳፱ ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር
ይሆን ዘንድ፥ አሰቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ
እንዲመስሉ አሰቀድሞ ደግሞ ወሰኖአልና፤
፴ አሰቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ
ጠራቸው፤ የጠራቸውንም እነዚህን ደግሞ
አጸደቃቸው፤ ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ
አከበራቸው።
፴፩ እንግዲህ ሰለዚህ ነገር ምን እንላለን?
እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?
፴፪ ለገዛ ልጁ ያልራራለት ነገር ግን ሰለ ሁላችን
አሳልፎ የሰጠው ያው ከእርሱ ጋር ደግሞ ሁሉን ነገር
እንዲያው እንዴት አይሰጠንም?
፴፫ እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከሳቸዋል?
የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው፥ የሚኰንንስ ማን ነው?
፴፬ የሞተው፥ ይልቁንም ከሙታን የተነሣው፥
በእግዚአብሔር ቀኝ ያለው፥ ደግሞ ሰለ እኛ
የሚማልደው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው።
፴፭ ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየናል? መከራ፥ ወይስ
ጭንቀት፥ ወይስ ሰደት፥ ወይስ ራብ፥ ወይስ ራቁትነት፥
ወይስ ፍርሃት፥ ወይስ ሰይፍ ነውን?
፴፮ ሰለ እንተ ቀኑን ሁሉ እንገደላለን፥ እንደሚታረዱ
በጎች ተቆጠርን ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።
፴፯ በዚህ ሁሉ ግን በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች
እንበልጣለን።
፴፰ ሞት ቢሆን፥ ሕይወትም ቢሆን፥ መላእክትም
ቢሆኑ፥ ግዛትም ቢሆን፥ ያለውም ቢሆን፥
የሚመጣውም ቢሆን፥ ኃይላትም ቢሆኑ፥
፴፱ ከፍታም ቢሆን፥ ዝቅታም ቢሆን፥ ልዩ
ፍጥረትም ቢሆን በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን
ካለ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን እንዳይችል
ተረድቼአለሁ።

፱

፩-፫ በሥጋ ዘመዶቼ ሰለ ሆኑ ሰለ ወንድሞቼ
ከክርስቶስ ተለይቼ እኔ ራሴ የተረገምሁ እንድሆን
እጸልይ ነበርና።
፬ እነርሱ እስራኤላውያን ናቸውና፥ ልጅነትና ክብር
ኪዳንም የሕግም መስጠት የመቅደስም ሥርዓት
የተሰፋውም ቃላት ለእነርሱ ናቸውና፤
፭ አባቶችም ለእነርሱ ናቸውና፤ ከእነርሱም ክርስቶስ
በሥጋ መጣ፥ እርሱም ከሁሉ በላይ ሆኖ ለዘላለም
የተባረከ አምላክ ነው፤ አሜን።
፮ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል የተሻረ አይደለም።
እነዚህ ከእስራኤል የሚወለዱ ሁሉ እስራኤል

አይደሉምና፤ የአብርሃምም ዘር ሰለሆኑ ሁላቸው
ልጆች አይደሉም፥
፯ ነገር ግን። በይሰሐቅ ዘር ይጠራልሃል ተባለ።
፰ ይህም፥ የተሰፋ ቃል ልጆች ዘር ሆነው ይቆጠራሉ
እንጂ እነዚህ የሥጋ ልጆች የሆኑ የእግዚአብሔር
ልጆች አይደሉም ማለት ነው።
፱ ይህ። በዚህ ጊዜ እመጣለሁ ለሳራም ልጅ
ይሆንላታል የሚል የተሰፋ ቃል ነውና።
፲ ይህ ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ርብቃ ደግሞ
ከእንዱ ከአባታችን ከይሰሐቅ በፀነሰች ጊዜ፥
፲፩ ልጆቹ ገና ሳይወለዱ፥ በጎ ወይም ክፉ ምንም
ሳያደርጉ፥ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ
የሚሆን የእግዚአብሔር እሳብ ይጸና ዘንድ፥
፲፪ ለእርሰዋ። ታላቁ ለታናሹ ይገዛል ተባለላት።
፲፫ ያዕቆብን ወደድሁ ኤሳውን ግን ጠላሁ ተብሎ
እንደ ተጻፈ ነው።
፲፬ እንግዲህ ምን እንላለን? በእግዚአብሔር ዘንድ
ዓመፃ አለ ወይ? አይደለም።
፲፭ ለሙሴ። የምምረውን ሁሉ እምረዋለሁ
ለምራራለትም ሁሉ እራራለታለሁ ይላልና።
፲፮ እንግዲህ ምሕረት ለወደደ ወይም ለሮጠ
አይደለም፥ ከሚምር ከእግዚአብሔር ነው እንጂ።
፲፯ መጽሐፍ ፈርዖንን። ኃይሌን በአንተ አሳይ ዘንድ
ሰሜም በምድር ሁሉ ይነገር ዘንድ ለዚህ አስነሣሁህ
ይላልና።
፲፰ እንግዲህ የሚወደውን ይምረዋል፥ የሚወደውንም
እልከኛ ያደርገዋል።
፲፱ እንግዲህ ሰለ ምን እስከ አሁን ድረስ ይነቅፋል?
ፈቃዱንስ የሚቃወም ማን ነው? ትለኛ ይሆናል።
፳ ነገር ግን፥ አንተ ሰው ሆይ፥ ለእግዚአብሔር
የምትመልስ ማን ነህ? ሥራ ሠሪውን። ሰለ ምን
እንዲህ አድርገህ ሠራኸኝ ይለዋልን?
፳፩ ወይም ሸክላ ሠሪ ከእንዱ ጭቃ ክፍል እንዱን
ዕቃ ለክብር እንዱንም ለውርደት ሊሠራ በጭቃ ላይ
ሥልጣን የለውምን?
፳፪-፳፬ የምሕረቱ ዕቃዎችም ከእይሁድ ብቻ
አይደሉም፥ ነገር ግን ከአሕዛብ ደግሞ የጠራን እኛ
ነን።
፳፭ እንዲሁ ደግሞ በሆሴዕ። ሕዝቤ ያልሆነውን
ሕዝቤ ብዬ፥ ያልተወደደችውንም የተወደደችው ብዬ
እጠራለሁ፤
፳፮ እናንተ ሕዝቤ አይደላችሁም በተባለላቸውም
ሰፍራ በዚያ የሕያው እግዚአብሔር ልጆች ተብለው
ይጠራሉ ይላል።
፳፯-፳፱ ኢሳይያስም እንደዚሁ። ጌታ ፀባኦት ዘር
ባላሰቀረልን እንደ ሰዶም በሆንን ገሞራንም በመሰልን
ነበር ብሎ አስቀድሞ ተናገረ።
፴ እንግዲህ ምን እንላለን? ጽድቅን ያልተከተሉት
አሕዛብ ጽድቅን አገኙ፥ እርሱ ግን ከእምነት የሆነ
ጽድቅ ነው፤
፴፩-፴፫ እስራኤል ግን የጽድቅን ሕግ እየተከተሉ ወደ
ሕግ አልደረሱም።

፲

፩ ወንድሞች ሆይ፥ የልቤ በጎ ፈቃድና ሰለ እስራኤል
ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው።
፪ በእውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ
እመሰክርላቸዋለሁና።
፫ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም
ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ፥ ለእግዚአብሔር ጽድቅ
አልተገዙም።
፬ የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ
ፍጻሜ ነውና።
፭ ሙሴ ከሕግ የሆነውን ጽድቅ የሚያደርገው ሰው
በእርሱ በሕይወት እንዲኖር ጽፎአልና።
፮ ከእምነት የሆነ ጽድቅ ግን እንዲህ ይላል።
በልብህ። ማን ወደ ሰማይ ይወጣል? አትበል፤ ይህ
ክርስቶስን ለማውረድ ነው፤
፯ ወይም። በልብህ። ወደ ጥልቁ ማን ይወርዳል?
አትበል፤ ይህ ክርስቶስን ከሙታን ለማውጣት ነው።
፰ ነገር ግን ምን ይላል? በአፍህ በልብህም ሆኖ
ቃሉ ቀርቦልሃል፤ ይህም የምንሰብከው የእምነት ቃል
ነው።
፱ ኢየሱስ ጌታ እንደ ሆነ በአፍህ ብትመሰክር
እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ
ብታምን ትድናለህና፤
፲ ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መሰክሮ
ይድናልና።
፲፩ መጽሐፍ። በእርሱ የሚያምን ሁሉ አያፍርም
ይላልና።
፲፪ በአይሁዳዊና በግሪክ ሰው መካከል ልዩነት
የለምና፤ እንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና፥ ለሚጠሩትም
ሁሉ ባለ ጠጋ ነው፤
፲፫ የጌታን ሰም የሚጠራ ሁሉ ይድናልና።
፲፬ እንግዲህ ያላመኑበትን እንዴት አድርገው
ይጠሩታል? ባልሰሙትስ እንዴት ያምናሉ? ያለ
ሰባኪስ እንዴት ይሰማሉ?
፲፭ መልካሙን የምሥራች የሚያወሩ እግሮቻቸው
እንዴት ያማሩ ናቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ ካልተላኩ
እንዴት ይሰብካሉ?
፲፮ ነገር ግን ሁሉ ለምሥራቹ ቃል አልታዘዙም።
ኢሳይያስ። ጌታ ሆይ፥ ምስክርነታችንን ማን አመነ?
ብሎአልና።
፲፯ እንግዲያስ እምነት ከመሰማት ነው መሰማትም
በእግዚአብሔር ቃል ነው።
፲፰ ዳሩ ግን። ባይሰሙ ነው ወይ? እላለሁ።
በእውነት። ድምፃቸው በምድር ሁሉ ላይ ቃላቸውም
እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።
፲፱ ነገር ግን። እስራኤል ባያውቁ ነው
ወይ? እላለሁ። ሙሴ እስቀድሞ። እኔ ሕዝብ
በማይሆነው አስቀናችኋለሁ በማያስተውልም ሕዝብ
አስቆጣችኋለሁ
፳ ብሎአል። ኢሳይያስም ደፍሮ። ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፥
ላልጠየቁኝም ተገለጥሁ አለ።
፳፩ ሰለ እስራኤል ግን። ቀኑን ሁሉ ወደማይታዘዝና
ወደሚቃወም ሕዝብ እጆቼን ዘረጋሁ ይላል።

፲፩

፩ እንግዲህ። እግዚአብሔር ሕዝቡን ጣላቸውን?
እላለሁ። አይደለም እኔ ደግሞ እስራኤላዊና
ከአብርሃም ዘር ከብንያምም ወገን ነኝና።

፪ እግዚአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን ሕዝብ
አልጣላቸውም። መጽሐፍ ስለ ኤልያስ በተጻፈው
የሚለውን፥ በእግዚአብሔር ፊት እስራኤልን እንዴት
እንደሚከስ፥ አታውቁምን?
፫ ጌታ ሆይ፥ ነቢያትህን ገደሉ መሠዊያዎችህንም
አፈረሱ እኔም ብቻዬን ቀረሁ ነፍሴንም ይሹአታል።
፬ ነገር ግን አምላካዊ መልስ ምን አለው? ለበአል
ያልሰገዱትን ሰባት ሺህ ሰዎች ለእኔ አስቀርቼአለሁ።
፭ እንደዚሁም በአሁን ዘመን ደግሞ በጸጋ የተመረጡ
ቅሬታዎች አሉ።
፮ በጸጋ ከሆነ ግን ከሥራ መሆኑ ቀርቶአል፤ ጸጋ
ያለዚያ ጸጋ መሆኑ ቀርቶአል።
፯ እንግዲህ ምንድር ነው? እስራኤል የሚፈልጉትን
አላገኙትም፤ የተመረጡት ግን አገኙት፤
፰ ሌሎቹም ደነዘዙ፤ እንዲሁም። ዓይኖቻቸው
እንዳያዩ ጆሮቻቸውም እንዳይሰሙ እግዚአብሔር
የእንቅልፍ መንፈስን እስከ ዛሬ ድረስ ሰጣቸው ተብሎ
ተጽፎአል። ዳዊትም።
፱ ማዕዳቸው ወጥመድና እሽክላ ማሰናከያም ፍዳም
ይሁንባቸው፤
፲ ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፥ ጀርባቸውንም
ዘወትር አጕብጥ ብሎአል።
፲፩ እንግዲህ። የተሰናከሉ እስኪወድቁ ድረስ ነውን?
እላለሁ። አይደለም፤ ነገር ግን እነርሱን ያሰቀናቸው
ዘንድ በእነርሱ በደል መዳን ለአሕዛብ ሆነ።
፲፪ ዳሩ ግን በደላቸው ለዓለም ባለ ጠግነት
መሸነፋቸውም ለአሕዛብ ባለ ጠግነት ከሆነ፥
ይልቁንስ መሙላታቸው እንዴት ይሆን?
፲፫-፲፭ የእነርሱ መጣል ለዓለም መታረቅ ከሆነ
ከሙታን ከሚመጣ ሕይወት በቀር መመለሳቸው ምን
ይሆን?
፲፮ በኩራቱም ቅዱስ ከሆነ ብሆው ደግሞ ቅዱስ
ነው፤ ሥሩም ቅዱስ ከሆነ ቅርንጫፎቹ ደግሞ ቅዱሳን
ናቸው።
፲፯ ነገር ግን ከቅርንጫፎች አንዳንዱ ቢሰበሩ አንተም
የበረሀ ወይራ የሆንህ በመካከላቸው ገብተህ ከእነርሱ
ጋር የወይራ ዘይት ከሚወጣው ሥር ተካፋይ ከሆንህ፥
በቅርንጫፎች ላይ አትመካ፤
፲፰ ብትመካባቸው ግን ሥሩ አንተን ይሸከምሃል
እንጂ ሥሩን የምትሸከም አንተ አይደለህም።
፲፱ እንግዲህ። እኔ እንድገባ ቅርንጫፎች ተሰበሩ ትል
ይሆናል።
፳ መልካም፤ እነርሱ ከአለማመን የተነሣ ተሰበሩ
አንተም ከእምነት የተነሣ ቆመሃል። ፍራ እንጂ
የትዕቢትን ነገር አታስብ።
፳፩ እግዚአብሔር እንደ ተፈጠሩት ለነበሩት
ቅርንጫፎች የራራላቸው ካልሆነ ለአንተ ደግሞ
አይራራልህምና።
፳፪ እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና
ተመልከት፤ ጭከናው በወደቁት ላይ ነው፥ በቸርነቱ
ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ
ላይ ነው፤ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ።
፳፫ እነዚያም ደግሞ በአለማመናቸው ጸንተው
ባይኖሩ በዛፉ ውስጥ ይገባሉ፤ እግዚአብሔር መልሶ
ሊያገባቸው ይችላልና።
፳፬ አንተ በፍጥረቱ የበረሀ ከነበረ ወይራ ተቆርጠህ
እንደ ፍጥረትህ ሳትሆን በመልካም ወይራ ከገባህ፥
ይልቁንስ እነዚያ በፍጥረታቸው ያሉት ቅርንጫፎች
በራሳቸው ወይራ እንዴት አይገቡም?
፳፭ ወንድሞች ሆይ፥ ልባሞች የሆናችሁ
እንዳይመስላችሁ ይህን ምሥጢር ታውቁ ዘንድ
እወዳለሁ፤ የአሕዛብ ሙላት እስኪገባ ድረስ ድንዛዜ
በእስራኤል በአንዳንድ በኩል ሆነባቸው፤
፳፮ እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ እንዲህ
ተብሎ እንደ ተጻፈ። መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል
ከያዕቆብም ኃጢአተኛነትን ያስወግዳል።
፳፯ ኃጢአታቸውንም ሰወሰድላቸው ከእነርሱ ጋር
የምገባው ኪዳን ይህ ነው።
፳፰ በወንጌልስ በኩል ስለ እናንተ ጠላቶች ናቸው፥
በምርጫ በኩል ግን ስለ አባቶች ተወዳጆች ናቸው፤
፳፱ እግዚአብሔር በጸጋው ሰጦታና በመጥራቱ
አይጸጸትምና።
፴ እናንተም ቀድሞ ለእግዚአብሔር እንዳልታዘዛችሁ፥
አሁን ግን ከአለመታዘዛቸው የተነሣ ምሕረት
እንዲገኛችሁ፥
፴፩ እንዲሁ በተማራችሁበት ምሕረት እነርሱ
ደግሞ ምሕረትን ያገኙ ዘንድ እነዚህ ደግሞ አሁን
አልታዘዙም።
፴፪ እግዚአብሔር ሁሉን ይምር ዘንድ ሁሉን
በአለመታዘዝ ዘግቶታልና።
፴፫ የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም
እንዴት ጥልቅ ነው፤ ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥
ለመንገዱም ፍለጋ የለውም።
፴፬ የጌታን ልብ ያወቀው ማን ነው?
፴፭ ወይስ አማካሪው ማን ነበር? ወይስ ብድራቱን
ይመልስ ዘንድ ለእርሱ አስቀድሞ የሰጠው ማን ነው?
፴፮ ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ
ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

፲፪

፩ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሰውነታችሁን
እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም
መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር
ርኅራኄ እለምናችኋለሁ፥ እርሱም ለአእምሮ የሚመች
አገልግሎታችሁ ነው።
፪ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ
ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ
ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም
አትምሰሉ።
፫ እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ የእምነትን መጠን
እንዳካፈለው፥ እንደ ባለ አእምሮ እንዲያስብ እንጂ
ማሰብ ከሚገባው አልፎ በትዕቢት እንዳያስብ
በመካከላችሁ ላለው ለእያንዳንዱ በተሰጠኝ ጸጋ
እናገራለሁ።
፬ በአንድ አካል ብዙ ብልቶች እንዳሉን፥ የብልቶቹም
ሁሉ ሥራ እንድ እንዳይደለ፥
፭ እንዲሁ ብዙዎች ሰንሆን በክርስቶስ አንድ አካል
ነን፥ እርስ በርሳችንም እያንዳንዳችን የሌላው ብልቶች
ነን።
፮ እንደ ተሰጠንም ጸጋ ልዩ ልዩ ሰጦታ አለን፤ ትንቢት
ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር፤
፯ አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤
የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤

፳፮ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ፤ የሚሰጥ በልግስና ይሰጥ፤ የሚገዛ በትጋት ይግዛ፤ የሚምር በደስታ ይማር።
፱ ፍቅራችሁ ያለ ግብዝነት ይሁን። ክፉውን ነገር ተጸየፉት፤ ከበጎ ነገር ጋር ተባበሩ፤
፲ በወንድማማች መዋደድ እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፤ እርስ በርሳችሁ ተከባበሩ፤
፲፩ ለሥራ ከመትጋት አትለግሙ፤ በመንፈስ የምትቃጠሉ ሁኑ፤ ለጌታ ተገዙ፤
፲፪ በተስፋ ደስ ይበላችሁ፤ በመከራ ታገሡ፤ በጸሎት ጽኑ፤
፲፫ ቅዱሳንን በሚያስፈልጋቸው እርዱ፤ እንግዶችን ለመቀበል ትጉ።
፲፬ የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፥ መርቁ እንጂ አትርገሙ።
፲፭ ደስ ከሚላቸው ጋር ደስ ይበላችሁ፥ ከሚያለቅሱም ጋር አልቅሱ።
፲፮ እርስ በርሳችሁ በአንድ አሳብ ተሰማሙ፤ የትዕቢትን ነገር እታስቡ፥ ነገር ግን የትሕትናን ነገር ለመሥራት ትጉ። ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ።
፲፯ ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ፤ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ።
፲፰ ቢቻላችሁስ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ።
፲፱ ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና።
፳ ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው፤ ቢጠማ አጠጣው፤ ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና።
፳፩ ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ።

፲፫

፩ ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።
፪ ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ።
፫ ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤
፬ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና።
፭ ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው።
፮ ስለዚህ ደግሞ ትገብራላችሁና፤ በዚህ ነገር የሚተጉ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ናቸውና።
፯ ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤ ግብር ለሚገባው ግብርን፥ ቀረጥ ለሚገባው ቀረጥን፥ መፈራት ለሚገባው መፈራትን፥ ክብር ለሚገባው ክብርን ስጡ።
፰ እርስ በርሳችሁ ከመዋደድ በቀር ለማንም ዕዳ አይኑርባችሁ፥ ሌላውን የሚወድ ሕግን ፈጽሞታልና።
፱ አታመንዝር፥ አትግደል፥ አትስረቅ፥ በውሸት አትመስክር፥ አትመኝ የሚለው ከሌላይቱ ትእዛዝ ሁሉ ጋር በዚህ። ባልንጀራህን እንደ ነፍስህ ውደድ በሚለው ቃል ተጠቅልሎአል።
፲ ፍቅር ለባልንጀራው ክፉ አያደርግም፤ ስለዚህ ፍቅር የሕግ ፍጻሜ ነው።
፲፩ ከእንቅልፍ የምትነሡበት ሰዓት አሁን እንደ ደረሰ ዘመኑን እወቁ፤ ካመንንበት ጊዜ ይልቅ መዳናችን ዛሬ ወደ እኛ ቀርቦአልና።
፲፪ ሌሊቱ አልፎአል፥ ቀኑም ቀርቦአል። እንግዲህ የጨለማውን ሥራ አውጥተን የብርሃንን ጋሻ ጦር እንልበስ።
፲፫ በቀን እንደምንሆን በአገባብ እንመላለስ፤ በዘፈንና በሰካር አይሁን፥ በዝሙትና በመዳራት አይሁን፥ በክርክርና በቅናት አይሁን፤
፲፬ ነገር ግን ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን ልበሱት፤ ምኞቱንም እንዲፈጽም ለሥጋ አታስቡ።

፲፬

፩ በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት፥ በአሳቡም ላይ አትፍረዱ።
፪ ሁሉን ይበላ ዘንድ እንደ ተፈቀደለት የሚያምን አለ፥ ደካማው ግን አትክልት ይበላል።
፫ የሚበላ የማይበላውን አይናቀው የማይበላውም በሚበላው አይፍረድ፥ እግዚአብሔር ተቀብሎታልና።
፬ አንተ በሌላው ሎሌ የምትፈርድ ማን ነህ? እርሱ ቢቆም ወይም ቢወድቅ ለገዛ ጌታው ነው፤ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊያቆመው ይችላልና ይቆማል።
፭ ይህ ሰው እንድ ቀን ከሌላ ቀን እንዲሻል ያስባል፥ ያ ግን ቀን ሁሉ እንድ እንደ ሆነ ያስባል፤ እያንዳንዱ በገዛ አእምሮው አጥብቆ ይረዳ።
፮ ቀንን የሚያከብር ለጌታ ብሎ ያከብራል፤ የሚበላም እግዚአብሔርን ያመሰግናልና ለጌታ ብሎ ይበላል፤ የማይበላም ለጌታ ብሎ አይበላም እግዚአብሔርንም ያመሰግናል።
፯ ከእኛ አንድ ሰንኳ ለራሱ የሚኖር የለምና፥ ለራሱም የሚሞት የለም፤
፰ በሕይወት ሆነን ብንኖር ለጌታ እንኖራለንና፥ ብንሞትም ለጌታ እንሞታለን። እንግዲህ በሕይወት ሆነን ብንኖር ወይም ብንሞት የጌታ ነን።
፱ ስለዚህ ነገር ሙታንንም ሕያዋንንም ይገዛ ዘንድ ክርስቶስ ሞቶአልና ሕያውም ሆኖአልና።
፲ አንተም በወንድምህ ላይ ስለ ምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለ ምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና።
፲፩ እኔ ሕያው ነኝ፥ ይላል ጌታ፥ ጉልበት ሁሉ ለእኔ ይንበረከካል መላስም ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል ተብሎ ተጽፎአልና።
፲፪ እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።
፲፫ እንግዲህ ከዛሬ ጀምሮ እርስ በርሳችን እንፈራረድ፤ ይልቁን ግን ለወንድም እንቅፋትን ወይም ማሰናከያን ማንም እንዳያኖርበት ይህን ቍረጡ።
፲፬ በራሱ ርኩስ የሆነ ነገር እንደ ሌለ በጌታ በኢየሱስ ሆኜ አውቄአለሁ ተረድቼአለሁም፤ ነገር ግን

ምንም ርኩሰ እንዲሆን ለሚቆጥር ለእርሱ ርኩሰ ነው።

፲፭ ወንድምህንም በመብል ምክንያት የምታሳዝን ከሆንህ እንግዲህ በፍቅር አልተመላለስህም። ክርስቶስ ስለ እርሱ የሞተለትን እርሱን በመብልህ አታጥፋው።

፲፮ እንግዲህ ለእናንተ ያለው መልካም ነገር አይሰደብ፤

፲፯ የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ሰላም በመንፈስ ቅዱስም የሆነ ደስታ ናት እንጂ መብልና መጠጥ አይደለችምና።

፲፰ እንደዚህ አድርጎ ለክርስቶስ የሚገዛ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛልና፥ በሰውም ዘንድ የተመሰገነ ነው።

፲፱ እንግዲያስ ሰላም የሚቆምበትን እርስ በርሳችንም የምንታነጽበትን እንከተል።

፳ በመብል ምክንያት የእግዚአብሔርን ሥራ አታፍርስ። ሁሉ ንጹሕ ነው፥ በመጠራጠር የተበላ እንደ ሆነ ግን ለዚያ ሰው ክፋ ነው።

፳፩ ሥጋን አለመብላት ወይንንም አለመጠጣት ወንድምህም የሚሰናከልበትን አለማድረግ መልካም ነው።

፳፪ ለእንተ ያለህ እምነት በእግዚአብሔር ፊት ለራስህ ይሁንልህ። ፈትኖ መልካም እንዲሆን በሚቈጥረው ነገር በራሱ ላይ የማይፈርድ ብፁዕ ነው።

፳፫ የሚጠራጠረው ግን ቢበላ በእምነት ሰላልሆነ ተኮንኖአል፤ በእምነትም ያልሆነ ሁሉ ኃጢአት ነው።

፲፭

፩ እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ራሳችንንም ደስ እንዳናሰኝ ይገባናል።

፪ እያንዳንዳችን እንድናንጸው እርሱን ለመጥቀም ባልንጀራችንን ደስ እናሰኝ።

፫ ክርስቶስ ራሱን ደስ አላሰኘምና፤ ነገር ግን። እነተን የነቀፉበት ነቀፋ ወደቀብኝ ተብሎ እንደ ተጻፈ ሆነበት።

፬ በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና።

፭-፮ ስለዚህ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ክብር እንደ ተቀበላችሁ እንዲሁ እርስ በርሳችሁ ተቀባበሉ።

፯-፯ ደግሞም። አሕዛብ ሆይ፥ ከሕዝቡ ጋር ደስ ይበላችሁ ይላል።

፲፩ ደግሞም። እናንተ አሕዛብ ሁላችሁ፥ ጌታን አመስግኑ ሕዝቦቹም ሁሉ ይወድሱት ይላል።

፲፪ ደግሞም ኢሳይያስ። የእሴይ ሥር አሕዛብንም ለገዛ የሚነሣው ይሆናል፤ በእርሱ አሕዛብ ተስፋ ያደርጋሉ ይላል።

፲፫ የተስፋ አምላክም በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተስፋ እንድትበዙ በማመናችሁ ደስታንና ሰላምን ሁሉ ይሙላባችሁ።

፲፬ እኔም ራሴ ደግሞ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ በበጎነት ራሳችሁ እንደ ተሞላችሁ፥ እውቀትም ሁሉ እንደ ሞላባችሁ፥ እርስ በርሳችሁም ደግሞ ልትገሠጹ እንዲቻላችሁ ስለ እናንተ ተረድቼአለሁ።

፲፭-፲፮ እንግዲህ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚሆን ነገር በክርስቶስ ኢየሱስ ትምክህት አለኝ።

፲፯-፳ እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሠራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ሰፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ፤

፳፩ ነገር ግን። ስለ እርሱ ያልተወራላቸው ያያሉ፥ ያልሰሙም ያስተውላሉ ተብሎ እንደ ተጻፈ ነው።

፳፪ ስለዚህ ደግሞ ወደ እናንተ እንዳልመጣ ብዙ ጊዜ ተከለከልሁ።

፳፫ አሁን ግን በዚህ አገር ሰፍራ ወደ ፊት ስለሌለኝ፥ ከብዙ ዓመትም ጀምሬ ወደ እናንተ ልመጣ ናፍቆት ስላለኝ፥

፳፬ ወደ እስጳንያ በሄድሁ ጊዜ ሳልፍ እናንተን እንዳይ፥ እስቀድሜም ጥቂት ብጠግባችሁ ወደዚያ በጉዞዬ እንድትረዱኝ ተስፋ እደርጋለሁ።

፳፭ አሁን ግን ቅዱሳንን ለማገልገል ወደ ኢየሩሳሌም እሄዳለሁ።

፳፮ መቄዶንያና አካይያ በኢየሩሳሌም ቅዱሳን መካከል ያሉትን ድሆች ይረዱ ዘንድ ወደዋልና።

፳፯ ወደዋልና፥ የእነርሱም ባለ ዕዳዎች ናቸው፤ አሕዛብ በእነርሱ መንፈሳዊ ነገርን ተካፋዮች ከሆኑ በሥጋዊ ነገር ደግሞ ያገለግሉአቸው ዘንድ ይገባቸዋልና።

፳፰ እንግዲህ ይህን ፈጽሜ ይህን ፍሬ ካተምሁላቸው በኋላ በእናንተ በኩል አልፌ ወደ እስጳንያ እሄዳለሁ፤

፳፱ ወደ እናንተም ስመጣ በክርስቶስ በረከት ሙላት እንድመጣ አውቃለሁ።

፴ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እኔ ወደ እግዚአብሔር እየጸለያችሁ ከእኔ ጋር ትጋደሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስና በመንፈስ ፍቅር እለምናችኋለሁ፤

፴፩-፴፫ የሰላምም አምላክ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

፲፮

፩ በክንክራኦስ ባለች ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የምትሆን እኅታችንን ፌቤንን አደራ ብያችኋለሁ፤

፪ ለቅዱሳን እንደሚገባ በጌታ ተቀበሉአት፥ እርስዋ ለብዙዎች ለእኔም ለራሴ ደጋፊ ነበረችና፥ ከእናንተም በምትፈልገው በማናቸውም ነገር እርዱአት።

፫ በክርስቶስ ኢየሱስ አብረውኝ ለሚሠሩ ለጵርስቅላና ለአቂላ ሰላምታ አቅርቡልኝ፤

፬ እነርሱም ስለ ነፍሴ ነፍሳቸውን ለሞት አቀረቡ፥ የአሕዛብም አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የሚያመሰግኑአቸው ናቸው እንጂ እኔ ብቻ አይደለሁም፤

፭ በቤታቸውም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከእስያ ለክርስቶስ በኩራት ለሆነው ለምወደው ለአጤኔጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።

፮ ስለ እናንተ ብዙ ለደከመች ለማርያ ሰላምታ አቅርቡልኝ።

፯ በሐዋርያት መካከል ሰመ ጥሩዎች ለሆኑ፥ ደግሞም ክርስቶስን በማመን ለቀደሙኝ፥ አብረውኝም ለታሰሩ ለዘመዶቼ ለአንዲራኒቆንና ለዩልያን ሰላምታ አቅርቡልኝ።

፰ በጌታ ለምወደው ለጵልያጦን ሰላምታ አቅርቡልኝ።

፱ በክርስቶስ አብሮን ለሚሠራ ለኢሩባኖን ለምወደውም ለስንጣክን ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲ በክርስቶስ መሆኑ ተፈትኖ ለተመሰገነው ለኤጤሌን ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከአርስጣባሉ ቤተ ሰዎች ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፩ ለዘመዴ ለሄሮድዮና ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከንርቀሱ ቤተ ሰዎች በጌታ ላሉት ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፪ በጌታ ሆነው ለሚደክሙ ለፕሮፊሞናና ለጢሮፊሞሳ ሰላምታ አቅርቡልኝ። በጌታ እጅግ ለደከመች ለተወደደች ለጠርሲዳ ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፫ በጌታ ሆኖ ለታወቀ ለሩፎን ለእኔና ለእርሱም እናት ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፬ ለአሰቀሪጦንና ለአፍለሶንጳ ለሄሮሜንም ለጳጥሮባም ለሄርማንም ከእነርሱም ጋር ላሉ ወንድሞች ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፭ ለፍሌጎንና ለዩልያ ለኔርያና ለእኅቱም ለአልንጦንም ከእነርሱ ጋር ላሉ ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ።
፲፮ በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ። የክርስቶስ አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፲፯ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና ማሰናከያን የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ፥ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ፤
፲፰ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ አይገዙምና፥ በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ።
፲፱ መታዘዛችሁ ለሁሉ ተወርቶአልና፤ እንግዲህ በእናንተ ደስ ይለኛል፤ ነገር ግን ለበጎ ነገር ጥበበኞች ለክፉም የዋሆች እንድትሆኑ እወዳለሁ።
፳ የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል። የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።
፳፩ አብሮኝ የሚሠራ ጢሞቴዎስ ዘመዶቼም ሉቂዮስና ኢያሶን ሱሲጴጥሮስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፳፪ ይህን መልእክት የጻፍሁ እኔ ጤርጥዮስ በጌታ ሰላምታ አቀርብላችኋለሁ።
፳፫ የእኔና የቤተ ክርስቲያን ሁሉ እስተናጋጅ ጋይዮስ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። የከተማው መጋቢ ኤርስጦስ ወንድማችንም ቁአስጥሮስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፳፬ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።
፳፭-፳፯ ብቻውን ጥበብ ላለው ለእግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

1ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ
ሊሆን የተጠራ ጳውሎስ ወንድሙም ሶስቴንስ፥
፪ በቆሮንቶስ ላለች ለእግዚአብሔር ቤተ
ክርስቲያን፥ በክርስቶስ ኢየሱስ ለተቀደሱት፥ የእነርሱና
የእኛ ጌታ የሆነውን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
ስም በየስፍራው ከሚጠሩት ሁሉ ጋር ቅዱሳን ለመሆን
ለተጠሩት፤
፫ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፬ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላመናችሁ በተሰጣችሁ
በእግዚአብሔር ጸጋ ምክንያት ሁልጊዜ ስለ እናንተ
አመሰግናለሁ፤
፭-፯ እንደዚህ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን
መገለጥ ስትጠባበቁ እንድ የጸጋ ሰጦታ እንኳ
አይጎድልባችሁም፤
፰ እርሱም ደግሞ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ቀን
ያለ ነቀፋ እንድትሆኑ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያጸናችኋል።
፱ ወደ ልጁ ወደ ጌታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ
ኅብረት የጠራችሁ እግዚአብሔር የታመነ ነው።
፲ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ሁላችሁ
እንድ ንግግር እንድትናገሩ በእንድ ልብና በእንድ
አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት
በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
ስም እለምናችኋለሁ።
፲፩ ወንድሞቼ ሆይ፥ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ
ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና።
፲፪ ይህንም እላለሁ። እያንዳንዳችሁ። እኔ የጳውሎስ
ነኝ፥ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፥ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፥ እኔስ
የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ።
፲፫ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ
ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?
፲፬-፲፮ የእስጢፋኖስንም ቤተ ሰዎች ደግሞ
አጥምቄአለሁ፤ ጨምሬ ሌላ አጥምቄ እንደ ሆነ
አላውቅም።
፲፯ ለማጥመቅ ክርስቶስ አልላከኝምና፥ ወንጌልን
ልስብክ እንጂ፤ የክርስቶስ መስቀል ከንቱ እንዳይሆን
በቃል ጥበብ አይደለም።
፲፰ የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ
ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና።
፲፱ የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ የአስተዋዮችንም
ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና።
፳ ጥበበኛ የት አለ? ጸፊስ የት አለ? የዚች ዓለም
መርማሪስ የት አለ? እግዚአብሔር የዚችን ዓለም
ጥበብ ሞኝነት እንዲሆን አላደረገምን?
፳፩ በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም
እግዚአብሔርን በጥበብዋ ሰላላወቀች፥ በሰብኪት
ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ
ፈቃድ ሆኖአልና።
፳፪ መቼም አይሁድ ምልክትን ይለምናሉ የግሪክ
ሰዎችም ጥበብን ይሻሉ፥
፳፫ እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስን እንሰብካለን፤
ይህም ለአይሁድ ማሰናከያ ለአሕዛብም ሞኝነት ነው፥
፳፬ ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም
ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ
የሆነው ክርስቶስ ነው።
፳፭ ከሰው ይልቅ የእግዚአብሔር ሞኝነት
ይጠበባልና፥ የእግዚአብሔርም ድካም ከሰው ይልቅ
ይበረታልና።
፳፮ ወንድሞች ሆይ፥ መጠራታችሁን ተመልከቱ፤
እንደ ሰው ጥበብ ጥበበኞች የሆኑ ብዙዎች፥
ኀያላን የሆኑ ብዙዎች፥ ባላባቶች የሆኑ ብዙዎች
አልተጠሩም።
፳፯ ነገር ግን እግዚአብሔር ጥበበኞችን እንዲያሳፍር
የዓለምን ሞኝ ነገር መረጠ፤ ብርቱንም ነገር
እንዲያሳፍር እግዚአብሔር የዓለምን ደካማ ነገር
መረጠ፤
፳፰ እግዚአብሔርም የሆነውን ነገር እንዲያጠፋ
የዓለምን ምናምንቴ ነገር የተናቀውንም ነገር
ያልሆነውንም ነገር መረጠ፥
፳፱-፴፩ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት
እንዳይመካ።

፪

፩ እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ በመጣሁ
ጊዜ በቃልና በጥበብ ብልጫ ለእግዚአብሔር
ምስክርነቴን ለእናንተ እየነገርሁ አልመጣሁም።
፪ በመካከላችሁ ሳለሁ ከኢየሱስ ክርስቶስ በቀር
እርሱም እንደተሰቀለ ሌላ ነገር እንዳላውቅ ቆርጬ
ነበርና።
፫ እኔም በድካምና በፍርሃት በብዙ መንቀጥቀጥም
በእናንተ ዘንድ ነበርሁ፤
፬-፭ በበሰሉት መካከል ግን ጥበብን እንናገራለን፥
ነገር ግን የዚችን ዓለም ጥበብ አይደለም
የሚሻሩትንም የዚችን ዓለም ገዦች ጥበብ አይደለም፤
፮ ነገር ግን እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዘመናት
በፊት ለክብራችን የወሰነውን፥ ተሰውሮም የነበረውን
የእግዚአብሔርን ጥበብ በምሥጢር እንናገራለን።
፯ ከዚችም ዓለም ገዦች አንዱ እንኳ ይህን
ጥበብ አላወቀም፤ አውቀውስ ቢሆኑ የክብርን ጌታ
ባልሰቀሉትም ነበር፤
፰ ነገር ግን። ዓይን ያላየችው ጆሮም ያልሰማው
በሰውም ልብ ያልታሰበው እግዚአብሔር ለሚወዱት
ያዘጋጀው ተብሎ እንድተጻፈ፥ እንዲህ እንናገራለን።
፱ መንፈስም የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ሰንኳ
ሳይቀር ሁሉን ይመረምራልና ለእኛ እግዚአብሔር
በመንፈሱ በኩል ገለጠው።
፲ በእርሱ ውስጥ ካለው ከሰው መንፈስ በቀር
ለሰው ያለውን የሚያውቅ ሰው ማን ነው? እንዲሁም
ደግሞ ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር
ያለውን ማንም አያውቅም።
፲፩ እኛ ግን ከእግዚአብሔር እንዲያው የተሰጠንን
እናውቅ ዘንድ ከእግዚአብሔር የሆነውን መንፈስ እንጂ
የዓለምን መንፈስ አልተቀበልንም።
፲፫ መንፈሳዊውን ነገር ከመንፈሳዊው ነገር ጋር
አስተያይተን መንፈስ በሚያስተምረን ቃል ይህን ደግሞ
እንናገራለን እንጂ የሰው ጥበብ በሚያስተምረን ቃል
አይደለም።
፲፬ ለፍጥረታዊ ሰው የእግዚአብሔር መንፈስ
ነገር ሞኝነት ነውና አይቀበለውም፤ በመንፈስም
የሚመረመር ሰለ ሆነ ሊያውቀው አይችልም።

፲፭ መንፈሳዊ ሰው ግን ሁሉን ይመረምራል ራሱ ግን በማንም አይመረመርም።
፲፮ እንዲያስተምረው የጌታን ልብ ማን አውቆት ነው? እኛ ግን የክርስቶስ ልብ አለን።

፫

፩ እኔም፥ ወንድሞች ሆይ፥ የሥጋ እንደ መሆናችሁ፥ በክርስቶስም ሕፃናት እንደ መሆናችሁ እንጂ መንፈሳውያን እንደ መሆናችሁ ልናገራችሁ አልቻልሁም።
፪ ገና ጽኑ መብል ለመብላት አትችሉም ነበርና ወተት ጋትኋችሁ፤
፫ ገና ሥጋውያን ናችሁና እስከ አሁን ድረስ ገና አትችሉም። ቅናትና ክርክር ስለሚገኝባችሁ ሥጋውያን መሆናችሁ አይደላችሁምን? እንደ ሰው ልማድስ አትመላለሱምን?
፬ አንዱ። እኔ የጳውሎስ ነኝ፥ ሁለተኛውም። እኔ የአጵሎስ ነኝ ቢል ሰዎች ብቻ መሆናችሁ አይደለምን?
፭ አጵሎስ እንግዲህ ምንድር ነው? ጳውሎስስ ምንድር ነው? በእነርሱ እጅ ያመናችሁ አገልጋዮች ናቸው፤ ለእያንዳንዳቸውም ጌታ እንደ ሰጣቸው ያገለግላሉ።
፮ እኔ ተከልሁ አጵሎስም አጠጣ ነገር ግን እግዚአብሔር ያሳድግ ነበር፤
፯ እንግዲያስ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ የሚተክል ቢሆን ወይም የሚያጠጣ ቢሆን እንዳች አይደለም።
፰ የሚተክልና የሚያጠጣ እኩድ ናቸው፥ ነገር ግን እያንዳንዱ እንደ ራሱ ድካም መጠን የራሱን ደመወዝ ይቀበላል።
፱ የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ፤ ከእርሱ ጋር አብረን የምንሠራ ነንና።
፲ የእግዚአብሔር ጸጋ እንደ ተሰጠኝ መጠን እንደ ብልሃተኛ የአናጺ አለቃ መሠረትን መሠረትሁ፥ ሌላውም በላዩ ያንጻል። እያንዳንዱ ግን በእርሱ ላይ እንዴት እንዲያንጽ ይጠንቀቅ።
፲፩ ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።
፲፪ ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፥ የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፤
፲፫ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፥ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል።
፲፬ ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤
፲፭ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፥ እርሱ ራሱ ግን ይድናል ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።
፲፮ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እንደ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንዲኖርባችሁ አታውቁምን?
፲፯ ማንም የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ቢያፈርስ እግዚአብሔር እርሱን ያፈርሰዋል፤ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ቅዱስ ነውና፥ ያውም እናንተ ናችሁ።
፲፰ ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ማንም በዚች ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ሞኝ ይሁን።
፲፱-፳፩ ስለዚህም ማንም በሰው አይመካ። ነገር ሁሉ የእናንተ ነውና፤
፳፪ ጳውሎስ ቢሆን አጵሎስም ቢሆን ኬፋም ቢሆን ዓለምም ቢሆን ሕይወትም ቢሆን ሞትም ቢሆን ያለውም ቢሆን የሚመጣውም ቢሆን፥
፳፫ ሁሉ የእናንተ ነው፥ እናንተም የክርስቶስ ናችሁ ክርስቶስም የእግዚአብሔር ነው።

፬

፩ እንዲሁ ሰው እኛን እንደ ክርስቶስ ሎሌዎችና እንደ እግዚአብሔር ምሥጢር መጋቢዎች ይቍጠረን።
፪ እንደዚህም ሲሆን፥ በመጋቢዎች ዘንድ የታመነ ሆኖ መገኘት ይፈለጋል።
፫ ነገር ግን በእናንተ ዘንድ ወይም በሌላ ሰው ዘንድ ብፈረድ ለእኔ ምንም አይደለም፤ እኔም በራሴ እንኳ አልፈርድም፤
፬ በራሴ ላይ ምንም አላውቅምና፥ ነገር ግን በዚህ አልጸድቅም፤ እኔን የሚፈርድ ግን ጌታ ነው።
፭ ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ እንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል።
፮ ወንድሞች ሆይ፥ ሰለ እኩዱ በእኩዱ ላይ እንዳችሁም እንዳይታበዩ። ከተጻፈው አትለፍ የሚለውን በእኛ ትማሩ ዘንድ፥ ይህን በእናንተ ምክንያት ሰለ ራሴና ሰለ አጵሎስ እንደ ምሳሌ ተናገርሁ።
፯ አንተ እንድትበልጥ ማን አድርጎሃል? ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ሰለ ምንድር ነው?
፰ አሁን ጠግባችኋል፤ አሁንስ ባለ ጠጎች ሆናችኋል፤ ያለ እኛ ነግሣችኋል፤ እኛ ደግሞ ከእናንተ ጋር እንድንነግሥ ብትነግሡ መልካም ይሆን ነበር።
፱ ለዓለም ለመላእክትም ለሰዎችም መጫወቻ ሆነናልና፤ እግዚአብሔር እኛን ሐዋርያቱን ሞት እንደ ተፈረደባቸው ሰዎች ከሁሉ ይልቅ የኋለኞች እንዳደረገን ይመስለኛልና።
፲ እኛ ሰለ ክርስቶስ ሞኞች ነን እናንተ ግን በክርስቶስ ልባሞች ናችሁ፤ እኛ ደካሞች ነን እናንተ ግን ኀይለኞች ናችሁ፤ እናንተ የከበራችሁ ናችሁ እኛ ግን የተዋረድን ነን።
፲፩ እስከዚህ ሰዓት ድረስ እንራባለን፥ እንጠማለን፥ እንራቆታለን፥ እንጐሰማለን፥ እንንከራተታለን፥
፲፪ በገዛ እጃችን እየሠራን እንደክማለን፤ ሲሰድቡን እንመርቃለን፥ ሲያሳድዱን እንታገሣለን፥ ክፉ ሲናገሩን እንማልዳለን፤
፲፫ እስከ አሁን ድረስ የዓለም ጥራጊ የሁሉም ጕድፍ ሆነናል።
፲፬ እንደምወዳችሁ ልጆቼ አድርጌ ልገሥጻችሁ እንጂ ላሳፍራችሁ ይህን አልጽፍም።
፲፭ በክርስቶስ አእላፍ ሞግዚቶች ቢኖሩአችሁ ብዙ አባቶች የሉአችሁም እኔ በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል ወልጄአችኋለሁና።
፲፮ እንግዲህ እኔን የምትመስሉ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ።

፲፯ ስለዚህ የምወደውንና የታመነውን በጌታ ልጄ የሆነውን ጢሞቴዎስን ልኬላችኋለሁ፥ እኔም በየስፍራው በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እንደማስተምር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚሆነውን መንገዴን እርሱ ያሳስባችኋል።
፲፰ እንዳንዱ ግን ወደ እናንተ የማልመጣ እየመሰላቸው የታበዩ አሉ፤
፲፱ ነገር ግን ጌታ ቢፈቅድ ፈጥኜ ወደ እናንተ እመጣለሁ፥ የትዕቢተኞችንም ኃይል አውቃለሁ እንጂ ቃላቸውን አይደለም፤
፳ የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና።
፳፩ ምን ትወዳላችሁ? በበትር ወይስ በፍቅርና በየውሃት መንፈስ ልምጣባችሁን?

፭

፩ በአጭር ቃል በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና።
፪ እናንተም ታብያችኋል፤ ይልቅስ እንድታዝኑ አይገባችሁምን? ይህን ሥራ የሠራው ከመካከላችሁ ይወገድ።
፫-፭ መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው።
፮ መመካታችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን?
፯ እንግዲህ ያለ እርሾ እንዳላችሁ አዲሱን ሊጥ ትሆኑ ዘንድ አሮጌውን እርሾ አስወግዱ። ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና፤
፰ ስለዚህ በቅንነትና በእውነት ቂጣ በዓልን እናድርግ እንጂ በአሮጌ እርሾ በክፋትና በግፍ እርሾም አይደለም።
፱ ከሴሰኞች ጋር እንዳትተባበሩ በመልእክቴ ጻፍሁላችሁ።
፲ በጠቅላላው የዚህን ዓለም ሴሰኞችን፥ ወይም ገንዘብን የሚመኙትን ነጣቂዎችንም፥ ወይም ጣዖትን የሚያመልኩትን አላልሁም፤ ይህስ ቢሆን ከዓለም ልትወጡ ይገባችሁ ነበር።
፲፩ አሁን ግን ወንድሞች ከሚባሉት አንዱ ሴሰኛ ወይም ገንዘብን የሚመኝ ወይም ጣዖትን የሚያመልክ ወይም ተሳዳቢ ወይም ሰካር ወይም ነጣቂ ቢሆን ከእርሱ ጋር እንዳትተባበሩ እጽፍላችኋለሁ፤ እንደነዚህ ካለው ጋር መብል እንኳን አትብሉ።
፲፪ በውጭ ባሉ ሰዎች ላይ መፍረድ ምን አግዶኝ? በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ እናንተ አትፈርዱምን?
፲፫ በውጭ ባሉቱ ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡት።

፮

፩ ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን?
፪ ቅዱሳን በዓለም ላይ እንዲፈርዱ አታውቁምን? በዓለምስ ላይ ብትፈርዱ ከሁሉ ይልቅ ትንሽ ስለሚሆን ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን?
፫ የትዳር ጉዳይ ይቅርና በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?
፬ እንግዲህ ስለ ትዳር ጉዳይ የፍርድ ቤት ቢያስፈልጋችሁ በቤተ ክርስቲያን የተናቁትን ሰዎች ፈራጆች አድርጋችሁ ታስቀምጣላችሁን?
፭ አሳፍራችሁ ዘንድ ይህን እላለሁ። እንደዚህ ነውን? በወንድሞች መካከል ሸማግሌ ሊሆን የሚችል አንድ አስተዋይ ሰው በእናንተ ዘንድ አይገኝምን?
፮ ነገር ግን ወንድም ወንድሙን ይከሳል፥ ይህም በማያምኑ ፊት ይደረጋልን?
፯ እንግዲህ ፈጽሞ የእርስ በርስ ሙግት እንዳለባችሁ በእናንተ ጉድለት ነው። ብትበደሉ አይሻልምን? ብትታለሉስ አይሻልምን?
፰ ነገር ግን እናንተ ትበድላላችሁ ታታልሉማላችሁ፥ ያውም ወንድሞቻችሁን።
፱ ወይስ ዓመፀኞች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዳይወርሱ አታውቁምን? አትሳቱ፤ ሴሰኞች ቢሆን ወይም ጣዖትን የሚያመልኩ ወይም አመንዝሮች ወይም ቀላጮች ወይም ከወንድ ጋር ዝሙት የሚሠሩ
፲ ወይም ሌቦች ወይም ገንዘብን የሚመኙ ወይም ሰካሮች ወይም ተሳዳቢዎች ወይም ነጣቂዎች የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
፲፩ ከእናንተም አንዳንዶቹ እንደ እነዚህ ነበራችሁ፤ ነገር ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በአምላካችንም መንፈስ ታጥባችኋል፥ ተቀድሳችኋል፥ ጸድቃችኋል።
፲፪ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን አይጠቅምም። ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ በእኔ ላይ ግን አንድ ነገር እንኳ አይሠለጥንብኝም።
፲፫ መብል ለሆድ ነው፥ ሆድም ለመብል ነው፤ እግዚአብሔር ግን ይህንም ያንም ያጠፋቸዋል። ሥጋ ግን ለጌታ ነው እንጂ ለዝሙት አይደለም፤ ጌታም ለሥጋ ነው፤
፲፬ እግዚአብሔርም ጌታንም አስነሣ እኛንም በኃይሉ ያስነሣናል።
፲፭ ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደ ሆነ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላድርጋቸውን? አይገባም።
፲፮ ወይስ ከጋለሞታ ጋር የሚተባበር አንድ ሥጋ እንዲሆን አታውቁምን? ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ ተብሎአልና።
፲፯ ከጌታ ጋር የሚተባበር ግን አንድ መንፈስ ነው።
፲፰-፳ ከዝሙት ሽሹ። ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው፤ ዝሙትን የሚሠራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል።

፯

፩ ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።
፪ ነገር ግን ስለ ዝሙት ጠንቅ ለእያንዳንዱ ለራሱ ሚስት ትኑረው ለእያንዳንዲቱ ደግሞ ለራስዋ ባል ይኑራት።
፫ ባል ለሚስቱ የሚገባትን ያድርግላት፥ እንደዚሁም ደግሞ ሚስቲቱ ለባልዋ።

፬ ሚስት በገዛ ሥጋዋ ላይ ሥልጣን የላትም፥ ሥልጣን ለባልዋ ነው እንጂ፤ እንዲሁም ደግሞ ባል በገዛ ሥጋው ላይ ሥልጣን የለውም፥ ሥልጣን ለሚስቱ ነው እንጂ።
፭ ለጸሎት ትተጉ ዘንድ ተሰማምታችሁ ለጊዜው ካልሆነ በቀር፥ እርስ በርሳችሁ አትከላከሉ፤ ራሳችሁን ሰለ አለመግዛት ሰይጣን እንዳይፈታተናችሁ ደግሞ አብራችሁ ሁኑ።
፮ ዳሩ ግን ይህን እንደ ፈቃድ እላለሁ እንጂ እንደ ትእዛዝ አይደለም።
፯ ሰው ሁሉ እንደ እኔ ሊሆን እወዳለሁና፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ከእግዚአብሔር ለራሱ የጸጋ ሰጦታ አለው፥ አንዱ እንደዚህ ሁለተኛውም እንደዚያ።
፰ ላላገቡና ለመበለቶች ግን እላለሁ። እንደ እኔ ቢኖሩ ለእነርሱ መልካም ነው፤
፱ ነገር ግን በምኞት ከመቃጠል መጋባት ይሻላልና ራሳቸውን መግዛት ባይችሉ ያግቡ።
፲-፲፩ ሌሎችንም እኔ እላለሁ፥ ጌታም አይደለም፤ ከወንድሞች ወገን ያለመነች ሚስት ያለችው ቢኖር እርሰዋም ከእርሱ ጋር ልትቀመጥ ብትሰማማ፥ አይተዋት፤
፲፫ ያላመነ ባል ያላት ሚስትም ብትኖር ይህ ከእርሰዋ ጋር ሊቀመጥ ቢሰማማ፥ አትተወው።
፲፬ ያላመነ ባል በሚስቱ ተቀድሶአልና፥ ያላመነችም ሚስት በባልዋ ተቀድሳለችና፤ አለዚያ ልጆቻችሁ ርኩሳን ናቸው፤ አሁን ግን የተቀደሱ ናቸው።
፲፭ የማያምን ግን ቢለይ ይለይ፤ ወንድም ቢሆን ወይም እኅት እንዲህ በሚመስል ነገር አይገዙም፤ እግዚአብሔር ግን በሰላም ጠርቶናል።
፲፮ አንቺ ሴት፥ ባልሽን ታድኚ እንደ ሆንሽ ምን ታውቂአለሽ? ወይስ አንተ ሰው፥ ሚስትህን ታድን እንደ ሆንህ ምን ታውቃለህ?
፲፯ ብቻ ለእያንዳንዱ እግዚአብሔር እንደ ከፈለለት እያንዳንዱም እግዚአብሔር እንደ ጠራው እንዲሁ ይመላለስ። እንዲሁም በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ እደነግጋለሁ።
፲፰ ማንም ተገርዞ ሳለ ተጠርቶ እንደ ሆነ፥ ወደ አለመገረዝ አይመለስ፤ ማንም ሳይገረዝ ተጠርቶ እንደ ሆነ አይገረዝ።
፲፱ መገረዝ ቢሆን አለመገረዝም ቢሆን ከንቱ ነው፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መጠበቅ ነው እንጂ።
፳ እያንዳንዱ በተጠራበት መጠራት እንደዚሁ ይኑር።
፳፩ ባሪያ ሆነህ ተጠርተህ እንደ ሆነ አይገድህም፤ አርነት ልትወጣ ቢቻልህ ግን አርነትን ተቀበል።
፳፪ ባሪያ ሆኖ በጌታ የተጠራ የጌታ ነጻ ነውና፤ እንዲሁም ነጻ ሆኖ የተጠራ የክርስቶስ ባሪያ ነው።
፳፫ በዋጋ ተገዝታችኋል፤ የሰው ባሪያዎች አትሁኑ።
፳፬ ወንድሞች ሆይ፥ እያንዳንዱ በተጠራበት እንደዚሁ ሆኖ በእግዚአብሔር ዘንድ ይኑር።
፳፭ ሰለ ደናግልም የጌታ ትእዛዝ የለኝም፥ ነገር ግን የታመንሁ እሆን ዘንድ ከጌታ ምሕረትን የተቀበልሁ እንደ መሆኔ ምክር እመክራለሁ።
፳፮ እንግዲህ ሰለ አሁኑ ችግር ይህ መልካም ይመሰለኛል፤ ሰው እንዲህ ሆኖ ቢኖር መልካም ነው።
፳፯ በሚስት ታሰረህ እንደ ሆንህ መፋታትን አትሻ፤ በሚስት አልታሰርህ እንደ ሆንህ ሚስትን አትሻ።
፳፰ ብታገባ ግን ኃጢአት አትሠራም ድንግሊቱም ብታገባ ኃጢአት አትሠራም፤ ነገር ግን እንዲህ በሚያደርጉ በሥጋቸው ላይ መከራ ይሆንባቸዋል፥ እኔም እራራላችሁ ነበር።
፳፱ ዳሩ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እናገራለሁ፤ ዘመኑ አጭር ሆኖአል፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሚስቶች ያሉአቸው እንደሌላቸው ይሁኑ፥
፴ የሚያለቅሱም እንደማያለቅሱ፥ ደስ የሚላቸውም ደስ እንደማይላቸው፥
፴፩ የሚገዙም ምንም እንደሌላቸው፥ በዚችም ዓለም የሚጠቀሙ በሙሉ እንደማይጠቀሙባት ይሁኑ፤ የዚች ዓለም መልክ አላፊ ነውና።
፴፪ ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ። ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው የጌታን ነገር ያስባል፤
፴፫ ያገባው ግን ሚስቱን እንዴት ደስ እንዲያሰኛት የዓለምን ነገር ያስባል፥ ልቡም ተከፍሎአል።
፴፬ ያልተጋባች ሴትና ድንግል በሥጋም በነፍስም እንዲቀደሱ የጌታን ነገር ያስባሉ፤ የተጋባች ግን ባልዋን እንዴት ደስ እንድታሰኘው የዓለምን ነገር ታስባለች።
፴፭ ይህንም ለራሳችሁ ጥቅም እላለሁ፤ በአገባብ እንድትኖሩ ሳትባክኑም በጌታ እንድትጸኑ ነው እንጂ ላጠምዳችሁ ብዬ አይደለም።
፴፮ ዳሩ ግን ማግባት ወደሚገባው ዕድሜ በደረሰ ጊዜ ሰለ ድንግልናው ያፈረ ሰው ቢኖር፥ የወደደውን ያድርግ፤ ኃጢአት የለበትም፤ ይጋቡ።
፴፯ ሳይናወጥ በልቡ የጸና ግን ግድ የለበትም፥ የወደደውን እንዲያደርግ ተፈቅዶለታል፤ ድንግልናውንም በልቡ ይጠብቅ ዘንድ ቢጸና፥ መልካም አደረገ።
፴፰ እንዲሁም ድንግልን ያገባ መልካም አደረገ ያላገባም የተሻለ አደረገ።
፴፱ ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት፤ ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት።
፵ እንደ ምክሬ ግን እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት፤ እኔም ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ያለ ይመስለኛል።

፰

፩ ለጣዖት ሰለ ተሠዋ ሥጋም፥ ሁላችን እውቀት እንዳለን እናውቃለን። እውቀት ያሰታብያል ፍቅር ግን ያንጸል።
፪ ማንም እንዳች የሚያውቅ ቢመሰለው ሊያውቅ እንደሚገባው ገና አላወቀም፤
፫ ማንም ግን እግዚአብሔርን ቢወድ እርሱ በእርሱ ዘንድ የታወቀ ነው።
፬ እንግዲህ ለጣዖት የተሠዋውን ሥጋ ሰለ መብላት፥ ጣዖት ሁሉ በዓለም ከንቱ እንደ ሆነ ከእንዱም በቀር ማንም አምላክ እንደሌለ እናውቃለን።
፭ መቼም ብዙ አማልክትና ብዙ ጌቶች አሉ፤ ነገር ግን በሰማይ ሆነ በምድርም ሆነ አማልክት የተባሉ ምንም ቢኖሩ፥
፮ ለእኛስ ነገር ሁሉ ከእርሱ የሆነ እኛም ለእርሱ የሆንን አንድ አምላክ አብ አለን፥ ነገር ሁሉም በእርሱ በኩል የሆነ እኛም በእርሱ በኩል የሆንን አንድ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አለን።

፯ ነገር ግን ይህ እውቀት በሁሉ ዘንድ አይገኝም፤ አንዳንዶች ግን ጣዖትን እስከ አሁን ድረስ ሰለ ለመዱ። ለጣዖት የተሠዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ሰለ ሆነ ይረክሳል።
፰ መብል ግን ወደ እግዚአብሔር አያቀርበንም፤ ባንበላም ምንም አይጎድለንም ብንበላም ምንም አይተርፈንም።
፱ ዳሩ ግን ይህ መብታችሁ ለደካሞች ዕንቅፋት እንዳይሆንባቸው ተጠንቀቁ።
፲ አንተ እውቀት ያለህ በጣዖት ቤት በማዕድ ስትቀመጥ አንድ ሰው ቢያይህ፥ ደካማ ሰው ቢሆን ለጣዖት የተሠዋውን ለመብላት ሕሊናው አይታነጽበትምን?
፲፩ በእነተ እውቀትም ይህ ደካማ ይጠፋል፥ እርሱም ክርስቶስ የሞተለት ወንድም ነው።
፲፪ እንዲህም ወንድሞችን እየበደላችሁ ደካማም የሆነውን ሕሊናቸውን እያቆሰላችሁ ክርስቶስን ትበድላላችሁ።
፲፫ ሰለዚህም መብል ወንድሜን የሚያሰናክለው ከሆነ፥ ወንድሜን እንዳላሰናክለው ለዘላለም ከቶ ሥጋ አልበላም።

፱

፩ እኔ ነጻ አይደለሁምን? ሐዋርያስ አይደለሁምን? ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስንስ አላየሁትምን? እናንተስ በጌታ ሥራዬ አይደላችሁምን?
፪ የሐዋርያነቴ ማኅተም በጌታ እናንተ ናችሁና ለሌሎች ሐዋርያ ባልሆን ለእናንተስ ምንም ቢሆን ሐዋርያ ነኝ።
፫-፭ እንደ ሌሎቹ ሐዋርያትና እንደ ጌታ ወንድሞች እንደ ኬፋም፥ እኅት ሚስታችንን ይዘን ልንዞር መብት የለንምን?
፮ ወይስ ሥራን ለመተው መብት የሌለን እኔና በርናባስ ብቻ ነን?
፯ ከቶ በገዛ ገንዘቡ በወታደርነት የሚያገለግል ማን ነው? ወይስ ወይን ተክሎ ፍሬውን የማይበላ ማን ነው? ወይስ መንጋ እየጠበቀ ከመንጋው ወተት የማይጠጣ ማን ነው?
፰ ይህን በሰው ሥልጣን ብቻ እላለሁን?
፱ ሕግስ ደግሞ ያን አይልምን? የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር ተብሎ በሙሴ ሕግ ተጽፎአልና። እግዚአብሔርስ ሰለ በሬዎች ይገደዋልን?
፲ ይህን የሚለው ፈጽሞ ሰለ እኛ አይደለምን? የሚያርስ በተሰፋ ሊያርስ የሚያበራይም እንዲካፈል በተሰፋ ሊያበራይ ሰለሚገባው በእውነት ሰለ እኛ ተጽፎአል።
፲፩ እኛ መንፈሳዊን ነገር የዘራንላችሁ ከሆንን የእናንተን የሥጋዊን ነገር እኛ ብናጭድ ትልቅ ነገር ነውን?
፲፪ ሌሎች በእናንተ ላይ ይህን መብት የሚካፈሉ ከሆኑ እኛማ ይልቁን እንዴታ? ነገር ግን የክርስቶስን ወንጌል እንዳንከለክል በሁሉ እንታገሣለን እንጂ በዚህ መብት አልተጠቀምንም።
፲፫ በመቅደስ ነገር የሚያገለግሉ ከመቅደስ የሆነውን ነገርን እንዲመገቡ፥ በመሠዊያውም የሚጸኑ ከመሠዊያው እንዲካፈሉ አታውቁምን?
፲፬ እንዲሁ ደግሞ ወንጌልን የሚሰብኩ ከወንጌል ቀለብ እንዲቀበሉ ጌታ ደንግጎአል።
፲፭ እኔ ግን ከእነዚህ ሁሉ ምንም አልተጠቀምሁም። እንዲህ እንዲሆንልኝ ይህን አልጽፍም፤ ማንም ትምክህቴን ከንቱ ከሚያደርግብኝ ሞት ይሻለኛልና።
፲፮ ወንጌልን ብሰብክ እንኳ የምመካበት የለኝም፤ ግድ ደርሶብኝ ነውና፤ ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ።
፲፯ ይህን በፈቃዴ ባደርገው ደመወዝ አለኝና፤ ያለ ፈቃዴ ግን ባደርገው መጋቢነት በአደራ ተሰጥቶኛል።
፲፰ እንግዲህ ደመወዜ ምንድር ነው? ወንጌልን እየሰበክሁ በወንጌል ካለኝ መብት በሙሉ እንዳልጠቀም ወንጌልን ያለ ዋጋ ብናገር ነው።
፲፱ ከሰው ሁሉ እርነት የወጣሁ ሰሆን የሚበልጡትን እንድጠቅም እንደ ባሪያ ራሴን ለሁሉ አሰገዛለሁ።
፳ እይሁድንም እጠቅም ዘንድ ከአይሁድ ጋር እንደ አይሁዳዊ ሆንሁ፤ ከሕግ በታች ያሉትን እጠቅም ዘንድ፥ እኔ ራሴ ከሕግ በታች ሳልሆን፥ ከሕግ በታች ላሉት ከሕግ በታች እንዳለሁ ሆንሁ፤
፳፩ ሕግ የሌላቸውን እጠቅም ዘንድ፥ ያለ እግዚአብሔር ህግ ሳልኖር ነገር ግን በክርስቶስ ሕግ በታች ሳለሁ፥ ሕግ ለሌላቸው ሕግ እንደ ሌለኝ ሆንሁ፤
፳፪ ደካሞችን እጠቅም ዘንድ ለደካሞች እንደ ደካማ ሆንሁ፤ በሁሉ መንገድ አንዳንዶችን አድን ዘንድ፥ ከሁሉ ጋር በሁሉ ነገር እንደ እነርሱ ሆንሁ።
፳፫ በወንጌልም ማኅበረተኛ እሆን ዘንድ ሰለ ወንጌል ሁሉን እደርጋለሁ።
፳፬ በእሽቅድምድም ሰፍራ የሚሮጡት፥ ሁሉ እንዲሮጡ ነገር ግን አንዱ ብቻ ዋጋውን እንዲቀበል አታውቁምን? እንዲሁም ታገኙ ዘንድ ሩጡ።
፳፭ የሚታገልም ሁሉ በነገር ሁሉ ሰውነቱን ይገዛል፤ እነዚያም የሚጠፋውን አክሊል ሊያገኙ ነው፥ እኛ ግን የማይጠፋውን።
፳፮ ሰለዚህ እኔ ያለ አሳብ እንደሚሮጥ ሁሉ እንዲሁ አልሮጥም፥ ነፋስን እንደሚጎሰም ሁሉ እንዲሁ አልጋደልም፤
፳፯ ነገር ግን ለሌሎች ከሰበክሁ በኋላ ራሴ የተጣልሁ እንዳልሆን ሥጋዬን እየጎሰምሁ አሰገዛዋለሁ።

፲

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ። አባቶቻችን ሁሉ ከደመና በታች ነበሩ ሁሉም በባሕር መካከል ተሻገሩ፤
፪ ሁሉም ሙሴን ይተባበሩ ዘንድ በደመናና በባሕር ተጠመቁ፤
፫ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መብል በሉ ሁሉም ያን መንፈሳዊ መጠጥ ጠጡ፤
፬ ይከተላቸው ከነበረው ከመንፈሳዊ ዓለት ጠጥተዋልና፥ ያም ዓለት ክርስቶስ ነበረ።
፭ እግዚአብሔር ግን ከእነርሱ በሚበዙት ደስ አላለውም፥ በምድረ በዳ ወድቀዋልና።
፮ እነዚህም ክፉ ነገር እንደ ተመኙ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን።
፯ ሕዝብም ሊበሉ ሊጠጡም ተቀመጡ ሊዘፍኑም ተነሡ ተብሎ እንደ ተጻፈ ከእነርሱ አንዳንዶቹ እንዳደረጉት ጣዖትን የምታመልኩ አትሁኑ።

፰ ከእነርሱም እንዳንዶቹ እንደ ሴሰኑ በአንድ ቀንም
ሁለት እልፍ ከሦስት ሺህ እንደ ወደቁ እንሴስን።
፱ ከእነርሱም እንዳንዶቹ ጌታን እንደ ተፈታተኑት
በእባቦቹም እንደ ጠፉ ጌታን እንፈታተን።
፲ ከእነርሱም እንዳንዶቹ እንዳንጎራጎሩ
በሚያጠፋውም እንደ ጠፉ አታንጐርጕሩ።
፲፩ ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም
የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ።
፲፪ ስለዚህ እንደ ቆመ የሚመሰለው እንዳይወድቅ
ይጠንቀቅ።
፲፫ ለሰው ሁሉ ከሚሆነው በቀር ምንም ፈተና
አልደረሰባችሁም፤ ነገር ግን ከሚቻላችሁ መጠን
ይልቅ ትፈተኑ ዘንድ የማይፈቅድ እግዚአብሔር የታመነ
ነው፥ ትታገሡም ዘንድ እንድትችሉ ከፈተናው ጋር
መውጫውን ደግሞ ያደርግላችኋል።
፲፬ ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ጣዖትን ከማምለክ
ሽሹ።
፲፭ ልባሞች እንደ መሆናችሁ እላለሁ፤ በምለው ነገር
እናንተ ፍረዱ።
፲፮ የምንባርከው የበረከት ጽዋ ከክርስቶስ ደም ጋር
ኅብረት ያለው አይደለምን? የምንቆርሰውስ እንጀራ
ከክርስቶስ ሥጋ ጋር ኅብረት ያለው አይደለምን?
፲፯ አንድ እንጀራ ስለ ሆነ፥ እኛ ብዙዎች ስንሆን
አንድ ሥጋ ነን፤ ሁላችን ያን አንዱን እንጀራ
እንካፈላለንና።
፲፰ በሥጋ የሆነውን እስራኤል ተመልከቱ፤
መሥዋዕቱን የሚበሉ የመሠዊያው ማኅበረተኞች
አይደሉምን?
፲፱ እንግዲህ ምን እላለሁ? ለጣዖት የተሠዋ
ምናምን ነው እላለሁን? ወይስ ጣዖት ምናምን
እንዲሆን እላለሁን?
፳ አይደለም፤ ነገር ግን አሕዛብ የሚሠዉት
ለአጋንንት እንዲሆን እንጂ ለእግዚአብሔር እንዳይሠዉ
እላለሁ፤ ከአጋንንትም ጋር ማኅበረተኞች እንድትሆኑ
አልወድም።
፳፩ የጌታን ጽዋና የአጋንንትን ጽዋ ልትጠጡ
አትችሉም፤ ከጌታ ማዕድና ከአጋንንት ማዕድ
ልትካፈሉ አትችሉም።
፳፪ ወይስ ጌታን እናስቀናውን? እኛስ ከእርሱ ይልቅ
እንበረታለንን?
፳፫ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ሁሉ ግን የሚጠቅም
አይደለም፤ ሁሉ ተፈቅዶልኛል፥ ነገር ግን ሁሉ የሚያንጽ
አይደለም።
፳፬ እያንዳንዱ የባልንጀራውን ጥቅም እንጂ አንድ
ሰንኳ የራሱን ጥቅም አይፈልግ።
፳፭ በሥጋ ገበያ የሚሸጠውን ሁሉ ከሕሊና የተነሣ
ሳትመራመሩ ብሉ፤
፳፮ ምድርና በእርስዋ የሞላባት ሁሉ የጌታ ነውና።
፳፯ ከማያምኑ ሰዎች አንዱም ቢጠራችሁ
ልትሄዱም ብትወዱ ከሕሊና የተነሣ ሳትመራመሩ
የሚያቀርቡላችሁን ሁሉ ብሉ።
፳፰ ማንም ግን። ይህ ለጣዖት የተሠዋ ነው ቢላችሁ
ከዚያ ካስታወቃችሁና ከሕሊና የተነሣ አትብሉ፤
፳፱ ስለ ባልንጀራህ ሕሊና እንጂ ስለ ገዛ ሕሊናህ
አልናገርም። እርነቴ በሌላ ሰው ሕሊና የሚፈርድ Avረ
ስለ ምንድር ነው?
፴ እኔም በጸጋ ብበላ፥ በነገሩ ስለማመሰግንበት ስለ
ምን እሰደባለሁ?
፴፩-፴፫ እንግዲህ የምትበሉ ወይም የምትጠጡ
ብትሆኑ ወይም ማናቸውን ነገር ብታደርጉ ሁሉን
ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት።

፲፩

፩ እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ።
፪ ወንድሞች ሆይ፥ በሁሉ ስለምታስቡኝና እሳልፌ
እንደ ሰጠኋችሁ ወግን ፈጽማችሁ ስለ ያዛችሁ
አመሰግናችኋለሁ።
፫ ነገር ግን የወንድ ሁሉ ራስ ክርስቶስ፥ የሴትም
ራስ ወንድ፥ የክርስቶስም ራስ እግዚአብሔር እንደ ሆነ
ልታውቁ እወዳለሁ።
፬ ራሱን ተከናንቦ የሚጸልይ ወይም ትንቢት የሚናገር
ወንድ ሁሉ ራሱን ያዋርዳል።
፭ ራስዋን ሳትሸፍን ግን የምትጸልይ ወይም ትንቢት
የምትናገር ሴት ሁሉ ራስዋን ታዋርዳለችና፤ እንደ
ተላጨች ያህል እንድ ነውና።
፮ ሴትም ራስዋን ባትሸፍን ጠጉርዋን ደግሞ
ትቆረጥ፤ ለሴት ግን ጠጉርዋን መቆረጥ ወይም
መላጨት የሚያሳፍር ከሆነ ራስዋን ትሸፍን።
፯ ወንድ የእግዚአብሔር ምሳሌና ክብር ስለ ሆነ
ራሱን መከናነብ አይገባውም፤ ሴት ግን የወንድ ክብር
ናት።
፰ ሴት ከወንድ ናት እንጂ ወንድ ከሴት አይደለምና።
፱ ሴት ስለ ወንድ ተፈጠረች እንጂ ወንድ ስለ ሴት
አልተፈጠረምና።
፲ ስለዚህ ሴት ከመላእክት የተነሣ በራስዋ ሥልጣን
ሊኖራት ይገባል።
፲፩ ነገር ግን በጌታ ዘንድ ሴት ያለ ወንድ ወንድም
ያለ ሴት አይሆንም።
፲፪ ሴት ከወንድ እንደ ሆነች እንዲሁ ወንድ ደግሞ
በሴት ነውና፤ ሁሉም ከእግዚአብሔር ነው።
፲፫ በእናንተ በራሳችሁ መካከል ፍረዱ፤ ሴት ራስዋን
ሳትሸፍን ወደ እግዚአብሔር ልትጸልይ ይገባታልን?
፲፬-፲፭ ዳሩ ግን ማንም ሊከራከር ቢፈቅድ፥ እኛ
ወይም የእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት እንዲህ ያለ
ልማድ የለንም።
፲፮ ነገር ግን በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለሚከፋ
እንጂ ለሚሻል ሰላልሆነ ይህን ትእዛዝ ሰስጥ
የማመሰግናችሁ አይደለም።
፲፯ በመጀመሪያ ወደ ማኅበር ስትሰበሰቡ
በመካከላችሁ መለያየት እንዳለ እሰማለሁና፥ በአንድ
በኩልም አምናለሁ።
፲፰ በእናንተ ዘንድ የተፈተኑት እንዲገለጡ
በመካከላችሁ ወገኖች ደግሞ ሊሆኑ ግድ ነውና።
፲፱ እንግዲህ አብራችሁ ስትሰበሰቡ የምትበሉት የጌታ
እራት አይደለም፤
፳፩ በመብላት ጊዜ እያንዳንዱ የራሱን እራት
ይበላልና፥ አንዱም ይራባል አንዱ ግን ይሰክራል።
፳፪ የምትበሉባቸውና የምትጠጡባቸው ቤቶች
የላችሁምን? ወይስ የእግዚአብሔርን ማኅበር
ትንቃላችሁን አንዳችም የሌላቸውን ታሳፍራላችሁን?
ምን ልበላችሁ? በዚህ ነገር ላመሰግናችሁን?
አላመሰግናችሁም።

፳፫ ለእናንተ ደግሞ አሳልፌ የሰጠሁትን እኔ ከጌታ
ተቀብያለሁና፤
፳፬ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት
እንጀራን አነሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም። እንካችሁ ብሉ፤
ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን
ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ።
፳፭ እንደዚሁም ከእራት በኋላ ጽዋውን ደግሞ
አነሥቶ። ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው፤
በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት
አለ።
፳፮ ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ፥ ይህንም ጽዋ
በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን
ትናገራላችሁና።
፳፯ ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም
የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ
አለበት።
፳፰ ሰው ግን ራሱን ይፈትን፥ እንዲሁም ከእንጀራው
ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ፤
፳፱ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ
ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና፥ ይጠጣልምና።
፴ ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ
ብዙዎች አሉ አያሌዎችም እንቀላፍተዋል።
፴፩ ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም
ነበር፤
፴፪ ነገር ግን በተፈረደብን ጊዜ ከዓለም ጋር
እንዳንኮነን በጌታ እንገሠጻለን።
፴፫ ስለዚህ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ ለመብላት
በተሰበሰባችሁ ጊዜ እርስ በርሳችሁ ተጠባበቁ።
፴፬ ማንም የራበው ቢኖር ለፍርድ እንዳትሰበሰቡ
በቤቱ ይብላ። የቀረውንም ነገር በመጣሁ ጊዜ
እደነግጋለሁ።

፲፪

፩ ስለ መንፈሳዊ ነገርም፥ ወንድሞች ሆይ፥ ታውቁ
ዘንድ እወዳለሁ።
፪ አሕዛብ ሳላችሁ በማናቸውም ጊዜ እንደምትመሩ
ድምፅ ወደሌላቸው ወደ ጣዖታት እንደ ተወሰዳችሁ
ታውቃላችሁ።
፫ ስለዚህ ማንም በእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር።
ኢየሱስ የተረገመ ነው የሚል እንደሌለ፥ በመንፈስ
ቅዱስም ካልሆነ በቀር። ኢየሱስ ጌታ ነው ሊል አንድ
እንኳ እንዳይችል አስታውቃችኋለሁ።
፬ የጸጋም ስጦታ ልዩ ልዩ ነው መንፈስ ግን አንድ
ነው፤
፭ አገልግሎትም ልዩ ልዩ ነው ጌታም አንድ ነው፤
፮ አሠራርም ልዩ ልዩ ነው፥ ሁሉን በሁሉ የሚያደርግ
እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።
፯ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ
ለጥቅም ይሰጠዋል።
፰ ለአንዱ ጥበብን መናገር በመንፈስ ይሰጠዋልና፥
ለአንዱም በዚያው መንፈስ እውቀትን መናገር
ይሰጠዋል፥
፱ ለአንዱም በዚያው መንፈስ እምነት፥ ለአንዱም
በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታ፥ ለአንዱም
ተአምራትን ማድረግ፥
፲ ለአንዱም ትንቢትን መናገር፥ ለአንዱም
መናፍስትን መለየት፥ ለአንዱም በልዩ ዓይነት ልሳን
መናገር፥ ለአንዱም በልሳኖች የተነገረውን መተርጎም
ይሰጠዋል፤
፲፩ ይህን ሁሉ ግን ያ አንዱ መንፈስ እንደሚፈቅድ
ለእያንዳንዱ ለብቻው እያካፈለ ያደርጋል።
፲፪ አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች
እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች
ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ፥ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ
ነው፤
፲፫ አይሁድ ብንሆን የግሪክ ሰዎችም ብንሆን
ባሪያዎችም ብንሆን ጨዋዎችም ብንሆን እኛ
ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን
ተጠምቀናልና። ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል።
፲፬ አካል ብዙ ብልቶች እንጂ አንድ ብልት
አይደለምና።
፲፭ እግር። እኔ እጅ አይደለሁምና የአካል ክፍል
አይደለሁም ብትል፥ ይህን በማለትዋ የአካል ክፍል
መሆንዋ ይቀራልን?
፲፮ ጆሮም። እኔ ዓይን አይደለሁምና የአካል ክፍል
አይደለሁም ቢል፥ ይህን በማለቱ የአካል ክፍል መሆኑ
ይቀራልን?
፲፯ አካል ሁሉ ዓይን ቢሆን መሰማት ወዴት በተገኘ?
ሁሉም መሰማት ቢሆን ማሽተት ወዴት በተገኘ?
፲፰ አሁን ግን እግዚአብሔር እንደ ወደደ ብልቶችን
እያንዳንዳቸው በአካል አድርጎአል።
፲፱ ሁሉም አንድ ብልት ቢሆንስ አካል ወዴት በሆነ?
፳ ዳሩ ግን አሁን ብልቶች ብዙዎች ናቸው አካል
ግን አንድ ነው።
፳፩ ዓይን እጅን። አታስፈልገኝም ልትለው አትችልም፥
ወይም ራስ ደግሞ እግሮችን። አታስፈልጉኝም ሊላቸው
አይችልም።
፳፪ ነገር ግን ደካሞች የሚመስሉ የአካል ብልቶች
ይልቁን የሚያስፈልጉ ናቸው፤
፳፫ ከአካልም ብልቶች ያልከበሩ ሆነው የሚመስሉን
በሚበዛ ክብር እናለብሳቸዋለን፥ በምናፍርባቸውም
ብልቶቻችን ክብር ይጨመርላቸዋል፤
፳፬-፳፭ አንድም ብልት ቢሣቀይ ብልቶች ሁሉ ከእርሱ
ጋር ይሣቀያሉ፤ አንድ ብልትም ቢከበር ብልቶች ሁሉ
ከእርሱ ጋር ደስ ይላቸዋል።
፳፯ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ
እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ።
፳፰ እግዚአብሔርም በቤተ ክርስቲያን አንዳንዶቹን
አስቀድሞ ሐዋርያትን፥ ሁለተኛም ነቢያትን፥
ሦስተኛም አስተማሪዎችን፥ ቀጥሎም ተአምራት
ማድረግን፥ ቀጥሎም የመፈወስን ስጦታ፥ እርዳታንም፥
አገዛዝንም፥ የልዩ ልዩ ዓይነት ልሳኖችንም አድርጎአል።
፳፱ ሁሉ ሐዋርያት ናቸውን? ሁሉስ ነቢያት ናቸውን?
ሁሉስ አስተማሪዎች ናቸውን? ሁሉስ ተአምራትን
ይሠራሉን?
፴ ሁሉስ የመፈወስ ስጦታ አላቸውን? ሁሉስ
በልሳኖች ይናገራሉን? ሁሉስ ይተረጉማሉን?
፴፩ ነገር ግን የሚበልጠውን የጸጋ ስጦታ
በብርቱ ፈልጉ። ደግሞም ከሁሉ የሚበልጥ መንገድ
አሳያችኋለሁ።

፲፫

፩ በሰዎችና በመላእክት ልሳን ብናገር ፍቅር ግን
ከሌለኝ እንደሚጮኽ ናስ ወይም እንደሚንሸዋሸዋ

ጸናጽል ሆኜአለሁ።
፪ ትንቢትም ቢኖረኝ ምሥጢርንም ሁሉና እውቀትን ሁሉ ባውቅ፥ ተራሮችንም እስካፈልስ ድረስ እምነት ሁሉ ቢኖረኝ ፍቅር ግን ከሌለኝ ከንቱ ነኝ።
፫ ድሆችንም ልመግብ ያለኝን ሁሉ ባካፍል፥ ሥጋዬንም ለእሳት መቃጠል አሳልፌ ብሰጥ ፍቅር ግን ከሌለኝ ምንም አይጠቅመኝም።
፬ ፍቅር ይታገሣል፥ ቸርነትንም ያደርጋል፤ ፍቅር አይቀናም፤ ፍቅር አይመካም፥ አይታበይም፤
፭ የማይገባውን አያደርግም፥ የራሱንም አይፈልግም፥ አይበሳጭም፥ በደልን አይቆጥርም፤
፮ ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤
፯ ሁሉን ይታገሣል፥ ሁሉን ያምናል፥ ሁሉን ተስፋ ያደርጋል፥ በሁሉ ይጸናል።
፰ ፍቅር ለዘወትር አይወድቅም፤ ትንቢት ቢሆን ግን ይሻራል፤ ልሳኖች ቢሆኑ ይቀራሉ፤ እውቀትም ቢሆን ይሻራል።
፱ ከእውቀት ከፍለን እናውቃለንና፥ ከትንቢትም ከፍለን እንናገራለንና፤
፲ ፍጹም የሆነ ሲመጣ ግን ተከፍሎ የነበረው ይሻራል።
፲፩ ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፥ እንደ ልጅም አሰብ ነበር፥ እንደ ልጅም እቈጥር ነበር፤ ጎልማሳ ሆኜ ግን የልጅነትን ጠባይ ሽሬአለሁ።
፲፪ ዛሬስ በመስተዋት በድንግዝግዝ እንደምናይ ነን በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን፤ ዛሬስ ከእውቀት ከፍዬ እውቃለሁ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ደግሞ እንደ ታወቅሁ እውቃለሁ።
፲፫ እንዲህም ከሆነ፥ እምነት ተስፋ ፍቅር እነዚህ ሦስቱ ጸንተው ይኖራሉ፤ ከእነዚህም የሚበልጠው ፍቅር ነው።

፲፬

፩ ፍቅርን ተከታተሉ፥ መንፈሳዊ ሰጦታንም ይልቁንም ትንቢት መናገርን በብርቱ ፈልጉ።
፪ በልሳን የሚናገርስ ለእግዚአብሔር እንጂ ለሰው አይናገርም፤ የሚያሰተውለው የለምና፥ በመንፈስ ግን ምሥጢርን ይናገራል፤
፫ ትንቢትን የሚናገር ግን ለማነጽና ለመምከር ለማጽናናትም ለሰው ይናገራል።
፬ በልሳን የሚናገር ራሱን ያንጻል፤ ትንቢትን የሚናገር ግን ማኅበሩን ያንጻል።
፭ ሁላችሁ በልሳኖች ልትናገሩ እወድ ነበር፥ ትንቢትን ልትናገሩ ግን ከዚህ ይልቅ እወዳለሁ፤ ማኅበሩ ይታነጽ ዘንድ ንግግሩን ባይተረጕም በልሳኖች ከሚናገር ትንቢትን የሚናገር ይበልጣል።
፮ አሁን ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ወደ እናንተ መጥቼ በልሳኖች ብናገር፥ በመግለጥ ወይም በእውቀት ወይም በትንቢት ወይም በትምህርት ካልነገርኋችሁ ምን እጠቅማችኋለሁ?
፯ ነፍስ የሌለበት ነገር እንኳ ዋሽንትም ክራርም ቢሆን ድምፅ ሲሰጥ የድምፁን ልዩነት ባይገልጥ በዋሽንት የሚነፋው ወይስ በክራር የሚመታው መዝሙር እንዴት ይታወቃል?
፰ ደግሞም መለከት የማይገለጥን ድምፅ ቢሰጥ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል?
፱ እንዲሁ እናንተ ደግሞ የተገለጠውን ቃል በአንደበት ባትናገሩ ሰዎች የምትናገሩትን እንዴት አድርገው ያስተውሉታል? ለነፋስ የምትናገሩ ትሆናላችሁና።
፲ በዓለም ምናልባት ቁጥር የሌለው የቋንቋ ዓይነት ይኖራል ቋንቋም የሌለው ሕዝብ የለም፤
፲፩ እንግዲህ የቋንቋውን ፍች ባላውቅ ለሚናገረው እንግዳ እሆናለሁ፥ የሚናገረውም ለእኔ እንግዳ ይሆናል።
፲፪ እንዲሁ ደግሞ እናንተ መንፈሳዊ ሰጦታን በብርቱ የምትፈልጉ ከሆናችሁ ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ እንዲበዛላችሁ ፈልጉ።
፲፫ ስለዚህ በልሳን የሚናገር እንዲተረጕም ይጸልይ።
፲፬ በልሳን ብጸልይ መንፈሴ ይጸልያል እእምሮዬ ግን ያለ ፍሬ ነው።
፲፭ እንግዲህ ምንድር ነው? በመንፈስ እጸልያለሁ በእእምሮም ደግሞ እጸልያለሁ፤ በመንፈስ እዘምራለሁ በእእምሮም ደግሞ እዘምራለሁ።
፲፮ እንዲያማ ካልሆነ፥ አንተ በመንፈስ ብትባርክ ባልተማሩት ሰፍራ የተቀመጠው የምትለውን ካላወቀ እንዴት አድርጎ ለምስጋናህ አሜን ይላል?
፲፯ አንተማ መልካም ታመሰግናለህ፥ ሌላው ግን አይታነጽበትም።
፲፰ ከሁላችሁ ይልቅ በልሳኖች እናገራለሁና እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤
፲፱ ነገር ግን ሌሎችን ደግሞ አስተምር ዘንድ በማኅበር እልፍ ቃላት በልሳን ከመናገር ይልቅ አምስት ቃላት በአእምሮዬ ልናገር እወዳለሁ።
፳ ወንድሞች ሆይ፥ በአእምሮ ሕፃናት አትሁኑ፤ ለክፋት ነገር ሕፃናት ሁኑ እንጂ በአእምሮ የበሰሉ ሁኑ።
፳፩ ሌሎችን ልሳኖች በሚናገሩ ሰዎችና በሌላ አንደበት ለዚህ ሕዝብ እነግራቸዋለሁ፥ እንዲህም ቢሆን አይሰሙኝም ይላል ጌታ ተብሎ በሕግ ተጽፎአል።
፳፪ እንግዲያስ በልሳኖች መናገር ለማያምኑ ምልክት ነው እንጂ ለሚያምኑ አይደለም፥ ትንቢት ግን ለሚያምኑ እንጂ ለማያምኑ አይደለም።
፳፫ እንግዲህ ማኅበር ሁሉ አብረው ቢሰበሰቡ ሁሉም በልሳኖች ቢናገሩና ያልተማሩ ወይም የማያምኑ ሰዎች ቢገቡ። አብደዋል አይሉምን?
፳፬ ሁሉ ትንቢት ቢናገሩ ግን የማያምን ወይም ያልተማረ ሰው ቢገባ በሁሉ ይወቀሳል፥ በሁሉም ይመረመራል፤
፳፭ በልቡም የተሰወረ ይገለጣል እንዲሁም። እግዚአብሔር በእውነት በመካከላቸው ነው ብሎ እየተናገረ በፊቱ ወድቆ ለእግዚአብሔር ይሰግዳል።
፳፮ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ምንድር ነው? በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለእያንዳንዱ መዝሙር አለው፥ ትምህርት አለው፥ መግለጥ አለው፥ በልሳን መናገር አለው፥ መተርጐም አለው፤ ሁሉ ለማነጽ ይሁን።
፳፯ በልሳን የሚናገር ቢኖር ሁለት ወይም ቢበዛ ሦስት ሆነው በተራቸው ይናገሩ አንዱም ይተርጕም፤
፳፰ የሚተረጕም ባይኖር ግን በማኅበር መካከል ዝም ይበልና ለራሱና ለእግዚአብሔር ይናገር።

፳፪ ነቢያትም ሁለት ወይም ሦስት ሆነው ይናገሩ
ሌሎችም ይለዩአቸው፤
፳፫ በዚያ ለሚቀመጥ ለሌላ ግን እንድ ነገር
ቢገለጥለት ፊተኛው ዝም ይበል።
፳፬ ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ ሁላችሁ
በእያንዳንዳችሁ ትንቢት ልትናገሩ ትችላላችሁ።
፳፭ የነቢያትም መናፍስት ለነቢያት ይገዛሉ፤
፳፮ እግዚአብሔርስ የሰላም አምላክ ነው እንጂ
የሁከት አምላክ አይደለምና፤ በቅዱሳንም አብያተ
ክርስቲያናት ሁሉ እንዲህ ነው።
፳፯ ሴቶች በማኅበር ዝም ይበሉ፤ ሕግ
ደግሞ እንደሚል እንዲገዙ እንጂ እንዲናገሩ
አልተፈቀደላቸውምና።
፳፰ ለሴት በማኅበር መካከል መናገር ነውር
ነውና፥ ምንም ሊማሩ ቢወዱ በቤታቸው ባሎቻቸውን
ይጠይቁ።
፳፱ ምን ነው? የእግዚአብሔር ቃል የወጣ ከእናንተ
ነውን? ወይስ ወደ እናንተ ብቻ ደርሶአልን?
፴ ማንም ነቢይ ወይም መንፈሳዊ የሆነ ቢመስለው
ይህች የጻፍሁላችሁ የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነች ይወቅ፤
፴፩ ማንም የማያውቅ ቢኖር ግን አይወቅ።
፴፪ ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ትንቢት ለመናገር
በብርቱ ፈልጉ፥ በልሳኖች ከመናገርም አትከልክሉ፤
፴፫ ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን።

፲፭

፩ ወንድሞች ሆይ፥ የሰበክሁላችሁን ደግሞም
የተቀበላችሁትን በእርሱም ደግሞ የቆማችሁበትን
በእርሱም ደግሞ የምትድኑበትን ወንጌል
አሳስባችኋለሁ፤
፪ በከንቱ ካላመናችሁ በቀር፥ ብታሰቡት፥ በምን
ቃል እንደ ሰበክሁላችሁ አሳስባችኋለሁ።
፫ እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ
ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ። መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ
ስለ ኃጢአታችን ሞተ፥ ተቀበረም፥
፬ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ፥
፭ ለኬፋም ታየ በኋላም ለአሥራ ሁለቱ፤
፮ ከዚያም በኋላ ከአምስት መቶ ለሚበዙ
ወንድሞች በአንድ ጊዜ ታየ፤ ከእነርሱም የሚበዙቱ
እስከ አሁን አሉ አንዳንዶች ግን አንቀላፍተዋል፤
፯ ከዚያም በኋላ ለያዕቆብ ኋላም ለሐዋርያት ሁሉ
ታየ፤
፰ ከሁሉም በኋላ እንደ ጭንጋፍ ለምሆን ለእኔ
ደግሞ ታየኝ።
፱ እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝና፥
የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ስላሳደድሁ ሐዋርያ
ተብዬ ልጠራ የማይገባኝ፤
፲ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ የሆንሁ እኔ ነኝ፤
ለእኔም የተሰጠኝ ጸጋው ከንቱ አልነበረም ከሁላቸው
ይልቅ ግን ደከምሁ፥ ዳሩ ግን ከእኔ ጋር ያለው
የእግዚአብሔር ጸጋ ነው እንጂ እኔ አይደለሁም።
፲፩ እንግዲህስ እኔ ብሆን እነርሱም ቢሆኑ እንዲሁ
እንሰብካለን እንዲሁም አመናችሁ።
፲፪ ክርስቶስ ከሙታን እንደ ተነሣ የሚሰበክ ከሆነ
ግን ከእናንተ አንዳንዶቹ። ትንሣኤ ሙታን የለም እንዴት
ይላሉ?
፲፫ ትንሣኤ ሙታንስ ከሌለ ክርስቶስ አልተነሣማ፤
፲፬ ክርስቶስም ካልተነሣ እንግዲያስ ሰብከታችን
ከንቱ ነው እምነታችሁም ደግሞ ከንቱ ናት፤
፲፭ ደግሞም። ክርስቶስን አስነሥቶታል ብለን
በእግዚአብሔር ላይ ሰለ መስከርን ሐሰተኞች
የእግዚአብሔር ምስክሮች ሆነን ተገኝተናል፤ ሙታን
ግን የማይነሡ ከሆነ እርሱን አላስነሣውም።
፲፮ ሙታን የማይነሡ ከሆነ ክርስቶስ አልተነሣማ፤
፲፯ ክርስቶስም ካልተነሣ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤
እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ አላችሁ።
፲፰ እንግዲያስ በክርስቶስ ያንቀላፉት ደግሞ
ጠፍተዋላ።
፲፱ በዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን
ከሆነ፥ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን።
፳ አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ
ከሙታን ተነሥቶአል።
፳፩ ሞት በሰው በኩል ሰለ መጣ ትንሣኤ ሙታን
በሰው በኩል ሆኖአልና።
፳፪ ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ
በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና።
፳፫ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤
ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፥ በኋላም በመምጣቱ
ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው፤
፳፬ በኋላም፥ መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ
አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትንም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ
ኃይልንም በሻረ ጊዜ፥ ፍጻሜ ይሆናል።
፳፭ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ በታች እስኪያደርግ ድረስ
ሊነግሥ ይገባዋልና።
፳፮ የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤
፳፯ ሁሉን ከእግሩ በታች እስገዝቶአልና። ነገር ግን።
ሁሉ ተገዝቶአል ሲል፥ ሁሉን ካስገዛለት በቀር መሆኑ
ግልጥ ነው።
፳፰ ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ
በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ
ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።
፳፱ እንዲያማ ካልሆነ፥ ሰለ ሙታን የሚጠመቁ ምን
ያደርጋሉ? ሙታንስ ከቶ የማይነሡ ከሆነ፥ ሰለ እነርሱ
የሚጠመቁ ሰለ ምንድር ነው?
፴ እኛስ ዘወትር በሚያሰፈራ ኑሮ የምንኖር ሰለ
ምንድር ነው?
፴፩ በጌታችን በክርስቶስ ኢየሱስ ባለኝ በእናንተ
ትምክህት እየማልሁ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ዕለት ዕለት
እሞታለሁ።
፴፪ እንደ ሰው በኤፌሶን ከአውሬ ጋር ከታገልሁ፥
ሙታንስ የማይነሡ ከሆነ፥ ምን ይጠቅመኛል? ነገ
እንሞታለንና እንብላና እንጠጣ።
፴፫ አትሳቱ፤ ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል
ያጠፋል።
፴፬ በጽድቅ ንቁ ኃጢአትንም አትሥሩ፤
እግዚአብሔርን የማያውቁ አሉና፤ አሳፍራችሁ ዘንድ
ይህን እላለሁ።
፴፭ ነገር ግን ሰው። ሙታን እንዴት ይነሣሉ?
በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር
ይሆናል።
፴፮ አንተ ሞኝ፥ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው
እይሆንም፤

፶፯ የምትዘራውም፥ ሰንዴ ቢሆን ከሌላም ዓይነት የእንዱ ቢሆን፥ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም፤

፶፰ እግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል ከዘሮችም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል።

፶፱ ሥጋ ሁሉ አንድ አይደለም፥ የሰው ሥጋ ግን አንድ ነው፥ የእንሰሳም ሥጋ ሌላ ነው፥ የወፎችም ሥጋ ሌላ ነው፥ የዓሣም ሥጋ ሌላ ነው።

፷ ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ፥ ምድራዊም አካል አለ፤ ነገር ግን የሰማያዊ አካል ክብር ልዩ ነው፥ የምድራዊም አካል ክብር ልዩ ነው።

፷፩ የፀሐይ ክብር አንድ ነው የጨረቃም ክብር ሌላ ነው የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው፤ በክብር እንዱ ኮከብ ከሌላው ኮከብ ይለያልና።

፷፪ የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፥ ባለመበስበስ ይነሣል፤

፷፫ በውርደት ይዘራል፥ በክብር ይነሣል፤ በድካም ይዘራል፥ በኃይል ይነሣል፤

፷፬ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፥ መንፈሳዊ አካል ይነሣል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ።

፷፭ እንዲሁ ደግሞ። ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ ተብሎ ተጽፎአል፤ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ።

፷፮ ነገር ግን አሰቀድሞ ፍጥረታዊው ቀጥሎም መንፈሳዊው ነው እንጂ መንፈሳዊው መጀመሪያ አይደለም።

፷፯ የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው።

፷፰ መሬታዊው እንደ ሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው፥ ሰማያዊው እንደ ሆነ ሰማያውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው።

፷፱ የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደ ለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን።

፸ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህን እላለሁ። ሥጋና ደም የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊወርሱ አይችሉም፥ የሚበሰብሰውም የማይበሰብሰውን አይወርስም።

፸፩-፸፫ ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊለብስ ይገባዋልና።

፸፬ ዳሩ ግን ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሲለብስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሲለብስ፥ በዚያን ጊዜ። ሞት ድል በመነሣት ተዋጠ ተብሎ የተጻፈው ቃል ይፈጸማል።

፸፭ ሞት ሆይ፥ መውጊያህ የት አለ? ሲኦል ሆይ፥ ድል መነሣትህ የት አለ?

፸፮ የሞት መውጊያ ኃጢአት ነው የኃጢአትም ኃይል ሕግ ነው፤

፸፯ ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መነሣትን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን።

፸፰ ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ድካማችሁ በጌታ ከንቱ እንዳይሆን አውቃችኋልና የምትደላደሉ፥ የማትነቃነቁም፥ የጌታም ሥራ ሁልጊዜ የሚበዛላችሁ ሁኑ።

፲፮

፩ ለቅዱሳንም ገንዘብን ሰለ ማዋጣት፥ ለገላትያ አብያተ ክርስቲያናት እንደ ደነገግሁት እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።

፪ እኔ ሰመጣ ይህ የገንዘብ ማዋጣት ያን ጊዜ እንዳይሆን፥ ከእናንተ እያንዳንዱ በየሳምንቱ በፊተኛው ቀን እንደ ቀናው መጠን እያሰቀረ በቤቱ ያሰቀምጥ።

፫ ሰመጣም ማናቸውም ቢሆኑ የታመኑ የሚመሰሉአችሁ ሰዎች ቸርነታችሁን ወደ ኢየሩሳሌም ያደርሱ ዘንድ ደብዳቤ ሰጥቼ እልካቸዋለሁ፤

፬ እኔ ደግሞ ልሄድ የሚገባኝ ብሆን ከእኔ ጋር አብረው ይሄዳሉ።

፭ በመቄዶንያም ሳልፍ ወደ እናንተ እመጣለሁ፤ በመቄዶንያ አድርጌ አልፋለሁና፤

፮ እናንተም ወደምሄድበት ወደ ማናቸውም ሰፍራ በጉዞዬ እንድትረዱኝ ምናልባት በእናንተ ዘንድ እቆይ ወይም እከርም ይሆናል።

፯ አሁን እግረ መንገዴን ሳልፍ ልጎበኛችሁ አልወድምና፤ ጌታ ቢፈቅደው የሆነውን ዘመን በእናንተ ዘንድ ልሰነብት ተሰፋ አደርጋለሁና።

፰ በኤፌሶን ግን እስከ በዓለ ኀምሳ ድረስ እሰነብታለሁ።

፱ ሥራ የሞላበት ትልቅ በር ተከፍቶልኛልና ተቃዋሚዎችም ብዙ ናቸው።

፲ ጢሞቴዎስም የመጣ እንደ ሆነ በእናንተ ዘንድ ያለ ፍርሃት እንዲኖር ተጠንቀቁ፤ እንደ እኔ ደግሞ የጌታን ሥራ ይሠራልና፤ እንግዲህ ማንም አይናቀው።

፲፩ ነገር ግን ከወንድሞቹ ጋር እጠብቀዋለሁና ወደ እኔ ይመጣ ዘንድ በሰላም በጉዞው እርዱት።

፲፪ ሰለ ወንድማችን ሰለ አጵሎስ ግን ከወንድሞቹ ጋር ወደ እናንተ ሊሄድ እጅግ አድርጌ ለምኜው ነበር፤ ዛሬም ለመምጣት ከቶ ፈቃድ አልነበረውም፥ ሲመቸው ግን ይመጣል።

፲፫ ንቁ፥ በሃይማኖት ቁሙ፥ ጎልምሱ ጠንክሩ።

፲፬ በእናንተ ዘንድ ሁሉ በፍቅር ይሁን።

፲፭ ወንድሞች ሆይ፥ የእስጢፋኖስ ቤተ ሰዎች የአካይያ በኩራት እንደ ሆኑ ቅዱሳንንም ለማገልገል ራሳቸውን እንደ ሰጡ ታውቃላችሁ፤

፲፮ እንደ እነርሱ ላሉትና አብሮ ለሚሠራ ለሚደክምም ሁሉ እናንተም እንድትገዙ እለምናችኋለሁ።

፲፯ በእስጢፋኖስና በፈርዶናጥስ በአካይቆስም መምጣት ደስ ይለኛል፥ እናንተ ሰለሌላችሁ የጎደለኝን ፈጽመዋልና፤ መንፈሴንና መንፈሳችሁን አሳርፈዋልና።

፲፰ እንግዲህ እንደነዚህ ያሉትን እወቁአቸው።

፲፱ የእስያ አብያተ ክርስቲያናት ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። አቂላና ጵርስቅላ በቤታቸው ካለች ቤተ ክርስቲያን ጋር በጌታ እጅግ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።

፳ ወንድሞች ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል። በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።

፳፩ እኔ ጳውሎስ ይህን ሰላምታ በገዛ እጄ ጽፌአለሁ።

፳፪ ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን የማይወድ ቢኖር የተረገመ ይሁን። ጌታችን ሆይ፥ ና።

፳፫ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።
፳፬ ፍቅሬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሁላችሁ ጋር ነው። አሜን።

2ኛ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ
የሆነ ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ፥ በአካይያ አገር
ሁሉ ከሚኖሩ ቅዱሳን ሁሉ ጋር በቆሮንቶስ ላለች
ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን፤
፪ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፫ የርኅራኄ አባት የመጽናናትም ሁሉ አምላክ የሆነ
የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት ይባረክ።
፬ እርሱ በመከራችን ሁሉ ያጽናናናል፥ ሰለዚህም
እኛ ራሳችን በእግዚአብሔር በምንጽናናበት መጽናናት
በመከራ ሁሉ ያሉትን ማጽናናት እንችላለን።
፭ የክርስቶስ ሥቃይ በእኛ ላይ እንደ በዛ፥ እንዲሁ
መጽናናታችን ደግሞ በክርስቶስ በኩል ይበዛልናልና።
፮ ዳሩ ግን መከራ ብንቀበል፥ ሰለ መጽናናታችሁና
ሰለ መዳናችሁ ነው፤ ብንጽናናም፥ እኛ ደግሞ
የምንሣቀይበት በዚያ ሥቃይ በመጽናት ሰለሚደረግ
ሰለ መጽናናታችሁ ነው።
፯ ተሰፋችንም ሰለ እናንተ ጽኑ ነው፤ ሥቃያችንን
እንደ ተካፈላችሁ እንዲሁም መጽናናታችንን ደግሞ
እንድትካፈሉ እናውቃለንና።
፰ በእሰያ ሰለ ደረሰብን መከራችን፥ ወንድሞች ሆይ፥
ታውቁ ዘንድ እንወዳለንና፤ ሰለ ሕይወታችን እንኳ
ተስፋ እስክንቆርጥ ድረስ ከኅቅማችን በላይ ያለ ልክ
ከብዶብን ነበር፤
፱ እዎን፥ ሙታንን በሚያነሣ በእግዚአብሔር እንጂ
በራሳችን እንዳንታመን፥ እኛ ራሳችን የሞትን ፍርድ
በውስጣችን ሰምተን ነበር።
፲-፲፩ ትምክህታችን ይህ ነውና፤ በእግዚአብሔር
ጸጋ እንጂ በሥጋዊ ጥበብ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር
ቅድሰናና ቅንነት በዚህ ዓለም ይልቁንም በእናንተ ዘንድ
እንደኖርን የሕሊናችን ምስክርነት ነው።
፲፫-፲፭ በዚህም ታምኜ፥ ሁለተኛ ጸጋ ታገኙ ዘንድ
አስቀድሜ ወደ እናንተ እንድመጣ፥
፲፮ በእናንተም መካከል ወደ መቄዶንያ እንዳልፍ
ደግሞም ከመቄዶንያ ወደ እናንተ መጥቼ ወደ ይሁዳ
በጉዞዬ እንድትረዱኝ አሰብሁ።
፲፯ እንግዲህ ይህን ሳሰብ ያን ጊዜ ቅሌትን አሳየሁን?
ወይስ በእኔ ዘንድ እዎን እዎን እይደለም አይደለም
ማለት እንዲሆን ያን የማሰበው በዓለማዊ ልማድ
ነውን?
፲፰ እግዚአብሔር ግን የታመነ ነው፥ ለእናንተም
የሚነገረው ቃላችን እዎንና አይደለም አይሆንም።
፲፱ በእኛ ማለት በእኔና በሰልዋኖስ በጢሞቴዎስም
በመካከላችሁ የተሰበከ የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ
ክርስቶስ እዎንና አይደለም አልነበረም፥ ነገር ግን
በእርሱ እዎን ሆኖአል።
፳ እግዚአብሔር ለሰጠው የተሰፋ ቃል ሁሉ እዎን
ማለት በእርሱ ነውና፥ ሰለዚህ ለእግዚአብሔር ሰለ
ክብሩ በእኛ የሚነገረው አሜን በእርሱ ደግሞ ነው።
፳፩ በክርስቶስም ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን
እግዚአብሔር ነው፥
፳፪ ደግሞም ያተመን የመንፈሱንም መያዣ በልባችን
የሰጠን እርሱ ነው።
፳፫ እኔ ግን ልራራላችሁ ሰል እንደ ገና ወደ ቆሮንቶስ
እንዳልመጣሁ በነፍሴ ላይ እግዚአብሔርን ምስክር
እጠራለሁ።
፳፬ ለደስታችሁ ከእናንተ ጋር የምንሠራ ነን እንጂ፥
በእምነታችሁ በእናንተ ላይ የምንገዛ አይደለንም።
በእምነታችሁ ቆማችኋልና።

፪

፩ ነገር ግን ዳግመኛ በኀዘን ወደ እናንተ እንዳልመጣ
ሰለ እኔ ቆረጥሁ።
፪ እኔስ ባሳዝናችሁ፥ እንግዲያስ በእኔ ምክንያት
ከሚያዝን በቀር ደስ የሚያሰኘኝ ማን ነው?
፫ ደስ ሊያሰኙኝ ከሚገባቸውም በመምጣቴ ኀዘን
እንዳይሆንብኝ ይህንኑ ጻፍሁላችሁ፥ ደስታዬ የሁላችሁ
ደስታ ነው ብዬ በሁላችሁ ታምኜአለሁና።
፬ በብዙ መከራና ከልብ ጭንቀት በብዙም
እንባ ጽፌላችሁ ነበርና፤ ይህም እናንተን አብዝቼ
የምወድበትን ፍቅር እንድታውቁ እንጂ እንዳሳዝናችሁ
አይደለም።
፭ ነገር ግን ማንም አሳዝኖ ቢሆን፥
እንዳልከብድባችሁ፥ በክፍል ሁላችሁን እንጂ እኔን
ያሳዘነ አይደለም።
፮ እንደዚህ ላለ ሰው ይህ ከእናንተ የምትበዙት
የቀጣችሁት ቅጣት ይበቃዋልና እንደዚህ ያለው ከልክ
በሚበዛ ኀዘን እንዳይዋጥ፥
፯ ይልቅ ተመልሳችሁ ይቅር ማለትና ማጽናናት
ይገባችኋል።
፰ ሰለዚህ ከእርሱ ጋር ፍቅርን እንድታጸኑ
እለምናችኋለሁ፤
፱ ሰለዚህ ደግሞ ጽፌ ነበርና፤ በሁሉ የምትታዘዙ
እንደ ሆናችሁ የእናንተን መፈተን አውቅ ዘንድ አሳቤ
ነበር።
፲ እናንተ ግን ይቅር የምትሉትን እኔ ደግሞ ይቅር
እለዋለሁ፤ እኔም ይቅር ካልሁ፥ ይቅር ያልሁትን ሰለ
እናንተ በክርስቶስ ፊት ይቅር ብዬአለሁ፥
፲፩ በሰይጣን እንዳንታለል፤ የእርሱን አሳብ
አንስተውምና።
፲፪ ሰለ ክርስቶስም ወንጌል ወደ ጢሮአዳ
በመጣሁ ጊዜ፥ ለጌታ ሥራ በር ምንም ቢከፈትልኝ፥
ቲቶን ወንድሜን ሰላላገኘሁት መንፈሴ ዕረፍት
አልነበረውም፥
፲፫ ነገር ግን ከእነርሱ ተሰናብቼ ወደ መቄዶንያ
ወጣሁ።
፲፬ ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ ድል በመንሣቱ
ለሚያዞረን በእኛም በየሰፍራው ሁሉ የእውቀቱን ሽታ
ለሚገልጥ ለእምላክ ምስጋና ይሁን፤
፲፭ በሚድኑቱና በሚጠፉቱ ዘንድ ለእግዚአብሔር
የክርስቶስ መዓዛ ነንና፤
፲፮ ለእነዚህ ለሞት የሚሆን የሞት ሽታ ለእነዚያም
ለሕይወት የሚሆን የሕይወት ሽታ ነን። ለዚህም ነገር
የሚበቃ ማን ነው?
፲፯ የእግዚአብሔርን ቃል ቀላቅለው እንደሚሸቃቅጡት
እንደ ብዙዎቹ እይደለንምና፤ በቅንነት ግን
ከእግዚአብሔር እንደ ተላክን በእግዚአብሔር ፊት
በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን።

፫

፩ እንደ ገና ራሳችንን ልናመሰግን እንጀምራለንን? ወይስ እንደ ሌሎች የማመሰገኛ መልእክት ወደ እናንተ ወይስ ከእናንተ ያስፈልገን ይሆንን?
፪ ሰዋች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልእክታችን እናንተ ናችሁ።
፫ እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው።
፬ በክርስቶስም በኩል ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ያለ እምነት አለን።
፭ ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤
፮ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።
፯ ዳሩ ግን የእስራኤል ልጆች ስለዚያ ስለ ተሻረው ስለ ፊቱ ክብር የሙሴን ፊት ትኩር ብለው መመልከት እስኪሳናቸው ድረስ፥ ያ በፊደላት በድንጋዮች ላይ የተቀረጸ የሞት አገልግሎት በክብር ከሆነ፥
፰ የመንፈስ አገልግሎት እንዴት ይልቅ በክብር አይሆንም?
፱ የኵነኔ አገልግሎት ክብር ከሆነ፥ ይልቅ የጽድቅ አገልግሎት በክብር አብዝቶ ይበልጣልና።
፲ ያ የከበረ እንኳ እጅግ በሚበልጠው ክብር ምክንያት በዚህ ነገር ክብሩን አጥቶአልና።
፲፩ ያ ይሻር የነበረው በክብር ከሆነ፥ ጸንቶ የሚኖረውማ እጅግ ይልቅ በክብር ሆኖአልና።
፲፪ እንግዲህ እንዲህ ያለ ተስፋ ካለን እጅግ ገልጠን እንናገራለን፥
፲፫ የዚያንም ይሻር የነበረውን መጨረሻ ትኩር ብለው የእስራኤል ልጆች እንዳይመለከቱ፥ በፊቱ መጋረጃ እንዳደረገ እንደ ሙሴ አይደለንም።
፲፬ ነገር ግን አሳባቸው ደነዘዘ። ብሉይ ኪዳን ሲነበብ ያ መጋረጃ ሳይወሰድ እስከ ዛሬ ድረስ ይኖራልና፤ በክርስቶስ ብቻ የተሻረ ነውና።
፲፭ ነገር ግን እስከ ዛሬ ድረስ የሙሴ መጻሕፍት በተነበቡ ጊዜ ሁሉ ያ መጋረጃ በልባቸው ይኖራል፤
፲፮ ወደ ጌታ ግን ዘወር ባለ ጊዜ ሁሉ መጋረጃው ይወሰዳል።
፲፯ ጌታ ግን መንፈስ ነው፤ የጌታም መንፈስ ባለበት በዚያ አርነት አለ።
፲፰ እኛም ሁላችን በመጋረጃ በማይከደን ፊት የጌታን ክብር እንደ መስተዋት እያብለጨለጭን መንፈስ ከሚሆን ጌታ እንደሚደረግ ያን መልክ እንመሰል ዘንድ ከክብር ወደ ክብር እንለወጣለን።

፬

፩ ስለዚህ ምክንያት ምሕረት እንደ ተሰጠን መጠን ይህ አገልግሎት ስላለን አንታክትም።
፪ ነገር ግን የሚያሳፍረውን ሰውር ነገር ጥለናልና በተንኮል አንመላለስም የእግዚአብሔርንም ቃል በውሸት አንቀላቅልም፤ እውነትን በመግለጥ ግን በእግዚአብሔር ፊት ለሰው ሕሊና ሁሉ ራሳችንን እናመሰግናለን።
፫ ወንጌላችን የተከደነ ቢሆን እንኳ የተከደነባቸው ለሚጠፉ ነው።
፬ ለእነርሱም የእግዚአብሔር ምሳሌ የሆነ የክርስቶስ የክብሩ ወንጌል ብርሃን እንዳያበራላቸው፥ የዚህ ዓለም አምላክ የማያምኑትን አሳብ አሳወረ።
፭ ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታ እንደ ሆነ እንጂ ራሳችንን እንሰብክምና፥ ስለ ኢየሱስም ራሳችንን ለእናንተ ባሪያዎች እናደርጋለን።
፮ በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ። በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።
፯ ነገር ግን የኃይሉ ታላቅነት ከእግዚአብሔር እንጂ ከእኛ እንዳይሆን ይህ መዝገብ በሸክላ ዕቃ ውስጥ አለን፤
፰ በሁሉ እንገፋለን እንጂ አንጨነቅም፤ እናመነታለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም፤
፱ እንሰደዳለን እንጂ አንጣልም፤ እንወድቃለን እንጂ አንጠፋም፤
፲ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሥጋችን ይገለጥ ዘንድ ሁልጊዜ የኢየሱስን መሞት በሥጋችን ተሸክመን እንዞራለን።
፲፩ የኢየሱስ ሕይወት ደግሞ በሚሞት ሥጋችን ይገለጥ ዘንድ እኛ ሕያዋን የሆንን ከኢየሱስ የተነሣ ዘወትር ለሞት አልፈን እንሰጣለንና።
፲፪ ስለዚህ ሞቱ በእኛ ሕይወቱም በእናንተ ይሠራል።
፲፫ ነገር ግን። አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ ተብሎ እንደ ተጻፈ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን፥ እኛ ደግሞ እናምናለን ስለዚህም እንናገራለን፤
፲፬ ጌታን ኢየሱስን ያስነሣው እኛን ደግሞ ከኢየሱስ ጋር እንዲያስነሣን ከእናንተም ጋር እንዲያቀርበን እናውቃለንና።
፲፭ በብዙዎች በኩል የተትረፈረፈው ጸጋ ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋናን ያበዛ ዘንድ፥ ሁሉ ስለ እናንተ ነውና።
፲፮-፲፰ ስለዚህም አንታክትም፥ ነገር ግን የውጭው ሰውነታችን ቢጠፋ እንኳ የውስጡ ሰውነታችን ዕለት ዕለት ይታደሳል።

፭

፩ ድንኳን የሚሆነው ምድራዊ መኖሪያችን ቢፈርስ፥ በሰማይ ያለ በእጅ ያልተሠራ የዘላለም ቤት የሚሆን ከእግዚአብሔር የተሠራ ሕንጻ እንዳለን እናውቃለንና።
፪ በዚህ ውስጥ በእውነት እንቃትታለንና፥
፫ ከሰማይም የሚሆነውን መኖሪያችንን እንድንለብስ እንናፍቃለንና ለብሰን ራቁታችንን አንገኝም።
፬ በእውነትም የሚሞተው በሕይወት ይዋጥ ዘንድ ልንለብስ እንጂ ልንገፈፍ የሚንወድ ስለ ሆነ፥ በድንኳኑ ያለን እኛ ከብደን እንቃትታለን።
፭ ነገር ግን ለዚሁ የሠራን እግዚአብሔር ነው እርሱም የመንፈሱን መያዣ ሰጠን።
፮-፰ ታምነናል ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በሰደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል።
፱ ስለዚህ ደግሞ ብናድር ወይም ተለይተን ብንሆን እርሱን ደስ የምናሰኝ ልንሆን እንቀናለን።

፲ መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ፥ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።

፲፩ እንግዲህ የጌታን ፍርሃት እውቀን ሰዎችን እናሰረዳለን ለእግዚአብሔር ግን የተገለጥን ነን፤ በሕሊናችሁም ደግሞ የተገለጥን እንደ ሆንን ተስፋ አደርጋለሁ።

፲፪ በመልክ እንጂ በልብ ለማይመኩ የሞትመልሱላቸው መልስ እንዲኖራችሁ፥ በእኛ ልትመኩ ምክንያት እንሰጣችኋለን እንጂ ራሳችንን ደግሞ ለእናንተ የምናመሰግን አይደለንም።

፲፫ እብዶች ብንሆን፥ ለእግዚአብሔር ነው፤ ባለ እእምሮዎች ብንሆን፥ ለእናንተ ነው።

፲፬ ይህን ሰለቆረጥን የክርስቶስ ፍቅር ግድ ይለናልና፤ እንዱ ሰለ ሁሉ ሞተ፤ እንግዲያስ ሁሉ ሞቱ፤

፲፭ በሕይወትም ያሉት ሰለ እነርሱ ለሞተውና ለተነሣው እንጂ ወደ ፊት ለራሳቸው እንዳይኖሩ ሰለ ሁሉ ሞተ።

፲፮ ሰለዚህ እኛ ከአሁን ጀምሮ ማንንም በሥጋ እንደሚሆን እናውቅም፤ ክርስቶስንም በሥጋ እንደ ሆነ ያወቅነው ብንሆን እንኳ፥ አሁን ግን ከእንግዲህ ወዲህ እንደዚህ አናውቀውም።

፲፯ ሰለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።

፲፰ ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤

፲፱ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ።

፳ እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ሰለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ሰለ ክርስቶስ እንለምናለን።

፳፩ እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ሰለ እኛ ኃጢአት አደረገው።

፮

፩ አብረንም እየሠራን የእግዚአብሔርን ጸጋ በከንቱ እንዳትቀበሉ ደግሞ እንለምናለን፤

፪ በተወደደ ሰዓት ሰማሁህ በመዳንም ቀን ረዳሁህ ይላልና፤ እነሆ፥ የተወደደው ሰዓት አሁን ነው፤ እነሆ፥ የመዳን ቀን አሁን ነው።

፫ አገልግሎታችንም እንዳይነቀፍ በእንዳች ነገር ማሰናከያ ከቶ እንሰጥም።

፬ ነገር ግን በሁሉ እንደ እግዚአብሔር አገልጋዮች ራሳችንን እናማጥናለን፤

፭ በብዙ መጽናት፥ በመከራ፥ በችግር፥ በጭንቀት፥ በመገረፍ፥ በወኅኒ፥ በሁከት፥ በድካም፥ እንቅልፍ በማጣት፥

፮ በመጦም፥ በንጽህና፥ በእውቀት፥ በትዕግሥት፥ በቸርነት፥ በመንፈስ ቅዱስ፥ ግብዝነት በሌለው ፍቅር፥

፯ በእግዚአብሔር ኃይል፥ ለቀኝና ለግራ በሚሆን በጽድቅ የጦር ዕቃ፥ በክብርና በውርደት፥

፰ በክፉ ወሬና በመልካም ወሬ ራሳችንን እናማጥናለን፤ እሳቾች ሰንባል እውነተኞች ነን፤

፱ ያልታወቁ ሰንባል የታወቅን ነን፤ የምንሞት ሰንመሰል እነሆ ሕያዋን ነን፤ የተቀጣን ሰንሆን አንገደልም፤

፲ ኀዘንተኞች ሰንሆን ዘወትር ደስ ይለናል፤ ድሆች ሰንሆን ብዙዎችን ባለ ጠጎች እናደርጋለን፤ አንዳች የሌለን ሰንሆን ሁሉ የእኛ ነው።

፲፩ እናንተ የቆሮንቶስ ሰዎች ሆይ፥ አፋችን ለእናንተ ተከፍቶአል ልባችንም ሰፍቶላችኋል፤

፲፪ በእኛ አልጠበባችሁም በሆዳችሁ ግን ጠቦባችኋል፤

፲፫ ልጆቼ እንደ መሆናችሁ ግን እላችኋለሁ፥ እናንተ ደግሞ ብድራት መልሳችሁልን ተሰፋፉ።

፲፬ ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አትጠመዱ፤ ጽድቅ ከዓመፅ ጋር ምን ተካፋይነት አለውና? ብርሃንም ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?

፲፭ ክርስቶሰስ ከቤልሆር ጋር ምን መሰማማት አለው? ወይስ የሚያምን ከማያምን ጋር ምን ክፍል አለው?

፲፮-፲፰ ለእግዚአብሔር ቤተ መቅደስም ከጣዖት ጋር ምን መጋጠም አለው? እኛ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነንና እንዲሁም እግዚአብሔር ተናገረ እንዲህ ሲል። በእነርሱ እኖራለሁ በመካከላቸውም እመላለሳለሁ፥ አምላካቸውም እሆናለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆናሉ።

፯

፩ እንግዲህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ የዚህ ተሰፋ ቃል ካለን፥ በእግዚአብሔር ፍርሃት ቅድሰናን ፍጹም እያደረግን ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ሁሉ ራሳችንን እናንጻ።

፪ በልባችሁ ሰፍራ እሰፋልን፤ ማንንም አልበደልንም፥ ማንንም አላጠፋንም፥ ማንንም አላታለልንም።

፫ ለኩነኔ አልልም፤ በኢንድነት ለመሞትና በእንድነት ለመኖር በልባችን እንዳላችሁ አሰቀድሜ ብዬአለሁና።

፬ ሰለ እናንተ እምነቴ ታላቅ ነው፥ በእናንተ ምክንያት ትምክህቴ ታላቅ ነው፤ መጽናናት ሞልቶብኛል፤ በመከራችን ሁሉ ደስታዬ ከመጠን ይልቅ ይበዛል።

፭ ወደ መቄዶንያም በመጣን ጊዜ፥ በሁሉ ነገር መከራን ተቀበልን እንጂ ሥጋችን ዕረፍት አልነበረውም፤ በውጭ ጠብ ነበረ፥ በውሰጥ ፍርሃት ነበረ።

፮ ነገር ግን ኀዘንተኞችን የሚያጽናና እምላክ በቲቶ መምጣት አጽናናን፤

፯ በመምጣቱም ብቻ አይደለም ነገር ግን ናፍቆታችሁንና ልቅሶአችሁን ሰለ እኔም ቅንዓታችሁን ሲናገረን በእናንተ ላይ በተጽናናበት መጽናናት ደግሞ ነው፤ ሰለዚህም ከፊት ይልቅ ደስ አለን።

፰ በመልእክቴ ያሳዘንኋችሁ ብሆን እንኳ አልጸጸትም፤ የተጸጸትሁ ብሆን እንኳ፥ ያ መልእክት ጥቂት ጊዜ ብቻ እንዳሳዘናችሁ እያለሁና እሁን ለንሰሐ ሰላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ሰላዘናችሁ አይደለም፤

፱ በምንም ከእኛ የተነሣ እንዳትጎዱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እዝናችኋልና።

፲ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን ጸጸት የሌለበትን፥ ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንሰሐ ያደርጋልና፤ የዓለም ኀዘን ግን ሞትን ያመጣል።

፲፩ እነሆ፥ ይህ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኀዘን እንዴት ያለ ትጋት፥ እንዴት ያለ መልስ፥ እንዴት ያለ ቁጣ፥ እንዴት ያለ ፍርሃት፥ እንዴት ያለ ናፍቆት፥ እንዴት ያለ ቅንዓት፥ እንዴት ያለ በቀል በመካከላችሁ አደረገ። በዚህ ነገር ንጹሐን እንደ ሆናችሁ በሁሉ አስረድታችኋል።

፲፪ እንግዲያስ የጻፍሁላችሁ ብሆን እንኳ፥ ስለ እኛ ያላችሁ ትጋታችሁ ከእናንተ ዘንድ በእግዚአብሔር ፊት እንዲገለጥ እንጂ፥ ስለ በዳዩ ወይም ስለ ተበዳዩ አልጻፍሁም። ስለዚህ ተጽናንተናል።

፲፫ በመጽናናታችንም ስለ ቲቶ ደስታ አብልጦ ደስ አለን፥ መንፈሱ በሁላችሁ ዐርፎአልና፤

፲፬ ለእርሱ በምንም ስለ እናንተ የተመካሁ እንደ ሆነ አላፈርሁምና፥ ነገር ግን ሁሉን ለእናንተ በእውነት እንደ ተናገርን፥ እንደዚህ ደግሞ ትምክህታችን በቲቶ ፊት እውነት ሆነ።

፲፭ ስለዚህም በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ እንዴት እንደተቀበላችሁት፥ የሁላችሁን መታዘዝ እያሰበ ፍቅሩ በእናንተ ላይ እጅግ በዝቶአል።

፲፮ በነገር ሁሉ ተማምኜባችኋለሁና ደስ ይለኛል።

፰

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ለመቄዶንያ አብያተ ክርስቲያናት የተሰጠውን የእግዚአብሔርን ጸጋ እናስታውቃችኋለን፤

፪ በብዙ መከራ ተፈትነው ሳሉ የደስታቸው ብዛትና የድህነታቸው ጥልቅነት የልግስናቸውን ባለ ጠግነት አብዝቶአል፤

፫ እንደ ዓቅማቸው መጠን ከዓቅማቸውም የሚያልፍ እንኳ ወደው እንደ ሰጡ እመስክርላቸዋለሁና።

፬ ለቅዱሳን በሆነው አገልግሎት እንዲተባበሩ ይህን ቸርነት በብዙ ልመና ከእኛ ይለምኑ ነበር፥

፭ አሰቀድመውም በእግዚአብሔር ፈቃድ ራሳቸውን ለጌታ ለእኛም ሰጡ እንጂ እንዳሰብን አይደለም።

፮ ስለዚህም ቲቶ አሰቀድሞ እንደ ጀመረ እንዲሁ ደግሞ ይህን ቸር ሥራ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ሊፈጽም ለመንን።

፯ ነገር ግን በነገር ሁሉ፥ በእምነትና በቃል በእውቀትም በትጋትም ሁሉ ለእኛም በፍቅራችሁ እንደ ተረፋችሁ፥ በዚህ ቸር ሥራ ደግሞ ትረፉ።

፰ ትእዛዝ እንደምሰጥ አልልም፥ ነገር ግን በሌሎች ትጋት በኩል የፍቅራችሁን እውነተኛነት ደግሞ ልመረምር እላለሁ፤

፱ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቸር ሰጥታ እውቃችኋልና፤ ሀብታም ሲሆን፥ እናንተ በእርሱ ድህነት ባለ ጠጎች ትሆኑ ዘንድ ስለ እናንተ ድሀ ሆነ።

፲ በዚህም ነገር ምክር እሰጣለሁ፤ ከአምና ጀምራችሁ ለማድረግ ብቻ ያይደለ ነገር ግን ለማሰብ ደግሞ አሰቀድማችሁ የጀመራችሁት ይህ ይጠቅማችኋልና፤

፲፩ አሁንም ለማሰብ በጎ ፈቃድ እንደ ነበረ፥ እንዲሁ እንዳላችሁ መጠን መፈጸም ደግሞ ይሆን ዘንድ፥ ማድረጉን ደግሞ ፈጽሙ።

፲፪ በጎ ፈቃድ ቢኖር፥ እንዳለው መጠን የተወደደ ይሆናል እንጂ እንደሌለው መጠን አይደለም።

፲፫ ለሌሎች ዕረፍት ለእናንተም መከራ እንዲሆን አይደለም፥ ትክክል እንዲሆን ነው እንጂ፤

፲፬ የእነርሱ ትርፍ ደግሞ የእናንተን ጉድለት እንዲሞላ በአሁኑ ጊዜ የእናንተ ትርፍ የእነርሱን ጉድለት ይሙላ፤ በትክክል እንዲሆን፥ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ።

፲፭ ብዙ ያከማቸ አላተረፈም፥ ጥቂትም ያከማቸ አላጎደለም።

፲፮ ነገር ግን በቲቶ ልብ ሰለ እናንተ ያንን ትጋት የሰጠ አምላክ ይመሰገን፤

፲፯ ምክራችንን ተቀብሎአልና፥ ትጋት ግን ሰለ በዛበት ወደ ወደ እናንተ ይወጣል።

፲፰ ከእርሱም ጋር ሰለ ወንጌል ሰብከት በአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ የተመሰገነውን ወንድም እንልካለን፤

፲፱ ይህም ብቻ አይደለም ነገር ግን የጌታን የራሱን ክብርና የእኛን በጎ ፈቃድ ለማሳየት በምናገለግለው በዚህ ቸር ሥራ ከእኛ ጋር እንዲጓደድ በአብያተ ክርስቲያናት ደግሞ ተመረጠ።

፳ ሰለምናገለግለው ሰለዚህ ለጋስ ሰጦታ ማንም እንዳይነቅፈን እንጠነቀቃለን፤

፳፩ በጌታ ፊት ብቻ ያይደለ ነገር ግን በሰው ፊት ደግሞ መልካም የሆነውን እናስባለንና።

፳፪ ብዙ ጊዜም በብዙ ነገር መርምረን ትጉ እንደ ሆነ ያገኘነውን፥ አሁንም በእናንተ እጅግ ሰለሚታመን ከፊት ይልቅ እጅግ ትጉ የሚሆነውን ወንድማችንን ከእነርሱ ጋር እንልካለን።

፳፫ ሰለ ቲቶ የሚጠይቅ ቢኖር ሰለ እናንተ አብሮኝ የሚሠራ ባልንጀራዬ ነው፤ ሰለ ወንድሞቻችን የሚጠይቅ ቢኖርም የአብያተ ክርስቲያናት መልእክተኞችና የክርስቶስ ክብር ናቸው።

፳፬ እንግዲህ የፍቅራችሁንና ሰለ እናንተ ያለውን የትምክህታችንን መግለጫ በአብያተ ክርስቲያናት ፊት ለእነርሱ ግለጡ።

፱

፩ ለቅዱሳን ሰለሚሆነው አገልግሎት ልጽፍላችሁ አያስፈልግምና፤

፪ በጎ ፈቃዳችሁን አውቄአለሁና፤ ሰለዚህም። አካይያ ከአምና ጀምሮ ተዘጋጅቶአል ብዬ ለመቄዶንያ ሰዎች በእናንተ እመካለሁ፥ ቅንዓታችሁም የሚበዙቱን አነሣሥቶአል።

፫ ነገር ግን ለእነርሱ እንዳልሁ፥ የተዘጋጃችሁ ትሆኑ ዘንድ በዚህም ነገር ሰለ እናንተ ያለው ትምክህታችን ከንቱ እንዳይሆን ወንድሞችን እልካለሁ፤

፬ ምናልባት የመቄዶንያ ሰዎች ከእኔ ጋር ቢመጡ፥ ያልተዘጋጃችሁም ሆናችሁ ቢያገኙአችሁ፥ እናንተ እንድታፍሩ አላልንም እኛ ግን በዚህ እምነታችን እንድናፍር እይሁን።

፭ እንግዲህ እንደ በረከት ሆኖ ከሰሰት የማይሆን ይህ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ አሰቀድመው ወደ እናንተ መጥተው፥ አሰቀድማችሁ ተሰፋ የሰጣችሁትን በረከት አሰቀድመው እንዲፈጽሙ ወንድሞችን እለምን ዘንድ እንዲያስፈልገኝ አሰብሁ።

፮ ይህንም እላለሁ። በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፥ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል።

፯ እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይሰጥ፥ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም።

፭-፯ ለዘሪ ዘርን ለመብላትም እንጀራን በብዙ
የሚሰጥ እርሱም የምትዘሩትን ዘር ይሰጣችኋል
ያበረክትላችሁማል፥ የጽድቃችሁንም ፍሬ ያሳድጋል፤
፰ በእኛ በኩል ለእግዚአብሔር የምስጋና ምክንያት
የሚሆነውን ልግስና ሁሉ እንድታሳዩ በሁሉ ነገር ባለ
ጠጎች ትሆናላችሁ።
፱ የዚህ ረድኤት አገልግሎት ለቅዱሳን
የሚጎድላቸውን በሙሉ የሚሰጥ ብቻ አይደለምና፥
ነገር ግን ደግሞ በብዙ ምስጋና ለእግዚአብሔር
ይበዛል፤
፲፫ በዚህ አገልግሎት ሰለ ተፈተናችሁ፥ በክርስቶስ
ወንጌል በማመናችሁ ስለሚሆን መታዘዝ እነርሱንና
ሁሉንም ስለምትረዱበት ልግስና እግዚአብሔርን
ያከብራሉ፥
፲፬ ራሳቸውም ሰለ እናንተ ሲያማልዱ፥ በእናንተ ላይ
ከሚሆነው ከሚበልጠው ከእግዚአብሔር ጸጋ የተነሣ
ይናፍቁአችኋል።
፲፭ ሰለማይነገር ሰጦታው እግዚአብሔር ይመስገን።

፲

፩ እኔም ራሴ ጳውሎስ፥ በእናንተ ዘንድ ፊት
ለፊት ሳለሁ ትሑት የሆንሁ፥ ከእናንተ ግን
ብርቅ የምደፍራችሁ፥ በክርስቶስ የዋህነትና ገርነት
እመክራችኋለሁ፤
፪ በዓለማዊ ልማድ እንደምንመላለስ በሚቆጥሩን
በአንዳንዶች ላይ እምኜ ልደፍር አሰባለሁ፥ በዚያ
እምነት ግን ከእናንተ ጋር ሆኜ እንዳልደፍር
እለምንችኋለሁ።
፫ በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ
ብንሆን፥ እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤
፬ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን
ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤
፭ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ
የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን
ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥
፮ መታዘዛችሁም በተፈጸመች ጊዜ አለመታዘዝን
ሁሉ ልንበቀል ተዘጋጅተናል።
፯ በፊታችሁ ያለውን ተመልከቱ። ማንም የክርስቶስ
መሆኑን ተረድቶ ቢሆን፥ ይህን እንደ ገና በራሱ
ይቁጠረው፤ እርሱ የክርስቶስ እንደ ሆነ እኛ ደግሞ
እንዲሁ ነን።
፰ ጌታ እናንተን ለማነጽ እንጂ እናንተን ለማፍረስ
ያይደለ በሰጠው በሥልጣናችን ከፊት ይልቅ ብመካ
እንኳ አላፍርም።
፱ በመልእክቶቼ የማስደነግጣችሁ አይምሰላችሁ።
፲ መልእክቶቹስ ከባድና ኃይለኛ ናቸው፥ ሰውነቱ
ግን ሲታይ ደካማ ነው፥ ንግግሩም የተናቀ ነው
ይላሉና።
፲፩ እንዲሁ የሚል ይህን ይቁጠረው፤ በሩቅ ሳለን
በመልእክታችን በኩል በቃል እንዳለን፥ በፊቱ ደግሞ
ሳለን በሥራ እንዲሁ ነን።
፲፪ ራሳቸውን ከሚያመሰግኑ ከአንዳንዶች ጋር
ራሳችንን ልንቆጥር ወይም ራሳችንን ልናስተያይ
አንደፍርምና፤ ነገር ግን እነርሱ ራሳቸውን ከራሳቸው
ጋር ሲያመዛዝኑ፥ ራሳቸውንም ከራሳቸው ጋር
ሲያስተያዩ፥ አያስተውሉም።
፲፫ እኛ ግን እግዚአብሔር እንደ ወሰነልን እስከ
እናንተ እንኳ እንደሚደርስ እንደ ክፍላችን ልክ እንጂ
ያለ ልክ አንመካም።
፲፬-፲፮ ወደ እናንተ እንደማንደርስ አድርገን ከመጠን
አናልፍምና፥ የክርስቶስን ወንጌል በመስበክ እስከ
እናንተ እንኳ ደርሰናልና፤

፲፩

፩ በጥቂቱ ሞኝነቴ ብትታገሡኝ መልካም ይሆን
ነበር፤ ቢሆንም በእርግጥ ታገሡኝ።
፪ በእግዚአብሔር ቅንዓት እቀናላችኋለሁና፥ እንደ
ንጽሕት ድንግል እናንተን ለክርስቶስ ላቀርብ ለአንድ
ወንድ አጭቻችኋለሁና፤
፫ ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፥
አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና
ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ።
፬ የሚመጣውም ያልሰበክነውን ሌላ ኢየሱስ
ቢሰብክ፥ ወይም ያላገኛችሁትን ልዩ መንፈስ ወይም
ያልተቀበላችሁትን ልዩ ወንጌል ብታገኙ፥ በመልካም
ትታገሡታላችሁ።
፭ ከእነዚህ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በአንድ ነገር እንኳ
እንደ ጎደልሁ ራሴን አልቆጥርምና።
፮ በአነጋገሬ ያልተማርሁ ብሆን እንኳ፥ በእውቀት ግን
እንዲህ አይደለሁም። ነገር ግን በሰው ሁሉ መካከል
በነገር ሁሉ ተገልጠንላችኋል።
፯ ወይስ የእግዚአብሔርን ወንጌል ያለ ደመወዝ ሰለ
ሰበክሁላችሁ፥ እናንተ ከፍ እንድትሉ ራሴን እያዋረድሁ
ኃጢአት እድርጌ ይሆንን?
፰ እናንተን ለማገልገል ደመወዝ እየተቀበልሁ
ሌሎችን አብያተ ክርስቲያናት ዘረፍሁ።
፱ ከእናንተም ጋር ሳለሁ በጎደለኝ ጊዜ፥ በማንም
አልከበድሁበትምና፤ ከመቄዶንያ የመጡት ወንድሞች
የጎደለኝን በሙሉ ሰጥተዋልና፤ በነገርም ሁሉ
እንዳልከብድባችሁ ተጠነቀቅሁ እጠነቀቅማለሁ።
፲ የክርስቶስ እውነት በእኔ እንዳለ፥ ይህ ትምክህት
በእኔ ዘንድ በአካይያ አገር እይከለከልም።
፲፩ ሰለ ምን? ሰለማልወዳችሁ ነውን? እግዚአብሔር ያውቃል።
፲፪ ነገር ግን በዚያ በሚመኩበት እንደ እኛ ሆነው
ሊገኙ፥ ምክንያትን ከሚፈልጉቱ ምክንያትን እቆርጥ
ዘንድ አሁን የማደርገውን ከዚህ ወዲህ ደግሞ
አደርጋለሁ።
፲፫ እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች የክርስቶስን
ሐዋርያት እንዲመስሉ ራሳቸውን እየለወጡ፥ ውሸተኞች
ሐዋርያትና ተንኮለኞች ሠራተኞች ናቸውና።
፲፬ ይህም ድንቅ አይደለም፤ ሰይጣን ራሱ የብርሃንን
መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና።
፲፭ እንግዲህ አገልጋዮቹ ደግሞ የጽድቅን አገልጋዮች
እንዲመስሉ ራሳቸውን ቢለውጡ ታላቅ ነገር
አይደለም፤ ፍጻሜአቸውም እንደ ሥራቸው ይሆናል።
፲፮ እንደ ገና እላለሁ። ለማንም ሰው ሞኝ የሆንሁ
አይምሰለው፤ ያለዚያ ግን እኔ ደግሞ ጥቂት እመካ
ዘንድ እንደ ሞኝ እንኳ ሆኜ ተቀበሉኝ።
፲፯ እንደዚህ ታምኜ ሰመካ የምናገረው፥ በሞኝነት
እንጂ ጌታ እንዳዘዘኝ አልናገርም።
፲፰ ብዙዎች በዓለማዊ ነገር ሰለሚመኩ እኔ ደግሞ
እመካለሁ።

፲፱ ልባሞች ሰለምትሆኑ በደስታ ሞቾችን ትታገሣላችሁና፤
፳ ማንም ባሪያዎች ቢያደርጋችሁ፥ ማንም ቢበላችሁ፥ ማንም ቢቀማችሁ፥ ማንም ቢኮራባችሁ፥ ማንም ፊታችሁን በጥፊ ቢመታችሁ ትታገሣላችሁና።
፳፩ ደካሞች መሰለን እንደ ነበርን በውርደት እላለሁ። ነገር ግን በሞኝነት እላለሁ፤ ማንም በሚደፍርበት እኔ ደግሞ እደፍርበታለሁ።
፳፪ ዕብራውያን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የእስራኤል ወገን ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የአብርሃም ዘር ናቸውን? እኔ ደግሞ ነኝ። የክርስቶስ አገልጋዮች ናቸውን?
፳፫ እንደ እብድ ሰው እላለሁ፤ እኔ እበልጣለሁ፤ በድካም አብዝቼ፥ በመገረፍ አብዝቼ፥ በመታሰር እትርፌ፥ በመሞት ብዙ ጊዜ ሆንሁ።
፳፬ አይሁድ አንድ ሲጎድል አርባ ግርፋት አምስት ጊዜ ገረፉኝ።
፳፭ ሦስት ጊዜ በበትር ተመታሁ፤ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወገርሁ፤ መርከቤ ሦስት ጊዜ ተሰበረ፤ ሌሊትና ቀን በባሕር ውሰጥ ኖርሁ።
፳፮ ብዙ ጊዜ በመንገድ ሄድሁ፤ በወንዝ ፍርሃት፥ በወንበዴዎች ፍርሃት፥ በወገኔ በኩል ፍርሃት፥ በአሕዛብ በኩል ፍርሃት፥ በከተማ ፍርሃት፥ በምድረ በዳ ፍርሃት፥ በባሕር ፍርሃት፥ በውሸተኞች ወንድሞች በኩል ፍርሃት ነበረብኝ፤
፳፯ በድካምና በጥረት ብዙ ጊዜም እንቅልፍ በማጣት፥ በራብና በጥም ብዙ ጊዜም በመጦም፥ በብርድና በራቁትነት ነበርሁ።
፳፰ የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው።
፳፱ የሚደክም ማን ነው፥ እኔም አልደክምምን? የሚሰናከል ማን ነው፥ እኔም አልናደድምን?
፴ ትምክህት የሚያስፈልግ ከሆነ፥ ከድካሜ በሚሆነው ነገር እመካለሁ።
፴፩ ለዘላለም የተባረከ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና አባት እንዳልዋሸ ያውቃል።
፴፪ በደማስቆ አርስጦስዮስ ከተባለ ንጉሥ በታች የሆነ የሕዝብ ገዥ ሊይዘኝ እየወደደ የደማስቆ ሰዎችን ከተማ ያስጠብቅ ነበር፥
፴፫ በቅጥሩም ባለ መስኮት በቅርጫት አወረዱኝና ከእጁ አመለጥሁ።

፲፪

፩ ትምክህት የሚያስፈልግ ነው፤ አይጠቅምም ነገር ግን ከጌታ ወዳለው ራእይና መገለጥ እመጣለሁ።
፪ ሰውን በክርስቶስ አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም ወይም ከሥጋ ውጭ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤ እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ።
፫ እንዲህ ያለውንም ሰው አውቃለሁ፥ በሥጋ እንደ ሆነ ወይም ያለ ሥጋ እንደ ሆነ አላውቅም፥ እግዚአብሔር ያውቃል፤
፬ ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ።
፭ እንደዚህ ሰላለው እመካለሁ፥ ሰለ ራሴ ግን ከድካሜ በቀር አልመካም።
፮ ልመካ ብወድስ ሞኝ አልሆንም፥ እውነትን እላለሁና፤ ነገር ግን ማንም ከሚያይ ከእኔም ከሚሰማ የምበልጥ አድርጎ እንዳይቆጥረኝ ትቼአለሁ።
፯ ሰለዚህም በመገለጥ ታላቅነት እንዳልታበይ የሥጋዬ መውጊያ፥ እርሱም የሚጎሰመኝ የሰይጣን መልእክተኛ ተሰጠኝ፤ ይኸውም እንዳልታበይ ነው።
፰ ሰለዚህ ነገር ከእኔ እንዲለይ ሦስት ጊዜ ጌታን ለመንሁ።
፱ እርሱም። ጸጋዬ ይበቃሃል፥ ኃይሌ በድካም ይፈጸማልና አለኝ። እንግዲህ የክርስቶስ ኃይል ያድርብኝ ዘንድ በብዙ ደስታ በድካሜ ልመካ እወዳለሁ።
፲ ሰለዚህ ሰለ ክርስቶስ በድካም በመንገላታትም በችግርም በሰደትም በጭንቀትም ደስ ይለኛል፤ ሰደክም ያን ጊዜ ኃይለኛ ነኝና።
፲፩ በመመካቴ ሞኝ ሆኜአለሁ፤ እናንተ ግድ አላችሁኝ፤ እናንተ እኔን ልታመሰግኑ ይገባ ነበርና። እኔ ምንም ባልሆን እንኳ፥ ከዋነኞቹ ሐዋርያት በምንም አልጎድልምና።
፲፪ በእርግጥ የሐዋርያነት ምልክት በመካከላችሁ በምልክትና በድንቅ ነገር በተአምራትም በሁሉ ትዕግሥት ተደረገ።
፲፫ እኔ ራሴ ካልከበድሁባችሁ ከዚህ በቀር፥ ከሌላ ቤተ ክርስቲያን ያነሳችሁበት በምን እኮ ነው? ይህን በደሌን ይቅር በሉልኝ።
፲፬ እነሆ፥ ወደ እናንተ እመጣ ዘንድ ሰዘጋጅ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ አልከብድባችሁምም፥ እናንተን እንጂ ያላችሁን አልፈልግምና። ወላጆች ለልጆች እንጂ ልጆች ለወላጆች ገንዘብ ሊያከማቹ አይገባቸውምና።
፲፭ እኔ ግን ሰለ ነፍሳችሁ በብዙ ደስታ ገንዘቤን እከፍላለሁ፥ ራሴን እንኳ እከፍላለሁ። ከመጠን ይልቅ ብወዳችሁ በዚህ ልክ ፍቅራችሁ የሚያንስ ነውን?
፲፮ ይሁን እንጂ እኔ አልከበድሁባችሁም፤ ነገር ግን ሸንጋይ ሆኜ በተንኰል ያዝኋችሁ።
፲፯ ወደ እናንተ ከላክኋቸው በአንዱ ሰንኳ አታለልኋችሁን?
፲፰ ቲቶን መከርሁት ከእርሱም ጋር ወንድሙን ላክሁት፤ ቲቶስ አታለላችሁን? በእንድ መንፈስ አልተመላለሰንምን? በእንድ ፍለጋስ አልተመላለስንም?
፲፱ ለእናንተ ሰለ ራሳችን እንድንመልስ ሁልጊዜ ይመሰላችኋልን? በእግዚአብሔር ፊት በክርስቶስ ሆነን እንናገራለን፤ ነገር ግን፥ ወዳጆች፥ እናንተን ልናንጻችሁ ሁሉን እንናገራለን።
፳ ሰመጣ፥ እንደምወደው ሳትሆኑ አገኛችሁ ይሆናል እኔም እንደምትወዱት ሳልሆን ታገኙኝ ይሆናል ብዬ እፈራለሁና፤ ምናልባት ክርክር ቅንዓትም ቁጣም እድመኝነትም ሐሜትም ማሾክሾክም ኩራትም ሁከትም ይሆናሉ፤
፳፩ እንደ ገና ሰመጣ በእናንተ ዘንድ አምላኬ እንዲያዋርደኝ፥ አስቀድመውም ኃጢአት ከሠሩትና ሰላደረጉት ርኩስትና ዝሙት መዳራትም ንስሐ ካልገቡት ወገን ሰለ ብዙዎች ምናልባት አዝናለሁ ብዬ እፈራለሁ።

፲፫

፩ ወደ እናንተ ሰመጣ ይህ ሦስተኛዬ ነው፤ ሁሉ

ነገር በሁለትና በሦስት ምስክር እፍ ይጸናል።
፬-፬ በድካም ተሰቅሎአልና፥ ነገር ግን በእግዚአብሔር ኃይል በሕይወት ይኖራል። እኛ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንደክማለንና፥ ነገር ግን ስለ እናንተ በሆነ በእግዚአብሔር ኃይል ከእርሱ ጋር በሕይወት እንኖራለን።
፭ በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ፤ ራሳችሁን ፈትኑ፤ ወይስ ምናልባት የማትበቁ ባትሆኑ፥ ኢየሱስ ክርስቶስ በእናንተ ውስጥ እንዳለ ስለ እናንተ አታውቁምን?
፮ እኛ ግን የማንበቃ እንዳይደለን ልታውቁ ተስፋ አደርጋለሁ።
፯ ክፉ ነገርንም ከቶ እንዳታደርጉ ወደ እግዚአብሔር እንጸልያለን፤ እኛ የምንበቃ ሆነን እንገለጥ ዘንድ አይደለም ነገር ግን እኛ ምንም እንደማንበቃ ብንሆን፥ እናንተ መልካሙን ታደርጉ ዘንድ ነው።
፰ ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም ለማድረግ አንችልምና።
፱ እኛ ስንደክም እናንተም ኃይለኞች ስትሆኑ ደስ ብሎናልና፤ እናንተ ፍጹማን ትሆኑ ዘንድ ለዚህ ደግሞ እንጸልያለን።
፲ ስለዚህ ጌታ ለማፍረስ ያይደለ ለማነጽ እንደ ሰጠኝ ሥልጣን፥ ከእናንተ ጋር ሳለሁ በቁርጥ እንዳልሠራ በሩቅ ሆኜ ይህን እጽፋለሁ።
፲፩ በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ደኅና ሁኑ። ፍጹማን ሁኑ፥ ምክሬን ስሙ፥ በአንድ ልብ ሁኑ፥ በሰላም ኑሩ፥ የፍቅርና የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።
፲፪ በተቀደሰ አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ።
፲፫ ቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፲፬ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ኅብረት ከሁላችሁ ጋር ይሁን። አሜን።

ወደ ገላትያ ሰዎች

፩-፫ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፬ ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ።
፭ ለአብ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።
፮ በክርስቶስ ጸጋ እናንተን ከጠራችሁ ከእርሱ ወደ ልዩ ወንጌል እንዲህ ፈጥናችሁ እንዴት እንዳለፋችሁ እደነቃለሁ፤
፯ እርሱ ግን ሌላ ወንጌል አይደለም፤ የሚያናውጡአችሁ የክርስቶስንም ወንጌል ሊያጣምሙ የሚወዱ እንዳንዶች አሉ እንጂ።
፰ ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይም ከሰማይ መልአክ፥ ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ፥ የተረገመ ይሁን።
፱ አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፥ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን።
፲ ሰውን ወይስ እግዚአብሔርን አሁን እሺ አሰኛለሁን? ወይም ሰውን ደስ ላሰኝ እፈልጋለሁን? አሁን ሰውን ደስ ባሰኝ የክርስቶስ ባሪያ ባልሆንሁም።
፲፩ ወንድሞች ሆይ፥ በእኔ የተሰበከ ወንጌል እንደ ሰው እንዳይደለ አስታውቃችኋለሁ፤
፲፪ ኢየሱስ ክርስቶስ ገልጦልኛል እንጂ እኔ ከሰው አልተቀበልሁትም አልተማርሁትምም።
፲፫ በአይሁድ ሥርዓት በፊት እንዴት እንደ ኖርሁ ሰምታችኋልና፤ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ያለ ልክ አሳድድና አጠፋ ነበር፥
፲፬ ለአባቶችም ወግ ከመጠን ይልቅ እየቀናሁ በወገኔ ዘንድ በዘመኔ ካሉት ብዙዎችን በአይሁድ ሥርዓት እበልጥ ነበር።
፲፭-፲፯ ከእኔም በፊት ሐዋርያት ወደ ነበሩት ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፥ ነገር ግን ወደ ዓረብ አገር ሄድሁ እንደ ገናም ወደ ደማስቆ ተመለስሁ።
፲፰ ከዚህ ወዲያ ከሦስት ዓመት በኋላ ኬፋን ልጠይቅ ወደ ኢየሩሳሌም ወጥቼ ከእርሱ ጋር አሥራ አምስት ቀን ሰነበትሁ፤
፲፱ ነገር ግን ከጌታ ወንድም ከያዕቆብ በቀር ከሐዋርያት ሌላ አላየሁም።
፳ ስለምፅፍላችሁም ነገር፥ እነሆ፥ በእግዚአብሔር ፊት ሐሰት አልናገርም።
፳፩ ከዚያ ወዲያ ወደ ሶርያና ወደ ኪልቅያ አገር መጣሁ።
፳፪ በክርስቶስም ያሉት የይሁዳ ማኅበሮች ፊቴን አያውቁም ነበር፤
፳፫ ነገር ግን። ቀድሞ እኛን ያሳድድ የነበረ፥ እርሱ በፊት ያጠፋው የነበረውን ሃይማኖት አሁን ይሰብካል ተብሎ ሲነገር ይሰሙ ነበር፤
፳፬ ስለ እኔም እግዚአብሔርን ያከብሩ ነበር።

፪

፩ ከዚያ ወዲያ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ ከበርናባስ ጋር ቲቶን ደግሞ ይዤ ወደ ኢየሩሳሌም ሁለተኛ ወጣሁ፤
፪ እንደ ተገለጠልኝም ወጣሁ፤ ምናልባትም በከንቱ እንዳልሮጥ ወይም በከንቱ ሮጬ እንዳልሆን በአሕዛብ መካከል የምሰብከውን ወንጌል አስታወቅኋቸው፤ ዋኖች ግን መሰለው ለሚታዩ ለብቻቸው አስታወቅኋቸው።
፫ ነገር ግን ከእኔ ጋር የነበረ ቲቶ እንኳ የግሪክ ሰው ሲሆን ይገረዝ ዘንድ ግድ አላሉትም፤
፬ ነገር ግን ባሪያዎች ሊያደርጉን በክርስቶስ ኢየሱስ ያለንን አርነታችንን ይሰልሉ ዘንድ ሾልከው በስውር ስለ ገቡ ስለ ሐሰተኞች ወንድሞች ነበረ።
፭ የወንጌልም እውነት በእናንተ ዘንድ ጸንቶ እንዲኖር ለአንድ ሰዓት እንኳ ለቅቀን አልተገዛንላቸውም።
፮ እለቆች የመሰሉት ግን፥ በፊት ማን እንደ ነበሩ እይገደኝም፤ እግዚአብሔር የሰውን ፊት አይቶ አያደላም፤ አለቆች የመሰሉት አንዳች እንኳ አልጨመሩልኝምና፥
፯ ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አየ፤
፰ ለተገረዙት ሐዋርያ እንዲሆን ለጴጥሮስ የሠራለት፥ ለእኔ ደግሞ ለአሕዛብ ሐዋርያ እንድሆን ሠርቶአልና።
፱ ደግሞ የተሰጠኝን ጸጋ አውቀው፥ አዕማድ መሰለው የሚታዩ ያዕቆብና ኬፋ ዮሐንስም እኛ ወደ አሕዛብ እነርሱም ወደ ተገረዙት ይሄዱ ዘንድ ለእኔና ለበርናባስ ቀኝ እጆቸውን ሰጡን፤
፲ ድሆችን እናስብ ዘንድ ብቻ ለመኑን፥ ይህንም ደግሞ ላደርግ ተጋሁ።
፲፩ ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና።
፲፪ እንዳንድ ከያዕቆብ ዘንድ ሳይመጡ ከአሕዛብ ጋር አብሮ ይበላ ነበርና፤ በመጡ ጊዜ ግን ከተገረዙት ወገን ያሉትን ፈርቶ ያፈገፍግ ነበርና ከእነርሱ ተለየ።
፲፫ የቀሩትም አይሁድ ደግሞ፥ በርናባስ ሰንኳ በግብዝነታቸው እስከ ተሳበ ድረስ፥ ከእርሱ ጋር አብረው ግብዞች ሆኑ።
፲፬ ነገር ግን እንደ ወንጌል እውነት በቅንነት እንዳልሄዱ ባየሁ ጊዜ በሁሉ ፊት ኬፋን። አንተ አይሁዳዊ ሳለህ በአይሁድ ኑሮ ያይደለ በአሕዛብ ኑሮ ብትኖር፥ አሕዛብ በአይሁድ ኑሮ ሊኖሩ እንዴት ግድ አልሃቸው? አልሁት።
፲፭ እኛ በፍጥረት አይሁድ ነን ኃጢአተኞችም የሆኑ አሕዛብ አይደለንም፤
፲፮ ነገር ግን ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን እውቀን፥ ሥጋን የለበሰ ሁሉ በሕግ ሥራ ስለማይጸድቅ፥ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል።
፲፯ ነገር ግን በክርስቶስ ልንጸድቅ የምንፈልግ ሰንሆን ራሳችን ደግሞ ኃጢአተኞች ሆነን ከተገኘን፥ እንግዲያስ ክርስቶስ የኃጢአት አገልጋይ ነዋ? አይደለም።

፲፭ ያፈረሰሁትን ይህን እንደ ገና የማንጽ ከሆንሁ
ራሴ ሕግ ተላላፊ እንድሆን አሰረዳለሁና።
፲፱ እኔ ለእግዚአብሔር ሕያው ሆኜ እኖር ዘንድ
በሕግ በኩል ለሕግ ሞቼ ነበርና።
፳ ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው
ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም
በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን
በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት
የምኖረው ነው።
፳፩ የእግዚአብሔርን ጸጋ አልጥልም፤ ጽድቅስ በሕግ
በኩል ከሆነ እንኪያስ ክርስቶስ በከንቱ ሞተ።

፫

፩ የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ
ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤
ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?
፪ ይህን ብቻ ከእናንተ እንድማር እወዳለሁ፤ በሕግ
ሥራ ወይም ከእምነት ጋር በሆነ መሰማት መንፈስን
ተቀበላችሁን?
፫ እንዲህን የማታስተውሉ ናችሁ? በመንፈስ
ጀምራችሁ አሁን በሥጋ ትፈጽማላችሁን?
፬ በውኑ ከንቱ እንደ ሆነስ እንደዚህ ያለ መከራ
በከንቱ ተቀበላችሁን?
፭ እንግዲህ መንፈስን የሚሰጣችሁ በእናንተም
ዘንድ ተአምራት የሚያደርግ፥ በሕግ ሥራ ነውን ወይስ
ከእምነት ጋር በሆነ መሰማት ነው?
፮ እንዲሁ አብርሃም በእግዚአብሔር አመነና ጽድቅ
ሆኖ ተቆጠረለት።
፯ እንኪያስ ከእምነት የሆኑት እነዚህ የአብርሃም
ልጆች እንደ ሆኑ እወቁ።
፰ መጽሐፍም እግዚአብሔር አሕዛብን በእምነት
እንዲያጸድቅ አሰቀድሞ አይቶ። በአንተ አሕዛብ
ሁሉ ይባረካሉ ብሎ ወንጌልን ለአብርሃም አሰቀድሞ
ሰበከ።
፱ እንደዚህ ከእምነት የሆኑት ካመነው ከአብርሃም
ጋር ይባረካሉ።
፲ ከሕግ ሥራ የሆኑት ሁሉ በእርግማን በታች
ናቸውና፤ በሕግ መጽሐፍ በተጻፉት ሁሉ ጸንቶ
የማይኖር የማያደርግም ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ
ተጽፎአልና።
፲፩ ጻድቅ በእምነት ይኖራል ተብሎአልና ማንም
በእግዚአብሔር ፊት በሕግ እንዳይጸድቅ ግልጥ ነው።
፲፪ ሕግም ከእምነት አይደለም ነገር ግን።
የሚያደርገው ይኖርበታል ተብሎአል።
፲፫ በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ
ተጽፎአልና ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ
እርግማን ዋጀን፤
፲፬ የመንፈስን ተሰፋ በእምነት እንድንቀበል፥
የአብርሃም በረከት ወደ አሕዛብ በኢየሱስ ክርስቶስ
ይደርስላቸው ዘንድ።
፲፭ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ሰው ልማድ እላለሁ።
የሰው ሰንኳ ቢሆን እርግጠኛውን ኪዳን ማንም
አይንቅም ወይም አይጨምርበትም።
፲፮ ለአብርሃምና ለዘሩም የተሰፋው ቃል ተነገረ።
ስለ ብዙዎች እንደሚነገር። ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ
አንድ እንደሚነገር ግን። ለዘርህም ይላል፥ እርሱም
ክርስቶስ።
፲፯ ይህንም እላለሁ፤ ከእራት መቶ ሠላሳ ዓመት
በኋላ የተሰጠው ሕግ አሰቀድሞ በእግዚአብሔር
የተረጋገጠውን ኪዳን የተሰፋውን ቃል እስኪሽር ድረስ
አያፈርሰም።
፲፰ ርስቱ በሕግ ቢሆንስ እንግዲያስ በተሰፋ ቃል
አይሆንም፤ በተሰፋ ቃል ግን እግዚአብሔር ለአብርሃም
ሰጥቶአል።
፲፱ እንግዲህ ሕግ ምንድር ነው? ተሰፋው
የተሰጠው ዘር እስኪመጣ ድረስ በመካከለኛ እጅ
በመላእክት በኩል ስለ ሕግ መተላለፍ ተጨመረ።
፳ መካከለኛውም ለአንድ ብቻ አይደለም
እግዚአብሔር ግን አንድ ነው።
፳፩ እንግዲህ ሕግ የእግዚአብሔርን የተሰፋ ቃል
የሚቃወም ነውን? አይደለም። ሕያው ሊያደርግ
የሚቻለው ሕግ ተሰጥቶ ቢሆንስ በእውነት ጽድቅ
ከሕግ በሆነ ነበር፤
፳፪ ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው
የተሰፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ
ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል።
፳፫ እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት
ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር።
፳፬ እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ
ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤
፳፭ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ
ከሞግዚት በታች አይደለንም።
፳፮ በእምነት በኩል ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ
የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁና፤
፳፯ ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ
ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና።
፳፰ አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ
ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤
ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።
፳፱ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ
የአብርሃም ዘር እንደ ተሰፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ።

፬

፩ ነገር ግን እላለሁ፥ ወራሹ ሕፃን ሆኖ ባለበት
ዘመን ሁሉ፥ ምንም የሁሉ ጌታ ቢሆን ከቶ ከባሪያ
አይለይም፥
፪ ነገር ግን አባቱ እስከ ቀጠረለት ቀን ድረስ
ከጠባቂዎችና ከመጋቢዎች በታች ነው።
፫ እንዲሁ እኛ ደግሞ ሕፃናት ሆነን ሳለን ከዓለም
መጀመሪያ ትምህርት በታች ተገዝተን ባሪያዎች ነበርን፤
፬ ነገር ግን የዘመኑ ፍጻሜ በደረሰ ጊዜ
እግዚአብሔር ከሴት የተወለደውን ከሕግም በታች
የተወለደውን ልጁን ላከ፤
፭ እንደ ልጆች እንሆን ዘንድ፥ ከሕግ በታች ያሉትን
ይዋጅ ዘንድ።
፮ ልጆችም ስለ ሆናችሁ እግዚአብሔር አባ አባት
ብሎ የሚጮኽ የልጁን መንፈስ በልባችሁ ውስጥ
ላከ።
፯ ስለዚህ ከእንግዲህ ወዲህ ልጅ ነህ እንጂ
ባሪያ አይደለህም፤ ልጅም ከሆንህ ደግሞ በክርስቶስ
የእግዚአብሔር ወራሽ ነህ።
፰ ነገር ግን በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ሳታውቁ
በባሕርያቸው አማልክት ለማይሆኑ ባሪያዎች ሆናችሁ
ተገዛችሁ፤

፱ አሁን ግን እግዚአብሔርን ሰታውቁ ይልቅስ በእግዚአብሔር ሰትታወቁ እንደ ገና ወደ ደካማ ወደሚናቅም ወደ መጀመሪያ ትምህርት እንዴት ትመለሳላችሁ? እንደ ገና ባሪያዎች ሆናችሁ ዳግመኛ ለዚያ ልትገዙ ትወዳላችሁን?
፲ ቀንንና ወርን ዘመንንም ዓመትንም በጥንቃቄ ትጠብቃላችሁ።
፲፩ ምናልባት በከንቱ ለእናንተ ደክሜአለሁ ብዬ እፈራችኋለሁ።
፲፪ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ደግሞ እንደ እናንተ ሆኜአለሁና። እንደ እኔ ሁኑ ብዬ እለምናችኋለሁ። አንዳችም አልበደላችሁኝም።
፲፫ በመጀመሪያ ወንጌልን በሰበክሁላችሁ ጊዜ ከሥጋ ድካም የተነሣ እንደ ነበረ ታውቃላችሁ፥
፲፬ በሥጋዬም ፈተና የሆነባችሁን ነገር አልናቃችሁትምና አልተጸየፋችሁትም ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር መልአክ አዎን እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ ተቀበላችሁኝ።
፲፭ እንግዲህ ደስ ማሰኘታችሁ ወዴት አለ? ቢቻልስ ዓይኖቻችሁን አውጥታችሁ በሰጣችሁኝ ብዬ እመሰክርላችኋለሁ።
፲፮ እንኪያስ እውነቱን ሰለ ነገርኋችሁ ጠላት ሆንሁባችሁን?
፲፯ በብርቱ ይፈልጉአችኋል፥ ለመልካም አይደለም ነገር ግን በብርቱ ትፈልጉአቸው ዘንድ በውጭ ሊያሰቀሩአችሁ ይወዳሉ።
፲፰ ነገር ግን ከእናንተ ዘንድ በምኖርበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁልጊዜ በመልካም ነገር ተፈላጊ ብትሆኑ መልካም ነው።
፲፱ ልጆቼ ሆይ፥ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ሰለ እናንተ ምጥ ይዞኛል።
፳ ሰለ እናንተ አመነታለሁና አሁን በእናንተ ዘንድ ሆኜ ድምፄን ልለውጥ በወደድሁ።
፳፩ እናንተ ከሕግ በታች ልትኖሩ የምትወዱ፥ ሕጉን አትሰሙምን? እሰኪ ንገሩኝ።
፳፪ አንዱ ከባሪያይቱ አንዱም ከጨዋይቱ የሆኑ ሁለት ልጆች ለአብርሃም እንደ ነበሩት ተጽፎአልና።
፳፫ ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደ ሥጋ ተወልዶአል፥ የጨዋይቱ ግን በተስፋው ቃል ተወልዶአል።
፳፬ ይህም ነገር ምሳሌ ነው፤ እነዚህ ሴቶች እንደ ሁለቱ ኪዳኖች ናቸውና። ከደብረ ሲና የሆነችው አንዲቱ ለባርነት ልጆችን ትወልዳለች፥ እርስዋም አጋር ናት።
፳፭ ይህችም አጋር በዓረብ ምድር ያለችው ደብረ ሲና ናት፤ አሁንም ያለችውን ኢየሩሳሌምን ትመሰላለች፥ ከልጆችዋ ጋር በባርነት ናትና።
፳፮ ላይኛይቱ ኢየሩሳሌም ግን በነጻነት የምትኖር ናት እርስዋም እናታችን ናት።
፳፯ እንቺ የማትወልጅ መካን፥ ደስ ይበልሽ፤ እንቺ አምጠሽ የማታውቂ፥ እልል በዪና ጩኺ፤ ባል ካላቱ ይልቅ የብቸኛይቱ ልጆች በዝተዋልና ተብሎ ተጽፎአል።
፳፰ እኛም፥ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ይስሐቅ የተሰፋ ቃል ልጆች ነን።
፳፱ ነገር ግን እንደ ሥጋ የተወለደው እንደ መንፈስ የተወለደውን በዚያን ጊዜ እንዳሳደደው ዛሬም እንዲሁ ነው።
፴ ነገር ግን መጽሐፍ ምን ይላል? የባሪያይቱ ልጅ ከጨዋይቱ ልጅ ጋር አይወርስምና ባሪያይቱን ከልጅዋ ጋር አውጣት።
፴፩ ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም።

፭

፩ በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻነት አወጣን፤ እንግዲህ ጸንታችሁ ቁሙ እንደ ገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ።
፪ እነሆ፥ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ። ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁም።
፫ ሕግንም ሁሉ እንዲፈጽም ግድ አለበት ብዬ ለሚገረዙት ሁሉ ለእያንዳንዳቸው ደግሜ እመሰክራለሁ።
፬ በሕግ ልትጸድቁ የምትፈልጉ ከክርስቶስ ተለይታችሁ ከጸጋው ወድቃችኋል።
፭ እኛ በመንፈስ ከእምነት የጽድቅን ተስፋ እንጠባበቃለንና።
፮ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ፥ በፍቅር የሚሠራ እምነት እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።
፯ በመልካም ትሮጡ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ ማን ከለከላችሁ?
፰ ይህ ማባበል ከሚጠራችሁ አልወጣም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ ያቦካል።
፱-፲ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እስከ አሁን መገረዝን ብሰብክ እስከ አሁን ድረስ ለምን ያሳድዱኛል? እንኪያስ የመሰቀል ዕንቅፋት ተወግዶአል።
፲፪ የሚያውኩአችሁ ይቆረጡ።
፲፫ ወንድሞች ሆይ፥ እናንተ ለእርነት ተጠርታችኋልና፤ ብቻ እርነታችሁ ለሥጋ ምክንያትን እይሰጥ፥ ነገር ግን በፍቅር እርስ በርሳችሁ እንደ ባሪያዎች ሁኑ።
፲፬ ሕግ ሁሉ በአንድ ቃል ይፈጸማልና፥ እርሱም። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ የሚል ነው።
፲፭ ነገር ግን እርስ በርሳችሁ ብትነካከሱ ብትበላሉ እርስ በርሳችሁ እንዳትጠፋፉ ተጠንቀቁ።
፲፮ ነገር ግን እላለሁ፥ በመንፈስ ተመላለሱ፥ የሥጋንም ምኞት ከቶ አትፈጽሙ።
፲፯ ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።
፲፰ በመንፈስ ብትመሩ ግን ከሕግ በታች አይደላችሁም።
፲፱ የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው እርሱም ዝሙት፥ ርኩሰት፥
፳ መዳራት፥ ጣዖትን ማምለክ፥ ምዋርት፥ ጥል፥ ክርክር፥ ቅንዓት፥ ቁጣ፥ እድመኛነት፥
፳፩ መለያየት፥ መናፍቅነት፥ ምቀኝነት፥ መግደል፥ ሰካር፥ ዘፋኝነት፥ ይህንም የሚመሰል ነው። አስቀድሜም እንዳልሁ፥ እንደዚህ ያሉትን የሚያደርጉ የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርሱም።
፳፪ የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት ነው።

፳፫ እንደዚህ ያሉትን የሚከለክል ሕግ የለም።
፳፬ የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ።
፳፭ በመንፈስ ብንኖር በመንፈስ ደግሞ እንመላለስ።
፳፮ እርስ በርሳችን እየተነሣሣንና እየተቀናናን በከንቱ አንመካ።

፮

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ሰው በማናቸውም በደል ሰንኳ ቢገኝ፥ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ።
፪ ከእናንተ እያንዳንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም እንዲሁም የክርስቶስን ሕግ ፈጽሙ።
፫ አንዱ ምንም ሳይሆን ምንም የሆነ ቢመሰለው ራሱን ያታልላልና።
፬ ነገር ግን እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሥራ ይፈትን፥ ከዚያም በኋላ ሰለ ሌላው ሰው ያልሆነ ሰለ ራሱ ብቻ የሚመካበትን ያገኛል፤
፭ እያንዳንዱ የገዛ ራሱን ሸክም ሊሸከም ነውና።
፮ ነገር ግን ቃሉን የሚማር ከሚያስተምረው ጋር መልካምን ነገር ሁሉ ይከፋፈል።
፯ አትሳቱ፤ እግዚአብሔር አይዘበትበትም። ሰው የሚዘራውን ሁሉ ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና፤
፰ በገዛ ሥጋው የሚዘራ ከሥጋ መበስበስን ያጭዳልና፥ በመንፈስ ግን የሚዘራው ከመንፈስ የዘላለምን ሕይወት ያጭዳል።
፱ ባንዝልም በጊዜው እናጭዳለንና መልካም ሥራን ለመሥራት እንታክት።
፲ እንግዲያስ ጊዜ ካገኘን ዘንድ ለሰው ሁሉ ይልቁንም ለሃይማኖት ቤተ ሰዎች መልካም እናድርግ።
፲፩ እንዴት ባሉ ታላላቆች ፊደላት በእጄ እንደ ጻፍሁላችሁ እዩ።
፲፪ በሥጋ መልካም ሆነው ሊታዩ የሚወዱ ሁሉ እንድትገረዙ ግድ አሉአችሁ፥ ነገር ግን ሰለ ክርስቶስ መሰቀል እንዳይሰደዱ ብቻ ነው።
፲፫ በሥጋችሁ እንዲመኩ ልትገረዙ ይወዳሉ እንጂ የተገረዙቱ ራሳቸው እንኳ ሕግን አይጠብቁም።
፲፬ ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መሰቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።
፲፭ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረት መሆን ይጠቅማል እንጂ መገረዝ ቢሆን ወይም አለመገረዝ አይጠቅምምና።
፲፮ በዚህም ሥርዓት በሚመላለሱ ሁሉ ላይ በእግዚአብሔር እስራኤልም ላይ ሰላምና ምሕረት ይሁን።
፲፯ እኔ የኢየሱስን ማኅተም በሥጋዬ ተሸክሜአለሁና ከእንግዲህ ወዲህ አንድ ሰንኳ አያድክመኝ።
፲፰ ወንድሞች ሆይ፥ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን። አሜን።

ወደ ኤፌሶን ሰዎች

፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ
የሆነ ጳውሎስ፥ በኤፌሶን ላሉት ቅዱሳን በክርስቶስ
ኢየሱስም ላሉት ምእመናን፤
፪ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ
ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፫ በክርስቶስ በሰማያዊ ሰፍራ በመንፈሳዊ በረከት
ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክና
አባት ይባረክ።
፬ ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን
በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።
፭ በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ
ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን።
፮ በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር
ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ።
፯ በውድ ልጁም፥ እንደ ጸጋው ባለ ጠግነት
መጠን፥ በደሙ የተደረገ ቤዛነታችንን አገኘን እርሱም
የበደላችን ሰርየት።
፰ ጸጋውንም በጥበብና በአእምሮ ሁሉ አበዛልን።
፱ በክርስቶስ ለማድረግ እንደ ወደደ እንደ አሳቡ፥
የፈቃዱን ምሥጢር አስታውቆናልና፤
፲ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለው አሳቡም
በሰማይና በምድር ያለውን ሁሉ በክርስቶስ
ለመጠቅለል ነው።
፲፩ እንደ ፈቃዱ ምክር ሁሉን የሚሠራ እንደ እርሱ
አሳብ፥ አስቀድመን የተወሰንን በክርስቶስ ደግሞ
ርስትን ተቀበልን።
፲፪ ይኸውም፥ በክርስቶስ አስቀድመን ተስፋ
ያደረግን እኛ ለክብሩ ምስጋና እንሆን ዘንድ ነው።
፲፫ እናንተም ደግሞ የእውነትን ቃል፥ ይኸውም
የመዳናችሁን ወንጌል፥ ሰምታችሁ ደግሞም በክርስቶስ
አምናችሁ፥ በተስፋው መንፈስ በመንፈስ ቅዱስ
ታተማችሁ፤
፲፬ እርሱም የርስታችን መያዣ ነው፥ ለእግዚአብሔር
ያለውን ሁሉ እስኪዋጅ ድረስ፥ ይህም ለክብሩ ምስጋና
ይሆናል።
፲፭ ስለዚህ እኔ ደግሞ በእናንተ ዘንድ ስለሚሆን
በጌታ በኢየሱስ ስለ ማመንና ለቅዱሳን ሁሉ ስለሚሆን
መውደድ ሰምቼ፥
፲፮ ስለ እናንተ እያመሰገንሁ ሰጸልይ ስለ እናንተ
ማሳሰብን አልተውም፤
፲፯ የክብር አባት የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
አምላክ እርሱን በማወቅ የጥበብንና የመገለጥን
መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ።
፲፰-፳፪ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛለት ከሁሉ
በላይም ራስ እንዲሆን ለቤተ ክርስቲያን ሰጠው።
፳፫ እርስዋም አካሉና ሁሉን በሁሉ የሚሞላ የእርሱ
ሙላቱ ናት።

፪

፩-፫ በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥
የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን
ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ
ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።
፬ ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ
ሆነ፥
፭ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን
እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥
በጸጋ ድናችኋልና፥
፮-፰ ጸጋው በእምነት አድናችኋልና፤ ይህም
የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤
፱ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም።
፲ እኛ ፍጥረቱ ነንና፤ እንመላለስበት ዘንድ
እግዚአብሔር አስቀድሞ ያዘጋጀውን መልካሙን ሥራ
ለማድረግ በክርስቶስ ኢየሱስ ተፈጠርን።
፲፩ ስለዚህ እናንተ አስቀድሞ በሥጋ አሕዛብ
የነበራችሁ፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት
ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤
፲፪ በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ
ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ
በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም
ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ።
፲፫ አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ
በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም
ቀርባችኋል።
፲፬-፲፮ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ
ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር
ያስታርቅ ዘንድ ነው።
፲፯ መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን፥
ቀርበው ለነበሩትም ሰላምን የምሰራች ብሎ ሰበከ፤
፲፰ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ
መግባት አለንና።
፲፱ እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር
ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ
እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።
፳ በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥
የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤
፳፩ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ ቅዱስ
ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤
፳፪ በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ
ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።

፫

፩ ስለዚህም አሕዛብ ስለ ሆናችሁ ስለ እናንተ
የክርስቶስ ኢየሱስ እስር የሆንሁ እኔ ጳውሎስ
ለእግዚአብሔር እንበረከካለሁ።
፪ ለእናንተ ስለ ተሰጠኝ ስለ እግዚአብሔር ጸጋ
መጋቢነት በእርግጥ ሰምታችኋል፤
፫ እስቀድሜ በአጭሩ እንደ ጻፍሁ፥ ይህን ምሥጢር
በመግለጥ አስታወቀኝ፤
፬ ይህንም ሰታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት
እንደማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ፤
፭-፯ እንደ ኃይሉ ሥራ እንደ ተሰጠኝም እንደ
እግዚአብሔር ጸጋ ሰጦታ መጠንየወንጌል አገልጋይ
ሆንሁለት።
፰-፲ ብዙ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጥበብ አሁን በቤተ
ክርስቲያን በኩል በሰማያዊ ሰፍራ ውስጥ ላሉት
አለቆችና ሥልጣናት ትታወቅ ዘንድ፤
፲፩ ይህም በክርስቶስ ኢየሱስ በጌታችን የፈጸመው
የዘላለም አሳብ ነበረ፥

፲፪ በእርሱም ዘንድ ባለ እምነታችን በኩል በመታመን ድፍረትና መግባት በእርሱ አለን።
፲፫ ስለዚህ ስለ እናንተ ስላለ መከራዬ እንዳትታክቱ እለምናችኋለሁ፥ ክብራችሁ ነውና።
፲፬-፲፯ እንግዲህ በእኛ እንደሚሠራው ኃይል መጠን ከምንለምነው ወይም ከምናሰበው ሁሉ ይልቅ እጅግ አብልጦ ሊያደርግ ለሚቻለው፥
፳፩ ለእርሱ በቤተ ክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ እስከ ትውልዶች ሁሉ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።

፬

፩ እንግዲህ በጌታ እስር የሆንሁ እኔ በተጠራችሁበት መጠራታችሁ እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እለምናችኋለሁ፤
፪ በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፤ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤
፫ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ።
፬ በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤
፭ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤
፮ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።
፯ ነገር ግን እንደ ክርስቶስ ስጦታ መጠን ለእያንዳንዳችን ጸጋ ተሰጠን።
፰ ስለዚህ። ወደ ላይ በወጣ ጊዜ ምርኮን ማረከ ለሰዎችም ስጦታን ሰጠ ይላል።
፱ ወደ ምድር ታችኛ ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፥ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው?
፲ ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።
፲፩ እርሱም አንዳንዶቹ ሐዋርያት፥ ሌሎቹም ነቢያት፥ ሌሎቹም ወንጌልን ሰባኪዎች፥ ሌሎቹም እረኞችና አስተማሪዎች እንዲሆኑ ሰጠ፤
፲፪-፲፬ እንደ ሰሕተት ሸንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህም እየተነሳፈፍን ሕፃናት መሆን ወደ ፊት እይገባንም፥
፲፭ ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ፤
፲፮ ከእርሱም የተነሣ አካል ሁሉ እያንዳንዱ ክፍል በልክ እንደሚሠራ፥ በተሰጠለት በጅማት ሁሉ እየተጋጠመና እየተያያዘ፥ ራሱን በፍቅር ለማነጽ አካሉን ያሳድጋል።
፲፯ እንግዲህ እሕዛብ ደግሞ በአእምሮአቸው ከንቱነት እንደሚመላለሱ ከእንግዲህ ወዲህ እንዳትመላለሱ እላለሁ በጌታም ሆኜ እመሰክራለሁ።
፲፰ እነርሱ ባለማወቃቸው ጠንቅ በልባቸውም ደንዳንነት ጠንቅ ልቡናቸው ጨለመ፥ ከእግዚአብሔርም ሕይወት ራቁ፤
፲፱ ደንዝዘውም በመመኘት ርኩሰትን ሁሉ ለማድረግ ራሳቸውን ወደ ሴሰኝነት አሳልፈው ሰጡ።
፳ እናንተ ግን ክርስቶስን እንደዚህ አልተማራችሁም፤
፳፩ በእርግጥ ሰምታችሁታልና፥ እውነትም በኢየሱስ እንዳለ በእርሱ ተምራችኋል፤
፳፪ ፊተኛ ኑሮአችሁን እያሰባችሁ እንደሚያታልል ምኞት የሚጠፋውን አሮጌውን ሰው አስወግዱ፥
፳፫ በአእምሮአችሁም መንፈስ ታደሱ፥
፳፬ ለእውነትም በሚሆኑ ጽድቅና ቅድስና እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረውን አዲሱን ሰው ልበሱ።
፳፭ ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ፥ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ።
፳፮ ተቆጡ ኃጢአትንም አታድርጉ፤
፳፯ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።
፳፰ የሰረቀ ከእንግዲህ ወዲህ አይስረቅ፥ ነገር ግን በዚያ ፈንታ ለጎደለው የሚያካፍለው እንዲኖርለት በገዛ እጆቹ መልካምን እየሠራ ይድከም።
፳፱ ለሚሰሙት ጸጋን ይስጥ ዘንድ፥ እንደሚያስፈልግ ለማነጽ የሚጠቅም ማናቸውም በጎ ቃል እንጂ ክፉ ቃል ከአፋችሁ ከቶ አይውጣ።
፴ ለቤዛም ቀን የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።
፴፩ መራርነትና ንዴት ቁጣም ጩኸትም መሳደብም ሁሉ ከክፋት ሁሉ ጋር ከእናንተ ዘንድ ይወገድ።
፴፪ እርስ በርሳችሁም ቸሮችና ርኅሩኆች ሁኑ፥ እግዚአብሔርም ደግሞ በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ።

፭

፩ እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥
፪ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።
፫ ለቅዱሳን እንደሚገባ ግን ዝሙትና ርኩሰት ሁሉ ወይም መመኘት በእናንተ ዘንድ ከቶ አይሰማ፤
፬ የሚያሳፍር ነገርም የሰንፍና ንግግርም ወይም ዋዛ የማይገቡ ናቸውና አይሁኑ፥ ይልቁን ምስጋና እንጂ።
፭ ይህን እወቁ፤ አመንዝራም ቢሆን ወይም ርኩስ ወይም የሚመኝ እርሱም ጣዖትን የሚያመልክ በክርስቶስና በእግዚአብሔር መንግሥት ርስት የለውም።
፮ ከዚህ የተነሣ በማይታዘዙት ልጆች ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ይመጣልና ማንም በከንቱ ንግግር አያታልላችሁ።
፯ እንግዲህ ከእነርሱ ጋር ተካፋዮች አትሁኑ፤
፰ ቀድሞ ጨለማ ነበራችሁና፥ አሁን ግን በጌታ ብርሃን ናችሁ፤
፱-፲፩ ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥
፲፪ እነርሱ በሰውር ስለሚያደርጉት መናገር እንኳ ነውር ነውና፤
፲፫ ሁሉ ግን በብርሃን ሲገለጥ ይታያል፤ የሚታየው ሁሉ ብርሃን ነውና።
፲፬ ስለዚህ። እንተ የምትተኛ ንቃ ከሙታንም ተነሣ ክርስቶስም ያበራልሃል ይላል።

፲፭ እንግዲህ እንደ ጥበበኞች እንጂ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ፤
፲፮ ቀኖቹ ክፉዎች ናቸውና ዘመኑን ዋጁ።
፲፯ ስለዚህ የጌታ ፈቃድ ምን እንደ ሆነ አስተውሉ እንጂ ሞኞች አትሁኑ።
፲፰ መንፈስ ይሙላባችሁ እንጂ በወይን ጠጅ አትስከሩ ይህ ማባከን ነውና፤
፲፱ በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ እርስ በርሳችሁ ተነጋገሩ፤ ለጌታ በልባችሁ ተቀኙና ዘምሩ፤
፳ ሁልጊዜ ስለ ሁሉ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምላካችንንና አባታችንን ስለ ሁሉ አመስግኑ።
፳፩ ለእያንዳንዳችሁ በክርስቶስ ፍርሃት የተገዛችሁ ሁኑ።
፳፪ ሚስቶች ሆይ፥ ለጌታ እንደምትገዙ ለባሎቻችሁ ተገዙ፤
፳፫ ክርስቶስ ደግሞ የቤተ ክርስቲያን ራስ እንደ ሆነ እርሱም አካሉን የሚያድን እንደ ሆነ ባል የሚስት ራስ ነውና።
፳፬ ዳሩ ግን ቤተ ክርስቲያን ለክርስቶስ እንደምትገዛ እንዲሁ ሚስቶች ደግሞ በሁሉ ለባሎቻቸው ይገዙ።
፳፭-፳፯ እድፈት ወይም የፊት መጨማደድ ወይም እንዲህ ያለ ነገር ሳይሆንባት ቅድስትና ያለ ነውር ትሆን ዘንድ ክብርት የሆነችን ቤተ ክርስቲያን ለራሱ እንዲያቀርብ ፈለገ።
፳፰ እንዲሁም ባሎች ደግሞ እንደ ገዛ ሥጋቸው አድርገው የገዛ ሚስቶቻቸውን ሊወዱአቸው ይገባቸዋል። የገዛ ሚስቱን የሚወድ ራሱን ይወዳል፤
፳፱-፴፪ ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።
፴፪ ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው፥ እኔ ግን ይህን ስለ ክርስቶስና ስለ ቤተ ክርስቲያን እላለሁ።
፴፫ ሆኖም ከእናንተ ደግሞ እያንዳንዱ የገዛ ሚስቱን እንዲህ እንደ ራሱ አድርጎ ይውደዳት፥ ሚስቱም ባልዋን ትፍራ።

፮

፩ ልጆች ሆይ፥ ለወላጆቻችሁ በጌታ ታዘዙ፥ ይህ የሚገባ ነውና።
፪-፬ እናንተም አባቶች ሆይ፥ ልጆቻችሁን በጌታ ምክርና በተግሣጽ አሳድጉአቸው እንጂ አታስቆጡአቸው።
፭ ባሪያዎች ሆይ፥ ለክርስቶስ እንደምትታዘዙ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ በልባችሁ ቅንነት በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ ታዘዙ፤
፮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚያደርጉ እንደ ክርስቶስ ባሪያዎች እንጂ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ አትሁኑ።
፯ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምትገዙ በትጋትና በበጎ ፈቃድ ተገዙ፤
፰ ባሪያ ቢሆን ወይም ጨዋ ሰው፥ እያንዳንዱ የሚያደርገውን መልካም ነገር ሁሉ ከጌታ በብድራት እንዲቀበለው ታውቃላችሁና።
፱ እናንተም ጌቶች ሆይ፥ ዛቻውን ትታችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው፥ በእነርሱና በእናንተ ላይ የሚገዛው ጌታ በሰማይ እንዳለ ለሰው ፊትም እንዳያደላ ታውቃላችሁና።
፲ በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሁኑ።
፲፩ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ።
፲፪ መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ሰፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።
፲፫ ስለዚህ በክፉው ቀን ለመቃወም፥ ሁሉንም ፈጽማችሁ ለመቆም እንድትችሉ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ አንሡ።
፲፬-፲፰ በሁሉም ላይ ጨምራችሁ የሚንበለበሉትን የክፉውን ፍላጻዎች ሁሉ ልታጠፉ የምትችሉበትን የእምነትን ጋሻ አንሡ፤
፲፯ የመዳንንም ራስ ቁር የመንፈስንም ሰይፍ ያዙ እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ነው።
፲፰ በጸሎትና በልመናም ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ፤ በዚህም አሳብ ስለ ቅዱሳን ሁሉ እየለመናችሁ በመጽናት ሁሉ ትጉ፤
፲፱ ደግሞ የወንጌልን ምሥጢር በግልጥ እንዳስታውቅ አፌን በመክፈት ቃል ይሰጠኝ ዘንድ ስለ እኔ ለምኑ፤
፳ ስለ ወንጌልም በሰንሰለት መልእክተኛ የሆንሁ፥ መናገር እንደሚገባኝ ስለ እርሱ በግልጥ እናገር ዘንድ ለምኑ።
፳፩ ነገር ግን እናንተ ደግሞ እንዴት እንዳለሁ ኑሮዬን እንድታውቁ የተወደደ ወንድምና በጌታ የታመነ አገልጋይ ቲኪቆስ ሁሉን ያስታውቃችኋል፤
፳፪ ወሬአችንን እንድታውቁና ልባችሁን እንዲያጽናና ወደ እናንተ የምልከው ስለዚህ ምክንያት ነው።
፳፫ ከእግዚአብሔር አብ ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምና ፍቅር ከእምነት ጋር ለወንድሞች ይሁን።
፳፬ ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ባለመጥፋት ከሚወዱ ሁሉ ጋር ጸጋ ይሁን፤ አሜን።

ወደ ፊልጵስዩስ ሰዎች

፩ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያዎች የሆኑ ጳውሎስና ጢሞቴዎስ በፊልጵስዩስ ለሚኖሩ ከኤጲስ ቆጶሳትና ከዲያቆናት ጋር በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት ቅዱሳን ሁሉ፤
፪ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፫-፮ በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤
፯ በእስራቴም ወንጌልንም መመከቻና መጽኛ በማድረግ ሁላችሁ ከእኔ ጋር በጸጋ ተካፋዮች ስለ ሆናችሁ፥ በልቤ ትኖራላችሁና ስለ ሁላችሁ ይህን ላሰብ ይገባኛል።
፰ በክርስቶስ ኢየሱስ ፍቅር ሁላችሁን እንዴት እንድናፍቃችሁ እግዚአብሔር ምስክሬ ነውና።
፱-፲፪ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ይህ የደረሰብኝ በእውነት ወንጌልን ለማስፋት እንደ ሆነ ታውቁ ዘንድ እወዳለሁ።
፲፫ ስለዚህም እስራቴ ስለ ክርስቶስ እንዲሆን በንጉሥ ዘበኞች ሁሉና በሌሎች ሁሉ ዘንድ ተገልጦአል፥
፲፬ በጌታም ካሉት ወንድሞች የሚበዙት ስለ እስራቴ ታምነው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲነግሩ ያለ ፍርሃት ከፊት ይልቅ ይደፍራሉ።
፲፭ አንዳንዶች ከቅንእትና ከክርክር እንኳ ሌሎች ግን ከበጎ ፈቃድ የተነሣ ክርስቶስን ይሰብኩታል፤
፲፮ እነዚህ ወንጌልን መመከቻ ለማድረግ እንደ ተሾምሁ አውቀው በፍቅር ይሰብካሉ፥
፲፯ እነዚያ ግን በእስራቴ ላይ መከራን ሊያመጡብኝ መስሎአቸው፥ ለወገናቸው የሚጠቅም ፈልገው በቅን አሳብ ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ ያወራሉ።
፲፰ ምን አለ? ቢሆንም በሁሉ ጎዳና፥ በማመካኘት ቢሆን ወይም በቅንነት ቢሆን፥ ክርስቶስ ይሰበካል ስለዚህም ደስ ብሎኛል።
፲፱ ወደ ፊትም ደግሞ ደስ ይለኛል፤ ይህ በጸሎታችሁና በኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ መሰጠት ለመዳኔ እንዲሆንልኝ አውቃለሁና፥
፳ ይህ ናፍቆቴ ተስፋዬም ነውና፤ በአንድ ነገር እንኳ አላፍርም ነገር ግን በህይወት ብኖር ወይም ብሞት፥ ክርስቶስ በግልጥነት ሁሉ እንደ ወትሮው አሁን ደግሞ በሰጋዬ ይከብራል።
፳፩ ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና።
፳፪ ነገር ግን በሰጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን፥ ምን እንድመርጥ ኣላስታውቅም።
፳፫ በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፤ ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤
፳፬ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው።
፳፭-፳፯ ይሁን እንጂ፥ መጥቼ ባያችሁ ወይም ብርቅ፥ በአንድ ልብ ስለ ወንጌል ሃይማኖት አብራችሁ እየተጋደላችሁ፥ በአንድ መንፈስ እንድትቆሙ ስለ ኑሮአችሁ እስማ ዘንድ፥ ለክርስቶስ ወንጌል እንደሚገባ ኑሩ።
፳፰ በአንድም ነገር እንኳ በተቃዋሚዎች አትደንግጡ፤ ይህም ለእነርሱ የጥፋት፥ ለእናንተ ግን የመዳን ምልክት ነው፥ ይህም ከእግዚአብሔር ነው፤
፳፱ ይህ ስለ ክርስቶስ ተሰጥቶአችኋልና፤ ስለ እርሱ መከራ ደግሞ ልትቀበሉ እንጂ በእርሱ ልታምኑ ብቻ አይደለም፤
፴ በእኔ ያያችሁት አሁንም በእኔ እንዳለ የምትሰሙት፥ ያው መጋደል ደርሶባችኋልና።

፪

፩ በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፥ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፥ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤
፪ በአንድ አሳብ ተሰማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤
፫ ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቊጠር፤
፬ እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።
፭ በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።
፮ እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥
፯ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥
፰ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።
፱ በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤
፲ ይህም በሰማይና በምድር ከምድርም በታች ያሉት ሁሉ በኢየሱስ ስም ይንበረከኩ ዘንድ፥
፲፩ መላስም ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ ክብር ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ እንደ ሆነ ይመስክር ዘንድ ነው።
፲፪ ስለዚህ፥ ወዳጆቼ ሆይ፥ ሁልጊዜ እንደ ታዘዛችሁ፥ በእናንተ ዘንድ በመኖሬ ብቻ ሳይሆን ይልቁን አሁን ሰርቅ፥ በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የራሳችሁን መዳን ፈጽሙ፤
፲፫ ስለ በጎ ፈቃዱ መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሠራ እግዚአብሔር ነውና።
፲፬-፲፮ በእነርሱም መካከል የሕይወትን ቃል እያቀረባችሁ በዓለም እንደ ብርሃን ትታያላችሁ፥ ስለዚህም በከንቱ እንዳልሮጥሁ በከንቱም እንዳልደከምሁ በክርስቶስ ቀን የምመካበት ይሆንልኛል።
፲፯ ነገር ግን በእምነታችሁ መሥዋዕትና አገልግሎት ተጨምሬ ሕይወቴ እንኳ ቢፈስ፥ ደስ ብሎኛል፤ ከሁላችሁም ጋር አብሬ ደስ ብሎኛል፤
፲፰ እናንተም ደግሞ እንዲሁ ደስ ይበላችሁ ከእኔም ጋር አብራችሁ ደስ ይበላችሁ።

፲፱ ነገር ግን ኑሮአችሁን ሳውቅ እኔ ደግሞ ደስ
እንዲለኝ ፈጥኜ ጢሞቴዎስን ልልክላችሁ በጌታ
በኢየሱስ ተስፋ እደርጋለሁ።
፳ እንደ እርሱ ያለ፥ ስለ ኑሮአችሁ በቅንነት
የሚጨነቅ፥ ማንም የለኝምና፤
፳፩ ሁሉ የራሳቸውን ይፈልጋሉና፥ የክርስቶስ
ኢየሱስን አይደለም።
፳፪ ነገር ግን ልጅ ለአባቱ እንደ ሚያገለግል ከእኔ ጋር
ሆኖ ለወንጌል እንደ አገለገለ መፈተኑን ታውቃላችሁ።
፳፫ እንግዲህ እንዴት እንደምሆን ባየሁ ጊዜ፥ እርሱን
ቶሎ እንድልክ ተስፋ እደርጋለሁ፤
፳፬ ራሴ ደግሞ ግን ፈጥኜ እንድመጣ በጌታ
ታምኜአለሁ።
፳፭ ነገር ግን ወንድሜንና ከእኔ ጋር አብሮ ሠራተኛ
ወታደርም የሚሆነውን፥ የእናንተ ግን መልእክተኛ
የሆነውና የሚያስፈልገኝን የሚያገለግለውን
አፍሮዲጡን እንድልክላችሁ በግድ አስባለሁ፤
፳፮ ሁላችሁን ይናፍቃልና፥ እንደ ታመመም ሰለ
ሰማችሁ ይተክዛል።
፳፯ በእውነት ታሞ ለሞት እንኳ ቀርቦ ነበርና፤
ነገር ግን እግዚአብሔር ማረው፥ ኀዘን በኀዘን ላይ
እንዳይጨመርብኝ ለእኔ ደግሞ እንጂ ለእርሱ ብቻ
አይደለም።
፳፰ እንግዲህ እንደ ገና ሰታዩት ደስ እንዲላችሁ
ለእኔም ኀዘኔ እንዲቃለል በብዙ ፍጥነት እልከዋለሁ።
፳፱ እንግዲህ በሙሉ ደስታ በጌታ ተቀበሉት፥ እርሱን
የሚመስሉትንም አክብሩአቸው፤
፴ በእኔ ዘንድ ካላችሁ አገልግሎት እናንተ
ስለሌላችሁ የጎደለኝን እንዲፈጽም፥ በነፍሱ ተወራርዶ
ከጌታ ሥራ የተነሣ እስከ ሞት ቀርቦአልና።

፫

፩ በቀረውስ፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ በጌታ ደስ
ይበላችሁ። ስለ አንድ ነገር መልሼ ልጽፍላችሁ እኔን
አይታክተኝም ለእናንተ ግን ደኅና ነው።
፪ ከውሾች ተጠበቁ፥ ከክፉዎችም ሠራተኞች
ተጠበቁ፥ ከሐሰተኛም መገረዝ ተጠበቁ።
፫ እኛ በመንፈስ እግዚአብሔርን የምናመልክ
በክርስቶስ ኢየሱስም የምንመካ በሥጋም የማንታመን
እኛ የተገረዝን ነንና።
፬ እኔ ግን በሥጋ ደግሞ የምታመንበት አለኝ። ሌላ
ሰው ማንም ቢሆን በሥጋ የሚታመንበት እንዳለው
ቢመሰለው፥ እኔ እበልጠዋለሁ።
፭ በሰምንተኛው ቀን የተገረዝሁ፥ ከእስራኤል
ትውልድ፥ ከብንያም ወገን፥ ከዕብራውያን ዕብራዊ
ነኝ፤ ስለ ሕግ ብትጠይቁ፥ ፈሪሳዊ ነበርሁ፤
፮ ስለ ቅንዓት ብትጠይቁ፥ ቤተ ክርስቲያንን አሳዳጅ
ነበርሁ፤ በሕግ ሰለሚገኝ ጽድቅ ብትጠይቁ፥ ያለ ነቀፋ
ነበርሁ።
፯ ነገር ግን ለእኔ ረብ የነበረውን ሁሉ ስለ ክርስቶስ
እንደ ጉዳት ቈጥሬዋለሁ።
፰-፲፪ አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደ
ሆንሁ አይደለም፥ ነገር ግን ስለ እርሱ በክርስቶስ
ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግሞ እይዛለሁ ብዬ
እፈጥናለሁ።
፲፫ ወንድሞች ሆይ፥ እኔ ገና እንዳልያዝሁት
እቈጥራለሁ፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ
ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥
፲፬ በክርስቶስ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ያለውን
የእግዚአብሔርን መጥራት ዋጋ እንዳገኝ ምልክትን
እፈጥናለሁ።
፲፭ እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤
በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር
ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል፤
፲፮ ሆኖም በደረሰንበት በዚያ እንመላለስ።
፲፯ ወንድሞች ሆይ፥ እኔን የምትመስሉ ሁኑ፥
እኛም እንደ ምሳሌ እንደምንሆንላችሁ፥ እንዲሁ
የሚመላለሱትን ተመልከቱ።
፲፰ ብዙዎች ለክርስቶስ መስቀል ጠላቶቹ ሆነው
ይመላለሳሉና፤ ብዙ ጊዜ ሰለ እነርሱ አልኋችሁ፥
አሁንም እንኳ እያለቀስሁ እላለሁ።
፲፱ መጨረሻቸው ጥፋት ነው፥ ሆዳቸው እምላካቸው
ነው፥ ክብራቸው በነውራቸው ነው፥ አሳባቸው ምድራዊ
ነው።
፳ እኛ አገራችን በሰማይ ነውና፥ ከዚያም ደግሞ
የሚመጣ መድኃኒትን እርሱንም ጌታን ኢየሱስ
ክርስቶስን እንጠባበቃለን፤
፳፩ እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ
እንደሚችልበት አሠራር፥ ክቡር ሥጋውን እንዲመስል
የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል።

፬

፩ ስለዚህ፥ የምወዳችሁና የምናፍቃችሁ፥ ደስታዬና
አክሊሌ የምትሆኑ ወንድሞቼ ሆይ፥ እንዲሁ በጌታ
ቁሙ፥ ወዳጆች ሆይ።
፪ በአንድ አሳብ በጌታ እንዲሰማሙ ኤዎድያንን
እመክራለሁ ሲንጤኪንንም እመክራለሁ።
፫ አንተም ደግሞ በሥራዬ አብረህ የተጠመድህ
እውነተኛ ሆይ፥ እንድታግዛቸው እለምንሃለሁ፤
ሰሞቻቸው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት
ከቀሌምንጦስና ደግሞ ከእኔ ጋር አብረው ከሠሩት
ከሌሎቹ ጋር በወንጌል ከእኔ ጋር አብረው
ተጋድለዋልና።
፬ ሁልጊዜ በጌታ ደስ ይበላችሁ፤ ደግሜ እላለሁ፥
ደስ ይበላችሁ።
፭ ገርነታችሁ ለሰው ሁሉ ይታወቅ።
፮ ጌታ ቅርብ ነው። በነገር ሁሉ በጸሎትና በምልጃ
ከምስጋና ጋር በእግዚአብሔር ዘንድ ልመናችሁን
አስታውቁ እንጂ በአንዳች አትጨነቁ።
፯ አእምሮንም ሁሉ የሚያልፍ የእግዚአብሔር ሰላም
ልባችሁንና አሳባችሁን በክርስቶስ ኢየሱስ ይጠብቃል።
፰ በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ እውነተኛ የሆነውን
ነገር ሁሉ፥ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ፥ ጽድቅ
የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ንጹሕ የሆነውን ነገር ሁሉ፥ ፍቅር
ያለበትን ነገር ሁሉ፥ መልካም ወሬ ያለበትን ነገር ሁሉ፥
በጎነት ቢሆን ምስጋናም ቢሆን፥ እነዚህን አስቡ፤
፱ ከእኔ የተማራችሁትንና የተቀበላችሁትን
የሰማችሁትንም ያያችሁትንም እነዚህን አድርጉ፤
የሰላምም አምላክ ከእናንተ ጋር ይሆናል።
፲ ነገር ግን አሁን ከጊዜ በኋላ ስለ እኔ እንደ ገና
ልታስቡ ስለ ጀመራችሁ፥ በጌታ እጅግ ደስ ይለኛል፤
ጊዜ አጣችሁ እንጂ፥ ማስብስ ታስቡ ነበር።

፲፭ ይህን ስል ስለ ጉድለት አልልም፤ የምኖርበት ኑሮ
ይበቃኛል ማለትን ተምሬአለሁና።
፲፮ መዋረድንም አውቃለሁ መብዛትንም አውቃለሁ፤
በእያንዳንዱ ነገር በነገርም ሁሉ መጥገብንና
መራብንም መብዛትንና መጉደልን ተምሬአለሁ።
፲፯ ኃይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን እችላለሁ።
፲፰ ሆኖም በመከራዬ ከእኔ ጋር ስለ ተካፈላችሁ
መልካም አደረጋችሁ።
፲፱ የፊልጵስዩስ ሰዎች ሆይ፥ ወንጌል በመጀመሪያ
ሲሰበክ፥ ከመቄዶንያ በወጣሁ ጊዜ፥ ከእናንተ ብቻ
በቀር ሌላ ቤተ ክርስቲያን በመስጠትና በመቀበል
ስሌት ከእኔ ጋር እንዳልተካፈለች እናንተ ደግሞ
ታውቃላችሁ፤
፳ በተሰሎንቄ እንኳ ሳለሁ፥ አንድ ጊዜና ሁለት ጊዜ
ያሰፈለገኝን ሰዳችሁልኝ ነበርና።
፳፩ በስሌታችሁ የሚበዛውን ፍሬ እንጂ ስጦታውን
ፈላጊ አይደለሁም።
፳፪ ነገር ግን ሁሉ አለኝ ይበዛልኝማል፤ የመዓዛ ሽታና
የተወደደ መሥዋዕት የሚሆነውን ለእግዚአብሔርም
ደስ የሚያሰኘውን ስጦታችሁን ከአፍሮዲጡ ተቀብዬ
ተሞልቼአለሁ።
፲፱ አምላኬም እንደ ባለ ጠግነቱ መጠን
በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ
ይሞላባችኋል።
፳ ለአምላካችንና ለአባታችንም እስከ ዘላለም ድረስ
ክብር ይሁን፤ አሜን።
፳፩ ለቅዱሳን ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ሰላምታ
አቅርቡ። ከእኔ ጋር ያሉቱ ወንድሞች ሰላምታ
ያቀርቡላችኋል።
፳፪ ቅዱሳን ሁሉ ይልቁንም ከቄሣር ቤት የሆኑቱ
ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፳፫ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ
ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ቆላስይስ ሰዎች

፩ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ
የሆነ ጳውሎስ ጢሞቴዎስም ወንድሙ፥
፪ በቈላስይስ ለሚኖሩ ቅዱሳንና በክርስቶስ ለታመኑ
ወንድሞች፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ይሁን።
፫-፮ ይህም በዓለም ሁሉ ደግሞ እንዳለ ወደ
እናንተ ደርሶአል፥ እግዚአብሔርንም ጸጋ በእውነት
ከሰማችሁበትና ካወቃችሁበት ቀን ጀምሮ፥ በእናንተ
ደግሞ እንዳለ እንዲህ በዓለም ፍሬ ያፈራል ያድግማል።
፯ ከተወደደ ከእኛም ጋር አብሮ ባሪያ ከሆነው
ከኤጳፍራ እንዲህ ተማራችሁ፥ እርሱም ሰለ እናንተ
ታማኝ የክርስቶስ አገልጋይ ነው።
፰ ደግሞም በመንፈስ ሰለሚሆን ሰለ ፍቅራችሁ
አስታወቀን።
፱ ሰለዚሁ እኛ ደግሞ ይህን ከሰማንበት ቀን
ጀምረን የፈቃዱ እውቀት መንፈሳዊ ጥበብንና አእምሮን
ሁሉ እንዲሞላባችሁ እየለመንን፥ ሰለ እናንተ ጸሎትን
አልተውንም።
፲-፲፪ ከደስታም ጋር በሁሉ ለመጽናትና ለመታገሥ
እንደ ክብሩ ጉልበት መጠን በኃይል ሁሉ እየበረታችሁ፥
በቅዱሳንም ርስት በብርሃን እንድንካፈል ያበቃንን
አብን እያመሰገናችሁ፥ በነገር ሁሉ ደስ ልታሰኙ ለጌታ
እንደሚገባ ትመላለሱ ዘንድ እንለምናለን።
፲፫-፲፭ እርሱም ከሁሉ በፊት ነው ሁሉም በእርሱ
ተጋጥሞአል።
፲፮ እርሱም የአካሉ ማለት የቤተ ክርስቲያን ራስ
ነው። እርሱም በሁሉ ፊተኛ ይሆን ዘንድ፥ መጀመሪያ
ከሙታንም በኩር ነው።
፲፱-፳፫ ይህም፥ ተመሥርታችሁና ተደላድላችሁ
ከሰማችሁትም ከወንጌል ተስፋ ሳትናወጡ፥
በሃይማኖት ጸንታችሁ ብትኖሩ ይሆናል። ያም ወንጌል
ከሰማይ በታች ባለው ፍጥረት ሁሉ ዘንድ የተሰበከ
ነው፥ እኔም ጳውሎስ የእርሱ አገልጋይ ሆንሁ።
፳፬ አሁን በመከራዬ ሰለ እናንተ ደስ ይለኛል፥
ሰለ አካሉም ማለት ሰለ ቤተ ክርስቲያን በሥጋዬ
በክርስቶስ መከራ የጐደለውን እፈጽማለሁ።
፳፭ ሰለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር
መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ
እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ።
፳፮ ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ
ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ
ተገልጦአል።
፳፯ ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው
የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ
ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው
ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው።
፳፰ እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ
እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ
በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው።
፳፱ ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ
እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ።

፪

፩ ሰለ እናንተና በሎዶቅያ ሰላሉት ፊቴንም በሥጋ
ሰላላዩት ሁሉ እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ
ልታውቁ እወዳለሁና።
፪ ልባቸው እንዲጸናና፥ በፍቅርም ተባብረው
በማስተዋል ወደሚገኝበት ወደ መረዳት ባለ
ጠግነት ሁሉ እንዲደርሱ የእግዚአብሔርንም ምሥጢር
እርሱንም ክርስቶስን እንዲያውቁ እጋደላለሁ።
፫ የተሰወረ የጥበብና የእውቀት መዝገብ ሁሉ
በእርሱ ነውና።
፬ ማንም በሚያባብል ቃል እንዳያስታችሁ ይህን
እላለሁ።
፭ በሥጋ ምንም እንኳ ብርቅ፥ በመንፈስ ከእናንተ
ጋር ነኝና፥ ሥርዓታችሁንም በክርስቶስም ያለውን
የእምነታችሁን ጽናት እያየሁ ደስ ይለኛል።
፮ እንግዲህ ጌታን ክርስቶስ ኢየሱስን እንደ
ተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ።
፯ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታነጹ፥ እንደ ተማራችሁም
በሃይማኖት ጽኑ፥ ምስጋናም ይብዛላችሁ።
፰ እንደ ክርስቶስ ትምህርት ሳይሆን፥ እንደ
ሰው ወግና እንደ ዓለማዊ እንደ መጀመሪያ
ትምህርት ባለ በፍልስፍና በከንቱም መታለል ማንም
እንዳይማርካችሁ ተጠበቁ።
፱ በእርሱ የመለኮት ሙላት ሁሉ በሰውነት ተገልጦ
ይኖራልና።
፲ ለአለቅነትና ለሥልጣንም ሁሉ ራስ በሆነ በእርሱ
ሆናችሁ ተሞልታችኋል።
፲፩ የሥጋንም ሰውነት በመገፈፍ፥ በክርስቶስ
መገረዝ፥ በእጅ ባልተደረገ መገረዝ በእርሱ ሆናችሁ
ደግሞ ተገረዛችሁ።
፲፪ በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀብራችሁ፥
በጥምቀት ደግሞ፥ ከሙታን ባስነሣው በእግዚአብሔር
አሠራር በማመናችሁ፥ ከእርሱ ጋር ተነሣችሁ።
፲፫ እናንተም በበደላችሁና ሥጋችሁን ባለመገረዝ
ሙታን በሆናችሁ ጊዜ፥ ከእርሱ ጋር ሕይወትን
ሰጣችሁ። በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ።
፲፬ በእኛ ላይ የነበረውን የሚቃወመንንም በትእዛዛት
የተጻፈውን የዕዳ ጽሕፈት ደመሰሰው። እርሱንም
በመስቀል ጠርቆ ከመንገድ አስወግዶታል።
፲፭ አለቅነትንና ሥልጣናትን ገፎ፥ ድል በመነሣት
በእርሱ እያዞራቸው በግልጥ አሳያቸው።
፲፮ እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ሰለ
በዓል ወይም ሰለ ወር መባቻ ወይም ሰለ ሰንበት
ማንም አይፍረድባችሁ።
፲፯ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥
አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።
፲፰ ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥
ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ
በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ።
፲፱ እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥
ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን
እየተቀበለ እየተጋጠመም፥ እግዚአብሔር በሚሰጠው
ማደግ ያድጋል።
፳-፳፪ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። አትያዝ፥
አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም

እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና።
፳፫ ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም።

፫

፩ እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፥ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦ ባለበት በላይ ያለውን እሹ።
፪ በላይ ያለውን አስቡ እንጂ በምድር ያለውን አይደለም።
፫ ሞታችኋልና፥ ሕይወታችሁም በእግዚአብሔር ከክርስቶስ ጋር ተሰውሮአልና።
፬ ሕይወታችሁ የሆነ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ እናንተ ደግሞ ከእርሱ ጋር በክብር ትገለጣላችሁ።
፭ እንግዲህ በምድር ያሉቱን ብልቶቻችሁን ግደሉ፥ እነዚህም ዝሙትና ርኩሰት ፍትወትም ክፉ ምኞትም ጣኦትንም ማምለክ የሆነ መጎምጀት ነው።
፮ በእነዚህም ጠንቅ የእግዚአብሔር ቍጣ በማይታዘዙ ልጆች ላይ ይመጣል።
፯ እናንተም ደግሞ ትኖሩባቸው በነበራችሁ ጊዜ፥ በፊት በእነዚህ ተመላለሳችሁ።
፰ አሁን ግን እናንተ ደግሞ ቍጣንና ንዴትን ክፋትንም፥ ከአፋችሁም ስድብን የሚያሳፍርንም ንግግር እነዚህን ሁሉ አስወግዱ።
፱ እርስ በርሳችሁ ውሸት አትነጋገሩ፥ አሮጌውን ሰው ከሥራው ጋር ገፋችሁታልና፥
፲ የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመሰል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል።
፲፩ በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።
፲፪ እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ምርጦች ቅዱሳን ሆናችሁ የተወደዳችሁም ሆናችሁ፥ ምሕረትን፥ ርኅራኄን፥ ቸርነትን፥ ትህትናን፥ የዋህነትን፥ ትዕግሥትን ልበሱ።
፲፫ እርስ በርሳችሁ ትዕግሥትን አድርጉ፥ ማንም በባልንጀራው ላይ የሚነቅፈው ነገር ካለው፥ ይቅር ተባባሉ። ክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉ።
፲፬ በእነዚህም ሁሉ ላይ የፍጹሜ ማሰሪያ የሆነውን ፍቅርን ልበሱት።
፲፭ በአንድ አካልም የተጠራችሁለት ደግሞ የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይግዛ። የምታመሰግኑም ሁኑ።
፲፮ የእግዚአብሔር ቃል በሙላት ይኑርባችሁ። በጥበብ ሁሉ እርስ በርሳችሁ አስተምሩና ገሥጹ። በመዝሙርና በዝማሬ በመንፈሳዊም ቅኔ በጸጋው በልባችሁ ለእግዚአብሔር ዘምሩ።
፲፯ እግዚአብሔር አብን በእርሱ እያመሰገናችሁ፥ በቃል ቢሆን ወይም በሥራ የምታደርጉትን ሁሉ በጌታ በኢያሱስ ስም አድርጉት።
፲፰ ሚስቶች ሆይ፥ በጌታ እንደሚገባ ለባሎቻችሁ ተገዙ።
፲፱ ባሎች ሆይ፥ ሚስቶቻችሁን ውደዱ መራራም አትሁኑባቸው።
፳ ልጆች ሆይ፥ ይህ ለጌታ ደስ የሚያሰኝ ነውና በሁሉ ለወላጆቻችሁ ታዘዙ።
፳፩ አባቶች ሆይ፥ ልባቸው እንዳይዝል ልጆቻችሁን አታበሳጩአቸው።
፳፪ ባሪያዎች ሆይ፥ በቅን ልብ ጌታን እየፈራችሁ እንጂ፥ ለሰው ደስ እንደምታሰኙ ለታይታ የምትገዙ ሳትሆኑ፥ በሥጋ ጌቶቻችሁ ለሆኑ በሁሉ ታዘዙ።
፳፫ ለሰው ሳይሆን ለጌታ እንደምታደርጉ፥ የምታደርጉትን ሁሉ በትጋት አድርጉት፥
፳፬ ከጌታ የርስትን ብድራት እንድትቀበሉ ታውቃላችሁና። የምታገለግሉት ጌታ ክርስቶስ ነውና።
፳፭ የሚበድልም የበደለውን በብድራት ይቀበላል፥ ለሰው ፊትም አድልዎ የለም።

፬

፩ ጌቶች ሆይ፥ እናንተ ደግሞ በሰማይ ጌታ እንዳላችሁ ታውቃላችሁና ለባሪያዎቻችሁ በጽድቅና በቅንነት አድርጉላቸው።
፪ ከማመሰገን ጋር በጸሎት እየነቃችሁ ለእርሱ ትጉ።
፫ በዚያን ጊዜም ሰለ እርሱ ደግሞ የታሰርሁበትን የክርስቶስን ምሥጢር እንድንነግር እግዚአብሔር የቃሉን ደጅ ይከፍትልን ዘንድ ሰለ እኛ ደግሞ ጸልዩ።
፬ ልናገር እንደሚገባኝ ያህል እገልጠው ዘንድ ጸልዩልኝ።
፭ ዘመኑን እየዋጃችሁ፥ በውጭ ባሉቱ ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ።
፮ ለእያንዳንዱ እንዴት እንድትመልሱ እንደሚገባችሁ ታውቁ ዘንድ ንግግራችሁ ሁልጊዜ፥ በጨው እንደ ተቀመመ፥ በጸጋ ይሁን።
፯ የተወደደ ወንድምና የታመነ አገልጋይ በጌታም አብሮኝ ባሪያ የሆነ ቲኪቆስ ኑሮዬን ሁሉ ያስታውቃችኋል።
፰-፲፩ ከእናንተ የሆነ የክርስቶስ ባሪያ ኤጳፍራ ሰላምታ ያቀርብላችኋል። በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁሉ ተረድታችሁና ፍጹማን ሆናችሁ እንድትቆሙ፥ ሁልጊዜ ሰለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል።
፲፫ ሰለ እናንተ በሎዶቅያም በኢያራ ከተማም ሰላሉቱ እጅግ እንዲቀና እመሰክርለታለሁና።
፲፬ የተወደደው ባለ መድኃኒቱ ሉቃስ ዴማስም ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፲፭ በሎዶቅያ ላሉቱ ወንድሞችና ለንምፋን በቤቱም ላለች ቤተ ክርስቲያን ሰላምታ አቅርቡልን።
፲፮ ይህችም መልእክት በእናንተ ዘንድ ከተነበበች በኋላ፥ በሎዶቅያ ሰዎች ማኅበር ደግሞ እንድትነበብ አድርጉ። ከሎዶቅያም የምትገኘውን መልእክት እናንተ ደግሞ አንብቡ።
፲፯ ለአክሪጳም። በጌታ የተቀበልኸውን አገልግሎት እንድትፈጽሙው ተጠንቀቅ በሉልኝ።
፲፰ በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው። እሰራቴን አስቡ። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን።

1ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

፩ ጳውሎስና ሲልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር አብ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ ክርስቲያን፤ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።

፪-፬ በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናልና።

፭ ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ በእናንተ ዘንድ ሰለ እናንተ እንዴት እንደ ነበርን ታውቃላችሁ።

፮ ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤

፯ ሰለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው።

፰-፲ ከእናንተ ወጥቶ የጌታ ቃል በመቄዶንያና በአካይያ ብቻ አልተሰማምና፥ ነገር ግን ምንም እንድንናገር እስከማያስፈልግ ድረስ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚሆን እምነታችሁ በሁሉ ሰፍራ ተወርቶአል።

፪

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ራሳችሁ ወደ እናንተ መግባታችን ከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁና።

፪ ነገር ግን እንደምታውቁት በፊልጵስዩስ አስቀድመን መከራ ተቀብለን ተንገላትተንም፥ በብዙ ገድል የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ እንናገር ዘንድ በአምላካችን ደፈርን።

፫ ልመናችን ከስሕተት ወይም ከርኩሰት ወይም ከተንኰል አልነበረምና፤

፬ ነገር ግን ወንጌልን እደራ ይሰጠን ዘንድ እግዚአብሔር የታመንን ሆነን እንዳገኘን መጠን፥ እንዲሁ እንናገራለን፥ ልባችንን የሚመረምር እግዚአብሔርን እንጂ ሰውን ደስ እንደምናሰኝ አይደለም።

፭ እንደምታውቁ፥ እያቈላመጥን ከቶ አልተናገርንም፥ እግዚአብሔርም እንደሚመሰክር እያመካኘን በመጐምጀት አልሠራንም፤

፮ የክርስቶስም ሐዋርያት እንደ መሆናችን ልንከብድባችሁ ሰንችል፥ ከእናንተ ቢሆን ወይም ከሌሎች ክብርን ከሰው አልፈለግንም።

፯ ነገር ግን ሞግዚት የራሷን ልጆች እንደምትከባከብ፥ በመካከላችሁ የዋሆች ሆንን፤

፰ እንዲሁም እያፈቀርናችሁ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለማካፈል ብቻ ሳይሆን የገዛ ነፍሳችንን ደግሞ እናካፍላችሁ ዘንድ በጎ ፈቃዳችን ነበረ፥ ለእኛ የተወደዳችሁ ሆናችሁ ነበርና።

፱ ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ሰንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።

፲ በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤

፲፩-፲፫ ሰለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ሰላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን።

፲፬ እናንተ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመሰሉ ሆናችኋልና፤ እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፥ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ ሰዎች ተቀብላችኋልና።

፲፭ እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፥ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፥ ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፥

፲፮ ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቍጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል።

፲፯ እኛ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ በልብ ያይደለ ፊት ለፊት ለጥቂት ጊዜ አጥተናችሁ፥ በብዙ ናፍቆት ፊታችሁን ለማየት እጅግ ሞከርን፤

፲፰ ወደ እናንተ ልንመጣ ወደን ነበርና፥ እኔ ጳውሎስም አንድና ሁለት ጊዜ፥ ሰይጣን ግን አዘገየን።

፲፱ ተስፋችን ወይስ ደስታችን ወይስ የትምክህታችን አክሊል ማን ነው? በጌታችን በኢየሱስ ፊት በመምጣቱ እናንተ አይደላችሁምን?

፳ እናንተ ክብራችን ደስታችንም ናችሁና።

፫

፩ ስለዚህ ወደ ፊት እንታገሥ ዘንድ ባልተቻለን ጊዜ፥ በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ።

፪ ሰለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤

፫ በዚህ መከራ ማንም እንዳይናውጥ፥ ለዚህ እንደ ተመረጥን ራሳችሁ ታውቃላችሁና።

፬ በእውነት ከእናንተ ጋር ሳለን፥ መከራ እንቀበል ዘንድ እንዳለን አሰቀድመን እንነግራችሁ ነበር፤ እንዲሁም ደግሞ ሆነ፥ ይህንም ታውቃላችሁ።

፭ ሰለዚህ እኔ ደግሞ ወደ ፊት እታገሥ ዘንድ ባልተቻለኝ ጊዜ። ፈታኝ ምናልባት ፈትኖአቸዋል ድካማችንም ከንቱ ሆኖአል ብዬ እምነታችሁን ለማወቅ ላክሁ።

፮ አሁን ግን ጢሞቴዎስ ከእናንተ ዘንድ ወደ እኛ መጥቶ ሰለ እምነታችሁና ሰለ ፍቅራችሁ የምሰራች ብሎ በነገረን ጊዜ፥ እኛም እናያችሁ ዘንድ እንደምንናፍቅ ታዩን ዘንድ እየናፈቃችሁ ሁልጊዜ በመልካም እንደምታሰቡን በነገረን ጊዜ፥

፯ ሰለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በእምነታችሁ በኩል በችግራችንና በመከራችን ሁሉ ሰለ እናንተ ተጽናናን፤

፰ እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና።

፱-፲፫ አምላካችንና አባታችን ራሱ ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ እናንተ መንገዳችንን ያቅና፤

ምዕራፍ ፬

፩ እንግዲህ በቀረውስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ልትመላለሱ እግዚአብሔርንም ደስ ልታሰኙ እንዴት እንደሚገባችሁ ከእኛ ዘንድ እንደ ተቀበላችሁ፥ እናንተ ደግሞ እንደምትመላለሱ፥ ከፊት ይልቅ ትበዙ ዘንድ በጌታ በኢየሱስ እንለምናችኋለን እንመክራችሁማለን።
፪ በጌታ በኢየሱስ የትኛውን ትእዛዝ እንደ ሰጠናችሁ ታውቃላችሁና።
፫ ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና፤
፬-፮ አሰቀድመን ደግሞ እንዳልናችሁና እንደ መሰከርንላችሁ፥ ጌታ ስለዚህ ነገር ሁሉ የሚበቀል ነውና ማንም በዚህ ነገር አይተላለፍ ወንድሙንም አያታልል።
፯ ለርኩሰት ሳይሆን እግዚአብሔር በቅድሰና ጠርቶናልና።
፰ እንግዲህ የሚጥል ሰውን የጣለ አይደለም፥ መንፈስ ቅዱሱን በእናንተ እንዲኖር የሰጠውን እግዚአብሔርን ነው እንጂ።
፱ እናንተ ራሳችሁ እርስ በርሳችሁ ልትዋደዱ በእግዚአብሔር ተምራችኋልና ስለ ወንድማማች መዋደድ ማንም ይጽፍላችሁ ዘንድ አያስፈልጋችሁም፤
፲-፲፫ ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።
፲፬ ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና።
፲፭ በጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና፤ እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉቱን አንቀድምም፤
፲፮ ጌታ ራሱ በትእዛዝ በመላእክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፤
፲፯ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው፥ ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን፤ እንዲሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን።
፲፰ ስለዚህ እርስ በርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።

ምዕራፍ ፭

፩ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ዘመናትና ስለ ወራት ምንም እንዲጻፍላችሁ አያስፈልጋችሁም፤
፪ የጌታ ቀን፥ ሌባ በሌሊት እንደሚመጣ፥ እንዲሁ ይመጣ ዘንድ ራሳችሁ አጥብቃችሁ አውቃችኋልና።
፫ ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም።
፬ እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ቀኑ እንደ ሌባ ይደርሰባችሁ ዘንድ በጨለማ አይደላችሁም፥
፭ ሁላችሁ የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም፤
፮ እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች እናንቀላፋ።
፯ የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፥ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና፤
፰ እኛ ግን ከቀን ሰለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤
፱ እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ።
፲ የምንነቃም ብንሆን፥ የምናንቀላፋም ብንሆን፥ ከእርሱ ጋር አብረን በሕይወት እንኖር ዘንድ ስለ እኛ ሞተ።
፲፩ ስለዚህ እናንተ ደግሞ እንደምታደርጉ፥ እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ አንዱም አንዱም ሌላውን ያንጸው።
፲፪-፲፫ ወንድሞች ሆይ፥ እንመክራችኋለን፤ ያለ ሥርዓት የሚሄዱትን ገሥጹአቸው፤ ድፍረት የሌላቸውን አጽኑአቸው፤ ለደካሞች ትጉላቸው፤ ሰውን ሁሉ ታገሡ።
፲፬ ማንም ለሌላው በክፉ ፈንታ ክፉ እንዳይመልስ ተጠንቀቁ፥ ነገር ግን ሁልጊዜ እርስ በርሳችሁ ለሁሉም መልካሙን ለማድረግ ትጉ።
፲፮ ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፤
፲፯-፲፱ መንፈስን አታጥፉ፤
፳-፳፪ ከማናቸውም ዓይነት ክፉ ነገር ራቁ።
፳፫ የሰላምም አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም ነፍሳችሁም ሥጋችሁም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።
፳፬ የሚጠራችሁ የታመነ ነው፥ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል።
፳፭ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ እኛ ጸልዩ።
፳፮ ከወንድሞች ሁሉ ጋር በተቀደሰ አሳሳም ሰላምታ ተሰጣጡ።
፳፯ ይህ መልእክት ለቅዱሳን ወንድሞች ሁሉ እንዲነበብ በጌታ አምላችኋለሁ።
፳፰ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፤ አሜን።

2ኛ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች

፩ ጳውሎስና ሲልዋኖስ ጢሞቴዎስም፥ በእግዚአብሔር በአባታችን በጌታ በኢየሱስ
ክርስቶስም ወደምትሆን ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች ቤተ
ክርስቲያን፤
፪ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታ ከኢየሱስ
ክርስቶስም ጸጋ ሰላምም ለእናንተ ይሁን።
፫ ወንድሞች ሆይ፥ እምነታችሁ እጅግ ሰለሚያድግ
የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ
ሰለሚበዛ፥ ሁልጊዜ ሰለ እናንተ እግዚአብሔርን
እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፤
፬ ሰለዚህ በምትታገሱበት በሰደታችሁና
በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ
በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ሰለ እናንተ
ራሳችን እንመካለን።
፭ ሰለ እርሱ ደግሞ መከራ ለምትቀበሉለት
ለእግዚአብሔር መንግሥት የምትበቁ ሆናችሁ
ትቈጠሩ ዘንድ፥ ይህ የእግዚአብሔር ቅን ፍርድ
ምልክት ነው።
፮-፲፪ እግዚአብሔርን የማያውቁትን፥ ለጌታችንም
ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የማይታዘዙትን ይበቀላል፤

፪

፩-፫ ማንም በማናቸውም መንገድ አያሰታችሁ፤
ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም
የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና።
፬ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ
በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ፥
አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩት ሁሉ
በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ
ነው።
፭ ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ
አይላችሁምን?
፮ በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን
አሁን ታውቃላችሁ።
፯ የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ
ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ።
፰ በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ
የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው
ዓመፀኛ ይገለጣል፤
፱-፲፫ እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥
ሁልጊዜ ሰለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ
አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም
በማመን ለመዳን እንደ በኩራት መርጦአችኋልና፤
፲፬ ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር
ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ።
፲፭-፲፯ እንግዲያስ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጸንታችሁ
ቁሙ፥ በቃላችንም ቢሆን ወይም በመልእክታችን
የተማራችሁትን ወግ ያዙ።

፫

፩-፭ ነገር ግን የሚያጸናችሁ ከክፉውም
የሚጠብቃችሁ ጌታ የታመነ ነው።
፮ የምናዛችሁንም አሁን እንድታደርጉ ወደ ፊትም
ደግሞ እንድታደርጉ ሰለ እናንተ በጌታ ታምነናል።
፭ ጌታም ወደ እግዚአብሔር ፍቅር ወደ ክርስቶስም
ትዕግሥት ልባችንን ያቅናው።
፮ ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ
ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም ሁሉ ትለዩ
ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም እናዛችኋለን።
፯ እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ
ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ ሥርዓት
አልሄድንምና፤
፰ ከእናንተ ዘንድ በእንዱ ሰንኳ እንዳንከብድበት፥
ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር
እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም።
፱ ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ
እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ሰለ ሆንን
አይደለም።
፲ ደግሞ ከእናንተ ጋር ሳለን። ሊሠራ የማይወድ
አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና።
፲፩ ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ
ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ሰለሚሄዱ ሰለ አንዳንዶች
ሰምተናልና።
፲፪ እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ
እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን።
፲፫ እናንተ ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ መልካም ሥራን
ለመሥራት አትታክቱ።
፲፬ በዚህ መልእክት ለተላከ ቃላችን የማይታዘዝ
ማንም ቢኖር፥ ይህን ተመልከቱት፥ ያፍርም ዘንድ
ከእርሱ ጋር አትተባበሩ።
፲፭ ነገር ግን እንደ ወንድም ገሥጹት እንጂ እንደ
ጠላት አትቊጠሩት።
፲፮ የሰላምም ጌታ ራሱ በሁሉ መንገድ ዘወትር
ሰላምን ይስጣችሁ። ጌታ ከሁላችሁ ጋር ይሁን።
፲፯ በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ
ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማሰረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ
እጽፋለሁ።
፲፰ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር
ይሁን።

1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ

፩ መድኃኒታችን እግዚአብሔር ተስፋችንም ኢየሱስ
ክርስቶስ እንዳዘዘው ትእዛዝ የኢየሱስ ክርስቶስ
ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፥
፪ በእምነት እውነተኛ ልጄ ለሆነ ለጢሞቴዎስ፤
ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከክርስቶስ ኢየሱስም
ከጌታችን ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን።
፫-፭ የትእዛዝ ፍጻሜ ግን ከንጹሕ ልብና ከበጎ ሕሊና
ግብዝነትም ከሌለበት እምነት የሚወጣ ፍቅር ነው፤
፮-፯ ነገር ግን ሰው እንደሚገባ ቢሰራበት ሕግ
መልካም እንደ ሆነ እናውቃለን፤
፱-፲፫ ለአገልግሎቱ ሾሞኝ ታማኝ አድርጎ ሰለ
ቈጠረኝ፥ ኃይል የሰጠኝን ክርስቶስ ኢየሱስን ጌታችንን
አመሰግናለሁ፤
፲፫ አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም
ብሆን፥ ይህን እደረገልኝ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን
ሰላደረግሁት ምህረትን አገኘሁ፥
፲፬ የጌታችንም ጸጋ በክርስቶስ ኢየሱስ ካሉ
ከእምነትና ከፍቅር ጋር አብልጦ በዛ።
፲፭ ኃጢአተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ
ዓለም መጣ የሚለው ቃል የታመነና ሁሉ እንዲቀበሉት
የተገባ ነው፤ ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ፤
፲፮ ሰለዚህ ግን፥ የዘላለምን ሕይወት ለማግኘት
በእርሱ ያምኑ ዘንድ ላላቸው ሰዎች ምሳሌ እንድሆን፥
ኢየሱስ ክርስቶስ ዋና በምሆን በእኔ ላይ ትዕግስቱን
ሁሉ ያሳይ ዘንድ፥ ምህረትን አገኘሁ።
፲፯ ብቻውን እምላክ ለሚሆን ለማይጠፋው
ለማይታየውም ለዘመናት ንጉሥ ምስጋናና ክብር እስከ
ዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።
፲፰ ጢሞቴዎስ ልጄ ሆይ፥ አስቀድሞ ሰለ አንተ እንደ
ተነገረው ትንቢት፥ በእርሱ መልካም ጦርነት ትዋጋ
ዘንድ ይህችን ትእዛዝ አደራ እሰጥሃለሁ፤
፲፱ እምነትና በጎ ሕሊና ይኑርህ፥ አንዳንዶች ሕሊናን
ጥለው፥ መርከብ አለ መሪ እንደሚጠፋ፥ በእምነት ነገር
ጠፍተዋልና፤
፳ ከእነዚያም፥ እንዳይሳደቡ ይማሩ ዘንድ ለሰይጣን
አሳልፌ የሰጠኋቸው፥ ሄሜኔዎስና እስክንድሮስ ናቸው።

፪

፩-፭ አንድ እግዚአብሔር አለና፥ በእግዚአብሔርና
በሰውም መካከል ያለው መካከለኛው ደግሞ አንድ
አለ፥ እርሱም ሰው የሆነ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤
፮ ራሱንም ለሁሉ ቤዛ ሰጠ፥ ይህም በገዛ ዘመኑ
ምስክርነቱ ነበረ፤
፯ እኔም ለዚህ ነገር አዋጅ ነጋሪና ሐዋርያ በእምነትና
በእውነትም የአሕዛብ አሰተማሪ ለመሆን ተሾምሁ፤
እውነት እናገራለሁ፤ አልዋሽም።
፰ እንግዲህ ወንዶች በሰፍራ ሁሉ አለ ቍጣና አለ
ክፉ አሳብ የተቀደሱትን እጆች እያነሱ እንዲጸልዩ
እፈቅዳለሁ።
፱-፲፭ ሴት በነገር ሁሉ እየተገዛች በዝግታ ትማር፤
፲፪ ሴት ግን በዝግታ ትኑር እንጂ ልታስተምር ወይም
በወንድ ላይ ልትሰለጥን አልፈቅድም።
፲፫ አዳም ቀድሞ ተፈጥሮአልና፥ በኋላም ሔዋን
ተፈጠረች።
፲፬ የተታለለም አዳም አይደለም፥ ሴቲቱ ግን ተታልላ
በመተላለፍ ወደቀች፤
፲፭ ነገር ግን በእምነትና በፍቅር በቅድስናም
ራሳቸውን እየገዙ ቢኖሩ በመውለድ ትድናለች።

፫

፩ ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ
ይመኛል የሚለው ቃል የታመነ ነው።
፪ እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል፤
የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን
የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሰራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥
ለማስተማር የሚበቃ፥
፫ የማይስክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ፥
የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድ፥
፬ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት
በመልካም የሚያስተዳድር፤
፭ ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ፥
የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል?
፮ በትዕቢት ተነፍቶ በዲያቢሎስ ፍርድ
እንዳይወድቅ፥ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።
፯ በዲያቢሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ፥
በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው
ይገባዋል።
፰ እንዲሁም ዲያቆናት ጭምቶች፥ በሁለት ቃል
የማይናገሩ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይጎመጁ፥
፱ ነውረኛ ረብ የማይወዱ፥ በንጹሕ ሕሊና
የሃይማኖትን ምሥጢር የሚይዙ ሊሆኑ ይገባቸዋል።
፲ እነዚህም ደግሞ አስቀድሞ ይፈተኑ፥ ከዚያም
በኋላ ያለ ነቀፋ ቢሆኑ በዲቁና ሥራ ያገልግሉ።
፲፩ እንዲሁም ሴቶች ጭምቶች፥ የማያሙ፥ ልከኞች፥
በነገር ሁሉ የታመኑ ሊሆኑ ይገባቸዋል።
፲፪ ዲያቆናት ልጆቻቸውንና የራሳቸውን ቤቶች
በመልካም እየገዙ እያንዳንዳቸው የአንዲት ሴት ባሎች
ይሁኑ።
፲፫ በዲቁና ሥራ በመልካም ያገለገሉ ለራሳቸው
ትልቅ ማዕርግና በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው እምነት
ብዙ ድፍረት ያገኛሉ።
፲፬ ፈጥኜ ወደ አንተ እንድመጣ ተስፋ አድርጌ ይህን
እጽፍልሃለሁ።
፲፭ ብዘገይ ግን፥ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር
እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም
የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር
ቤተ ክርስቲያን ነው።
፲፮ እግዚአብሔርንም የመምሰል ምሥጢር ያለ
ጥርጥር ታላቅ ነው፤ በሥጋ የተገለጠ፥ በመንፈስ
የጸደቀ፥ ለመላእክት የታየ፥ በአሕዛብ የተሰበከ፥
በዓለም የታመነ፥ በክብር ያረገ።

፬

፩-፭ እነዚህ ውሸተኞች መጋባትን ይከለክላሉ፥
እምነውም እውነትን የሚያውቁ ከምስጋና ጋር ይቀበሉ
ዘንድ እግዚአብሔር ከፈጠረው መብል እንዲርቁ
ያዝዛሉ።
፮ እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፥
ከምስጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም፤

፭ በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት የተቀደሰ ነውና።
፮ ስለዚህ ወንድሞችን ብታሳስብ፥ በእምነትና በተከተልኸው በመልካም ትምህርት ቃል የምትመገብ የኢየሱስ ክርስቶስ መልካም አገልጋይ ትሆናለህ።
፯ ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ሴቶች ጨዋታ ከሚመስለው ተረት ራቅ። እግዚአብሔርን ለመምሰል ግን ራስህን አስለምድ።
፰ ስውነትን ለሥጋዊ ነገር ማሰለመድ ለጥቂት ይጠቅማልና፤ እግዚአብሔርን መምሰል ግን የአሁንና የሚመጣው ሕይወት ተስፋ ሰላለው፥ ለነገር ሁሉ ይጠቅማል።
፱ ይህ ቃል የታመነ ሁሉም እንዲቀበሉት የተገባ ነው፤
፲ ይህን ለማግኘት እንደክማለንና፥ ሰለዚህም እንሰደባለን፤ ይህም ሰውን ሁሉ ይልቁንም የሚያምኑትን በሚያድን በሕያው አምላክ ተስፋ ሰለምናደርግ ነው።
፲፩-፲፫ እስክመጣ ድረስ ለማንበብና ለመምከር ለማስተማርም ተጠንቀቅ።
፲፬ በትንቢት ከሽማግሌዎች እጅ መጫን ጋር የተሰጠህን፥ በእነተ ያለውን የጸጋ ሰጦታ ቸል አትበል።
፲፭ ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ፥ ይህንም አዘውትር።
፲፮ ለራስህና ለትምህርትህ ተጠንቀቅ፥ በእነዚህም ጽና፤ ይህን ብታደርግ፥ ራስህንም የሚሰሙህንም ታድናለህና።

ምዕ ፭

፩-፪ በእውነት ባልቴቶች የሆኑትን ባልቴቶች አክብር።
፫ ማንም ባልቴት ግን ልጆች ወይም የልጅ ልጆች ቢኖሩአት፥ እነርሱ አሰቀድመው ለገዛ ቤተ ሰዎቻቸው እግዚአብሔርን መምሰል ያሳዩ ዘንድ፥ ለወላጆቻቸውም ብድራትን ይመልሱላቸው ዘንድ ይማሩ፤ ይህ በእግዚአብሔር ፊት መልካምና የተወደደ ነውና።
፭ ብቻዋንም ኖራ በእውነት ባልቴት የምትሆን በእግዚአብሔር ተስፋ ታደርጋለች፥ ሌትና ቀንም በልመና በጸሎትም ጸንታ ትኖራለች፤
፮ ቅምጥሊቱ ግን በሕይወትዋ ሳለች የሞተች ናት።
፯ ያለ ነቀፋ እንዲሆኑ ይህን ደግሞ እዘዝ።
፰ ነገር ግን ለእርሱ ሰለ ሆኑት ይልቁንም ሰለ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ማንም ቢሆን፥ ሃይማኖትን የካደ ከማያምንም ሰው ይልቅ የሚከፋ ነው።
፱ ባልቴት በመዝገብ ብትጻፍ ዕድሜዋ ከሰድሳ ዓመት እንዳያንስ፥ የአንድም ባል ሚስት የነበረች እንድትሆን ያስፈልጋል፤
፲ ልጆችን በማሳደግ እንግዶችንም በመቀበል፥ የቅዱሳንንም እግሮች በማጠብ፥ የተጨነቁትንም በመርዳት በጎንም ሥራ ሁሉ በመከተል፥ ይህን መልካም ሥራ በማድረግ የተመሰከረላት ልትሆን ይገባል።
፲፩ ባል የሞተባቸውን ቆነጃጅት ግን አትቀበል፤ በክርስቶስ ላይ ተነሥተው ሲቀማጠሉ ሊያገቡ ይወዳሉና፤
፲፪ የፊተኛውንም እምነታቸውን ሰለ ናቁ ይፈረድባቸዋል፤
፲፫ ከዚህም ጋር ቤት ለቤት እየዞሩ ሥራን መፍታት ደግሞ ይማራሉ፥ የማይገባውንም እየተናገሩ ለፍላፊዎችና በነገር ገቢዎች ይሆናሉ እንጂ፥ ሥራ ፈቶች ብቻ አይደሉም።
፲፬ እንግዲህ ቆነጃጅት ሊያገቡ፥ ልጆችንም ሊወልዱ፥ ቤቶቻቸውንም ሊያስተዳድሩ፥ ተቃዋሚውም የሚሳደብበትን አንድን ምክንያት ሰንኳ እንዳይሰጡ እፈቅዳለሁ፤
፲፭ ከአሁን በፊት አንዳንዶች ሰይጣንን እንዲከተሉ ፈቀቅ ብለዋልና።
፲፮ ባልቴቶች ያሉት የሚያምን ቢሆን ወይም የምታምን ብትሆን፥ ይርዱአቸው፥ ቤተ ክርስቲያንም እውነተኞችን ባልቴቶች እንድትረዳ አይክበዱባት።
፲፯ በመልካም የሚያስተዳድሩ ሽማግሌዎች፥ ይልቁንም በመስበክና በማስተማር የሚደክሙት፥ እጥፍ ክብር ይገባቸዋል።
፲፰ መጽሐፍ። የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር፥ ደግሞ። ለሠራተኛ ደመወዙ ይገባዋል ይላልና።
፲፱ ከሁለት ወይም ከሦስት ምስክር በቀር በሽማግሌ ላይ ክስ አትቀበል።
፳ ሌሎቹ ደግሞ እንዲፈሩ፥ ኃጢአት የሚሰሩትን በሁሉ ፊት ገሥጻቸው።
፳፩ አንድን እንኳ በአድልዎ ሳታደርግ፥ እነዚህን ያለ መዘንበል እንድትጠብቅ በእግዚአብሔርና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በተመረጡትም መላእክት ፊት እመክርሃለሁ።
፳፪ በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን፥ በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር፤ ራስህን በንጽህና ጠብቅ።
፳፫ ሰለ ሆድህና ሰለ በሽታህ ብዛት ጥቂት የወይን ጠጅ ጠጣ እንጂ፥ ወደ ፊት ውኃ ብቻ አትጠጣ።
፳፬ የአንዳንዶች ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው ፍርድንም ያመለክታል፥ ሌሎችን ግን ይከተላቸዋል፤
፳፭ እንዲሁ መልካም ሥራ ደግሞ የተገለጠ ነው፥ ያልተገለጠም ከሆነ ሊሰወር አይችልም።

ምዕ ፮

፩ የእግዚአብሔር ሰምና ትምህርቱ እንዳይሰደብ፥ ከቀንበር በታች ያሉቱ ባሪያዎች ሁሉ ለገዙአቸው ጌቶች ክብር ሁሉ እንደ ተገባቸው ይቊጠሩአቸው።
፪ የሚያምኑም ጌቶች ያሉአቸው፥ ወንድሞች ሰለ ሆኑ አይናቁአቸው፥ ነገር ግን በመልካም ሥራቸው የሚጠቅሙ የሚያምኑና የተወደዱ ሰለ ሆኑ፥ ከፊት ይልቅ ያገልግሉ።
፫ እነዚህን አስተምርና ምከር። ማንም ልዩ ትምህርት የሚያስተምር ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ በሆነው ጤናማ ቃልና እግዚአብሔርን ለመምሰል በሚስማማ ትምህርት የማይጠጋ ቢሆን፥
፬-፭ ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤
፮ ወደ ዓለም ምንም እንኳ እላመጣንምና፥
፯ እንዳችንም ልንወሰድ እይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፥ እርሱ ይበቃናል።
፱ ደሩ ግን ባለ ጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ

በሚጎዳም በብዙ ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ።
፲ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፥ አንዳንዶች ይህን ሲመኙ፥ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ሥቃይ ራሳቸውን ወጉ።
፲፩ አንተ ግን፥ የእግዚአብሔር ሰው ሆይ፥ ከዚህ ሽሽ፤ ጽድቅንና እግዚአብሔርን መምሰል እምነትንም ፍቅርንም መጽናትንም የዋህነትንም ተከታተል።
፲፪ መልካሙን የእምነት ገድል ተጋደል፥ የተጠራህለትንም በብዙም ምስክሮች ፊት በመልካም መታመን የታመንህለትን የዘላለምን ሕይወት ያዝ።
፲፫ ሁሉን በሕይወት በሚጠብቅ በእግዚአብሔር ፊት፥ በጴንጤናዊውም በጲላጦስ ዘንድ መልካሙን መታመን በመሰከረ በክርስቶስ ኢየሱስ ፊት አዝሃለሁ፤
፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እስኪገለጥ ድረስ ያለ እድፍና ያለ ነቀፋ ሆነህ ትእዛዙን ጠብቅ፤
፲፭ ያንም መገለጡን በራሱ ጊዜ ብፁዕና ብቻውን የሆነ ገዥ፥ የነገሥታት ንጉሥና የጌቶች ጌታ፥ ያሳያል።
፲፮ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ እንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን።
፲፯ በአሁኑ ዘመን ባለ ጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፥ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ ባለ ጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።
፲፰-፲፱ ጢሞቴዎስ ሆይ፥ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ፥ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ፤
፳፩ ይህ እውቀት አለን ብለው፥ አንዳንዶች ሰለ እምነት ሰተዋልና። ጸጋ ከአንተ ጋር ይሁን።

2ኛ ወደ ጢሞቴዎስ

፩ በክርስቶስ ኢየሱስ እንደሚሆን የሕይወት ተስፋ፥ በእግዚአብሔር ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያ የሆነ ጳውሎስ፥
፪ ለተወደደው ልጄ ለጢሞቴዎስ፤ ከእግዚአብሔር አብ ከጌታችንም ከክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን።
፫ ሌትና ቀን በልመናዬ ሳላቋርጥ ስለማሰብህ እንደ አባቶቼ አድርጌ በንጹሕ ሕሊና የማመልከውን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፤
፬ እንባህን እያሰብሁ በደስታ እሞላ ዘንድ ላይህ እናፍቃለሁ።
፭ በእንተ ያለውን ግብዝነት የሌለበትን እምነትህን አሰባለሁ፤ ይህም እምነት ቀድሞ በአያትህ በሎይድ በእናትህም በኤውንቄ ነበረባቸው፥ በአንተም ደግሞ እንዳለ ተረድቼአለሁ።
፮ ስለዚህ ምክንያት፥ እሳት እንደሚያቀጣጥል ሰው፥ እጆቼን በመጫኔ በአንተ ያለውን የእግዚአብሔርን ሰጦታ እንድታነሣሣ አሳሰብሃለሁ።
፯ እግዚአብሔር የኃይልና የፍቅር ራስንም የመግዛት መንፈስ እንጂ የፍርሃት መንፈስ አልሰጠንምና።
፰ እንግዲህ በጌታችን ምስክርነት ወይም በእስረኛው በእኔ አትፈር፥ ነገር ግን እንደ እግዚአብሔር ኃይል መጠን ስለ ወንጌል አብረኸኝ መከራን ተቀበል፤
፱ ያዳነን በቅዱሰም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር ነውና፥ ይህም እንደ ራሱ እሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም፤ ይህም ጸጋ ከዘላለም ዘመናት በፊት በክርስቶስ ኢየሱስ ተሰጠን፥
፲-፲፪ ስለዚህም ምክንያት ይህን መከራ ደግሞ ተቀብዬአለሁ፥ ነገር ግን አላፍርበትም፤ ያመንሁትን አውቃለሁና፥ የሰጠሁትንም አደራ እስከዚያ ቀን ድረስ ሊጠብቅ እንዲችል ተረድቼአለሁ።
፲፫ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለ እምነትና ፍቅር አድርገህ፥ ከእኔ የሰማኸውን ጤናማ ቃል ምሳሌ ያዝ፤
፲፬ መልካሙን አደራ በእኛ በሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ ጠብቅ።
፲፭ በእሲያ ያሉቱ ሁሉ ከእኔ ፈቀቅ እንዳሉ ታውቃለህ፥ ከእነርሱም ፊሎጎስና ሄርዋጌስ ናቸው።
፲፮ ጌታ ልሄኔሲፎሩ ቤተ ሰዎች ምሕረትን ይስጥ፥ ብዙ ጊዜ አሳርፎኛልና፤
፲፯ በሰንሰለቴም አላፈረበትም፥ ነገር ግን በሮሜ ባደረ ጊዜ ፈልጎ ፈልጎ አገኘኝ፤
፲፰ በዚያን ቀን ከጌታ ምሕረትን እንዲያገኝ ጌታ ይስጠው፤ በኤፌሶንም እንዴት እንዳገለገለኝ አንተ በደኅና ታውቃለህ።

፪

፩ እንግዲህ፥ ልጄ ሆይ፥ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው ጸጋ በርታ።
፪ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ።
፫ እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ በጎ ወታደር ሆነህ፥ አብረኸኝ መከራ ተቀበል።
፬ የሚዘምተው ሁሉ ለጦር ያስከተተውን ደስ ያሰኝ ዘንድ ትዳር በሚገኝበት ንግድ ራሱን አያጠላልፍም።
፭ ደግሞም በጨዋታ የሚታገል ማንም ቢሆን፥ እንደሚገባ አድርጎ ባይታገል፥ የድሉን አክሊል አያገኝም።
፮ የሚደክመው ገበሬ ፍሬውን ከሚበሉት መጀመሪያ እንዲሆን ይገባዋል።
፯ የምለውን ተመልከት፤ ጌታም በነገር ሁሉ ማስተዋልን ይስጥህ።
፰ በወንጌል እንደምሰብከው፥ ከሙታን የተነሣውን፥ ከዳዊት ዘርም የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን አስብ፤
፱ ይህንም በመሰበክ እንደ ክፉ አድራጊ እስክታሰር ድረስ መከራ እቀበላለሁ፥ የእግዚአብሔር ቃል ግን አይታሰርም።
፲ ስለዚህ እነርሱ ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ ያለውን መዳን ከዘላለም ክብር ጋር እንዲያገኙ ስለ ተመረጡት በነገር ሁሉ እጸናለሁ።
፲፩ ቃሉ የታመነ ነው እንዲህ የሚለው። ከእርሱ ጋር ከሞትን፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ በሕይወት እንኖራለን፤
፲፪ ብንጸና፥ ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሣለን፤ ብንክደው፥ እርሱ ደግሞ ይክደናል፤
፲፫ ባናምነው፥ እርሱ የታመነ ሆኖ ይኖራል፤ ራሱን ሊክድ አይችልምና።
፲፬ ይህን አሳስባቸው፥ በቃልም እንዳይጣሉ በእግዚአብሔር ፊት ምከራቸው፥ ይህ ምንም የማይረባ የሚሰሙትንም የሚያፈርስ ነውና።
፲፭ የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሠራተኛ ሆነህ፥ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።
፲፮ ነገር ግን ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍ ራቅ፤ ኃጢአተኝነታቸውን ከፊት ይልቅ ይጨምራሉና፥
፲፯ ቃላቸውም እንደ ጭንቁር ይባላል፤
፲፰ ከእነርሱም ሄሜኔዎስና ፊሊጦስ ናቸው፤
፲፱ እነዚህም። ትንሣኤ ከአሁን በፊት ሆኖአል እያሉ፥ ስለ እውነት ስተው፥ የአንዳንዶችን እምነት ይገለብጣሉ።
፳ ሆኖም። ጌታ ለእርሱ የሆኑትን ያውቃል፥ ደግሞም። የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፅ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል።
፳፩ በትልቅም ቤት የእንጨትና የሸክላ ዕቃ ደግሞ አለ እንጂ የወርቅና የብር ዕቃ ብቻ እይደለም፥ እኩሌቶቹም ለክብር፥ እኩሌቶቹም ለውርደት ይሆናሉ፤
፳፪ እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ቢያነጻ፥ ለክብር የሚሆን የተቀደሰም ለጌታውም የሚጠቅም ለበጎም ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ ዕቃ ይሆናል።
፳፫ ከክፉ የጎልማሳነት ምኞት ግን ሽሽ፥ በንጹሕም ልብ ጌታን ከሚጠሩ ጋር ጽድቅን እምነትን ፍቅርን ሰላምን አጥብቀህ ተከተል።
፳፫ ነገር ግን ጠብን እንዲያመጣ አውቀህ ከሰነፎችና ካልተማሩ ምርመራ ራቅ፤
፳፬-፳፮ የጌታም ባሪያ ለሰው ሁሉ ገር ለማስተማርም የሚበቃ ለትዕግሥትም የሚጸና ሊሆን እንጂ ሊጣላ አይገባውም።

፫

፩ ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን

እንዲመጣ ይህን እወቅ።
፪ ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥
፫ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥
፬ ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤
፭ የእምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ።
፮-፰ ኢያኔስና ኢያንበሪስም ሙሴን እንደ ተቃወሙት፥ እንዲሁ እነዚህ ደግሞ እእምሮአቸው የጠፋባቸው ሰለ እምነትም የተጣሉ ሰዎች ሆነው፥ እውነትን ይቃወማሉ።
፱ ዳሩ ግን የእነዚያ ሞኝነት ደግሞ ግልጥ እንደ ሆነ፥ ሞኝነታቸው ለሁሉ ይገለጣልና ከፊት ይልቅ አይቀናላቸውም።
፲ አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን አሳቤንም እምነቴንም ትዕግሥቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፤
፲፩ በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገሥሁትንም ስደት ታውቃለህ፤ ጌታም ከሁሉ አዳነኝ።
፲፪ በእውነትም በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔርን እየመሰሉ ሊኖሩ የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።
፲፫ ነገር ግን ክፉዎች ሰዎችና አታላዮች፥ እያሳቱና እየሳቱ፥ በክፋት እየባሱ ይሄዳሉ።
፲፬ አንተ ግን በተማርህበትና በተረዳህበት ነገር ጸንተህ ኑር፥ ከማን እንደ ተማርኸው ታውቃለህና፤
፲፭-፲፯ ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳን መጻሕፍትን አውቀሃል።

፬

፩ በእግዚአብሔር ፊት በሕያዋንና በሙታንም ሊፈርድ ባለው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት፥ በመገለጡና በመንግሥቱም እመክርሃለሁ፤
፪ ቃሉን ስበክ፥ በጊዜውም አለጊዜውም ጽና፥ ፈጽመህ እየታገሥህና እያስተማርህ፥ ዝለፍና ገሥጽ ምከር።
፫ ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ሰለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ።
፬ እውነትንም ከመስማት ጆሮቻቸውን ይመልሳሉ፥ ወደ ተረትም ፈቀቅ ይላሉ።
፭ አንተ ግን ነገርን ሁሉ በልክ አድርግ፥ መከራን ተቀበል፥ የወንጌል ሰባኪነትን ሥራ አድርግ፥ አገልግሎትህን ፈጽም።
፮ በመሥዋዕት እንደሚደረግ፥ የእኔ ሕይወት ይሠዋልና፥ የምሄድበትም ጊዜ ደርሶአል።
፯ መልካሙን ገድል ተጋድዬአለሁ፥ ሩጫውን ጨርሼአለሁ፥ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፤
፰ ወደ ፊት የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል፥ ይህንም ጻድቅ ፈራጅ የሆነው ጌታ ያን ቀን ለእኔ ያስረክባል፥ ደግሞም መገለጡን ለሚወዱት ሁሉ እንጂ ለእኔ ብቻ አይደለም።
፱ በቶሎ ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤
፲ ዴማስ የአሁኑን ዓለም ወዶ ትቶኛልና፥ ወደ ተሰሎንቄም ሄዶአል፤ ቄርቂስም ወደ ገላትያ ቲቶም ወደ ዳልማጥያ ሄደዋል፤
፲፩ ሉቃስ ብቻ ከእኔ ጋር አለ። ማርቆስ ለአገልግሎት ብዙ ይጠቅመኛልና ይዘኸው ከአንተ ጋር አምጣው።
፲፪ ጢኪቆስን ግን ወደ ኤፌሶን ላክሁት።
፲፫ ስትመጣ በጢሮአዳ ከአክርጳ ዘንድ የተውሁትን በርኖሱንና መጻሕፍቱን ይልቁንም በብራና የተጻፉትን አምጣልኝ።
፲፬ የናስ አንጥረኛው እስክንድሮስ እጅግ ከፋብኝ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይመልስለታል።
፲፭ አንተም ደግሞ ከእርሱ ተጠበቅ፥ የምንናገረውን እጅግ ተቃውሞአልና።
፲፮ በፊተኛው ሙግቴ አንድ ሰንኳ አልደረስልኝም፥ ሁሉም ተዉኝ እንጂ፤ ይህንም አይቊጠርባቸው፤
፲፯ ዳሩ ግን የሰብከቴ ሥራ በእኔ እንዲፈጸም አሕዛብም ሁሉ እንዲሰሙት፥ ጌታ በእኔ አጠገብ ቆሞ አበረታኝ፥ ከአንበሳ አፍም ዳንሁ።
፲፰ ጌታም ከክፉ ነገር ሁሉ ያድነኛል ለሰማያዊውም መንግሥት ይጠብቀኛል፤ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።
፲፱ ለጵርስቅላና ለአቂላ ለሄኔሲፎሩም ቤተ ሰዎች ሰላምታ አቅርብልኝ።
፳ ኤርስጦስ በቆሮንቶስ ቀረ፥ ጥሮፊሞስን ግን ታሞ በሚሊጢን ተውሁት።
፳፩ ከክረምት በፊት እንድትመጣ ትጋ። ኤውግሎስና ጴዴስ ሊኖስም ቅላውዲያም ወንድሞችም ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል።
፳፪ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመንፈስህ ጋር ይሁን። ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ቲቶ

፩-፫ በዘመኑም ጊዜ፥ መድኃኒታችን እግዚአብሔር እንዳዘዘ፥ ለእኔ አደራ በተሰጠኝ ሰብከት ቃሉን ገለጠ፤
፬ በሃይማኖት ኅብረት እውነተኛ ልጁ ለሚሆን ለቲቶ፤ ከእግዚአብሔር አብ ከመድኃኒታችንም ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም ይሁን።
፭ ስለዚህ ምክንያት የቀረውን እንድታደራጅ በየከተማውም፥ እኔ እንተን እንዳዘዝሁ፥ ሽማግሌዎችን እንድትሾም በቀርጤስ ተውሁህ፤
፮ የማይነቀፍና የእንዲት ሚስት ባል የሚሆን፥ የሚያምኑም ልጆች ያሉት፥ ሰለ መዳራትም ወይም ሰለ አለመታዘዝ የማይከሰስ ማንም ቢኖር፥ ሹመው።
፯ ኤጲስ ቆጶስ፥ እንደ እግዚአብሔር መጋቢ፥ የማይነቀፍ ሊሆን ይገባዋልና፤ የማይኮራ፥ የማይቆጣ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ፥ ነውረኛ ረብ የማይወድ፥
፰ ነገር ግን እንግዳ ተቀባይ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚወድ፥ ጠንቃቃ፥ ጻድቅ፥ ቅዱስ፥ ራሱን የሚገዛ ይሁን፤
፱ ሕይወት በሚገኝበት ትምህርት ደግሞ ሊመክር ተቃዋሚዎቹንም ሊወቅሰ ይችል ዘንድ፥ እንደተማረው በታመነ ቃል ይጽና።
፲ የማይታዘዙና ከንቱ የሚናገሩ የሚያታልሉ ይልቁንም ከተገረዙት ወገን የሚሆኑ ብዙ ናቸውና፤
፲፩ እነዚህም ሰለ ነውረኛ ረብ የማይገባውን እያስተማሩ ቤቶችን በሞላው ሰለ ሚገለብጡ፥ አፋቸውን መዝጋት ይገባል።
፲፪ የገዛ ራሳቸው ነቢይ የሆነ ከእነርሱ አንዱ። የቀርጤስ ሰዎች ዘወትር ውሸተኞች፥ ክፉዎች አራዊት፥ በላተኞች፥ ሥራ ፈቶች ናቸው ብሎአል።
፲፫-፲፭ ሁሉ ለንጹሖች ንጹሕ ነው፤ ለርኩሳንና ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም የለም፥ ነገር ግን አእምሮአቸውም ሕሊናቸውም ረክሶአል።
፲፮ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ በግልጥ ይናገራሉ፥ ዳሩ ግን የሚያስጸይፉና የማይታዘዙ ለበጎ ሥራም ሁሉ የማይበቁ ሰለ ሆኑ፥ በሥራቸው ይክዱታል።

፪

፩ እንተ ግን ሕይወት ለሚገኝበት ትምህርት የሚገባውን ተናገር።
፪ ሽማግሌዎች ልከኞች፥ ጭምቶች፥ ራሳቸውን የሚገዙ፥ በእምነትና በፍቅር በመጽናትም ጤናሞች እንዲሆኑ ምከራቸው፤
፫ እንዲሁም አሮጊቶች ሴቶች አካሄዳቸው ለቅዱስ አገልግሎት የሚገባ፥ የማያሙ፥ ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዙ፥ በጎ የሆነውን ነገር የሚያስተምሩ ይሁኑ፤
፬-፭ ጎበዞችም እንዲሁ ራሳቸውን እንዲገዙ ምከራቸው።
፮-፲፩ ሰዎችን ሁሉ የሚያድን የእግዚአብሔር ጸጋ ተገልጦአልና፤
፲፪-፲፬ መድኃኒታችንም ከዓመፅ ሁሉ እንዲቤዠን፥ መልካሙንም ለማድረግ የሚቀናውን ገንዘቡም የሚሆነውን ሕዝብ ለራሱ እንዲያነጻ፥ ሰለ እኛ ነፍሱን ሰጥቶአል።
፲፭ ይህን በሙሉ ሥልጣን ተናገርና ምከር ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።

፫

፩-፫ እኛ ደግሞ አስቀድመን የማናስተውል ነበርንና፤ የማንታዘዝ፥ የምንስት፥ ለምኞትና ለልዩ ልዩ ተድላ እንደ ባሪያዎች የምንገዛ፥ በክፋትና በምቀኝነት የምንኖር፥ የምንጣላ፥ እርስ በርሳችን የምንጠላላ ነበርን።
፬ ነገር ግን የመድኃኒታችን የእግዚአብሔር ቸርነትና ሰውን መውደዱ በተገለጠ ጊዜ፥
፭ እንደ ምሕረቱ መጠን ለአዲስ ልደት በሚሆነው መታጠብና በመንፈስ ቅዱስ በመታደስ አዳነን እንጂ፥ እኛ ሰላደረግነው በጽድቅ ሰለ ነበረው ሥራ አይደለም፤
፮-፯ ቃሉ የታመነ ነው። እግዚአብሔርንም የሚያምኑት በመልካም ሥራ በጥንቃቄ እንዲጸኑ፥ እነዚህን አስረግጠህ እንድትናገር እፈቅዳለሁ። ይህ መልካምና ለሰዎች የሚጠቅም ነው፤
፱ ነገር ግን ሞኝነት ካለው ምርመራና ከትውልዶች ታሪክ ከክርክርም ሰለ ሕግም ከሚሆን ጠብ ራቅ፤ የማይጠቅሙና ከንቱዎች ናቸውና፤
፲-፲፪ አርጢሞንን ወይም ቲኪቆስን ወደ እንተ ሰልክ፥ ወደ ኒቆጵልዮን ወደ እኔ እንድትመጣ ትጋ፤ በዚያ ልከርም ቈርጬአለሁና።
፲፫ ሕግ አዋቂውን ዜማስንና አጵሎስን ምንም እንዳይጎድልባቸው በጉዞአቸው ተግተህ እርዳ።
፲፬ ከወገናችንም ያሉት ደግሞ ፍሬ ቢሶች ሆነው እንዳይቀሩ፥ የግድ ሰለሚያስፈልገው ነገር በመልካም ሥራ እንዲጸኑ ይማሩ።
፲፭ ከእኔ ጋር ያሉት ሁሉ ሰላምታ ያቀርቡልሃል። በእምነት ለሚወዱን ሰላምታ አቅርብልን። ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ፊልሞና

፩ የክርስቶስ ኢየሱስ እስር ጳውሎስ ወንድሙም ጢሞቴዎስ፥ ለተወደደውና አብሮን ለሚሠራ
ለፊልሞና፥
፪ ለእኅታችንም ለአፍብያ፥ ከእኛም ጋር አብሮ ወታደር ለሆነ ለአርክጳ፥ በቤትህም ላለች ቤተ
ክርስቲያን፤
፫ ከእግዚአብሔር ከአባታችን ከጌታም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፬-፭ የእምነትህም ኅብረት፥ በእኛ ዘንድ ያለውን በጎ ነገር ሁሉ በማወቅ፥ ለክርስቶስ ኢየሱስ ፍሬ እንዲያፈራ
እለምናለሁ፤
፯ የቅዱሳን ልብ በእነተ ሰራ ሰለ ዐረፈ፥ ወንድሜ ሆይ፥ በፍቅርህ ብዙ ደስታንና መጽናናትን
አግኝቼአለሁና።
፰ ስለዚህ የሚገባውን አዝህ ዘንድ በክርስቶስ ምንም እንኳ ብዙ ድፍረት ቢኖረኝ፥
፱ ይልቁንም እንደዚህ የሆንሁ እኔ ጳውሎስ ሸማግሌው፥ አሁንም ደግሞ የኢየሱስ ክርስቶስ እስር
የሆንሁ፥ ስለ ፍቅር እለምናለሁ።
፲-፲፪ እርሱን እልከዋለሁ፤
፲፫ እንተም ልቤ እንደሚሆን ተቀበለው። እኔስ በወንጌል እስራት ሰለ እንተ እንዲያገለግለኝ ለራሴ
ላስቀረው እፈቅድ ነበር፥
፲፬ ነገር ግን በጎነትህ በፈቃድህ እንጂ በግድ እንዳይሆን፥ ሳልማከርህ ምንም እንኳ ላደርግ
አልወደድሁም።
፲፭ ተቀብለህ ለዘላለም እንድትይዘው ሰለዚህ ምናልባት ለጊዜው ተለይቶሃልና፤
፲፮ ከእንግዲህ ወዲህ እንደ ባሪያ አይሆንም፥ ነገር ግን ለእኔ በተለየ የተወደደ ወንድም ከሆነ፥ ለእንተማ
ይልቅ በሰጋውም በጌታም ዘንድ ከባሪያ የሚሻል የተወደደ ወንድም እንዴት አይሆንም።
፲፯ እንግዲህ እንደ ባልንጀራ ብትቈጥረኝ፥ እንደ እኔ አድርገህ ተቀበለው።
፲፰ በእንዳች ነገር የበደለህ ቢኖር ግን ወይም ብድር ያለበት እንደሆነ፥ ይህን በእኔ ላይ ቍጠር፤
፲፱ እኔ ጳውሎስ። እኔ እመልሰዋለሁ ብዬ በእጄ እጽፋለሁ፤ ከዚህም በላይ ለእኔ የራስህ ደግሞ ብድር
እንዳለብህ አልልህም።
፳ እዎን፥ ወንድሜ ሆይ፥ በጌታ እኔ እንድጠቀምብህ ይሁን፤ በክርስቶስ ልቤን አሳርፍልኝ።
፳፩ ከምልህ ይልቅ አብልጠህ እንድታደርግ አውቄ እንድትታዘዝም ታምኜ እጽፍልሃለሁ።
፳፪ ደግሞ ከዚህም ጋር የማስተናገጃ ቤት አዘጋጅልኝ፤ በጸሎታችሁ ለእናንተ እንድሰጥ ተሰፋ
አደርጋለሁና።
፳፫ በክርስቶስ ኢየሱስ ከእኔ ጋር የታሰረ ኤጳፍራ
፳፬ አብረውኝም የሚሰሩ ማርቆስና አርስጥሮኮስ ዴማስም ሉቃስም ሰላምታ ያቀርቡልሃል።
፳፭ የጌታችን የኢሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከመንፈሳችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

ወደ ዕብራውያን

፩ ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና
በብዙ ጎዳና ለአባቶቻችን በነቢያት ተናግሮ፥
፪ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን
በፈጠረበት በልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ
ተናገረን፤
፫ እርሱም የክብሩ መንጸባረቅና የባሕርዩ ምሳሌ
ሆኖ፥ ሁሉን በሰልጣኑ ቃል እየደገፈ፥ ኃጢአታችንን
በራሱ ካነጻ በኋላ በሰማያት በግርማው ቀኝ ተቀመጠ፤
፬ ከመላእክት ይልቅ እጅግ የሚበልጥ ስምን በወረሰ
መጠን እንዲሁ ከእነርሱ እብዝቶ ይበልጣል።
፭ ከመላእክትስ። አንተ ልጄ ነህ፥ እኔ ዛሬ
ወልጄሃለሁ፥ ደግሞም። እኔ አባት እሆነዋለሁ እርሱም
ልጅ ይሆነኛል
፮ ያለው ከቶ ለማን ነው? ደግሞም በኩርን
ወደ ዓለም ሲያገባ። የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉም
ለእርሱ ይሰገዱ ይላል።
፯ ስለ መላእክትም። መላእክቱን መናፍስት
አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ
፰ ይላል፤ ስለ ልጁ ግን። አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ
እስከ ዘላለም ድረስ ይኖራል፤ የመንግሥትህ በትር
የቅንነት በትር ነው።
፱ ጽድቅን ወደድህ ዓመፅንም ጠላህ፤ ስለዚህ
እግዚአብሔር አምላክህ ከጓደኞችህ ይልቅ በደስታ
ዘይት ቀባህ
፲ ይላል። ደግሞ። ጌታ ሆይ፥ አንተ ከጥንት ምድርን
መሠረትህ፥ ሰማዮችም የእጆችህ ሥራ ናቸው፤
፲፩ እነርሱም ይጠፋሉ አንተ ግን ጸንተህ ትኖራለህ፤
ሁሉም እንደ ልብስ ያረጃሉ፥
፲፪ እንደ መጎናጸፊያም ትጠቀልላቸዋለህ
ይለወጡማል፤ አንተ ግን አንተ ነህ፥ ዓመቶችህም
ከቶ አያልቁም
፲፫ ይላል። ነገር ግን ከመላእክት። ጠላቶችህን
የእግርህ መረገጫ እስካደርግልህ ድረስ በቀኜ
ተቀመጥ
፲፬ ከቶ ለማን ብሎአል? ሁሉ መዳንን ይወርሱ
ዘንድ ሰላላቸው ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉም
መናፍስት አይደሉምን?

፪

፩ ስለዚህ ከሰማነው ነገር ምናልባት እንዳንወሰድ፥
ለእርሱ አብልጠን ልንጠነቀቅ ያሰፈልገናል።
፪ በመላእክት የተነገረው ቃል ጽኑ ከሆነ፥
መተላለፍና አለመታዘዝም ሁሉ የጽድቅን ብድራት
ከተቀበለ፥ እኛስ እንዲህ ያለውን ታላቅ መዳን ቸል
ብንለው፥ እንዴት እናመልጣለን?
፫ ይህ በጌታ በመጀመሪያ የተነገረ ነበርና፥
የሰሙትም ለእኛ አጸኑት፥
፬ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ
በምልክትና በድንቅ ነገር በልዩ ልዩ ተአምራትም፥
መንፈስ ቅዱስንም በማደል አብሮ መስክረለት።
፭ ስለ እርሱ የምንናገርበትን የሚመጣውን ዓለም
ለመላእክት ያሰገዛው አይደለምና።
፮ ነገር ግን እንዱ በአንድ ሰፍራ። ታሰበው ዘንድ
ሰው ምንድር ነው? ወይስ ትጎበኘው ዘንድ የሰው
ልጅ ምንድር ነው?
፯ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አሳነስኸው፤ የክብርና
የምስጋና ዘውድ ጫንህለት፥ በእጆችህም ሥራ ላይ
ሾምኸው፤
፰ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት ብሎ
መስክረ። ሁሉን ከእርሱ በታች ባሰገዛ ጊዜ
ያልተገዛለት ምንም አልተወምና። አሁን ግን ሁሉ እንደ
ተገዛለት ገና እናይም፤
፱ ነገር ግን በእግዚአብሔር ጸጋ ሰለ ሰው ሁሉ
ሞትን ይቀምስ ዘንድ፥ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት
እንሶ የነበረውን ኢየሱስን ከሞት መከራ የተነሣ
የክብርና የምስጋናን ዘውድ ተጭኖ እናየዋለን።
፲ ብዙ ልጆችን ወደ ክብር ሲያመጣ የመዳናቸውን
ራስ በመከራ ይፈጽም ዘንድ፥ ከእርሱ የተነሣ ሁሉ
በእርሱም ሁሉ ለሆነ፥ ለእርሱ ተገብቶታልና።
፲፩-፲፫ ስለዚህም ምክንያት። ስምህን ለወንድሞቼ
እነግራቸዋለሁ በማኅበርም መካከል በዜማ
እመሰግንሃለሁ፤ ደግሞም። እኔ በእርሱ እታመናለሁ፤
ደግሞም። እነሆኝ እኔን እግዚአብሔር የሰጠኝንም
ልጆች ሲል ወንድሞች ብሎ ሊጠራቸው አያፍርም።
፲፬-፲፮ የአብርሃምን ዘር ይዞአል እንጂ የያዘው
የመላእክትን አይደለም።
፲፯ ስለዚህ የሕዝብን ኃጢአት ለማስተሰረይ፥
ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ የሚምርና የታመነ
ሊቀ ካህናት እንዲሆን፥ በነገር ሁሉ ወንድሞቹን
ሊመስል ተገባው።
፲፰ እርሱ ራሱ ተፈትኖ መከራን ሰለ ተቀበለ
የሚፈተኑትን ሊረዳቸው ይችላልና።

፫

፩ ስለዚህ፥ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፋዮች የሆናችሁ
ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ፥ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና
ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመልከቱ፤
፪ ሙሴ ደግሞ በቤቱ ሁሉ የታመነ እንደሆነ፥ እርሱ
ለሾመው የታመነ ነበረ።
፫ ቤትን የሚያዘጋጀው ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ
ክብር እንዳለው መጠን፥ እንዲሁ እርሱ ከሙሴ ይልቅ
የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተቆጥሮአልና።
፬ እያንዳንዱ ቤት በአንድ ሰው ተዘጋጅቶአልና፥
ሁሉን ያዘጋጀ ግን እግዚአብሔር ነው።
፭ ሙሴስ በኋላ ሰለሚነገረው ነገር ምስክር ሊሆን
በቤቱ ሁሉ እንደ ሎሌ የታመነ ነበረ፥ ክርስቶስ ግን
እንደ ልጅ በቤቱ ላይ የታመነ ነው፤
፮ እኛም የምንደፍርበትን የምንመካበትንም ተስፋ
እስከ መጨረሻው እጽንተን ብንጠብቅ ቤቱ ነን።
፯ ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል።
፰-፲ ስለዚህ ያን ትውልድ ተቆጥቼ። ዘወትር
በልባቸው ይስታሉ መንገዴን ግን አላወቁም አልሁ፤
፲፩ እንዲሁ። ወደ ዕረፍቴ አይገቡም ብዬ በቍጣዬ
ማልሁ።
፲፪ ወንድሞች ሆይ፥ ምናልባት ሕያው
እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ
ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤

፲፫ ነገር ግን ከእናንተ ማንም በኃጢአት መታለል እልከኛ እንዳይሆን፥ ዛሬ ተብሎ ሲጠራ ሳለ፥ በእያንዳንዱ ቀን እርስ በርሳችሁ ተመካከሩ፤
፲፬ የመጀመሪያ እምነታችንን እስከ መጨረሻው አጽንተን ብንጠብቅ፥ የክርስቶስ ተካፋዮች ሆነናልና፤
፲፭ እየተባለ። ዛሬ ድምጹን ብትሰሙት፥ በማስመረር እንደሆነ ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ።
፲፮ ሰምተው ያስመረሩት እነማን ነበሩ? በሙሴ ተመርተው ከግብጽ የወጡ ሁሉ አይደሉምን?
፲፯ አርባ አመትም የተቆጣባቸው እነማን ነበሩ? ሬሳቸው በምድረ በዳ የወደቀ፥ ኃጢአትን ያደረጉት እነርሱ አይደሉምን?
፲፰ ካልታዘዙትም በቀር ወደ እረፍቱ እንዳይገቡ የማለባቸው እነማን ነበሩ?
፲፱ ባለማመናቸውም ጠንቅ ሊገቡ እንዳልተቻላቸው እናያለን።

፬

፩ እንግዲህ ወደ ዕረፍቱ ለመግባት ተስፋ ገና ቀርቶልን ከሆነ፥ ምናልባት ከእናንተ ማንም የማይበቃ መስሎ እንዳይታይ እንፍራ።
፪ ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምስራች ተሰብኮልናልና፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።
፫ ሥራው ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ምንም እንኳ ቢፈጸም። እንዲህ። ወደ ዕረፍቴ እይገቡም ብዬ በቁጣዬ ማልሁ እንዳለ፥ እኛስ ያመንን ወደ ዕረፍቱ እንገባለን።
፬ ስለ ሰባተኛው ቀን በእንድ ስፍራ። እግዚአብሔርም በሰባተኛው ቀን ከሥራው ሁሉ ዐረፈ ብሎአልና፤
፭ በዚህ ስፍራም ደግሞ። ወደ ዕረፍቴ አይገቡም።
፮ እንግዲህ አንዳንዶች በዚያ እንዲገቡ ስለ ቀሩ፥ ቀድሞም የምስራች የተሰበከላቸው ባለመታዘዝ ጠንቅ ስላልገቡ።
፯ ዛሬ ድምፁን ብትሰሙት ልባችሁን እልከኛ አታድርጉ በፊት እንደ ተባለ፥ ይህን ከሚያህል ዘመን በኋላ በዳዊት ሲናገር። ዛሬ ብሎ አንድ ቀን እንደ ገና ይቀጥራል።
፰ ኢያሱ እሳርፎአቸው ኖሮ ቢሆንስ፥ ከዚያ በኋላ ስለ ሌላ ቀን ባልተናገረ ነበር።
፱ እንግዲያስ የሰንበት ዕረፍት ለእግዚአብሔር ሕዝብ ቀርቶላቸዋል።
፲ ወደ ዕረፍቱ የገባ፥ እግዚአብሔር ከሥራው እንዳረፈ፥ እርሱ ደግሞ ከሥራው አርፎአልና።
፲፩ እንግዲህ እንደዚያ እንደ አለመታዘዝ ምሳሌ ማንም እንዳይወድቅ ወደዚያ ዕረፍት ለመግባት እንትጋ።
፲፪ የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ሰሜትና አሳብ ይመረምራል፤
፲፫ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይኖቹ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ፥ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።
፲፬ እንግዲህ በሰማያት ያለፈ ትልቅ ሊቀ ካህናት የእግዚአብሔር ልጅ ኢየሱስ ስላለን፥ ጸንተን ሃይማኖታችንን እንጠብቅ።
፲፭ ከኃጢአት በቀር በነገር ሁሉ እንደ እኛ የተፈተነ ነው እንጂ፥ በድካማችን ሊራራልን የማይችል ሊቀ ካህናት የለንም።
፲፮ እንግዲህ ምሕረትን እንድንቀበል በሚያስፈልገንም ጊዜ የሚረዳንን ጸጋ እንድናገኝ ወደ ጸጋው ዙፋን በእምነት እንቅረብ።

፭

፩ ሊቀ ካህናት ሁሉ ስለ ኃጢአት መባንና መስዋዕትን ሊያቀርብ ከሰው ተመርጦ ለእግዚአብሔር በሆነው ነገር ሁሉ ስለ ሰው ይሾማልና፤
፪ እርሱ ራሱም ደግሞ ድካምን ስለሚለብስ፥ ላልተማሩትና ለሚስቱት ሊራራላቸው ይችላል፤
፫ በዚህም ምክንያት ስለ ሕዝብ እንደሚያቀርብ እንዲሁ ስለ ራሱ ደግሞ መስዋዕትን ስለ ኃጢአት ሊያቀርብ ይገባዋል።
፬ እንደ አሮንም በእግዚአብሔር ከተጠራ በቀር ማንም ክብሩን ለራሱ የሚወስድ የለም።
፭ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ ሊቀ ካህናት ሊሆን ራሱን አላከበረም ነገር ግን። አንተ ልጄ ነህ እኔ ዛሬ ወልጄሃለሁ ያለው እርሱ ነው፤
፮ እንደዚህም በሌላ ስፍራ ደግሞ። አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ይላል።
፯ እርሱም በስጋው ወራት ከሞት ሊያድነው ወደሚችል ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ፥ እግዚአብሔርንም ስለ መፍራቱ ተሰማለት፤
፰ ምንም ልጅ ቢሆን፥ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ፤
፱-፲ ስለ እርሱም የምንናገረው ብዙ ነገር አለን፥ ጆሮቻችሁም ስለ ፈዘዙ በቃል ልንተረጉመው ጭንቅ ነው።
፲፪ ከጊዜው የተነሳ አስተማሪዎች ልትሆኑ ሲገባችሁ፥ አንድ ሰው ስለ እግዚአብሔር ቃላት መጀመሪያ ያለውን የሕፃንነትን ትምህርት እንዲያስተምራችሁ እንደ ገና ያስፈልጋችኋልና፤ የሚያስፈልጋችሁም ወተት ነው እንጂ ጠንካራ ምግብ አይደለም።
፲፫ ወተት የሚጋት ሁሉ ሕፃን ስለ ሆነ የጽድቅን ቃል አያውቅምና፤
፲፬ ጠንካራ ምግብ ግን መልካሙንና ክፉውን ለመለየት በሰራቸው የለመደ ልቡና ላላቸው ለፍጹማን ሰዎች ነው።

፮

፩-፫ እግዚአብሔርም ቢፈቅድ ይህን እናደርጋለን።
፬ አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን ስማያዊውንም ስጦታ የቀመሱትን ከመንፈስ ቅዱስም ተካፋዮች ሆነው የነበሩትን
፭ መልካሙንም የእግዚአብሔርን ቃልና ሊመጣ ያለውን የዓለም ኃይል የቀመሱትን
፮ በኋላም የካዱትን እንደገና ለንስሐ እነርሱን ማደስ የማይቻል ነው፤ ለራሳቸው የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና ያዋርዱትማልና።

፯ ብዙ ጊዜ በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን ዝናብ የምትጠጣ መሬት፥ ለሚያርሱአትም ደግሞ የምትጠቅምን አትክልት የምታበቅል፥ ከእግዚአብሔር በረከትን ታገኛለችና፤
፰ እሾህና ኩርንችትን ግን ብታወጣ፥ የተጣለች ናት ለመረገምም ትቀርባለች፥ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።
፱ ሰለ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ምንም እንኳ እንዲሁ ብንናገር፥ ኢብልጦ የሚሻለውና ለመዳን የሚሆነው እንዲሆንላችሁ ተረድተናል።
፲ እግዚአብሔር፥ ቅዱሳንን ሰላገለገላችሁ እሰከ አሁንም ሰለምታገለግሉአቸው፥ ያደረጋችሁትን ሥራ ለሰሙም ያሳያችሁትን ፍቅር ይረሳ ዘንድ ዓመፀኛ አይደለምና።
፲፩-፲፪ እንዲሁም እርሱ ከታገሰ በኋላ ተሰፋውን አገኘ።
፲፫ ሰዎች ከእነርሱ በሚበልጠው ይምላሉና፥ ለማሰረዳትም የሆነው መሐላ የሙግት ሁሉ ፍጻሜ ይሆናል፤
፲፯-፲፱ ይህም ተሰፋ እንደ ነፍስ መልሕቅ አለን እርሱም እርግጥና ጽኑ የሆነ ወደ መጋረጃውም ውሰጥ የገባ ነው፤
፳ በዚያም ኢየሱስ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህናት የሆነው፥ ሰለ እኛ ቀዳሚ ሆኖ ገባ።

፯

፩ የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤
፪ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አሰራትን አካፈለው። የሰሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፥ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው።
፫ አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የሉትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።
፬ የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አሰራት የሰጠው ይህ ሰው እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ አስኪ ተመልከቱ።
፭ ከሌዊ ልጆችም ክህነትን የሚቀበሉት ከህዝቡ ማለት ከወንድሞቻቸው፥ እነርሱ ምንም ከአብርሃም ወገብ ቢወጡ፥ ከእነርሱ አሥራትን በሕግ እንዲያስወጡ ትእዛዝ አላቸው፤
፮ ትውልዱ ከእነርሱ የማይቈጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቶአል፥ የተሰፋ ቃል የነበረውንም ባርኮአል።
፯ ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው።
፰ በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያሰወጣሉ፥ በዚያ ግን የሚያስወጣ በሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው።
፱ ይህንም ለማለት ሲፈቀድ፥ አሥራትን የሚያሰወጣ ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል፤
፲ መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና።
፲፩ እንግዲህ ህዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን፥ እንደ አሮን ሹመት የማይቈጠር፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሳ ወደፊት ሰለ ምን ያስፈልጋል?
፲፪ ክህነቱ ሲለወጥ፥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና።
፲፫ ይህ ነገር የተነገረለት እርሱ በሌላ ወገን ተካፍሎአልና፥ ከዚያም መሠዊያውን ያገለገለ ማንም የለም፤
፲፬ ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደወጣ የተገለጠ ነውና፥ ሰለዚህም ነገድ ሙሴ ምንም እንኳ ሰለ ክህነት አልተናገረም።
፲፭-፲፯ እነተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና።
፲፰-፲፱ እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖአል።
፳፫ እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ሰለ ከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው፤
፳፬ እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ሰለሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው፤
፳፭ ሰለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ሰለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል።
፳፮ ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ፥ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባልና፤
፳፯ እርሱም እንደነዚያ ሊቃነ ካህናት አሰቀድሞ ሰለ ራሱ ኃጢአት በኋላም ሰለ ሕዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መሥዋዕትን ሊያቀርብ አያሰፈልገውም፤ ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈጽሞ አድርጎአልና።
፳፰ ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና፤ ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን ልጅ ይሾማል።

፰

፩ ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፤
፪ እርሱም የመቅደስና የእውነተኛይቱ ድንኳን አገልጋይ ነው፥ እርሰዋም በሰው ሳይሆን በጌታ የተተከለች ናት።
፫ ሊቀ ካህናት ሁሉ መባንና መሥዋዕትን ሊያቀርብ ይሾማልና፤ ሰለዚህም ለዚህ ደግሞ የሚያቀርበው እንዳች ሊኖረው የግድ ነው።
፬ እንግዲህ በምድር ቢኖርስ፥ እንደ ሕግ መባን የሚያቀርቡት ሰላሉ፥ ካህን እንኳ ባልሆነም፤
፭ እነርሱም ሙሴ ድንኳኒቱን ሊሠራ ሳለ እንደ ተረዳ፥ ለሰማያዊ ነገር ምሳሌና ጥላ የሚሆነውን ያገለግላሉ። በተራራው እንደ ተገለጠልህ ምሳሌ ሁሉን ታደርግ ዘንድ ተጠንቀቅ ብሎት ነበርና።
፮ አሁን ግን በሚሻል ተሰፋ ቃል በተመሠረተ በሚሻል ኪዳን ደግሞ መካከለኛ እንደሚሆን በዚያ ልክ እጅግ የሚሻል አገልግሎት አግኝቶአል።
፯ ፊተኛው ኪዳን ነቀፋ ባይኖረው፥ ለሁለተኛው ሰፍራ ባልተፈለገም ነበር።

፰ እነርሱን እየነቀፈ ይላቸዋልና። እነሆ፥ ከእስራኤል
ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን የምገባበት
ወራት ይመጣል ይላል ጌታ፤
፱ ከግብፅ አገር እወጣቸው ዘንድ እጆቸውን
በያዝሁበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ኪዳን
አይደለም፤ እነርሱ በኪዳኔ አልጸኑምና፥ እኔም ቸል
አልኋቸው ይላል ጌታ።
፲ ከዚያ ወራት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምገባው
ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል ጌታ፤ ሕጌን በልቡናቸው
እኖራለሁ በልባቸውም እጽፈዋለሁ፥ እኔም አምላክ
እሆንላቸዋለሁ እነርሱም ሕዝብ ይሆኑልኛል።
፲፩ እያንዳንዱም ጐረቤቱን እያንዳንዱም
ወንድሙን። ጌታን እወቅ ብሎ እያስተምርም ከታናሹ
ጀምሮ እስከ ታላቁ ድረስ ሁሉ ያውቁኛልና።
፲፪ ዓመፃቸውን እምራቸዋለሁና፥ ኃጢአታቸውንም
ደግሜ አላስብም።
፲፫ አዲስ በማለቱ ፊተኛውን አስረጅቶአል፤ አሮጌና
ውራጅ የሆነውስ ሊጠፋ ቀርቦአል።

፱

፩ ፊተኛይቱም ደግሞ የአገልግሎት ሰርዓትና የዚህ
ዓለም የሆነው መቅደስ ነበራት።
፪ የመጀመሪያይቱ ድንኳን ተዘጋጅታ ነበርና፥
በእርስዋም ቅድስት በምትባለው ውስጥ መቅረዙና
ጠረጴዛው የመስዋዕቱም ኅብስት ነበረባት፤
፫ ከሁለተኛውም መጋረጃ ወዲያ ቅድስተ ቅዱሳን
የምትባለው ድንኳን ነበረች፥
፬ በዚያም ውስጥ የወርቅ ማዕጠንት ነበረ
ሁለንተናዋም በወርቅ የተለበጠች የኪዳን ታቦት፤
በእርስዋም ውስጥ መና ያለባት የወርቅ መሶብና
የበቀለች የአሮን በትር የኪዳኑም ጽላት ነበሩ፥
፭ በላይዋም ማስተሰሪያውን የሚጋርዱ የክብር
ኪሩቤል ነበሩ፤ ስለ እነዚህም ስለ እያንዳንዳቸው
ልንናገር አሁን እንችልም።
፮ ይህም እንደዚህ ተዘጋጅቶ ሳለ፥ ካህናት
አገልግሎታቸውን እየፈጸሙ ዘወትር በፊተኛይቱ
ድንኳን ይገቡባታል፤
፯ በሁለተኛይቱ ግን ሊቀ ካህናት ብቻውን በዓመት
አንድ ጊዜ ይገባባታል፥ እርሱም ስለ ራሱና ስለ ሕዝቡ
ስሕተት የሚያቀርበውን ደም ሳይዝ አይገባም፤
፰ ፊተኛይቱም ድንኳን በዚህ ገና ቆማ ሳለች፥
ወደ ቅድስት የሚወስደው መንገድ ገና እንዳልተገለጠ
መንፈስ ቅዱስ ያሳያል።
፱-፲፩ ነገር ግን ክርስቶስ ይመጣ ዘንድ ላለው
መልካም ነገር ሊቀ ካህናት ሆኖ፥ በምትበልጠውና
በምትሻለው በእጅችም ባልተሠራች ማለት ለዚህ
ፍጥረት ባልሆነች ድንኳን፥
፲፪ የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ
ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች
ደም አይደለም።
፲፫ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም በረከሱትም ላይ
የተረጨ የጊደር አመድ ሥጋን ለማንጻት የሚቀድሱ
ከሆኑ፥
፲፬ ነውር የሌለው ሆኖ በዘላለም መንፈስ ራሱን
ለእግዚአብሔር ያቀረበ የክርስቶስ ደም እንዴት ይልቅ
ሕያውን እግዚአብሔርን ልታመልኩ ከሞተ ሥራ
ሕሊናችሁን ያነጻ ይሆን?
፲፭ ስለዚህም የፊተኛው ኪዳን ሲጸና ሕግን
የተላለፉትን የሚቤዥ ሞት ስለ ሆነ፥ የተጠሩት
የዘላለምን ርስት የተስፋ ቃል እንዲቀበሉ እርሱ የአዲስ
ኪዳን መካከለኛ ነው።
፲፮ ኑዛዜ ያለ እንደሆነ የተናዛዡን ሞት ማርዳት
የግድ ነውና፤
፲፯ ሰው ሲሞት ኑዛዜው ይጸናልና፥ ተናዛዡ
በሕይወት ሲኖር ግን ከቶ አይጠቅምም።
፲፰ ስለዚህም ፊተኛው ኪዳን እንኳ ያለ ደም
አልተመረቀም።
፲፱-፳፩ እንዲሁም በድንኳኒቱና በማገልገያው ዕቃ
ሁሉ ደምን ረጨ።
፳፪ እንደ ሕጉም ከጥቂቶች በቀር ነገር ሁሉ በደም
ይነጻል፥ ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም።
፳፫ እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር
በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉቱ ራሳቸው ከእርሱ
ይልቅ በሚበልጥ መስዋዕት ሊነጹ የግድ ነበረ።
፳፬ ክርስቶስ በእጅ ወደ ተሰራች፥ የእውነተኛይቱ
ምሳሌ ወደ ምትሆን ቅድስት አልገባምና፥ ነገር ግን
በእግዚአብሔር ፊት ስለ እኛ አሁን ይታይ ዘንድ ወደ
እርሰዋ ወደ ሰማይ ገባ።
፳፭ ሊቀ ካህናትም በየዓመቱ የሌላውን ደም ይዞ
ወደ ቅድስት እንደሚገባ፥ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ
አልገባም፤
፳፮ እንዲህ ቢሆንስ፥ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ
ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገው ነበር፤ አሁን ግን
በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር
አንድ ጊዜ ተገልጦአል።
፳፯ ለሰዎችም አንድ ጊዜ መሞት ከእርሱ በኋላም
ፍርድ እንደ ተመደበባቸው፥
፳፰ እንዲሁ ክርስቶስ ደግሞ፥ የብዙዎችን ኃጢአት
ሊሸከም አንድ ጊዜ ከተሰዋ በኋላ፥ ያድናቸው
ዘንድ ለሚጠባበቁት ሁለተኛ ጊዜ ያለ ኃጢአት
ይታይላቸዋል።

፲

፩ ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል
ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ
ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን
ሊፈጽም ከቶ አይችልም።
፪ እንደዚህማ ባይሆን፥ የሚያመልኩት አንድ ጊዜ
ነጽተው ከዚያ በኋላ በሕሊናቸው ኃጢአትን ሰላላወቁ
ማቅረብን በተዉ አልነበረምን?
፫ ነገር ግን በዚያ መሥዋዕት በየዓመቱ የኃጢአት
መታሰቢያ አለ፤
፬ የኮርማዎችና የፍየሎች ደም ኃጢአትን
እንዲያሰወግድ የማይቻል ነውና።
፭ ስለዚህ ወደ ዓለም ሲገባ። መሥዋዕትንና መባን
አልወደድህም ሥጋን ግን አዘጋጀህልኝ፤
፮ በሙሉ በሚቃጠል መሥዋዕትና ስለ ኃጢአት
በሚሰዋ መሥዋዕት ደስ አላለህም።
፯ በዚያን ጊዜ። እነሆ፥ በመጽሐፍ ጥቅልል ስለ
እኔ እንደ ተጻፈ፥ አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ
መጥቼአለሁ አልሁ

፳፭ ይላል። በዚህ ላይ። መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም ሰለ ኃጢአትም የሚሰዋ መሥዋዕትን አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፥ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው፥
፳፮ ቀጥሎ። እነሆ፥ እምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል። ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል።
፲ በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል።
፲፩ ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያሰወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞአል፤
፲፪ እርሱ ግን ሰለ ኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፥
፲፫ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል።
፲፬ አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና።
፲፭-፲፮ ብሎ ከተናገረ በኋላ፥ ኃጢአታቸውንና ዓመጻቸውንም ደግሜ አላሰብም ይላል።
፲፯ የእነዚህም ሰርየት ባለበት ዘንድ፥ ከዚህ ወዲህ ሰለ ኃጢአት ማቅረብ የለም።
፲፱-፳፭ በእግዚአብሔርም ቤት ላይ የሆነ ታላቅ ካህን ሰላለን፥
፳፪ ከክፉ ሕሊና ለመንጻት ልባችንን ተረጭተን ሰውነታችንንም በጥሩ ውኃ ታጥበን በተረዳንበት እምነት በቅን ልብ እንቅረብ፤
፳፫ የተሰፋን ቃል የሰጠው የታመነ ነውና እንዳይነቃነቅ የተሰፋችንን ምስክርነት እንጠብቅ፤
፳፬ ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤
፳፭ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።
፳፮ የእውነትን እውቀት ከተቀበልን በኋላ ወደን ኃጢአት ብናደርግ ከእንግዲህ ወዲህ ሰለ ኃጢአት መሥዋዕት አይቀርልንምና፥
፳፯ የሚያሰፈራ ግን የፍርድ መጠበቅ ተቃዋሚዎችንም ሊበላ ያለው የእሳት ብርታት አለ።
፳፰ የሙሴን ሕግ የናቀ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ቢመሰክሩበት ያለ ርኅራኄ ይሞታል፤
፳፱ የእግዚአብሔርን ልጅ የረገጠ ያንንም የተቀደሰበትን የኪዳኑን ደም እንደ ርኩስ ነገር የቆጠረ የጸጋውንም መንፈስ ያክፋፋ፥ እንዴት ይልቅ የሚብስ ቅጣት የሚገባው ይመሰላችኋል?
፴ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራትን እመልሳለሁ ያለውን እናውቃለንና፤ ደግሞም። ጌታ በሕዝቡ ይፈርዳል።
፴፩ በሕያው እግዚአብሔር እጅ መውደቅ የሚያሰፈራ ነው።
፴፪-፴፬ የሚበልጥና ለዘወትር የሚኖር ገንዘብ በሰማይ ራሳችሁ እንዳላችሁ አውቃችሁ፥ በእሰራቴ ራራችሁልኝ የገንዘባችሁንም ንጥቂያ በደስታ ተቀበላችሁ።
፴፭ እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ።
፴፮ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተሰፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያሰፈልጋችኋልና።
፴፯ ገና በጣም ጥቂት ጊዜ ነው፥ ሊመጣ ያለውም ይመጣል አይዘገይምም፤
፴፰ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል ወደ ኋላም ቢያፈገፍግ፥ ነፍሴ በእርሱ ደስ አይላትም።
፴፱ እኛ ግን ነፍሳቸውን ሊያድኑ ከሚያምኑቱ ነን እንጂ ወደ ጥፋት ከሚያፈገፍጉ አይደለንም።

፲፩

፩ እምነትም ተሰፋ ሰለምናደርገው ነገር የሚያሰረግጥ፥ የማናየውንም ነገር የሚያሰረዳ ነው።
፪ ለሽማግሌዎች የተመሰከረላቸው በዚህ ነውና።
፫ ዓለሞች በእግዚአብሔር ቃል እንደ ተዘጋጁ፥ ሰለዚህም የሚታየው ነገር ከሚታዩት እንዳልሆነ በእምነት እናሰተውላለን።
፬ አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ፥ በዚህም፥ እግዚአብሔር ሰለ ሰጦታው ሲመሰክር፥ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ተመሰከረለት፤ ሞቶም ሳለ በመሥዋዕቱ እስከ አሁን ይናገራል።
፭ ሄኖክ ሞትን እንዳያይ በእምነት ተወሰደ፥ እግዚአብሔርም ሰለ ወሰደው አልተገኘም። ሳይወሰድ እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመሰክሮለታልና፤
፮ ያለ እምነትም ደስ ማሰኘት አይቻልም፤ ወደ እግዚአብሔር የሚደርስ እግዚአብሔር እንዳለ ለሚፈልጉትም ዋጋ እንዲሰጥ ያምን ዘንድ ያሰፈልገዋልና።
፯ ኖኅ ገና ሰለማይታየው ነገር ተረድቶ እግዚአብሔርን እየፈራ ቤተ ሰዎቹን ለማዳን መርከብን በእምነት አዘጋጀ፥ በዚህም ዓለምን ኰነነ፥ በእምነትም የሚገኘውን ጽድቅ ወራሽ ሆነ።
፰ አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ሰፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፥ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ።
፱ ለእንግዶች እንደሚሆን በተሰፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ፥ ያን የተሰፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይሰሐቅና ከያዕቆብ ጋር፥ እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፤
፲ መሠረት ያላትን፥ እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና።
፲፩ ተሰፋ የሰጠው የታመነ እንደ ሆነ ሰለ ቈጠረች፥ ሣራ ራሰዋ ደግሞ ዕድሜዋ እንኳ ካለፈ በኋላ ዘርን ለመፅነስ ኃይልን በእምነት አገኘች።
፲፪ ሰለዚህ ደግሞ በብዛታቸው እንደ ሰማይ ኮከብ እንደማይቈጠርም በባሕር ዳር እንዳለ አሸዋ የነበሩት የሞተን ሰው እንኳ ከመሰለው ከአንዱ ተወለዱ።
፲፫ እነዚህ ሁሉ አምነው ሞቱ፥ የተሰጣቸውን የተሰፋ ቃል አላገኙምና፤ ዳሩ ግን ከሩቅ ሆነው አዩትና ተሳለሙት፥ በምድሪቱም እንግዶችና መጻተኞች እንዲሆኑ ታመኑ።
፲፬ እንዲህ የሚሉት ለእነርሱ የሚሆነውን አገር እንዲፈልጉ ያመለክታሉና።
፲፭ ያን የወጡበትን አገር አሰበው ቢሆኑ፥ ሊመለሱ ጊዜ በሆነላቸው ነበር፤

፲፭ አሁን ግን የሚበልጠውን እርሱም ሰማያዊ
አገር ይናፍቃሉ። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላካቸው
ተብሎ ሊጠራ በእነርሱ አያፍርም፥ ከተማን
አዘጋጅቶላቸዋልና።
፲፮-፲፱ እግዚአብሔር ከሙታን እንኳ ሊያስነሣው
እንዲቻለው አሰቦአልና፥ ከዚያም ደግሞ በምሳሌ
አገኘው።
፳ ይሰሐቅ ሊመጣ ስላለው ነገር ያዕቆብንና ዔሳውን
በእምነት ባረካቸው።
፳፩ ያዕቆብ ሲሞት በእምነት የዮሴፍን ልጆች
እያንዳንዳቸው ባረካቸው፥ በዘንጉም ጫፍ ተጠግቶ
ሰገደ።
፳፪ ዮሴፍ ወደ ሞት ቀርቦ ሳለ በእምነት ስለ
እስራኤል ልጆች መውጣት አስታወሰ፥ ስለ አጥንቱም
አዘዛቸው።
፳፫ ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን
መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት
የንጉሥንም አዋጅ አልፈሩም።
፳፬ ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ እንዳይባል
በእምነት እምቢ አለ፤
፳፭-፳፯ የንጉሡን ቊጣ ሳይፈራ የግብፅን አገር የተወ
በእምነት ነበር፤ የማይታየውን እንደሚያየው አድርጎ
ጸንቶአልና።
፳፰ አጥፊው የበኩሮችን ልጆች እንዳይነካ ፋሲካንና
ደምን መርጨትን በእምነት አደረገ።
፳፱ በደረቅ ምድር እንደሚያልፉ በኤርትራ ባሕር
በእምነት ተሻገሩ፥ የግብፅ ሰዎች ግን ሲሞክሩ ተዋጡ።
፴ የኢያሪኮ ቅጥር ሰባት ቀን ከዞሩበት በኋላ
በእምነት ወደቀ።
፴፩ ጋለሞታይቱ ረዓብ ሰላዮችን በሰላም
ስለ ተቀበለቻቸው ከማይታዘዙ ጋር በእምነት
አልጠፋችም።
፴፪ እንግዲህ ምን እላለሁ? ስለ ጌዴዎንና ስለ
ባርቅ ስለ ሶምሶንም ስለ ዮፍታሔም ስለ ዳዊትና
ስለ ሳሙኤልም ስለ ነቢያትም እንዳልተርክ ጊዜ
ያጥርብኛልና።
፴፫ እነርሱ በእምነት መንግሥታትን ድል ነሡ፥
ጽድቅን አደረጉ፥ የተሰጠውን የተሰፋ ቃል አገኙ፥
፴፬ የአንበሶችን እፍ ዘጉ፥ የእሳትን ኃይል አጠፉ፥
ከሰይፍ ስለት አመለጡ፥ ከድካማቸው በረቱ፥
በጦርነት ኃይለኞች ሆኑ፥ የባዕድ ጭፍሮችን አባረሩ።
፴፭ ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ፤
ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ
እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤
፴፮ ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም
በላይ በእሰራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤
፴፯ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ
ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ
መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ
ለብሰው ዞሩ፤
፴፰-፴፱ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና
በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ።

፲፪

፩-፫ በነፍሳችሁ ዝላችሁ እንዳትደክሙ፥
ከኃጢአተኞች በደረሰበት እንዲህ ባለ መቃወም
የጸናውን አስቡ።
፬ ከኃጢአት ጋር እየተጋደላችሁ ገና ደምን እስከ
ማፍሰስ ድረስ አልተቃወማችሁም፤
፭-፯ ለመቀጣት ታገሡ፤ እግዚአብሔር እንደ ልጆች
ያደርግላችኋልና፤ አባቱ የማይቀጣው ልጅ ማን ነው?
፰ ነገር ግን ሁሉ የቅጣት ተካፋይ ሆኖአልና
ያለ ቅጣት ብትኖሩ ዲቃላዎች እንጂ ልጆች
አይደላችሁም።
፱ ከዚህም በላይ የቀጡን የሥጋችን አባቶች ነበሩን
እናፍራቸውም ነበር፤ እንዴትስ ይልቅ ለመናፍስት አባት
አብልጠን ልንገዛና በሕይወት ልንኖር በተገባን?
፲ እነርሱ መልካም ሆኖ እንደ ታያቸው ለጥቂት ቀን
ይቀጡን ነበርና፥ እርሱ ግን ከቅድስናው እንድንካፈል
ለጥቅማችን ይቀጣናል።
፲፩ ቅጣት ሁሉ ለጊዜው የሚያሳዝን እንጂ ደስ
የሚያሰኝ አይመስልም፥ ዳሩ ግን በኋላ ለለመዱት
የሰላምን ፍሬ እርሱም ጽድቅን ያፈራላቸዋል።
፲፪ ስለዚህ የላሉትን እጆች የሰለሉትንም ጉልበቶች
አቅኑ፤
፲፫ ያነከሰውም እንዲፈወስ እንጂ እንዳይናጋ፥
ለእግራችሁ ቅን መንገድ አድርጉ።
፲፬ ከሰው ሁሉ ጋር ሰላምን ተከታተሉ ትቀደሱም
ዘንድ ፈልጉ፥ ያለ እርሱ ጌታን ሊያይ የሚችል የለምና።
፲፭ የእግዚአብሔር ጸጋ ለማንም እንዳይጎድለው፥
ብዙዎቹም የሚረክሱበት አንድ መራራ ሥር ወደ ላይ
በቅሎ እንዳያሰጨንቅ፥ ሴሰኛም የሚሆን እንዳይገኝ፥
፲፮ ወይም ስለ አንድ መብል በኩርነቱን እንደ ሸጠ
እንደ ዔሳው ለዚህ ዓለም የሚመች ሰው እንዳይሆን
ተጠንቀቁ።
፲፯ ከዚያ በኋላ እንኳ በረከቱን ሊወርስ በወደደ
ጊዜ እንደ ተጣለ ታውቃላችሁና፤ በእንባ ተግቶ ምንም
ቢፈልገው ለንስሐ ሰፍራ አላገኘምና።
፲፰ ሊዳሰስ ወደሚችል ወደሚቃጠልም እሳት ወደ
ጭጋግም ወደ ጨለማም ወደ ዐውሎ ነፋስም
ወደ መለከት ድምፅም ወደ ቃሎችም ነገር
አልደረሳችሁምና፤
፲፱ ያንም ነገር የሰሙት ሌላ ቃል
እንዳይጨመርባቸው ለመኑ፤
፳ እንስሳ እንኳ ተራራውን ቢነካ ተወግሮ ይሙት
የምትለውን ትእዛዝ ሊታገሡ አልቻሉምና፤
፳፩ ሙሴም። እጅግ እፈራለሁ እንቀጠቀጥማለሁ
እስኪል ድረስ የሚታየው እጅግ የሚያሰፈራ ነበር፤
፳፪ ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው
እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም
ኢየሩሳሌም፥ በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ እእላፋት
መላእክት፥
፳፫ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኩራት
ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥
ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥
፳፬ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደሚሆን
ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን
ወደሚናገር ወደ መርጨት ደም ደርሳችኋል።
፳፭ ለሚናገረው እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፤ እነዚያ
በምድር ላስረዳቸው እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፥
ከሰማይ ከመጣው ፈቀቅ የምንል እኛስ እንዴት
እናመልጣለን?

፳፮ በዚያም ጊዜ ድምፁ ምድርን አናወጠ፥ አሁን ግን። እንድ ጊዜ ደግሜ እኔ ሰማይን እናውጣለሁ እንጂ ምድርን ብቻ አይደለም ብሎ ተስፋ ሰጥቶአል።
፳፯ ዳሩ ግን። እንድ ጊዜ ደግሜ የሚል ቃል፥ የማይናወጡት ጸንተው እንዲኖሩ፥ የሚናወጡት የተፈጠሩ እንደሚሆኑ ይለወጡ ዘንድ ያሳያል።
፳፰ ስለዚህ የማይናወጥን መንግሥት ስለምንቀበል በማክበርና በፍርሃት እግዚአብሔርን ደስ እያሰኘን የምናመልክበትን ጸጋ እንያዝ፤
፳፱ አምላካችን በእውነት የሚያጠፋ እሳት ነውና።

፲፫

፩-፫ ከእነርሱ ጋር እንደ ታሰረ ሆናችሁ እስሮችን አስቡ፥ የተጨነቁትንም ራሳችሁ ደግሞ በሥጋ እንዳለ ሆናችሁ አስቡ።
፬ መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹሕ ይሁን፤ ሴሰኞችንና አመንዝሮችን ግን እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል።
፭ እካሄዳችሁ ገንዘብን ያለ መውደድ ይሁን፥ ያላችሁም ይብቃችሁ፤ እርሱ ራሱ። አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤
፮ ስለዚህ በድፍረት። ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል? እንላለን።
፯ የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው።
፰ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንትና ዛሬ እስከ ለዘላለምም ያው ነው።
፱ ልዩ ልዩ ዓይነት በሆነ በእንግዳ ትምህርት እትወሰዱ፤ ልባችሁ በጸጋ ቢጸና መልካም ነው እንጂ በመብል አይደለም፤ በዚህ የሚሠሩባት አልተጠቀሙምና።
፲ መሠዊያ አለን፥ ከእርሱም ሊበሉ ድንኳኒቱን የሚያገለግሉ መብት የላቸውም።
፲፩ ሊቀ ካህናት ስለ ኃጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም ያቀርባልና፤ ሥጋቸው ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል።
፲፪ ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።
፲፫ እንግዲህ ነቀፌታውን እየተሸከምን ወደ እርሱ ወደ ሰፈሩ ውጭ እንውጣ፤
፲፬ በዚህ የምትኖር ከተማ የለችንምና፥ ነገር ግን ትመጣ ዘንድ ያላትን እንፈልጋለን።
፲፭ እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት።
፲፮ ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።
፲፯ ለዋኖቻችሁ ታዘዙና ተገዙ፤ እነርሱ ስሌትን እንደሚሰጡ አድርገው፥ ይህንኑ በደስታ እንጂ በኃዘን እንዳያደርጉት፥ ይህ የማይጠቅማችሁ ነበርና፥ ስለ ነፍሳችሁ ይተጋሉ።
፲፰ ጸልዩልን፤ በነገር ሁሉ በመልካም እንድንኖር ወደን፥ መልካም ሕሊና እንዳለን ተረድተናልና።
፲፱ ይልቁንም ፈጥኜ እንድመለስላችሁ ይህን ታደርጉ ዘንድ እጥብቄ እለምናችኋለሁ።
፳ በዘላለም ኪዳን ደም ለበጎች ትልቅ እረኛ የሆነውን ጌታችንን ኢየሱስን ከሙታን ያወጣው የሰላም አምላክ፥
፳፩ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን በእናንተ እያደረገ፥ ፈቃዱን ታደርጉ ዘንድ በመልካም ሥራ ሁሉ ፍጹማን ያድርጋችሁ፤ ለእርሱ እስከ ዘላለም ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።
፳፪ ወንድሞች ሆይ፥ የምክርን ቃል እንድትታገሡ እመክራችኋለሁ፥ በጥቂት ቃል ጽፌላችኋለሁና።
፳፫ ወንድማችን ጢሞቴዎስ እንደ ተፈታ እወቁ፥ ቶሎ ብሎም ቢመጣ ከእርሱ ጋር እያችኋለሁ።
፳፬ ለዋኖቻችሁ ሁሉና ለቅዱሳን ሁሉ ሰላምታ አቅርቡልኝ። ከኢጣልያ የሆኑቱ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፳፭ ጸጋ ከሁላችሁ ጋር ይሁን፤ አሜን።

የያዕቆብ መልእክት

፩ የእግዚአብሔርና የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ ያዕቆብ ለተበተኑ ለአሥራ ሁለቱ ወገኖች፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን።
፪-፬ ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።
፭ ከእናንተ ግን ማንም ጥበብ ቢጎድለው፥ ሳይነቅፍ በልግስና ለሁሉ የሚሰጠውን እግዚአብሔርን ይለምን፥ ለእርሱም ይሰጠዋል።
፮ ነገር ግን በምንም ሳይጠራጠር በእምነት ይለምን፤ የሚጠራጠር ሰው በነፋስ የተገፋና የተነቃነቀ የባሕርን ማዕበል ይመስላልና።
፯-፲፩ ፀሐይ ከትኩሳት ጋር ይወጣልና፥ ሣርንም ያጠወልጋልና፥ አበባውም ይረግፋልና፥ የመልኩም ውበት ይጠፋልና፤ እንዲሁ ደግሞ ባለ ጠጋው በመንገዱ ይዝላል።
፲፪ በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ሰለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና።
፲፫ ማንም ሲፈተን። በእግዚአብሔር እፈተናለሁ አይበል፤ እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንምና፤ እርሱ ራሱስ ማንንም አይፈትንም።
፲፬ ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል።
፲፭ ከዚህ በኋላ ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች።
፲፮ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ አትሳቱ።
፲፯ በጎ ስጦታ ሁሉ ፍጹምም በረከት ሁሉ ከላይ ናቸው፥ መለወጥም በእርሱ ዘንድ ከሌለ በመዞርም የተደረገ ጥላ በእርሱ ዘንድ ከሌለ ከብርሃናት አባት ይወርዳሉ።
፲፰ ለፍጥረቱ የበኩራት ዓይነት እንድንሆን በእውነት ቃል አስቦ ወለደን።
፲፱ ስለዚህ፥ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ሰው ሁሉ ለመስማት የፈጠነ ለመናገርም የዘገየ ለቍጣም የዘገየ ይሁን፤
፳ የሰው ቍጣ የእግዚአብሔርን ጽድቅ አይሠራምና።
፳፩ ስለዚህ ርኩሰትን ሁሉ የክፋትንም ትርፍ አስወግዳችሁ፥ ነፍሳችሁን ማዳን የሚችለውን በውስጣችሁም የተተከለውን ቃል በየዋህነት ተቀበሉ።
፳፪ ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ።
፳፫ ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይመስላል፤
፳፬ ራሱን አይቶ ይሄዳልና፥ ወዲያውም እንደ ምን እንደ ሆነ ይረሳል።
፳፭ ነገር ግን ነጻ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፥ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው፥ በሥራው የተባረከ ይሆናል።
፳፮ አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው።
፳፯ ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው።

፪

፩ ወንድሞቼ ሆይ፥ በክብር ጌታ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ያለውን እምነት ለሰው ፊት በማድላት አትያዙ።
፪ የወርቅ ቀለበት ያደረገና የጌጥ ልብስ የለበሰ ሰው ወደ ጉባኤአችሁ ቢገባ፥ እድፍ ልብስም የለበሰ ድህ ሰው ደግሞ ቢገባ፥
፫ የጌጥ ልብስም የለበሰውን ተመልክታችሁ። እንተሰ በዚህ በመልካም ሰፍራ ተቀመጥ ብትሉት፥ ድህውንም። እንተሰ ወደዚያ ቁም ወይም ከእግሬ መረገጫ በታች ተቀመጥ ብትሉት፥ ራሳችሁን መለያየታችሁ አይደለምን?
፬ ክፉ አሳብ ያላቸውም ዳኞች መሆናችሁ አይደለምን?
፭ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፥ ስሙ፤ እግዚአብሔር በእምነት ባለ ጠጎች እንዲሆኑ ለሚወዱትም ተስፋ ሰለ እርሱ የሰጣቸውን መንግሥት እንዲወርሱ የዚህን ዓለም ድሆች አልመረጠምን?
፮ እናንተ ግን ድሆችን አዋረዳችሁ። ባለ ጠጎቹ የሚያስጨንቁአችሁ አይደሉምን? ወደ ፍርድ ቤትም የሚጎትቱአችሁ እነርሱ አይደሉምን?
፯ የተጠራችሁበትን መልካሙን ስም የሚሰድቡ እነርሱ አይደሉምን?
፰ ነገር ግን መጽሐፍ። ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድ እንደሚል የንጉሥን ሕግ ብትፈጽሙ መልካም ታደርጋላችሁ፤
፱ ለሰው ፊት ግን ብታደሉ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፥ ሕግም እንደ ተላላፊዎች ይወቅሳችኋል።
፲ ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ፥ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል፤ አታመንዝር ያለው ደግሞ። አትግደል ብሎአልና፤
፲፩ ባታመነዝርም፥ ነገር ግን ብትገድል፥ ሕግን ተላላፊ ሆነሃል።
፲፪ በነጻነት ሕግ ፍርድን ይቀበሉ ዘንድ እንዳላቸው ሰዎች እንዲህ ተናገሩ፥ እንዲህም አድርጉ።
፲፫ ምሕረትን ለማያደርግ ምሕረት የሌለበት ፍርድ ይሆናልና፤ ምሕረትም በፍርድ ላይ ይመካል።
፲፬ ወንድሞቼ ሆይ፥ እምነት አለኝ የሚል፥ ሥራ ግን የሌለው ሰው ቢኖር ምን ይጠቅመዋል? እምነቱስ ሊያድነው ይችላልን?
፲፭ ወንድም ወይም እኅት ራቁታቸውን ቢሆኑ የዕለት ምግብንም ቢያጡ፥
፲፮ ከእናንተ እንዱም። በደኅና ሂዱ፥ እሳት ሙቁ፥ ጥገቡም ቢላቸው ለሰውነት ግን የሚያስፈልጉትን ባትሰጡአቸው ምን ይጠቅማቸዋል?
፲፯ እንደዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው።
፲፰ ነገር ግን አንድ ሰው። አንተ እምነት አለህ እኔም ሥራ አለኝ፤ እምነትህን ከሥራህ ለይተህ አሳየኝ፥ እኔም እምነቴን በሥራዬ አሳይሃለሁ ይላል።

፲፱ እግዚአብሔር አንድ እንደ ሆነ አንተ ታምናለህ፤ መልካም ታደርጋለህ፤ አጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል።
፳ አንተ ከንቱ ሰው፥ እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህን?
፳፩ አባታችን አብርሃም ልጁን ይስሐቅን በመሠዊያው ባቀረበ ጊዜ በሥራ የጸደቀ አልነበረምን?
፳፪ እምነት ከሥራው ጋር አብሮ ያደርግ እንደ ነበረ፥ በሥራም እምነት እንደ ተፈጸመ ትመለከታለህን?
፳፫ መጽሐፍም። አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቈጠረለት ያለው ተፈጸመ፤ የእግዚአብሔርም ወዳጅ ተባለ።
፳፬ ሰው በእምነት ብቻ ሳይሆን በሥራ እንዲጸድቅ ታያላችሁ።
፳፭ እንደዚሁም ጋለሞታይቱ ረዓብ ደግሞ መልእክተኞቹን ተቀብላ በሌላ መንገድ በሰደደቻቸው ጊዜ በሥራ አልጸደቀችምን?
፳፮ ከነፍስ የተለየ ሥጋ የሞተ እንደ ሆነ እንዲሁ ደግሞ ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።

፫

፩ ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ብዙዎቹ አስተማሪዎች አይሁኑ፥ የባሰውን ፍርድ እንድንቀበል ታውቃላችሁና።
፪ ሁላችን በብዙ ነገር እንሰናከላለንና፤ በቃል የማይሰናከል ማንም ቢኖር እርሱ ሥጋውን ሁሉ ደግሞ ለጋታ የሚችል ፍጹም ሰው ነው።
፫ እነሆ፥ ፈረሶች ይታዘዙልን ዘንድ ልጓም በአፋቸው ውስጥ እናገባለን፥ ሥጋቸውንም ሁሉ እንመራለን።
፬ እነሆ፥ መርከቦች ደግሞ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆኑ በዐውሎ ነፋስም ቢነዱ፥ የመሪ ፈቃድ ወደሚወደው ሰፍራ እጅግ ታናሽ በሆነ መቅዘፊያ ይመራሉ።
፭ እንዲሁም አንደበት ደግሞ ትንሽ ብልት ሆኖ በታላላቅ ነገር ይመካል። እነሆ፥ ትንሽ እሳት እንዴት ያለ ትልቅ ጫካ ያቃጥላል።
፮ አንደበትም እሳት ነው። አንደበት በብልቶቻችን መካከል ዓመፀኛ ዓለም ሆኖአል፤ ሥጋን ሁሉ ያሳድፋልና፥ የፍጥረትንም ሩጫ ያቃጥላል፥ በገሃነምም ይቃጠላል።
፯ የአራዊትና የወፎች የተንቀሳቃሾችና በባሕር ያለ የፍጥረት ወገን ሁሉ በሰው ይገራል፥ ደግሞ ተገርቶአል፤
፰ ነገር ግን አንደበትን ሊገራ ማንም ሰው አይችልም፤ የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው።
፱ በእርሱ ጌታንና አብን እንባርካለን፤ በእርሱም እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠሩትን ሰዎች እንረግማለን፤
፲ ከአንድ አፍ በረከትና መርገም ይወጣሉ። ወንድሞቼ ሆይ፥ ይህ እንዲህ ሊሆን አይገባም።
፲፩ ምንጭስ ከአንድ አፍ የሚጣፍጥንና የሚመርን ውኃ ያመነጫልን?
፲፪ ወንድሞቼ ሆይ፥ በለስ ወይራን ወይስ ወይን በለስን ልታፈራ ትችላለችን? ከጨው ውኃም ጣፋጭ ውኃ አይወጣም።
፲፫ ከእናንተ ጥበበኛና አስተዋይ ማን ነው? በመልካም አነዋወሩ ሰራውን በጥበብ የዋህነት ያሳይ።
፲፬ ነገር ግን መራራ ቅንዓትና አድመኛነት በልባችሁ ቢኖርባችሁ፥ አትመኩ በእውነትም ላይ አትዋሹ።
፲፭ ይህ ጥበብ ከላይ የሚወርድ አይደለም፤ ነገር ግን የምድር ነው፥ የሥጋም ነው፥ የአጋንንትም ነው፤
፲፮ ቅንዓትና አድመኛነት ባሉበት ሰፍራ በዚያ ሁከትና ክፉ ሰራ ሁሉ አሉና።
፲፯ ላይኛይቱ ጥበብ ግን በመጀመሪያ ንጽሕት ናት፥ በኋላም ታራቂ፥ ገር፥ እሺ ባይ ምሕረትና በጎ ፍሬ የሞላባት፥ ጥርጥርና ግብዝነት የሌለባት ናት።
፲፰ የጽድቅም ፍሬ ሰላምን ለሚያደርጉት ሰዎች በሰላም ይዘራል።

፬

፩ በእናንተ ዘንድ ጦርና ጠብ ከወዴት ይመጣሉ? በብልቶቻችሁ ውስጥ ከሚዋጉ ከእነዚህ ከምኞቶቻችሁ አይደሉምን?
፪ ትመኛላችሁ ለእናንተም አይሆንም፤ ትገድላላችሁ በብርቱም ትፈልጋላችሁ፥ ልታገኙም አትችሉም፤ ትጣላላችሁ ትዋጉማላችሁ ነገር ግን አትለምኑምና ለእናንተ አይሆንም፤
፫ ትለምናላችሁ፥ በምኞቶቻችሁም ትከፍሉ ዘንድ በክፉ ትለምናላችሁና አትቀበሉም።
፬ አመንዝሮች ሆይ፥ ዓለምን መውደድ ለእግዚአብሔር ጥል እንዲሆን አታውቁምን? እንግዲህ የዓለም ወዳጅ ሊሆን የሚፈቅድ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል።
፭ ወይስ መጽሐፍ። በእኛ ዘንድ ያሳደረው መንፈስ በቅንዓት ይመኛል ያለው በከንቱ እንደ ተናገረ ይመስላችኋልን?
፮ ነገር ግን ጸጋን አብልጦ ይሰጣል፤ ስለዚህ። እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማል፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል ይላል።
፯ እንግዲህ ለእግዚአብሔር ተገዙ፤ ዲያብሎስን ግን ተቃወሙ ከእናንተም ይሸሻል፤
፰ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ወደ እናንተም ይቀርባል። እናንተ ኃጢአተኞች፥ እጆቻችሁን አንጹ፤ ሁለት አሳብም ያላችሁ እናንተ፥ ልባችሁን አጥሩ።
፱ ተጨነቁና እዘኑ አልቅሱም፤ ሳቃችሁ ወደ ኀዘን ደስታችሁም ወደ ትካዜ ይለወጥ።
፲ በጌታ ፊት ራሳችሁን አዋርዱ ከፍ ከፍም ያደርጋችኋል።
፲፩ ወንድሞች ሆይ፥ እርስ በርሳችሁ አትተማሙ። ወንድሙን የሚያማ በወንድሙም የሚፈርድ ሕግን ያማል በሕግም ይፈርዳል፤ በሕግም ብትፈርድ ፈራጅ ነህ እንጂ ሕግን አድራጊ አይደለህም።
፲፪ ሕግን የሚሰጥና የሚፈርድ አንድ ነው፤ እርሱም ሊያድን ሊያጠፋም የሚችል ነው፤ በሌላው ግን የምትፈርድ አንተ ማን ነህ?
፲፫ አሁንም። ዛሬ ወይም ነገ ወደዚህ ከተማ እንሄዳለን በዚያም ዓመት እንኖራለን እንነግድማለን እናተርፍማለን የምትሉ እናንተ፥ ተመልከቱ፥ ነገ የሚሆነውን አታውቁምና።
፲፬ ሕይወታችሁ ምንድር ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፍዋለት ናችሁና።
፲፭ በዚህ ፈንታ። ጌታ ቢፈቅድ ብንኖርም ይህን ወይም ያን እናደርጋለን ማለት ይገባችኋል።
፲፮ አሁን ግን በትዕቢታችሁ ትመካላችሁ፤ እንደዚህ ያለ ትምክህት ሁሉ ክፉ ነው።

፲፯ እንግዲህ በጎ ለማድረግ አውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።

፭

፩ አሁንም እናንተ ባለ ጠጎች፥ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ።
፪ ሀብታችሁ ተበላሽቶአል፥ ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል።
፫ ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፥ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል። ለኋለኛው ቀን መዝገብን አከማችታችኋል።
፬ እነሆ፥ እርሻችሁን ያጨዱት የሠራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፥ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባኦት ጆሮ ገብቶአል።
፭ በምድር ላይ ተቀማጥላችኋል በሴሰኝነትም ኖራችኋል፤ ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል።
፮ ጻድቁን ኰንናችሁታል ገድላችሁትማል፤ እናንተን አይቃወምም።
፯ እንግዲህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ታገሡ። እነሆ፥ ገበሬው የፊተኛውንና የኋለኛውን ዝናብ እስኪቀበል ድረስ እርሱን እየታገሠ የከበረውን የመሬት ፍሬ ይጠብቃል።
፰ እናንተ ደግሞ ታገሡ፥ ልባችሁንም አጽኑ፤ የጌታ መምጣት ቀርቦአልና።
፱ ወንድሞች ሆይ፥ እንዳይፈረድባችሁ እርስ በርሳችሁ አታጕረምርሙ፤ እነሆ፥ ፈራጅ በደጅ ፊት ቆሞአል።
፲ ወንድሞች ሆይ፥ የመከራና የትዕግሥት ምሳሌ የሆኑትን በጌታ ስም የተናገሩትን ነቢያትን ተመልከቱ።
፲፩ እነሆ፥ በትዕግሥት የጸኑትን ብፁዓን እንላቸዋለን፤ ኢዮብ እንደ ታገሠ ሰምታችኋል፥ ጌታም እንደ ፈጸመለት አይታችኋል፤ ጌታ እጅግ የሚምር የሚራራም ነውና።
፲፪ ከሁሉም በፊት፥ ወንድሞቼ ሆይ፥ በሰማይ ቢሆን በምድርም ቢሆን በሌላ መሐላም ቢሆን በምንም አትማሉ፤ ነገር ግን ከፍርድ በታች እንዳትወድቁ ነገራችሁ አዎን ቢሆን አዎን ይሁን፥ አይደለምም ቢሆን አይደለም ይሁን።
፲፫ ከእናንተ መከራን የሚቀበል ማንም ቢኖር እርሱ ይጸልይ፤ ደስ የሚለውም ማንም ቢኖር እርሱ ይዘምር።
፲፬ ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ሽምግሌዎች ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት።
፲፭ የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ያስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደ ሆነ ይሰረይለታል።
፲፮ እርስ በርሳችሁ በኃጢአታችሁ ተናዘዙ። ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች።
፲፯ ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ፥ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፥ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፥
፲፰ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች።
፲፱ ወንድሞቼ ሆይ፥ ከእናንተ ማንም ከእውነት ቢሰት አንዱም ቢመልሰው፥
፳ ኃጢአተኛን ከተሳሳተበት መንገድ የሚመልሰው ነፍሱን ከሞት እንዲያድን፥ የኃጢአትንም ብዛት እንዲሸፍን ይወቅ።

1ኛ የጴጥሮስ መልእክት

፩-፲ ለእናንተም ስለሚሰጠው ጸጋ ትንቢት የተናገሩት ነቢያት ሰለዚህ መዳን ተግተው እየፈለጉ መረመሩት፤
፲፩ በእነርሱም የነበረ የክርስቶስ መንፈስ፥ ሰለ ክርስቶስ መከራ ከእርሱም በኋላ ስለሚመጣው ክብር አሰቀድሞ እየመሰከረ፥ በምን ወይም እንዴት ባለ ዘመን እንዳመለከተ ይመረምሩ ነበር።
፲፪ ለእነርሱም ከሰማይ በተላከ በመንፈስ ቅዱስ ወንጌልን የሰበኩላችሁ ሰዎች አሁን ባወሩላችሁ ነገር እናንተን እንጂ ራሳቸውን እንዳላገለገሉ ተገለጠላቸው፤ ይህንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ።
፲፫ ሰለዚህ የልቡናችሁን ወገብ ታጥቃችሁና በመጠን ኖራችሁ፥ ኢያሱስ ክርስቶስ ሲገለጥ የምታገኙትን ጸጋ ፈጽማችሁ ተሰፋ አድርጉ።
፲፬ እንደሚታዘዙ ልጆች ባለማወቃችሁ አሰቀድሞ የኖራችሁበትን ምኞት አትከተሉ።
፲፭-፲፯ ለሰው ፊትም ሳያደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደ ሥራው የሚፈርደውን አባት ብላችሁ ብትጠሩ በእግዳድነታችሁ ዘመን በፍርሃት ኑሩ።
፲፰-፳፪ ለእውነት እየታዘዛችሁ ግብዝነት ለሌለበት ለወንድማማች መዋደደ ነፍሳችሁን አንጽታችሁ እርስ በርሳችሁ ከልባችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ።
፳፫ ዳግመኛ የተወለዳችሁት ከሚጠፋ ዘር አይደለም፥ በሕያውና ለዘላለም በሚኖር በእግዚአብሔር ቃል ከማይጠፋ ዘር ነው እንጂ።
፳፬ ሥጋ ሁሉ እንደ ሣር ክብሩም ሁሉ እንደ ሣር አበባ ነውና፤ ሣሩ ይጠወልጋል አበባውም ይረግፋል፤
፳፭ የጌታ ቃል ግን ለዘላለም ይኖራል። በወንጌልም የተሰበከላችሁ ቃል ይህ ነው።

፪

፩ እንግዲህ ክፋትን ሁሉ ተንኰልንም ሁሉ ግብዝነትንም ቅንዓትንም ሐሜትንም ሁሉ አሰወግዳችሁ፥
፪-፬ በሰውም ወደ ተጣለ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ወደ ተመረጠና ክቡር ወደ ሆነው ወደ ሕያው ድንጋይ ወደ እርሱ እየቀረባችሁ፥
፭ እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደሰ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳን ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሠሩ።
፮ በመጽሐፍ። እነሆ፥ የተመረጠና የከበረን የማዕዘን ራስ ድንጋይ በጽዮን እኖራለሁ በእርሱም የሚያምን አያፍርም ተብሎ ተጽፎአልና።
፯ እንግዲህ ክብሩ ለእናንተ ለምታምኑት ነው፤ ለማያምኑ ግን አናጢዎች የጣሉት ድንጋይ እርሱ የማዕዘን ራስ የዕንቅፋትም ድንጋይ የማሰናከያም ዓለት ሆነ፤
፰ የማያምኑ ሰለ ሆኑ በቃሉ ይሰናከሉበታልና፤ ለዚህ ደግሞ የተመደቡ ናቸው።
፱ እናንተ ግን ከጨለማ ወደሚደነቅ ብርሃኑ የጠራችሁን የእርሱን በጎነት እንድትናገሩ የተመረጠ ትውልድ፥ የንጉሥ ካህናት፥ ቅዱስ ሕዝብ፥ ለርስቱ የተለየ ወገን ናችሁ፤
፲ እናንተ ቀድሞ ወገን አልነበራችሁም አሁን ግን የእግዚአብሔር ወገን ናችሁ፤ እናንተ ምሕረት ያገኛችሁ አልነበራችሁም አሁን ግን ምሕረትን አግኝታችኋል።
፲፩ ወዳጆች ሆይ፥ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ እለምናችኋለሁ፤
፲፪ ሰለሚመለከቱት ሰለ መልካም ሥራችሁ፥ ክፉ እንደምታደርጉ በዚያ እናንተን በሚያሙበት ነገር፥ በሚጎበኝበት ቀን እግዚአብሔርን ያከብሩት ዘንድ በአሕዛብ መካከል ኑሮአችሁ መልካም ይሁን።
፲፫ ሰለ ጌታ ብላችሁ ለሰው ሥርዓት ሁሉ ተገዙ፤ ለንጉሥም ቢሆን፥ ከሁሉ በላይ ነውና፤
፲፬ ለመኳንንትም ቢሆን፥ ክፉ የሚያደርጉትን ለመቅጣት በጎም የሚያደርጉትን ለማመሰገን ከእርሱ ተልከዋልና ተገዙ።
፲፭ በጎ እያደረጋችሁ፥ የማያውቁትን ሞኞች ዝም ታሰኙ ዘንድ እንዲህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነውና፤
፲፮ እርነት ወጥታችሁ እንደ እግዚአብሔር ባሪያዎች ሁኑ እንጂ ያ እርነት ለክፋት መሸፈኛ እንዲሆን አታድርጉ።
፲፯ ሁሉን አክብሩ፥ ወንድሞችን ውደዱ፥ እግዚአብሔርን ፍሩ፥ ንጉሥን አክብሩ።
፲፰ ሎሌዎች ሆይ፥ ለበጎዎችና ለገሮች ጌቶቻችሁ ብቻ ሳይሆን ለጠማሞች ደግሞ በፍርሃት ሁሉ ተገዙ።
፲፱ በግፍ መከራን የሚቀበል ሰው እግዚአብሔርን እያሰበ ኃዘንን ቢታገሥ ምሰጋና ይገባዋልና።
፳ ኃጢአት አድርጋችሁ ሰትጎሰሙ ብትታገሡ፥ ምን ክብር አለበት? ነገር ግን መልካም አድርጋችሁ መከራን ሰትቀበሉ ብትታገሡ፥ ይህ ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ ምሰጋና ይገባዋል።
፳፩ የተጠራችሁለት ለዚህ ነውና፤ ክርስቶስ ደግሞ ፍለጋውን እንድትከተሉ ምሳሌ ትቶላችሁ ሰለ እናንተ መከራን ተቀብሎአልና።
፳፪ እርሱም ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤
፳፫ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፤
፳፬ ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ በሥጋው ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ፤*ፍ1*
፳፭ በመገረፉ ቁሰል ተፈወሳችሁ። እንደ በጎች ትቅበዘበዙ ነበርና፥ አሁን ግን ወደ ነፍሳችሁ እረኛና ጠባቂ ተመልሳችኋል።

፫

፩-፮ ለእናንተም ጠጕርን በመሸረብና ወርቅን በማንጠልጠል ወይም ልብስን በመጎናጸፍ በውጭ የሆነ ሽልማት አይሁንላችሁ፥
፬ ነገር ግን በእግዚአብሔር ፊት ዋጋው እጅግ የከበረ የዋህና ዝግተኛ መንፈስ ያለውን የማይጠፋውን ልብስ ለብሶ የተሰወረ የልብ ሰው ይሁንላችሁ።
፭ እንዲህ በቀድሞ ዘመን በእግዚአብሔር ተሰፋ ያደረጉት ቅዱሳት ሴቶች ደግሞ ለባሎቻቸው ሲገዙ ተሸልመው ነበርና፤

፮ እንዲሁም ሣራ ለአብርሃም። ጌታ ብላ
እየጠራችው ታዘዘችለት፤ እናንተም ከሚያሰደነግጥ
ነገር አንዳች እንኳ ሳትፈሩ መልካም ብታደርጉ ልጆችዋ
ናችሁ።
፯ እንዲሁም፥ እናንተ ባሎች ሆይ፥ ደካማ
ፍጥረት ሰለ ሆኑ ከሚሰቶቻችሁ ጋር በማሰተዋል
አብራችሁ ኑሩ፤ ጸሎታችሁ እንዳይከለከል አብረው
ደግሞ የሕይወትን ጸጋ እንደሚወርሱ አድርጋችሁ
አክብሩአቸው።
፰ በመጨረሻው ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ፥ የሌላው
መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ፥ እንደወንድሞች
ተዋደዱ፥ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ፤
፱ ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ሰድብን በሰድብ
ፈንታ አትመልሱ በዚህ ፈንታ ባርኩ እንጂ፥ በረከትን
ልትወርሱ ለዚህ ተጠርታችኋልና።
፲ ሕይወትን ሊወድ መልካሞችንም ቀኖች ሊያይ
የሚፈልግ ሰው፥ መላሱን ከክፉ ከንፈሮቹንም
ተንኰልን ከመናገር ይከልክል፤
፲፩ ከክፉ ፈቀቅ ይበል፥ መልካምንም ያድርግ፥
ሰላምን ይሻ ይከተለውም፤
፲፪ የጌታ ዓይኖች ወደ ጻድቃን ናቸውና፥ ጆሮዎቹም
ለጸሎታቸው ተከፍተዋል፥ የጌታ ፊት ግን ክፉ ነገርን
በሚያደርጉ ላይ ነው።
፲፫ በጎንም ለማድረግ ብትቀኑ የሚያሰጨንቃችሁ
ማን ነው?
፲፬ ነገር ግን ሰለ ጽድቅ እንኳ መከራን
ብትቀበሉ ብፁዓን ናችሁ። ማሰፈራራታቸውንም
አትፍሩ አትናወጡም፥
፲፭ ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርሰቶሰ በልባችሁ
ቀድሱት። በእናንተ ሰላለ ተሰፋ ምክንያትን
ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልሰ ለመሰጠት ዘወትር
የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት
ይሁን።
፲፮ በክርሰቶሰ ያለውን መልካሙን ኑሮአችሁን
የሚሳደቡ ሰዎች ክፉን እንደምታደርጉ በሚያሙበት
ነገር እንዲያፍሩ በጎ ሕሊና ይኑራችሁ።
፲፯ የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲህ ቢሆን፥ ክፉ ሰለ
ማድረግ ሳይሆን በጎ ሰለ ማድረግ መከራን ብትቀበሉ
ይሻላችኋልና።
፲፰ ክርሰቶሰ ደግሞ ወደ እግዚአብሔር
እንዲያቀርበን እርሱ ጻድቅ ሆኖ ሰለ ዓመፀኞች አንድ
ጊዜ በኃጢአት ምክንያት ሞቶአልና፤ በሥጋ ሞተ
በመንፈሰ ግን ሕያው ሆነ፥
፲፱ በእርሱም ደግሞ ሄዶ በወኅኒ ለነበሩ ነፍሳት
ሰበከላቸው፤
፳ ጥቂቶች ማለት ሰምንት ነፍሰ በውኃ የዳኑበት
መርከብ ሲዘጋጅ፥ የእግዚአብሔር ትዕግሥት በኖኅ
ዘመን በቁየ ጊዜ ቀድሞ እልታዘዙም።
፳፩ ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቅት ምሳሌው
ሆኖ አሁን ያድነናል፥ የሰውነትን እድፍ ማሰወገድ
አይደለም፥ ለእግዚአብሔር የበጎ ሕሊና ልመና ነው
እንጂ፥ ይህም በኢየሱሰ ክርሰቶሰ ትንሣኤ ነው፤
፳፪ እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም
ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር
ቀኝ አለ።

፬

፩-፫ የአሕዛብን ፈቃድ ያደረጋችሁበት በመዳራትና
በሥጋ ምኞትም በሰካርም በዘፈንም ያለ ልክም
በመጠጣት ነውርም ባለበት በጣዖት ማምለክ
የተመላለሳችሁበት ያለፈው ዘመን ይበቃልና።
፬ በዚህም ነገር ወደዚያ መዳራት ብዛት ከእነርሱ
ጋር ሰለማትሮጡ እየተሳደቡ ይደነቃሉ፤
፭ ግን እነርሱ በሕያዋንና በሙታን ላይ ሊፈርድ
ለተዘጋጀው መልሰ ይሰጣሉ።
፮ እንደሰዎች በሥጋ እንዲፈረድባቸው በመንፈሰ
ግን እንደ እግዚአብሔር እንዲኖሩ ሰለዚህ ምክንያት
ወንጌል ለሙታን ደግሞ ተሰብኮላቸው ነበርና።
፯ ዳሩ ግን የነገር ሁሉ መጨረሻ ቀርቦአል። እንግዲህ
እንደ ባለ እእምሮ እሰቡ፥
፰ ትጸልዩም ዘንድ በመጠን ኑሩ፤ ፍቅር የኃጢአትን
ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርሰ በርሳችሁ
አጥብቃችሁ ተዋደዱ።
፱ ያለ ማንጐራጐር እርሰ በርሳችሁ እንግድነትን
ተቀባበሉ፤
፲ ልዩ ልዩን የእግዚአብሔርን ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች
እንደ መሆናችሁ፥ እያንዳንዳችሁ የጸጋን ሰጦታ እንደ
ተቀበላችሁ መጠን በዚያው ጸጋ እርሰ በርሳችሁ
አገልግሉ፤
፲፩ ማንም ሰው የሚናገር ቢሆን፥ እንደ እግዚአብሔር
ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢሆን፥ እግዚአብሔር
በሚሰጠኝ ኃይል ነው ብሎ ያገልግል፤ ክብርና ሥልጣን
እስከ ዘላለም ድረሰ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱሰ
ክርሰቶሰ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር
ዘንድ፤ አሜን።
፲፪ ወዳጆች ሆይ፥ በእናንተ መካከል እንደ እሳት
ሊፈትናችሁ ሰለሚሆነው መከራ ድንቅ ነገር እንደ
መጣባችሁ አትደነቁ፤
፲፫ ነገር ግን ክብሩ ሲገለጥ ደግሞ ሐሤት
እያደረጋችሁ ደሰ እንዲላችሁ፥ በክርሰቶሰ መከራ
በምትካፈሉበት ልክ ደሰ ይበላችሁ።
፲፬ ሰለ ክርሰቶሰ ሰም ብትነቀፉ የክብር መንፈሰ
የእግዚአብሔር መንፈሰ በእናንተ ላይ ያርፋልና ብፁዓን
ናችሁ።
፲፭ ከእናንተ ማንም ነፍሰ ገዳይ ወይም ሌባ ወይም
ክፉ አድራጊ እንደሚሆን ወይም በሌሎች ጕዳይ
እንደሚገባ ሆኖ መከራን እይቀበል፤
፲፮ ክርሰቲያን እንደሚሆን ግን መከራን ቢቀበል
ሰለዚህ ሰም እግዚአብሔርን ያመሰግን እንጂ አይፈር።
፲፯ ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ
የሚጀመርበት ጊዜ ደርሶአልና፤ አሰቀድሞም በእኛ
የሚጀመር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ
መጨረሻቸው ምን ይሆን?
፲፰ ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመፀኛውና
ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?
፲፱ ሰለዚህ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ
መከራን የሚቀበሉ፥ መልካምን እያደረጉ ነፍሳቸውን
ለታመነ ፈጣሪ አደራ ይሰጡ።

፭

፩ እንግዲህ እኔ፥ ከእነርሱ ጋር ሸማግሌ የክርሰቶሰም
መከራ ምሰክር ደግሞም ለገለጥ ካለው ክብር

ተካፋይ የሆንሁ፥ በመካከላቸው ያሉትን ሽማግሌዎች እመክራቸዋለሁ፤
፪ በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፥ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጐብኙት፤
፫ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ፤
፬ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ።
፭ እንዲሁም፥ ጐበዞች ሆይ፥ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፥ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና፥ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል።
፮ እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤
፯ እርሱ ስለ እናንተ ያሰባልና የሚያሰጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት።
፰ በመጠን ኑሩ ንቁም፥ ባላጋራችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን ፈልጎ እንደሚያገሣ እንበሳ ይዞራልና፤
፱ በዓለም ያሉት ወንድሞቻችሁ ያን መከራ በሙሉ እንዲቀበሉ እያወቃችሁ በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት።
፲ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ዘላለም ክብሩ የጠራችሁ የጸጋ ሁሉ አምላክ ለጥቂት ጊዜ መከራን ከተቀበላችሁ በኋላ ራሱ ፍጹማን ያደርጋችኋል ያጸናችሁምል ያበረታችሁማል።
፲፩ ለእርሱ ክብርና ኃይል እስከዘላለም ድረስ ይሁን፤ አሜን።
፲፪ እየመከርኋችሁና የምትቆሙባት ጸጋ እውነትኛ የእግዚአብሔር ጸጋ እንድትሆን እየመሰከርሁላችሁ፥ የታመነ ወንድም እንደ ሆነ በቈጠርሁት በሰልዋኖስ እጅ በአጭሩ ጽፌላችኋለሁ።
፲፫ ከእናንተ ጋር ተመርጣ በባቢሎን ያለች ቤተ ክርስቲያን ልጇም ማርቆስ ሰላምታ ያቀርቡላችኋል።
፲፬ በፍቅር አሳሳም እርስ በርሳችሁ ሰላምታ ተሰጣጡ። በክርስቶስ ላላችሁ ለሁላችሁ ሰላም ይሁን። አሜን።

2ኛ የጴጥሮስ መልእክት

፩ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፥ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር
እምነትን ላገኙ፤
፪-፬ ስለ ክፉ ምኞት በዓለም ካለው ጥፋት
አምልጣችሁ ከመለኮት ባሕርይ ተካፋዮች በተሰፋ ቃል
እንድትሆኑ፥ በእነዚያ ክብርና በጎነት የተከበረና እጅግ
ታላቅ የሆነ ተሰፋን ሰጠን።
፭ ስለዚህም ምክንያት ትጋትን ሁሉ እያሳያችሁ
በእምነታችሁ በጎነትን ጨምሩ፥
፮ በበጎነትም እውቀትን፥ በእውቀትም ራስን
መግዛት፥ ራስንም በመግዛት መጽናትን፥ በመጽናትም
እግዚአብሔርን መምሰል፥
፯ እግዚአብሔርንም በመምሰል የወንድማማችን
መዋደድ፥ በወንድማማችም መዋደድ ፍቅርን ጨምሩ።
፰ እነዚህ ነገሮች ለእናንተ ሆነው ቢበዙ፥ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ እውቀት ሥራ ፈቶችና ፍሬ ቢሶች
እንዳትሆኑ ያደርጉአችኋልና፤
፱ እነዚህ ነገሮች የሌሉት ዕውር ነውና፥ በቅርብም
ያለውን ብቻ ያያል፥ የቀደመውንም ኃጢአቱን መንጻት
ረስቶአል።
፲ ስለዚህ፥ ወንድሞች ሆይ፥ መጠራታችሁንና
መመረጣችሁን ታጸኑ ዘንድ ከፊት ይልቅ ትጉ፤
እነዚህን ብታደርጉ ከቶ አትሰናከሉምና።
፲፩ እንዲሁ ወደ ዘላለሙ ወደ ጌታችንና
መድኃኒታችን ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መንግሥት
መግባት በሙላት ይሰጣችኋልና።
፲፪ ስለዚህ እነዚህን ነገሮች ምንም ብታውቁ
በእናንተም ዘንድ ባለ እውነት ምንም ብትጸኑ፥ ስለ
እነዚህ ዘወትር እንዳሳስባችሁ ቸል አልልም።
፲፫ ሁልጊዜም በዚህ ማደሪያ ሳለሁ በማሳሰቤ
ላነቃችሁ የሚገባኝ ይመስለኛል።
፲፬ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ
ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን እውቃለሁና።
፲፭ ከመውጣቴም በኋላ እነዚህን ነገሮች እንድታሰቡ
በየጊዜው ትችሉ ዘንድ እተጋለሁ።
፲፮ የእርሱን ግርማ አይተን እንጂ በብልሃት
የተፈጠረውን ተረት ሳንከተል የጌታችንን የኢየሱስ
ክርስቶስን ኃይልና መምጣት አስታወቅናችሁ።
፲፯ ከገናናው ክብር። በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው
ልጄ ይህ ነው የሚል ያ ድምፅ በመጣለት ጊዜ
ከእግዚአብሔር አብ ክብርንና ምስጋናን ተቀብሎአልና፤
፲፰ እኛም በቅዱሱ ተራራ ከእርሱ ጋር ሳለን ይህን
ድምፅ ከሰማይ ሲወርድ ሰማን።
፲፱ ከእርሱም ይልቅ እጅግ የጸና የትንቢት ቃል አለን፤
ምድርም እስኪጠባ ድረስ የንጋትም ኮከብ በልባችሁ
እስኪወጣ ድረስ፥ ሰው በጨለማ ሰፍራ የሚበራን
መብራት እንደሚጠነቀቅ ይህን ቃል እየጠነቀቃችሁ
መልካም ታደርጋላችሁ።
፳ ይህን በመጀመሪያ እወቁ፤ በመጽሐፍ ያለውን
ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም
አልተፈቀደም፤
፳፩ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ
ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ
ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።

፪

፩ ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ
መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ
ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም
የዋጃቸውን ጌታ እንኳ ክደው የሚፈጥንን ጥፋት
በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፋ ኑፋቄን አሹልከው
ያገባሉ፤
፪ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል
በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል።
፫ ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር
ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ
አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም።
፬ እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት
ሳይራራላቸው ወደ ገሃነም ጥሎ በጨለማ ጉድጓድ
ለፍርድ ሊጠበቁ አሳልፎ ከሰጣቸው፥
፭ ለቀደመውም ዓለም ሳይራራ ከሌሎች ሰባት
ጋር ጽድቅን የሚሰብከውን ኖኅን አድኖ በኃጢአተኞች
ዓለም ላይ የጥፋትን ውኃ ካወረደ፥
፮ ኃጢአትንም ያደርጉ ዘንድ ላሉት ምሳሌ አድርጎ
ከተማዎችን ሰዶምንና ገሞራን አመድ እስኪሆኑ ድረስ
አቃጥሎና ገልብጦ ከፈረደባቸው፥
፯-፲፩ ዳሩ ግን መላእክት በኃይልና በብርታት
ከእነርሱ ይልቅ ምንም ቢበልጡ በጌታ ፊት በእነርሱ
ላይ የሰድብን ፍርድ አያመጡም።
፲፪ እነዚህ ግን ለመጠመድና ለመጥፋት
በፍጥረታቸው እንደ ተወለዱ እእምሮ እንደ ሌላቸው
እንስሶች ሆነው፥ በማያውቁት ነገር እየተሳደቡ
በጥፋታቸው ይጠፋሉ፤
፲፫ የዓመፃቸውን ደመወዝ ይቀበላሉ። በቀን ሲዘፍኑ
እንደ ተድላ ይቆጥሩታል፤ ነውረኞችና ርኩሳን ሆነው
ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣ ይዘፍናሉ፤
፲፬ ምንዝር የሞላባቸው ኃጢአትንም የማይተዉ
ዓይኖች አሉአቸው፤ የማይጸኑትን ነፍሳት ያታልላሉ፤
መመኘትን የለመደ ልብ አላቸው፤ የተረገሙ ናቸው።
፲፭ ቅንን መንገድ ትተው ተሳሳቱ፤ የባሶርን ልጅ
የበለዓምን መንገድ ተከተሉ፤ እርሱ የዓመፃን ደመወዝ
ወደደ፥
፲፮ ነገር ግን ስለ መተላለፉ ተዘለፈ፤ ቃል የሌለው
አህያ በሰው ቃል ተናግሮ የነቢዩን እብድነት አገደ።
፲፯ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው
እነዚህ ውኃ የሌለባቸው ምንጮች በዐውሎ ነፋስም
የተነዱ ደመናዎች ናቸው።
፲፰ ከንቱና ከመጠን ይልቅ ታላቅ የሆነውን
ቃል ይናገራሉና፥ በስሕተትም ከሚኖሩት አሁን
የሚያመልጡትን በሥጋ ሴሰኛ ምኞት ያታልላሉ።
፲፱ ራሳቸው የጥፋት ባሪያዎች ሆነው። አርነት
ትወጣላችሁ እያሉ ተስፋ ይሰጡአቸዋል፤ ሰው
ለተሸነፈበት ለእርሱ ተገዝቶ ባሪያ ነውና።
፳ በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ
እውቀት ከዓለም ርኩሰት ካመለጡ በኋላ ዳግመኛ
በእርሱዋ ተጠላልፈው የተሸነፉ ቢሆኑ፥ ከፊተኛው
ኑሮአቸው ይልቅ የኋለኛው የባሰ ሆኖባቸዋል።

፳፩ እውቀዋት ከተሰጣቸው ከቅድስት ትእዛዝ ከሚመለሱ የጽድቅን መንገድ ባላወቁት በተሻላቸው ነበርና።
፳፪ ውሻ ወደ ትፋቱ ይመለሳል፥ ደግሞ። የታጠበች እርያ በጭቃ ለመንከባለል ትመለሳለች እንደሚባል እውነተኞች ምሳሌዎች ሆኖባቸዋል።

፫

፩-፪ በመጨረሻው ዘመን እንደ ራሳቸው ምኞት የሚመላለሱ ዘባኞች በመዘበት እንዲመጡ ይህን በፊት እወቁ፤
፫ እነርሱም። የመምጣቱ የተሰፋ ቃል ወዴት ነው? አባቶች ከሞቱባት ጊዜ፥ ከፍጥረት መጀመሪያ ይዞ ሁሉ እንዳለ ይኖራልና ይላሉ።
፭ ሰማያት ከጥንት ጀምረው ምድርም በእግዚአብሔር ቃል ከውኃ ተጋጥማ በውኃ መካከል እንደ ነበሩ ወደው እያሰተውሉምና፤
፮ በዚህም ምክንያት ያን ጊዜ የነበረ ዓለም በውኃ ሰጥሞ ጠፋ፤
፯ አሁን ያሉ ሰማያትና ምድር ግን እግዚአብሔርን የማያመልኩት ሰዎች እስከሚጠፉበት እስከ ፍርድ ቀን ድረስ ተጠብቀው በዚያ ቃል ለእሳት ቀርተዋል።
፰ እናንተ ግን ወዳጆች ሆይ፥ በጌታ ዘንድ አንድ ቀን እንደ ሺህ ዓመት፥ ሺህ ዓመትም እንደ አንድ ቀን እንደ ሆነ ይህን አንድ ነገር አትርሱ።
፱ ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ሰለ ተሰፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ሰለ እናንተ ይታገሣል።
፲ የጌታው ቀን ግን እንደ ሌባ ሆኖ ይመጣል፤ በዚያም ቀን ሰማያት በታላቅ ድምፅ ያልፋሉ፥ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኩሳት ይቀልጣል፥ ምድርም በእርሰዋም ላይ የተደረገው ሁሉ ይቃጠላል።
፲፫-፲፫ ነገር ግን ጽድቅ የሚኖርባትን አዲሰ ሰማይና አዲሰ ምድር እንደ ተሰፋ ቃሉ እንጠብቃለን።
፲፬ ሰለዚህ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን እየጠበቃችሁ ያለ ነውርና ያለ ነቀፋ ሆናችሁ በሰላም በእርሱ እንድትገኙ ትጉ፥
፲፭ የጌታችንም ትዕግሥት መዳናችሁ እንደ ሆነ ቍጠሩ። እንዲህም የተወደደው ወንድማችን ጳውሎስ ደግሞ እንደ ተሰጠው ጥበብ መጠን ጻፈላችሁ፥ በመልእክቱም ሁሉ ደግሞ እንደ ነገረ ሰለዚህ ነገር ተናገረ።
፲፮ በእነዚያ ዘንድ ለማሰተዋል የሚያሰቸግር ነገር አለ፥ ያልተማሩትና የማይጸኑትም ሰዎች ሌሎችን መጻሕፍት እንደሚያጣምሙ እነዚህን ደግሞ ለገዛ ጥፋታቸው ያጣምማሉ።
፲፯ እንግዲህ እናንተ፥ ወዳጆች ሆይ፥ ይህን አሰቀድማችሁ ሰለምታውቁ፥ በዓመፀኞቹ ሰሕተት ተሰባችሁ ከራሳችሁ ጽናት እንዳትወድቁ ተጠንቀቁ፤
፲፰ ነገር ግን በጌታችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና እውቀት እደጉ። ለእርሱ አሁንም እስከ ዘላለምም ቀን ድረስ ክብር ይሁን፤ አሜን።

1ኛ የዮሐንስ መልእክት

፩ ስለ ሕይወት ቃል ከመጀመሪያው
የነበረውንና የሰማነውን በዓይኖቻችንም ያየነውን
የተመለከትነውንም እጆቻችንም የዳሰሱትን እናወራለን፤
፪ ሕይወትም ተገለጠ አይተንማል እንመሰክርማለን፥
ከአብ ዘንድ የነበረውንም ለእኛም የተገለጠውን
የዘላለምን ሕይወት እናወራላችኋለን፤
፫ እናንተ ደግሞ ከእኛ ጋር ኅብረት
እንዲኖራችሁ ያየነውንና የሰማነውን ለእናንተ ደግሞ
እናወራላችኋለን። ኅብረታችንም ከአባት ጋር ከልጁም
ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው።
፬ ደስታችሁም እንዲፈጸም ይህን እንጽፍላችኋለን።
፭ ከእርሱም የሰማናት ለእናንተም የምናወራላችሁ
መልእክት። እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም
በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት።
፮ ከእርሱ ጋር ኅብረት አለን ብንል በጨለማም
ብንመላለስ እንዋሻለን እውነትንም አናደርግም፤
፯ ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን
ብንመላለስ ለእያንዳንዳችን ኅብረት አለን፥ የልጁም
የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ከኃጢአት ሁሉ ያነጻናል።
፰ ኃጢአት የለብንም ብንል ራሳችንን እናሰታለን፥
እውነትም በእኛ ውስጥ የለም።
፱ በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን
ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።
፲ ኃጢአትን አላደረግንም ብንል ሐሰተኛ
እናደርገዋለን ቃሉም በእኛ ውስጥ የለም።

፪

፩ ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን
እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ
ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ
ክርስቶስ ነው።
፪ እርሱም የኃጢአታችን ማስተሰሪያ ነው፥
ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ
ሁሉ ኃጢአት እንጂ።
፫ ትእዛዛቱንም ብንጠብቅ በዚህ እንዳወቅነው
እናውቃለን።
፬ አውቄዋለሁ የሚል ትእዛዛቱንም የማይጠብቅ
ውሸተኛ ነው እውነትም በእርሱ ውስጥ የለም።
፭ ቃሉን ግን የሚጠብቅ ሁሉ በእርሱ የእግዚአብሔር
ፍቅር በእውነት ተፈጽሞአል። በእርሱ እንዳለን በዚህ
እናውቃለን፤
፮ በእርሱ እኖራለሁ የሚል እርሱ እንደ ተመላለሰ
ራሱ ደግሞ ሊመላለስ ይገባዋል።
፯ ወንድሞች ሆይ፥ ከመጀመሪያ የነበረቻችሁ
አሮጌ ትእዛዝ እንጂ የምጽፍላችሁ አዲስ ትእዛዝ
አይደለችም፤ አሮጌይቱ ትእዛዝ የሰማችኋት ቃል ናት።
፰ ዳግመኛ አዲስ ትእዛዝን እጽፍላችኋለሁ፥ ይህም
ነገር በእርሱ በእናንተም እውነተኛ ነው፤ ጨለማው
ያልፋልና እውነተኛውም ብርሃን አሁን ይበራል።
፱ በብርሃን አለሁ የሚል ወንድሙንም የሚጠላ
እስከ አሁን በጨለማ አለ።
፲ ወንድሙን የሚወድ በብርሃን ይኖራል
ማሰናከያም የለበትም፤
፲፩ ወንድሙን የሚጠላ ግን በጨለማ አለ፥
በጨለማም ይመላለሳል፥ የሚሄድበትንም አያውቅም፥
ጨለማው ዓይኖቹን አሳውሮታልና።
፲፪ ልጆች ሆይ፥ ኃጢአታችሁ ስለ ስሙ
ተሰርዮላችኋልና እጽፍላችኋለሁ።
፲፫ አባቶች ሆይ፥ ከመጀመሪያ የነበረውን
አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ። ጎበዞች ሆይ፥ ክፉውን
አሸንፋችኋልና እጽፍላችኋለሁ። ልጆች ሆይ፥ አብን
አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ።
፲፬ አባቶች ሆይ፥ ከመጀመሪያ የነበረውን
አውቃችኋልና እጽፍላችኋለሁ። ጐበዞች ሆይ፥
ብርቱዎች ስለ ሆናችሁ የእግዚአብሔርም ቃል
በእናንተ ስለሚኖር ክፉውንም ስለ አሸነፋችሁ
እጽፍላችኋለሁ።
፲፭-፲፮ ዓለሙም ምኞቱም ያልፋሉ፤ የእግዚአብሔርን
ፈቃድ የሚያደርግ ግን ለዘላለም ይኖራል።
፲፰ ልጆች ሆይ፥ መጨረሻው ሰዓት ነው፥
የክርስቶስም ተቃዋሚ ይመጣ ዘንድ እንደ ሰማችሁ
አሁን እንኳ ብዙዎች የክርስቶስ ተቃዋሚዎች
ተነሥተዋል፤ ስለዚህም መጨረሻው ሰዓት እንደ ሆነ
እናውቃለን።
፲፱ ከእኛ ዘንድ ወጡ፥ ዳሩ ግን ከእኛ ወገን
አልነበሩም፤ ከእኛ ወገንስ ቢሆኑ ከእኛ ጋር ጸንተው
በኖሩ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉ ከእኛ ወገን እንዳልሆኑ
ይገለጡ ዘንድ ወጡ።
፳ እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል፥ ሁሉንም
ታውቃላችሁ።
፳፩ እውነትን የምታውቁ ስለ ሆናችሁ፥ ውሸትም
ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን
ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም።
፳፪ ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ
በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ
ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው።
፳፫ ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም፤
በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው።
፳፬ እናንተስ ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ጸንቶ
ይኑር። ከመጀመሪያ የሰማችሁት በእናንተ ቢኖር፥
እናንተ ደግሞ በወልድና በአብ ትኖራላችሁ።
፳፭ እርሱም የሰጠን ተስፋ ይህ የዘላለም ሕይወት
ነው።
፳፮ ስለሚያስቱአችሁ ሰዎች ይህን ጽፌላችኋለሁ።
፳፯ እናንተስ ከእርሱ የተቀበላችሁት ቅባት በእናንተ
ይኖራል፥ ማንም ሊያስተምራችሁ አያሰፈልጋችሁም፤
ነገር ግን የእርሱ ቅባት ስለ ሁሉ እንደሚያስተምራችሁ፥
እውነተኛም እንደ ሆነ ውሸትም እንዳልሆነ፥ እናንተንም
እንዳስተማራችሁ፥ በእርሱ ኑሩ።
፳፰ አሁንም፥ ልጆች ሆይ፥ በሚገለጥበት ጊዜ
እምነት እንዲሆንልን በመምጣቱም በእርሱ ፊት
እንዳናፍር በእርሱ ኑሩ።
፳፱ ጻድቅ እንደ ሆነ ካወቃችሁ ጽድቅን የሚያደርግ
ሁሉ ከእርሱ እንደ ተወለደ እወቁ።

፫

፩ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ

እንዴት ያለውን ፍቅር እንደ ሰጠን እዩ፥ እንዲሁም ነን። ስለዚህ ምክንያት ዓለም እርሱን ስላላወቀው እኛን አያውቀንም።

፪ ወዳጆች ሆይ፥ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን፥ ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥ እርሱ እንዳለ እናየዋለንና እርሱን እንድንመሰል እናውቃለን።

፫ በእርሱም ይህን ተስፋ የሚያደርግ ሁሉ እርሱ ንጹሕ እንደ ሆነ ራሱን ያነጻል።

፬ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ ዓመፅን ደግሞ ያደርጋል፥ ኃጢአትም ዓመፅ ነው።

፭ እርሱም ኃጢአትን ሊያሰወግድ እንደ ተገለጠ ታውቃላችሁ፥ በእርሱም ኃጢአት የለም።

፮ በእርሱ የሚኖር ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፤ ኃጢአትን የሚያደርግ ሁሉ አላየውም አላወቀውምም።

፯ ልጆች ሆይ፥ ማንም አያሰታችሁ፤ እርሱ ጻድቅ እንደ ሆነ ጽድቅን የሚያደርግ ጻድቅ ነው።

፰ ኃጢአትን የሚያደርግ ከዲያብሎስ ነው፥ ዲያብሎስ ከመጀመሪያ ኃጢአትን ያደርጋልና።

፱ ስለዚህ የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ። ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም።

፲ የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።

፲፩ ከመጀመሪያ የሰማችኋት መልእክት። እርስ በርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና፤

፲፪ ከክፉው እንደ ነበረ ወንድሙንም እንደ ገደለ እንደ ቃየል አይደለም፤ ስለ ምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ፥ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለ ነበረ ነው።

፲፫ ወንድሞች ሆይ፥ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ።

፲፬ እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለ ሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገርን እናውቃለን፤ ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል።

፲፭ ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።

፲፮ እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን እውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል።

፲፯ ነገር ግን የዚህ ዓለም ገንዘብ ያለው፥ ወንድሙም የሚያስፈልገው ሲያጣ አይቶ ያልራራለት ማንም ቢሆን፥ የእግዚአብሔር ፍቅር በእርሱ እንዴት ይኖራል?

፲፰ ልጆቼ ሆይ፥ በሥራና በእውነት እንጂ በቃልና በአንደበት እንዋደድ።

፲፱-፳፩ ወዳጆች ሆይ፥ ልባችንስ ባይፈርድብን በእግዚአብሔር ዘንድ ድፍረት አለን፥

፳፪ ትእዛዙንም የምንጠብቅና በፊቱ ደስ የሚያሰኘውን የምናደርግ ስለሆንን የምንለምነውን ሁሉ ከእርሱ እናገኛለን።

፳፫ ትእዛዚቱም ይህች ናት፥ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናምን ዘንድ፥ ትእዛዝንም እንደ ሰጠን እርስ በርሳችን እንዋደድ ዘንድ።

፳፬ ትእዛዙንም የሚጠብቅ በእርሱ ይኖራል እርሱም ይኖርበታል፤ በዚህም በእኛ እንዲኖር ከሰጠን ከመንፈሱ እናውቃለን።

፬

፩ ወዳጆች ሆይ፥ መንፈስን ሁሉ አትመኑ፥ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደ ሆነ መርምሩ፤ ብዙዎች ሐሰተኞች ነቢያት ወደ ዓለም ወጥተዋልና።

፪ የእግዚአብሔርን መንፈስ በዚህ ታውቃላችሁ፤ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የሚታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር ነው፥

፫ ኢየሱስ ክርስቶስም በሥጋ እንደ መጣ የማይታመን መንፈስ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፤ ይህም የክርስቶስ ተቃዋሚው መንፈስ ነው፤ ይህም እንዲመጣ ሰምታችኋል፥ አሁንም እንኳ በዓለም አለ።

፬ ልጆች ሆይ፥ እናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸውማል፥ በዓለም ካለው ይልቅ በእናንተ ያለው ታላቅ ነውና።

፭ እነርሱ ከዓለም ናቸው፤ ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል።

፮ እኛ ከእግዚአብሔር ነን፤ እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል፤ ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም። የእውነትን መንፈስና የስሕተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን።

፯ ወዳጆች ሆይ፥ ፍቅር ከእግዚአብሔር ስለ ሆነ፥ የሚወደውም ሁሉ ከእግዚአብሔር ስለ ተወለደ እግዚአብሔርንም ስለሚያውቅ፥ እርስ በርሳችን እንዋደድ።

፰ ፍቅር የሌለው እግዚአብሔርን አያውቅም፥ እግዚአብሔር ፍቅር ነውና።

፱ በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር በእኛ ዘንድ ተገለጠ፥ በእርሱ በኩል በሕይወት እንኖር ዘንድ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደ ዓለም ልኮታልና።

፲ ፍቅርም እንደዚህ ነው፤ እግዚአብሔር እርሱ ራሱ እንደ ወደደን ስለ ኃጢአታችንም ማስተስሪያ ይሆን ዘንድ ልጁን እንደ ላከ እንጂ እኛ እግዚአብሔርን እንደ ወደድነው አይደለም።

፲፩ ወዳጆች ሆይ፥ እግዚአብሔር እንዲህ አድርጎ ከወደደን እኛ ደግሞ እርስ በርሳችን ልንዋደድ ይገባናል።

፲፪ እግዚአብሔርን ማንም ከቶ አላየውም፤ እርስ በርሳችን ብንዋደድ እግዚአብሔር በእኛ ይኖራል ፍቅሩም በእኛ ፍጹም ሆኖአል።

፲፫ ከመንፈሱ ስለ ሰጠን፥ በእርሱ እንድንኖር እርሱም በእኛ እንዲኖር በዚህ እናውቃለን።

፲፬ እኛም አይተናል አባትም ልጁን የዓለም መድኃኒት ሊሆን እንደ ላከው እንመሰክራለን።

፲፭ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ በሚታመን ሁሉ እግዚአብሔር በእርሱ ይኖራል እርሱም በእግዚአብሔር ይኖራል።

፲፮ እኛም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር አውቀናል አምነንማል። እግዚአብሔር ፍቅር ነው፥ በፍቅርም የሚኖር በእግዚአብሔር ይኖራል እግዚአብሔርም በእርሱ ይኖራል።

፲፯ በፍርድ ቀን ድፍረት ይሆንልን ዘንድ ፍቅር በዚህ ከእኛ ጋር ተፈጽሞአል፤ እርሱ እንዳለ እኛ ደግሞ እንዲሁ በዚህ ዓለም ነንና።

፲፯ ፍጹም ፍቅር ፍርሃትን አውጥቶ ይጥላል እንጂ
በፍቅር ፍርሃት የለም፥ ፍርሃት ቅጣት አለውና፤
የሚፈራም ሰው ፍቅሩ ፍጹም አይደለም።
፲፱ እርሱ አስቀድሞ ወዶናልና እኛ እንወደዋለን።
፳ ማንም። እግዚአብሔርን እወዳለሁ እያለ
ወንድሙን ቢጠላ ሐሰተኛ ነው፤ ያየውን ወንድሙን
የማይወድ ያላየውን እግዚአብሔርን ሊወደው እንዴት
ይችላል?
፳፩ እግዚአብሔርንም የሚወድ ወንድሙን ደግሞ
እንዲወድ ይህች ትእዛዝ ከእርሱ አለችን።

፭

፩ ክርስቶስ ነው ብሎ በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ
ከእግዚአብሔር ተወልዶአል፥ ወላጁንም የሚወድ ሁሉ
ከእርሱ የተወለደውን ደግሞ ይወዳል።
፪ እግዚአብሔርን ስንወድ ትእዛዛቱንም ስናደርግ
የእግዚአብሔርን ልጆች እንድንወድ በዚህ እናውቃለን።
፫ ትእዛዛቱን ልንጠብቅ የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ
ነውና፤ ትእዛዛቱም ከባዶች አይደሉም።
፬ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን
ያሸንፋልና፤ ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው።
፭ ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ
ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው?
፮ በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ
ክርስቶስ፤ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ
አይደለም።
፯ መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ
ነው።
፰ የሚመሰክሩት መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት
ናቸውና፤ ሦስቱም በአንድ ይሰማማሉ።
፱ የሰውን ምስክር ብንቀበል የእግዚአብሔር ምስክር
ከእርሱ ይልቅ ይበልጣል፤ ስለ ልጁ የመሰከረው
የእግዚአብሔር ምስክር ይህ ነውና።
፲ በእግዚአብሔር ልጅ የሚያምን በነፍሱ ምስክር
አለው፤ በእግዚአብሔር የማያምን እግዚአብሔር
ስለ ልጁ የመሰከረውን ምስክር ስላላመነ ሐሰተኛ
አድርጎታል።
፲፩ እግዚአብሔርም የዘላለምን ሕይወት እንደ ሰጠን
ይህም ሕይወት በልጁ እንዳለ ምስክሩ ይህ ነው።
፲፪ ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ
የሌለው ሕይወት የለውም።
፲፫ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ
በእግዚአብሔር ልጅ ስም ለምታምኑ ይህን
ጽፌላችኋለሁ።
፲፬ በእርሱ ዘንድ ያለን ድፍረት ይህ ነው፤ እንደ
ፈቃዱ እንዳች ብንለምን ይሰማናል።
፲፭ የምንለምነውንም ሁሉ እንዲሰማልን ብናውቅ
ከእርሱ የለመነውን ልመና እንደ ተቀበልን እናውቃለን።
፲፮ ማንም ወንድሙን ሞት የማይገባውን ኃጢአት
ሲያደርግ ቢያየው ይለምን፥ ሞትም የማይገባውን
ኃጢአት ላደረጉት ሕይወት ይሰጥለታል። ሞት
የሚገባው ኃጢአት አለ፤ ስለዚያ እንዲጠይቅ
አልልም።
፲፯ ዓመፃ ሁሉ ኃጢአት ነው፥ ሞትም የማይገባው
ኃጢአት አለ።
፲፰ ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን
እንዳያደርግ፥ ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተወለደው
ራሱን እንዲጠብቅ ክፉውም እንዳይነካው እናውቃለን።
፲፱ ከእግዚአብሔር እንደ ሆንን ዓለምም በሞላው
በክፉው እንደ ተያዘ እናውቃለን።
፳ የእግዚአብሔርም ልጅ እንደ መጣ፥ እውነተኛም
የሆነውን እናውቅ ዘንድ ልቡናን እንደ ሰጠን
እናውቃለን፤ እውነተኛም በሆነው በእርሱ አለን፥
እርሱም ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱ እውነተኛ
አምላክና የዘላለም ሕይወት ነው።
፳፩ ልጆች ሆይ፥ ከጣዖታት ራሳችሁን ጠብቁ።

2ኛ የዮሐንስ መልእክት

፩-፫ ከእግዚአብሔር አብና ከአብ ልጅ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ምሕረት ሰላምም በእውነትና በፍቅር ከእኛ ጋር ይሆናሉ።

፬ ትእዛዝን ከአብ እንደ ተቀበልን ከልጆችሽ በእውነት የሚሄዱ እንዳንዶችን ሰለ አገኘኋቸው እጅግ ደስ ብሎኛል።

፭ አሁንም፥ እመቤት ሆይ፥ እርስ በርሳችን እንድንዋደድ እለምንሻለሁ፤ ይህች ከመጀመሪያ በእኛ ዘንድ የነበረች ትእዛዝ ናት እንጂ አዲስ ትእዛዝን እንደምጽፍልሽ አይደለም።

፮ እንደ ትእዛዛቱም እንሄድ ዘንድ ይህ ፍቅር ነው፤ ከመጀመሪያ እንደ ሰማችሁ፥ በእርሰዋ ትሄዱ ዘንድ ትእዛዙ ይህች ናት።

፯ ብዙ አሳቾች ወደ ዓለም ገብተዋልና እነርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንደ መጣ የማያምኑ ናቸው፤ ይህ አሳቹና የክርስቶስ ተቃዋሚው ነው።

፰ ሙሉ ደመወዝን እንድትቀበሉ እንጂ የሠራችሁትን እንዳታጠፉ ለራሳችሁ ተጠንቀቁ።

፱ ለሚወጣ ሁሉ በክርስቶስም ትምህርት ለማይኖር ሰው አምላክ የለውም፤ በክርስቶስ ትምህርት ለሚኖር አብና ወልድ አሉት።

፲ ማንም ወደ እናንተ ቢመጣ ይህንም ትምህርት ባያመጣ በቤታችሁ አትቀበሉት ሰላምም አትበሉት፤

፲፩ ሰላም የሚለው ሰው በክፉ ሥራው ይካፈላልና።

፲፪ እንድጽፍላችሁ የምፈልገው ብዙ ነገር ሳለኝ በወረቀትና በቀለም ልጽፈው አልወድም፥ ዳሩ ግን ደስታችሁ ፍጹም እንዲሆን ወደ እናንተ ልመጣ እፍ ለአፍም ልናገራችሁ ተስፋ አደርጋለሁ።

፲፫ የተመረጠችው የእኅትሽ ልጆች ሰላምታ ያቀርቡልሻል።

3ኛ የዮሐንስ መልእክት

፩ ሽማግሌው በእውነት እኔ ለምወደው ለተወደደው
ለጋይዮስ።
፪ ወዳጅ ሆይ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ
እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸልያለሁ።
፫ ወንድሞች መጥተው እኒተ በእውነት እንደምትሄድ
ስለ እውነትህ ሲመስክሩ እጅግ ደስ ብሎኛልና።
፬ ልጆቼ በእውነት እንዲሄዱ ከመሰማት ይልቅ
የሚበልጥ ደስታ የለኝም።
፭ ወዳጅ ሆይ፥ ምንም እንግዶች ቢሆኑ፥ ለወንድሞች
በምታደርገው ሁሉ የታመነ ሥራ ትሠራለህ፥ እነርሱም
በማኅበር ፊት ስለ ፍቅርህ መስክረዋል፤
፮ ለእግዚአብሔር እንደሚገባ አድርገህ በጉዞአቸው
ብትረዳ መልካም ታደርጋለህ፤
፯ ከአሕዛብ አንዳች ሳይቀበሉ ስለ ስሙ
ወጥተዋልና።
፰ እንግዲህ ከእውነት ጋር አብረን እንድንሠራ እኛ
እንዲህ ያሉትን በእንግድነት ልንቀበል ይገባናል።
፱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጻፍሁ፤ ዳሩ ግን ዋናቸው
ሊሆን የሚወድ ዲዮጥራጢስ አይቀበለንም።
፲ ስለዚህ፥ እኔ ብመጣ፥ በእኛ ላይ በክፉ ቃል
እየለፈለፈ የሚያደርገውን ሥራውን አሳስባለሁ፤ ይህም
ሳይበቃው እርሱ ራሱ ወንድሞችን አይቀበልም፥
ሊቀበሉአቸውም የሚወዱትን ከልክሎ ከቤተ
ክርስቲያን ያወጣቸዋል።
፲፩ ወዳጅ ሆይ፥ በጎ የሆነውን እንጂ ክፉን
አትምሰል። በጎ የሚያደርግ ከእግዚአብሔር ነው፤
ክፉን የሚያደርግ ግን እግዚአብሔርን አላየውም።
፲፪ ለድሜጥሮስ ሁሉ ይመስክሩለታል፥ እውነት
ራስዋም ትመስክርለታለች፤ እኛም ደግሞ
እንመስክርለታለን፥ ምስክርነታችንም እውነት እንደ ሆነ
ታውቃላችሁ።
፲፫-፲፭ ልጽፍልህ የምፈልገው ብዙ ነገር ነበረኝ፥ ዳሩ
ግን በቀለምና በብርዕ ልጽፍልህ አልወድም፤

የይሁዳ መልእክት

፩ የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያ የያዕቆብም ወንድም
የሆነ ይሁዳ፥ በእግዚአብሔር አብ ተወደው ለኢየሱስ
ክርስቶስም ተጠብቀው ለተጠሩ፤
፪ ምሕረትና ሰላም ፍቅርም ይብዛላችሁ።
፫ ወዳጆች ሆይ፥ ስለምንካፈለው ስለ መዳናችን
ልጽፍላችሁ እጅግ ተግቼ ሳለሁ፥ ለቅዱሳን አንድ
ጊዜ ፈጽሞ ስለ ተሰጠ ሃይማኖት እንድትጋደሉ
እየመከርኋችሁ እጽፍላችሁ ዘንድ ግድ ሆነብኝ።
፬ ከብዙ ጊዜ በፊት ለዚህ ፍርድ የተጻፉ እንዳንዶች
ሰዎች ሾልከው ገብተዋልና፤ ኃጢአተኞች ሆነው
የአምላካችንን ጸጋ በሴሰኝነት ይለውጣሉ ንጉሣችንንና
ጌታችንንም ብቻውን ያለውን ኢየሱስ ክርስቶስን
ይክዳሉ።
፭ ዳሩ ግን ሁሉን አንድ ጊዜ ፈጽሞ ምንም
የተማራችሁ ብትሆኑ ጌታ ከግብፅ አገር ሕዝቡን
እድኖ የማያምኑትን በኋላ እንዳጠፋቸው ላሳስባችሁ
እወዳለሁ።
፮ መኖሪያቸውንም የተዉትን እንጂ የራሳቸውን
አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እስራት
ከጨለማ በታች እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ
ጠብቆአቸዋል።
፯ እንዲሁም እንደ እነርሱ ዝሙትን ያደረጉና ሌላን
ሥጋ የተከተሉ ሰዶምና ገሞራ በዙሪያቸውም የነበሩ
ከተማዎች በዘላለም እሳት እየተቀጡ ምሳሌ ሆነዋል።
፰ እንዲሁም እነዚህ ሰዎች ደግሞ እያለሙ
ሥጋቸውን ያረክሳሉ ጌትነትንም ይጥላሉ ሥልጣን
ያላቸውንም ይሳደባሉ።
፱ የመላእክት አለቃ ሚካኤል ግን ከዲያብሎስ
ጋር በተከራከረ ጊዜ ስለ ሙሴ ሥጋ ሲነጋገር። ጌታ
ይገሥጽህ አለው እንጂ የሰድብን ፍርድ ሊናገረው
አልደፈረም።
፲ እነዚህ ግን የማያውቁትን ሁሉ ይሳደባሉ፥
አእምሮም እንደሌላቸው እንስሶች በፍጥረታቸው
በሚያውቁት ሁሉ በእርሱ ይጠፋሉ።
፲፩ ወዮላቸው፥ በቃየል መንገድ ሄደዋልና ስለ
ደመወዝም ለበለዓም ስሕተት ራሳቸውን አሳልፈው
ሰጥተዋል በቆሬም መቃወም ጠፍተዋል።
፲፪ እነዚህ ከእናንተ ጋር ሲጋበዙ በፍቅር ግብዣችሁ
እንደ እድፍ ናቸው፤ እንደ እረኞች ያለ ፍርሃት ራሳቸውን
ይጠብቃሉ፤ በነፋስ የተወሰዱ ውኃ የሌለባቸው
ደመናዎች፥ ፍሬ የማያፈሩ ሁለት ጊዜ የሞቱ
ከነሥራቸው የተነቀሉ በበጋ የደረቁ ዛፎች፥
፲፫ የገዛ ነውራቸውን አረፋ እየደፈቁ ጨካኝ የባሕር
ማዕበል፥ ድቅድቅ ጨለማ ለዘላለም የተጠበቀላቸው
የሚንከራተቱ ከዋክብት ናቸው።
፲፬-፲፭ እነዚህ እንደ ምኞታቸው እየሄዱ
የሚያንጎራጉሩና ስለ ዕድላቸው የሚያጕረመርሙ
ናቸው፥ እንዲረባቸውም ለሰው ፊት እያደሉ አፋቸው
ከመጠን ይልቅ ታላቅ ቃል ይናገራል።
፲፮ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ በጌታችን በኢየሱስ
ክርስቶስ ሐዋርያት ቀድሞ የተነገረውን ቃል አስቡ፤
፲፯ እነርሱ። በመጨረሻው ዘመን በኃጢአተኝነት
እንደ ገዛ ምኞታቸው እየሄዱ ዘባኞች ይሆናሉ
ብለዋችኋልና።
፲፰ እነዚህ የሚያለያዩ ሥጋውያንም የሆኑ መንፈስም
የሌላቸው ሰዎች ናቸው።
፲፱ እናንተ ግን፥ ወዳጆች ሆይ፥ ከሁሉ ይልቅ በተቀደሰ
ሃይማኖታችሁ ራሳችሁን ለማነጽ እየተጋችሁ በመንፈስ
ቅዱስም እየጸለያችሁ፥
፳፩ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስደውን
የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠባበቁ
በእግዚአብሔር ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ።
፳፪ አንዳንዶች ተከራካሪዎችንም ውቀሱ፥
፳፫ አንዳንዶችንም ከእሳት ነጥቃችሁ አድኑ፥
አንዳንዶችንም በሥጋ የረከሰውን ልብስ እንኳ
እየጠላችሁ በፍርሃት ማሩ።
፳፬ ሳትሰናከሉም እንዲጠብቃችሁ፥ በክብሩም ፊት
በደስታ ነውር የሌላችሁ አድርጎ እንዲያቆማችሁ
ለሚችለው
፳፭ ብቻውን ለሆነ አምላክና መድኃኒታችን ከዘመን
ሁሉ በፊት አሁንም እስከ ዘላለምም ድረስ በጌታችን
በኢየሱስ ክርስቶስ ክብርና ግርማ ኃይልም ሥልጣንም
ይሁን፤ አሜን።

የዮሐንስ ራእይ

፩ ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥
፪ እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መስክረ።
፫ ዘመኑ ቀርቦአልና የሚያነበው፥ የትንቢቱን ቃል የሚሰሙትና በውስጡ የተጻፈውን የሚጠብቁት ብፁዓን ናቸው።
፬-፮ መንግሥትም ለእምላኩና ለአባቱም ካህናት እንድንሆን ላደረገ፥ ለእርሱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ክብርና ኃይል ይሁን፤ አሜን።
፯ እነሆ፥ ከደመና ጋር ይመጣል፤ ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል፥ የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ። አዎን፥ አሜን።
፰ ያለውና የነበረው የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ እምላክ። እልፋና ዖሜጋ እኔ ነኝ ይላል።
፱ እኔ ወንድማችሁ የሆንሁ ከእናንተም ጋር አብሬ መከራውንና መንግሥቱን የኢየሱስ ክርስቶስንም ትዕግሥት የምካፈል ዮሐንስ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክር ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ።
፲ በጌታ ቀን በመንፈስ ነበርሁ፥ በኋላዬም የመለከትን ድምፅ የሚመስል ትላቅ ድምፅ ሰማሁ፥
፲፩ እንዲሁም። የምታየውን በመጽሐፍ ጽፈህ ወደ ኤፌሶንና ወደ ስምርኔስ ወደ ጴርጋሞንም ወደ ትያጥሮንም ወደ ሰርዴስም ወደ ፊልድልፍያም ወደ ሎዶቅያም በእስያ ወዳሉት ወደ ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ላክ አለኝ።
፲፪ የሚናገረኝንም ድምፅ ለማየት ዘወር አልሁ፤ ዘወርም ብዬ ሰባት የወርቅ መቅረዞች አየሁ፥
፲፫ በመቅረዞቹም መካከል የሰው ልጅ የሚመስለውን አየሁ፥ እርሱም እስከ እግሩ ድረስ ልብስ የለበሰው ደረቱንም በወርቅ መታጠቂያ የታጠቀ ነበር።
፲፬ ራሱና የራሱ ጠጕርም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፥ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ነበሩ፤
፲፭ እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፥ ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበረ።
፲፮ በቀኝ እጁም ሰባት ከዋክብት ነበሩት፥ ከአፉም በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ወጣ፤ ፊቱም በኃይል እንደሚበራ እንደ ፀሐይ ነበረ።
፲፯ ባየሁትም ጊዜ እንደ ሞተ ሰው ሆኜ ከእግሩ በታች ወደቅሁ። ቀኝ እጁንም ጫነብኝ እንዲህም አለኝ። አትፍራ፤ ፊተኛውና መጨረሻው ሕያውም እኔ ነኝ፥
፲፰ ሞቼም ነበርሁ እነሆም፥ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ነኝ፥ የሞትና የሲኦልም መክፈቻ አለኝ።
፲፱ እንግዲህ ያየኸውን አሁንም ያለውን ከዚህም በኋላ ይሆን ዘንድ ያለውን ጻፍ።
፳ በቀኝ እጄ ያየሃቸው የሰባቱ ከዋክብትና የሰባቱ የወርቅ መቅረዞች ምሥጢር ይህ ነው፤ ሰባቱ ከዋክብት የሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት መላእክት ናቸው፥ ሰባቱም መቅረዞች ሰባቱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው።

፪

፩ በኤፌሶን ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። በቀኝ እጁ ሰባቱን ከዋክብት የያዘው በሰባቱም የወርቅ መቅረዞች መካከል የሚሄደው እንዲህ ይላል።
፪ ሥራህንና ድካምህን ትዕግሥትህንም አውቃለሁ፤ ክፉዎችንም ልትታገሥ እንዳትችል፥ እንዲሁም ሳይሆኑ። ሐዋርያት ነን የሚሉቱን መርምረህ ሐሰተኞች ሆነው እንዳገኘሃቸው አውቃለሁ፤
፫ ታግሠህማል፥ ሰለ ስሜም ብለህ ጸንተህ አልደከምህም።
፬ ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና።
፭ እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንሰሐም ግባ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ፤ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንሰሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሰፍራው እወሰዳለሁ።
፮ ነገር ግን ይህ አለህ፤ እኔ ደግሞ የምጠላውን የኒቆላውያንን ሥራ ጠልተሃልና።
፯ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ። ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ።
፰ በሰምርኔስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሞቶ የነበረው ሕያውም የሆነው ፊተኛውና መጨረሻው እንዲህ ይላል።
፱ መከራህንና ድህነትህን አውቃለሁ፥ ነገር ግን ባለ ጠጋ ነህ፤ የሰይጣንም ማኅበር ናቸው እንጂ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን የሚሉት የሚሳደቡትን ሰድብ አውቃለሁ።
፲ ልትቀበለው ያለህን መከራ አትፍራ። እነሆ፥ እንድትፈተኑ ዲያብሎስ ከእናንተ አንዳንዶቻችሁን በወኅኒ ሊያገባችሁ አለው፥ አሥር ቀንም መከራን ትቀበላላችሁ። እስከሞት ድረስ የታመነህ ሁን የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ።
፲፩ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ። ድል የነሣው በሁለተኛው ሞት አይጐዳም።
፲፪ በጴርጋሞንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል።
፲፫ የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ፤ ሰሜንም ትጠብቃለህ፥ ሰይጣንም በሚኖርበት፥ በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ በነበረበት ዘመን እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም።
፲፬ ዳሩ ግን ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉና እንዲሴስኑ በእስራኤል ልጆች ፊት ማሰናከያን ሊያኖርባቸው ባላቅን ያስተማረ የበልዓምን ትምህርት የሚጠብቁ በዚያ ከአንተ ጋር ሰላሉ፥ የምነቅፍብህ ጥቂት ነገር አለኝ።
፲፭ እንዲሁ የኒቆላውያንን ትምህርት እንደ እነዚህ የሚጠብቁ ሰዎች ከአንተ ጋር ደግሞ አሉ።
፲፮ እንግዲህ ንሰሐ ግባ፤ አለዚያ ፈጥኜ እመጣብሃለሁ፥ በአፌም ሰይፍ እዋጋቸዋለሁ።
፲፯ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ። ድል ለነሣው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ፥ ነጭ ድንጋይንም እሰጠዋለሁ፥

በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር እንድ ሰንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ሰም ተጽፎአል።
፲፰ በትያጥሮንም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። እንደ እሳት ነበልባል የሆኑ ዓይኖች ያሉት በእቶንም የነጠረ የጋለ ናስ የሚመስሉ እግሮች ያሉት የእግዚአብሔር ልጅ እንዲህ ይላል።
፲፱ ሥራህንና ፍቅርህን እምነትህንም አገልግሎትህንም ትዕግሥትህንም ከፊተኛውም ሥራህ ይልቅ የኋለኛው እንዲበዛ አውቃለሁ።
፳ ዳሩ ግን። ነቢይ ነኝ የምትለውን ባሪያዎቼንም እንዲሴስኑና ለጣዖት የታረደውን እንዲበሉ የምታስተምረውንና የምታስተውን ያችን ሴት ኤልዛቤልን ስለምትተዋት የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤
፳፩ ንስሐም እንድትገባ ጊዜ ሰጠኋት ከዝሙትዋም ንስሐ እንድትገባ አልወደደችም።
፳፪ እነሆ፥ በአልጋ ላይ እጥላታለሁ፥ ከእርስዋም ጋር የሚያመነዝሩትን ከሥራዋ ንስሐ ባይገቡ በታላቅ መከራ እጥላቸዋለሁ፤
፳፫ ልጆችዋንም በሞት እገድላቸዋለሁ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ሁሉ ኩላሊትንና ልብን የምመረምር እኔ እንደ ሆንሁ ያውቃሉ፥ ለእያንዳንዳችሁም እንደ ሥራችሁ እሰጣችኋለሁ።
፳፬ ዳሩ ግን ይህን ትምህርት ለማትይዙ ሁሉ የሰይጣንንም ጥልቅ ነገር እነርሱ እንደሚሉት ለማታውቁ ለእናንተ በትያጥሮን ለቀራችሁት እላለሁ፤ ሌላ ሸክም አልጭንባችሁም፥
፳፭ ነገር ግን እስክመጣ ድረስ ያላችሁን ጠብቁ።
፳፮-፳፰ የነጋትንም ኮከብ እሰጠዋለሁ።
፳፱ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ።

፫

፩ በሰርዴስም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስትና ሰባቱ ከዋክብት ያሉት እንዲህ ይላል። ሥራህን አውቃለሁ ሕያው እንደ መሆንህ ስም አለህ ሞተህማል።
፪ ሥራህን በእምላኬ ፊት ፍጹም ሆኖ አላገኘሁትምና የነቃህ ሁን፥ ለሞቱም ያላቸውን የቀሩትን ነገሮች አጽና።
፫ እንግዲህ እንዴት እንደ ተቀበልህና እንደ ሰማህ አስብ፥ ጠብቀውም ንስሐም ግባ። እንግዲያስ ባትነቃ እንደ ሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም።
፬ ነገር ግን ልብሳቸውን ያላረከሱ በሰርዴስ ጥቂት ስዎች ከእነተ ጋር አሉ፥ የተገባቸውም ስለ ሆኑ ነጭ ልብስ ለብሰው ከእኔ ጋር ይሄዳሉ።
፭ ድል የነሣው እንዲሁ በነጭ ልብስ ይጐናጸፋል፥ ስሙንም ከሕይወት መጽሐፍ አልደመስስም፥ በአባቴና በመላእክቱም ፊት ለስሙ እመሰክርለታለሁ።
፮ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ።
፯ በፊልድልፍያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። የዳዊት መክፈቻ ያለው፤ የሚከፍት፥ የሚዘጋም የሌለ፤ የሚዘጋ፥ የሚከፍትም የሌለ፤ ቅዱስና እውነተኛ የሆነው እርሱ እንዲህ ይላል።
፰ ሥራህን አውቃለሁ፤ እነሆ፥ በእነተ ፊት የተከፈተ በር ሰጥቼአለሁ ማንምም ሊዘጋው አይችልም፤ ኃይልህ ምንም ትንሽ ቢሆን ቃሌን ጠብቀሃልና፥ ስሜንም አልካድህምና።
፱ እነሆ፥ አይሁድ ሳይሆኑ። አይሁድ ነን ከሚሉ ነገር ግን ከሚዋሹ ከሰይጣን ማኅበር አንዳንዶችን እሰጥሃለሁ እነሆ፥ መጥተው በእግሮችህ ፊት ይሰግዱ ዘንድ እኔም እንደ ወደድሁህ ያውቁ ዘንድ እደርጋቸዋለሁ።
፲ የትዕግሥቴን ቃል ሰለ ጠበቅህ እኔ ደግሞ በምድር የሚኖሩትን ይፈትናቸው ዘንድ በዓለም ሁሉ ላይ ሊመጣ ካለው ከፈተናው ሰዓት እጠብቅሃለሁ።
፲፩ እነሆ፥ ቶሎ ብዬ እመጣለሁ፤ ማንም አክሊልህን እንዳይወስድብህ ያለህን አጽንተህ ያዝ።
፲፪ ድል የነሣው በአምላኬ መቅደስ ዓምድ እንዲሆን እደርገዋለሁ፥ ወደ ፊትም ከዚያ ከቶ አይወጣም፤ የአምላኬን ሰምና የአምላኬን ከተማ ሰም፥ ማለት ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደውን አዲሲቱን ኢየሩሳሌምን፥ አዲሱንም ሰሜን በእርሱ ላይ እጽፋለሁ።
፲፫ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ።
፲፬ በሎዶቅያም ወዳለው ወደ ቤተ ክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ። አሜን የሆነው፥ የታመነውና እውነተኛው ምስክር፥ በእግዚአብሔርም ፍጥረት መጀመሪያ የነበረው እንዲህ ይላል።
፲፭ በራድ ወይም ትኩስ እንዳይደለህ ሥራህን እውቃለሁ። በራድ ወይም ትኩስ ብትሆንስ መልካም በሆነ ነበር።
፲፮ እንዲሁ ለብ ሰላልህ በራድም ወይም ትኩስ ሰላልሆንህ ከአፌ ልተፋህ ነው።
፲፯ ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ እንድም ሰንኳ እያሰፈልገኝም የምትል ሰለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድህም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ሰለማታውቅ፥
፲፰ ባለ ጠጋ እንድትሆን በእሳት የነጠረውን ወርቅ፥ ተጐናጽፈህም የራቁትነትህ ኃፍረት እንዳይገለጥ ነጭ ልብስን፥ እንድታይም ዓይኖችህን የምትኳለውን ኩል ከእኔ ትገዛ ዘንድ እመክርሃለሁ።
፲፱ እኔ የምወዳቸውን ሁሉ እገሥጻቸዋለሁ እቀጣቸውማለሁ፤ እንግዲህ ቅና ንስሐም ግባ።
፳ እነሆ በደጅ ቆሜ እንኳኳለሁ፤ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ፥ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል።
፳፩ እኔ ደግሞ ድል እንደ ነሣሁ ከአባቴም ጋር በዙፋኑ ላይ እንደተቀመጥሁ፥ ድል ለነሣው ከእኔ ጋር በዙፋኔ ላይ ይቀመጥ ዘንድ እሰጠዋለሁ።
፳፪ መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይሰማ።

፬

፩ ከዚያ በኋላም አየሁ፥ እነሆም በሰማይ የተከፈተ ደጅ፥ እንደ መለከትም ሆኖ ሲናገረኝ የሰማሁት ፊተኛው ድምፅ። ወደዚህ ውጣና ከዚህ በኋላ ሊሆን የሚያሰፈልገውን ነገር አሳይሃለሁ አለ።

፪ ወዲያው በመንፈስ ነበርሁ፤ እነሆም፥ ዙፋን በሰማይ ቆሞአል በዙፋኑም ላይ ተቀማጭ ነበረ፤
፫ ተቀምጦም የነበረው በመልኩ የኢያስጲድንና የሰርዲኖን ዕንቊ ይመስል ነበር። በመልኩም መረግድን የመሰለ ቀስተ ደመና በዙፋኑ ዙሪያ ነበረ።
፬ በዙፋኑ ዙሪያም ሀያ አራት ዙፋኖች ነበሩ፥ በዙፋኖቹም ላይ ነጭ ልብስ ለብሰው በራሳቸውም የወርቅ አክሊል ደፍተው ሀያ አራት ሽማግሌዎች ተቀምጠው ነበር።
፭ ከዙፋኑም መብረቅና ድምፅ ነጐድጓድም ይወጣል፤ በዙፋኑም ፊት ሰባት የእሳት መብራቶች ይበሩ ነበር፥ እነርሱም ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።
፮ በዙፋኑም ፊት ብርሌ የሚመስል የብርጭቆ ባሕር ነበረ። በዙፋኑም መካከል በዙፋኑም ዙሪያ፥ በፊትና በኋላ ዓይኖች የሞሉአቸው አራት እንሰሶች ነበሩ።
፯ ፊተኛውም እንሰሳ አንበሳን ይመስላል፥ ሁለተኛውም እንሰሳ ጥጃን ይመስላል፥ ሦስተኛውም እንሰሳ እንደ ሰው ፊት ነበረው፥ አራተኛውም እንሰሳ የሚበረውን ንስር ይመስላል።
፰ አራቱም እንሰሶች እያንዳንዳቸው ስድስት ክንፎች አሉአቸው፥ በዙሪያቸውና በውስጣቸውም ዓይኖች ሞልተውባቸዋል፤ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ ቅዱስ፥ የነበረውና ያለ የሚመጣውም ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክ እያሉ ቀንና ሌሊት አያርፉም።
፱-፲፩ እንሰሶቹም በዙፋን ላይ ለተቀመጠው ከዘላለምም እስከ ዘላለም በሕይወት ለሚኖረው ለእርሱ ክብርና ውዳሴ ምስጋናም በሰጡት ጊዜ፥

፭

፩ በዙፋኑ ላይም በተቀመጠው በቀኝ እጁ ላይ በውስጥና በኋላ የተጻፈበት በሰባትም ማኅተም የተዘጋ መጽሐፍን አየሁ።
፪ ብርቱም መልአክ። መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ማኅተሞቹንም ይፈታ ዘንድ የሚገባው ማን ነው? ብሎ በታላቅ ድምፅ ሲያውጅ አየሁ።
፫ በሰማይም ቢሆን በምድርም ላይ ቢሆን ከምድርም በታች ቢሆን መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው ማንም አልተቻለውም።
፬ መጽሐፉን ሊዘረጋ ወይም ሊመለከተው የሚገባው ማንም ስላልተገኘ እጅግ አለቀስሁ።
፭ ከሽማግሌዎቹም አንዱ። አታልቅስ፤ እነሆ፥ ከይሁዳ ነገድ የሆነው አንበሳ እርሱም የዳዊት ሥር መጽሐፉን ይዘረጋ ዘንድ ሰባቱንም ማኅተም ይፈታ ዘንድ ድል ነሥቶአል አለኝ።
፮ በዙፋኑና በአራቱ እንሰሶች መካከልም በሽማግሌዎችም መካከል እንደ ታረደ በግ ቆሞ አየሁ፥ ሰባትም ቀንዶችና ሰባት ዓይኖች ነበሩት እነርሱም ወደ ምድር ሁሉ የተላኩ የእግዚአብሔር መናፍስት ናቸው።
፯ መጥቶም በዙፋን ላይ ከተቀመጠ ከዚያ ከቀኝ እጁ መጽሐፉን ወሰደው።
፰ መጽሐፉንም በወሰደ ጊዜ አራቱ እንሰሶችና ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በበጉ ፊት ወደቁ፥ እያንዳንዳቸውም በገናንና የቅዱሳን ጸሎት የሆነ ዕጣን የሞላበትን የወርቅ ዕቃ ያዙ።
፱-፲፩ አየሁም፥ በዙፋኑም በእንሰሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቍጥራቸውም እእላፋት ጊዜ እእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበር፥
፲፪ በታላቅም ድምፅ። የታረደው በግ ኃይልና ባለ ጠግነት ጥበብም ብርታትም ክብርም ምስጋናም በረከትም ሊቀበል ይገባዋል አሉ።
፲፫ በሰማይና በምድርም ከምድርም በታች በባሕርም ላይ ያለ ፍጥረት ሁሉ በእነርሱም ውስጥ ያለ ሁሉ። በረከትና ክብር ምስጋናም ኃይልም ከዘላለም እስከ ዘላለም በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው፥ ለበጉም ይሁን ሲሉ ሰማሁ።
፲፬ አራቱም እንሰሶች። አሜን አሉ፥ ሽማግሌዎቹም ወድቀው ሰገዱ።

፮

፩ በጉም ከሰባቱ ማኅተም አንዱን በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ከአራቱም እንሰሶች አንዱ ነጐድጓድ በሚመስል ድምፅ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።
፪ አየሁም፥ እነሆም፥ አምባላይ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ቀስት ነበረው፥ አክሊልም ተሰጠው፥ ድልም እየነሣ ወጣ ድል ለመንሣት።
፫ ሁለተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሁለተኛው እንሰሳ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።
፬ ሌላም ዳማ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ ለተቀመጠው ሰላምን ከምድር ይወስድ ዘንድ ሰዎችም እርስ በርሳቸው እንዲተራረዱ ሥልጣን ተሰጠው፥ ታላቅም ሰይፍ ተሰጠው።
፭ ሦስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ ሦስተኛው እንሰሳ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ። አየሁም፥ እነሆም፥ ጕራቻ ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው በእጁ ሚዛን ያዘ።
፮ በአራቱም እንሰሶች መካከል ድምፅ። አንድ እርቦ ሰንዴ በዲናር ሦስት እርቦ ገብስም በዲናር፥ ዘይትንና ወይንንም አትጕዳ ሲል ሰማሁ።
፯ አራተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ የአራተኛው እንሰሳ ድምፅ። መጥተህ እይ ሲል ሰማሁ።
፰ አየሁም፥ እነሆም፥ ሐመር ፈረስ ወጣ፥ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ሰሙ ሞት ነበረ። ሲኦልም ተከተለው፤ በሰይፍና በራብም በሞትም በምድርም አራዊት ይገድሉ ዘንድ ከምድር በአራተኛዋ እጅ ላይ ሥልጣን ተሰጣቸው።
፱ አምስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ፥ ሰለ እግዚአብሔር ቃልና ሰለ ጠበቁት ምስክር የታረዱትን የሰዎች ነፍሳት ከመሠዊያ በታች አየሁ።
፲ በታላቅ ድምፅም እየጮኹ። ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፥ እስከ መቼ ድረስ አትፈርድም ደማችንንስ በምድር በሚኖሩት ላይ እስከ መቼ አትበቀልም? አሉ።
፲፩ ለእያንዳንዳቸውም ነጭ ልብስ ተሰጣቸው፥ እንደ እነርሱም ደግሞ ይገደሉ ዘንድ ያላቸው የባሪያዎች ባልንጀራዎቻቸውና የወንድሞቻቸው ቍጥር እስኪፈጸም ድረስ፥ ገና ጥቂት ዘመን እንዲያርፉ ተባለላቸው።
፲፪ ስድስተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ አየሁ፥ ታላቅም የምድር መናወጥ ሆነ፥ ፀሐይም እንደ ማቅ ጠጕር ጥቁር ሆነ፥ ጨረቃም በሞላው እንደ ደም ሆነ፥

፲፫ በለሰም በብርቱ ነፋስ ተናውጣ ቃርያዋን ፍሬ
እንደምትጥል የሰማይ ከዋክብት ወደ ምድር ወደቁ፥
፲፬ ሰማይም እንደ መጽሐፍ ተጠቅልሎ አለፈ፥
ተራራዎችና ደሴቶችም ሁሉ ከስፍራቸው ተወሰዱ።
፲፭ የምድርም ነገሥታትና መኳንንት ሻለቃዎችም
ባለ ጠጋዎችም ኃይለኛዎችም ባሪያዎችም ጌቶችም
ሁሉ በዋሾችና በተራራዎች ዓለቶች ተሰወሩ፥
፲፮ ተራራዎችንና ዓለቶችንም። በላያችን ውደቁ
በዙፋኑም ከተቀመጠው ፊት ከበጉም ቊጣ ሰውሩን፤
፲፯ ታላቁ የቁጣው ቀን መጥቶአልና፥ ማንስ ሊቆም
ይችላል? አሉአቸው።

፯

፩ ከዚህም በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው
አራት መላእክት አየሁ፥ እነርሱም ነፋስ በምድር ቢሆን
ወይም በባሕር ወይም በማንም ዛፍ እንዳይነፍስ
አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ።
፪ የሕያው አምላክ ማኅተም ያለውም ሌላ መልአክ
ከፀሐይ መውጫ ሲወጣ አየሁ፥ ምድርንና ባሕርንም
ሊጐዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት በታላቅ ድምፅ
እየጮኸ።
፫ የአምላካችንን ባሪያዎች ግምባራቸውን
እስክናትማቸው ድረስ ምድርን ቢሆን ወይም ባሕርን
ወይም ዛፎችን አትጕዱ አላቸው።
፬ የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ፤ ከእስራኤል ልጆች
ነገድ ሁሉ የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።
፭ ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተሙ፥ ከሮቤል
ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከጋድ ነገድ አሥራ ሁለት
ሺህ፥
፮ ከአሴር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከንፍታሌም
ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥
፯ ከምናሴ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከስምዖን ነገድ
አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከሌዊ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥
ከይሳኮር ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥
፰ ከዛብሎን ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከዮሴፍ ነገድ
አሥራ ሁለት ሺህ፥ ከብንያም ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ
ታተሙ።
፱ ከዚህ በኋላ አየሁ፥ እነሆም፥ አንድ እንኳ
ሊቆጥራቸው የማይችል ከሕዝብና ከነገድ ከወገንም
ከቋንቋም ሁሉ እጅግ ብዙ ሰዎች ነበሩ፤ ነጭ ልብስም
ለብሰው የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው
በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፤
፲ በታላቅም ድምፅ እየጮሁ። በዙፋኑ ላይ
ለተቀመጠው ለአምላካችንና ለበጉ ማዳን ነው አሉ።
፲፩ መላእክቱም ሁሉ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ
በአራቱም እንሰሶቹ ዙሪያ ቆመው ነበር፤ በዙፋኑም ፊት
በግምባራቸው ተደፉ፥ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ።
፲፪ አሜን፥ በረከትና ክብር ጥበብም ምስጋናም
ውዳሴም ኃይልም ብርታትም ከዘላለም እስከ ዘላለም
ድረስ ለአምላካችን ይሁን፤ አሜን አሉ።
፲፫ ከሽማግሌዎቹም አንዱ ተመልሶ። እነዚህ ነጩን
ልብስ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ መጡ?
አለኝ።
፲፬ እኔም። ጌታ ሆይ፥ አንተ ታውቃለህ አልሁት።
አለኝም። እነዚህ ከታላቁ መከራ የመጡ ናቸው፥
ልብሳቸውንም አጥበው በበጉ ደም አነጹ።
፲፭ ስለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት አሉ፥
ሌሊትና ቀንም በመቅደሱ ያመልኩታል፥ በዙፋኑም ላይ
የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።
፲፮ ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፥ ከእንግዲህም
ወዲህ አይጠሙም፥ ፀሐይም ትኵሳትም ሁሉ ከቶ
አይወርድባቸውም፤
፲፯ በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው
ይሆናልና፥ ወደ ሕይወትም ውኃ ምንጭ ይመራቸዋልና፤
እግዚአብሔርም እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።

፰

፩ ሰባተኛውንም ማኅተም በፈታ ጊዜ እኩል ሰዓት
የሚያህል ዝምታ በሰማይ ሆነ።
፪ በእግዚአብሔርም ፊት የሚቆሙትን ሰባቱን
መላእክት አየሁ፥ ሰባትም መለከት ተሰጣቸው።
፫ ሌላም መልአክ መጣና የወርቅ ጥና ይዞ
በመሰዊያው አጠገብ ቆመ፤ በዙፋኑም ፊት ባለው
በወርቅ መሰዊያ ላይ ለቅዱሳን ሁሉ ጸሎት
እንዲጨምረው ብዙ ዕጣን ተሰጠው።
፬ የዕጣኑም ጢስ ከቅዱሳን ጸሎት ጋር ከመልአኩ
እጅ በእግዚአብሔር ፊት ወጣ።
፭ መልአኩም ጥናውን ይዞ የመሰዊያውን እሳት
ሞላበት ወደ ምድርም ጣለው፤ ነጐድጓድና ድምፅም
መብረቅም መናወጥም ሆነ።
፮ ሰባቱንም መለከት የያዙ ሰባቱ መላእክት ሊነፉ
ተዘጋጁ።
፯ ፊተኛውም መልአክ ነፋ፤ ደምም የተቀላቀለበት
በረዶና እሳት ሆነ፥ ወደ ምድርም ተጣለ፤
የምድርም ሲሶው ተቃጠለ የዛፎችም ሲሶው ተቃጠለ
የለመለመም ሣር ሁሉ ተቃጠለ።
፰ ሁለተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእሳት የሚቃጠል
ታላቅ ተራራን የሚመስል ነገር በባሕር ተጣለ፤
የባሕርም ሲሶው ደም ሆነ
፱ በባሕርም ከሚኖሩ ሕይወት ካላቸው ፍጥረቶች
ሲሶው ሞተ የመርከቦችም ሲሶው ጠፋ።
፲ ሦስተኛውም መልአክ ነፋ፤ እንደ ችቦም የሚቃጠል
ታላቅ ኮከብ ከሰማይ ወደቀ፥ በወንዞችና በውኃም
ምንጮች ሲሶ ላይ ወደቀ። የኮከቡም ስም እሬቶ
ይባላል።
፲፩ የውኃውም ሲሶ መራራ ሆነ መራራም ስለተደረገ
በውኃው ጠንቅ ብዙ ሰዎች ሞቱ።
፲፪ አራተኛውም መልአክ ነፋ፤ የፀሐይ ሲሶና የጨረቃ
ሲሶ የከዋክብትም ሲሶ ተመታ፥ የእነዚህ ሲሶ ይጨልም
ዘንድ፥ የቀንም ሲሶው እንዳያበራ፥ እንዲሁም የሌሊት።
፲፫ እየሁም፥ አንድም ንስር በሰማይ መካከል እየበረረ
በታላቅ ድምፅ። ሊነፉ ያላቸው የሦስቱ መላእክት
መለከት ስለሚቀረው ድምፅ በምድር ላይ ለሚኖሩት
ወዮላቸው፥ ወዮላቸው፥ ወዮላቸው ሲል ሰማሁ።

፱

፩ አምስተኛውም መልአክ ነፋ፤ ከሰማይም ወደ
ምድር ወድቆ የነበረ ኮከብ አየሁ፥ የጥልቁም ጕድጓድ
መክፈቻ ተሰጠው።
፪ የጥልቁንም ጕድጓድ ከፈተው፤ ጢስም ከታላቅ
እቶን እንደሚወጣ ጢስ ሆኖ ከጕድጓዱ ወጣ ፀሐይና
አየርም በጕድጓዱ ጢስ ጨለሙ።

፫ ከጢሱም አንበጣዎች ወደ ምድር ወጡ፥ የምድርም ጊንጦች ሥልጣን እንዳላቸው ሥልጣን ተሰጣቸው።
፬ የእግዚአብሔርም ማኅተም በግምባራቸው ከሌለባቸው ሰዎች በቀር በምድር ያለውን ሣር ቢሆንም ወይም ማናቸውንም የለመለመ ነገር ወይም ማናቸውንም ዛፍ እንዳይጐዱ ተባለላቸው።
፭ እምሰትም ወር ሊሣቅዩአቸው ተሰጣቸው እንጂ ሊገድሉአቸው አይደለም፤ እነርሱም የሚሣቅዩት ሥቃይ ጊንጥ ሰውን ነድፎ እንደሚሣቅይ ነው።
፮ በዚያም ወራት ሰዎች ሞትን ይፈልጋሉ አያገኙትምም፥ ሊሞቱም ይመኛሉ ሞትም ከእነርሱ ይሸሻል።
፯ የአንበጣዎቹም መልክ ለጦርነት እንደ ተዘጋጁ ፈረሶች ነው፥ በራሳቸውም ላይ ወርቅ እንደሚመስሉ አክሊሎች ነበሩአቸው፥ ፊታቸውም እንደ ሰው ፊት ነበረ፤
፰ የሴቶችን ጠጒር የሚመስል ጠጒር ነበራቸው፥ ጥርሳቸውም እንደ አንበሳ ጥርስ ነበረ፥
፱ የብረት ጥሩር የሚመስልም ጥሩር ነበራቸው፥ የክንፋቸውም ድምፅ ወደ ጦርነት እንደሚጋልቡ እንደ ብዙ ፈረሶች ሰረገላዎች ድምፅ ነበረ።
፲ እንደ ጊንጥም ጅራት ያለ ጅራት አላቸው በጅራታቸውም መውጊያ አለ፥ ሰዎችንም አምሰት ወር እንዲጐዱ ሥልጣን አላቸው።
፲፩ በእነርሱም ላይ ንጉሥ አላቸው እርሱም የጥልቅ መልአክ ነው፥ ስሙም በዕብራይስጥ አብዶን በግሪክም አጶልዮን ይባላል።
፲፪ ፊተኛው ወዮ አልፎአል፤ እነሆ፥ ከዚህ በኋላ ገና ሁለት ወዮ ይመጣል።
፲፫ ሰድሰተኛውም መልአክ ነፋ፤ በእግዚአብሔርም ፊት ካለ በወርቅ ከተሠራ መሠዊያ ቀንዶች አንድ ድምፅ ሰማሁ፥
፲፬ መለከትም ያለውን ሰድሰተኛውን መልአክ። በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ የታሰሩትን አራቱን መላእክት ፍታቸው አለው።
፲፭ የሰዎችንም ሲሶ እንዲገድሉ ለሰዓቱና ለቀኑ ለወሩም ለዓመቱም ተዘጋጅተው የነበሩ አራቱ መላእክት ተፈቱ።
፲፮ የፈረሰኞችም ጭፍራ ቁጥር እልፍ ጊዜ እልፍ፥ እልፍ ጊዜ እልፍ ነበረ፤ ቁጥራቸውን ሰማሁ።
፲፯ ፈረሶቹንና በእነርሱም ላይ የተቀመጡትን እንዲሁ በራእይ አየሁ፤ እሳትና ያክንት ዲንም የሚመስል ጥሩር ነበራቸው፤ የፈረሶቹም ራስ እንደ አንበሳ ራስ ነበረ፥ ከአፋቸውም እሳትና ጢስ ዲንም ወጣ።
፲፰ ከአፋቸውም በወጡት በእሳቱና በጢሱ በዲኑም በእነዚህ ሦስት መቅሰፍቶች የሰዎቹ ሲሶ ተገደለ።
፲፱ የፈረሶቹ ሥልጣን በአፋቸውና በጅራታቸው ነውና፤ ጅራታቸው እባብን ይመስላልና፥ ራስም አላቸው በእርሱም ይጐዳሉ።
፳ በእነዚህም መቅሠፍቶች ያልተገደሉት የቀሩቱ ሰዎች ለአጋንንትና ያዩ ወይም ይሰሙ ወይም ይሄዱ ዘንድ ለማይችሉ ከወርቅና ከብር ከናስም ከድንጋይም ከእንጨትም ለተሠሩ ለጣዖቶች እንዳይሰግዱ ሰለ እጆቸው ሥራ ንስሐ አልገቡም፤
፳፩ ሰለ መግደላቸውም ቢሆን ወይም ሰለ አሰማታቸው ወይም ሰለ ዝሙታቸው ወይም ሰለ ሰርቆታቸው ንሰሐ አልገቡም።

፲

፩ ሌላም ብርቱ መልአክ ደመና ተጐናጽፎ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፤ በራሱም ላይ ቀስተ ደመና ነበረ፥ ፊቱም እንደ ፀሐይ እግሮቹም እንደ እሳት ዓምዶች ነበሩ፥
፪ የተከፈተችንም ታናሽ መጽሐፍ በእጁ ያዘ። ቀኝ እግሩንም በባሕር ላይ ግራውንም በምድር ላይ አኖረ፥
፫ እንደሚያገሣም እንበሳ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።
፫ በጮኸም ጊዜ ሰባቱ ነጐድጓድ በየድምፃቸው ተናገሩ።
፬ ሰባቱ ነጐድጓድ በተናገሩ ጊዜ ልጽፍ አሰብሁ፤ ከሰማይም። ሰባቱ ነጐድጓድ የተናገሩትን ነገር በማኅተም ዝጋው አትጻፈውም የሚል ድምፅ ሰማሁ።
፭ በባሕርና በምድርም ላይ ሲቆም ያየሁት መልአክ ቀኝ እጁን ወደ ሰማይ አሻቅቦ ዘረጋ፥
፮ ሰማይንና በእርሱም ያሉትን፥ ምድርንና በእርሰዋም ያሉትን፥ ባሕርንና በእርሱም ያሉትን በፈጠረው፥ ከዘላለምም እስከ ዘላለም ድረስ ሕያው ሆኖ በሚኖረው ምሎ።
፯ ወደ ፊት አይዘገይም፥ ዳሩ ግን ሰባተኛው መልአክ ሊነፋ ባለው ጊዜ ድምፁም በሚሰማበት ዘመን፥ ለባሪያዎቹ ለነቢያት የምሰራች እንደ ሰበከላቸው የእግዚአብሔር ምሥጢር ይፈጸማል አለ።
፰ ከሰማይም የሰማሁት ድምፅ እንደ ገና ሲናገረኝና። ሂድና በባሕርና በምድር ላይ ከሚቆመው መልአክ በእጁ ያለችውን የተከፈተችውን መጽሐፍ ውሰድ ሲል ሰማሁ።
፱ ወደ መልአኩም ሄጄ። ታናሺቱን መጽሐፍ ስጠኝ አልሁት። እርሱም። ውሰድና ብላት፥ ሆድህንም መራራ ታደርገዋለች በአፍህ ግን እንደ ማር ትጣፍጣለች አለኝ።
፲ ከመልአኩም እጅ ታናሺቱን መጽሐፍ ወሰጄ በላኋት በአፌም እንደ ማር ጣፋጭ ሆነች፤ ከበላኋት በኋላም ሆዴ መራራ ሆነ።
፲፩ በብዙ ወገኖችና በአሕዛብም በቋንቋዎችም በነገሥታትም ላይ እንደ ገና ትንቢት ትናገር ዘንድ ይገባሃል ተባለልኝ።

፲፩

፩ በትር የሚመስል መለኪያ ለእኔ ተሰጠኝ፥ እንዲህም ተባለልኝ። ተነሥተህ የእግዚአብሔርን መቅደስና መሠዊያውን በዚያም የሚሰግዱትን ለካ።
፪ በመቅደሱም ውጭ ያለው እድሞ ለአሕዛብ ተሰጥቶአልና ተወው አትለካውም፤ እነርሱም እርባ ሁለት ወር የተቀደሰችውን ከተማ ይረግጡአታል።
፫ ለሁለቱም ምስክሮቼ ማቅ ለብሰው ሺህ ከሁለት መቶ ሰድሳ ቀን ትንቢት ሊናገሩ እሰጣለሁ።
፬ እነዚህ በምድር ጌታ ፊት የሚቆሙ ሁለቱ ወይራዎችና ሁለቱ መቅረዞች ናቸው።
፭ ማንምም ሊጐዳቸው ቢወድ እሳት ከአፋቸው ይወጣል ጠላቶቻቸውንም ይበላል፤ ማንም ሊጐዳቸው ቢወድም እንዲሁ ሊገደል ይገባዋል።

፮ እነዚህ ትንቢት በሚናገሩበት ወራት ዝናብ እንዳይዘንብ ሰማይን ሊዘጉ ሥልጣን አላቸው፥ ውኃዎችንም ወደ ደም ሊለውጡ በሚፈልጉበትም ጊዜ ሁሉ በመቅሠፍት ሁሉ ምድርን ሊመቱ ሥልጣን አላቸው።
፯ ምስክራቸውን ከፈጸሙ በኋላ ከጥልቁ የሚወጣው አውሬ ይዋጋቸዋል ያሸንፋቸውማል ይገድላቸውማል።
፰ በድናቸውም በታላቂቱ ከተማ አደባባይ ይተኛል እርሷዋም በመንፈሳዊ ምሳሌ ሰዶምና ግብጽ የተባለች ደግሞ ጌታቸው የተሰቀለባት ናት።
፱ ከወገኖችና ከነገዶችም ከቋንቋዎችም ከአሕዛብም የሆኑ ሰዎች ሦስት ቀን ተኩል በድናቸውን ይመለከታሉ፥ በድናቸውም ወደ መቃብር ሊገባ አይፈቅዱም።
፲ እነዚህም ሁለት ነቢያት በምድር የሚኖሩትን ስለ ሣቀዩ በምድር የሚኖሩት በእነርሱ ላይ ደስ ይላቸዋል በደስታም ይኖራሉ እርስ በርሳቸውም ስጦታ ይስጣጣሉ።
፲፩ ከሦስቱ ቀን ተኩልም በኋላ ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፥ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው።
፲፪ በሰማይም። ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ።
፲፫ በዚያም ሰዓት ታላቅ የምድር መናወጥ ሆነ፥ ከከተማይቱም አሥረኛው እጅ ወደቀ፥ በመናወጥም ሰባት ሺህ ሰዎች ተገደሉ፥ የቀሩትንም ፍርሃት ያዛቸው፥ ለሰማዩም አምላክ ክብር ሰጡ።
፲፬ ሁለተኛው ወዮ አልፎአል፤ እነሆ፥ ሦስተኛው ወዮ በቶሎ ይመጣል።
፲፭ ሰባተኛው መልአክ ነፋ፤ በሰማይም። የዓለም መንግሥት ለጌታችንና ለእርሱ ለክርስቶስ ሆነች፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣል
፲፮ የሚሉ ታላላቅ ድምፆች ሆኑ። በእግዚአብሔርም ፊት በዙፋኖቻቸው የተቀመጡ ሀያ አራቱ ሽማግሌዎች በግምባራቸው ተደፍተው
፲፯ ለእግዚአብሔር እየሰገዱ እንዲህ አሉ። ያለህና የነበርህ ሁሉን የምትገዛ ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፥ ትልቁን ኃይልህን ስለ ያዝህ ስለ ነገሥህም እናመሰግንሃለን፤
፲፰ አሕዛብም ተቈጡ፥ ቍጣህም መጣ፥ በሙታንም ትፈርድ ዘንድ ዘመን መጣ፥ ለባሪያዎችህም ለነቢያትና ለቅዱሳን ስምህንም ለሚፈሩት ለታናናሾችና ለታላላቆችም ዋጋቸውን ትሰጥ ዘንድ፥ ምድርንም የሚያጠፉትን ታጠፋ ዘንድ ዘመን መጣ።
፲፱ በሰማይም ያለው የእግዚአብሔር መቅደስ ተከፈተ፥ የኪዳኑም ታቦት በመቅደሱ ታየ፥ መብረቅና ድምፅም ነጐድጓድም የምድርም መናወጥ ታላቅም በረዶ ሆነ።

፲፪

፩ ታላቅ ምልክትም በሰማይ ታየ ፀሐይን ተጐናጽፋ ጨረቃ ከእግሮችዋ በታች ያላት በራሰዋም ላይ የአሥራ ሁለት ከዋክብት አክሊል የሆነላት አንዲት ሴት ነበረች።
፪ እርሰዋም ፀንሳ ነበር፥ ምጥም ተይዛ ልትወልድ ተጭንቃ ጮኸች።
፫ ሌላም ምልክት በሰማይ ታየ፤ እነሆም ታላቅ ቀይ ዘንዶ፤ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ነበሩት በራሶቹም ላይ ሰባት ዘውዶች ነበሩ፥
፬ ጅራቱም የሰማይን ከዋክብት ሲሶ እየሳበ ወደ ምድር ጣላቸው። ዘንዶውም ሴቲቱ በወለደች ጊዜ ሕፃንዋን እንዲበላ ልትወልድ ባላት ሴት ፊት ቆመ።
፭ አሕዛብንም ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ልጅ ወንድ ልጅ ወለደች፤ ልጅዋም ወደ እግዚአብሔርና ወደ ዙፋኑ ተነጠቀ።
፮ ሴቲቱም ሺህ ከሁለት መቶ ሰድሳ ቀን በዚያ እንዲመግቡአት በእግዚአብሔር ተዘጋጅቶላት ወደ ነበረው ሰፍራ ወደ በረሀ ሸሸች።
፯-፱ ዓለሙንም ሁሉ የሚያስተው፥ ዲያብሎስና ሰይጣን የሚባለው ታላቁ ዘንዶ እርሱም የቀደመው እባብ ተጣለ፤ ወደ ምድር ተጣለ መላእክቱም ከእርሱ ጋር ተጣሉ።
፲ ታላቅም ድምፅ በሰማይ ሰማሁ እንዲህ ሲል። አሁን የአምላካችን ማዳንና ኃይል መንግሥትም የክርስቶስም ሥልጣን ሆነ፥ ቀንና ሌሊትም በአምላካችን ፊት የሚከሳቸው የወንድሞቻችን ከሳሽ ተጥሎአልና።
፲፩ እነርሱም ከበጉ ደም የተነሣ ከምስክራቸውም ቃል የተነሣ ድል ነሡት፥ ነፍሳቸውንም እስከ ሞት ድረስ አልወደዱም።
፲፪ ስለዚህ፥ ሰማይና በውስጡ የምታድሩ ሆይ፥ ደስ ይበላችሁ፤ ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።
፲፫ ዘንዶውም ወደ ምድር እንደ ተጣለ ባየ ጊዜ ወንድ ልጅ የወለደችውን ሴት አሳደዳት።
፲፬ ከእባቡም ፊት ርቃ እንድ ዘመን፥ ዘመናትም፥ የዘመንም እኩሌታ ወደ ምትመገብበት ወደ ሰፍራዋ ወደ በረሀ እንድትበር ለሴቲቱ ሁለት የታላቁ ንሥር ክንፎች ተሰጣት።
፲፭ እባቡም ሴቲቱ በወንዝ እንድትወሰድ ሊያደርግ ወንዝ የሚያህልን ውኃ ከአፉ በሰተ ኋላዋ አፈሰሰ።
፲፮ ምድሪቱም ሴቲቱን ረዳቻት፥ ምድሪቱም አፍዋን ከፍታ ዘንዶው ከአፉ ያፈሰሰውን ወንዝ ዋጠችው።
፲፯ ዘንዶውም በሴቲቱ ላይ ተቈጥቶ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁትን የኢየሱስም ምስክር ያላቸውን ከዘርዋ የቀሩትን ሊዋጋ ሄደ፤ በባሕርም አሸዋ ላይ ቆመ።

፲፫

፩ እንድም አውሬ ከባሕር ሲወጣ አየሁ፤ አሥር ቀንዶችና ሰባት ራሶች ነበሩት፥ በቀንዶቹም ላይ አሥር ዘውዶች በራሶቹም ላይ የሰድብ ሰም ነበረ።
፪ ያየሁትም አውሬ ነብር ይመስል ነበር፥ እግሮቹም እንደ ድብ እግሮች፥ አፉም እንደ አንበሳ አፍ ነበሩ። ዘንዶውም ኃይሉንና ዙፋኑን ትልቅም ሥልጣን ሰጠው።

፫ ከራሶቹም ለሞት እንደ ታረደ ሆኖ እንዲን አየሁ፥ ለሞቱ የሆነውም ቍሰል ተፈወሰ። ምድርም ሁሉ አውሬውን እየተከተለ ተደነቀ፥
፬ ለዘንዶውም ሰገዱለት፥ ለአውሬው ሥልጣንን ሰጥቶታልና፤ ለአውሬውም። አውሬውን ማን ይመስለዋል፥ እርሱንስ ሊዋጋ ማን ይችላል? እያሉ ሰገዱለት።
፭ ታላቅነም ነገርና ሰድብን የሚናገርበት አፍ ተሰጠው፥ በአርባ ሁለት ወርም እንዲሠራ ሥልጣን ተሰጠው።
፮ እግዚአብሔርንም ለመሳደብ ሰሙንና ማደሪያውንም በሰማይም የሚያድሩትን ሊሳደብ አፉን ከፈተ።
፯ ቅዱሳንንም ይዋጋ ዘንድ ድልም ያደርጋቸው ዘንድ ተሰጠው፥ በነገድና በወገንም በቋንቋም በሕዝብም ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጠው።
፰ ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ ሕይወት መጽሐፍ ሰሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል።
፱ ጆሮ ያለው ቢኖር ይሰማ።
፲ ይማረክ ዘንድ ያለው ማንም ቢኖር ወደ ምርኮነት ይሄዳል፤ በሰይፍ የሚገድል ማንም ቢኖር ራሱ በሰይፍ እንዲገደል ይገባዋል። የቅዱሳን ትዕግሥትና እምነት በዚህ ነው።
፲፩ ሌላም አውሬ ከምድር ሲወጣ አየሁ፥ የበግ ቀንዶችን የሚመስሉ ሁለት ቀንዶችም ነበሩት እንደ ዘንዶም ይናገር ነበር።
፲፪ በፊተኛውም አውሬ ሥልጣን በእርሱ ፊት ሁሉን ያደርጋል። ለሞቱ የሆነውም ቍሰል ተፈወሰለት ለፊተኛው አውሬ ምድርና በእርሱ የሚኖሩት እንዲሰግዱለት ያደርጋል።
፲፫ እሳትንም እንኳ ከሰማይ ወደ ምድር በሰው ፊት እሰኪያወርድ ድረስ ታላላቆችን ምልክቶች ያደርጋል።
፲፬ በአውሬውም ፊት ያደርግ ዘንድ ከተሰጡት ምልክቶች የተነሣ በምድር የሚኖሩትን ያሰታል፤ የሰይፍም ቍሰል ለነበረውና በሕይወት ለኖረው ለአውሬው ምስልን እንዲያደርጉ በምድር የሚኖሩትን ይናገራል።
፲፭ የአውሬው ምስል ሊናገር እንኳ ለአውሬውም ምስል የማይሰግዱለትን ሁሉ ሊያሰገድላቸው፥ ለአውሬው ምስል ትንፋሽ እንዲሰጠው ተሰጠው።
፲፮ ታናናሾችና ታላላቆችም ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው ምልክትን እንዲቀበሉ፥
፲፯ የአውሬውም ሰም ወይም የሰሙ ቍጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደርጋል። ጥበብ በዚህ አለ።
፲፰ እእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቍጥሩ የሰው ቍጥር ነውና፥ ቍጥሩም ሰድሰት መቶ ሰድሳ ሰድሰት ነው።

10

፩ እየሁም፥ እነሆም፥ በጉ በጽዮን ተራራ ቆሞ ነበር፥ ከእርሱም ጋር ሰሙና የአባቱ ሰም በግምባራቸው የተጻፈላቸው መቶ አርባ አራት ሺህ ነበሩ።
፪ እንደ ብዙ ውኃም ድምፅና እንደ ታላቅ ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ከሰማይ ድምፅን ሰማሁ፥ ደርዳሪዎችም በገና እንደሚደረድሩ ያለ ድምፅ ሰማሁ።
፫ በዙፋኑም ፊት በአራቱም እንሰሶችና በሽማግሌዎቹ ፊት አዲስ ቅኔ ዘመሩ፤ ከምድርም ከተዋጁት ከመቶ አርባ አራት ሺህ በቀር ያን ቅኔ ሊማር ለማንም አልተቻለውም።
፬ ከሴቶች ጋር ያልረከሱ እነዚህ ናቸው፥ ድንግሎች ናቸውና። በጉ ወደሚሄድበት የሚከተሉት እነዚህ ናቸው። ለእግዚአብሔርና ለበጉ በኩራት እንዲሆኑ ከሰዎች የተዋጁ እነዚህ ናቸው።
፭ በአፋቸውም ውሸት አልተገኘም፤ ነውር የለባቸውም።
፮ በምድርም ለሚኖሩ ለሕዝብም ለነገድም ለቋንቋም ለወገንም ሁሉ ይሰብክ ዘንድ የዘላለም ወንጌል ያለው ሌላ መልአክ ከሰማይ መካከል ሲበር አየሁ፤
፯ በታላቅ ድምፅም። የፍርዱ ሰዓት ደርሶአልና እግዚአብሔርን ፍሩ ክብርንም ሰጡት፤ ሰማይንና ምድርንም ባሕርንም የውኃንም ምንጮች ለሠራው ሰገዱለት አለ።
፰ ሌላም ሁለተኛ መልአክ። አሕዛብን ሁሉ የዝሙትዋን ቍጣ ወይን ጠጅ ያጠጣች ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥ ወደቀች እያለ ተከተለው።
፱ ሦስተኛም መልአክ ተከተላቸው፥ በታላቅ ድምፅ እንዲህ እያለ። ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግምባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥
፲ እርሱ ደግሞ በቍጣው ጽዋ ሳይቀላቅል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቍጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፥ በቅዱሳንም መላእክትና በበጉ ፊት በእሳትና በዲን ይሳቀያል።
፲፩ የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥ ለአውሬውና ለምስሉም የሚሰግዱ የሰሙንም ምልክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም።
፲፪ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁት ኢየሱስንም በማመን የሚጸኑት ቅዱሳን ትዕግሥታቸው በዚህ ነው።
፲፫ ከሰማይም። ከእንግዲህ ወዲህ በጌታ የሚሞቱ ሙታን ብፁዓን ናቸው። መንፈስ። አዎን፥ ከድካማቸው ያርፉ ዘንድ፥ ሥራቸውም ይከተላቸዋል ይላል ብለህ ጻፍ የሚል ድምፅ ሰማሁ።
፲፬ እየሁም፥ እነሆም ነጭ ደመና፥ በደመናውም ላይ የሰውን ልጅ የሚመስል ተቀምጦአል፥ በራሱም ላይ የወርቅ አክሊል በእጁም ሰለታም ማጭድ ነበረው።
፲፭ ሌላ መልአክም ከመቅደሱ ወጥቶ በደመናው ላይ ለተቀመጠው። የማጨድ ሰዓት ሰለ ደረሰ ማጭድህን ሰደድና እጨድ፥ የምድሪቱ መከር ጠውልጓልና ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ።
፲፮ በደመናውም ላይ የተቀመጠው ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው ምድርም ታጨደች።
፲፯ ሌላ መልአክም በሰማይ ካለው መቅደስ ወጣ፥ እርሱም ደግሞ ሰለታም ማጭድ ነበረው።
፲፰ በእሳትም ላይ ሥልጣን ያለው ሌላ መልአክ ከመሠዊያው ወጥቶ ሰለታም ማጭድ ያለውን። ዘለላዎቹ ፈጽመው በሰለዋልና ሰለታሙን ማጭድህን

ሰደድና በምድር ያለውን የወይን ዛፍ ዘለላዎች ቊረጥ ብሎ በታላቅ ድምፅ ጠራ።
፲፱ መልአኩም ማጭዱን ወደ ምድር ጣለው፥ በምድርም ካለው ከወይን ዛፍ ቈርጦ ወደ ታላቁ ወደ እግዚአብሔር ቊጣ መጥመቂያ ጣለ።
፳ የወይኑም መጥመቂያ ከከተማ ውጭ ተረገጠ፥ እስከ ፈረሶች ልጓምም የሚደርስ ደም ርቀቱ ሺህ ሰድስት መቶ ምዕራፍ ሆኖ ከመጥመቂያው ወጣ።

፲፬

፩ ሌላም ታላቅና ድንቅ ምልክት በሰማይ አየሁ፤ የእግዚአብሔር ቊጣ በእነርሱ ሰለሚፈጸም ኋለኛዎቹን ሰባት መቅሠፍቶች የያዙ ሰባት መላእክት ታዩ።
፪ በእሳትም የተቀላቀለውን የብርጭቆ ባሕር የሚመሰለውን አየሁ፥ በአውሬውና በምስሉም በሰሙም ቊጥር ላይ ድል ነሥተው የነበሩት የእግዚአብሔርን በገና ይዘው በብርጭቆ ባሕር ላይ ሲቆሙ አየሁ።
፫-፭ ከዚህም በኋላ አየሁ፥ የምስክርም ድንኳን መቅደስ በሰማይ ተከፈተ፥
፮ ሰባቱንም መቅሠፍት የያዙ ሰባቱ መላእክት ከመቅደሱ ወጡ፤ ከተልባ እግርም የተሠራ ጥሩ የጌጥ ልብስ ለበሱ ደረታቸውንም በወርቅ መታጠቂያ ታጠቁ።
፯ ከአራቱም እንሰሶች አንዱ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ የሚኖር የእግዚአሔር ቊጣ የሞላባቸውን ሰባት የወርቅ ጽዋዎች ለሰባቱ መላእክት ሰጣቸው።
፰ ከእግዚአብሔርም ክብርና ከኃይሉ ጢስ በመቅደሱ ሞላበት፥ የሰባቱ መላእክት ሰባቱ መቅሰፍት እስኪፈጸሙ ድረስ አንድ እንኳ ወደ መቅደሱ ይገባ ዘንድ አልቻለም።

፲፮

፩ ለሰባቱም መላእክት። ሄዳችሁ የእግዚአብሔርን ቊጣ ጽዋዎች በምድር ውሰጥ አፍስሱ የሚል ታላቅ ድምፅ ከመቅደሱ ሰማሁ።
፪ ፊተኛውም ሄደ ጽዋውን በምድር ውሰጥ አፈሰሰ፤ የአውሬውም ምልክት ባለባቸው ለምስሉም በሚሰግዱ ሰዎች ክፉኛ የሚነዘንዝ ቊስል ሆነባቸው።
፫ ሁለተኛውም ጽዋውን በባሕር ውሰጥ አፈሰሰ፤ እንደ ሞተም ሰው ደም ሆነ፥ በባሕርም ከሚኖሩት ሕይወት ያለበት ነፍስ ሁሉ ሞተ።
፬ ሦስተኛውም ጽዋውን በወንዞችና በውኃ ምንጮች ውሰጥ አፈሰሰ፤ እነርሱም ደም ሆኑ።
፭ የውኃውም መልአክ። ያለህና የነበርህ ጌታ ሆይ፥ ቅዱስ ሆይ፥ እንዲህ ሰለፈረድህ ጻድቅ ነህ፤
፮ የቅዱሳንና የነቢያትን ደም ሰላፈሰሱ ደምን ደግሞ አጠጥተሃቸዋል፥ የሚገባቸው ነውና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።
፯ ከመሰዊያውም። አዎን፥ ሁሉን የምትገዛ ጌታ አምላክ ሆይ፥ ፍርዶችህ እውነትና ጽድቅ ናቸው ብሎ ሲናገር ሰማሁ።
፰ አራተኛውም ጽዋውን በፀሐይ ላይ አፈሰሰ፤ ሰዎችንም በእሳት ልታቃጥል ተሰጣት።
፱ ሰዎችም በታላቅ ትኵሳት ተቃጠሉ፥ በነዚህም መቅሠፍቶች ላይ ሥልጣን ያለውን የእግዚአብሔርን ሰም ተሳደቡ፥ ክብርንም እንዲሰጡት ንሰሐ አልገቡም።
፲ አምስተኛውም ጽዋውን በአውሬው ዙፋን ላይ አፈሰሰ፤ መንግሥቱም ጨለማ ሆነች ከሰቃይም የተነሳ መላሶቻቸውን ያኝኩ ነበር፥
፲፩ ከሰቃያቸውና ከቊሰላቸውም የተነሳ የሰማይን አምላክ ተሳደቡ፥ ከሰራቸውም ንሰሐ አልገቡም።
፲፪ ሰድሰተኛውም ጽዋውን በታላቁ ወንዝ በኤፍራጥስ ላይ አፈሰሰ፤ ከፀሐይም መውጫ ለሚመጡ ነገሥታት መንገድ እንዲሰናዳላቸው ውኃው ደረቀ።
፲፫ ከዘንዶውም አፍና ከአውሬው አፍ ከሐሰተኛውም ነቢይ አፍ ጓጕንቸሮች የሚመሰሉ ሦስት ርኩሳን መናፍስት ሲወጡ አየሁ፤
፲፬ ምልክት እያደረጉ የአጋንንት መናፍስት ናቸውና፥ በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር እንዲያሰከትቱአቸው ወደ ዓለም ሁሉ ነገሥታት ይወጣሉ።
፲፭ እነሆ፥ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ፤ ራቁቱን እንዳይሄድ እፍረቱንም እንዳያዩ ነቅቶ ልብሱን የሚጠብቅ ብፁዕ ነው።
፲፮ በዕብራይሰጥም አርማጌዶን ወደሚባል ሰፍራ እሰከተቱአቸው።
፲፯ ሰባተኛውም ጽዋውን በአየር ውሰጥ አፈሰሰ፤ ከመቅደሱም ውሰጥ። ተፈጽሞአል የሚል ታላቅ ድምጽ ከዙፋኑ ወጣ።
፲፰ መብረቅና ድምጽም ነጎድጓድም ሆኑ፥ ትልቅም የምድር መናወጥ ሆነ፤ ሰው በምድር ከተፈጠረ ጀምሮ እንዲህ ያለ ታላቅ መናውጥ ከቶ አልነበረም፤ ከሁሉ በለጠ።
፲፱ ታላቂቱም ከተማ በሦስት ተከፋፈለች፥ የአሕዛብም ከተማዎች ወደቁ። ታላቂቱም ባቢሎን የብርቱ ቊጣው ወይን ጠጅ የሞላበትን ጽዋ እንዲሰጣት በእግዚአብሔር ፊት ታሰበች።
፳፩ ደሴቶችም ሁሉ ሸሹ ተራራዎችም አልተገኙም።
፳፩ በሚዛንም አንድ ታላንት*ፍ1* የሚያህል ታላቅ በረዶ በሰዎች ላይ ከሰማይ ወረደባቸው፤ ሰዎቹም ከበረዶው መቅሰፍት የተነሳ እግዚአብሔርን ተሳደቡ፥ መቅሰፍቱ እጅግ ታላቅ ነውና።

፲፯

፩ ሰባቱንም ጽዋዎች ከያዙ ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ። ና በብዙም ውኃዎች ላይ የተቀመጠችውን የታላቂቱን ጋለሞታ ፍርድ አሳይሃለሁ፤
፪ የምድርም ነገሥታት ከእርሰዋ ጋር ሴሰኑ በምድርም የሚኖሩ ከዝሙትዋ ወይን ጠጅ ሰከሩ ብሎ ተናገረኝ።
፫ በመንፈሰም ወደ በረሀ ወሰደኝ፤ የሰድብም ሰሞኝ በሞሉበት፥ ሰባት ራሶችና አሥር ቀንዶችም ባሉበት በቀይ አውሬ ላይ አንዲት ሴት ተቀምጣ አየሁ።
፬ ሴቲቱም በቀይና በሐምራዊ ልብስ ተጐናጽፋ በወርቅና በከበሩ ድንጋዮች በዕንቈችም ተሸልማ ነበር፥ በእጅዋም የሚያሰጸይፍ ነገር የዝሙትዋም ርኩሰት የሞላባትን የወርቅ ጽዋ ያዘች፤
፭ በግምባርዋም ምሰጢር የሆነ ሰም። ታላቂቱ ባቢሎን፥ የጋለሞታዎችና የምድር ርኩሰት እናት ተብሎ ተጻፈ።

፮ ሴቲቱም በቅዱሳን ደምና በኢየሱስ ምስክሮች
ደም ሰክራ እየኋት። ባየኋትም ጊዜ እጅግ ታላቅ ድንቅ
አደነቅሁ።
፯ መልአኩም አለኝ። የምትደነቅ ስለ ምንድር
ነው? የሴቲቱን ምስጢርና የሚሸከማትን፥ ሰባት
ራሶችና አሰር ቀንዶች ያሉትን የአውሬውን ምስጢር
እኔ እነግርሃለሁ።
፰ ያየኸው አውሬ አሰቀድሞ ነበረ፥ አሁንም የለም፥
ከጥልቁም ይወጣ ዘንድ አለው፥ ወደ ጥፋትም
ይሄዳል፤ ሰሞቻቸውም ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ
በሕይወት መጽሐፍ ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ
አውሬው አሰቀድሞ እንደነበረ አሁንም እንደሌለ፥ ነገር
ግን እንዳለ ሲያዩ ያደንቃሉ።
፱ ጥበብ ያለው አእምሮ በዚህ ነው። ሰባቱ ራሶች
ሴቲቱ የተቀመጠችባቸው ሰባት ተራራዎች ናቸው፥
፲ ሰባት ነገሥታት ደግሞ ናቸው፤ አምስቱ ወድቀዋል
አንዱም አለ፥ የቀረውም ገና አልመጣም፤ ሲመጣም፥
ጥቂት ጊዜ ሊቆይ ይገባዋል።
፲፩ የነበረውና የሌለውም አውሬ ራሱ ደግሞ
ስምንተኛው ነው ከሰባቱም አንዱ ነው፥ ወደ ጥፋትም
ይሄዳል።
፲፪ ያየሃቸውም አሰሩ ቀንዶች ገና መንግሥትን
ያልተቀበሉ አሰር ነገሥታት ናቸው፥ ዳሩ ግን ከአውሬው
ጋር ለአንድ ሰዓት እንደ ነገሥታት ሥልጣንን ይቀበላሉ።
፲፫ እነዚህ አንድ አሳብ አላቸው፥ ኃይላቸውንና
ሥልጣናቸውንም ለአውሬው ይሰጣሉ።
፲፬ እነዚህ በጉን ይወጋሉ፤ በጉም የጌቶች ጌታና
የነገሥታት ንጉሥ ስለ ሆነ እነርሱን ድል ይነሣል፥
ከእርሱም ጋር ያሉ የተጠሩና የተመረጡ የታመኑም
ደግሞ ድል ይነሣሉ።
፲፭ አለኝም። ጋለሞታይቱ የተቀመጠችባቸው
ያየሃቸው ውኃዎች፥ ወገኖችና ብዙ ሰዎች አሕዛብም
ቋንቋዎችም ናቸው።
፲፮ ያየኃቸውም አሰር ቀንዶችና አውሬው
ጋለሞታይቱን ይጣላሉ፤ ባዶዋንና ራቁትዋንም
ያደርጓታል፥ ሥጋዋንም ይበላሉ፥ በእሳትም
ያቃጥሉአታል።
፲፯ እግዚአብሔር አሳቡን እንዲያደርጉ አንድንም
አሳብ እንዲያደርጉ የእግዚአብሔርም ቃል እስኪፈጸም
ድረስ መንግሥታቸውን ለአውሬው እንዲሰጡ
በልባቸው አግብቶአልና።
፲፰ ያየሃትም ሴት በምድር ነገሥታት ላይ የምትነግሥ
ታላቂቱ ከተማ ናት።

፲፰

፩ ከዚህ በኋላ ታላቅ ሰልጣን ያለው ሌላ መልአክ
ከሰማይ ሲወርድ አየሁ፥ ከክብሩም የተነሣ ምድር
በራች።
፪ በብርቱም ድምፅ። ታላቂቱ ባቢሎን ወደቀች፥
ወደቀች፥ የአጋንንትም ማደሪያ ሆነች፥ የርኩሳንም
መናፍስት ሁሉ መጠጊያ የርኩሳንና የተጠሉም ወፎች
ሁሉ መጠጊያ ሆነች፤
፫ አሕዛብ ሁሉ ከዝሙትዋ ቍጣ ወይን ጠጅ የተነሳ
ወድቀዋልና፥ የምድርም ነገሥታት ከእርስዋ ጋር ሴሰኑ
የምድርም ነጋዴዎች ከቅምጥልነትዋ ኃይል የተነሳ ባለ
ጠጋዎች ሆኑ ብሎ ጮኸ።
፬ ከሰማይም ሌላ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ
ሲል። ሕዝቤ ሆይ፥ በኃጢአትዋ እንዳትተባበሩ
ከመቅሠፍትዋም እንዳትቀበሉ ከእርስዋ ዘንድ ውጡ፤
፭ ኃጢአትዋ እስከ ሰማይ ድረስ ደርሶአልና፥
እግዚአብሔርም ዓመፃዋን አሰበ።
፮ እርስዋ እንደ ሰጠች መጠን ብድራት መልሱላት፥
እንደ ሥራዋም ሁለት እጥፍ ደርቡባት፤ በቀላቀለችው
ጽዋ ሁለት እጥፍ እድርጋችሁ ቀላቅሉባት፤
፯ ራሰዋን እንደ አከበረችና እንደ ተቀማጠለች
ልክ ሥቃይና ኀዘን ሰጡአት። በልብዋ። ንግሥት
ሆኜ እቀመጣለሁ ባልቴትም አልሆንም ኀዘንም ከቶ
አላይም ስላለች፥
፰ ስለዚህ በአንድ ቀን ሞትና ኀዘን ራብም የሆኑ
መቅሰፍቶችዋ ይመጣሉ፥ በእሳትም ትቃጠላለች፤
የሚፈርድባት እግዚአብሔር ብርቱ ነውና።
፱ ከእርስዋም ጋር የሴሰኑና የተቀማጠሉ የምድር
ነገሥታት የመቃጠልዋን ጢስ ሲያዩ ስለ እርስዋ ዋይ
ዋይ እያሉ ያለቅሳሉ፤
፲ ሥቃይዋንም ከመፍራት የተነሣ በሩቅ ቆመው።
አንቺ ታላቂቱ ከተማ፥ ብርቱይቱ ከተማ ባቢሎን፥
ወዮልሽ፥ ወዮልሽ፥ በአንድ ሰዓት ፍርድሽ ደርሶአልና
እያሉ ይናገራሉ።
፲፩ የመርከባቸውንም ጭነት ከእንግዲህ ወዲህ
የሚገዛ የለምና የምድር ነጋዴዎች ያለቅሱላታል
ያዝኑላትማል፤
፲፪ ጭነትም ወርቅና ብር የከበረም ድንጋይ ዕንቁም፥
ቀጭንም ተልባ እግር ቀይም ሐርም ሐምራዊም ልብስ
የሚሸትም እንጨት ሁሉ፥ ከዝሆን ጥርስም የተሰራ
ዕቃ ሁሉ፥ እጅግም ከከበረ እንጨት ከናስም ከብረትም
ከዕብነ በረድም የተሰራ ዕቃ ሁሉ፥
፲፫ ቀረፋም ቅመምም የሚቃጠልም ሽቱ ቅባትም
ዕጣንም የወይን ጠጅም ዘይትም የተሰለቀ ዱቄትም
ስንዴም ከብትም በግም ፈረሰም ሰረገላም ባሪያዎችም
የሰዎችም ነፍሳት ነው።
፲፬ ነፍስሽም የጎመጀችው ፍሬ ከአንቺ ዘንድ
አልፎአል፥ የሚቀማጠልና የሚያጌጥም ነገር ሁሉ
ጠፍቶብሻል፥ ሰዎችም ከእንግዲህ ወዲህ ከቶ
አያገኙአቸውም።
፲፭-፲፭ የመቃጠልዋንም ጢስ ባዩ ጊዜ። ታላቂቱን
ከተማ የምትመስላት ምን ከተማ ነበረች? እያሉ
ጮኹ።
፲፱ በራሳቸውም ላይ ትቢያ ነስንሰው እያለቀሱና
እያዘኑ። በባሕር መርከቦች ያሉአቸውን ሁሉ ከባለ
ጠግነትዋ የተነሣ ባለ ጠጋዎች ላደረገች ለታላቂቱ
ከተማ ወዮላት፥ ወዮላት፥ በአንድ ሰዓት ጠፍታለችና
እያሉ ጮኹ።
፳ ሰማይ ሆይ፥ ቅዱሳን ሐዋርያት ነቢያትም
ሆይ፥ በእርስዋ ላይ ደስ ይበላችሁ፥ እግዚአብሔር
ፈርዶላችኋልና።
፳፩ አንድም ብርቱ መልአክ ትልቅን ወፍጮ
የሚመስልን ድንጋይ አንሰቶ ወደ ባሕር ወረወረው
እንዲህ ሲል። ታላቂቱ ከተማ ባቢሎን እንዲህ ተገፍታ
ትወድቃለች ከእንግዲህም ወዲህ ከቶ አትገኝም።
፳፪ በገና የሚመቱና የሚዘምሩም ድምፅ እንቢልታንና
መለከትንም የሚነፉ ድምፅ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ
ውስጥ ከቶ አይሰማም፥ የእጅ ጥበብም ሁሉ አንድ
ብልሃተኛ እንኳ ከእንግዲህ ወዲህ በአንቺ ውስጥ

ከቶ አይገኝም፥ የወፍጮ ድምጽም ከእንግዲህ ወዲህ በእንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፥
፳፫ የመብራትም ብርሃን ከእንግዲህ ወዲህ በእንቺ ውስጥ ከቶ አይበራም፥ የሙሽራና የሙሽራይቱም ድምጽ ከእንግዲህ ወዲህ በእንቺ ውስጥ ከቶ አይሰማም፤ ነጋዴዎችሽ የምድር መኳንንት ነበሩና፥ በአስማትሽም አሕዛብ ሁሉ ስተዋልና።
፳፬ በእርስዋም ውስጥ የነቢያትና የቅዱሳን ደም በምድርም የታረዱ ሁሉ ደም ተገኝባት።

፲፰

፩-፫ ደግመውም። ሃሌ ሉያ አሉ፤ ጢስዋም ለዘላለም እስከ ዘላለም ይወጣል።
፬ ሀያ አራቱም ሽማግሌዎችና አራቱ እንስሶች በፊታቸው ተደፍተው በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለእግዚአብሔር። አሜን፥ ሃሌ ሉያ እያሉ ሰገዱለት።
፭ ድምፅም። ባሪያዎቹ ሁሉ እርሱንም የምትፈሩት ታናናሾችና ታላላቆች ሆይ፥ አምላካችንን አመስግኑ
፮ ሲል ከዙፋኑ ወጣ። እንደ ብዙ ሕዝብም ድምፅ፥ እንደ ብዙ ውኃዎችም ድምፅ፥ እንደ ብርቱም ነጐድጓድ ድምፅ ያለ ድምፅ ሰማሁ እንዲህ ሲል። ሃሌ ሉያ፤ ሁሉን የሚገዛ ጌታ አምላካችን ነግሦአልና።
፯ የበጉ ሰርግ ሰለ ደረሰ ሚስቱም ራሰዋን ሰላዘጋጀች ደስ ይበለን ሐሤትም እናድርግ ክብርንም ለእርሱ እናቅርብ።
፰ ያጌጠና የተጣራ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ እንድትጐናጸፍ ተሰጥቶአታል። ቀጭኑ የተልባ እግር የቅዱሳን ጽድቅ ሥራ ነውና።
፱ እርሱም። ወደ በጉ ሰርግ እራት የተጠሩ ብፁዓን ናቸው ብለህ ጻፍ አለኝ። ደግሞም። ይህ የእግዚአብሔር እውነተኛ ቃል ነው አለኝ።
፲ ልሰግድለትም በእግሩ ፊት ተደፋሁ። እርሱም። እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር የኢየሱሰም ምሰክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ሰገድ፤ የኢየሱሰ ምሰክር የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ።
፲፩ ሰማይም ተከፍቶ አየሁ፥ እነሆም አምባላይ ፈረስ፥ የተቀመጠበትም የታመነና እውነተኛ ይባላል፥ በጽድቅም ይፈርዳል ይዋጋልም።
፲፪ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነበልባል ናቸው፥ በራሱ ላይም ብዙ ዘውዶች አሉ፥ ከእርሱም በቀር አንድ እንኳ የማያውቀው የተጻፈ ሰም አለው፤
፲፫ በደምም የተረጨ ልብስ ተጐናጽፎአል፥ ሰሙም የእግዚአብሔር ቃል ተብሎአል።
፲፬ በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በአምባላዮች ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር።
፲፭ አሕዛብንም ይመታበት ዘንድ ሰለታም ሰይፍ ከአፉ ይወጣል፤ እርሱም በብረት በትር ይገዛቸዋል፤ እርሱም ሁሉን የሚገዛ የእግዚአብሔርን የብርቱ ቍጣውን ወይን መጥመቂያ ይረግጣል።
፲፮ በልብሱና በጭኑም የተጻፈበት። የነገሥታት ንጉሥና የጌታዎች ጌታ የሚል ሰም አለው።
፲፯-፲፱ በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ አውሬውና የምድር ነገሥታት ጭፍራዎቻቸውም ተከማችተው አየሁ።
፳ አውሬውም ተያዘ በእርሱም ፊት ተአምራትን እያደረገ የአውሬውን ምልክት የተቀበሉትን ለምሰሌም የሰገዱትን ያሳተ ሐሰተኛው ነቢይ ከእርሱ ጋር ተያዘ፤ ሁለቱም በሕይወት ሳሉ በዲን ወደሚቃጠል ወደ እሳት ባሕር ተጣሉ።
፳፩ የቀሩትም በፈረስ ላይ ከተቀመጠው ከአፉ በሚወጣው ሰይፍ ተገደሉ፤ ወፎችም ሁሉ ከሥጋቸው ጠገቡ።

፲፱

፩ የጥልቁንም መክፈቻና ታላቁን ሰንሰለት በእጁ የያዘ መልአክ ከሰማይ ሲወርድ አየሁ።
፪ የቀደመውንም እባብ ዘንዶውን እርሱም ዲያብሎስና ሰይጣን የተባለውን ያዘው፥
፫ ሺህ ዓመትም አሰረው፥ ወደ ጥልቅም ጣለው አሕዛብንም ወደ ፊት እንዳያስት ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በእርሱ ላይ ዘግቶ ማሳተም አደረገበት፤ ከዚያም በኋላ ለጥቂት ጊዜ ይፈታ ዘንድ ይገባዋል።
፬ ዙፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ሰለ ኢየሱሰም ምሰክርና ሰለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቈረጡባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥ ለአውሬውና ለምሰሌም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።
፭ የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም። ይህ የፊተኛው ትንሣኤ ነው።
፮ በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፥ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።
፯ ሺሁም ዓመት ሲፈጸም ሰይጣን ከእስራቱ ይፈታል፥
፰ በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ፥ ጎግንና ማጎግን፥ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያሰከትታቸው ይወጣል፤ ቍጥራቸውም እንደ ባሕር አሸዋ የሚያህል ነው።
፱ ወደ ምድርም ሰፋት ወጡ የቅዱሳንንም ሰፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ወርዳ በላቻቸው።
፲ ያሳታቸውም ዲያብሎስ አውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳሉበት ወደ እሳቱና ወደ ዲኑ ባሕር ተጣለ፥ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሣቀያሉ።
፲፩ ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ሰፍራም አልተገኘላቸውም።
፲፪ ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደ ነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ።
፲፫ ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ።

፲፱ ሞትና ሲኦልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው።
፲፭ በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።

፳፩

፩ እኔ አዲስ ሰማይንና አዲስ ምድርንም አየሁ፥ ፊተኛው ሰማይና ፊተኛይቱ ምድር አልፈዋልና፥ ባሕርም ወደ ፊት የለም።
፪ ቅድስቲቱም ከተማ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፥ ለባልዋ እንደ ተሸለመች ሙሽራ ተዘጋጅታ፥ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ።
፫ ታላቅም ድምፅ ከሰማይ። እነሆ፥ የእግዚአብሔር ድንኳን በሰዎች መካከል ነው ከእነርሱም ጋር ያድራል፥ እነርሱም ሕዝቡ ይሆናሉ እግዚአብሔርም እርሱ ራሱ ከእነርሱ ጋር ሆኖ አምላካቸው ይሆናል፤
፬ እንባዎችንም ሁሉ ከዓይኖቻቸው ያብሳል፥ ሞትም ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ ኀዘንም ቢሆን ወይም ጩኸት ወይም ሥቃይ ከእንግዲህ ወዲህ አይሆንም፥ የቀደመው ሥርዓት አልፎአልና ብሎ ሲናገር ሰማሁ።
፭ በዙፋኑም የተቀመጠው። እነሆ፥ ሁሉን አዲስ አደርጋለሁ አለ። ለእኔም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸውና ጻፍ አለኝ።
፮ አለኝም። ተፈጽሞአል። አልፋና ዖሜጋ፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ። ለተጠማ ከሕይወት ውኃ ምንጭ እንዲያው እኔ እሰጣለሁ።
፯ ድል የሚነሣ ይህን ይወርሳል አምላክም እሆነዋለሁ እርሱም ልጅ ይሆነኛል።
፰ ዲሩ ግን የሚፈሩና የማያምኑ የርኩሳንም የነፍሰ ገዳዮችም የሴሰኞዎችም የአስማተኞዎችም ጣዖትንም የሚያመልኩ የሐሰተኞዎችም ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው፤ ይኸውም ሁለተኛው ሞት ነው።
፱ ሰባቱም ኋለኞዎች መቅሠፍቶች የሞሉባቸውን ሰባቱን ጽዋዎች ከያዙት ከሰባቱ መላእክት አንዱ መጥቶ። ወደዚህ ና፥ የበጉንም ሚስት ሙሽራይቱን አሳይሃለሁ ብሎ ተናገረኝ።
፲-፲፪ ታላቅና ረጅም ቅጥር ነበራት፥ አሥራ ሁለትም ደጆች ነበሩአት በደጆቹም አሥራ ሁለት መላእክት ቆሙ፥ የአሥራ ሁለቱም የእስራኤል ልጆች ነገዶች ሰሞች ተጽፈውባቸው ነበር።
፲፫ በምሥራቅ ሦስት ደጆች፥ በሰሜንም ሦስት ደጆች፥ በደቡብም ሦስት ደጆች፥ በምዕራብም ሦስት ደጆች ነበሩ።
፲፬ ለከተማይቱም ቅጥር አሥራ ሁለት መሠረቶች ነበሩአት፥ በእነርሱም ውስጥ የአሥራ ሁለቱ የበጉ ሐዋርያት ሰሞች ተጽፈው ነበር።
፲፭ የተናገረኝም ከተማይቱንና ደጆችዋን ቅጥርዋንም ይለካ ዘንድ የወርቅ ዘንግ ነበረው።
፲፮ ከተማይቱም አራት ማዕዘን ነበራት፥ ርዝመትዋም እንደ ስፋትዋ ልክ ነበረ። ከተማይቱንም በዘንግ ለካት አሥራ ሁለትም ሺህ ምዕራፍ ሆነች፤ ርዝመትዋና ስፋትዋ ከፍታዋም ትክክል ነው።
፲፯ ቅጥርዋንም ለካ፥ መቶ አርባ አራት ክንድ በሰው ልክ፥ እርሱም በመልአክ ልክ።
፲፰ ቅጥርዋም ከኢያስጲድ የተሠራ ነበረ፥ ከተማይቱም ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረች።
፲፱ የከተማይቱም ቅጥር መሠረት በከበረ ድንጋይ ሁሉ ተጌጦ ነበር፤ ፊተኛው መሠረት ኢያስጲድ፥ ሁለተኛው ሰንፔር፥ ሦስተኛው ኬልቄዶን፥ አራተኛው መረግድ፥
፳ አምስተኛው ሰርዶንክስ፥ ስድስተኛው ሰርድዮን፥ ሰባተኛው ክርሶቲሎቤ፥ ስምንተኛው ቢረሌ፥ ዘጠነኛው ወራውሬ፥ አሥረኛው ክርስጵራሰስ፥ አሥራ አንደኛው ያክንት፥ አሥራ ሁለተኛው አሜቴስጢኖስ ነበረ።
፳፩ አሥራ ሁለቱም ደጆች አሥራ ሁለት ዕንቆች ነበሩ፤ እያንዳንዱ ደጅ ከአንድ ዕንቍ የተሠራ ነበረ። የከተማይቱም አደባባይ ጥሩ ብርጭቆ የሚመስል ጥሩ ወርቅ ነበረ።
፳፪ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ አምላክና በጉ መቅደሰዋ ናቸውና መቅደስ በእርሰዋ ዘንድ አላየሁም።
፳፫ ለከተማይቱም የእግዚአብሔር ክብር ስለሚያበራላት መብራትዋም በጉ ስለ ሆነ፥ ፀሐይ ወይም ጨረቃ እንዲያበሩላት አያስፈልጓትም ነበር።
፳፬ አሕዛብም በብርሃንዋ ይመላለሳሉ፥ የምድርም ነገሥታት ክብራቸውን ወደ እርሰዋ ያመጣሉ፤
፳፭ በዚያም ሌሊት ስለሌለ ደጆችዋ በቀን ከቶ አይዘጉም፥
፳፮ የአሕዛብንም ግርማና ክብር ወደ እርሰዋ ያመጣሉ።
፳፯ ለበጉም በሆነው በሕይወት መጽሐፍ ከተጻፉት በቀር፥ ጸያፍ ነገር ሁሉ ርኩሰትና ውሸትም የሚያደርግ ወደ እርሰዋ ከቶ አይገባም።

፳፪

፩ በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ።
፪ በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ አሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ።
፫ ከእንግዲህም ወዲህ መርገም ከቶ አይሆንም። የእግዚአብሔርና የበጉም ዙፋን በእርሰዋ ውስጥ ይሆናል፥ ባሪያዎቹም ያመልኩታል፥ ፊቱንም ያያሉ፥
፬ ሰሙም በግምባሮቻቸው ይሆናል።
፭ ከእንግዲህም ወዲህ ሌሊት አይሆንም፥ ጌታ አምላክም በእነርሱ ላይ ያበራላቸዋልና የመብራት ብርሃንና የፀሐይ ብርሃን አያስፈልጋቸውም፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ይነግሣሉ።
፮ እርሱም። እነዚህ ቃሎች የታመኑና እውነተኞዎች ናቸው፥ የነቢያትም መናፍስት ጌታ አምላክ በቶሎ ሊሆን የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ እንዲያሳይ መልአኩን ሰደደ።
፯ እነሆም፥ በቶሎ እመጣለሁ። የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል የሚጠብቅ ብፁዕ ነው አለኝ።
፰ ይህንም ያየሁትና የሰማሁት እኔ ዮሐንስ ነኝ። በሰማሁትና ባየሁትም ጊዜ ይህን ባሳየኝ በመልአኩ እግር ፊት እሰግድ ዘንድ ተደፋሁ።
፱ እርሱም። እንዳታደርገው ተጠንቀቅ፤ ከአንተ ጋር ከወንድሞችህም ከነቢያት ጋር የዚህንም መጽሐፍ ቃል

ከሚጠብቁ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ፤ ለእግዚአብሔር ሰገድ አለኝ።
፲ ለእኔም። ዘመኑ ቀርቦአልና የዚህን መጽሐፍ ትንቢት ቃል በማሳተም አትዝጋው።
፲፩ ዓመፀኛው ወደ ፊት ያምፅ፥ ርኩሱም ወደ ፊት ይርከስ፥ ጻድቁም ወደ ፊት ጽድቅ ያድርግ፥ ቅዱሱም ወደፊት ይቀደስ አለ።
፲፪ እነሆ፥ በቶሎ እመጣለሁ፥ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ።
፲፫ አልፋና ዖሜጋ፥ ፊተኛውና ኋለኛው፥ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።
፲፬ ወደ ሕይወት ዛፍ ለመድረስ ሥልጣን እንዲኖራቸው በደጆችዋም ወደ ከተማይቱም እንዲገቡ ልብሳቸውን የሚያጥቡ ብፁዓን ናቸው።
፲፭ ውሻዎችና አስማተኞች ሴሰኛዎችም ነፍሰ ገዳዮችም ጣዖትንም የሚያመልኩት ውሸትንም የሚወዱና የሚያደርጉ ሁሉ በውጭ አሉ።
፲፮ እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመስክርላችሁ መልአኬን ላክሁ። እኔ የዳዊት ሥርና ዘር ነኝ፥ የሚያበራም የንጋት ኮከብ ነኝ።
፲፯ መንፈሱና ሙሽራይቱም። ና ይላሉ። የሚሰማም። ና ይበል። የተጠማም ይምጣ፥ የወደደም የሕይወትን ውኃ እንዲያው ይውሰድ።
፲፰ በዚህ መጽሐፍ የተጻፈውን የትንቢት ቃል ለሚሰማ ሁሉ እኔ እመሰክራለሁ፤ ማንም በዚህ ላይ አንዳች ቢጨምር እግዚአብሔር በዚህ መጽሐፍ የተጻፉትን መቅሠፍቶች ይጨምርበታል፤
፲፱ ማንምም በዚህ በትንቢት መጽሐፍ ከተጻፉት ቃሎች አንዳች ቢያጎድል፥ በዚህ መጽሐፍ ከተጻፉት ከሕይወት ዛፍና ከቅድስቲቱ ከተማ እግዚአብሔር ዕድሉን ያጎድልበታል።
፳ ይህን የሚመሰክር። አዎን፥ በቶሎ እመጣለሁ ይላል። አሜን፥ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፥ ና።
፳፩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከሁላችን ጋር ይሁን፤ አሜን።